# እግዚአብሔርን የመምሰል

# ዶክትሪን

# እግዚአብሔርን የመምሰል

# ዶክትሪን

*የሪፎርምድ ዶክትሪን የመጀመሪያው የአስተምህሮ መጽሐፍ*

**ሮናልድ ሓንኮ**

# ለወላጆቼ የተበረከተ

በአስተምሮታቸው እና በምሳሌያዊ ኑሯቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪን ፍቅር በልቤ ለቀረጹ፤ እና እነዚህን ዶክትሪኖች ከልጅነቴ ጀምሮ ላስተማሩኝ ሐርማን እና ዊልማ ሓንኮ።

እነዚህን አስተምር እና ምከር። ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት የማይጠጋ ቢሆን፥ በትዕቢት ተነፍቶአል አንዳችም አያውቅም፥ ነገር ግን ምርመራን በቃልም መዋጋትን እንደ በሽተኛ ይናፍቃል፤ ከእነዚህም ቅንዓትና ክርክር ስድብም ክፉ አሳብም እርስ በርስ መናደድም ይወጣሉ፥ አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ፥ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እንደነዚህ ካሉት ራቅ።

1ኛ ጢሞቴዎስ 6:3-5

# ማውጫ

*XIII.* መቀድም ፩

*XVI.* መቀድም ፪

**መግቢያ**

2. የዶክትሪን አስፈላጊነት

**ክፍል ፩**

**እግዚአብሔር**

**እና ቃሉ**

5. መገለጥ
6. አጠቃላይ መገለጥ
8. የእግዚአብሔር ቃልየ
9. መጽሐፍ ቅዱስ
11. የመጽሐፍ ቅዱስ በቂነት
12. የመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍ
14. የመጽሐፍ ቅዱስ መላ ፍጹማዊ በመንፈስ መነሳሳት
16. የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍ
18. የመጽሐፍ ቅዱስ ህይወት አዘልነት
19. የመጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት የለሽነት
21. የመጽሐፍ ቅዱስ ባለስልጣንነት
22. የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም
24. የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት
26. የመጽሐፍ ቅዱስ ብሩህነት
27. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች
29. እግዚአብሔርን ማወቅ
31. የእግዚአብሔር ስያሜዎች
32. ጅሆቫ የሚለው ስም
34. እግዚአብሔር የሚለው ስም
35. የሠራዊት ጌታ የሚለው ስም
36. አባት የሚለው ስም
38. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት
39. የሰው ሀላፊነት
41. የእግዚአብሔር ባህሪያት
43. የእግዚአብሔር ቅድስና
44. የእግዚአብሔር አንድነት
46. የእግዚአብሔር ኢ-ተለዋጭነት
47. የእግዚአብሔር መንፈሳዊነት
49. የእግዚአብሔር በራሱ በቂ መሆኑ
51. የእግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ መገኘት
52. የእግዚአብሔር ፍቅር
54. የእግዚአብሔር ጸጋ
56. ጸጋ እና ድህነት
57. የእግዚአብሔር ምህረት
58. የእግዚአብሔር ጽድቅ

60. የእግዚአብሔር ጥበብ
61. የእግዚአብሔር ልህቀት
63. የእግዚአብሔር ቀላልነት ወይም ፍጹምነት
64. ሥላሴ
65. የሥላሴ አስፈላጊነት
67. የሥላሴ ቤተሰብ
68. ኪዳኑ
70. ዘላለማዊው ቃልኪዳን
71. አንዲት ኪዳን
73. የጸጋ ኪዳን
74. የኪዳኑ ቃል
75. አስቀድሞ መወሰን (ፕሪደስትኔሽን)
77. ያለ ቅድመ ሁኔታ መመረጥ
78. ሪፕሮቤሽን (እግዚአብሔር ያልተቀበሉትን አይቀበልም፣ አለመመረጥ)
80. የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች
82. የእግዚአብሔር ሁሉን አቀፍ (አጠቃላይ) ድንጋጌዎች
84. የእግዚአብሔር አጥጋቢ ድንጋጌዎች
85. የእግዚአብሔር ቅድመ ሁኔታ የለሽ ፈቃድ
87. የእግዚአብሔር ጠቢብ ድንጋጌዎች
88. የእግዚአብሔር ፈቃድ
90. የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ፈቃድ እና የድንጋጌው ፈቃድ

## ክፍል ፪

## ሰው እና የእርሱ አለም

94. መላዕክት
95. ጋኔኖች
97. ፍጥረት በስድስት ቀናቶች
99. ዝግመታዊ ለውጥ
101. ቴይስቲክ ዝግመታዊ ለውጥ
102. ዴይ-ኤህ የፍጥረት ንድፈ ሀሳብ
104. የእግዚአብሔር መግቦት
106. መጠበቅ እና መግቦት
107. መንግስቱ እና መግቦቱ
109. የእግዚአብሔር ሁሉን አቀፍ መግቦት
110. መግቦቱ እና “የወል ጸጋ”
112. መግቦቱ እና የሀጥያት ገደብ
113. የሰው መፈጠር
115. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል
116. አዳም እና የሰው ዘር ግንኙነት
118. መብት/ይገባኛል (ሜሪት)
119. የመጀመሪያው ገነት
120. ሁለት ዛፎች

122. የሰይጣን ውሸት
123. መልካሙን እና ክፉውን የሚለይ ዛፍ
125. የህይወት ዛፍ
126. የሰው ውድቀት
128. ሀጥያት እና መዘዙ
129. የመጀመሪያው (ዋናው) ሀጥያት
131. መላ ብልሹነት
132. የሰው ነጻ "ፈቃድ"

## ክፍል ፫

## ክርስቶስ እና ስራው

137. የአዳኛችን ስሞች
138. ኢየሱስ የሚለው ስም
140. ክርስቶስ የሚለው ስም
141. "ጌታ" የሚለው ስም
142. የእግዚአብሔር አንዲያ ልጅ የሚለው ስም
144. የሰው ልጅ የሚለው ስም
146. አማኑኤል የሚለው ስም
147. ከስሞች ሁሉ በላይ ስም
148. የክርስቶስ እውነተኛ የሰውነት ባህሪ
150. የክርስቶስ ፍጹም የሰውነት ባህሪ
151. የክርስቶስ ሀጥያት የለሽ የሰውነት ባህሪ
152. የክርስቶስ ደካማ የሰውነት ባህሪ
154. የክርስቶስ ፈተናዎች
156. የክርስቶስ ማዕከላዊ የሰውነት ባህሪ
157. የክርስቶስ ዘላለማዊ መገኘት/ ውልደት
158. የክርስቶስ ከድንግል መወለድ
160. የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት አንድነት
161. የማይነጣጠል የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት አንድነት
163. የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት ህብረት
164. የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት መካከል ያለው ልዩነት
166. በክርስቶስ በኩል ያለው የእግዚአብሔር ኪዳን
167. የክርስቶስ ሦስት ቢሮዎች
169. ክርስቶስ ዋና ነብያችን
170. ክርስቶስ ብቸኛው ሊቀካህናችን
172. ክርስቶስ ዘላለማዊ ንጉሳችን
173. የክርስቶስ አቋም፣ ውርደቱ እና መክበሩ
174. የክርስቶስ ዝቅ ብሎ መወለድ

176. የክርስቶስ የመከራ ህይወት
177. የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት
179. የተወሰነ ስርየት
180. የክርስቶስ ወደ ሲኦል መውረድ
181. የክርስቶስ መቀበር
183. የክርስቶስ ትንሳኤ
184. የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ
186. የክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጥ
187. የክርስቶስ ዳግም መምጣት

## ክፍል ፬
## ኪዳኑ እና ድህነት

192. የኪዳኑ ባህሪ
193. ከአዳም ጋር የነበረው ኪዳን
195. ከኖህ ጋር የነበረው ኪዳን
196. ከአብርሃም ጋር የነበረው ኪዳን
198. ኪዳኑ እና የርስት ተስፋው
199. ከእስራኤል ጋር የነበረው ኪዳን
200. አንድ የእግዚአብሔር ህዝብ
202. ህጉ እና ኪዳኑ
203. በኪዳኑ ውስጥ የህጉ አገልግሎት
205. ከዳዊት ጋር የነበረው ኪዳን
206. አዲሱ ኪዳን
208. የአዲሱ እና የደሮው ኪዳን ንጽጽር
209. የኪዳኑ ፍጻሜ
210. የኪዳኖቹ ማጠቃለያ
211. የድነት ስርዓት
212. ልንቋቋመው የማንችለው ጸጋ
214. ዳግም ውልደት
216. መጠራት
218. ጥሪ እና ስብከት
219. ግብዣ ሳይሆን ጥሪ ነው
221. የእምነት ባህሪ/ ፍሬ ነገር
222. እምነት እና እውቀት
224. እምነት እና መታመን
226. መጽደቅ
227. በእምነት መጽደቅ
229. መጽደቅ እና መመረጥ
231. መጽደቅ እና ስርየት
232. ጉዲፈቻ/ አዶፕሽን
234. ሰላም
236. መለወጥ
237. መቀደስ
239. ቅድስና
241. ተቃርኖ (አንቲ ቴሲስ)
242. መጽናት
243. የቅዱሳን ጽናት
246. ቅዱሳን

248. መክበር

## ክፍል ፫
## ቤተክርስቲያን እና ስርዓቶቿ

252. ቤተክርስቲያን
253. ጉባዔ እና አካል
255. የቤተክርስቲያን ስሞች
256. የቤተክርስቲያን ሌሎች ስሞች
258. ቤተክርስቲያን እና እስራኤል
259. ቤተክርስቲያን እና መንግስት
261. የቤተክርስቲያን ተዋጊዎች
262. ድል ነሺ ቤተክርስቲያን
264. ያልተወለደችው ቤተክርስቲያን
266. የቤተክርስቲያን መመረጥ
267. የቤተክርስቲያን ቅድስና
269. የቤተክርስቲያን አለማቀፋዊነት
271. ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን
272. የቤተክርስቲያን አንድነት
274. ቤተክርስቲያን በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን
276. የቤተክርስቲያን ቢሮዎች
277. የሽማግሌዎች ቢሮ
279. የዲያቆን ቢሮ
281. የመጋቢ እና የአስተማሪ ቢሮ
282. የቤተክርስቲያን መንግስት
284. እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን
286. የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች
288. ወንጌል
289. ስብከት
291. ክርስቶስ እና ስብከት
293. የክርስቲያናዊ ቅጣት አስፈላጊነት
294. ክርስቲያናዊ የቅጣት/ተግሳጽ መንገድ
296. ቁርባን
297. ሁለቱ ቁርባናት
299. የጥምቀት ተምሳሌት
300. የጥምቀት ምልክት እና እውነታነት
302. የጥምቀት ትርጉም
304. የጥምቀት መንገዶች
305. የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እኛ የኢየሱስ ጥምቀት
307. የሕጻናት ጥምቀት በአዲስ ኪዳን
308. የቤተሰብ ጥምቀት
310. ጥምቀት እና የመንግስቱ መግብያ
311. ጥምቀት እና መገርዝ
313. አማኝ ያልሆኑ እና ኪዳኑ
314. እምነት እና ጥምቀት

316. ንሰሐ መግባትና መጠመቅ
317. ቅጣት/ተግሳጽ እና ህዝብን ማጥመቅ
319. የጌታ እራት
320. በጌታ እራት የክርስቶስ መገኘት
322. ቂጣና ወይን በጌታ እራት
325. የጌታ እራት ህብስት እና ወይን
326. እራስን መመርመር እና የጌታ እራት

## ክፍል ፮

## የክርስቶስ መመለስ እና ነገረ ፍጻሜ

328. የመጨረሻው ቀን
329. ልዩ ልዩ የክርስቶስ መምጣቶች
331. የክርስቶስ ዳግም መምጣት
332. አንድ የክርስቶስ የመጨረሻ መምጣት
334. የክርስቶስ የመምጣቱ ምልክቶች
336. መነጠቅ
338. የክርስቶስ በድንገት እና ሳይጠበቅ መምጣት
340. የክርስቶስ በቶሎ መምጣት
342. አስደናቂው የክርስቶስ መምጣት
343. የሺህ ዘመን
345. የዲስፐሽናሊዝም እና የቅድመ ሺ አመት ንጽጽር
346. የቅድመ ሺህ ዘመን ስህተቶች
348. የዲስፐንሽናሊዝም ስህተቶች
349. የዲስፐንሽናሊዝም ተጨማሪ ስህተቶች
351. ድህረ ሺህ ዘመን
352. የድህረ ሺህ ዘመን ስህተቶች
354. አሜሊኒያልዝም
356. ቃል በቃላዊነት (ቀጥታዊነት) እና ራዕይ 20
358. አንዲት ትንሳኤ
359. ሞት
361. የትንሳኤያችን አስፈላጊነት
362. የትንሳኤው አካል
364. የትንሳኤው አስደናቂነት
365. የነፍስ አለመሞት
367. መካከለኛው ስፍራ
369. ታላቁ መከራ
370. የክርስቶስ ተቃዋሚ
372. ፍርዱ
373. አንድ የመጨረሻ ፍርድ ብቻ
375. የፍርዱ አላማ
376. ሲኦል

378. ዘላለማዊ ቅጣት

379. ሰማይ

381. አዲስ ሰማያት እና ምድር

382. ሰማያዊ ክብር

# መቅድም ፩

በሚስዮናዊ ስራ ውስጥ ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች መካከል ወንጌልን እና የእግዚአብሔር ቃል እውነታን በግልጽ እና በቀለለ መንገድ ማቅረብ ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪኖችን ደግሞ በጥልቀትና በተመጠነ መልኩ ማስተላለፍ ዋነኞቹ ናቸው። ባለንበት ዘመን ክርስቶስን እናውቃለን የሚሉ ብዙዎች ያሉት በግራ መጋባት፣ በመቅበዝበዝ ፣ በጥቂት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት እና በተለያዩ ቤትክርስቲያናት በሚናፈሱት የሃይማኖት አስተምህሮዎች (ዶክትሪን) ንፋስ በቀላሉ በመነዳት ነው። በአንድ ወቅት ለቅዱሳን የነበረው የመጀመሪያው የእምነት እውቀት አሁን ሊያውቁት በሚገባቸው ሰዎች አእምሮ ውስጥ የለም። በዚህ ዘመን ፣ የሚስዮናዊ ስራ የእግዚአብሔርን ቃል ክርስቶስን ላላወቁት ብቻ ሳይሆን እውነተኛውን ወንጌል ላልተረዱ ሰዎችም ማዳረስ ነው። ሚስዮናዊው ክርስቲያን ነን ለሚሉትም ጭምር ስለ እምነቱ ማስተማር እና ያልዳኑትን ደግሞ ወደ ንሰሃና በክርስቶስ ወዳለ እምነት መጥራት ይኖርበታል።

በዚህ ዘመን የአንባቢዎች መመናመን ብሎም ጠንከር ያሉ መጽሐፍትን ማንበብ እና ለሰዓታት ትኩረት የማድረግ ክህሎት መቀነሱ በፓስተሮች ወይም በሚሶናዊያን ፊት የተደነቀረ ከባድ ስራ ነው። እነዚህን የዘመናችንን ድክመቶች የሚደርሱ ፣ ትክክለኛ ዶክትሪን ያላቸውን እና ጠቃሚ የሆኑ መጽሐፍትን ማግኘትም ከባድ ሆኗል ። በ1940ዎቹ ሬቨረንድ ኸርማን ሆክሲማ ከዚህ ችግር በመነሳት አጫጭር ስብከቶችን በራዲዮ ጣቢያው እንዲያስተላልፍ ግድ ሆነበት። ከጊዜ በኋላም እነዚህ ስብከቶቹ በመጽሐፍ መልክ መሰብሰብ ቻሉ። ለዚህም የ *"ጸጋው አስገራሚነት"* የተሰኘው መጽሐፉ አንዱና ምርጡ ማሳያ ሲሆን በሬቨረንድ ሮናልድ ሃንኮ እና በሬቨረንድ ሮናልድ ካሜንጋ የተጻፈ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና የካልቪኒዝምን አምስት ነጥቦችን በስፋት የሚዳስሰው *"በፀጋ ድነናል"* የተሰኘውን መጽሐፍም በተጨማሪነት መጥቀስ ይቻላል።

*"ዶክትሪን፡ እግዚአብሔርን በመምሰል"* የተሰኘው ይህ መጽሐፍም ይህንን መንገድ በመከተል ዶርትሪንን በቀላል መንገድ ለማቅረብ ይሞክራል። ይህ የሬቨረንድ ሓንኮ መጽሐፍ በሚስዮናዊነት ስራው ወቅት ያፈሰሰው የትጋቱ ፍሬ ነው። በዚህ ስራ ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹን ሃስቦች ያዳበረው የተሓድሶ እምነት በፕሪሲቢቴሪያን አብያተክርስቲያናት ውስጥ

አብቦ በነበረበት ወቅት፣ በሰሜናዊው አየርላንድ በሚስዮናዊነት ረጅም አመታትን ባገለገለበት ጊዜ ውስጥ ነው።

ሀሳቦቹን በተመጠነ እና በተሟላ መንገድ ስለገለጻቸው ብቻቸውን መቆም የሚችሉ እና መሰረታዊ ዶክትሪንን ያነገቡ ናቸው። ከዚህ ጎን ለጎን ጸሐፊው የተሓድሶ እምነት ነጥቦችን በመከተል አንድነታቸውን በጠበቀ መልኩ ማቅረብ ችሏል። ይህም ለዚህ የዶክትሪን ጥናት ሁለት እጥፍ የሆነ ገጽታን ያላብሰዋል። የመጀመሪያው ገጽታ አንዱ ርዕስ ብቻውን ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦች ጋር ተጣምሮ ሙሉ የዳበረ ዶክትሪን በመሆን በተደጋጋሚ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መሆን መቻሉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ርዕሶቹ በአንድነት የተሓድሶ አስተምህሮን መስመር የጠበቁ በመሆናቸው ሙሉ የሆነን ምልከታ የመስጠት አቅም ማዘላቸው ነው። ከሁለተኛው ገጽታ አንጻር፣ *ዶክትሪን፡ እግዚአብሔርን በመመሰል* የተሰኘው ይህ መጽሐፍ  የተሓድሶ አስተምህሮ ቀኖና መመሪያ ሆኖ መቅረብ ይችላል።

ይህን መሰል ስራ ለተሓድሷዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በክርስቲያናዊ ትምህርቶች እና በተቋም ስብስቦች ለጥናት እና ውይይት ይጠቅማል። መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ ለቡድን ጥናት ማጥኛነት አልያም በእያንዳንዱ ርዕስ ላይ ለመወያየት መዋል ይችላል። በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ትክክለኛ አስተምህሮ በተለያዩ ቦታዎች ለማስተማር የተጠሩ ፤ ሽማግሌዎች፣ ወላጆች፣ አስተማሪዎች እና የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም መሪዎች  ለዝግጅታቸው አጋዥነት ማዋል ይችላሉ።

አማኝ ይህንን ጽሁፍ ማንበቡ በውስጡ ላለው ተስፋ ትክክለኛን ምላሽ እንዲሰጥ ያስችለዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን የዶግማቲዝም ጽሑፍ ለሚከብደው እና ሸክም ለሚሆንበት ሰው ይህ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስን በበለጠ ጥናት እንዲያጠናው በሚገፋፋ መልኩ የተሐድሶ አስተምህሮን ያቀርብልናል።

እያንዳንዱን ርዕስ በአንድ ወይም በሁለት ገጾች ላይ በተሟላ ይዘት ለማስፈር መሞከር አስቸጋሪ ነው። ሬቨረንድ ሃንኮ ይህን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወኑ በጭራሽ ቀላል የሚባል አይደለም። በተጨማሪም የክርስትና ህይወት እና ጉዞ ሊሸከመው የሚገባውን እውነት በማዘሉ ጸሐፊው ጠቃሚ የሆነን የማጥኛ መጽሐፍን ሰጥቶናል። እምነትን እና ስራን፤ አስተምህሮን (ዶክትሪን) እና ህይወትን፣ እውነት እና ተግባርን በማጣመር ሃሳቦቹ (ርዕሶቹ) በእውቀት እየመሩን

እግዚአብሔርን የመምሰል ጉዟችንን ያጠሩታል። የዚህ መጽሐፍ ርዕስ አመራረጥ በዚህ ምክኒያት ተገቢ ነው።

ጌታም ይህንን የድካም ፍሬ ለመንግስቱ እና ለክብሩ መጠቀሙን ይቀጥል።

ሬቨረንድ ቶማስ ማይርሰማ

## መቀድም ፪

በስምንት አመት ግዜ ውስጥ በዩናይትድ ኪንግደም ላለው የሚስዮናዊ ስራ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲሆን ተብለው የተበተኑ ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ ተከታታይ ጹሁፎች ይህንን መጽሐፍ ጠነሰሱት። የጽሁፎቹ ተቀባይነት እና ከበርካታ አንባቢያን ዘንድ የደረሱን ማበረታቻዎች እነዚህን ጹሁፎች በመጽሐፍ መልክ ለማዘጋጀት ምክንያት ሆነዋል።

ከመጀመሪያዎቹ ጽሁፎች ጥቂቶቹ በመጽሐፉ ውስጥ ባይካተቱም የእነርሱን የሃሳብ ክፍተት እንዲሞሉ ወደ ሃምሳ የሚሆኑ አዳዲስ ጽሁፎች ተጨምረውበታል። አብዛኞቹ የመጀመርያዎቹ ጽሁፎች ማሻሻያ ሲደረግላቸው አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ አዲስ ተጽፈዋል።

ይህ መጽሐፍ የተሐድሶ *ሥነ*-መለኮታዊ ነጥቦችን የተከተለ ሲሆን የተለምዶ ስማቸውን ባይጠቀምም *ዶክትሪን፡ እግዚአብሔርን በመምሰል ላይ የተመሰረተ* ስድስቱም ክፍሎች ከአስተምህሮው (ከዶግማው) ስድስት ክፍሎች የተወሰዱ ናቸው።

ሃሳቦቹ በመጀመሪያ የተጻፉት በጣም በቀለለ መልኩ ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያዎች እንዲኖራቸው እና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ (ዶክትሪን) ህይወት ላይ የሚተገበር እንደሆነ የሚያሳይ ለሚስዮናዊያን መመስከሪያነት እንዲውሉ ነበሩ። የተሐድሶ እምነትን በሚስዮናዊያን መስክም ሆነ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለማስተማር ይጠቀማል ተብሎ ሰለታመነ ይህ ባህሪያቸው ተጠብቋል።

ስለተሓድሶ እምነት የሚያውቁም የበለጠ ለማንበብ እንዲበረታቱ ሲባል ጽሁፎቹ የተመጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። በዩናይትድ ስቴትም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ለተሓድሶ ቤተክርስትያናት ውድቀት አስተዋጾ ካደረጉ ነገሮች መካከል የእግዚአብሔር ሰዎች አለማንበባቸው አንዱ እንደሆነ ጽኑ እምነቴ ነው። እነዚህ ጽሁፎች በቀላሉ ተነበው የጸጋን እና በድህነት ላይ ያለውን የእግዚሃብሄር ሉዓላዊነትን በጥልቀት ለማጥናት የበለጠ እንደሚያበረታቱ እምነቴ ነው።

እግዚአብሔር ይህንን ጥረት ይባርክ፤ ለመልካምም ይጠቀምበት።

ሬቨረንድ ሮናልድ ሃንኮ

# መግቢያ

## የዶክትሪን አስፈላጊነት

እንደቀድሞው ዶክትሪን ከፍ ያለ ቦታ አይሰጠውም። በብዙ ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ውስጥ ዶክትሪን ችላ በመባሉ ለክርስትና መሰረታዊ አስተምህሮዎች ጠንካራ መረዳት የለም ። በትምህርታቸው እና በስብከታቸው ታማኝ በሆኑ ቤተክርስቲያናት እንኳን ዶክትሪንን የመማር እና የመረዳት ፍላጎት የላቸውም፣ ስለዚህም አብዛኛው ወጣት ዶክትሪን/አስተምህሮ ያሰለቸዋል መሪዎችም በወጣቶች የላይ ላይ እውቀት መርካታቸው ይስተዋላል።

"ተግባራዊ" ስብከት እና ትምህርት የሚል ረብሻ፤ ስብከቱ ተጨምቆ እስከሚወጣ ሥነ-ስርዓት እና የአምልኮ ግዜ ላይ የሚደረግ አጽንዖት፤ አብዛኛውን ጊዜ የዶክትርን እጥረት እንዳለ ያመላክታል። ከሰባኪያን ስብከት ሰዎች የሚያገኙት በጣም ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራርያ ሲሆን አያሌ ምሳሌ፥ ታርክ እና መዝናኛ ደግሞ ታክሎበታል።

የተሓድሶ መጽሐፍትን እና በየጊዜው የሚጻፉ የዶክትሪን/አስተምህሮ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት ማጣት በእግዚአብሔር ሰዎች የግል ህይወት ያለ የዶክትሪን ግድ የለሽነት መገለጫ ነው። አንዳንዶች መሰል መጽሐፍቶችን ይገዛሉ ነገር ግን አያነብቧቸውም ሌሎች ደግሞ መጽሐፍቶችን ለመግዛት እንኳን ፍላጎት የላቸውም። ቢያነብቡ እንኳን ከላይ ከላይ ያሉ ጽሁፎችን ያነባሉ፤ በብዛት ደግሞ "እንዴት -" የሚለውን ጥያቄ እንጂ ከዚያ የዘለለ ጥያቄን የማይመልሱ መጽሐፍት ናቸው። በአጠቃላይ የሚመዝን ምልከታ ያለው ነገር አይነበብም ማለት ይቻላል። አባቶቻቸው እና አያቶቻቸው እንደ እነሱ ቀለም ሳይቆጥሩ ሥነ-መለኮትን ማንበብ ብቻ ሳይሆን በስፋት እና በድንብ ተረድተውት ሳለ ሰዎች ግን ዶክትሪን/አስተምህሮን አክብደው ከራሳቸው አርቀውታል።

ቤተክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን ህዝቦች ከማይመዝን እውቀት፣ ከወድቀት እና ከሚገጥሟቸው ፈተናዎች ሁሉ እንታደግ ዘንድ ወደ ዶክትሪን መመለስ እጅግ አስፈላጊ ነው። እንደ ማስረጃ ወደ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ታላቁ ተሓድሶ መመለከት በቂ ነው። ይህ ተሓስዶ ዋናው ጉዳዮ ወደ ዶክትሪን/አስተምህሮ መመለስ ሲሆን አስትመህሮቶቹም በእምነት ብቻ መጽደቅ እና የቤተክርስቲያን እና የሥርዓቶቿ በሉዓላዊ ጸጋ መመራት ናቸው። ወደ ዶክትሪን

ወይንም አስተምህሮ ለመመለስ ፍላጎት ሳይኖረን የቤተክርስቲያንን መነቃቃት ሆነ ተሓድሶ ተስፋ ማድረግ አንችልም።

በ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:26-17 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ቅዱስ መጽሐፍት ለብዙ ነገር ትርፋማ እንደሆኑ ነገሮን ከሁሉ አስቀድሞ ግን ለትምህርት/ዶክትሪን እንደሚጠቅሙን ይናገራል (KJVን ይመ.)። በእርግጥም በቅድሚያ ዶክትሪንን ካላስተማረን ለማረጋገጫነት፣ ለማስተካከያነት ሆነ ለጽድቅ መመሪያነት ሊጠቅመን አይችልም። ለዚህ ሁሉ ዶክትሪን ቀዳሚ ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የዶክትሪን/አስተምህሮ አስፈላጊነት ላይ በተለያየ መንገድ አጽንዖት ሲሰጥ እንመለከታለን። በዩሀንስ 17:3 ላይ የእግዚአብሔር እና የክርስቶስ ኢየሱስ እውቀት ዘላለማዊ ህይወት እንደሆነ እንማራለን። ከዚህም የሚበልጥ ምንም የለም። ዶክትሪንን በስርዓት ከተማርነው፣ ከተረዳነው፣ እና ካመንነው የእግዚአብሔር እና የልጁ እውቀት ሆነልን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ ሌላ ምንም አያስተምረንም። ኢየሱስም እንዲህ ይላልና "እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው" (የዩሃንስ ወንጌል 5:39)።

ስለዚህም ዶክትሪንን ልብ እንበል። የሥነ-መለኮታዊያን ብቻ ሳይሆን የዘላለም ህይወትን የሚፈልግ ሰው ሁሉ መሰረት ነው። የበለጠ "ተግባራዊ" ነገሮችን ፍለጋ ዶክትሪንን ጥግ አናስይዝ ነገር ግን ዶክትሪን የሚወቅሰውን፣ የሚያስተካክለውን፣ እናም የሚያስተምረውን የጽድቅ መንገድ እንረዳ። ከሁሉ በላይ ካለው እና ከሚኖረው እግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ያገናኘናል። በእርሱም እንኖራለን፣ እንራመዳለን፣ አካላችንም የተጠበቀ ነውና ያለ ዶክትሪን መሆን ያለእግዚሃብሄር መሆን ነው።

**ክፍል ፩**

# እግዚአብሔር እና ቃሉ

**መገለጥ**

ከእግዚአብሔር እጅግ አስገራሚ ስራዎች መካከል አንዱ መገለጡ ነው። መኖሩን ለእኛ መግለጡ ብቻውን ታላቅ እና የሚያስደንቅ ነገር ነው። እርሱ ለእራሱ በቂ ነው፣ የሚያስፈልገው ነገር ሆነ ሰው የለም፤ ሆኖም ግን እራሱን በእጆቹ ስራ ለመግለጥ ፈቀደ።

ከዚህም በላይ የሚያስገርመው ደግሞ እግዚአብሔር *እራሱን (ማንነቱን)* ለእኛ መግለጡ ነው። እኛ በፊቱ ፍጥረታት፤ የእጆቹ ስራዎች፤ ከአፈርም እጅግ የምናንስ ነን። እርሱ ደግሞ ሁሉን ቻይ፣ ዘላለማዊ፣ የላቀ አምላክ እና ፍጹም ከመረዳታችን ያለፈ ነው፤ ሆኖም ግን ማንነቱን እና ክብሩን ለእኛ አሳወቀን።

ይልቁንም ደግሞ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16 ላይ እርሱን ማንም አላየውም፤ ሊያየውም አይችልም፤ በማይታይ ብርሃን ውስጥ ያለ እና ለዘላለም ከአይናችን የተሰወረ ነው እንደሚል ስናስታውስ እርሱ ለእኛ መገለጡ ታምር እንደሆነ እናስተውላለን። ታላቅ የሆነው እርሱ በሰው ልጅ ቋንቋ ተናግሮ ደግሞም ከሁሉም ታናሽ የሆንን እኛ እንድንረዳው ማድረጉ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ጆን ካልቪን እንዳለው - ወላጅ ህጻንን እንደሚያወራው እግዚአብሔርም ለእኛ አወራልን። በእርግጥም የመገለጡ ታምር ይህ ነው።

ሌላኛው የታምራቱ አካል ደግሞ እግዚአብሔር አእምሯቸውን እና ልባቸውን ለከደኑ *ሀጥያተኞች* እራሱን መግለጡ ነው። ይህም በመገለጥ እና በጸጋ መካከል ያለውን ግንኙነት ያስረዳናል። የመገለጡም የመጨረሻ አላማ የእግዚአብሔር ሰዎች ድህነት ነው።

ይሄ ሀሳብ እግዚአብሔር እራሱን ወደ ሚገልጥባቸው የተለያዩ መንገዶች ያመራናል። የቤልጂየሙ የእምነት አዋጅ በመዝሙር 91 መሰረት ሁለት መንገዶችን ያቀርብልናል እነርሱም፡- በፍጥረቱ እና በመጽሐፍ ቅዱስ[1] እግዚአብሔር እራሱን ይገልጣል የሚል ሲሆን፣ ሌሎች ተጨማሪ መንገዶችም አሉ። እግዚአብሔር እራሱን በታርክ ውስጥ ይገልጣል ይህንን ስንል የእራሱን ታሪክ በሰው ልብ ውስጥ ገልጧል ማለታችን ነው። ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ በብሉይ ኪዳን እራሱን በህልም፣በራዕይ፣ በመላዕክት እና በሌሎች መንገዶች ገልጧል።

በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን መገለጥ የቢልጂየሙ የእምነት አዋጅ "ያማረ እና ሞገሳም መጽሐፍ"[2] ብሎ ያስቀምጠዋል። ልክ ታላቅ ሰዓሊ/አናጺ የሰራው ስራ የሰዓሊውን/የአናጺውን ማንነት እንደሚገልጥ፤ እግዚአብሔርም ስራው ማንነቱን ይገልጣል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር እራሱን በሰው ልብ ውስጥ መግለጡ እና በታሪክ መካከል መግለጡ ላልዳኑት ሀጥያተኞች የሚያሸብር መጽሐፍ ነው። ያልዳነው

ሀጥያተኛ ከዚህ መገለጥ ውስጥ ቁጣ እና ፍርድ ብቻ ያነብባል በዚህም ምክኒያት ይህንን መገለጥ በማጉደፍ ከእራሱ ያርቀዋል (ሮሜ 1:26) ።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እንደሚያድን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ገልጦልናል። ታዲያ መገለጥን ስናስብ በተለየ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን ማሰብ ይቀድመናል።

የእግዚአብሔርን መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከማወቅ በተጨማሪም በፍጥረት እና በዘመናት መካከል ያለውን የእግዚአብሔርን መገለጥ በማየት ማትረፍ እንችላለልን። ጆን ካልቪን እንዳለው ቅዱሱን መጽሐፍ እንደ መነጽር በመጠቀም በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ጸጋ ማንበብ እንችላለን። በጸሐይ ጮራ እና በአበቦች፤ በቅንጣት ዘር እና በተራራዎች ውስጥ በጸጋው በኩል የድህነታችን ባለቤት ታላቁ እግዚአብሔር መሆኑን እንድንመለከት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።

ታድያ የፍጥረትን "ያማረ እና ሞገሳም መጽሐፍ" ማንበብ እንማር ነገር ግን ታላቁን እና ከሁሉም የሚበልጠውን እና የእግዚአብሔርን ቃል የያዘውን ቅዱሱን መጽሐፍ አንርሳ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከጸጋው ብዛት በልጁ በኩል እራሱን የገለጠልንን ለማወቅ እንማራለንና።

## አጠቃላይ መገለጥ

"አጠቃላይ መገለጥ" የሚለውን ስያሜ በብዛት እግዚአብሔር እራሱን በፍጥረት፣ በሰዎች ልብ ውስጥ እና በዘመናት መካከል መግለጡን ለመናገር እንጠቀምበታለን። ይህንን ስያሜ ያገኘው ከ "ልዩ መገለጥ" ማለትም በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆነው የእግዚአብሔር አዳኝነት መገለጥ ለመለየት ሲባል ነው።

አጠቃላይ መገለጥ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሲጥቀስ እናያለን በተለይም ደግሞ በሮሜ 1: 18-32 ይህንን ሀሳብ በግልጥ እንመለከታለን። ይህ ክፍል እግዚአብሔር እራሱን በፍጥረት (ቁ. 20, 25) እና በሰው ልጅ ህሊና ውስጥ (ቁ. 19፡ ቃሉን ልብ ይበሉ) እንደገለጠ ይናገራል።

አጠቃላይ መገለጥ የማዳን ሃይል የለውም በተጨማሪም አንዳንዶች የጋራ ጸጋ (common grace) የሚለውን ስያሜ ሊሰጡት ቢሞክሩም አጠቃላይ መገለጥ የጋራ ጸጋ አይደለም። ሆኖም ሮሜ

ምዕራፍ 1 እንደሚያስረዳው ክፉዎች ያለምክኒያት ይሆኑ ዘንድ የተሰጠ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው። (ቁጥ 18, 20)

ታዲያ የአጠቃላይ መገለጥ አላማ ይህ ከሆነ የድህነትን መንገድ አያሳየንም ማለት ነው። ደግሞም ክፉዎች ይህንን ተገንዝበው በሚሰጡት የህሊና ወይንም የእውቀት መልስ መዳን ይችላሉ የሚለው ምልከታ ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት የለሽ እና ሌላ የድህነት መንገድን የሚናገር ሰዋዊ ሀይማኖት ነው ማለት ነው።

አጠቃላይ መገለጥ ሰውን የማዳን አቅም አለው የሚለውን ሀሳብ ሮሜ ምዕራፍ 1 ሲቃወመው እናያለን። ክፉዎች በእርግጥም “የማይታየው የእግዚአብሔርን ባሕርይ” በተለይ ዘላለማዊ ሀይሉ እና አምላክነቱ ተገልጦላቸዋል (ቁጥ 20) ። ቁጥር 19 ላይ ስለእግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው እንዳለ በእነርሱ ግልጥ እንደሆነ በመናገር እግዚአብሔር እራሱን “ለእነርሱ” የገለጠበት *ውስጣዊ* መገለጥ ጭምር መኖሩን ያሳየናል።

ይህ ወደ ትልቅ ነገር ይጠቁመናል። እግዚአብሔር በፍጥረቱ በኩል ተገልጧልና በፍርድ ቀን እግዚአብሔር መኖሩን አላወኩም የሚልን መማጸኛ ወይም ምክኒያት የሚሰጥ ሰው እንዳይኖር ያደርገዋል። ሮሜ 1ን በመመልከት ኤቲይስት (እግዚአብሔር የለም የሚል ሰው) የለም ማለት ይቻላል።ስለዚህም ወንጌልን ያልሰሙ ሀጥያተኞች በሙሉ በዚህ መገለጥ ምክኒያት በፍርድ ቀን ይኮነናሉ።

ይህም ሆነ ያሃ ሀጥያተኞችን በተመለከተ የእግዚአብሔር መገለጥ ውጤት/አላማ እነርሱ እግዚአብሔርን ማክበር የማይፈልጉ፣ ባለማመስገን የሚቀጥሉ፣ በውስጣቸውም የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ክብር ደግሞ በተለያየ ምስል ወይንም ጌታ እንዲቀይሩት ማድረግ ነው። (ቁ. 21-25)

በቀላሉ ክፉዎች ጣዖትን ሲያመልኩ የማያውቁትን አምላክ ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት ወይንም ሙከራ ሳይሆን *ከሚያውቁት* እውነተኛ አምላክ የሚያደርጉት ሽሽት ነው።

ሮሜ 1 እንደሚያስረዳን እውነትን እየፈለጉ ሳይሆን እየተጫኑት ነው። ፍልስፍናቸው እና ሃይማኖታቸው የእውነት ወይንም የፍቅር እምቡጦች ሳይሆኑ እውነትን በክህደት እና ውሸት የለወጡ ሀሳቦች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስም ደግሞ ይህንን ባህርያቸውን በግልጽ እያረጋገጠልን ድህነት በወንጌል ስብከት ብቻ እንደሆነ ይደመድምልናል (ሮሜ. 1:16 ሮሜ. 10:14, 17, 1ኛ ቆሮ. 1:18, 21) ። ወደ ድህነት የሚያመጣ

የእግዚአብሔር ሃይል እና ጥበብ ብቸኛው ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑ የተገለፀው በወንጌል ብቻ ስለሆነ ያለወንጌል ምንም አይነት የድህነት ተስፋ የለም።

ስለዚህ አጠቃላይ መገለጥ ወንጌልን ለማይሰሙ እና ለማይቀበሉ ሰዎች የጥፋተኝነትን ጥልቀት ለመጨመር ብቻ ያገለግላል። ከዚህ የተለየ ትምህርትን ማስተማር የመዳን ብቸኛ መንገድ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም እና ፍጹም ታዛዥነቱ መሆኑን መካድ እና የእርሱን እና የመስቀሉን ስም ማጥፋት ነው።

## የእግዚአብሔር ቃል

እግዚአብሔር ከታላቅነቱ የተነሳ እራሱን ለእኛ ካልገለጠልን በስተቀረ ልናውቀው አንችልም። ታላቅ ነውና ልናየው ሆነ ልንዳስሰው ስለማንችል (1ኛ ጢሞ. 6:16) አዳኝነቱን እና አባትነቱን በቃሉ ገለጠልን። እኛ በምሳሌው የተፈጠርነው እንኳን ቀዳሚ የእርስ በእርስ መግባቢያ ስልታችን ንግግር በመሆኑ በቃል መገለጡ የተለየ እና አዲስ ሊሆንብን አይገባም።

ታዲያ እግዚአብሔር ለሰው መናገሩ ብቻ ታምር ነው። ወሰን የሌለው እና ዘላለማዊ አምላክ ስለራሱ እና ክብሩ የተገደበ አእምሮ እና ኢ-ፍፁማዊ አንደበት ላለን ለእኛ በመናገር ስለማንነቱ የተወሰነ ነገርን እንድናውቅ ማስቻሉ በቅድሚያ የሚያስደንቅ ታምር ነው። *እግዚአብሔርን* ራሱን አወቅነው በቃሉም በኩል ከእርሱ ጋር ህብረት አለን።

እግዚአብሔር ለሰው መናገሩ ታምር የሆነበት ሁለተኛ ምክኒያት ልክ ከሰዎች ጋር እንዳለን ንግግር የእግዚአብሔር ንግግር ለእኛ ከመግባቢያነት ያለፈ መሆኑ ነው። ንግግሩ ከእራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንዲኖረን፤ እንድናውቀው እና እንድንወደው የሚያስችለን መንገድ ነው። ባል የውድ ሚስቱን ድምጽ ከማንም አብልጦ እንደሚያውቀው እና ለጆሮው እንደሚማርከው እኛም ድምፁን በመስማት እግዚአብሔርን በእውነት እናውቀዋልን እንወደዋለንም (ማህለይ. 2:14) ።

በቃሉ ያለው የእግዚአብሔር መገለጥ ታምራዊ የሆነበት ሦስተኛው ምክኒያት ደግሞ ቃሉ በአየር ላይ እንዳለ ተራ የድምፅ ርግብግቢት ወይም በወረቀት ላይ እንደሰፈረ ተራ ፅሁፍ ሳይሆን ህያውና ዘላለማዊ መሆኑ ነው (1ኛ ጵጥ. 1:23) ። የምንሰማው እና የምናነብበው ቃል ብቻ ሳይሆን በሚታየው አለም ውስጥ የሚጨበጥ

ህያው የሆነው እና የማይታየው የእግዚአብሔር መገለጥ ነው (1ኛ ዩሀንስ 1:1) ይኸውም እግዚአብሔርን ልናየው ባንችልም ቃሉ ስጋን ለብሶ በልጁ መልክ ተግልጦልናል።

በመጨረሻም እግዚአብሔር ለእኛ መናገሩ የእርሱ ታላቅ የሆነ የበላይነት እና የምህረት ስራ በመሆኑ ቃሉን ታምራዊ ያደርገዋል። በሀጥያት የወደቅን ነንና እራሱን ከእኛ ቢያገልል እና ቢደብቅ አይገባውም ነበር? ነገር ግን ይናገረናል፤ የሚናገረውም ሰላምን ነው።

እግዚአብሔር በአባትነቱ እና በአዳኝነቱ ምህረት ለእኛ መናገር የቻለው ሥጋን ለብሶ በመጣው፣ በምናነብበው እና በምንሰብከው ቃል መካከል ሊነጣጠል የማይችል ቁርኝት ስላለ ነው። አንደኛው ያለ ሌላኛው ሊኖር አይችልም። በተጻፈው ቃል ብቻ ሥጋ የለበሰውን ቃል እናውቃለን፤ ያለ ቃሉ እግዚአብሔር ይገለጣል እያሉ የሚያወሩ ሰዎች ቢኖሩም ለእኛ ከተጻፈው ቃል ውጭ ሌላ መንገድ የለም። የተጻፈውንም ቃል ሥጋ የለበሰው ቃል ካልገለጠለት በቀር ማንም ሊረዳው እና ሊቀበለው አይችልም።

ይህንን ስንል በሁለቱም ጥግ ልንሸሸው የሚገባ ስህተት አለ። በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፎ ያለቀ መጽሐፍ ነውና ከክርስቶስ ጋር ህብረት ማድረግ እና ድምጹን መስማት ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይቻላል የሚለውን እሳቤ አለመቀበል ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበቡ ነገር ግን ክርስቶስን በውስጡ አላገኘነውም ማለት (ዩሀንስ 5:39-40) ሳይገባን በከንቱ ድካም እየለፋን መሆኑን መርሳት የለብንም።

መጽሐፍ ቅዱስን እንዳንጠራጠር እና እንዳንረሳ ከጥንት ጀምሮ በጽሑፍ ተቀምጠው በእግዚአብሔር ከነይዘታቸው ተጠብቀውልናል። እግዚአብሔርም እራሱን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መግለጥ የፈለገው በዚህ ቃል ብቻ ነው። ክርስቶስ እንዲህ ይላለና "እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው" (ዩሀንስ 5:39) ። ስለዚህም በቅን አእምሮ መጽሐፍትን ልብ እንበል (ዕብ 2:1) ።

## መጽሐፍ ቅዱስ

የእግዚአብሔርን ቃል በጽሑፍ ማስቀመጥ ለምን አስፈለገ? እግዚአብሔር በግዜያት መካከል እራሱን በተለያየ መንገድ ለህዝቡ አሳውቆ የለም? ከመጻፉ በፊት ቃሉን አስቀድሞ አልሰጠንም?

ከጽሑፎች መካከል ለመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አክብሮት ስንሰጥ እና የህይወታችን ሆነ እምነታችን ዋና መሪ አድርገን ስንወስደው ጣዖት አምላኪነት አይሆንብንም?

"ሰው ሁሉ ውሸታም እና የከንቱ ከንቱ ነውና"[3] ስለዚህም እግዚአብሔር ቃሉን በጽሑፍ መልክ ካቀረበበት መጽሐፍ ውጪ ቃሉን የማንቀበልበት እና የማንፈልግበት ዋነኛ ምክኒያት ይህ ነው። የተጻፈውም ቃል የተናገረውን ለመካድ፣ ለመለወጥ እና ለመመረዝ በጣሩት ሁሉ ላይ እንደ ምስክር ይቆማል።

ይህንን ስንል የተጻፈልንን የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች ሳይጠመዝዙ ይሰማሉ ወይንም ደግሞ አለመታዘዛቸውን አቁመዋል እያልን አይደለም። ነገር ግን ቃሉ በጽሑፍ መቀመጡ ለዚህ ተግባራቸው ምክኒያት እንዳይሰጡ ያለሰበብ ይተዋቸዋል ማለታችን ነው።

ፍጥረት በስድስት ቀን ተፈጥሯል የሚለውን ሀሳብ በዘፍጥረት 1 እና በተጨማሪም ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጥልንን መለኮታዊ አፈጣጠር ሊክዱ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ዝም ማለት እንዳለባቸው እንደሚያስተምር ሊክዱ አይችሉም። ይህንን ትምህርት ጊዜ ገደብ እና ባህል ገደብ ሊሉት ይችላሉ ነገር ግን ቃሉ የሚለው ግልጽ ነው። በመካዳቸውም የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ሳይሆን የዘላለምን ህይወት ያጣሉና (ራዕይ 22:18-19)።

ሰው ሁሉ ከሀዲ እና የእግዚአብሔርን ቃል ለእራሱ ምቾት የሚያጣምም ከመሆኑ ባሻገር በፍጥረታችን እንኳን የተበላሸን እና የተዋረድን ከመሆናችን የተነሳ በነብያት፣ በመላዕክት ወይም በጆሮኣችን ቀጥታ ቃሉን ቢነግረን መልዕክቱ አይገባንም ነበር። በእርግጠኝነት ቃሉን እናበላሸው እና ከአገባቡም ውጪ እንረዳው ነበር።

በጽሒፈት ቃሉን ባይሰጠን ኖሮ የነገረንን እንኳን አናስታውስም ነበር። ከእኛ መካከል ያለፈው እሁድ የተሰበከውን ስብከት ሙሉ በሙሉ ስያዘንፍ የሚያስታውስ አለ? ማን ነው አጣርቶ እንደሰማ እና እንደሚያስታውስ እርግጠኛ መሆን የሚችለው? ለአንድ ንግግር ሁለት ምስክሮችን ብታቆሙ በእርግጠኝነት የተለያየ መረዳታቸውን ይነግሯችኋል።

ከዛም ባለፈ እግዚአብሔር ከተናገራቸው ነገሮች መካከል ለእኛ የማይስማሙን እና ለመስማት የማንፈልጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ስንሰማቸው ድካማችንን እና ሀጥያታችንን ስለሚያጎሉብን ልንረሳቸው

ወይም ደግሞ ከድካማችን እና ከሀጥያታችን ጋር በሚሄድ መልኩ ልንተረጉማቸው እንፈልጋለን ። ሰዎች በተጻፈው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ይህንን ማድረግ ከቻሉ ቃሉ ባይጻፍ ኖሮ ይህንኑ ከማድረግ የሚያግዳቸው እንደሌለ ማረጋገጫ ነው።

ታዲያ አልሰማንም ወይንም አጥርተን አልሰማንም እንዳንል በጥበቡ እና በምህረቱ እግዚአብሔር የተጻፈውን ቃሉን ሰጠን። እኛም ለቃሉ ሊሰጥ የሚገባውን ክብር እየሰጠን ስለእግዚአብሔር እና ስለፈቃዱ ለማወቅ ሌላ ቦታ በመሄድ አንባዝን።

## የመጽሐፍ ቅዱስ በቂነት

እንደ ደቀመዛሙርቱ ከክርስቶስ ጋር ብታሳልፉ፣ ታምራቶቹን ብታዩ፣ ትምህርቱንም ብትሰሙና በገሊላም በይሁዳም ብተከተሉት የሚበልጥ ጠንካራ እምነት እና የተቀደሰ ህይወት ይኖረን ነበር ብላችሁ አስባችሁ ታውቁ ኖሯል? ጴጥሮስ ይህንን እንዳናስብ ቅዱስ ቃሉን እንደዚህ ገልጾታል “ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን” (2ኛ ጴጥ. 1:19) ። “የእርሱን ግርማ አይተን” (ቁ. 16) ይህንን ካዩ ደቀመዛሙርት የተሻለ እና የተረጋገጠ ነገር አለን። ይህንን አስተውሉ! መጽሐፍ ቅዱስ በቂ ነው ከሚል በላይ የጸና እና ዋጋ ያለው ጠንካራ እውነት ከየት ይመጣል?

ጴጥሮስ ምን እንደሚል አብረን እንመልከት። በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡16 -18 ላይ ጴጥሮስ ስለክርስቶስ መልክ መቀየር ይናገራል። ከሞቱ ጥቂት ጊዜ በፊት በገሊላ ተራራ የክርስቶስ መልክ መቀየሩን ያስረዳል። ይህንን ታሪክ በተመሳሳይ በማቴዎስ 17:1-8, ማርቆስ 9:2-8 እና ሉቃስ 9: 28-36 ማግኘት ይቻላል። አብረውት የነበሩት ሦስት ደቀመዛሙርት እነርሱም ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዩሀንስ ክርስቶስን ብቻ ሳይሆን ሙሴን እና ኤልያስን አይተዋቸዋል ደግሞም እግዚአብሔር እራሱ ስለክርስቶስ ሲመሰክር ሰምተውታል። ከዛ በላይም ክርስቶስን በሰማያዊ ክብሩ አይተውታል እኛም ደግሞ ልክ እንደ እነርሱ ዳግም ሲመጣ እናየዋለን። ከዚህም ሀሳብ በመነሳት ጴጥሮስ በቁጥር 16 ላይ ስለ ክርስቶስ “ኃይልና መምጣት” ይናገራል ማለት ነው። ከዚህ የሚበልጥ ታዲያ ምን አለ?

ጴጥሮስ “እኛስ? እንዴት እርግጠኛ ልንሆን እንችላለን? አላየነውም። የክብሩም የአይን እማኞች አልነበርንም” ብለን እንዳንስብ ይህንን ጻፈልን። ጴጥሮስ ገና ጥያቄያችንን ሳናቀርብ - መጽሐፍ ቅዱስ የጸና የትንቢት ቃል

ነው - ብሎ መልሱን መልሶልናል። ከአይን እማኝነት ይበልጣል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ በቂ ነው እያልን በእርሱ ውስጥ ለእምነት እና ለህይወት የሚሆነን ነገር ሁሉ እናገኛለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የጸና ቃል የሆነው ለምን እንደሆን ታውቁ ኖሯል? ጴጥሮስ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ስለመጻፉ በመናገር ይህንን ያብራራልናል፡ “ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ” (2ኛ ጴጥ. 1:21) ። በሌላ አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የተለያዩ ጽሐፊዎች መጻፍ ስለፈልጉ አይደለም። ምን መጻፍ እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው እነርሱ አልወሰኑም። ያስታወሱትን ነገር ሁሉ፣ ያመሳከሩበትን ምንጮች በሙሉ፣ እቅዳቸውን፣ በእጆቻቸው ሲፅፉት እና ሲያርሙት መንፈስ ቅዱስ ይህንን ሁሉ እንዲያደርጉ አንቀሳቀሳቸው። “ተነድተው” የሚለው ቃል ትርጓሜ ይህ ነው። አጻፋቸው! እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ውጤቱም መጽሐፍ ቅዱስ በጨለማ ስፍራ የሚያበራ ብርሃን እንዲሆን ነው። ይህ አለም የሞት ጥላ መንደር እና በእግዚአብሔር ቁጣ የተያዘ ምድር ነው (ኢሳ 9:2, 19)። መጽሐፍ ቅዱስ በአዲሱ ሰማይ እና ምድር ላይ ጨለማ እንደሌለ በዚህ ምድር ደግሞ ንጋት እንደሌለ ይነግረናል። በመንፈሳዊ እይታ ይህ አለም ሁሌም ጨለማ ብቻ ነው። በዙርያችን እንደምናየውም በመጨረሻዎቹ ቀናት ጨለማው እየከበደ እየመጣ ነው። የንጋቱ ኮከብ ክርስቶስ እስከሚወጣልን ድረስ በጨለማ ውስጥ ያለን ብቸኛው ብርሃናችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ስለዚህም ለመጽሐፍ ቅዱስ ልብ ስጡ። ልባሱ ከተዘጋ ሊያበራ አይችልም። እለተ እለት አንብቡት። እግዚአብሔርም በልባችሁ ብርሃኑን እንዲያበራላችሁ እየጸለያችሁ አጥኑት። የከበረውን እውነታ አሰላስሉ። በህይወታችሁም መንገድ ላይ እንዲበራ ፍቀዱለት ብርሃኑንም ደግሞ ተከተሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍ

የመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ አጻጻፍ ከዶክትሪኖች ሁሉ የሚበልጥ ዶክትሪን ነው። በሃይማኖት እና እግዚአብሔርን በመምሰል ውስጥ ያለ የትኛውም ዶክትሪን ሆነ መመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ የመነጨ ነው። ያለ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርንም ሆነ የላከልንንና የዘላለም ህይወት የሆነውን ክርስቶስ ማወቅ

አንችልም። እግዚአብሔር ስለ እራሱ በክርስቶስ የሚገልጠው ነገር ሁሉ በቃሉ ውስጥ አለ። ያለ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን እንዴት ማስደሰት እንደምንችል ልናውቅ አንችልም ምክኒያቱም ለቅድስና ያለን ብቸኛ መመርያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል ካልሆነ የሁሉን ነገር መሰረት እናጣለን ማለት ነው።

2ኛ ጢሞቴዎስ 3:15-17 መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት ተጽፏል የሚለውን ዶክትሪን/አስተምህሮ ያስተምራል። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ቃሉን "የእግዚአብሔር መንፈስ" በማለት አስቀምጦታል *(በእግዚአብሄር መንፈስ አነሳሽነት* የትጻፉ ቃላቶች ሁሉ አንድ ግሪክ ቃል አላቸው የእርሱም ትርጓሜ "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" ነው) ። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ስራ እንደሆነ ይህ ሃሳብ በደማቅ ገልጾታል ("እስትንፋስ" እና "መንፈስ" በግሪክ አንድ ቃል ናቸው) ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በቃል ንግግር ነው ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ስለሆነ ፍጹም እና ግድፈት የለሽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን መቃረን እግዚአብሔርን መቃረን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ የእግዚአብሔርን ጣፋጭ ድምጽ እንሰማለን፤ መልካም መዓዛ ያለውን እስትንፋሱን እናሸታለን፤ ከንፈሮቹም "እንደ አበቦች ናቸው፥ የሚፈስስ ከርቤንም ያንጠበጥባሉ" (ማህለይ 5:13) ። ማን ታድያ ደፍሮ ይህንን ቃል ይነቅፋል?

በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ መለኮታዊ *አነሳሽነት* ስለመጻፉ ብቻ ሳይሆን *በመላ ፍጹማዊነት* በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ስለመጻፉ ይናገራል። ይህንንም ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉት ክፍሎች በሙሉ፤ የተለያዩ የጽህፈት ዘይቤ ያላቸው ሆነ የተለያዩ ሀሳብ አዘል ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ አነሳሽነት ተጽፈዋል። ዶክትሪን ብቻ ሳይሆን ስነ መልክአምድሩ፣ ታሪክ፣ ስነ ፍጥረት፣ ባህል፣ እና የህይወት ዘይቤ ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ስለተጻፈ እንከን የለሽ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ አነሳሽነት በመጻፉ ለአራት ዋና ነገሮች ይጠቅማል። እነርሱም ፦ ለአስትምህሮ፣ ለተግሳሣጽ፣ ለማቅናት፣ እና በቅድስና ላለ መመሪያነት ናቸው (ቁ. 15 -17)። ይህንን ሀሳብ ስንመለከት ያማረ የመጽሐፍ ቅዱስ ብቁነትን በእነዚህ አራት ሃሳቦች ውስጥ እናያለን። ለድህነት የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለንና። የድህነትን መንገድ ያመለክቱናል (የአስተምህሮ ትርጉም ይህ ነው)፤ ሀጥያታችንን በመኮነን ወደመንገዱ ያመለክቱናል (የማቅናት ትርጉም ይህ ነው) ፤ ኃጢአታችንን ባንረዳ ኖሮ የክርስቶስ እና መስቀሉ ጥቅም አይገባንም ነበር። በማቅናት ደግሞ

በመንገዱ እንድንሄድ ይጠብቁናል፣ ማለትም ስንደክም እና ስንቅበዘበዝ እንደገና ይመልሱናል ማለታችን ነው። በመንገዱም ላይ ያሳድጉናል (መመሪያ በመባል የተተረጎመው ቃል ኤፌሶን 6:4 ላይ “አሳደገ” ተብሎ ተተርጉሟል) ። ወደ መንፈሳዊ እድገት፣ ፍፁምነት፣ እና በክርስቶስ ወዳለው ክብር ይመሩናል። በክርስቲያን ህይወት ውስጥ ከዚህ የበለጠ አስፈላጊ ነገር የለም! መጽሐፍ ቅዱስም በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ ጥበብ ያሳድገናል “ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል” (ቁ. 15)።

ታዲያ ምን የቀረብን ነገር አለ? ስለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደሆኑ እንቀበል እንደ አግባባቸውም እንጠቀምባቸው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ መላ ፍጹማዊ በመንፈስ መነሳሳት

መላ ፍጹማዊነት የሚለው ቃል “ሙሉ በሙሉ” የሚለውን ቃል ያመላክታል። ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ መላ ፍጹማዊ በመንፈስ መነሳሳት ብለን ስንናገር የምናወራው መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጽፏል ለማለት ነው።

ለዚህ እውነት ትኩረት መሰጠት አለበት ምክኒያቱም የተለያዩ ሰዎች በመንፈስ አነሳሽነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈ እናምናለን እያሉ የመንፈስ ቅዱስ መላ ፍጹማዊነት ስራን ግን ይክዳሉ። አንዳንዶች በዘፍጥረት ከምዕራፍ 1-3 ያለውን ክፍል አይቀበሉም፣ አንዳንዶች ደግሞ ጳውሎስ ሴቶች በቤተክርስቲያን ሊኖራቸው ስለሚገባው ቦታ የተናገረውን አይቀበሉም፤ ሌሎች ደግሞ ሮሜ 9 ስለ ሉዓላዊ ምርጫ የሚመሰክረውን እና ስለ አስቀድሞ መወሰን የሚናገረውን መቀበል አይፈልጉም። መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ አስተምህሮ እና የድህነት ትምህርት ቢኖረውም የሥነ-መልክዓምድር፣ የፍጥረት ታርክ እና ታሪክ ላይ ግን ችግር ሊኖረው እንደሚችል ያስባሉ። ይህም ማለት መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ አነሳሽነት እንደተጻፈ አያምኑም ማለት ነው።

እንደዚህ የሚሉ ሀሳቦች ቢኖሩም እኛ ግን በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ አነሳሽነት እናምናለን ይህም ሀሳብ ብዙ ትርጉሞች አሉት።

በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ አነሳሽነት ተጽፏል ስንል ቅዱሳት መጻሕፍት (እነርሱ ብቻ) በእግዚአብሔር አነሳሽነት ተጽፈዋል ማለታችን ነው። ከእነርሱ መካከል ያነሰ ወይም የሚበልጥ ስልጣን ሆነ አስፈላጊነት ያለው የለም። ሁሉም እኩል ናቸው።

ሁለተኛው ምልከታ ደግሞ ቅዱሳት መጽሐፍት በተለያዩ የሥነ-ጽሁፍ አይነቶች እንዲጻፉ ተደርገዋል። ይህም ማለት ታሪክ፣ ግጥም፣ ደብዳቤዎች፣ ትንቢቶች ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው እና የሚጠቅሙ ናቸው ማለት ነው (2ኛ ጢሞ 3:16) ።

ሦስተኛው ደግሞ ፍጹም (ሙሉ በሙሉ) አነሳሽነት ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ዘርፎች በሳይንስ፣ በተፈጥሮ ታሪኮች፣ የሰዎች ታርክ እናም በሥነ-መልክአምድር ጉዳዮች ሁሉ ላይ በአነሳሹ መንፈስ ተጽፏል ማለት ነው። ደግሞም የሚያስደንቁ ምሳሌዎችን ስለዚህ መመልከት እንችላለን። መሬት ክብ እንደነበረች ሰዎች በማይቀበሉበት ዘመን እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክብነቷ ተናግሯል (ኢሳ. 40:22) ። ሳይንስ ስለ ውኆች ዑደት ከመረዳቱ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አስረድቷል (መዝ. 104:5-13) ። መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር አነሳሽነት ተጽፏል የሚለው እምነት መጽሐፍ ቅዱስ ሊሳሳት ይችላል የሚለውን ሀሳብ ያጥለዋል ማለት ነው።

አራተኛው ትርጓሜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከህይወታችን ጋር እንዲሄድ ተደርጎ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ተጽፎልናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉ ትዕዛዛት ሆነ ልናሟላቸው የሚገቡን ነገሮች በጊዜ ወይም በባህል የተገደቡ አይደሉም። በሰዎች በኩል የተሰጠን ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ የሚለን ነገር ሁሉ ከዘላለማዊው እግዚአብሔር ተሰጥቶናል ስለዚህ ይሄ ከእኛ ባህል እና ጊዜ ጋር አይጣጣምም ብለን ወደጎን የምንገፋው ጉዳይ የለም።

አምስተኛ ፍጹም አነሳሽነት ስንል የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዋሰው፣ ቃላት፣ እና አገባብ በመንፈስ አነሳሽነት ተጽፈዋል ማለታችን ነው። እግዚአብሔር በዘፍጥረት 17:7 ላይ ዘርህ እንጂ ዘሮችህ አለማለቱ ትልቅ ልዩነት አለው (ገላ. 3:16 ይመ) ። በእምነት መጽደቃችን እንጂ በእምነታችን አለመጽደቃችን እጅግ ትልቅ ልዩነት አለው (የፊተኛው ቀድሞ የተሰራ ስራ እንዳለ ያመለክታል የኃላኛው እምነታችን ስራው እንደሆነ ያመለክታል) ። እያንዳንዱ ደብዳቤ፣ ቃል፣ እና ዓረፍተ ነገር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በትልቅ ጥንቃቄ ሊተረጎም ይገባዋል። በፍጹም የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ስለምናምን የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን አንቀበልም። ምክኒያቱም እነዚህ መጽሐፎች በትክክለኛው ትርጉም እና በሰዎች ማብራሪያ

መካከል ያሉ ድርድሮች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ እንደምሳሌ ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥንን (NIV)ን መጥቀስ እንችላለን።

ይህንን ትምህርት እንደ ተራ ስብከት ከማየት አልፈን መጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም እና ግድፈት የሌለሽ የእግዚአብሔር ቃል አድርገን እየወሰድን አለም ሁሉ እንኳን ቢቃረነን ቃሉን ሳንጠራጠር፣ በሙላት እየተቀበልነው፣ እየተገዛንለት፣ እየታዘዝነው እና እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ በመቀበል እንጸናለን ወይንስ አንጸናም? በፍጹም የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ላይ ያለን እምነት የሚፈተነው በዚህ ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍ

መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል በመንፈስ ቅዱስ ስለመጻፉ ያለው ዶክትሪን ከመላ ፍጹማዊ የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ዶክትሪን ጋር ተዛማጅነት አለው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የንግግር መድረክ ነው።

ይህንን አትኩሮት ሰጥተን የምንናገረው አንዳንዶች እግዚአብሔርን በመፍራት መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳው አስተምህሮን እና ዶክትሪንን እንጂ እያንዳንዱን ቃል እና ዝርዝር አይደለም ብለው ስለሚቀባጥሩ ሀሳባቸውን ለመቃረን ነው። እንደዚህ አይነት ትምህርት በአጭሩ መዛከር ነው ምክኒያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እና ሀሳብ በመንፈስ ተነሳስቶ የተጻፈ ነው ለማለት ሰዎች ሀሳቡን ለመጻፍ የሚጠቀሙት ቃላቶችም በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፉ እና ግድፈት የለሽ መሆን አለባቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍ እኛን የኢንጊሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ ክርስቲያኖች የንጉስ ያዕቆብ ዕትም (KJV) እንድንጠቀም ያደርገናል። ከዚህ ዕትም ዋነኛ ባህሪዎች መካከል አንዱ በዕብራይስጥ እና በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ነገር ግን በኢንጊሊዘኛው ቋንቋ አቻ የሌላቸውን ቃላቶች *በኢታሊክስ (italics)* ያስቀምጣቸዋል። ሙሉ የሆነን ትርጉም ለማግኘት እነዚህን አቻ ለሌላቸው ቃላቶች ተመሳሳዮቻቸውን ማስገባት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ነገር ግን በዚህ መልኩ በማስቀመጥ እነዚያ ቃላቶች በሰዎች የተጨመሩ እንጂ የእግዚአብሔር ቃል በቃል ንግግር እንዳልሆኑ አንባቢያን ማወቅ አለባቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍን የሚያስተምሩ የተለያዩ ክፍሎች አሉ። ለምሳሌ፡- መዝሙር 12:6 ፣ ምሳሌ 30:5 ፣ እና ራዕይ 22:18-19 እግዚአብሄር የተናገራቸው እና እንዲጻፉ ስላደረጋቸው *ቃሎች* የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው (መዝሙር 50:17 ፥ መዝሙር. 119:130) ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ቃል በቃል የተናገራቸው ንግግሮች እጅግ አስፈላጊ እንደሆኑ የሚናገሩ አስገራሚ ዶክትሪኖች ወይም አስተምህሮች አሉ። በተጨማሪም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ደግሞ የቃላት አመራረጥ ትልቅ የትርጉም ልዩነትን ሲያመጣ እናያለን።

ዘፍጥረት 17:7 ላይ *ዘርህ* ሳይሆን *ዘሮችህ* ተብሎ ቢቀመጥ የአብዢ ቃላት ልዩነት ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ መምጣት ትንቢት መሆኑ ይቀር ነበር (ገላ. 3:16ን ይመ.) ። በአዳዲሶቹ ትርጉሞች ይህ ስለክርስቶስ የሚያወራው ክፍል ሙሉ በሙሉ የለም ምክኒያቱም በዘፍጥረት 17:7 ላይ ያለውን ክፍል "ከትውልድ" ጋር በሚል ተተርጉሟል (ይህ የሚገኘው በNIV ዕትም ላይ ነው) ።

አንዳንድ ጊዜ በመጀመሪያው ቋንቋ የተጻፉ ጉዳዮች ሀሳቡን ለመረዳት ከባድ ያደርጉታል እንደምሳሌም ዕብራውያን 11:11 መመልከት እንችላለን። በዚህ ክፍል ላይ ሳራ ልጅ ለ"መጸነስ" ሀይልን ተቀበለች ይላል። የግሪኩ ተተካካይ ቃል በተለመዶ ለተባዕት "አስገኘ" ወይም "ወለደ" የሚልን ትርጉም ይሰጣል። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለተጠቀሰ የእኛ ስራ ይህንን ቃል የተጠቀመበትን ምክኒያት መረዳት ነው እንጂ ከእኛ ሀሳብ ጋር በሚስማማ መልኩ መተርጎም አይደለም የNIV ዕትም ይህንኑ ሲያደርግ እንመለከታለን። የNIVው ዕትም መልሶ አብርሃም አባት መሆን ቻለ በሎ ያስቀምጠዋል ነገር ግን በዛ ቁጥር ላይ አብርሃም በጭራሽ አልተጠቀሰም። እንደነዚህ አይነት ለውጦች የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል በመንፈስ አነሳሽነት መጻፍን ይክዳሉ።

ተመሳሳይ የሆኑ መጥቀስ የምንችላቸው ስህተቶች አሉ ነገር ግን ሊቀርልን የሚገባው ሀሳብ እግዚአብሔር የሚለውን ሁሉ በጥሞና ማዳመጥ እንዳለብን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ዋና ሀሳብ ወይም ፍሬ ነገር አውቀናል ብሎ መርካት በቂ አይደለም። በጥንቃቄ እና በትክክል እርሱን መስማታችንን፣ ማመናችንን፣ እና መታዘዛችንን ማረጋገጥ አለብን። እራሱን ለእኛ በጥንቃቄ ለመግለጥ ቃሉን በጽሁፍ ካስቀመጠልን ቃሉን በጥንቃቄ የማናዳምጠው፣ የማንታዘዘው፣ እና ደግሞ የእግዚሃብሄር ቃል ንጹህ መሆኑን የማናምነው እኛ ማን ሰለሆንን ነው (መዝ. 12:6)?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ህይወት አዘልነት

መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች በኩል በመሰጠቱ ብዙዎች ይሰናከላሉ። ምክንያታቸውም የሰዎች ሀሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ሊካተት ይችላል የሚል እምነት ነው፤ ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል፣ ስህተት የለሽ፣ እርስ በእርሱ የማይቃረን እና የሰዎች ጉድለት የማይገድበው መሆኑን አያምኑም።

መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች በኩል መሰጠቱን አንክድም። ነገር ግን ይህ በጣም አላስፈላጊ/የማያሳስብ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ ከስድሳ ስድስቱ መጽሓፍት ውስጥ የአስራ ሁለት መጽሓፍት ጸሓፍያንን አናውቅም። ጸሓፊውን በምናውቅባቸውም መጽሐፍት ህያው የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት እውነታነቱ አይቀየሬ ነው።

ህያው የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ማለት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ከመጻፋቸው በፊት መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ አነሳሽነቱን ዘመናትን አስቀድሞ ጀምሮ ነበር ማለታችን ነው። የመክብብን መጽሐፍ እንደምሳሌ በመውሰድ ህያው አነሳሽነት የሚለውን ሀሳብ መመልከት እንችላለን - እግዚአብሔር የመጽሐፉን መጻፍ ያነሳሳው ሰለሞንን በአንዴ አስነስቶ እንዲጽፍ በማድረግ አይደለም (2ኛ ጴጥ. 1:21) ነገር ግን ሰለሞን ብቁ ጸሓፊ እንዲሆን እና ለመጻፍ የሚያስችሉትን ሁናቴዎች ሁሉ አስቀድሞ በማዘጋጀት እንጂ።

ሰለሞን የመክብብን መጽሐፍ እንዲጽፍ እግዚአብሔር ማነሳሳቱን የጀመረው ከመቶ እንዲየውም ከሺህ አመታት በፊት ሲሆን ታሪክን እየቀለሰ፣ በእስራኤል እና በነገስታት መካከል የነበሩትን ክንዋኔዎች ሁሉ ለሰለሞን እንዲሆነው አድርጎ አስቀድሞ አሰናዳለት። የአይሁድን መንግስት፣ የአስራ ሁለቱን ነገድ፣ ከእነርሱም ከይሁዳ ነገድ ቤተሰብ አንዱ የሆነውን የእሰይን ቤተሰብ ሲመሰርት እግዚአብሔር ከብዙ አመታት በፊት ለዚህ መጽሐፍ አነሳሽነቱን መጀመሩን እንመለከታለን። እግዚአብሔር ዳዊትን ሲያነግስ፣ ከእርሱ ቀጥሎ የሚወርሰውን ልጁን ሰለሞንን ደግሞ ሲያነግስ፣ ለመክብብ መጽሐፍ መጻፍ እያመቻቸ ነበር። ዳዊት ቤርሳቤህ ስትታጠብ ሲመለከት፣ ከቤርሳቤህ ጋር ሲያመነዝር ፤እርሷን ለማግባት ባለቤቷንም ሲያስገድል እግዚአብሔር ለመጽሐፉ መጻፍ ሁሉን እያሰናዳ ነበር።

እግዚአብሔር የሰለሞንን ህይወት ሲያሰናዳ ከክርስቶስ ባሻገር በአለም ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ (ከክርስቶስ በቀር) ጥበበኛ እና ደግሞ ከባድ በሆነም ሀጥያት የወደቀ ሰው እንዲሆንም ሆኗል። ስለዚህም የመክብብ መጽሐፍ ሲጻፍ የሰለሞን ንስሃ እና ያለ እግዚአብሔር ህይወት ከንቱ መሆኑን መስካሪ መጽሐፍ ሆነ።

በመጨረሻም የህያው የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ወደ ስላሴ መማክርት እና በምድር ሁሉ ላይ እግዚአብሔር አስቀድሞ በሉዓላዊነቱ ያልደነገገው እና ወደመሆን ያላመጣው አንዳች ነገር እንደሌለ ወደሚያስረዳው እውነት

ይመራናል። እኛ እንኳን ንሰሃ እየገባን እና እያመንን የደህንነታችን ባለቤት መሆን ካልቻልን እና የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃድ ነው ካልን ሰለሞንስ መክብብን ከእራሱ ልምምድ ተነስቶ ቢጽፍም የመጽሐፉ እውነተኛ ባለቤት መሆን እንዴት ይችላል? የሉዓላዊው እግዚአብሔር እና የመንፈሱ ዘላለማዊ ፈቃድ በህያው ቃሉ በኩል የድህነታችን እና ደህንነትን ያሳወቁን መጽሐፍት ጀማሪ እና ፈጻሚ ነው። እንዴት ትልቅ አምላክ ነው! እንዴት የሚደንቅ መጽሐፍ ነው!

## የመጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት የለሽነት

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ፍጹም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ተሳስቷል ማለት እግዚአብሔር ተሳስቷል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት ሊኖረው ይችላል ብሎ ማሰብም የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት እና ኢ-ተለዋጨነትን መካድ ነው።

ዩሀንስ 10:35 የመጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት የለሽነትን በግልጽ ያስረዳናል። በዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ “መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና” ይላል። የሚጠቀመውም ነጠላ ቃል “መጽሐፉ” የሚለው ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሰዎች እና በተለያዩ ግዜያት የተጻፈ ቢሆንም አንድ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያመለክተናል። አንድ ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስን ለመቀየር የሚደርግ ጥረት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን ከማጥፋት ጋር አንድ ነው። ማንም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ክፍሎችን እየካደ መጽሐፉን ተቀብያለው ማለት አይችልምና።

ክርስቶስ መጽሐፉን አትሻሩት ሳይሆን መጽሐፉ ሊሻር አይችልም ማለቱ የሚያስገርም ነው። ይህንንም ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስህተት ለማግኘት ሆነ የሚያዛቸውን ትዕዛዘት ለመሻር ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ከንቱ ልፋትን ይለፋሉ ማለቱ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስህተት ለማግኘት የሚጥሩት ጥረት እግዚአብሔርን እና እርሱ የቀባው ላይ ምክር ወይንም ሀሳብ ለመስጠት የሚያደርጉትን ሙከራ ያሳያል፣ በሰማያት ላይ የተቀመጠውም ይስቅባቸዋል (መዝ. 2:2-4) ። መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን እነርሱ እራሳቸው ይሻራሉ ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስህተት ለማግኘት ስለሚጥሩ በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ይጣላሉ።

የዩሀንስ 10:35 ዐውደ ንባብን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው፣ ክርስቶስም በዚህ ክፍል ብሉይ ኪዳንን በመጥቀስ አምላክነቱን ያጸናልና። መዝሙር 82:6 የምድርን ነገስታት *ኣማልክት* ብሎ አስቀምጦታል። እነርሱ

አማልክት ከተባሉ በአብ ተቀድሶ ወደ ምድር የተላከልን እርሱ “የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ” ቢል እግዚአብሔርን መሳደብ አይደለም በማለት ክርስቶስ በዩሀንስ 10:35 ላይ ይናገራል። ታዲያ “እንዴት የምድር ነገስታት አማልክት ይባላሉ?” ወደ ሚለው ጥያቄ ሳንገባ ክርስቶስ የተናገረውን የሚደንቅ ንግግር ልብ እንበል። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይህ ባይጻፍ እኛ እንደዚህ የማለት ድፍረቱ አይኖረንም ነበር፤ ተጠቅሶልን እንኳን ለመረዳት ይከብደናልና። ስለዚህም ኢየሱስ ይህንን ንግግር እውነት እና ግድፈት የሌለበት መመሪያ አድርጎ የወሰደው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኝ ነው። እርሱም ቃሉን የጠቀሰበት እና መጽሐፍ ቅዱስን የተጠቀመበት መንገድ “መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና” የሚለውን ጭብጥ መልዕክት የሚያስረዳ ነው።

ኢየሱስ የመዝሙር 82ን ቃል “ህግ” ነው ማለቱ ከዋና ሀሳቦች ውስጥ አንዱ ነው። እርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት የሌለው የእግዚአብሔር ቃል ነውና መለኮታዊ የሕይወት ህግ እና መርህ ነው ይለናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሁሉ ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና ። ይህንንም ስንል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለእኛ ያልፈቀደው ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሚያስፈልገን አንዳች ምክር የለም። ታሪክ ቢሆን፣ ግጥሞች ቢሆኑ፣ ትንቢቶች ቢሆኑ፣ ደብዳቤዎችም ሁሉ ለእኛ የተሰጡ የእግዚአብሔር ህግጋት ናቸው፤ ይህም ከሁሉ የሚበልጥ መረዳት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት የለሽ እና ፍጹም ነው ብቻ ማለት በቂ አይደለም። ለቃሉ መስገድ አለብን፤ ለትምህርቱ በየትኛውም ጉዳይ ላይ መገዛት እና እንደ ፈቃደኛ እና ታዛዥ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ትምህርቱን መቀበል አለብን። ይህ ካልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት ተጽፏል እና ግድፈት የለሽ ነው ብለን የምናውጀው የእምነት አቋም ተራ ግብዝነት ይሆንብናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ግድፈት የለሽ እንደሆነ ታምናለህ/ታምኛለሽ? እንግዲህ ይህንን ጥያቄ እራስህን/ሽን ጠይቂ/ቅ፡ “በድርጊቴ እና በማምነው ሁሉ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሆነ መመሪያዬ/ ህጌ ነው?”

## የመጽሐፍ ቅዱስ ባለስልጣንነት

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፈ እና ግድፈት የለሽ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ከፍተኛው ባለስልጣን ነው። ከእርሱ በላይ የሆነ የሰው ህግ ፣ አገዛዙን የሚበልጥ ሌላ ሰው ሰራሽ አገዛዝ፤ ሆነ ትምህርቱን መጻረር የሚችል ምንም አይነት ትምህርት የለም።

በዶክትሪን/በአስትምሮ ሁሉ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ባለስልጣን ነው። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ አስተምህሮ/ዶክትሪን ከሁሉም በፊት መቅደሙ ይህንን ያስረዳናል። ክፍሉ በዋነኝነት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ቢያወራም መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ የሆነው ስልጣን ስላለው እንደሆነ ግን ከዚሁ ክፍል እንረዳለን። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በጉዳዮች ሁሉ በተለይም ደግሞ በዶክትሪን ዙሪያ አሳራጊ ቃል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያናዊ ኑሮ እና ልምምድ ሁሉ ላይ ተመሳሳይ ስልጣን አለው። ከብዙ ሺህ አመታት በፊት የተለያየ ባህል ላላቸው ህዝቦች መጻፉ በስልጣኑ ላይ ለውጥ አያመጣም። ምክኒያቱም ቃሉ የሁሉ ነገር ጀማሪ እና ፈጻሚ የሆነው እና የማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የዚህ አለም ባህል ቢለወጥም የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን እና ቃሉን መቀየር አይችልም።

ሴቶች በቤት እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ስላላቸው ቦታ ጳውሎስ የጻፈበት ባህል ከእኛ የሚለይ ባህል መሆኑ የተናገረውን ቃል አይሽረውም። ምክኒያቱም ቃሉ የጳውሎስ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ነውና።

የዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቃል በአሁን ጊዜ ያሉትን የሀሰት ትምህርቶች እና ልምምዶችን አስቀድሞ ማሳሰቡ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት መጻፉን ለሚያምኑ ሰዎች እጅግ የሚያስገርም ነው። በ2ኛ ጴጥሮስ 3:1-7 የሚገኘው ክፍል ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዩኒፎርሚቴሪያኒዝምን በመጥቀስ ዝግመታዊ ለውጥ የሚለውን ሀሳብ ሲገድለው እናያለን

ዩኒፎርሚቴሪያኒዝም ማለት ሁሉም ነገር ከአለም ፍጥረት ጀምሮ እንደነበር ሳይለወጥ ይቀጥላል የሚል እሳቤ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን በታሪክ፣ በሥነ-መልክአምድር፣ በሥነ-ጥበብ፣ ሆነ በየትኛውም ትምህርት ሁሉ ላይ ሀሳብ ስላለው የበላይ ስልጣኑ የተጠበቀ ነው። ስልጣኑም በሥነ-መለኮት እና ክርስቲያናዊ ኑሮ ላይ ብቻ አይደለም። ስልጣኑ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ አማኝ ከሳይንስ ተቃርኖ በሚቀርብበት ጊዜ እንኳን መጽሐፍ ቅዱስን ማመን አለበት።

የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን የእራሱ የእግዚአብሔር ስልጣን እንደሆነ መረዳት አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ካልን ባለ *ሙሉ* ስልጣን ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን መካድ እግዚአብሔርን መካድ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስን መቃረንም እግዚአብሔርን መቃረን ነው።

ማንም የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ ሀሳብ ተቀብሎ ሌላውን አልቀበልም ማለት አይችልም። ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን ተቀብሎ ስለፍጥረት የሚናገረውን ሀሳብ አለመቀበል አይችልም። ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ሁሉም በእግዚአብሔር ስልጣን የከበረ ነው። እግዚአብሔር ሆነ የእግዚአብሔር ቃል በፈቃዳችን የምንቀበለው ሆነ የምንሽረው አይደለም። ቃሉ ሊሻር አይችልም (ዩሀንስ 10:35) ።

የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ማወጅ አንድ ነገር ነው፤ ነገር ግን ለእርሱ መገዛት ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው። በክርስቲያናዊ ህይወታችን የተኛውም ቦታ ላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን ተገዢነት ይፈተናል። እንዲሁም ደግሞ ከፈቃዳችን ጋር ሲተላለፍ አልያም አስተምህሮው ከስጋዊ ፍላጎቶቻችን ጋር ሲጻረር (ሁሌም እንደሚጻረረው) መጽሐፍ ቅዱስን መቀበል ከባድ ነው።

ስለዚህም በጸጋው ብቻ መታዘዝ እንችላለን። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን እንደሰጠን የሚያስፈልገንንም ጸጋ በዛው ልክ ይሰጠናል። ቅዱስ አውስጢኖስ ጋር በመስማማት ይህንን እንላለን "ትእዛዝህን ስጠን፤ ፈቃድህንም እዘዝ"[4] ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ማንም በእራሱ የመተርጎም ስልጣን የለውም። ሰዎች የራሳቸው የመተርጎም መብት እንዳላቸው ያስባሉ። የእኔ "አተረጓጎም" ወይም የሌሎች ሰዎች አተረጓጎም ሲሉ ብዙ ጊዜ እንመለከታለን። ይህ ደግሞ ስህተት ነው (2ኛ ጴጥ. 1:20) ። በመጨረሻም አንድ ተቀባይነት ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም አለ እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ እራሱን በእራሱ የሚተረጉምበት መንገድ ነው። ትርጓሜ የእግዚአብሔር እንጂ የሰው አይደለም።

ከተሓድሶ ዋና መመሪያዎች መካከል መጽሐፍ ቅዱስ እራሱን ይተረጉማል የሚለው አንዱ ነው።ይህ ለመረዳት ግር የሚለን ሀሳብ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ጸሐፊው እርሱም የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ሊናገር የፈልገውን ሊያብራራልን ስልጣን እና ኃይል አለው። የእኔ መረዳት ሆነ አተረጓጎም አንዳች ዋጋ የለውም። የእግዚአብሔር ትርጉም ብቻውን ዋጋ አለው።

2ኛ ጴጥሮስ 1:20-21 መጽሐፍ ቅዱስ *በግላችን* የምንተረጉመው መጽሐፍ እንዳልሆነ በግልጽ ሲያስተምረን እንመለከታለን። ሀሳቡ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት መጽሐፍ ቅዱስ መጻፉ ላይ እንጂ አተረጓጎሙ ላይ የሚያተኩር ስላልሆነ ይህ ንግግር ከቦታው ያለአግባብ የተወሰደ ይመስላል። ነገር ግን የዚህ ክፍል ምልከታ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ ካነሳሳው ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የመተርጎም ስልጣን የለውም የሚል ነው።

መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ይተረጉማል ነገር ግን በረቂቅ መንገድ አይደለም - ማለትም በድብቅ እና በሚስጥራዊ መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም መገለጥ ለእኛ በግላችን አይሰጠንም። "እግዚአብሔር አሳይቶኛል" ወይንም "እግዚአብሔር ይህንን ገለጦልኛል" ማለት ትክክል አይደለም። እንደዚህ አይነት ንግግር የመጽሐፍ ቅዱስ በቂነትን ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት መጻፉንም ይጻረራል። ይህንን የሚል ሰው እግዚአብሔር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ለግሉ የሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት አለ አያለ ነው። ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የሚኖረው መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእራሱ ሲነፃጸር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለን ቃል ለመረዳት የምንፈልግ ከሆነ፥ ለምሳሌ "ጥምቀት" ሚለውን ቃል ብንወስድ ይህንን ቃል የተለያዩ ክፍሎች ላይ ከነአገባቡ በማየት እና በማነጻጸር ትክክለኛውን ትርጓሜ እና መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን እንዴት ለመጠቀም እንደፈለገ መረዳት እንችላለን። ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ትርጓሜ ከእራሱ እንድንረዳ ጥንቁቅ ጥናት አስፈላጊ ነው። አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያለ ጥናት መረዳት እንደሚችል የሚያስብ ሰው ሞኝ እና ትዕቢተኛ ነው።

ስለዚህም የእራሳችንን ሀሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳንቀላቅል መጠንቀቅ እና በትህትና እና በጸሎት የሚለውን መቀበል አለብን። ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ለመረዳት ጸጋ፣ መገዛት እና ጸሎት ያስፈልገዋልና።

ማንም ሰው፣ የወንጌል አገልጋዮችም ቢሆኑ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ነን ማለት አይችሉም። እያንዳንዱ አተረጓጎም፣ እያንዳንዱ የሀይማኖት ትምህርት፣ እና እያንዳንዱ ስብከት ጽኑ የመፈተሻ ብርሃን በሆነው በእግዚአብሔር ቃል መፈተን አለበት። ምክኒያቱም ማንም በግሉ መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም መብት የለውም። የሐዋርያት ስብከት እንኳን በጥንቃቄ ተመርምሮ እና ሂስ ተስጥቶበታል (ሐዋርያት 17:10-11) ። ስብከት ሁሉ እንደሌላው በመንፈስ ቅዱስ ካለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ጋር መስማማት አለበት።

ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንድንፈልግ እና እንድናገኘው፣ የሚገባውንም ክብር እንድንሰጥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ጸጋ አብዝቶ ይስጠን! (ዕብ. 2:1)

## የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት

የእግዚአብሔር ቃል፣ ጸሐፊውም መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስም አንድ ነው። እግዚአብሔር በስድሳ ስድስት የተያዩ ድምጾች አይናገርም ሊናገርም አይችልም። እርሱ በኃይል፣ በአላማ፣ እና በህልውናው አንድ ነው። እርሱ አንድ እንደሆነ ቃሉ እና መገለጡም አንድ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መሆኑ እጅግ ዋና ጉዳይ ነው። በአንድነቱ ምክኒያት መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእራሱ አይጻረርም። አንዱ መጽሐፍ ከሌላኛው መጽሐፍ፣ የብሉይ ኪዳን ትምህርት ከአዲስ ኪዳን ጋር ትምህርት ጋር ወይንም ደግሞ አንድ ጸሐፊ ከሌላኛው ጸሐፊ ጋር አይቃረንም።

ስለዚህም አንዳንዶች “የጳውሎስ ሥነ-መለኮት” ከኢየሱስ ሥነ-መለኮት ጋር ወይንም ከጴጥሮስ ሥነ-መለኮት ጋር ይለያያል ያላሉ ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም። አልያም ደግሞ ፍቺን ወይንም ሴቶች

በቤተክርስቲያን ያላቸውን ቦታ እና የመሳሰሉትን ሀሳቦች በማንሳት ኢየሱስ ከሙሴ፣ ከጳውሎስ እና የዩሀንስ የተለየ ምልከታ አለው ማለት አይችልም።

የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት አስተምህሮ ዲስፐንሴሽናሊዝምን ይቃወማል። ዲስፐንሴሽናሊዝም ማለት በብሉይ እና አዲስ ኪዳን፣ በእስራኤል እና በአዲሷ ቤተክርስቲያን መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም የሚል እሳቤ ነው። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረው ኪዳን እና አሁን ከአዲሲቷ ቤተክርስቲያን ጋር ያለው ኪዳን የተለያየ ነው የሚለው የባፕቲስት አስተምህሮ የመጽሐፍ ቅዱስ አንደነትን ይክዳል። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ነው ስለዚህም ሁለት እና ሦስት የተለያዩ ቃል ኪዳኖችን አያስተምረንም።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ከሆነ ሌላ መገለጥ፣ ሌላ ኪዳን፣ ሌሎች የእግዚአብሔር ህዝቦች፣ ወይንም ደግሞ የተለያዩ የመዳኛ መንገዶች ሊኖሩት አይችልም። የዲስፐንሴሽናሊዝምን ትምህርት እና የአማኝ ጥምቀትን የማንቀበለው እነዚህን ትምህርቶች የሚቃረኑ ክፍሎችን ብቻ ይዘን ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነው ሊሻርም አይችልም የሚለውን ክፍል ጭምር ይዘን ነው (ዩሀንስ 10:35) ።

በአዲስ ኪዳን ከተደገሙ የብሉይ ኪዳን አስተምህሮዎች በቀር በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ላይ ብሉይ ሊዳን ስልጣን የለውም ማለት የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነትን መካድ ነው። በብሉይ ኪዳን የተጻፈው ሁሉ ለእኛ ለአዲስ ኪዳን ክርስትያኖች ተጽፎልናል (1 ቆሮ 10:11) ።

ኢየሱስ በዩሀንስ 10:35 ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት በእርሱ ላይ እንደተፈጸመ ያስታውሰናል። ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ የአዳኛችን የክርስቶስ ኢየሱስ እና በእርሱ በኩል የመጣልን የእግዚአብሔር ጸጋ መገለጥ ነው። ቻርለስ ስፐርጀን እንዳለው “መጽሐፍ ቅዱስን የቱም ጋር ብትገምሱት የበጉ ደም ይፈስሳል።”[5] በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ክርስቶስን ማግኘት አላማችን ሊሆን ይገባል ይህንንም ስናደርግ በእርግጠኝነት መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ድምጽ እንደሚናገር እንረዳለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት አስተምህሮ ሌሎች አስተምህሮችን ለመገምገም ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት እጅግ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ከሆነ የትኛውም ክፍል ከሌላው ተነጥሎ ሊጠና፣ ሊታመን ሆነ ሊጠቀስ አይችልም። ከእግዚአብሔር ቃል ተነስተን የምናስበው ሆነ የምንናገረው ነገር የትኛውንም ክፍል አይቃረንም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ጊዜ ሰጥተን ልናጠናው እና ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው አስተምህሮውን በጥልቀት ልንረዳው ይገባል።

ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት አስተምህሮ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አስፈላጊ በመሆኑ የትኛውንም ክፍል ልንዘነጋው እንደማይገባ ያስተምረናል። መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ፣ ማንበብ፣ ማጥናት፣ መማር እና የሚገባውን ክብር መስጠት አለብን። አንተ ይህን ታደርጋለህ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ብሩህነት

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብሩህነት ሰምታችሁ ምናልባትም ደግሞ ትርጉሙ ምን ይሆን ብላችሁ ጠይቃችሁ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ብሩህ ነው ስንል ግልጽ እና በቀላሉ መረዳት የምንችለው መጽሐፍ ነው እያልን ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ድንቅ ታምራቶች መካከል አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ብሩህነት ሲሆን የእግዚአብሔርን ማንነት ለእኛ ይገልጥልናል። እርሱ ዘላለማዊ እና ወሰን የለሽ አምላክ ሆኖ ሳለ ለእኛ እራሱን መግለጥ ብቻ ሳይሆን በቀለለ መንገድ አብራርቶ ማንነቱን ማስረዳቱ የሚያስገርም ነው።

ይህንን ስንል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት የሚከብዱን ክፍሎች ወይንም መጽሐፍት መኖራቸውን እየካድን አይድለም ምክኒያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ይህንን ያስተምረናልና (መዝ. 78:2 2ኛ ጴጥ. 3:16) ። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት አስተምሮን፣ ስለ እግዚአብሔር ክብር እና ስለ ድህነታችን ልናውቅ የሚያስፈልገንን ሁሉ በግልጽ እንደሚያስተምረን መረዳት አስፈላጊ ነው።

መዝሙር 119:105 ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብሩህነት ያስተምራል- “ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።” መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ባይሆን ብርሃን ተብሎ አይሰየምም ነበር። ደግሞም ይህ ክፍል በግልጽ ለመንገዳችን እና ለሕይወታችን መጽሐፍ ቅዱስ መብራት መሆኑን ይነግረናል ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታችንን ወደ እግዚአብሔር ክብር የሚመራ አስተማማኝ መመሪያ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ በመሆኑ ያልተማሩ ሰዎች እና ህጻናት ይረዱታል። ስለዚህ ያልተማሩ ስዎች እና ህጻናት መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያነብቡ ሊከለከሉ አይገባም። ወንጌል ለሚሰበክላቸው ህዝቦች በሙሉ እንዲያነብቡት እና ይህ ብርሃን እስከመጨረሻው አብሯቸው እንዲሆን በቋንቋቸው ሊተረጎምላቸው ይገባል።

ወደ ስህተት እንዳንገባ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ብሩህነት ልንረዳቸው የሚገቡን ነጥቦች አሉ።

የመጀመሪያው ነጥብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት የሚያዳግቱ ክፍሎች በመኖራቸው ሁሌም በቀለለ መልኩ ሀሳቡን የሚያብራሩ ክፍሎችን እንደ ፋኖስ በመጠቀም እነርሱን መተርጎም አለብን። ለመረዳት ከሚከብዱ ክፍሎች የምናገኘው ትርጉም ከዋና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች እና በግልጽ ከተማርናቸው የሕይወት መርሆች ጋር ሊቃረኑ አይችሉም።

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ለአማኞች ብቻ የተገለጠ መሆኑ ነው። ያላመነ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት አይችልም ይህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እውቀት በመሆኑ ትርጓሜው በመንፈስ ብቻ ይስተዋላል (1ኛ ቆሮ. 2:14) ። የመጽሐፍ ቅዱስን ዋና እውነታዎች ለምሳሌ የክርስቶስ ኢየሱስ አምላክነትን የማይቀበል ሰው ስናነጋግር ይህንን ማስታወስ አለብን። እንደዚህ አይነት ሰው ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ባለመቻሉ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እውነትን እንደሚናገር መጠራጠር የለብንም። ችግሩ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይደለም። ችግሩ የዛ ሰው ልብ እና አእምሮ ነው። ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ነገር ከመረዳቱ በፊት ልቡ መከፈት እና አእምሮው በመንፈስ ቅዱስ መብራት አለበት። ይህ ከሌለው ማስረጃዎች፣ ሥነ- አመንክዮ(ሎጂክ)፣ እና ክርክር ፋይዳ ቢስ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ብርሃን በመሆኑ ብርሃኑን ሁሌም መከተል አለብን። የ1ኛ ዩሀንስ 1:6-7 ቃልኪዳን እና ማስጠንቀቂያ ለእኛ ተሰጥቶናል- “ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።”

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች

የእግዚአብሔርን ቃል በሚያነቡበት ጊዜ ሰዎች ቃሉን በቀጥታ ማግኘት እስከሚያቅታቸው ድረስ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መብዛት እጅጉን ጨምሯል። በየጊዜው እየተሰራ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንደ ኢምንት ጉዳይ የምናልፈው አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የእውነትም በቂ እና በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ትርጓሜን መጠቀም እጅግ አስፈላጊ ነው።

ጥሩ ነው የምንለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ከመንገሬ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ሰዎች በቀላሉ ከተወሰደባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የትርጓሜዎች መብዛት መሆኑን እንድታስተውሉ ላሳስባችሁ። ብዙ ትርጉሞች ከመኖራቸው የተነሳ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲሰበክ ሆነ ሲጠቀስ የምናውቀው ወይንም ከዚህ ቀደም ሰምተነው የምናውቅ አይመስለንም። ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ልጆች በመማራቸው መጽሐፍ ቅዱስን ቶሎ የመሸምደድ እና የማስታወስ አቅማቸው ተዳክሟል። በቤታቸው አንደኛውን ትርጉም ይሰማሉ፣ ትምህርት ቤት ሌላኛውን ይሰማሉ፣ ሌላኛውን ደግሞ በቤተክርስቲያናቸው፣ አንዳንድ ልጆች ደግሞ የተለያዩ ህብረቶች እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ላይ በሌላ ትርጉም ይሀንኑ ክፍል ይሰማሉ ግን አንዱንም ማስታወስ አይችሉም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የበዙት በስልጣኔ፣ በሀይማኖት ክህደት፣ እና በጥርጣሬ ዘመን እንጂ ቤተክርስቲያን ጠንካራ እና ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ በሆነችበት ዘመን አለመሆኑ ብዙ ነገር ያመላክታል። ይህ ብቻውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን እንድንጠራጠር በቂ ምክኒያት ነው። አብዛኛዎቹ ቃል በቃል ትርጓሜዎች ሳይሆኑ የቃሉን ይዘት በእራሳቸው አረዳድ የሚተረጉሙ ናቸው። ለምሳሌ "ሊቪኝግ ባይብል (The Living Bible)" መጥቀስ ይቻላል ፤ አንዳንዶች ደግሞ በቀጥተኛ ትርጉም እና በራስ መረዳት ትርጉም መካከል ሲሆኑ ለዚህም ምሳሌ የ"NIV"ን ዕትም መጥቀስ ይቻላል።

እንድትጠቀሙበት የምንመክረው ብቸኛው የኢንጊሊዘኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ዕትም የ"KJV ወይም (King James Version)" በብሪቴን ውስጥ ደግሞ አውቶራይዝድ ቨርዥን (Authorised Version) ተብሎ የሚጠራውን ዕትም መሆኑ ግልጽ ሳይሆንላችሁ አልቀረም ። ወደዚህ ትርጓሜ ለመጠቆማችን ብዙ ምክኒያቶች ቢኖሩንም ዋናው ምክኒያት ታማኒ እና ቀጥተኛ የግሪክ እና የዕብራይስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜን መጠቀማቸው ነው። የዚህ ሀሳብ እውነታ ግልጽ በመሆኑ የ1603 G.C KJV ዕትም የ1600ዎቹ የኢንጊሊዘኛ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤን አይጠቀምም፤ ነገር ግን የግሪኩን እና የዕብራይስጡን ትርጓሜ በታማኝነት ለመተርጎም በጣሩት ጥረት "መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኢንጊሊዘኛ አጻጻፍ ዘይቤ" እንዲፈጠሩ ሆኗል። ከKJV ዕትም አንዱ የታማኒነት ምሳሌ ከዕብራይስጥ እና ከግሪክ ወደ ኢንጊሊዘኛ ትርጉም የሌላቸውን ቃላት *በኢታሊክስ (italics*) ማስቀመጡ ነው።

የKJVን ትርጉም በታ ለማስጠበቅ ይህንን እላለሁ፣ የዘመኑ ዕትሞች የKJV ትርጓሜዎች በጊዜያቸው ያላወቁት ጽሁፍ ወይንም መጽሐፍ ላይ የተመሰረቱ ናቸው የሚለው ሀሳብ በጭራሽ ትክክል አይደለም።

ከእነርሱ ጊዜ በኃላ የተገኙ ጽሁፎች ቢኖሩም እንኳን ሌሎች የብራና ዕትሞችን ያውቁ ነበር። እነርሱ ያውቋቸው የነበሩት ጹሑፎች ግን አንዳንዶቹ የጥንት ናቸው፣ በተጨማሪም ደግሞ በውስጣቸው ብዙ ግድፈት እና ልዩ ልዩ ለውጦች ተካትተውበታል። አብዛኞቹ ከ(80-90%) ያሉት የብራና ጽሑፎች ግን “የተሰጠው መጽሐፍ (Received Text)” ከሚለው ጋር ይስማማሉ፤ የKJV ትርጓሜም እዚህ ላይ የትመሰረተ ነው።

እንደ KJVው ዕትም ታማኒ፣ ጥሩ እና ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የሚያስፈልግበትን ምክኒያት ተርጓሚዎች እራሳቸው ገልጸውታል -“ትርጉም ብርሃንን ለማስገባት መስኮቱን የሚከፍትልን ፤ የለውዙን ፍሬ እንድንበላ ገለባውን የሚፈትግልን፤ ቅድስተ ቅዱሳንን እንድናይ መጋረጃውን የሚገልጥልን ፤ውሃውን እንድናገኝ የምንጩን ክዳን የሚያነሳልን ነው።”[6] ስለዚህም እግዚአብሔር በአቅርቦቱ እና በጸጋው ለሰጠን ቃሉ ታማኝ እንሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪም የሚያረካ ነገር አይኑረን።

## እግዚአብሔርን ማወቅ

የክርስትና ሀይማኖት አጠቃላይ ጉዳይ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። የክርስትና አላማ፤ የመጨረሻው ግብ እና ጥረት፣ እና ታላቁ በረከት እርሱን ማወቅ ነው። ክርስቶስ በዩሀንስ 17:3 ላይ እንደሚለው፣ ይህቺ የዘላለም ሕይወት ናት።

እግዚአብሔርን ማወቅ ብቸኛው እውነተኛ እውቀት ነው። ያለእርሱ ወይንም ከእርሱ ተለይተን እኛ ራሳችንን ማወቅ አንችልም። ይህ እውነት የሆነው እኛ የተበላሸ እና አታላይ ልብ ያለን ሀጥያተኞች ስለሆንን ብቻ ሳይሆን (ኤር. 17:9) በእግዚአብሔር የተፈጠርን እና ከእርሱ ጋር ባለን ህብረት ልንኖር የተሰራን ስለሆንም ጭምር ነው (መዝ. 30:5)። ያለ እርሱ ማን እና ምን እንደሆንን ልንረዳ አንችልም።

ስራችን እንኳን የሚፈተነው ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ህብረት አንጻር ነው። ማንም ስራው እና ንግግሩ መልካም ይሁን ክፉ ከእግዚአብሔር ፍጹም ቅድስና ጋር ካላነጻጸረው ሊያውቅ አይችልም። ይህ ደግሞ በዚህ ዘመን የሥነ-ምግባር መስፈርቶች እጅግ የወረዱ የመሆናቸውን ምክኒያት ያስረዳናል። አብዛኞች፣ ሀይማኖት አለን የሚሉትን ጨምሮ እግዚአብሔርን አያውቁትም። ለእግዚአብሔር ነገር ጭፍን በመሆናቸውም ምንም አይነት የሥነ-ምግባር መስፈርት የላቸውም።

እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ስለእግዚአብሔር ዶክትሪኖችን እና እውነታዎችን መሸምደድ አይደለም። ምንም ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ቢሆኑም ይህንን ስንል ስለእግዚአብሔር የሚያስተምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪኖች እና አስተምህሮዎች አስፈላጊ አይደሉም ለማለት አይደለም። እውቀት የእምነት አካል ነው ያለ እምነትም እውቀት ከንቱ ነው። አንድ ሰው ስለእግዚአብሔር ምንም ሳያውቅ እርሱን አምናለው ማለት አይችልም። ነገር ግን እግዚአብሔርን ማወቅ ከዚህ እጅግ የላቀ ነው፤ እጅግ የላቀ ረቂቅ በመሆኑም አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን ሁሉ በአእምሮው ሸምድዶ፣ ምናልባትም ደግሞ ከልጅነቱ ተምሮት እግዚአብሔርን ግን ላያውቀው ይችላል።

እግዚአብሔርን ማወቅ *ልምምድም* ነው። እግዚአብሔር እጅግ የላቀ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው በአእምሮው ልፋት እና በእውቀት ትጋት ሊያውቀው አይችልም። ሊተዋወቀው፣ ሊሰማው፣ አብሮት ሊሄድ እናም ሰው ጓደኛውን እንደሚያውቀው እርሱን ሊያውቀው ይገባል። በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ስለማወቅ ይናገራል፤ "*ማወቅ*" የሚለው ቃል "*ፍቅር*" ከሚለው ቃል ጋር አቻው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የጋብቻን የፍቅር ጥልቅ ግንኙነት ለመግለጽ ባል ሚስቱን የሚያውቅበትን መንገድ እንደሚናገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ማወቅ ልክ እንደዚሁ ነው ይለናል። እርሱን አለመውደድ እርሱን በእውነት አለማወቅ ነው።

ስለዚህም እግዚአብሔርን ማወቅ በእርሱ መደሰት ነው፤ ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ ነው፤ እርሱን መታዘዝ ነው። ጸጋው፣ ምህረቱ እና ክብሩ እጅግ ግሩም በመሆኑም በእርሱ ደስ የማይሰኝ እና የማይወደው ሰው እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ ማለት አይችልም። ይህ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር የሚናገረውን ነገር በጥልቀት ቢያውቅም እግዚአብሔርን እየካደው፣ እየጠላው እና ለእርሱ ጀርባውን በመስጠት የእውነት እግዚአብሔርን እንደማያውቅ እያሳየ ነው። አእምሮው እውር ልቡም ደግሞ የጠነከረ ነው።

እግዚአብሔርን ቃሉ እንደሚገልጸው ታውቀዋለህ? ሁሌም አዲስ፣ እውነተኛ የደስታ ምንጭ እና እንቁ እንደሆነ ትናገራለህ? እርሱን እና ክብሩን በሙሉ ልብ እና በሙሉ ኃይል ተወደዋለህ? በእርሱ ተደሰታለህ? ትታዘዘዋለህ?

## የእግዚአብሔር ስያሜዎች

እግዚአብሔር እራሱን ለእኛ ከሚገልጥባቸው መንገዶች መካከል አንዱ በሥያሜዎቹ በኩል ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ብዙ ስሞቹን ለእኛ ሰጥቶናል። መጠሪያዎቹም እጅግ ብዙ የሆኑት እግዚአብሔር ታላቅ እና ክብሩም የማያልቅ በመሆኑ ነውና እያንዳንዱ ስም ስለእርሱ ማንነት ቢናገርም ሁሉም ቢሰበሰቡ የእርሱን ወሰን የለሽ ምስጋና ሊገልጹ አይችሉም።

ስሞቹን በምናጠናበት ወቅት የእግዚአብሔር መጠሪያ ከእኛ ስም ጋር ተመሳሳይ እንዳልሆነ መረዳት ቁልፍ ጉዳይ ነው። የእኛ ስም ሊቀየር የሚችል መጠሪያ ሲሆን ስማችን ቢቀየር እንኳን ምንነታችንን እና ማንነታችንን አይቀይርም።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ስሞች ምንነቱን እና ማንነቱን ይገልጹልናል። እግዚአብሔር እንደማይቀየረው ሁሉ እነዚህ መጠሪያዎችም አይቀየሩም። አንዳንዶች እንደሚያደርጉት እነዚህን ስሞች ያለ አግባብ እና ያለ አገባብ መጠቀም እግዚአብሔርን ማቃለል ነው ስለዚህም እግዚአብሔር ስሙን እንደ ከንቱ፣ ትርጉም እና ቅድስና የለሽ አድርጎ የሚጠራውን ሰው የፈርድበታል።

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ታላቅ ሀጥያት ነው። ይህ ሀጥያት ከአስርቱ ሦስተኛው ትዕዛዝ ሲሆን ትላቅ ቅጣት አለው፤(ዘጵ. 20:7) የዚህ ግልባጭ ሀጥያት ደግሞ የእግዚአብሔርን ስም በጭራሽ አለመጥራት ነው። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ በመጥራቱ ይፈረደበታል ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስም ባለመጥራቱም ደግሞ ይፈረድበታል።

ሦስተኛው ትዕዛዝ እንደ አስርቱ ትዕዛዛት የሚከለክለው ብቻ ሳይሆን የሚያዝዘውም ጉዳይ አለ፤ ትዕዛዙም ደግሞ በቅድስና፣ በክብር እና እግዚአብሔርን በሚያደንቅ መልኩ ስሙን እንድንጠራ ነው። የእግዚአብሔርን ስሞች በዘፈቀደ ሳይሆን ማንነቱን ገላጭ እንደሆኑ እያስተዋልን መጥራት መለማመድ አለብን።

ስንጸልይ የእግዚአብሔርን ስም ወደ አእምሯችን በመጣልን መልኩ እንጠራዋለን ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ እንድንጸልይ አያስተምረንም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም በጥንቃቄ ሲጠራ እና የሚጠቀመውም ሰው ከሚያቀርበው ልመና ወይንም ምስጋና እና አምልኮ ጋር የሚሄድ፤ አንድ የተወሰነን የእግዚአብሔር የማንነት እውነትን ለማጉላት ይጠራዋል።

ለምሳሌ *ጅሆቫ* የሚለውን ስም ለልጆቻችን የገባውን ኪዳን እያሰብን እግዚአብሔርን ለመለመን መጠቀም እንችላለን። ለዚህ ልመና ከ*ጅሆቫ* የሚበልጥ ስም የት አለ! ደግሞ ሀጥያታችንን ስንናዘዝ *ቅዱስ* የሚለውን ስም በመጥራት በእውነት እራሳችንን ዝቅ በማድረግ ትክክለኛ ንሰሃ ማቅረብ እንችላለን።

አይሁዳዊያን *ጅሆቫ* የሚለው ስም ቅዱስ እና ፍጹም በመሆኑ በፍርሃት አለመጠቀማቸው ትክክል አልነበረም ምክኒያቱም እግዚአብሔር ስሙን የሰጠን እንድንጠቀምበት፤ ከእርሱ ጋር እንድንነጋገርበት እና ስለ እርሱ እንድናወራበት ነው። ከእርሱ ጋር አለመነጋገር እና ሰለእርሱ ከሌሎች ጋር አለማውራት ማለት እግዚአብሔር እንደሌለ መቁጠር፤ እርሱን መካድ እና እርሱን መቃወም ነው እኛም ይህንን ደግሞ ማድረግ የለብንም ።

ጥሪያችን የእግዚአብሔርን ስም እንድንጠቀምበት ነው። ስንጠራው ደግሞ በአክብሮት፣ በቅዱስ ፍርሃት፣ በምስጋና፣ በጸሎት ፣ ስለእርሱ በመናገር እና እርሱን በሚያከብር መልኩ መሆን አለበት። ያኔ ብቻ እርሱን የእውነት በመታዘዝ እና ስሙንም በአግባብ በመጥራት ህይወት ውስጥ እንኖራለን።

ስሞቹን ታውቃላችሁ? ስሞቹንስ ትጠቀማላችሁ?

## *ጅሆቫ* የሚለው ስም

*ጅሆቫ* የሚለው ስም ከእግዚአብሔር ዋና ስሞች መካከል አንዱ ሲሆን በKJVው ዕትም **ጌታ** ተብሎ ተተርጉሟል። በተጨማሪም ይህንን ስም የ*ኢየሱስ* ስም ውስጥ ተሰርጎ እናገኘዋለን። በኢየሱስ ስም ውስጥ በኢንጊልዘኛው ትርጉም Je (ጂ) - የሚለው ቃል ከ Jehovah (ጅሆቫ) ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ የቃል አመሰራረት አለው። ይህንን መሰል የቃል አመሰራረት ያላቸው ስሞችም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ (Eli-JAH/ ኢላ - ጃ, Jo-shua/ ጆ-ሽዋ, JEHO-sahphat/ ጆ-ሳፋት, እና JE-dediah/ ጀ-ደዳያ)።

እግዚአብሔር *ጅሆቫ* የሚለውን ስም ለሙሴ እና ለእስራኤል የገለጠው የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚያስታውስ እና እስራኤልን ከግብጽ ባርነት እንደሚያላቅቅ ምስክር እንዲሆናቸው ነው (ዘጽ. 3:11-15) ። በወቅቱም የ*ጅሆቫ*ን ትርጉም አብሮ ሰጣቸው፡ “እግዚአብሔርም ሙሴን። <<ያለና የሚኖር>>እኔ ነኝ አለው፤ እንዲህ ለእስራኤል ልጆች። <<ያለና የሚኖር>>ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው” (ዘጽ. 3:14) ።

ስለዚህም *ጅሆቫ* የሚለው ስም የእግዚአብሔር ኢ-ተለዋጭነትን ይገልጥልናል። የተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ *ኣሉ*፤ *ነበሩ*፤ *ወደፊትም* አላቸው። እነዚህ ሁሉ በጊዜ ቀመር ውስጥ ይቀያየራሉ፤ እግዚአብሔር ግን ትላንት፣ ዛሬ፣ ወይንም ነገ የለውም። እርሱ *ነው*! ለመረዳት የሚያዳግት ሀሳብ ቢሆንም ለእኛ ትናንት ወይንም ነገ የሆነልን ነገር ለእርሱ ነገም ሆነ ትናንት አይደለም። ሁሉም ነገር ለዘላለም በፊቱ ነው፤ ለእርሱም አመታት ሆነ ሚሊንየሞች ምንም ለውጥ አያመጡም። እኛ በለውጥ ውስጥ ስለምንኖር እና ሁልጊዜም እየተለወጥን ስለሆነ ይህንን ማሰብ እንኳ እጅግ ይከብደናል፡ "ለውጥ እና መበስበስ በማየው ሁሉ አለ"[7] ። መረዳት አለመቻላችንም የአምላክነቱ ሌላ ማመላከቻ ነው ምክኒያቱም እርሱን ፍጹም መረዳት ብችል ከእኛ ትንሽ እና ደካማ አእምሮ በምን ይበልጥ ነበር?

ዘጸአት 3 የሚያመላክተን *ጅሆቫ* የሚለው ስም እግዚአብሔር ከህዝቡ *ጋ*ር ባለው ግንኙነት የማይቀየር አምላክ መሆኑን ነው። የእርሱን ኢ-ተለዋጭነት የሚያብራራው በማይጨበጥ መልኩ ሳይሆን በፍቅሩ፣ በምህረቱ፣ በቃል ኪዳኑ፣ በጸጋው እና የእራሱን ህዝብ ለማዳን እና ለመባረክ ባለው የማይለወጥ ማንነት ነው።

ይህ ስም የእግዚአብሔር ህዝቦች ከዘላለም ጀምሮ እና የማይለወጡ የራሱ ህዝቦች እንደሆኑ ያስታውሰናል ። ህዝቡ የእርሱ *የሚሆኑ* ሳይሆኑ ተራሮች ከመወለዳቸው እና አለም ከመፈጠሯ በፊት የእርሱ ነበሩ ናቸው (መዝ. 90:2) ። ስለዚህም በዘላለም እና በጊዜያት ውስጥ እርሱ መኖሪያቸው ይሆናል።

*ጅሆቫ* የሚለው ስም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም ሲሆን እግዚአብሔርም የቃል ኪዳን አምላክነቱን የገለጠበት ስም ነው። በዘጸአት 3 ላይ ይህ በግልጽ ተጻፏል፡ ኪዳኑን በሚያስታውስበት እና በሚጠብቅበት ጊዜ *ጅሆቫ* የሚለውን ስም እና ትርጓሜውን ገለጠው።

ስለዚህም ጅሆቫ የሚለው ስም የእግዚአብሔርን አለመለወጥ በመግለጥ ታማኝነቱን ደግሞ ያሳየናል። የእግዚአብሔር ታማኝነት ከመረጣቸው እና ከሚወዳቸው የቃል ኪዳን ህዝቡ *ጋ*ር ባለው ግንኙነት ውስጥ ያለው ኢ-ተለዋጭነት ነው። በምንም አይነት መንገድ አይጥላቸውም፣ አይረሳቸውም በዘላለም ፍቅሩም ይወዳቸዋል። በዚህ ፍቅሩም ወደ እራሱ ያቀርባቸዋል።

ታማኝነቱን የሚያውቁ ሁሉ *ጅሆቫ* የሚለውን ስሙን በደስታ እና አብዝተው ይጥሩት። በእርግጥም ከዚህ የሚበልጥ ስም የለም።

## *እግዚአብሔር* የሚለው ስም

*እግዚአብሔር* የሚለው ስም ሁሉን ቻይ ጌታን ለመግለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዛት የተጠቀሰ ስም ነው። ሉዓላዊነቱን፣ ስለ ሥላሴ እና ስለ ወሰን የለሽ ፍጹምነቱም ይናገራል።በብዙ የብሉይ ኪዳን ስሞችም ውስጥ ተካትቶ እናገኘዋለን። ለምሳሌ ኤል-ያስ፣ ኤል-ሳ፣ ዳን-ኤል፣ ናትና-ኤል ውስጥ እግዚአብሔር (በዕብራይስጥ *ኤሎሂም*) የሚለው ስም አጥሮ ሲገባ እንመለከታለን። ስሙ የተካተተባቸው አብዛኞቹ እግዚአብሔር ክብሩን በአንድም በሌላም ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ስዎች በመሆናቸው ነው።

*ኤሎሂም* የሚለው የዕብራይስጥ ቃል በብዙ ቁጥር ቃል ተቀምጧል (ቀጥተኛ ትርጉሙም "አምላኮች" ነው) ። ይህ የሚያሳየን ከአንድ አምላክ በላይ አምላክ አለ ወይንም ደግሞ የእግዚአብሔር ህዝቦች ያመለኩት በብዙ አማልክት ነበር ማለት አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር አንድ ብቻ እንዳልሆነ (ዘፍ. 1:26, እግዚአብሔር እራሱን በብዙ ቁጥር ሲጠራ እንመለከታለን) ፤ ልዩ እና ወሰን የለሽ ፍጹምነት እና ክብርን (አንድ ሆኖ ሳለ በክብር፣ በኃይል፣ በስልጣን ብዙ ነው) የተላበሰ መሆኑን ያሳየናል።

ስለዚህም *እግዚአብሔር* የሚለው ስም በሥነ-መለኮት መነጽር ሲተረጎም "ክቡራን" ወይንም "ኃያላን" የሚለው የብዛት ትርጉም አለው። ይህም እግዚአብሔር መሆኑን ያስተምረናል እንደ እርሱም ያለ ማንም እንደሌለ፣ እርሱ ብቻውን አምልኳችን፣ ምስጋናችን እና መታዘዛችን እንደሚገባው ያሳየናል። ይህ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ መጥራቱም ስለዚህ ምክኒያት አያስገርመንም።

ይሄም ስም እርሱን ከአህዛብ ጣዖቶች ይለየዋል። በአህዛብ እና በአማልክቶቻቸው ላይ አምላክ ነው። *አማልክት* ተብለው የሚጠሩት ማየት፣ መስማት፣ መናገር፣ ወይንም ማዳን ስለማይችሉ በዚህ ውስጥ እርሱ ብቻውን እውነተኛ አምላክ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ነው (መዝ. 115:4-8) ። እነዚህን አማልክትን የሚያመልኩ ሰዎችም ከአምላኮቻቸው በምንም አይሻሉም።

እግዚአብሔር በህዝቦቹ ላይ አምላክ ነው። የሉዓላዊ ጸጋው እና ምህረቱን ክቡርነት፣ የፍቅሩ እና የኃይሉን ግርማዊነት በልዩነት ለእነርሱ ይገልጥላቸዋል። በዕብራይስጥ በብዙ ቁጥር የተቀመጠው ይህ ስም እያንዳንዱን አማኝ እግዚአብሔርን ለማመስገን እና ለማምለክ ያለውን የማያልቅ ምክኒያት ሊያስታውሰው ይገባል። እርሱን ለማናገር ሆነ ስለእርሱ ለመናገር በመፈልግ እነዚህ ነገሮች ላይ አትኩሮት ለመስጠት ስንፈልግ

*እግዚአብሔር* የሚለውን ስም መጠቀም አለብን። እግዚአብሔርን በማይፈሩ ስንፈተን እና በስደት እና በመከራ ውስጥ ስንሆን እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን መርሳት የለብንም።በምናመልከውም ጊዜ ይህንን ስሙን ለመጠቀም አግባብ የሆነበት ቦታ ነው። የአምላክነቱ አካል የሆኑትን ሥላሴን ማንሳት ስንፈልግ ይህንን ስም እንጠቀማለን። በየትኛውም ጊዜ የእርሱን ሁሉን ቻይነት፣ ኃይል፣ እና የማያልቅ ክብር መረዳት ስንፈልግ ይህ ስም ከአፋችን እና ከልባችን መለየት የለበትም።

ስለዚህም ይህንን ታላቅ ስም በአግባቡ እና በስርዓት እንጠቀመው።

## *የሠራዊት ጌታ የሚለው ስም*

*የሠራዊት ጌታ* (1ኛ ሳሙ. 1:3, መዝ. 2፡10፣ ኢሳ. 1:9, ሃጌ 1:2)፣ *የሠራዊት አምላክ* (መዝ. 80:7) ወይንም *የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር* (መዝ 59:5, መዝ 80:4, ኤር 5:14, ኤር 15:16) የሚለው ስም የእግዚአብሔር የተለያዩ ስሞች ላይ "ሠራዊት" ተጨምሮበት ነው ። እግዚአብሔር በሰዎች፣ በመላዕክት እና በአጠቃላይ ፍጥረቱ ላይ ሉዓላዊነቱን የሚያሳይ ስም ነው።

ሠራዊት የሚለው ስም በህይወት ያሉ ፍጥረታትን እና በድን የሆኑትን ፍጥረታትን፡ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ክዋክብት፣ ምድር እና ሞላዋን ሁሉ ይወክላል (ዘፍ 2:1, ዘዳግም 4:19, ነህ 9:6, መዝ 33:6) ። ሠራዊት የሚለው ስም አእላፍ እና በየትኛውም መደብ ላይ ያሉ መላዕክትን (ዘፍ 32:2, 1ኛ ነገሥት 22:19, ሉቃስ 2:13)፣ የጨለማ እና የገሃነም ሥልጣናትን የያዘ፣ በምድር ላይ ያሉ ብዙ ቢሊዮን ህዝቦችን እና ኃይላቸውንም ያካተተ ነው (ዳን 8:10-11, ኤፌ 6:12)።

እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ነው ማለት ፍጥረት ሁሉ በፈቃዱ ሆነ ያለፈቃዱ፣ በሰማይም፣ በምድርም እና በገሃነምም የእርሱን ፈቃድ የሚያደርግ ባሪያ ነው። የሠራዊት ጌታ የሚለው ስምም ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በፍጥረቱ በኩል ስለሚያሳካው አላማ ይናገራል። የበላይ ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ ፈቃዱን በፍጥረት በኩል ለማስፈጸም ይጠቀምባቸዋል። ማንም ሊጠይቀው ሆነ ሊያማክረው አይችልም (ዳን. 4:35) ።

ፍጥረታት በሙሉ እንደ ሠራዊት መገለጣቸውም በውበት አንድነት እንደ ታላቅ ጦር ሥራዊት የእርሱን ፈቃድ ፈጻሚ መሆናቸውን ያሳያል። እያንዳንዱ ፍጥረት በግሉ ሊያገለግለው ይገባል። ወደደም ጠላም እንደ ታላቅ እና ግዙፍ የጦር ሥራዊት አላማውን እና እቅዱን ይፈጽማል።

*የሠራዊት ጌታ* የሚለው ስም እግዚአብሔር የውጊያ እና የጦር አምላክ፣ የቁጣ እና የፍርድ አምላክ መሆኑን ይገልጣል (2ኛ ዜና 20:15, መዝ 24:8, ኢሳ 13:4) ። በሠራዊቱ በኩል ፍርድን፣ ፍትህን፣ እና ጽድቅን እየፈጸመ ጠላቶቹን ያጠፋል ህዝቡንም ያድናል።

*የሠራዊት ጌታ* የሚለው ስም ሰይጣንን ሠራዊቱን እና ህዝቡን የእግዚአብሔር ታላቅ ሥራዊት አካል አድርጎ መግለጡ ይገርማል ምክኒያቱም እነዚህ ሁሉ በራሳቸውም መንቀሳቀስ አይችሉምና። ከሁሉም በላይ የሚገርመው ደግሞ የሁሉን ቻዩ እጅ መሳሪያ ሆነው የእራሳቸውን ፍርድ እና የዘላለም መጥፋት ይፈጽማሉ። በእርሱ ላይ በሚያምጹበት ጊዜ እንኳን አላማውን እየፈጸሙ ነው (ሐዋ 4:28) ። ስለዚህ እነርሱ ሲያምጹ እርሱ ያፌዝባቸዋል (መዝ. 2:4) ። እንዴት ድንቅ አምላክ ነው!

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህንን ስም የእግዚአብሔር ህዝብ በሚያልፍበት ሁናቴ ውስጥ የአምላካቸው ማንነት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ተጠቅሞታል። በሐጌ መጽሐፍ ላይ እግዚአብሔር *የሠራዊት ጌታ* የሚለውን ስም ደጋግሞ ሲጠቀም እናየዋለን ይህንንም ያደረገው እግዚአብሔር እስራኤላዊያን ቤተመቅደሱን እንዳይሰሩ ከከለከሏቸው ጠላቶቻቸው በላይ መሆኑን ለማሳየት ነው። በፍጥረት ሁሉ ላይ ደግሞም እስራኤላዊያኖች እንደ ሰለሞን ያማረን ቤተመቅደስ ለመስራት ሲነሱ በጎደላቸው ወርቅ እና ብር ላይ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነበር (ሐጌ 2:1-9) ። ይህ ለእኛ ዛሬም ሉዓላዊነቱን ያስታውሰናል።

ይህ ሉዓላዊ የሠራዊት አምላክ ደግ አምላክ እንደሆነ እናስታውስ በፈቃዳችንም ለእርሱ እንገዛ።

## *አባት* የሚለው ስም

ለእግዚአብሔር ህዝቦች *አባት* የሚለው ስም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ፍቅር ስለሚገልጽ እጅግ የተወደደ ስም ነው። ይህ ስም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ከህዝቡ ጋር ያለው ቃል ኪዳን ላይ አጽኖት ይሰጣል። ስለዚህም ከእርሱ ጋር ባላቸው ህብረት ከሌሎች ስሞች ሁሉ በላይ እንዲጠቀሙት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራቸዋል (ማቲ 6:9) ።

*ኣባት* የሚለው ስም ከህዝቡ *ጋር* ያለውን ህብረት ብቻ ሳይሆን በሥላሴ ውስጥ ባለው ህብረት ውስጥ እርሱን ይወክላል። *ኣባት* የሆነው እኛን ልጆቹ ሲያደርገን አይደለም ። ይህንን ብንል ኢ-ተለዋጭነቱን ካድን ማለት ነው ነገር ግን እርሱ የሥላሴ የመጀመሪያው አካል ስለሆነ ለዘላለም *ኣብ (ኣባት)* ነው።

በሥላሴ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር አባትነት እና ለእኛ ለልጆቹ ያለው ዘላለማዊ ፍቅር አቻ ናቸው። በዘላለም ውስጥ እኛን መረጠን የአባትነት ፍቅሩንም አካፈለን፤ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለህዝቡ አባት ነው። ይደንቃል አይደል?

አባት የሚለውን ስም ብሉይ ኪዳን ውስጥ ህዝቡ ከጥቂት ክፍሎች በስተቀር ሲጠቀመው አናይም (መዝ 68:5, መዝ 103:13, ኢሳ 9:6, ኢሳ 63:16) ። ይህ ለምን ሆነ?

የእግዚአብሔር ህዝቦች እርሱን እንደ አባት ያላወሩበት እና ስሙን ያላነሱት በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን መካከል ባለው ልዩነት ነው። በሁለቱ መካከል የመርህ ልዩነት የለም ነገር ግን ብሉይ ኪዳን የኪዳኑ ዘመን ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ ኪዳኑ የሚፈጸምበት ዘመን ነበር።

የክርስቶስ በስጋ ወደ ምድር መምጣት *ኣባት* በሚለው ስም ላይ ታላቅ ለውጥ አምጥቷል። በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር እኛን ይቀርበናል፤ ቅዱስ ቤተመቅደስ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ አካልም በእኛ ውስጥ ያድራል (ዩሀንስ 2:19-21) ። በክርስቶስ በኩል የፍቅሩን ግሩምነት ይገልጥልናል ወደ ድህነትም ሙላት ይወስደናል።

ምናልባት የእግዚአብሔር የጉዲፈቻ ልጆች እንደሆንን ብናስብ የበለጠ ጉዳዩን መረዳት እንችል ይሆናል። የብሉይ ኪዳን አማኞች በቃል ኪዳን የእግዚአብሔር ልጆች ነበሩ። ደግሞም የእግዚአብሔር ህዝቦች ለመሆን የተመረጡ እና በእርሱ የተወደዱ እንደሆኑ ተነግሯቸው ነበር። ከህዝቦች ሁሉ ተለይተው የእርሱ ቤተሰብ ነበሩ ነገር ግን እግዚአብሔር ከመጋረጃው ጀርባ ነበር፤ የሚገለጥላቸውም በጥላ እና በተለያዩ ምልክቶች ነበር።

ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ይህ መጋረጃ ተነስቶ ወደ ዙፋኑ እና ወደ መገኘቱ በነጻ መግባት ሆነልን (ዕብ 10:19-22) ። በአዲስ ኪዳን ብቻ እግዚአብሔር እኛን ከመቅረቡ የተነሳ ከክርስቶስ ጋር አንድ ስጋ እና አንድ አጥንት ሆነናል (ኤፌ 5:29-30) ። በአዲስ ኪዳን ብቻ ከዚህ አለም እና ከእስሯ ነጻ ወጥተን እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ልጆች ተቆጠርን (ገላ 4:1-5) ። ስለዚህም በአዲስ ኪዳን ብቻ ከሞት በተነሳው በገናናው ኢየሱስ መንፈስ በኩል በልዩ ልዩ ቋንቋ እና ምድር ሳንያዝ የመለመን እና “አባ አባት” የምንልበት ድፍረት አለን (ገላ 4:6-7) ።

ይህንን ስንል በብሉይ ኪዳን የነበሩ አማኞች ምንም ነገር አልነበራቸውም ለማለት ሳይሆን በአዲስ ኪዳን ያለን የተሻለ ነው ለማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ለጻድቃን ቃል የተገባው ሁሉ ለእኛ በአዲስ ኪዳን ተፈጸመልን። ይህንንም መቼም እንዳንረሳው ይሁንልን።

## የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት

ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እናምናለን ቢሉም በአብዝኞች የምንመለከተው የአፍ ሽር-ጉድ ብቻ መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው ስንል በአጭሩ *እግዚአብሔር* ነው ማለታችን ነው። ይህም ማለት ኤ. ደብሊው ፒንክ *የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት*[8] በተሰኘው ግሩም መጽሐፉ ላይ እንደሚገልጸው እግዚአብሔር እንደ እግዚአብሔርነቱ የሚወደውን በሚወደው ጊዜ ያደርጋል። ይህ ማለት እርሱ *ሙሉ በሙሉ* የነገሮች ሁሉ ተቆጣጣሪ ነው።

እግዚአብሔር በፍጥረታት ላይ ሉዓላዊ ነው። እርሱ በምድር እና በሰማይ ባሉ ነገሮች ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ፈጣሪ ነው። ያለ እርሱ መኖር አይችሉም ለክብሩም ደግሞ ይኖራሉ። የዝግመታዊ ለወጥ ሃሳብ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት መካድ ነው ምክኒያቱም እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ያለውን ቦታ ወስዶ አላማቢስ ለሆነ የእድል ቦታውን ይሰጠዋል።

እግዚአብሔር አዘጋጅ አምላክ በመሆኑ ሉዓላዊ ነው። በፍጥረታት የሚከናወነውን ሁሉ እርሱ ይፈጽማል፣ ይቆጣጠራል ደግሞም ሉዓላዊነቱ ወደሚያመቸው ሁሉ ይመራል። መልካም ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ክፉ ነገሮች ጨምሮ፡ ህመም፣ በሽታ፣ ሞት፣ ጦርነት፣ ዐውሎ ንፋስ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ እና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ሁሉ ከእርሱ ይመጣሉ እርሱም ይጠቀምባቸዋል።

ይህ ቁልፍ እውነት "በተፈጥሮ" በሚያምኑ ሰዎች፣ ክፉ ነገር ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር አይመጣም በሚሉ እና በጸሎታቸው ነገርን መለወጥ *እንደሚችሉ* በሚያስቡ ሰዎች ይካዳል። እግዚአብሔር *እግዚአብሔር* ነው። እርሱ ብቻውን በስልጣን ላይ አለ ያለእርሱም የሚሆን አንዳች ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እግዚአብሔር በአጋንንት እና በመላዕክት ላይ ሉዓላዊነቱን ይመሰክራል። ሰይጣን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ኢዮብ ላይ ምንም ማድረግ አይችልም ነበር (ኢዮብ 1:12, ኢዮብ 2:6)። እግዚአብሔር እራሱ ሰይጣንን

ያስረዋል ደግሞም ይፈታዋል (ራዕይ 20:1-2, 7) ዳቢሎስም በእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ስራው ሁሉ ይጠየቅበታል እግዚአብሔርም ደግሞ ይፈርድበታል (ቁጥ 14-15)።

እግዚአብሔር በድህነት እና በፍርድ ላይም ሉዓላዊ ነው። እንደምናየውም እርሱ አንዳንዶችን ለድህነት ይመርጣል አንዳንዶችን ደግሞ አይመርጥም (ሮሜ 9:21, ኤፌ 1:4) ። እርሱ ልጁ ለአንዳንዶች ብቻ እንዲሞት ላከ (ዩሀንስ 10:15, 26, ዩሀንስ 17:2) ። ለአንዳንዶች እምነትን ይሰጣል ለአንዳንዶች ደግሞ አይሰጥም (ኢፌ 2:8-10) ። እርሱ ብቻውን ልብን ይከፍታል (ሐዋ. 16:14) እርሱ እራሱ ፈቃዱን እና ደስ የሚያሰኘውን ነገር እንድናደርግ በእኛ ውስጥ ይሰራል (ፊሊ 2:12-13) ። የእኛ መልካም ስራ እንኳን በእርሱ አስቀድሞ የተወሰነ ነው (ኤፌ 2:10) ።

እግዚአብሔር በሀጥያት ላይ ሉዓላዊ ነው። ለዘላለም ሀጥያት ላይ መፍረድ ብቻ ሳይሆን (ሐዋ 2:23, ሐዋ 4:27-38) ሀጥያትን ይቆጣጠረዋል፣ ለእራሱ አላማ ይጠቀመዋል። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ማለት ሁሉ ነገር ከእርሱ፣ በእርሱ እና ለእርሱ ነው ማለት ነው (ሮሜ 11:36) ። ይህም ደግሞ በእርግጥ ነው፤ ይህ ካልሆነ እርሱ አምላክ አይደለም። እርሱ ብቻውን ክብር፣ ሞገስ፣ ኃይል፣ እና ገዛት ከአሁን እስከ ዘላለም ይገባዋል።

ይህንን እውነት መቀበል የምንችለው በእምነት ብቻ ነው። የአማኝ ልብ እንኳ አንዳንድ ጊዜ የለግማል ምክኒያቱም ልቡ የትምክህት ሁሉ፤ በቂ ነኝ የማለት እና በእራስ፣ በፍጥረት እና በሌሎች ላይ የመተማመን፤ እና በጥበብ የመመካት ሁሉ ምንጭ ሰለሆነ ነው። ነገር ግን እምነት ስለሚያምን በእውነት ውስጥ እረፍትን ያገኛል። እምነትም እንዲህ ይላል “ይህ አምላክ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላካችን ነውና እስከ መጨረሻው የሚመራንም እርሱ ነው” (መዝ 48:14) ።

## የሰው ሀላፊነት

አንዳንዶች በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰዎች ሀላፊነት መካከል መቃረን እንዳለ ያስባሉ። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚቆጣጠር እና የሚመራ ከሆነ፤ ለዘላለምም በፈቃዱ ነገሮችን ሀጥያትንም ጭምር እንዲሆኑ ከወሰነ፤ ሰው ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ተጠያቂ አይደለም ማለት ነው፤ ሰውም “እግዚአብሔር አደረገው። አስቀድሞ ወሰነው። ይህ ሁኔታ ሊለወጥ አይችልም። የእኔ ጥፋት አይደለም።” ማለት ይችላል ብለው ያስባሉ።

በእግዚአብሔር ፍጹም ሉዓላዊነት እናምናለን ነገር ግን በዚህ ውስጥ የሰው ልጅ ለስራው፣ ለሀሳቡ እና ለልቡ ፍላጎት ሁሉ ተጠያቂ ነው። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ የሚነሱት ክርክሮች ሁሉ ረብ የለሽ ናቸው ምክኒያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና ሰዎች ስለ ሀጥያታቸው እንደሚፈርደባቸው ለሚያቀርቡትም አቤቱታ ጆሮ እንደማይሰጥ ስለሚመሰክር ነው (ሮሜ 9:20) ።

አንድ ሰው ሌላ ሰው ላይ ጥፋትን ካጠፋ ሀላፊነቱ የእራሱ ነው። በሌሎች ሰዎች በኩል እንኳን ሊያደርገው ቢሞክር የመጀመሪያውን ሀላፊነት የሚሸከመው ይህ ሰው እራሱ ነው። እኔ እራሴ የመሳሪያውን ምላጭ ጎትቼ ነፍስ ላላጠፋ እችላለው ነገር ግን ካቀድኩት እና ክንዋኔውን ካቀነባበርኩ ነፍስ በማጥፋት ተጠያቂ ነኝ።

ነገር ግን ይህ ለእግዚአብሔር እውነት አይደለም። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ሀላፊነት መካከል ያለውን ግንኙነት ገልጠን ማብራራት ባንችልም እግዚአብሔር ሉዓላዊ መሆኑ እና የሰው ልጅ ደግሞ ሀላፊነት እንዳለበት የማይካድ እውነት ነው። እግዚአብሔር ታላቅ ነውና ለሰው ልጆች እና ለሰይጣን ክፋት ተጠያቂ ሳይሆን እርሱ ብቻውን መወሰን እና መቆጣጠር ይችላል።

2ኛ ሳሙኤል 24:1 እና 1ኛ ዜና 21:1 ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑ ክፍሎች ናቸው። 1ኛ ዜና 21:1 ዳዊት ህዝቡን በመቁጠር የሰራው ሀጥያት በሰይጣን ምክኒያት ነው ሲል እንመለከታለን ። ሰይጣን ዳዊት ህዝቡን እንዲቆጥር አነሳሳው። ነገር ግን 2ኛ ሳሙኤል 24:1 እግዚአብሔርም ከሀጥያቱ ጀርባ እንደነበር ያሳየናል። ዳዊት ይህንን ሀጥያት እንዲፈጽም *ሲያነሳሳው* እናያለን። ይህ እግዚአብሔር ሀጥያት እንዲፈጸም ብቻ ሳይሆን በሉዓላዊነቱ ሰይጣንን በመቆጣጠር ይህ እንዲሆን ያደርጋል። ነገር ግን ስለ ሀጥያቱ ዳዊት ሲጠየቅ “እግዚአብሔር እንድፈጽመው አደርገኝ” ወይንም “ሰይጣን እንድፈጽመው አደረገኝ” ሳይሆን ሙሉ ሀላፊነቱን ወስዶ “እኔ በድያለሁ” አለ (2ኛ ሳሙ 24:17, 1ኛ ዜና 21:17) ።

ከሁሉም የሚበልጠው ምሳሌም የክርስቶስ ኢየሱስ መሰቀል ነው። የሐዋሪያት *ሥራ* 2:23 የክርስቶስ ለሞት መሰጠት አስቀድሞ የተወሰነ እና በእግዚአብሔር የታወቀ መሆኑን ይነግረናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ እና እውቀት ክርስቶስን ወደ መስቀል መራው። የሐዋራያት *ሥራ* 4:26-28ም ክርስቶስን የሰቀሉት ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ቀድሞ የወሰነውን ተግባር ፈጸሙ ይለናል። ታዲያ ክርስቶስን በመስቀላቸው ተጠያቂ አይደሉም? በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ጥፋት የለባቸውም? አይደለም። የሐዋሪያት *ሥራ* 2:23 እጆቻቸው አስቀድሞም የክፋት እጅ እንደነበር፤ ክርስቶስን እንደሰቀሉት እና እንደገደሉት ይናገራል። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ሀላፊነታቸውን አላጠፋም።

ለሀጥያትህ ሀላፊነቱን ትወስዳለህ? አሁን ባታምንበት እንኳን በፍርድ ቀን መውሰድህ አይቀሬ ነው። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ለጥፋትህ ማመካያ አይሆንም። ነገር ግን ክርስቶስ ብቻውን ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊያድንህ ይችላል።

## የእግዚአብሔር ባህሪያት

የዚህ ዘመን ትልቅ የቤተክርስቲያን ድክመት እግዚአብሔርን አለማወቅ ነው። ምዕመናን ክርስቶስ “እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ” እንዳላቸው ሳምራዊያን ሆነዋል (ዩሀንስ 4:22) ።

በዩሀንስ 17:3 ላይ እግዚአብሔርን *የማወቅ* ጥቅም ተገልጦልናል “እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን *ያውቁ* ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።” ከዚህ በላይ ዋና ጉዳይ የት አለ?

ሆኖም ግን “ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል” (ሆሴዕ 4:6) የሚለው የትንቢት ቃል እየተፈጸመ አለ ። በትንቢቱ ጊዜ የነበሩት የእግዚአብሔር ሰዎች *እግዚአብሔርን* ማወቅ ጎድሏቸው ነበር። ቁጥር 1 ይህንን በግልጽ ሲያስቀምጠው እንመለከታለን “እውነትና ምሕረት እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድር ስለሌለ ※※※” በዚህ ዘመንም ይህ እውነት ነው!

በሆሴዕ ዘመን ቤተክርስቲያን እውቀትን አልተቀበለችም። በይበልጥም ደግሞ መንፈሳዊ መሪዎቿ እና ካህናቶቿ የእግዚአብሔርን ህግ በመርሳታቸው እና በመቃወማቸው እግዚአብሔር ልጆቹን እንደሚረሳ እና ክብራቸውን ወደ ነውር እንደሚለውጥ አስጠነቀቃቸው (ቁጥ 6-7) ። በዚህ ዘመን ያለችውም ቤተክርስቲያን ይህንን የእግዚአብሔር ቃል ሰምታ ፍርዱን ሊያመጣ እንደሆነ ብታውቅ እንዴት መልካም ነበር! ቤተክርስቲያን ወደ ጌታዋ ተመልሳ ብትፈወስ እንዴት ያማረ ነበር!

ስለእነዚህ ነገሮች በማሰባችን ስለ እግዚአብሔር ባህሪያት ልንጽፍ ተነሳን። በባህሪያቶቹም እርሱን እናውቀዋለን፤ እርሱንም በማወቅ የዘላለም ህይወት አለን።

ባህሪ ማለት የግል መገለጫ ነው፡ ለምሳሌ የአይን ቀለም፣ የጠባይ አይነት እና የመሳሰሉትን ያካትታል። የእግዚአብሔር ባህሪያት የምንላቸው የእርሱ አንድነት፣ መንፈሳዊነት፣ ሉዓላዊነት፣ ጸጋ፣ መልካምነት እና በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ላይ ስለእርሱ ሊያብራሩልን የተጠቀሱትን ቃላቶች ያካትታል። ስለእግዚአብሔር

ባህሪያት ስናወራ እርሱ በቃሉ በኩል ሰለ እራሱ እና ስለክብሩ የገለጠልንን እናብራራለን ማለት ነው። በእነዚህ ባህሪያትም ምክኒያት ማን እና ምን እንደሆነ እናውቃለን።

የእግዚአብሔር ባህሪያት የሥነ-መለኮት የክርክር እና የወይይት ሀሳብ ብቻ ናቸው ብለን ማሰብ የለብንም። ለእኛ እጅግ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ቃላቶችን በመጠቀም ስለእግዚአብሔር ባህሪ የግለጠለንም ለዚሁ ነው።

መዝሙር 89:5 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ባህሪያትን *ተዓምራትህን* ብሎ ያስቀምጠዋል። በሌላ አማርኛ የእርሱ ባህሪያት እግዚአብሔር ግሩምነቱን እና ድንቅነቱን እያሳየን በእርሱ ፊት በመገረም እና በመደነቅ እንድንቆም ያደርገናል ማለት ነው።

መዝሙር 78:4 የእግዚአብሔርን ባህሪያት *ምስጋናው* ብሎ ያስቀምጠዋል። በዚህም የመገለጡ ምክኒያት እርሱን ለዘላለም እንድናመልከው እና እንድናደንቀው እንደሆነ እንረዳለን። የዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን እንደሚገባው የማያከብረው ሊያውቀው እንደሚገባው ስለማያውቀው ነው።

መዝሙር 78 የሚመጣው ትውልድ ተስፋውን በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርገው፤ ስራውን የማይረሳው እና ትዕዛዛቱን የሚጠብቀው የእግዚአብሔርን ባህሪ ባወቀበት መጠን ነው ይላል (ቁ 4-8) ። እግዚአብሔር እንደዚህ አይነት ትውልድን ለቤተክርስቲያን ይስጥ፤ ቤተክርስቲያንንም በእውቀቱ በተለይም ባህሪውን በማወቅ ይባርክ።

## የእግዚአብሔር ቅድስና

ከእግዚአብሔር ዋና ባህሪያት መካከል አንዱ ቅድስናው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በብዛት በተለይም ደግሞ በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ቅዱስ ተብሎ ሲገለጽ እንመለከታለን።

ቅድስናው ለእኛ እጅግ አስፈላጊ ነው ምክኒያቱም ያለቅድስናው ማንም እግዚአብሔርን ሊያየው አይችልምና (ዕብ 12:14) ። እርሱን ልናየው ከወደድን እንደ እርሱ መሆን አለብን፤ ይልቁንም ደግሞ በቅድስናው እርሱን መምሰል አለብን።

የእግዚአብሔር ቅድስና ምንድነው?

የቅድስና ዋና ሀሳብ መለየት ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት ቅዱስ ነበሩ - ማለትም በህይወታቸው እና በጥሪያቸው ከሌሎች እስራኤላዊያን የተለዩ ነበሩ። ኢየሩሳሌምም እንደዚሁ ከሌሎች ከተማዎች ሁሉ የተለየች በመሆኗ ቅድስት ነበረች። ስለዚህ ወደ ቅድስና መጠራታችን ከክፉዎች እና ከስራቸው መለየታችንን ያካተተ ነው ማለት ነው (2ኛ ቆሮ 6:14-18)።

ኢየሱስም ቅዱስ ነው። ዕብራዊያን 7:26 እንደሚናገረው እርሱ "ከሀጥያተኞች የተለየ" ነው። በእርሱ ውስጥ ሀጥያት የለም ደግሞም ሊኖር አይችልም። ቅድስናውን መካድ የድህነታችንን መሠረት መካድ ነው።

የእግዚአብሔር ቅድስና ይህ ነው "ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ፥ ከፍ ያለው ልዑል ※※※" (ኢሳ 57:15) ። እርሱ በክብሩ ከሌሎች ሁሉ የተለየ ነው "ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል" (1ኛ ጢሞ 6:16) ይህንን አንርሳ።

ቅድስናውን በቅዱስ ስሙ ገልጦልናል (መዝ 111:9) ። ይህም ስም ከስሞች ሁሉ የተለየ ስም ነው። በከንቱ ባለመጥራት ይህንን ስም የተለየ ልናደርገው ይገባል። እንዴት በዚህ ዘመን ይህ እውነት ተረስቷል? በዕለተ ዕለት ንግግራችን ብቻ ሳይሆን በጸሎታችን እንኳን የተረሳ እውነት ሆኗል።

የእግዚአብሔር ቃልም የ*እርሱ ቃ*ል በመሆኑ ቅዱስ ነው (ሮሜ 1:2) ። ከሰው ሀሳብ እና ጥበብ ሁሉ የተለየ አድርገን ልንጠቀምበት ይገባናል።

የእግዚአብሔር ቀን ቅዱስ ቀን ነው፤ ከሌሎችም ቀናቶች ሁሉ የተለየ ነው። ይህ ቀንም ለእግዚአብሔር እና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር፣ ይህንንም ክብር ከሞት በመነሳቱ ስላገኘው ለእነርሱ የተለየ ቀን ሊሆን ይገባል።

መለየት ሁለት ገጽታ አለው እነርሱም *ከነገሮች* መለየት እና *ለአንድ ነገር* መለየት ናቸው።

የእግዚአብሔር ቅድስና ማለት እርሱ *ከ*ሀጥያት ሁሉ የተለየ ነው ማለት ነው፤ አይኖቹም ንጹህ በመሆናቸው ክፉትን ሊያዩ አይችሉም (ዕንባቆም 1:13) ። እግዚአብሔር በክፉት ደስ አይለውም ክፉትም ከእርሱ *ጋ*ር ሊኖር አይችልም (መዝ 5:4) ። ስለዚህም ከክፉት እራሱን መለየት ብቻ ሳይሆን ይቃወመዋል ደግሞም ያጠፋዋል፤ ክብሩንም በዚህ ይገልጣል። ቅድስናውም *ለእራሱ* እና *ለክብሩ* የተለየ እና የተሰጠ እንደሆነ ይገልጣል (ኢሳ 42:8) ።

ቅዱስ ለመሆን *ከሀጥያት* መለየት ብቻ በቂ አይደለም ነገር ግን *ለእግዚአብሔርም* መለየት ያስፈልገናል። ጠጪን ከመጠጥ መለየት ብቻ ቅዱስ አያደርገውም ነገር ግን ለእግዚአብሔር መለየት እና መሰጠት አለበት። ስለዚህም ለእግዚአብሔር በሁሉ ነገር የተለየን መሆን አለብን። ያኔ ብቻ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ እኛም መቀደስ እንችላለን (1 ጴጥ 1:16) ። ያኔ ብቻ እርሱን ልናየው እንችላለን ደግሞም በእርሱ እንኖራለን።

## የእግዚአብሔር አንደነት

"እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።" በዘዳግም 6:4 ላይ ያለው ይህ ቃል በአውደ አገባቡ መሰረት ስለእግዚአብሔር የአንድነት ባህሪ አስፈላጊነት ይገልጻል።

ይህ ክፍል የእግዚአብሔር የአንድነት ባህሪ የህግጋቶቹ ልብ፣ የነቢያት እና የተጻፉት ትዕዛዛት ሁሉ ደግሞ መደገፊያ እንደሆነ ያስየናል (ማት 22:35-40, ሉቃስ 10:25-28)። እግዚአብሔር አንድ ነው፡ ከሚለው ህግ ውጪ በእውነትም ሌላ ህግ የለም።

የእግዚአብሔር አንድነት ለእግዚአብሔር ሰዎች መጠራት መሠረት ነው (ዘዳ 6:5) ። በቤታችን መግቢያ ላይ ልንሰቅለው፣ ሁልጊዜም ቅርባችን እና በአይናችን ስር እንዲሆን ያስፈልጋል (ቁጥ 8-9) ። የእግዚአብሔር አንድነት ልጆቻችንን የምናስተምረው ዋና ጉዳይ፣ የንግግራችን ሁሉ ቁልፍ ሃሳብ፣ የህይወታችን መመሪያ፣ የጥሞናችን ጭብጥ፣ የጸሎታችንም ደግሞ መሰረት ሊሆን ይገባል (ቁጥ.7) ። አንድነቱ የበረከታችን ሁሉ ምንጭ (ቁጥ 10-11) እና በእግዚአብሔር ፊት ያለን ቅድስና የማዕዘን ደንጋይ (ቁጥ 25) ነው። የእግዚአብሔርን አንድነት መርሳት ማለት ከእስራታችን የፈታንን ጌታ መርሳት እና መተው ነው (ቁጥ. 12)።

የእግዚአብሔር አንድነት ለምን እጅግ አስፈላጊ ሆነ?

በመጀመሪያ የሥላሴ እውነት አካል ነው ስለዚህም እግዚአብሄር *እውነተኛ* አምላክ መሆኑን የሚያሳየን እውነት ነው። እርሱ ሦስት አካል ነው ሆኖም ግን አንድ ነው። በሦስትም ሆኖ አንድ ከሆነው አምላክ ውጪ ማምለክ እና ማገልገል ማለት ከእውነተኛ አምላክ ወደ ጣዖት መዞር ማለት ነው። ተስፋችን እና ድህነታችን ሁሉ በዚህ ላይ የተመሰረተ ነውና። 1ኛ ቆሮንቶስ 8:5-6 የሚለውን አስተውሉ " መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ

እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን"።

ሁለተኛ የእግዚአብሔር አንድነት ስንል እርሱ ብቸኛ አምላክ ነው ማለታችን ነው። ሌላ አምላክ የለም። ማንም ሆነ ምንም ከእርሱ ጋር ሊወዳደር አይችልም ማለታችን ነው (ኢሳ 40:18) ።

የእግዚአብሔር አንድነት ሕይወታችንን የሚመራ እውነት የሆነውም ስለዚህ ነው። እርሱ ብቻውን እግዚአብሔር (አምላክ) ስለሆነ ከእርሱ ውጪ ልንወድደው፣ ልናመልከው፣ ልናገለግለው፣ እና ልንታዘዝለት የተገባው ማንም የለም። ልናውቀው ፣ ልናከብረው እና ልንፈራው የተገባው እርሱ ብቻ ነው። ለእርሱ ብቻ እንገዛለን። በእርሱ ብቻ እንታመናለን። ከእርሱ ብቻ ሁሉን እንጠብቃለን፤ ወደ እርሱ ብቻም እንጸልያለን።

የእግዚአብሔር ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 8:5-6 የሚናገረው ይሄንኑ ነው። እኛ በእርሱ ውስጥ ነን በእርሱም ብቻ አለን። በስራ ቦታ፣ ስንጫወት፣ በቤታችን፣ በትምህርት ቤታችን፣ ስነተኛ እና ስንነቃ፣ ስንበላ፣ ስናስብ፣ ስንናገር፣ ስንጸልይ፣ ስንራመድ ለዘላለም እና እስከ ዘላለም መጨረሻ ድረስ ለእኛ አንድ አምላክ አለን። ከዚህ ውጪ ያለ አምልኮ ሁሉ ጣዖትን ማምለክ ነው።

ለሰው ልጆቹ ሁሉ ይህ ቢሆን መልካም ነው ምክኒያቱም ይህ አንድ አምላክ ፈጥሯቸዋል፣ እስትንፋስን፣ ህይወትን እና ሁሉን ነገር የሰጣቸውም እርሱ ነው (የሐዋሪያት ስራ 17:25)። ምክንያቱም ይህ ተወዳዳሪ የሌለው አምላክ በጸጋው አማኞችን ከትምክህት እና ከሀጥያት በማዳን አይናቸውን ከፍተው እርሱ ብቻውን እግዚአብሔር እንደሆነ እንዲረዱ አድረጓቸዋል።

የእግዚአብሔርን አንድነት እያሰበ ሙሴ እንዲህ ይላል "አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ" (ዘዳግም 6:5) ። አንተስ ተወደዋለህ?

## የእግዚአብሔር ኢ-ተለዋጭነት

የእግዚአብሔርን አይለወጤነት በተለምዶ የምናስበው አመትን ጨርሰን ወደሌላኛው ስንሸጋገር ነው። ብዙ ነገሮች በምድር ላይ በየአመቱ ይከሰታሉ እነዚህ ነገሮችም ሕይወታችንን በተለያየ መንገድ ይለውጡታል። የማያቋርጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ለውጥ አለ። እያንዳንዱ ቀን ሕይወታችንን የሚለውጥ ዜና ይዞ ይመጣልናል። አሁን የምንኖርበትም አለም በአያቶቻችን ዘመን የነበረውን በፍጹም አይመስልም።

ፖለቲካዊ ለውጦች እና ጦርነቶች የሀገራትን ድንበር ቀይረዋል፣ ሀገራትን አጥፍተዋል፣ ገንብተዋል። የህዋ ዘመን ከጨለማው ዘመን በላይ የጨለማ ዘመን አለመሆኑ አጠራጣሪ ቢሆንም ከጨለማ ዘመን ወደ ህዋ ዘመን ተሸጋግረናል። ምናልባትም ይህ ጊዜ የበለጠ የጨለማ ዘመን የሆነው ወደ ነገር ሁሉ መጨረሻ የተጠጋ ስለሆነ ይሆናል።

በቤተክርስቲያን ውስጥ እንኳን ብዙ ለውጦች ሆነዋል። ባለፉት አመታት ታላቁን ተሓድሶ ማምጣት ብቻ ሳይሆን በተሓድሰው ያፈራናቸው ሁሉ ያጣንበት ዘመን ሆኗል። የብዙዎች ፍቅር እጅጉን ቀዝቅዟል፤ አመፃም በዝቷል (ማቴ 24:10-12) ። በእጅጉ ታማኝ የሆኑ ቤተክርስቲያኖች ሁሉ "የተከበበች ከተማ"ን መስለዋል (ኢሳ 1:8) ። የጊዜው ነገሮች ሁሉ ከክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ጋር አይስማሙም።

ሁሉም አስደሳች ባይሆንም በቤቶቻችንም ውስጥ ብዙ ለውጥ ተፈጥሯል ። ለአንዳድኖች አዲስ አመት ጤንነትን እና ደስታን፣ ትዳር እና ልጆችን፣ ስኬትን እና ደህና መሆንን ያመጣል። ለሌሎች ደግሞ ማጣት እና ችግር ፣ ስቃይ እና ህመምን ያመጣባቸዋል። ምናልባት አንዳንዶቻችን ባለፉት አመታት ስላጣናቸው የተወደዱ ቤተሰቦቻቸው እያዘንን ይሆናል፤ አንዳንዶች ደግሞ እጅግ ከባድ ፈተናን ተፈትነው ይሆናል።

ቀጣዩ አመት ምን ያመጣ ይሆን? የሚቀጥሉት አስርት አመታትስ? ቀጥዩ ምዕተ አመትስ ምን ያመጣ ይሆን?

ይህንን ማንም አያውቅም፣ አንዳንዶች ነቢያት እንደሆኑ ቢያስቡም እንኳን። እርግጠኛ መሆን የምንችለው በአንድ ጉዳይ ነው እርሱም ይህች አለም ካለች የሀጥያት፣ የጨለማ እና የሞት አለም በመሆኗ የአመታት መቀያየር የበለጠ ለውጥ እና መበስበስን ያመጣል።

ሆኖም ግን እግዚአብሔር አይለወጥም። ኢ-ተለዋጭነት ማለት ይህ ነው። እርሱ ሊለወጥ *አይችልም*፡ እርሱ ጅሆቫ ነው አይለወጥም (ሚልኪያስ 3:6) ፤ "መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት" ነው (ያዕቆብ 1:17) ። እኛም "አንተ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላክ ነህ" እያልን እናውጃለን (መዝ 90:2) ።

እግዚአብሔር አላማውን እና በነገሮች ላይ ያለውን እቅድ አልቀየረም። አሁንም እርሱ የሰዎችን ድህነት ይወስናል። ወይንም ደግሞ ሁሉን ቻይነቱ፣ የሰማይ እና የምድር ሉዓላዊ አምላክነቱ ይቀየር ዘንድ በስልጣን እና በኃይል አልተለወጠም። በእኛ ላይ የሚሆነውን ጨምር ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል ይመራልም (መዝ

115:3)። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ፍቅሩን እና ምህረቱን አልቀየረም። የተወን እና የረሳን በሚመስለን ጊዜ አልረሳንም አልተወንምም። በዚህም ደግሞ እርግጠኛ መሆን እንችላለን ምክኒያቱም በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የማይለወጠው እግዚአብሔር እራሱን ገልጦልናልና “ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው” (ዕብራዊያን 13:8)። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር አይለወጤነት ነገሮች ሁሉ ለበጎ እንደሚሆኑልን(ሮሜ 8:28) እና የጸጋ መልካም ስራ በጊዜው እንደሚፈጸም ማረጋገጫችን ነው (ፊሊ. 1:6) ።

አምላካችን የማይለወጥ መሆኑን ማወቅ እንዴት የሚደግፍ እና የሚያስደስት ነው? በእርሱ በማይለወጠው ኢየሱስ በኩል እናርፋለን።

## የእግዚአብሔር መንፈሳዊነት

አዲስ ኪዳን ስለ አምልኮ የሚያስተምረን ነገር ሁሉ የተመሰረተው እግዚአብሔር መንፈስ ነው በሚለው እውነት ላይ ነው። በዩሀንስ 4:24 ላይ ኢያሱስ እንዲህ ይላል “እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” ። ይህ ምን ማለት ነው? ለምንስ አስፈላጊ ነገር ሆኖ ተገኘ? የእግዚአብሔር መንፈስነት በግላችን እና እንደ ቤተክርስቲያን ላለን አምልኮ መሰረት የሆነው ስለምን ነው?

በአምልኮ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስነት እርሱ የ *ማይታይ* መሆኑን ይገልጽልናል። አለመታየት ብቻ ሳይሆን እርሱ እጅግ ትልቅ እና ሞገሳም ከመሆኑ የተነሳ *ሊታይ አይችልም* ማለት ነው። በአይናችን ፀሀይን መመልከት እንደማንችል ሁሉ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ ሊኖር አይችልም (1ኛ ጢሞ. 6:16: “ሊያይም አይቻለውም” የሚለውን አስተውሉ) ።

ስለ እግዚአብሔር ልናይ የምንችለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት ላይ ያለውን ክብሩን ብቻ ነው በእርሱም የአምላክነቱ ክብር ያድራል (2ኛ ቆሮ 4:6, ቆላስያስ 2:9) ። ዩሀንስ 14:9 ላይ ኢየሱስ እንደሚለው “እኔን ያየ አብን አይቶአል” ።

ይህ እግዚአብሔርን ለማምለክ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ በእጅ በተሰራ አልያም በልብ እና በአእምሮ በተሳለ ምስል ሊመለክ አይችልም። ያልታየን አምላክ ማን ሊስል ይችላል? እንዲህ አይነት ምስል ቢፈጠር እንኳን ከውሸት እና ከሀሰት ውጪ ምን ሊሆን ይቻላል?

ይህ እውነት ከሆነ እያንዳንዱ የሀሰት አስተምህሮ (ዶክትሪን) ፣ እያንዳንዱ ስለእግዚአብሔር ትክክል ያልሆነ ንግግርም የእግዚአብሔር ክብር የጎደለው በመሆኑ "ፍጡር ምሳሌ" ነው። ስለዚህም በአምልኮ ውስጥ ስለ ሀሳባችን ሆነ ንግግራችን እንጠንቀቅ!

ሁለተኛ እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ እራሱን እና ክብሩን በገለጠበት በቃሉ በኩል ብቻ ሊመለክ ይገባዋል። "የሚሰግዱለትም.... *በእውነት* ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" ሲል ክርስቶስ ይህንን ማለቱ ነው (ዩሀንስ 4:24) ።

ይህ እውነታ የአምልኳችን አካል ብቻ ሳይሆን የአምልኳችን *መርህ* መሆን አለበት። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በአምልኮ ጊዜ ማድረግ ያለብንን እና እንዴት ማድረግ እንዳለብን ይቆጣጠራል። ይህ መሆኑም አስፈላጊ ነው። ምክኒያቱም ሰው አይቶት የማያውቀውን አምላክ ለማምለክ ምን ማድረግ እንዳለበት በምን ሊያውቅ ይችላል? የትኛው የሚገባ አምልኮ መሆኑን ያውቃል?

ሦስተኛው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ከልብ እንጂ በውጫዊ ስርዓተ አምልኮ ብቻ ሊመለክ አይገባውም። ዩሀንስ 4:24 ላይ "በመንፈስ........ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" የሚለው ሀሳብ "በመንፈስ ቅዱስ" ማለቱ ሳይሆን "በመንፈሳችን" ማለቱ ነው። ይህ *ሥጋዊ* እና ውጫዊ ከሆነው ነገር ሁሉ ተቃራኒ ነው።

በዚህ ዘመን ይህ እውነት እንዴት ተረስቷል! በእውነት ፋንታ ብዙ ነገሮች በአምልኳችን ሰርገው ገብተዋል። በእውነተኛ አምልኮ ፈንታ የተለምዶ ውጫዊ ስርዓት ወይንም ከዘመናችን አለማዊ መዝናኛዎች በሚበልጡ እና በሚረብሽ ስጋዊነት ተተክቷል። እንዲህ አይነቱ አምልኮ እግዚአብሔርን አያስደስትም።

እግዚአብሔርን ደስ ከማያሰኙት አምልኮዎች መካከል አንዱ እግዚአብሔርን በምስል እና በፎቶ ማምለክ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ይፀየፋል። ማንም ያላየውን እርሱን አይመስሉትም ሊመስሉትም አይችሉም። እነዚህን ማምለክ ደግሞ በእይታ እና በመዳሰስ የተመሰረተን አምልኮ ይፈጥራል ይህም አምልኮ ከእግዚአብሔር መንፈሳዊነት፣ ማንም ካላየው እና ካልዳሰሰው አምላክ ጋር የማይሄድ አምልኮ ነው።

ስለዚህም አባታችን በሉዓላዊ ጸጋው መንፈስ መሆኑን ለብዙዎች እንዲያስተምር እና ጣዖት አምላኪነት እና ንቀት በበዛበት በዚህ ዘመን በእውነት እና በመንፈስ የሚያመልኩን እውነተኛ አምላኪዎችን እንዲያገኝ ጸልዩ።

**የእግዚአብሔር በራሱ በቂ መሆኑ**

መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረን ትሁት አድራጊ እውነቶች መካከል እግዚአብሔር በራሱ ብቁ እና የማንንም እርዳታ የማይሻ መሆኑ ነው። ከእራሱ ውጪ የሚፈልገው አንዳችም ነገር የለም። ነገርን ሁሉ - በሺህ ተራራዎች ላይ ያሉ እንስሶችም - ጭምር የእርሱ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን እርሱ ላይ የሚጨምሩት አንዳች ነገር የለም። ምንም ነገር ባይፈጥር እንኳን ብቻውን ምሉዕ እና ክቡር ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል በሮሜ 11:34-36 ላይ ይህንኑ እንዲ በማለት ይናገራል “የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።”

ማንም ሰው በሁሉን አዋቂ እግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን ሊያውቅ አይችልም ፤ እግዚአብሔርም ሁሉን አዋቂ እና በዘላለም እና በፍጹም እውቀቱ የማያውቀው ነገር ባለመኖሩ አዲስን ነገር የሚነግረው የለም። በጸሎትም ሆነ በሌላ መንገድ የምናሳውቀው አዲስ ነገር የለም።

ማንም ለእግዚአብሔር መስጠት ሚችለው ነገር የለም። ምስጋናን፣ ክብርን እና ውዳሴን እንኳን “ስንሰጥ” ክብሩ ላይ የምንጨምረው ቅንጣት ታህል ነገር የለም። የቤተክርስቲያን ድህነት ክብሩ ላይ የሚጨምረው አንዳች ነገር የለም ነገር ግን አስቀድሞ ለግሉ የነበረው ክብር በቤተክርስቲያን ላይ ተገለጠ እንጂ። እርሱ የሁሉ ነገር ምንጭ፣ ምክንያት እና መደምደሚያ ነው።

ከምንም በላይ *ጅሆቫ* የሚለው ታላቅ ስም የእግዚአብሔርን *በራስ በቂነት* ይገልጥልናል። በዚህ ስም መሰረት እርሱ ሁሉ በሁሉም የሆነው “እኔ ነኝ” ነው።

ይህ እውነት በተለይም በድህነታችን ላይ እጅግ አስፈላጊ ነው። አብዛኞች እኛ ባንኖር ኖሮ እግዚአብሔር መሃሪ፣ የፍቅር እና የጸጋ አምላክ አይሆንም ብለው ያስባሉ ደግሞም እርሱ የፍቅር እና የምህረት አምላክ እንዲሆን እኛ እናስፈልገዋለን ብለው ያስባሉ። አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር የምድርን ሰው ሁሉ ካልወደደ እና ለሁሉም ጸጋን ካልሰጠ የፍቅር አምላክ አይደለም ብለው ያምናሉ ። ይህ የእግዚአብሔር በራስ በቂነትን መካድ ነው። እኛ ባንፈጠር እንኳ እግዚአብሔር አሁንም የጸጋ እና የፍጹም ፍቅር አምላክ መሆኑ አይቀየሬ ነው። እኛን ፈጥሮን በራሳችን በሀጥያት ስንወድቅ አይቶን ማንንም ባያድን እንኳ የእርሱ መሃሪነት፣ ፍቅርነት እና ጸጋ ሰጪነት አይጓደልም ነበር።

ይህ እንዴት ትሁት የሚያደርግ እውነት ነው። ለአንዳንዶች ብቻ ቢገለጥም እግዚአብሔር የሚያሳየውን ምህረት እና ጸጋን እንዴት አጉልቶ ያሳያል። እንዴት ያለ ታላቅ አምላክ ነው!

ከዚህም በላይ አለ። የእግዚአብሔር በራስ ብቁ መሆን ሌላኛው ገጽታ እኛ በእርሱ ላይ መደገፋችን ነው። እኛ የእራሳችን የሆነ ነገር ምንም የለንም፤ ያለእርሱ ማድረግ የምንችለው ነገር የለም፤ ያለእርሱ ደግሞ ምንም ነን! ። ከእርሱ ተለይተን ለመኖር ማሰባችን ምነኛ ሞኝነት ነው። ለነፍሳችን እና ለስጋችን በሚያስፈልግን ሁሉ እርሱን ባለመለመናችን እና ፊታችንን ወደ እርሱ ባለማዞራችን ምንያህል ሞኞች ነን።

ሙሉ በሙሉ በእርሱ በመታመንና የተገለጠልንን የጸጋውን እና የምህረቱን ግሩምነት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባራችንም ከፍ ከፍ እያደረግን የእግዚአብሔርን በራስ በቂነት እንመስክር።

## የእግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ መገኘት

እግዚአብሔርን ማወቅ የዘላለም ህይወት ነው። በቅድስና ሕይወት እና በሀጥያት ሕይወት፤ መንፈሳዊ ሰላም በተሞላ ሕይወት እና እንደ እረፍት የለሽ የባህር ማዕበል በሆነ ሕይወት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ (ኢሳ 57:20-21) ።

ሕይወትን ከሚሰጡ የእግዚአብሔር እውቀቶች መካከል በሁሉ ስፍራ የመገኘቱ እውቀት አንዱ ነው። በሁሉ ስፍራ እንደመገኘቱ እግዚአብሔር የቦታን እና የጊዜን ገደብ ያልፋል ። ርቀት እና ቦታ በእርሱ ዘንድ ትርጉም የለሽ ነው ። ሁሉን ቦታ የሚሞላ ሆኖም ግን በቦታ የማይገደብ እርሱ ነው፤ በሁሉም ስፍራ ይገኛል። ስለዚህም እርሱ እራሱ በኤርሚያስ 23:23-24 "እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር" በማለት ይናገራል።

ለሕይወታችን ይህ እንዴት ያለ እውነት ነው! እግዚአብሔር በምንሄድበት እና በምናደርገው ነገር ሁሉ እና በምንሄድበት ቦታ መገኘቱን ከማወቅ የሚበልጥ ለቅድስና፣ ለትህትና እና ለእግዚአብሔራዊ ፍቅር የሚጠቅም ታላቅ ኃይል ምን አለ?

አብዛኞች የክፋት ስራቸውን መደበቅ የሚችሉ ይመስላቸዋል። ምናልባትም ከሌሎች ሰዎች በሮቻቸው ዘግተው፣ በጨለማ፣ እና በፍርሃት መደበቅ ይችላሉ ። እግዚአብሔር ግን የሚያደርጉትን ያውቃል።

ሀጥያታቸውንም በሚፈጽሙበት በዚያ ቦታ እርሱ አለ “የእግዚአብሔር ዓይኖች በስፍራ ሁሉ ናቸው፤ ክፉዎችንና ደጎችን ይመለከታሉ” (ምሳሌ 15:3)።

ስለዚህም ምስክር ስለሌለ ሀጥያቴ አይታወቅም ብሎ የሚያስብ እንዴት ሞኝ ነው። እስራኤላዊያን በሲና ተራራ እንዳደረጉት እኛም በእግዚአብሔር መገኘት ፊት ለፊት ሀጥያት ስንሰራ እንዴት ሞኞች ነን። ሁሌም ይገኛል ለእያንዳንዱ ስራ፣ ሀሳብ እና ንግግር ምስክር ሊሆን በስፍራው አለ። እርሱ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ ዳኛ ነው።

ለሚያምኑቱ እና ንስሃ ለሚገቡት ሰዎች እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ መገኘቱ መልካም ነገር ነው በተለየ መንገድ ለእነርሱ ይገኛልና። የተሰበረ ልብ እና የተዋረደ መንፈስ ላላቸው እና በእውነት ለሚጠሩት እርሱ ቅርብ ነው (መዝ 34:18, መዝ 145:18)። እንደ አባት እና እንደ አዳኛቸው ለእነርሱ ይገኝላቸዋል።

ጩኸታቸውን ይሰማል፣ የተሰበረውን ልባቸውን ያያል፣ ያድናቸዋል፣ይፈውሳቸዋልም።

እግዚአብሔር ለህዝቡ በፈተና እና በመከራ ጊዜ ቅርብ ነው "በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው፤ በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፥ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው" (ኢሳ 63:9) ። ይህ እውነት ዛሬም አልተቀየረም።

በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ለህዝቡ ቅርብ ነው። ክርስቶስ አማኑኤል "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ነው ። ይህም በሁሉ ስፍራ የመገኘቱ ማዳን መገለጥ ነው። እግዚአብሄር በክርስቶስ እና በእርሱ በኩል ለዘላለም ከእኛ ጋር የሆነ አምላካችን፣ አዳኛችን እና አባታችን ነው።

እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ እንደሚገኝ ታውቃለህ? የእርሱ በሁሉ ስፍራ መገኘት ከሀጥያት መንገድህ መልሶ ወደ የሕይወት እና ልብ መንጻት ይመራሀል? በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበርር፣ እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣ በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች" (መዝ 139:10) ትላለህ?

## የእግዚአብሔር ፍቅር

የእግዚአብሔር ፍቅር በሚያሳዝን ሁኔታ በብዙ ክርስቲያኖች መካከል ያለ ትልቅ የመከራከሪያ ርዕስ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ይወዳል? ፣ ሁሉንም ሊያድን ይፈልጋል? የሚሉት ጥያቄዎች በተለያየ መንገድ የሚመለሱ ሲሆኑ ጥያቄዎቹም እጅግ አስፈላጊ ናቸው። አስቀድሞ ከመመረጥ፤ ለአንዳንዶች ብቻ እግዚአብሔር ያለው ዘላለማዊ ፍቅር፤ ከክርስቶስ ሞት ጋር እና ከታላቁ የእግዚአብሔር ፍቅር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ነው።

የዚህ ጥናት አላማ ዩሀንስ 3:16 እና መሰል ክፍሎች ላይ የሚገኘውን "አለምን ሁሉ" የሚለውን ቃል ማብራራት አይደለም። ለእነዚህ ክፍሎች ምላሽ የሚፈልግ ሰው ያለ እንደሆን በሆመር ሲ.ሆክሴማ የተጻፈውን "እግዚአብሔር አለምን ወድዋልና"[9] የተሰኘውን በራሪ ወረቀት ማንበብ ወይም በፒንክስ ማጣቀሻ ላይ ስለ "እግዚአብሄር ሉዓላዊነት"[10] የተሰጠውን ማብራሪያ መመልከት ይችላል። በዚህ ጽሁፍ

የምናነሳው የእግዚአብሔር ፍቅር ምን እንደሆነ በመረዳት ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚነሱ ጥያቄዎን መመለስ ነው።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ከምንም በላይ ለእራሱ፣ ለክብሩ እና ለቅድስናው ያለው ፍቅር ይበልጣል። አንደኛ ዩሀንስ 4:16 እግዚአብሔር ፍቅር ነው ሲል ይህን ያመላክተናል። እንደ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስነቱ እግዚአብሔር በእራሱ የፍቅር ተምሳሌት ነው። የፍቅር አምላክ እንዲሆን ሆነ የፍቅር አምላክነት ክብሩ ይሟላ ዘንድ እኛ አናስፈልገውም። ከዘላለም እስከ ዘላለም እርሱ በእራሱ በሥላሴነት ውስጥ ፍቅር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅርን "የፍጻሜ ማሰሪያ" ብሎ ገልጦታል (ቆላ 3:14) ። ፍቅር ከተራ ስሜት እጅግ የሚበልጥ ነው። ይህ በቅዱስ ሥላሴነት በሚኖሩት ሦስት አካሎች ውስጥ ያለው ማስተሳሰሪያ ነው።

እግዚአብሔር የእራሱን ክብር ስለሚወድድ ፤ ፍቅርም ደግሞ የፍጹምነት ማሰሪያ በመሆኑ እግዚአብሔር ሰዎችን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ካልሆነ በቀር መውደድ አይችልም (ኢሳ 42:8, ሕዝ. 39:25) ። ይህም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር "በክርስቶስ" በኩል ለተወሰኑት ብቻ መሆኑ ለመመረጥ ምክኒያት ሆኗል። በእርሱም ብቻ ፍጹማኖች ነን። ለዚህም ነው በዩሀንስ 3:16 ላይ ያለው "*አለምን*" የሚለው ቃል ሁሉንም ሰው የማይወክለው (ዩሀንስ 17:9 ፣ 1ኛ ዩሀንስ 4:7-9 በሁለተኛው ክፍል ያለውን "እኛ" የሚለውን ቃል ይመ.)። ከክርስቶስ ኢየሱስ ውጪ ከሆኑት ጋር እግዚአብሔር የፍጹምነትን ማሰሪያ ማድረግ አይችልም።

መዝሙር 5:4 እግዚአብሔር ከክርስቶስ ውጪ ሊወደን እንደማይችል የበለጠ ሲያሳየን "አንተ በደልን የማትወድድ አምላክ ነህና፤ ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም" በማለት ይናገራል ። በክፉት እና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ የፍጹምነት ማሰሪያ በጭራሽ ሊኖር አይችልም። የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲሆንላቸው የሚወዳቸው ሁሉ በክርስቶስ በኩል የተመረጡ እና የተቤዡ መሆን አለባቸው።

የዚህ ሀሳብ ሌላኛው ገጽታ ደግሞ እግዚአብሔር ክፋትን እና ክፉ አድራጊን መጥላቱ ነው (መዝ.5:5-6)። ይህ ለመናገር የሚከብድ ቢሆንም ይህንን አለማለት ግን ስሙን መስደብ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ከሀጥያታቸው እና ከአመጻቸው ሳያድናቸው ይወዳቸዋል ማለት ቅዱስ እና ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ክፋትን ይወዳል ማለት ነው። ይህንን ለማሰብ የሚደፍር ማነው?

የአማኞች ደስታ እና ሀሴት የተመሰረተው በእግዚአብሔር ፍቅር እውቀት ላይ መሆኑን አንርሳ። ይህ ማለት እግዚአብሔር ህዝቦቹን ከሀጥያታቸው ሁሉ በማዳን ፍጹማን ያደርጋቸዋል ማለት ነው። የእርሱ ፍቅር

የፍጻሜ ማሰሪያ ነው። ህዝቡን ወደ ህብረቱ ያስገባቸዋል የእርሱንም መለኮታዊ ማንነት እንዲካፈሉ ያደርጋቸዋል። ፍቅሩ ፍጹም ያደርጋቸዋል። “እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል” (1ኛ ዩሀንስ 4:16)። እንዴት ያለ መባረክ እና ደስታ ነው!

## የእግዚአብሔር ጸጋ

ጸጋ ምንድነው? ብዙ ጊዜ ሉዓላዊ ጸጋ ወይንም የድህነት ጸጋ ብለን እንናገራለን። ነገር ግን ጸጋ ምን ማለት እንደሆነ ተረድተናል?

አንዳንዶች እንዳልተረዱት ግልጽ ነው። ስለ “የወል (የጋራ) ጸጋ” በማንሳት እግዚአብሔር ለሁሉም ጸጋን ይሰጣል ብለው ይናገራሉ። የጸጋን እውነተኛ ትርጉም ቢረዱ ኖሮ ጸጋ የጋራ እንዳልሆነ በተረዱ ነበር። አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ካላዳነ ወይም ለሁሉም እድልን እስካልሰጠ ድረስ ባለጸጋ ወይም ጸጋ ሰጪ አይደለም ብለው ያጉረመሩማሉ ። ጸጋ ምን እንደሆነ ቢረዱ ግን እንደዚህ አይነት ሀሳብ ባልኖራቸው ነበር።

እኛም የጸጋን ምንነት ተረድተነዋል ባልነው መጠን የተረዳነው አይመስለኝም። ጸጋ እግዚአብሔር *ባህሪ* እንደሆነ እናውቃለን? እግዚአብሔር በማንነቱ ጸጋን ሰጪ በመሆኑ ማንንም ባይፈጥር ሆነ ባያድን ጸጋ ሰጪ እንደሆነ እናውቃለን? ይህ ሁሉ እንኳን ቢሆን ኖሮ ጸጋ የእግዚአብሔር አንዱ ውበቱ የሆነው ባህሪው ነው። እኛ የጸጋው መጠቀሚያዎች ወይም ተቀባዮች ባንሆን እንኳን እርሱ በእራሱ ጸጋ ሰጪ መሆኑን ይቀጥላል።

ጸጋ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው ስንል ይህንን ማለታችን ነው። ጸጋ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት ብቻ የሚያብራራ አይደለም። አምላክ አለመሆን እንደማይችለው ሁሉ ጸጋ ሰጪም አለመሆን አይችልም። ይህ ማንነቱ ነው።

ብዙ ጊዜ ጸጋን “ያለተገባ ስጦታ” ብለን እንተረጉመዋለን። በእርግጥ ይህ ስህተት ባይሆንም የጸጋ ሙሉ ትርጉም ግን አይደለም። ይህ ትርጉም እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ጸጋ ምን አይነት እንደሆነ በማብራራት ፤ የእርሱ የማዳን ጸጋ ሉዓላዊ፣ ነጻ እና ለማንም ይህንን ጸጋ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ አትኩሮት ይስጣል። ነገር ግን ጸጋ እንደ እግዚአብሔር ባህሪ ምን አይነት ትርጉም እንዳለው አያብራራልንም።

የተለመደው ትርጉም እንደሚያብራራው ጸጋ የእግዚአብሔር ውለታ ወይንም ስጦታ ነው። ይህም ጸጋ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው ስንል እግዚአብሔር *ለእራሱ* ውለታን (ስጦታን) ያደርጋል ማለታችን ነው። በቀላሉ እግዚአብሔር በመጀመሪያ እራሱን ይወዳል፣ የእራሱንም ክብር ከምንም በፊት ያስቀድማል ማለታችን ነው ይህንንም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል።

*ጸጋ* የሚለው ቃልም ተወዳጅ (loveliness) ወይም ውበት (beauty) የሚል ትርጉም ሲኖረው በተለይም ደግሞ በሰዎች ሁናቴ እና ንግግር ውስጥ የሚታይ ውስጣዊ ውበት ወይም መወደድ ማለት ነው። ስለዚህም አንድን ሰው ጸጋ የተላበሰ ነው ስንል ንግግሩ ወይም ባህሪው ጸጋ/ሞገስ አለው ማለታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስም አንዳንድ ሰዎች ጸጋን እና ሞገስን (ውብ መሆንን) በእግዚአብሔር አይን ሲያገኙ ያሳየናል (ዘፍ.6:8 ፣ ሉቃስ 1:30) ።

እግዚአብሔር ባለጸጋ (ሞገስ) ነው ስንል በክብሩ ሁሉ ከሁሉ በላይ ያማረ፣ የሚወደድ እና የውስጣዊው የንጽህናው እና የክብሩም ውበት በድርጊቱ እና በንግግሩ ሁሉ ላይ ይንጸባረቃል ማለታችን ነው። ስለዚህም እራሱ ላይ ጸጋ መላበስን/ሞገስን ይመለከታል። እንደ ሦስት አካል በአንድ አምላክነቱ እርሱ እራሱን እና ድርጊቱን ከምንም አስበልጦ ይወዳል ፤ ስራውም ከማንም ጋር በማይወዳደር መልኩ ያማረ እንድሆነ ያምናል። ጸጋ (ሞገስ) የእግዚአብሔር ባህሪ ነው ስንል ይህንን ማለታችን ነው።

እግዚአብሔር ባለጸጋ (ባለሞገስ) እንዲሆን እኛ እንደማናስፈልገው መረዳት ትሁት ያደርጋል አይደል? እርሱ በእራሱ ማንንም ባያድን ለዘላለም ባለጸጋ ነው ። ስለዚህም እኛን ማዳኑ እጅግ የሚገርም እና ለዘላለም ሳናቋርጥ ልናመሰግንበት የሚገባን ምክንያት ነው።

## ጸጋ እና ድህነት

ጸጋ እንደ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ማለት እንደሆነ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር እኛን በማዳን ውስጥ ስለሚያሳየው ጸጋ እንነጋገራለን።

ጸጋ ሰው በሚሆነው እና በሚያደርገው ነገር ሁሉ የሚገለጥ እና ሌሎች ደግሞ እንደ ባለሞገሳም እንዲመለከቱት የሚያደርግ ውስጣዊ ውበት ወይም ተወዳጅነት ነው የሚለውን ትርጓሜ በመከተል

በድህነታችን ውስጥ የተገለጠልን የእግዚአብሔር ጸጋ ደግሞ እንደ እርሱ እንድንሆን እና በእርሱ ዘንድ ሞገስ እንዲኖረን እግዚአብሔር ከእራሱ ውበት ያካፈለን ስጦታ ነው ማለት እንችላለን። እግዚአብሔር ህዝቡን ሲታደግ የሰጣቸው ተወዳጅነት በንግግራቸው እና በድርጊቶቻቸው ሁሉ የሚገለጥ ነው። ጸጋውን የተቀበለ ሰው የእግዚአብሔርን መውደድ/ተወዳጅነት/ያማረ ማንነት አለማሳየት አይችልም።

ይህ የጋራ ጸጋ የሚያስተምረውን ትምህርት መቀበል የሌለብን አንዱ ምክንያት ነው። ክፉዎች እና የማያምኑ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ሆነ አንዳች የእርሱን መውደድ/ተወዳጅነት/ ጸጋ ሊያገኙ ይገባል የሚለው ሀሳብ ይህን የሚቃረን ንግግር ነው። እግዚአብሔር በክፎችን እና ባልዳኑት ላይ ይፈርድባቸዋል ወደ ገሃነምም ይጥላቸዋል። የእርሱን መውደድ/ተወዳጅነት የተካፈለ እና ጸጋውን የተቀበለን ሰው እንዴት ወደ ዘላለም ጨለማ ይጥላል? ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም።

ስለ እግዚአብሔር የማዳን ጸጋ ሌሎች መጠቀስ ያለባቸው ብዙ ባህሪያት አሉ። እነዚህ ባህሪያቶችም ጸጋ የጋራ ያልሆነበትን ምክንያት ያመለክቱናል።

የመጀመሪያው ባህሪ ጸጋ የእግዚአብሔር ባህሪ ብቻ ሳይሆን *ስጦታም* መሆኑ ነው። ይህ እስካሁን በተነጋገርነው ጉዳይ ላይ ግልጽ ቢሆንም በግሉ አትኩሮትን ይሻል። መጽሐፍ ቅዱስ በብዛት እግዚአብሔር ጸጋን ሲሰጥ ያሳየናል (መዝ 84:11, ምሳ 3:34, ያዕቆም 4:6, 1ኛ ጴጥ. 5:5) ። የጸጋን ነጻ ስጦታነት እና የማይገባን መሆኑን ለማሳየት ጸጋ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው በማለት ተናግረናል። አንድ ነገር የእውነት እንደተሰጠን የምናውቀው ከእግዚአብሔር ባህሪነት አልፎ ለእኛ ሲገለጥልን ነው።

ሁለተኛ፣ ጸጋ *ኃይል* ነው። ይህ የ*እግዚአብሔር* ጸጋ ከማለታችን ጋር ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ሀሳብ፣ የእግዚአብሔር ባህሪ እና የእግዚአብሔር ንግግር እንደ እኛ ተራ ሳይሆን የሁሉንቻይ ኃይል በውስጡ ያዘለ ነው። ይህም እግዚአብሔር ለሁሉም ጸጋን የማይሰጥበት ሌላኛው ምክንያት ነው። ጸጋው ከንቱ ፣ ለማዳን እና ለመታደግ የሚበቃ ሃይል የሌለው ወይንም የማይሳካለት ሊሆን አይችልም። ይህንን አለመቀበል እግዚአብሔር እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው።

ሦስተኛ፣ ጸጋው *አዳኝ* ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ለሰው ከዚህ ጸጋ በስተቀር ስለሌላ ጸጋ ሲናገር አናገኘውም። መመረጥ እና ስርየት የግል እንደሆነ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ አስቀድሞ የተወሰነው እና የተገዛው ጸጋ የግል በመሆኑ አንዳንዶችን ብቻ የሚያድን መሆን አለበት።

በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን ማግኘታችን እጅግ ይደንቃል። በተለይም እኛ በእርሱ ዘንድ ውብ እና ተወዳጅ መሆናችንን ማስረዳቱም የበለጠ ይገርማል። ይህ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር በክርስቶስ እና በስራው በኩል ብቻ ስለሚመለከተን ነው። ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር አንድያ ልጅነቱ የእርሱ ፍጹም መታዘዝ እና ለእግዚአብሔር መሰጠት ከአስር ሺህ ውቦች በላይ ብቻውን ያማረ (ውብ) ያደርገዋል። በእርሱም ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አለን።

## የእግዚአብሔር ምህረት

ምህረቱ ለእኛ ስለሚያስፈልገን ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ምህረት የምናስበው ከራሳችን ጋር በማገናኘት ነው። በብዛትም ርህራሄ ላይ እናተኩራለን። እግዚአብሔር ለእኛ ምህረት አደረገ የምንለው እርሱ ሲራራልን እና ከሀጥያታችን ውጥን ቅጥ እና ጥፋት ሲያድነን ነው (ምሳሌ 16:6)።

ነገር ግን ምህረት ይህ ብቻ አይደለም። ምህረት ሁል ጊዜ የማንነቱ መገለጫ እና ያለ ምህረት እግዚአብሔር ሊሆን (እራሱን ሊሆን) የማይችልበት *ባህሪው* መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ስለዚህም እግዚአብሔር እኛ የምህረቱ መገለጫ ባንሆን ኖሮ እንኳን መሃሪ (በምህረት የተሞላ) ነው። የሰው ልጅ ለዘላለም ቢጠፋ እና ማንም ባይድን እንኳን እርሱ መሃሪ ነው። እርሱ በራሱ መሃሪ ነው (ሉቃስ 6:36)።

ይህም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ካላዳነ እንዴት መሃሪ፣ አፍቃሪ፣ ሩህሩህ ሊሆን ይችላል ብለው የሚናገሩ ሰዎች እንደተሳሳቱ ያመለክተናል። መሃሪ ለመሆን ማንንም ማዳን አያስፈልገውም። ምህረቱን ለየትኛውም ፍጥረት ባያሳይ መሃሪ አምላክ መሆኑ አይቀርም (ኤፌ 2:4)። እርሱ በእራሱ በቂ ፣ ማንም የማይደግፈው እና ምንም የማያስፈልገው *እግዚአብሔር* ነው።

ምህረት እንደ እግዚአብሔር ባህሪ ምንድነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ልናስተውላቸው የሚገቡን ነገሮች አሉ።

ከግላች ጋር ባለው ግንኙነት እንኳን ምህረት አንድን ሰው ለማዳን ካለ ፍላጎት የዘለለ ነገር እንደሆነ ልንረዳ ይገባል። ምህረት አንድ ሰው ደስተኛ እና በበረከት የተሞላ እንዲሆን የመፈለግ ጥልቅ መሻት ነው። ለሚጠፉት ሰዎች ያለ ርህራሄ እና እነርሱንም ለማዳን ያለ መሻት ይህንን ቀጥሎ የሚመጣ ጉዳይ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ምህረት በመጀመሪያ እራሱ ከማንም በላይ የተባረከ እና ለዘላለምም ብሩክ እንዲሆን ያለው

መሻት ነው። እርሱ የሚጠፋ ወይንም የተቸገር ስላይደለ ርህራሄ አያስፈልገውም ነገር ግን የእራሱን ዘላለማዊ ብሩክነት እና ክብር ይሻል። ይህም ምህረቱ የባህሪው አንድ አካል ሆኖ ሲገለጥ ያሳየናል (ዘጽ 34:6)።

እግዚአብሔር ሊምረን ሲፈልግ ብቻ በምህረቱ ውስጥ ርህራሄን፣ ፍቅርን እና የማዳኑን መሻት ያሳየናል ምክንያቱም እኛ የጠፋን እና የምንበሰብስ፣ የርህራሄውም ትክክለኛ መገለጫ መሆናችን ነው (ኤር 5፡11) ። ነገር ግን የመጨረሻው መሻቱ የእርሱ ክብር እና ብሩክነነት በስሙ እና በማንነቱ ላይ እንዲሆን ነው። ስለዚህም በምህረቱ እኛን ማዳን ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር እንድንሆን እና ለዘላለም በእርሱ እንድንደሰት ከፍ ያደርገናል።

እንደ ባህሪነት የእግዚአብሔር ምህረት ኃይል አለው። አንዳንዶች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚያሳየው ኃይል የለሽ የርህራሄ ስሜት (pity)፤ እንዲሁም ለሰዎች ሁሉ የሚሰማው ሀዘን ነገር ግን ተግባር የሌለው ወይንም አላማውን መፈጸም የማይችል አቅም የለሽ ስሜት አይደለም ። እንደሌሎች ባህሪያቶቹ የእግዚአብሔር ምህረት ሉዓላዊ ፣ ሁሉን የሚችል ፣ የማይለወጥ ፣ ዘላለማዊ በመሆኑ ምህረቱን ለአንዳንዶች ብቻ እንዳደረገው ሁሉ ይህንን ምህረት ሲያሳይ አይሳሳትም (ኤፌ 2:4-5, ቲቶ 3:5, 1ኛ ጴጥ 1:3) ። የእግዚአብሔር ምህረት ባዶ እና ተግባር የለሽ ስሜት አይደለም። የምህረቱ መገለጫዎች ወደ ገሀነም ሊገቡ አይችሉም። ምህረት *የእግዚአብሔር (ምህረት)* ስለሆነ እና የሁሉን ቻይነቱ እና መለኮታዊ ባህሪው መገለጫ በመሆኑ የእግዚአብሔር ምህረት "የጋራ (ለሁሉም የተሰጠ)" ነው ብለን አናምንም።

ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ምህረት ለሁሉም ሳይሆን እኛ ሳይገባን ስለተገለጠልን መግለጥ ከምንችለው በላይ እናመሰግነዋለን። እግዚአብሔር ለእኛ እንዲህ መራራቱ እና እኛን መባረኩ ከአእምሮ በላይና በህዝቡ ሁሉ በታላቅ ሀሴት የሚታመን እውነት ነው።

## የእግዚአብሔር ጽድቅ

ልክ እንደ ጸጋው፣ ምህረቱ እና ፍቅሩ የእግዚአብሔር ጽድቅ "የሚተላለፍ" ባህሪ ነው። ይህንን ስንል ጻድቅ እንድንሆን ጽድቁን እንደ ስጦታ ይሰጠናል ማለታችን ነው። እግዚአብሔር ባህሪውን ሁሉ እየሰጠን እርሱን እንድንመስል ማድረጉ እጅግ የሚገርም ነው። ከዚህም ይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ ለእኛ *ለሀጥያተኞች* ይህንን ስጦታ መስጠቱ ነው (ሮሜ 4:5) ።

ከእግዚአብሔር አስደናቂ ስጦታዎች መካከል ከጽድቁ የሚበልጥ ስጦታ የለም። ይህንን ስጦታ የሰጠን እኛ በእራሳችን ምንም ጽድቅ የሌለን እና ያለጽድቅ በእርሱ ፊት በመቆማችን የሚፈረድብን ሰዎች በመሆናችን ነው። የጽድቅን ስጦታ ሲሰጠን ግን በእርሱ ፊት ንጹህ፣ ትክክል እና ክስ የለሽ ሆነን እንቆማለን።

መጽደቅ የእራሱ እግዚአብሔር ጽድቅ ስጦታ እንደሆነ ታውቃላቹ? ይህ በአለም ሊገኝ የማይችል የጽድቅ ስጦታ ከሰማይ የሚመጣ በመሆኑ ሉተር *ኤልየን(alien)* ጽድቅ በማለት ይገልጸዋል (ሮሜ 3:21) ። እግዚአብሔር ይህንን ጽድቅ ያዘጋጀልን በልጁ ስቃይ እና ሞት ሲሆን የሚሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ ስራ እና በእምነት ነው (ዕም. 2:4, ሮሜ 1:17, ሮሜ 3:22-26) ።

የሚደንቀውም ጉዳይ ይህ ሁሉ ጽድቅ ከእግዚአብሔር የመነጨ መሆኑ ነው። በዚህ ጊዜ አብዛኞች ወንጌላዊያን *ነጻ እና በጸጋ* ያለውን የጽድቅ የተሓድሶ አስተምህሮ በመተው በእምነት *እና* በስራ ያለውን ከሮማን ካቶሊክ አስተምህሮ ብዙም የማይለየውን ትምህርት እያስተማሩ ነው። እውነታው ይህ ነው እግዚአብሔር የራሱን ቅድስና መስጠት ብቻ ሳይሆን - የሚሰጠውንም ቅድስና ያገኘው እና የተቀበለው በአካሉ በክርስቶስ በኩል ነው። እኛ ይህንን ለመቀበል እና ለማግኘት ምንም አናደርግም (ሮሜ 3:24) ። የተሰጠን ጽድቅ የእኛ ጽድቅ እንዲሆን የሚያደርግልን *እምነት* የእኛ ስራ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ኤፌ 2:8-10) ። በመጽድቅ ውስጥ እግዚአብሔር በዘላለም ፣ በክርስቶስ እና በመንፈስ ቅዱስ ከሰራው ስራ ውጪ ሌላ ስራ የለም (ሮሜ 11:6)።

ሆኖም ግን እግዚአብሔር ጻድቅ የሆነው ለእኛ ጽድቅን ያካፍለን ዘንድ አይደለም። እርሱ ጻድቅ እንዲሆን እኛ አናስፈልገውም። እርሱ በራሱ ጻድቅ ነው (መዝ 11:7, መዝ 116:5, ዳን 9:7, ዩሀንስ 17:25, ራዕይ 16:5) ።

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ጽድቅ ማለት ለህግ መገዛት ማለት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በየትኛው ህግ ነው የሚረጋግጠው? በየትኛው መስፈርትስ ነው የሚለካው? መልሱም እርሱ በራሱ የክፋት እና የመልካምነት መስፈርት ነው (መዝ 35:24) ። የእርሱ ፍጹምነት ፍጥረት ሁሉ የሚገዛለት እና እርሱም ስራውን እና ቃሉን የሚያስገዛበት መስፈርት ነው። እርሱ በአድሎ ሊከሰስ አይችልም (ሮሜ 9:14) ። በእግዚአብሔር አንዲት ስራ ሆነ ንግግር ላይ ማንም ስህተትን ሊያገኝ አይችልም (መዝ 19:9, ሮሜ 9:20) ። ስራው ሁሉ - እርሱ ስለሚሰራው ትክክል ነው። የእርሱ ጽድቅ ማለት ይህ ነው።

እግዚአብሔር እኛን ጻድቅ አደረገን ማለት እርሱ በታምሩ እና በንጹህ ጸጋው ወደ እርሱ የፍጹምነት መስፈርት እንድንለወጥ ያረጋግጥልናል ማለት ነው። ልጁን በመስቀል ላይ ስለሀጥያታችን እንዲሰቃይ እና የእግዚአብሔርን ሞገስ በእርሱ ስራ እንድናገኝ ይህንን አድርጓል። ምስጋና ለእርሱ ይሁን።

## የእግዚአብሔር ጥበብ

እግዚአብሔር ጠቢብ ነው። ይህንን እውነት ብናምንም እንኳ በተደጋጋሚ እንረሳዋለን። ስለዚህ እራሳችንን መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር ጥበብ የሚያሳስበንን ደጋግመን ማስታወሳችን እግጅ ጠቃሚ ነው።

ጥበብ ማለት ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር ክብር እንዴት ማድረግ እንዳለብን ማወቅ ነው። ብዙ ሰዎች ለእራሳቸው እና ለጥቅማቸው እንዴት ነገሮችን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ክብር ነገሮችን እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። እውቀት አላቸው ጥበብ ግን የላቸውም። እነዚህም በልባቸው አምላክ የለም የሚሉ ናቸው (መዝ 14:1)።

ጥበብ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ለእርሱ ክብር ነገሮችን እንዴት ማድረግ እንዳለብን እርሱ ብቻ ያስተምረናል። ቃሉ የጥበብ ሁሉ ምንጭ ነው፤ መንፈሱም አስተማሪ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን እስካልቀየረልን ድረስ ምንም ልንማር አንችልም።

እግዚአብሔር ለሚጠይቁት ሁሉ ጥበብን እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል። እርሱም በእምነት ጥበብን ለሚጠይቀው ሁሉ እንደማይነፍገው ነግሮናል (ያቆብ 1:5-6) ። ስለዚህም ለሞኝነት ምንም ማመካኛ የለም። ጥቂት በመማራችን ወይም በልጅነታችን እውቀት ሊጎድለን ይችላል ነገር ግን ጥበብ ከጎደለን ምንም ማመካኛ የለንም። የጥበብ ማነስ እግዚአብሔርን ካለመፈለግ ይመነጫልና።

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባለው ግንኙነትም ማጉረምረም አይቻልም። በቃሉ ጥቢብ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በፈተናዎቻችን ሁሉ ለእርሱ እንድነገዛ ፣ ስለመልካምነቱ እንድናመሰግነው እና በምህረቱ መታመን እንድንችል የመረዳት ጥበብን እና እውቀቱን ለክብሩ መጠቀም እንድንችል ቃል ገብቶልናል።

በዚህም እግዚአብሔር የሰጠንን ይህንን ጥበብ ለክብሩ እንጂ ለራሳችን ባለመኖር እናሳያለን። በጸጋ ከእንግዲህ ወዲህ ሞኞች ሳንሆን ጥበበኞች፣ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ የምናውቅ እና በምናደርገው ሁሉ የእርሱን ክብር የምንሻ መሆናችንን እናሳያለን። የሀጥያትን ሞኝነት እና የእውነተኛ ጥበብ መጉደልን በውስጣችን

በምናይበት ጊዜ እንኳን እርሱን የጥበብ ምንጭ አድርገን ጥበብን ከእርሱ በመገፈለግ እና ሳይሰስት እና ሳይገደብ እንደሚሰጠንም በማመን እርሱ ጥበቡን እንደሰጠን እናሳያለን።

ጥበብ ስጦታ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ባህሪም ነው። እንደ ባህሪ ጥበብ እግዚአብሔር ሰለሁሉም ነገር ያለውን እውቀት እና ሁሉንም ነገር ለክብሩ የማድረግ አስገራሚ ችሎታውን ያሳየናል። እርሱ ነገሮች እንዴት እንደሚከናወኑ እና እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ማወቅ ብቻ ሳይሆን ለዘላለም አስቀድሞ ሁሉን ስለሚያውቅ ነገርን ሁሉ በጥበብ አስቀድሞ የፍርዱን ክብር እና ጸጋው እንዲገለጥ ወስኗል።

እግዚአብሔር ለክብሩ አስቀድሞ ሁሉን ነገር በጥበብ በማድረጉ ምክንያት በእኛ ላይ የሚከሰተው "መጥፎ" ነገር ሁሉ ለመልካም የሚሆን እንጂ ከእርሱ ፍቅር የሚለየን አይደለም። እግዚአብሔር በጥበቡ ችግራችንም (መከራችንም ሳይቀር) ለዘላለም እንዴት ለክብሩ እንደሚሆን ያውቃል። የእርሱ ጥበብ እርሱን የምንታመንበትን እና አባታችን እንደሆነ እንድናምን ምክንያት ይሆነናል።

ይህ ለህይወታችን እንዴት የሚገርም ባህሪ ነው! የእግዚአብሔርን ጥበብ ስንረሳ እርሱ በእኛ ላይ ያለውን ውሳኔ (ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት) መጠራጠር እንጀምራለን። እርሱ ጥበበኛ እንደሆነ ስንረሳ ለእኛ ባለው መንገድ ላይ በተለይም መንገዱ ከባድ ሲሆንብን መነጫነጭ እና ማጉረምረም እንጀምራለን። የእርሱ ጥበብ ሁሉ ነገር ተጠቅልሎ ለመልካም እንደሚሆንልን እና የምንፈራው እና የምናጉረመርምበት ምንም እንደሌለ ያረጋግጥልናል።

## የእግዚአብሔር ልህቀት

ሌላኛው የእግዚአብሔር ባህሪ ከሁሉ በላይ መላቁ ነው። ይህ ባህሪው ልክ እንደሌሎች ባህሪያቱ እርሱ ብቻውን አምላክ እንደሆነ ያሳየናል። እርሱ የላቀ ነው ስንል እርሱ ከሁሉም በላይ ፣ ከእርሱ ውጪ ወይንም ከእርሱ ጋር የሚስተካከል ማንም እና ምንም የለም ማለታችን ነው።

እግዚአብሔር ከ*ፍጥረት* በላይ ነው። ፈጣሪ ስለሆነም ከሁሉ በላይ ሊሆን ይገባዋል። አንድ ሰዓሊ/አርቲስት ከየትኛውም ስራዎቹ በላይ እንደሆነ  እግዚአብሔርም ከስራዎቹ ሁሉ በላይ ነው። ስለዚህም የእግዚአብሔር ብልጫነት (ልህቀት) ተፈጥሮ አምላክ ነው ለሚለው እምነት - *ፓንቲይዝም* (pantheism) መልስ ነው። ይህ እጅግ ክፉ ትምህርት የተመሰረተው ዘመነኛ በሆነው አስተሳሰብ ላይ ሲሆን በተለይም ደግሞ በአዲሱ ዘመን

እንቅስቃሴ (New Age movement) እና በተለያዩ የተፈጥሮ ጥብቃ ቡድኖች የሚታሰብ ነው ለእነዚህም ሰዎች የሁሉ ነገር ዋና ተፈጥሮ ነው።

እግዚአብሔር ከቦታ እና ከጊዜ በላይ ነው። የእርሱ ዘላለም ከጊዜ አንጻር ሲቀመጥ በጊዜ ላይ የላቀ ነው፤ የእርሱም በሁሉ ቦታ መገኘት ከቦታ አንጻር በቦታ ላይ ያለው ልህቀቱ ነው። ጊዜ እርሱ የፈጠረው አንድ ነገር ቢሆንም፤ እርሱ በጊዜ አይገደብም። ይህንን መረዳት ለእኛ የሚከብደን ስለእርሱ የምናወራው በትላንት፣ በዛሬ እና በነገ ውስጥ ሆነን በመሆኑ ነው። እውነታው ግን ከትናንት፣ ከዛሬ እና ከነገ አንጻር እርሱ "ያለና የሚኖር (I AM)" ነው። በእርሱ ውስጥ ጊዜ የለም። በአጽናፈ አለሙ አይገደብም። የተዘረጋው ጠፈር እና የፍጥረት አይነት ሁሉ የእጆቹ ስራ ውጤት ነው። እርሱ በዚህ ሁሉ ውስጥ ይገኛል ፤ አብሮትም አለ። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ነው።

ከእኛም አንጻር እግዚአብሔር የላቀ ነው። በዚህም ምክንያት የእርሱን ስራ እና መንገድ ሙሉ በሙሉ መረዳት አንችልም። ሁል ጊዜ የእርሱ ሀሳብ እና መንገድ ከእኛ እጅግ የላቀ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ባንረዳውም ልናምነው ይገባል (ኢሳ 55:8-9) ። ስራው ልንረዳው ከምችለው ሁሉ በላይ ነው። የእርሱ መንገድ የጥንት እውቀት ፤ ክብሩም ፍለጋ የሌለው ነው። የእርሱ ባህሪያት የማይቆጠር ፣ ምስጋናውም ማለቂያ የሌለው ፣ ክብሩም ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው።

እርሱ የላቀ ቢሆንም ከእኛ የራቀ አይደለም (ኤር 23:23) ስለዚህ የእግዚአሔር ልህቀት ለአማኝ አያስቸግረውም ። ይልቅ ይጠጋጋናል ፤ በእምነትም በኩል ተወዳጅነቱን እና መልካምነቱን ለህዝቡ ይገልጥልናል። ህዝቡ ሁሉን ነገር ከእጆቹ የሚቀበሉት አምላክ እውነተኛ ፣ የሚኖር እና ተወዳዳሪ የሌለው መሆኑን ስለሚረዱ የእርሱን ልህቀት በእጅጉ ይወደዋል። በልህቀቱ ውስጥ እርሱን የሚታመኑበትን፣ የሚደገፉበትን እና ለእምነታቸው እና ለተስፋቸው የሚሆንን መሰረት ያገኛሉ። ደስ የማያሰኙ ነገሮችን ወደ እነርሱ ሲያመጣ ፣ ፈተና እና መከራ ሲደርስባቸውም "የልቤ አምላክ ሆይ፥ ልቤና ሥጋዬ አለቀ፤ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው" ይላሉ (መዝ 73:26)።

እግዚአብሔር ብቻ ይችላል። እግዚአብሔር ብቻ ትልቅ ነው። እርሱ ብቻ ከሀሳባችን፣ ከንግግራችን እና ከስራችን የላቀ ነው። ስለዚህም እርሱ ብቻ እምነታችን ይገባዋል።

## የእግዚአብሔር ቀላልነት ወይም ፍጹምነት

በሥነ-መለኮት መጽሐፍት ላይ ምናልባት “የእግዚአብሄር ቀላልነት” የሚል የእግዚአብሔርን ባህሪ አንብባችሁ ይሆናል። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም ስለዚህ ግራ ሊያጋባ በመቻሉ “ፍጹምነት” የሚል ሌላ ቃል መጠቀም የተሻለ ይሆናል። የእግዚአብሔር “ቀላልነት” የአንድነቱ አካል ነው -በባህሪው እና በስራው ሁሉ አንድ ነው። መጋጨት፣ መጣረስ ሆነ አለመጣጣም በስራዎቹ እና በባህሪያቶቹ ውስጥ የለም። ባህሪያቶቹ ሁሉ አንድ ናቸው። እግዚአብሔር ያለ ድካም እና ግድፈት በሁሉም አቅጣጫ ፍጹም ነው።

የእግዚአብሔር ፍጹምነት እግዚአብሔር ፍቅር *ነው*፣ እውነት *ነው* ፣ ብርሀን *ነው* በሚሉት ክፍሎች የበለጠ ይብራራል (1ኛ ዩሀንስ 1:5, 1ኛ ዩሀንስ 4:8, 1ኛ ዩሀንስ 5:6) ። እርሱ ብርሀን *ነው* ማለት በእርሱ ዘንድ ለጨለማ ቦታ የለውም ማለት ነው። እርሱ ፍቅር *ነው* ማለት ፍቅሩን ሊሸር የሚችል ምንም ነገር ሆነ ሁኔታ በእርሱ ውስጥ የለም ማለት ነው። እነዚህ ባህሪያች በተግባራቸው ብዙም የተለያዩ እንዳልሆኑ መመልከት እንችላለን። እንደ አልማዝ ገጽታዎች የማይለያዩ ናቸው። እያንዳንዱ በራሱ ገጽታ ክብሩን ሲገልጡ እና ሲያንጸባርቁ ፤ በአንድነት ሆነው ደግሞ ውድ የሆነን እንቁ ይሰራሉ። ባህሪያቱን መነጣጠል ማለት ባህሪያቱን ማጥፋት ማለት ነው።

እንደምሳሌ የእግዚአብሔርን ምህረት እንመልከት። ምህረት በሀጥያት እና በጉስቁልና በመያዛችን እግዚአብሔር ለእኛ መራራቱ ብቻ ሳይሆን ጉስቁልናችንም የሚያድንበት ነው። እኛን ለመርዳት ያለው ተራ መሻት ሳይሆን የሚሰጠን እውነተኛ እርዳታ ነው። የእርሱ ምህረት እና ሁሉን ቻይነት አንድ ናቸው። መቼም ለሊለያዩ ፣ ሊቃረኑ አይችልይም።

እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑንም አስቡ። የእግዚአብሔር ፍጹምነት (ቀላልነት) ማለት ፍቅሩ ከፍርዱ፣ ከዘላለማዊነቱ ፣ እና ከሁሉን ቻይነቱ ወይንም ከሌሎቹ ባህሪያቶቹ ጋር ሊነጣጠል አይችልም ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር ሁልጊዜም በቅን ይፈርዳል፤ በፍጹም ፍርድ ካልሆነ በስተቀርም በሌላ መንገድ ሊገለጥ አይችልም። በሌላ አማርኛ የፍርዱን ግዴታ በክርስቶስ ሞት በኩል ሳይወጣ ማንንም ሊወድ አይችልም።

የእግዚአብሔር ፍቅር ሁል ጊዜ ዘላለማዊ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ለዛሬ ብቻ ነው የሚባል አይደለም ምክኒያቱም ፍቅሩ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይዘረጋል። የሚወዳቸውን አስቀድሞ ይወዳቸው ነበር ለዘላለምም

ይወዳቸዋል። ስለዚህም ፍቅሩ ሁሉን ቻይ ነው። ይህ ባዶ ንግግር  ሳይሆን የፍቅሩ ትክክለኛ መገለጫ እንድንሆን የሚያደርገን ሃይል ነው።

የእግዚአብሔር ፍጹምነት እግዚአብሔር ሁሉንም እንደማይወድ እና ለሁሉም ጸጋን እንደማይሰጥ ያሳየናል። ንግግራችን ከዚህ በተቃራኒ ከሆን  እግዚአብሔር ከኃይሉ እና ከስልጣኑ የተለየ ማንነት አለው ያልን ነው። በዚህም እግዚአብሔር ከፍርዱ፣ ከቅድስናው እና ከጽድቁ ጋር የሚጣረስ ፍቅር እና ጸጋ አለው ፤ እርሱ ፍቅሩን በክርስቶስ በኩል ጻድቅ ላልሆኑ እና ለማይሆኑ ሰዎች ያሳያል እያልን ነው።

አማኞች ስለእግዚአብሔር ፍጹምነት ማወቃቸው እንዴት ያለ በረከት ነው! ምህረቱ በከንቱ እንዳልሆነ ማወቅ እና ማስተዋል ጸጋው ሊመለስለት የማይችል ፍቅሩም የማይባክን እንደሆነ መረዳት ነው።

## ሥላሴ

የሥላሴ አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ውስጥ ዋነኛው ሆኖም ግን በቂ ትኩረት የተነፈገው የመጽሐፍ ቅዱስ አስትምህሮ ነው። ብዙሃኑ ክርስቲያን ይህ አስተምህሮ ክርስትናን ከሌሎች የእምነት ወገኖች የሚለየው ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ ቢያውቅም ያለውን ትክክለኛ ጥቅም ግን አልተረዳም። ከህይወቱ እና እምነቱ ማረጋገጫነት ጋር ሚያገናኘው ነገር እንዳለ አያስብም።

የሥላሴ አስተምህሮ ለአማኞች ልዩ ዋጋ እንዳለው ማሳወቅ ትልቁ ምኞታችን ነው። አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስን ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ደግሞ የዘላለም ህይወት ነው (ዩሀንስ 17:3) ።

በሥላሴ ማመን በሦስት አምላክ ማመን አይደለም። ጅሆቫ ዊትነስ እና እንደ እስልምና ያሉ የሀሰት ሃይማኖቶች ክርስትና በሦስት አምላክ የማመን ሃይማኖት ነው ይላሉ። ነገር ግን ትክክል አይደሉም። እኛ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ አምላክ እንደሆነ እናምናለን (ዘዳ 6:4) ። ሥላሴ “የሦስት አንድነት” የሚለው ስም አትኩሮቱ እዚህ ላይ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን በመከተል በእግዚአብሔር ውስጥ ሦስት አካላት እነርሱም፡ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እንዳሉ እንረዳለን። በተጨማሪም እውነተኛ ሦስት አካላት ሲሆኑ የተለየ ማንነታቸውን እና ግላዊ ባህሪያቸውን የሚገልጥ የተለያየ ስም (አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ) አላቸው።

ሥላሴን የሚቀበሉ አብዛኞች የአብ፣ የወልድን እና የመንፈስ ቅዱስን ግላዊ አካልነት አይቀበሉም። ለምሳሌ አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ የምንጠቀመው ኃይል ብቻ እንጂ አካል እንደሆነ አይቀበሉም ። ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የሆነውን የ"የአንድ አምላክ" አስተምህሮ እያስተማሩ ሥላሴን ይክዳሉ። በዚህ የሀሰት አስተምህሮ መሰረት አብ ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እራሱን በተለያየ *ስራ* ፣ *ስም* ወይም *መንገድ* ሲገልጥ ነው ብለው ያስተምራሉ። ይህ አስተምሮ በቀደመው የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተወገዘ እና ሞኖአርኪያኒዝም (monarchianism ) ወይም ሳቤሊያኒዝም (Sabellianism) ተብሎ የተሰየመ ነው።

ከዚህ አስተምህሮ ጋር በመቃረን መጽሐፍ ቅዱስ አብ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስን በባህሪያቸው እውነተኛ አካል አድርጎ ያቀርብልናል። ደግሞም አንድ አምላክ እንደሆኑ አትኩሮት ሰጥቶ ይናገራል። ተራ የእግዚአብሔር ስም ፣ ስራ ወይም ኃይል አይደሉም። እነርሱ ብቻቸውን አካል ካልሆኑ ስለ ክርስቶስ የምናምነው ነገር ሁሉ ኪሳራ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሥላሴ ውስጥ የእኛን ሃጥይተኛውን በመልበስ የእኛን መልክ የሚይዝ ፣ በእኛ ቦታ የሚቆም ፣ ሀጥያታችንን እንደ እራሱ ሀጥያት የሚወስድልን ፣ በሞቱ የሚቤዠን እና በአብ ፊት እኛን የሚወክለን አካል የለንም ማለት ነው። በተመሳሳይ ደግሞ በልባችን ውስጥ የሚኖር እና ወደ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለ የግል ህብረት የሚያቀርበን መንፈስ ቅዱስ የሚባለው አካል የለም ማለት ነው። ስለዚህም ስለ ሥላሴ ይህንን እናውጃለን መዝሙር 48:14 "ለዓለምና ለዘላለም ይህ አምላካችን ነው፥ እርሱም ለዘላለም ይመራናል"።

## የሥላሴ አስፈላጊነት

ወሳኝ የሆነው የሥላሴ አስተምህሮ በሚያምኑቱ ዘንድ የሚሰጠው ትኩረት በጣም ያነሰ ነው። ይህ አስተምህሮ ከሌሎች አለማዊ ሀይማኖቶች (heathen religions) እና ከመሰል ሃይማኖቶች ክርስትናን የሚለይ እንደሆነ ቢረዱም በግላዊ ህይወታቸው ላይ ያን ይህል ስፍራን አይሰጡትም። ይህ የተወሳሰበ እና ለመረዳት የሚከብድ ፤ ከህይወታችን እና በክርስትና ውስጥ ካለን ማረጋገጫ ጋር ጥቂት ግንኙነት ያለው

ይመስላል። ሆነም ቀረ ይህ አስትምህሮ በጣም አስፈላጊ እና በቤተሰባዊ ኑሮ እንኳ ወደ ተግባር መለወጥ የሚችል ነው።

በመጀመሪያ - የሥላሴ አስተምህሮ በሦስትነት የተገለጠው እግዚአብሔር ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንደሚያስተምር እናስተውል። የሚያስተምረንም እርሱ በአእምሮዋችን ልንረዳው ከምንችለው በላይ እንደሆነ በማሳየት ነው። ከኢዮብ ጋር “የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን?ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?” በማለት አብረን እንድንጠይቅ ያደርገናል (ኢዮብ 11:7)። እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው። እርሱን ሙሉ በሙሉ መረዳት ብንችል ከእኛ የተገደበ አእምሮ በላይ አይሆንም ነበር። እርሱ እንዲህ ባይሆን አምላክ ሳይሆን በእራሳችን ሀሳብ እና ልብ የፈጠርነው ጣዖት ይሆን ነበር!

በዚህም ምክኒየት የሥላሴ አስተምህሮ የእውነተኛ መመለስ፣ ትህትና፣ መገዛት እና አምልኮ ምንጭ ነው። ይህም እግዚአብሔር እግዚአብሔር መሆኑን እያስታወሰን በጉልበቶቻችን ተንበርክከን ከኢዮብ ጋር አብረን “መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ” እንድንል ያደርገናል (ኢዮብ 42:5-6) ።

ሁለተኛ - የሥላሴ አስተምህሮ እግዚአብሔር ፍጹም ድህነታችን እና ተስፋችን እንደሆነ ያስተምረናል። የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ በእርሱ ውስጥ እናገኛለን። እርሱ ስለ ክርስቶስ ሲል አባታችን ነው። እርሱ አንድያ ልጁ እና ፤ታላቅ ወንድማችን ነው። እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነው እንደ ንፋስም ይመጣል ይሄዳል መኖሩን ሳናውቅ በፊት እንኳ በልባችን ውስጥ በማይገደብ ኃይል ይሰራል።

የእግዚአብሔርን ፍቅር ማወቅ ስንፈልግ ልጅ ወደ አባቱ እንደሚመለከት ወደ አባታችን እንጸልያለን። ማንም ፍላጎታችንን፣ ችግራችንን እና ፈተናችንን እንደማይረዳን በምናስብበትም ሰዓት ልጁ ወደ ምድር ስጋ ለብሶ እንደመጣ እና የሚሰማንን ስሜት እንደተሰማው ያስታውሰናል (ዕብ 4:15) ። ልጁ የእውነትም ታላቅ ወንድማችን ነው። ከእግዚአብሔር እና ከሰላም ሁሉ ሩቅ እንደሆንን በሚሰማን ጊዜ መንፈሱ ከመንፈሳችን ጋር በመሆን የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ይመሰክርናል።

በችግር እና ስላም በማጣት፣ በብቸኝነት እና በሀዘን፣ በደስታ እና በመታዘዝ ውስጥ እንደ እስላም አምላክ የራቀ ሳይሆን ወደ እኛ የቀረበ አባት የሆነ፣ ልጅ የሆነ እና መንፈስ ቅዱስ የሆነ አምላክ አለን።

እርሱ የምንወደው እና በመተማመን የምንደገፈው አምላካችን ነው። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለንም ከእርሱም ውጪ አምልኳችን እና መፈራት የሚገባው የለም።

## ሥላሴ እና ቤተሰብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ሥላሴያዊ አስተምህሮ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ከቤተሰባዊ ኑሮ በላይ የሚያስተምር ጉዳይ የለም። የቤተሰብ እና በቤተሰብ ውስጥ ላለ የተለያየ ጥሪ መሰረት ነው።

ይህንን አስተውሉ! እግዚአብሔር ሦስት አካል እና አንድ አምላክ ነው የሚለው አዋጅ እግዚአብሔር የ*ቤተሰብ* አምላክ እንድሆነ ያመላክተናል። በሥላሴ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አባት፣ ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ አድርጎ ያቅርባል ይህም ማለት በሥላሴ ውስጥ እግዚአብሔር ቤተሰብ ነው። በዚህ ቤተሰብ ውስጥ እርሱ በፍጹም ህብረት ፣ በፍጹም አንድነት እና ፍቅር ውስጥ ይኖራል።

የእግዚአብሔር ቃልም ስለ ቤተሰብ በብዛት የሚናገረው (መዝ 68:6, መዝ 107:41) እግዚአብሔር ቤተሰብን የሚያድነውም ስለዚህ ነው (ኤር 31:1, አሞጽ 3:2, ሐዋ.16 31-34)። ቤተሰብ ሁልጊዜ የሥላሴ ክብር ማንጸባረቂያ ነው።

ይህ ብዙ በተግባር ላይ የሚውሉ ምልከታዎችን ይሰጠናል። የመጀመሪያው ጉዳይ በዚህ ጊዜ ዘመን የቤተሰብ እና የቤተሰብ መርሆች የጠፋበትን ምክኒያት ያመለክተናል። የእግዚአብሔር ሥላሴያዊ ማንነት ማንጸባረቂያ ለመሆን በመፈጠሩ ያለ እግዚአብሔር ቤተሰብ ሊበለጽግ አይችልም።

ከዚህም በተጨማሪ ሥላሴ ቤተሰባዊ ኑሮን እንዴት መኖር እንዳለብን ያስተምረናል። ከእግዚአብሔር ስለ ቤተሰባዊ ኑሮ የምንማረው በመጽሐፍ ቅዱስ ስለቤተሰብ የተጻፈልንን ብቻ በማጥናት አይደለም። ነገር ግን ወደ እርሱ በመቅረብ ለልጆቻችን አባት (እና እናት) መሆንን እንማራለን። ልጆቻችንንም ወደ ቅዱስ ልጁ ኢየሱስ እያስጠጋን ከእርሱ የልጅነት ጥሪያቸውን እንዲማሩ እናደርጋለን። እኛም ወደ መንፈስ ቅዱስ በመቅረብ ስለ ሰላም፣ አንድነት፣ ፍቅር፣ ህብረት እና በቤተሰባዊ ኑሮ ውስጥ ያለን በረከት ከእርሱ እንማራለን። እነዚህን ሁሉ ሊያስተምረን የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። እርሱ የቤተሰባችን እና የመለኮት የበረከት ምንጭ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ንጽጽር በመዝሙር 103:13 ላይ “አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል” በማለት ያቀርበዋል። ተመሳሳይ ንጽጽርን በኤፌሶን 6:1-4 እና በቆላሲያስ 3:18-21 ላይ እናገኛለን። የልጆች መታዘዝ፣ የሚስቶች መገዛት፣ የባሎች ፍቅር እና የአባቶች ምህረት ወይም ርህራሄ “ትክክል” ወይንም “ደስ የሚያሰኝ” የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን እርሱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ስለሆነ (ኤፌ 1:5) ፣ የተወደደው ልጅ እና የፍጥረት ሁሉ የበኩር ስለሆነ (ቆላ 1:13, 15) እና እርሱ ብቻውን መንፈስ ስለሆነ ነው (ኤፌ 4:4)።

ለቤተሰብ የሆነው እውነት ሁሉ ለቤተክርቲያንም ነው። ቤተክርስትያን *ቤተሰብ* ወይንም *ቤት* ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ተቀመጦልናል (ገላ 6:10, ኤፌ 2:19, ኤፌ 3:15) ። ቤተክርስቲያን ከቤተሰብ የተሰራች ናት (ሐዋ 5:42, ሐዋ 20:20) የተሰጠውም ቢሮ እና ሀላፊነት የቤተሰብን መልክ ይያዘ ነው (1ኛ ቆሮ 4:15, ገላ 4:19, 1ኛ ጢሞ 5:1-2)። በእውነቱ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አብ አባት የሆነበት የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነው። በታላቅ ወንድማችን በክርስቶስ በኩል ለህግጋቱ እንገዛለን በእግዚአብሔር ቤትም እንኖራለን (2ኛ ቆሮ 6:18, ዕብ 2:13)። ስለዚህም ቤተክርስቲያን ስለቤተሰባዊ ኑሮ ከእግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅድሱ ቤተሰብ መማር አለበት።

ለቤተሰባችን እና ለታላቋ ቤተሰብ ቤተክርስቲያን በዋናነት መውሰድ ያለብን ጉዳይ ፤ እግዚአብሔርን ማወቅ እና እግዚአብሔር እራሱን በሥላሴ በኩል የገለጠበትን መገለጥ መረዳት ነው። እግዚአብሔር ይህንን እውቀት ይግለጥልን!

## ኪዳኑ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን በተደጋጋሚ ይናገራል። ይህ ኪዳን ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስም በተደጋጋሚ ስለኪዳን ለምን ይናገራል? እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ይፈልጋሉ።

መጀመሪያ ይህ ኪዳን የእግዚአብሔር ኪዳን መሆኑን ማስታወስ አለብን። ይህም ማለት እግዚአብሔር በእራሱ እና ከእራሱ ጋር የገባው ኪዳን ነው። ከእኛ ጋር ኪዳን ሲገባ እርሱ ያለእኛ የነበረው ማንነት(የኪዳን አምላክነት) መገለጥ ነው።

ይህ እግዚአብሔር ለሚገልጠው ነገር ሁሉ እውነት ነው። ለእኛ የሚገልጥልን ሁሉ የማንነቱ መገለጥ ነው - ስለክብሩ፣ ስለኃይሉ፣ እና ስራው የሚያወራ ነው። ይህ እጅግ ትሁት የሚያደርግ ሀሳብ ነው። ከኪዳኑ አንጻር ስንመለከትም እግዚአብሔር የኪዳን አምላክ ለመሆን እኛ እንደማናስፈልገው እነረዳለን ። እርሱ በእራሱ የኪዳን አምላክ ነው።

የእግዚአብሔር ኪዳን በሦስቱ የሥላሴ አካላት፡ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ግንኙነት መካከል ያለ ኪዳን ነው ብለን እናምናለን። በዚህም ጽሁፍ ኪዳኑ ህብረት ወይንም ማሰሪያ እንደሆነ ለማሳየት እንሞክራለን። ይህም እውነት ከሆነ ከጅምሩ ሦስቱን የሥላሴ አካላት አንድ አምላክ አድርጎ ያስተሳሰራቸው ማሰሪያ ኪዳን ነው ማለት ነው።

በሦስቱ አካላት መካከል ያለውን የሥላሴ መለኮታዊ ግንኙነትን የሚያብራራ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ለምሳሌ ምሳሌ 8:22-21 አንዱ ነው። በዚህ ክፍል “እኔ” ብሎ የሚናገረው እና በቁጥር 12 ላይ “ጥበብ” ብሎ እራሱን የገለጠው ወልድ ነው (1ኛ ቆሮ 1:24 ያነጻጽሩት)። በቁጥር 30 ላይ ከአብ ጋር ባለው ግንኙነትም “እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ፤ ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ፥ በፊቱም ሁልጊዜ ደስ ይለኝ ነበርሁ” ተብሎ ተገልጿል። የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ለዘላለም በእራሱ ውስጥ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ባለው ግንኙነት ይኖራል።

ይህንን ግንኙነት የሚገልጹ እነዚህ ክፍሎች ዩሀንስ 10:15 “.........አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው....” ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 2:10 “መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና” ተጠቃሽ ናቸው። እግዚአብሔር እንዴት የተባረከን ህይወት በእራሱ ውስጥ ይኖራል!

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኪዳን ሲገባ ወደ ሕብረቱ እኛን በማስገባት አካሉ ያደርገናል። ወደ ቤተሰቡ አስገብቶንም በክርስቶስ ኢየሱስ እና በመንፈስ ቅዱስ በኩል አባታችን ሆኗል። እንዴት ግሩም ነው!

መጽሐፍ ቅዱስም በ2ኛ ጴጥሮስ 1:4 ላይ የመለኮቱ ባህሪ ተካፋዮች እንደሆንን ይናገራል። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የገባውን ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ባይነግረን በጭራሽ ደፍረን ልናስበው የማንችለው እውነት ነው። ኢየሱስ በዩሀንስ 17:23 ላይ “እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል” በማለት ይህንኑ ይናገራል።

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኪዳኑን ሲያደርግ ወደተባረከው ህብረት ገብተናል። በዚያም ህብረት የእርሱን ሙላት እና በጸጋው ላይ ጸጋን ተቀብለናል (ዩሀንስ 1:16) ። ስለዚህም እርሱ በእኛ ይኖራል ፣ ከእኛም ጋር ይራመዳል ለዘላለምም አምላካችን ይሆናል (2ኛ ቆሮ 6:16) ። ከእርሱ ተለይቶ መኖር የእውነትም ሞት ነው (መዝ 73:27) ። እርሱን ማወቅ ደግሞ የዘላለም ህይወት ነው (ዩሀንስ 17:3) ።

መዘንጋት የሌለብን አንድ እውነት ግን እርሱ የኪዳን አምላክ ይሆን ዘንድ እኛ እንደማናስፈልገው ነው። ከእኛ ጋር ያለው ኪዳን ሁልጊዜም የጸጋ ኪዳን (ንጹህ እና የማይገባን ስጦታ) ነው።

## ዘላለማዊው ቃልኪዳን

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ኪዳን ዘላለማዊ መሆኑንን በተደጋጋሚ ይናገራል። ይህም የሆነው *ከዘላለም* ጀምሮ ኪዳኑ በቅዱስ *ሥላሴ* መካከል ያለ ህብረት በመሆኑ ነው። እግዚአብሔርም እኛን ወደ ተባረከው *ሥላሴያዊ* ህብረት ስለቀላቀለን እና የመለኮቱ ተካፋዮች ስላደረገን ደግሞ ኪዳኑ *ለዘላለም* ነው (2ኛ ጴጥ. 1-4) ። የህብረቱ ግንኙነት እና ፍቅር ለዘላለም አያልቅም። እግዚአብሔር ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አምላካችን ይሆናል እኛም ለዘላለም ህዝቦቹ ነን (ራዕይ. 21:3) ።

በዚህ ስናምን የእግዚአብሔርን ኪዳን እንደተለምዶው ውል ወይንም ስምምነት አናየውም። የእግዚአብሔርን ሰዎች ወደ ድህነት ማምጣት በሦስቱ የሥላሴ አካላት መካከል ያለ ስምምነት ወይንም እግዚአብሔር ለህዝቦቹ በአዳም ወይም በክርስቶስ በኩል የገባው ስምምነት አይደለም። ኪዳን "ስምምነት" ሊሆን አይችልም።

ስምምነት ወይም ውል ዘለቄታ ያለው አይደለም። የውሉ መስፈርቶች ምንም ይሁኑ ምን ሲጠናቀቁ ስምምነቱም እንዲሁ ይጠናቀቃል፤ ቀጣይነትም አይኖረውም። ከፍጻሜው በኋላ ለታሪክ ይቀመጥ ይሆናል እንጂ የመስራት ኃይል አይኖረውም።

ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ሳስቀምጠው ውል ወይንም ስምምነት *ወደ መደምደሚያ የሚወስድ መንገድ ነው* ። ለምሳሌ - መድኃኒት ወደ ተሻለ ጤና የሚወስድ መንገድ ነው። ጤነኛ ስንሆን መድኃኒቱ ስለማያስፈልገን መተው እንችላለን። ኪዳኑ የድህነት መንገድ ብቻ ከሆነ ድህነትን የሚሰጥ ስምምነት እንጂ ድህነታችንን ከተቀበልን በኃላ ኪዳኑ ባላስፈለገን ነበር።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ኪዳኑ ዘላለማዊ እንደሆነ ስለሚነገረን ሊቆም ወይም የማያስፈልግ ሊሆን አይችልም። ወደ ድምዳሜ የሚያደርሰን መንገድ ሳይሆን ራሱ ድምዳሜው ነው። ወደ ድህነት የሚወስድ መንገድ ሳይሆን ራሱ ድህነት ነው። ስራውን ጨርሶ ወደ ጎን የምናስቀምጠው ውል ሳይሆን ብሩክ የሆነ እና ለዘላለም የሚቆይ በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል ያለ ግንኙነት ነው።

የድህነት ዋና አላማ በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ያለው ህብረት አይደለምን? ራዕይ 21:2 ላይ የሚናገረው የላቀው የድህነት ክብር በመጨረሻ እግዚአብሔር አምላካችን እኛም ህዝቦቹ ስንሆን አይደለምን? እኛም ይህ የእግዚአብሔር ኪዳን እንደሆነ እናምናለን። ኪዳኑም ዘላለማዊ ነው።

ዩሀንስ 17:3 እንደሚናገረው የዘላለም ህይወት ማለት አብን እና የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ለህዝቡ የገባው ዘላለማዊ ኪዳን ነው። በእውነት ከዚህ የሚበልጥ አስገራሚ ነገር ከየት አለ። የወርቅ መንገድ እንኳን ከእዚህ ጋር አይወዳደርም። የእውነተኛ ድኅነት ፣ የመንግስተ ሰማይ እና የዘላለማዊ ህይወት ክብር ዘላለማዊው ኪዳን ብቻ ነው።

ነገር ግን ሁሉ ከዚህ ሊካፈሉ አይችሉም። ክርስቶስ ወደ አብ ክብር መግቢያ ብቸኛው መንገድ በመሆኑ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑት ብቻ እግዚአብሔርን ማወቅ እና ማየት ይሰጣቸዋል። ስለዚህም ዩሀንስ 17:3 እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስንም ስለማወቅ ይናገራል።

## አንዷት ኪዳን

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው የእግዚአብሔር ኪዳን ዘላለማዊ ከሆነ ሊኖር የሚችለው አንድ ኪዳን ብቻ ነው። ጊዜያዊ ኪዳን ሊተካ ይችላል ፤ የእግዚአብሔር ኪዳን ግን ጊዜያዊ አይደለም።

ኪዳኑ የማይሻር ከሆነም ከአንድ ኪዳን በቀር ሌላ ኪዳን የለም። መጽሐፍ ቅዱስ በመሳ 2:1፣ መዝ 89:34 ፣ በኤር 33:20-21 እና በተለያዩ ሌሎች ክፍል ውስጥ ይህ ኪዳን እንደማይሻር  ይናገራል። ስለዚህም ብቸኛው ኪዳን ይህ ነው።

ኪዳኑ የእግዚአብሔር ኪዳን ከሆነ እና የእግዚአብሔር ኪዳን በሥላሴ ሦስት አካላት መካከል ያለው ህብረት ከሆነ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ኪዳኑም አንድ ነው።

ብዙ ኪዳን አለ ከሚለው የዲስፔንሽናሊዝም (dispensationalism) አመለካከት ጋር በመቃረን አንዲት ኪዳን አለች ብለን እናምናለን። በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መካከል በተለይም በኪዳን ዙርያ ልዩነት አለ ብለው የሚያምኑትን ባፕቲስቶች በመቃረን አንድ ኪዳን አለ ብለን እናስተምራለን። አስቀድሞ የነበረውን ከአዳም ጋር "የሥራ ኪዳን" ነበር የሚለውንም አስተምህሮ እንቃወማለን።

ስለዘላለማዊ ኪዳን (ነጠላ) የሚያወሩ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህንን ይመሰክሩልናል። ለዚህም አንባቢያንን ወደ ዘፍጥረት 17:7, 2 ሳሙኤል 23:5, መዝሙር 105:8-10, ኢሳይያስ 55:3, ሕዝቂኤል 16:60-62 እና ወደ ዕብራውያን 13:20 እንመራለን።

ታዲያ ኪዳንን በብዙ ቁጥር የሚያስቀምጡትን ክፍሎች ምን እንላለን (ሮሜ 9:4, ገላ 4:24, እና ሌሎችም)? ስለ አዲስ እና ስለ ብሉይ ኪዳን የሚያወሩትን ክፍሎችስ እንዴት እንረዳለን (ኤር 31:31-33, ዕብ 8:6-13)?

መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ይቃረናል (እግዚአብሔር እራሱን ይቃረናል) በሚለውን ሀሳብ ለመቀበል ካልሆነ በስተቀረ እነዚህን ክፍሎች ስለ አንድ ኪዳን ከሚያወሩት ክፍሎች ጋር ለማስታረቅ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን እንድናደርግ በሚጠቀመው አንዳንድ ቋንቋ ያመለክተናል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ኪዳኑን *ሲያስታውስ* (ዘሌዋ. 26:42, ሉቃስ 1:72) ፣ ኪዳኑን ሲሰጥ (ዘኍል 25:12, ሐዋ. 7:8) ፣ ኪዳኑን ሲናገር (ዘዳ 4:13)፣ ኪዳኑን ደግሞ ሲጠብቅ (1ኛ ነገሥት 8:23) ያሳየናል። እነዚህ አገላለጾች እግዚአብሔር ኪዳኑን ሲመሰርት ወይንም ኪዳኑን ሲገባ የድሮውን ኪዳን በመሻር አዲስ ዘላለማዊ ኪዳን እያመጣ ሳይሆን የጸጋ ኪዳኑን የገለጠበትን አዲስ መገለጥ እንድንመለከት ይረዳናል። በዚህም መንገድ ብቻ አዲስ እና ብሉይ ኪዳን ቢኖርም አንድ ኪዳን አለ።

ይህ ኪዳን ከጸጋ ኪዳን ውጪ ሊሆን አይችልም። ለእኛ ከሰጠን የማይገባ ስጦታ በስተቀረ ከእግዚአብሔር ጋር በህብረት ለመኖር የሚያስችል ምንም ምክንያት የለም። አዳም እንኳን ታዝዞ ከአብ ጋር በኪዳን ውስጥ መቆየት ቢችልም ወደ ዚያ ህብረት የመጣው በመብቱ ወይንም በችሎታው አይደለም።

ስለዚህም ከአዳም ጋር የነበረው ኪዳን የጸጋ ሳይሆን በስራ ስለተገባው ተሰጥቶታል የሚለውን አስተምህሮ አንቀበልም። ከዚህም በበለጠ አዳም በነበረው ኪዳን ውስጥ ቢታዘዝ ኖሮ ዘላለማዊ ሕይወትን በመታዘዙ ያገኛል የሚለውን አስተምህሮ አንቀበልም።

ሉቃስ 17:10 ላይ ተገብቶን ያገኘነው አንዳች ነገር እንደሌላለ እንዲህ በማለት ይገልጣል “እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፤ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ” ። የእግዚአብሔር ዘላለማዊው ኪዳን የጸጋ ኪዳን ብቻ ነው።

## የጸጋ ኪዳን

የእግዚአብሔር ኪዳን በእርሱ እና በህዝቡ መካከል ያለ ህብረት/ግንኙነት ከሆነ ኪዳኑ ሊሆን የሚችለው የጸጋ ኪዳን ብቻ ነው ።

ከህያው እግዚአብሔር ጋር በጓደኝነት፣ በህብረት እና በፍቅር መኖር መቻላችን እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን የማይገባ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መኖሩ እና አምላካችን መሆኑ በጭራሽ የማይታሰብ ሆኖ ሳለ ሀጥያተኛ ብንሆንም “በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ” (2 ቆሮ 6:16) የሚል ኪዳንን ሰጠን። እንዴት ግሩም ነው!

ለእኛ እውነት የሆነው ሁሉ ለአዳምም እውነት ነው ። ማን በድፍረት አዳም እግዚአብሔርን አውቆ እና ወድዶ መፈጠሩ ያልተገባው ስጦታ አይደለም ብሎ ይከራከራል? በእውነትም ስለሚገባው አይደለም ። እርሱ በእንደዚህ አይነት ክብር ባይፈጠር ኖሮ በጥረቱ ከእግዚአብሔር ጋር የመሆን አቅም አልነበረውም። ከሉቃስ 17:10 “እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ። የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ” ማንምም ከእግዚአብሔር ፊት ተገብቶት እንደማይቆም እንማራለን።

ስለዚህም ስለተገባን ተቀብለናል የሚል በስራችን ላይ የተመሰረተን ኪዳን አንቀበልም። እግዚአብሔር ከአዳም ጋር የነበረው ኪዳን በሥራ ላይ የተመሰረተ ነው ብለን ለመናገር ከቶ አንደፍርም። የሥራ ኪዳን ብቻውን ያለ ኪዳን ሳይሆን የቀድሞው ኪዳን መገለጥ መሆኑን በግልጽ መረዳት አለብን ።  በተጨማሪም የአዳም መታዘዝ እና መልካም ሥራ የኪዳኑ ምክንያት ወይንም መሰረት ሳይሆን አዳም በተገባለት ኪዳን መኖር የሚችለው በመታዘዝ ውስጥ ሲቆይ ብቻ ነው።

ይህም ማለት በሌላ አነጋገር ኪዳኑ የሚፈጸመውም የሚጠበቀውም ያለ ሰው እርዳታ ወይንም አጋዥነት በእግዚአብሔር ብቻ ነው። ሰው በኪዳኑ ውስጥ ሀላፊነት እና ግዴታ ቢኖርበትም ይህ ኪዳን በሰው ላይ የተደገፈ ኪዳን አይደለም ማለታችን ነው።

ምናልባት ይህ ምሳሌ ለመረዳት ይረዳን ይሆናል። ለመኖር መብላት እንዳለብን እናውቃለን፣ ነገር ግን በህይወት የምንኖረው በምግብ እና በመጠጥ አቅም እንዳልሆነ እናስተውላለን። ህይወታችንንም ያገኘነው ከምግብ እና ከመጠጥ አይደለም። በህይወታችን እያንዳንዱን ሴኮንድ የሰጠን እግዚአብሔር ላይ የተደገፈ ነው። ምግብ እና መጠጥ ህይወትን *ማስቀጠያ መንገዶች* እንጂ የህይወት *ምክንያት* አይደሉም። በተመሳሳይ መታዘዝ የእግዚአብሔር ኪዳን በረከት እና ሥልጣን እንድንጠቀም የሚያደርገን መንገድ ነው እንጂ ለኪዳኑ ምክንያት ወይንም መሰረት አይደለም።

ኪዳኑ የጸጋ ስለሆነ የተረጋገጠ እና ዘላለማዊ ኪዳን ነው ስለዚህም ሊሻር አይችልም። አዳም ታማኝ ባይሆንም ፤ እኛም የእርሱን ኮቴ ብንከተልም እግዚአብሔር ግን ታምኖልን ኪዳኑን ሳይሽር ከአፉ የወጣውንም ቃል አልቀየረም (መዝ 89:34) ። የእርሱ ታማኝነት እጅግ ትልቅ ነው። የኪዳን አምላክ ነውና ለእርሱ ብቻ ክብር ይሁን።

## የኪዳኑ ቃል

ከእግዚአብሔር ኪዳን አስደናቂ ነገሮች መካከል አንደኛው በቃል ኪዳኑ በኩል ኪዳኑን ለእኛ ማሳወቁ ነው። በዚህ ቃልኪዳን ውስጥ የገባልን ኪዳን የጸጋ ኪዳን መሆኑን አሳይቶናል። በቃል ኪዳኑም ውስጥ ምህረቱን አበዛልን ፤ በጸጋ ላይ ጸጋንም ጨመረልን።

ይህ ቃል ኪዳን በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲጠቀስ እና የኪዳኑ ቀመር ሲሆን እንመለከታለን። ቃላቶቹ ላይ ጥቂት ለውጥ አድርገን የእግዚአብሔርን ቃል አስቀመጥነው“እኔ አምላካችሁ እሆናለው እናንተም ህዝቦቼ ትሆናላችሁ” (ዘፍ. 17:7-8, ዘዳ 7:6, 2ኛ ቆሮ 6:16, ራዕ 21:3) ።

እግዚአብሔርን እንደአምላካችን ከማግኘት የበለጠ ሌላ ቃል ኪዳን ለማንም ሊኖረው ሆነ ሊያስበው አይችልም፥ እርሱን ማወቅ መቻላችን፣ መውደዳችን፣ ከእርሱ ጋር ህብረት ማድረጋችን እጅግ ይገርማል። የኪዳኑም ሙሉ ቃል ኪዳን ይህ ብቻ ባለመሆኑ እግዚአብሔር በጸጋ ላይ ጸጋ እናም በበረከት ላይ በረከትን ይጨምርልናል።

እግዚአብሔር በምህረቱ በዚህ ቃል ኪዳን ላይ የልጆቻችንም አምላክ እንደሚሆን ጨመረልን። እኛ ከእርሱ ምንም ባይገባንም እንኳን ድህነታችንን ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችንም የድህነትን ቃል ገባልን። እንዴት የሚገርም ጸጋ ነው!

ስለ አማኞች ልጆች የሚናገረው እግዚአብሔር ቃል በአዲስ እና በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገባ የቃል ኪዳኑ አካል ነው። የመጀመሪያው ዘፍጥረት 17:7-8 ላይ እግዚአብሔር ከአብርሀም ጋር በነበረው ህብረት ውስጥ ይገኛል። በድጋሚም ሐዋሪያት ሥራ 2:39 ላይ በምትገኘው የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እናገኘዋለን።

ይህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ልጆቻችንን ሁሉ እንደሚያድን ማስተማመኛ ኪዳን እንዳልሆነ እና ሊሆንም እንደማይችል ልናውቅ ይገባናል። ኤሳው ወይንም ቃዬን በእግዚአብሔር ህዝቦች ቤተሰብ ውስጥ ምን ጊዜም እንደማይጠፉ ማስታወስ ግድ ነው፤ ለቤተሰብ ሀዘን ቢሆኑም ። እግዚአብሔር የሰጠው ቃል ኪዳን ከህዝቡ እና ከቤተሰባቸው ጋር እንደሚቀጥል፤ ከእነርሱ እና ከቤተሰቦቻቸው አልፎ የትውልድ ሀረጋቸው ከኪዳኑ እንደማይቆረጥ ማረጋገጫ ነው።

የአማኞች ልጆች ሲጠመቁ ይህንን ተስፋ ለማስታወስ እና ለመወከል ነው። ይህ ቃልኪዳን የኪዳኑን መመሪያዎች እና መርሆች እንድንከተል ደግሞም ተፈጻሚ ኪዳን እንደሆነ ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔር ጸጋው እንዴት ታላቅ እንደሆነ የሚያሳይ ቃል ኪዳን ነው።

እኛም ይህ *ቃልኪዳን* በማይለወጠው እና በማይዋሸው እግዚአብሔር የተሰጠን መሀላ እንደሆነ አጽንሆት ልንሰጥ እንወዳለን። ወላጆች ቤታቸውን ሲመሩ ለሚገጥማቸው የትኛውም ፈተና እና መከራ ይህንን አጥብቀው ሊይዙ ይገባል። ልጃቸው ሲጠፋ ወይንም ሳይታዘዝ ሲቀር በጸሎት እንዲተጉ የሚያደርጋቸው ምክንያትም ይህ ነው።

እግዚአብሔርም በዚህ በጣም ውድ በሆነው ቃልኪዳኑ ለብዙዎች ጸጋውን እና የኪዳኑን ፍጻሜ ያሳይ (መዝ 25:14) ።

## አስቀድሞ መወሰን (ፕሪደስትኔሽን)

ሰዎችን ብዙ ጊዜ የሚከብደው አስተምህሮ አስቀድሞ መወሰን (ፕሪደስትኔሽን) ነው። የሚከብድበትም ምክኒያት እንደዚህ አስተምህሮ እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ የሚገለጥበት፤ እኛም በፊቱ በትህትና

በመቅረብ ታላቅነቱን እንድናደንቅ የሚያደርግ አስተምህሮ ባለመኖሩ ነው። ለትዕቢተኛ እና ሀጥያተኛው ልባችን ይህን መሰል ትህትና እጅግ ከባድ ነው ምክኒያቱም የሞኝነት ትዕቢታችን የእራሳችንን ዕጣ ፈንታ እንደምንቆጣጠር ስለሚያሳስበን ነው።

አስቀድሞ መወሰን ማለት ከቃሉ እንደምንረዳው እግዚአብሔር በዘላለም ውስጥ አስቀድሞ የምክኒያታዊ፣ የአሳቢ፣ እና ባለፈቃድ ፍጥረቶቹን፤ መላዕክት ቢሆኑ ሰዎች፣ የወደቁ ቢሆኑ ያልወደቁ፣ ዕጣ ፈንታቸውን ወስኗል። ይህንንም አለም ከመፈጠሩ በፊት በዘላለም ምክሩ አደረገ (predestination *በሚለው ቃል ውስጥ የምናገኘው* pre- *የሚለው ቅጥያ ቀድሞ ፣ በፊት የሚልን ትርጉም አለው*) ። በዘላለም ውስጥ እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለመንግስተ ሰማይ መርጧል አንዳንዶችን ደግሞ አልመረጠም። ይህ የእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የወሰነው ዘላለማዊ ፍጻሜ ነው እንጂ ሰው በእራሱ ፍጻሜውን አይመርጥም።

ይህንን አስትምህሮ የሚቃረኑ ብዙ አስተምህሮዎች አሉ። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ አሸንጉሊት ናቸው፣ አንዳንዶችን አስቀድሞ ለገሃነም በመወሰኑ እግዚአብሔር አምባ ገነናዊ እና ጨካኝ ያደርገዋል፣ እግዚአብሔር የሀጥያት ጀማሪ ነው ማለት ነው እያሉ ሰዎች ይናገራሉ ። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አስቀድሞ መወሰንን ያስተምረናል።

“ፕሪደስትኔሽን” የሚለው ኢንጊሊዘኛው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ቦታ ተጠቅሷል  በሮሜ 8:29, 30 እና ኤፌሶን 1፡5, 11። በ”ፕሪዲስትኔሽን” የተተካው የግሪክ ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ “አስቀድሞ ምልክት የተደረገበት” ማለት ነው።  ይህም ቃል በሐዋሪያት *ሥራ* 4:28 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 2:7 ላይ ቢጠቀስም በተየ መልኩ ተተርጉሟል። የአስቀድሞ መወሰን ሀሳቦችም በሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የተገለጹ ቢሆንም ምናልባትም በሮሜ 9:11-13 ላይ እንደተጠቀሰው ሌሎች ክፍሎች ላይ አልተጠቀሰም ማለት እንችላለን። “ልጆቹ ገና ሳይወለዱ፥ በጎ ወይም ክፉ ምንንም ሳያደርጉ፥ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ፥ለእርስዋ። ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት።ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።”

መላዕክት እና ሰይጣን እንኳን ሳይቀሩ በእግዚአብሔር አስቀድሞው ተወስነዋል። ይህንን በግልጽ 1ኛ ጢሞቴዎስ 5:21 “*ስለተመረጡ* መላዕክት” በማለት ሲነግረን ይሁዳ 6 ላይ ስለወደቁት መላዕክት “መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።” በማለት ይናገራል።

ለመላዕክት እንደሆነው ሁሉ ለሰዎችም ነው። አንዳንዶች ለዘላለም ህይወት እና ለመንግስተ ሰማይ ተጠርተዋል ይህም ሀሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ *መመረጥ* በሚል ቃል ተቀምጦልን እናየዋለን። አንዳንዶች ደግሞ ታልፈዋል ወይንም ደግሞ አልተመረጡም፤ አለመመረጣቸውም አንዳንድ ጊዜ "ሪፕሮቤሽን" ተብሎ ይጠራል።

አብዛኞች መጽሐፍ ቅዱስ ስለመመረጥ የሚያወራውን ለመቀበል ዝግጁ ቢሆኑም ስላለመመረጥ ወይንም የሪፕሮቤሽንን አስተምህሮ መቀበል አይፈልጉም። አለመመረጥ እና መመረጥ አብረው የሚሄዱ ነገሮች መሆናቸው እጅግ ግልጽ ነው፤ አንዳንዶች ተመርጠዋል እያለን ሌሎች በእግዚአብሔር ለዘላለም ህይወት እንዳልተመረጡ አለማመልከት አይቻልም። ቃል በቃል ባይጻፍም *"ሪጀክሽን" ወይንም "ሪፕሮቤሽን"* አለመመረጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ስለ መመረጥ እና እግዚአብሔርም ያልተቀበሉትን ስላለመቀበሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እናያለን።

ሁለቱም የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እና ዘላለማዊ ስራ መሆናቸውን ይህ ቃል በግልጽ ይመሰክራል "በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቈጠራሉ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም። ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም።" (ዳን. 4:35)

## ያለ ቅድመ ሁኔታ መመረጥ

ስለ አስቀድሞ መወሰን ከተነጋገርን አሁን ደግሞ ስለአስደናቂው የመጽሐፍ ቅዱስ የመመረጥ አስተምህሮ ልናወራ እንወዳአለን። መመረጥ በአስቀድሞ መወሰን እንድንገርም የሚያደርገን ውብ ገጽታ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ መመረጥን በተደጋጋሚ በማንሳቱ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመመረጥ አያስተምርም ብሎ መካድ አዳጋች ነው። ስለዚህም ጥያቄያችን መመረጥ አለ ወይንስ የለም ሳይሆን መመረጥ ምንድነው? መቼ ተመረጥን? የሚል ይሆናል።

መመረጥ እግዚአብሔር በፈቃዱ ከዘላለም አንስቶ አንዳንዶችን ለድህነት እና ለዘላለም ህይወት የጠራበት መጥራት እንደሆነ እናምናለን። የሰዎችን ምላሽ አይቶ አይመርጥም ነገር ግን የመረጣቸውን "ዓለም ሳይፈጠር" (ሮሜ 9:10-13, ኤፌ 1:3-6) መረጣቸው።

የመመረጥ አስተምህሮ የሚጠላ እና የሚካድ እንዳልሆነ ለመረዳት፤ መመረጥ የእግዚአብሔር ውሳኔ ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ እና የማይቀየር *ፍቅሩ* መገለጥ እንደሆነ ማስተዋል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዶችን

እንደመረጠ ብቻ ሳይሆን ለምን እንደመረጣቸው ጭምርም ይነግረናል። ይህንንም በማድረግ የእግዚአብሔርን የልብ ወገግታ በጥቂቱ ያሳየናል። እግዚአብሔር አንዳንዶችን የመረጠው እንዲሁ *ስለወደዳቸው* ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው። ህዝቡንም ሁሌም ይወድዳል።

ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ያለ ምክንያት ነው። ሰው ለሰራው ስራ የተሰጠው ክፍያ አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎችን የወደደው እነርሱ አስቀድመው ስለወደዱት አይደለም ይልቁንም ለመውደድም ቀዳሚ ለዘላለምም ወዳጅ እርሱ ነው (1ኛ ዩሀንስ 4:19) ።

ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ሉዓላዊ እና ኃያል ነው። በክርስቶስ ኢየሱስም በኩል ሙሉ ድህነትን ክርስቶስ ለሞተላቸው ስለሚሰጣቸው ሳይፈጸም የሚቀር አይደለም (ዩሀንስ 3:16) ።

በመጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ አወቃቸው *(foreknowledge)* የሚለው ቃል ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እየተናገረ እንዳለ እናምናለን። ቀድሞ የነበረውን እውቀት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ከነገሮች ጅማሬ በፊት የነበረውንም ፍቅር ገላጭ ነው። አስቀድሞ “አወቃቸው *(foreknowledge*)” በሚለው ቃል ውስጥ ያለው “ማወቅ *(know*)” የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ቦታ በባልና በሚስት መካከል ወይንም ደግሞ በሚስት እና በባል መካከል ያለን ጥልቅ ፍቅር ለመግለጽ ሲጠቀስ እናያለን (ዘፍ 4:1, 25) ።

ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር ህዝቡን አስቀድሞ ያውቃል (ዘፍ 18:19) ። እነርሱን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከውስጥ፣ ከልብ በሆነ ፍቅር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከዘላለም ጀምሮ ይወዳቸዋል።

ለማመስገን እንዴት ደስ የሚያሰኝ ምክኒያት ነው! በክርስቶስ መስቀል ስር እና ለጥፉ ሀጥያተኞች በሰራው የመልካም ስራ ብርሃን ውስጥ ለሆንን የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት አስደናቂ ነው። ደግሞም ለዘላለም፣ ሳይለወጥ እና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የእራሱ የሆኑትን መውደዱን ስናስብ እንዴት እጅግ ይበልጥ ያስገርመናል። ይህ በእውነትም “አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ” ፤ ቁመቱም፣ ርዝማኔውም ሀይሉም ጥልቀቱም ሊለካ የማይችል ፍቅር ነው (ኤፌ. 3:17-19) ።

### *ሪፕሮቤሽን* (እግዚአብሔር ያልተቀበሉትን አይቀበልም፣ አለመመረጥ)

ካልቪኒስቶች እግዚአብሔር በጸጋው ብዛት አንዳንዶችን ብቻ ወደ ድህነት መጥራቱን "በመመረጥ" ያምናሉ ። አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር ለዘላለም የተቀሩትን እንዳልተቀበላቸው (አለመመረጥ) ያምናሉ። ነገር ግን የአጽኖት መጠኑ የተለያየ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች ጠንከር ያለ ቋንቋን በመጠቀም "እግዚአብሔር አንዳንዶች እንዲጠፉ ወስኖባቸዋል" ብለው ሲያምኑ ሌሎች ደግሞ ለስለስ ያለውን በመጠቀም እግዚአብሔር በዘላለም ውስጥ አንዳንዶችን "ያልፋቸዋል" ወይንም "በሀጥያታቸው ውስጥ እንዲቀሩ ይተዋቸዋል" ብለው ያምናሉ። ሁሉቱም ግን የሚያመለክቱት አለመመረጥን ነው።

መመረጥ እና አልመመረጥ አንድላይ *ደብል ፕሪዴስትኔሽን (ጥንድ አስቀድሞ ውሳኔ)* ይባላሉ። የተሓድሶ የእምነት አዋጅ በግልጽ *ጥንድ አስቀድሞ ውሳኔን* ያስተምራል። የካልቪኒዝም የመጀመሪያው አምስት ነጥቦች የሆኑት የዶርት ቀኖናዎች ይህንን ሲያስተምሩ[11] በተመሳሳይ የዌስትሚንስተር የእምነት አዋጅም ይህንኑ ያስተምራል[12]።

*መጽሐፍ ቅዱስ አለመመረጥን (ሪፕሮቤሽን) ያስተምራል?* የሚከተሉትን ክፍሎች እንመልከት።

ሮሜ 9:10-13 ያዕቆብ እና ኤሳው ከመወለዳቸው በፊት እግዚአብሔር አስቀድሞ አንደኛውን መጥላቱን ያናገራል። እንደገናም ሮሜ 9:21-22 አንዳንድ ሰዎችን ለውርደት የተሰሩ ሸክላዎች እና "ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ ዕቃዎች" ብሎ ያስቀምጣል። 1ኛ ጴጥሮስ 2:6-8ም አንዳንዶች ባለመታዘዛቸው ለመሰናከል *የታጠሩ* እንደሆኑ ይናገራል። ይሁዳ 4 ደግሞ ለፍርድ ቀን *ስለተዘጋጁ* ሰዎች ይናገራል። ይሁዳ 6ም ከወደቁት መላዕክት *ጋር* በማያያዝ ስላለመመረጥ ይናገራል።

በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀማቸውን ጠንካራ ቃላት እናስተውል። ከምንም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በእውነትም እንዲሁ ከነሀጥያታቸው እያለፋቸው ሳይሆን ለጥፋት

እንደወሰናቸው እና እንደመረጣቸው በግልጽ ሲያሳይ እንመለከታለን። በየትኛውም መንገድ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጠኝነት ለጥፋት መወሰንን ያስተምረናል።

ስለ አለመመረጥ ስነነጋገር ሁለት ነገሮች ላይ አጽንዖት እንሰጣለን፡ የመጀመሪያው - እግዚአብሔር ባለመምረጡ የሀጥያት ጸሐፊ አይደለም ደግሞም ሀጥያተኞችን ሀላፊነታቸውን ከመውሰድ አያግዳቸውም። ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔር ባለመምረጥ ውስጥ አላማ አለው የሚለው ጉዳይ ነው።

በመመረጥ እና ባለመመረጥ መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት ይህ ነው - እግዚአብሔር ህዝቡ እንዲድን በሉዓላዊነቱ ከዘላለም ጀምሮ በመምረጡ እና ለድህነታቸው የሚያስፈልገውን ነገር በማድረጉ የመዳናቸውን ክብር እና ምስጋና እርሱ ለእራሱ መውሰዱ ነው። ባለመምረጡ ሉዓላዊ ቢሆንም አለመምረጡ የእርሱን ስም ዝቅ አያደርግም። በዚህ መልኩ መመረጥ እና አለመመረጥ እኩል አይደሉም። እግዚአብሔር በመመረጥ ውስጥ የድህነት ጀማሪ ሲሆን ባለመምረጡ ምክንያት እርሱ የሀጥያት ጽሐፊ አይደለም።

በሮሜ 9:17-20 እግዚአብሔር የሀጥያተኞችን ስህተት መፈለጉ ልክ አይደለም የሚል ሀሳብ ትክክል እንዳይደለ እንመለከታለን "ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ?" በተመሳሳይ ደግሞ ክፉዎችም ስለሀጥያታቸው ሙሉ ሀላፊነትን እንደሚወስዱ ይናገራል። በሐዋሪያት ሥራ 2:23 ላይ ክርስቶስን በመስቀል ለሀጥያት መሰዋቱ ቀድሞ መወሰኑ ብቻ ሳይሆን እንዲሰዋ "ክፉ እጆችን" አስቀድሞ እርሱ እንደወሰነ በግልጽ ተቀምጦልናል።

ይህ ሁሉ አለመመረጥ ያለፈቃድ መሆኑን አያመላክትም። እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለዘላለም ያለምክንያት አይመርጥም ማለትም ትክክል አይደለም። ሮሜ 9:22-23 እግዚአብሔር ቁጣው እና ኃይሉ ይታወቅ ዘንድ እና የክብሩ ታላቅነት በምህረት እቃዎቹ ውስጥ ይገለጥ ዘንድ ነው በማለት ሁለት ምክኒያቶችን ያቀርብልናል ። በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ላይ በግልጥ እንደምናየው አለመመረጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ምህረት ያሳይል (ሐዋ. 4:24-28) ።

አለመመረጥ ለስጋችን የሚከብድ አስተምህሮ ቢሆንም ሰው የእግዚአብሔርን ቁጣ እና ኃይል ይፈራ ዘንድ ለታላቅ ምህረቱም እጅግ የላቀ ምስጋና እንዲያቀርብ ሰዎች ይህንን መማር እንዳለባቸው እናምናለን (ኢሳ 43:4) ። በምስጋናው ብዙዎች እንዲንቀጠቀጡ በዚህች እለት ይሁን!

## የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አስቀድሞ መወሰኑን ታምናላችሁ? እርሱ ካልወሰናቸው ነገሮች ለምን ይሆናሉ? እነዚህን ጥያቄዎች በሚቀጥሉት ሀሳቦች ውስጥ ለማጠቃለል እንሞክራለን።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ላይ አስቀድሞ መወሰኑን ያስተምረናል። ይህንንም የሚያደርገው ስለ እግዚአብሔር *ድንጋጌዎች* በመናገር ነው።

የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች የምንላቸው እርሱ በፍጥረት ላይ፣ በታሪክ ውስጥ እና በድህነታችን የነበረውን፣ ሊሆን ያለውን እና የሚሆነውን ሁሉ አስቀድሞ በሉዓላዊነቱ ከዘላለም ያስቀመጣቸው ውሳኔዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተሉት ሀሳቦች ውስጥ ስለ እነዚህ ድንጋጌዎች ይነግረናል።

***ምክሩ*** (መዝ. 73:24, ኤፌ 1:11) ውሳኔዎቹ ሁሉ የሥላሴ ሦስቱ አካላት አላማ እና ፈቃድ መሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል።

***አላማው*** (ኢሳ, 14:24-27, ኤፌ 1:11) እነዚህ ድንጋጌዎች ሰውን የሚያስገድዱ ሳይሆኑ የእግዚአብሔርን ክብር ዋና አላማቸው የሚያደርጉ መሆናቸውን ያመለክታል ።

***መልካም ሀሳቡ*** (ኢሳ44:28, ሉቃስ 12:32) የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች በማንም ሆነ በምንም፣ በሰዎች ሆነ በፍጥረታት ድርጊት ላይ እንደማይደገፉ አጽንዖት ይሰጣል። የእርሱ ድንጋጌዎች ነጻ እና በእራሳቸው የሚቆሙ ናቸው ። የሚደነግገው ሁሉ እርሱን ደስ ስለሚያሰኘው ይደነግገዋል።

***ፈቃዱ*** (ሮሜ 1:10, ኤፌ 1:5) ድንጋጌዎቹ ሁሉ ተራ ዕጣ ፈንታ ሳይሆኑ የህያው አምላክ ልብ እና ሀሳብ መፈጸሚያ መሆናቸውን ያሳየናል።

***የእርሱ ውሳኔ*** (ኢሳ 19:17, ሉቃስ 22:22) ድንጋጌዎቹ እና ህግጋቱ የጸኑ እና የማይቀየሩ እንደማይቀየሩ የሚናገረው እውነት ላይ አጽንዖት ይስጣል።

***የእርሱ ድንጋጌ*** (መዝ 2:7)እርሱ ታላቅ ንጉስ፣ ሉዓላዊ ፈጣሪ እና የሰማይ እና የምድር ጌታ እንደሆነ እና ሁሉን እንደሚወስን ያስታውሰናል።

የእግዚአብሔርን ድንጋጌ ለማሳየት የተጠቀምናቸው ጥቅሶች ድንጋጌዎቹ አስፈላጊ መሆናቸውን ያሳዩናል። በዚህ ክፉ እና የተረበሸ አለም ውስጥ ተስፋ ወይንም ሰላም እንዲኖረን ከፈለግን እነዚህን ድንጋጌዎች ማወቅ እጅግ አስፈላጊነው።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ሁሉን ነገር እንደወሰነ እና እንዳዘጋጀ ማመን የትኛውም ሰው ሊኖረው ከሚችለው መጽናኛ ሁሉ በላይ አጽናኝ ነው። ምክኒያቱም በዚህ እውቀት በኩል ነገሮች ሁሉ በተራ እድል እና ዕጣ ፈንታ የሚፈጠሩ ሳይሆኑ ሁሉን ነገር በሚያውቀው እና በጠቢቡ የተወሰኑ ውሳኔዎች እንደሆኑ ስለምንረዳ ነው። ስለዚህም በህይወታችን እና በታሪክ ውስጥ የሚፈጠረውን የሚወስን ሌላ ሀይል - ክፉ ሀይል - አለ ብለን መደምደም የለብንም። ብንደመድምም ይህ ሀሳብ ያለ ተስፋ ሆነ ሰላም የተወናልና።

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በመወሰኑ እንዲያርፍ ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር ጠቢብ እና መልካም መሆኑን ማመን እናም ደግሞ የእግዚአብሔርን ምህረት እና ጸጋም መቀበል አለበት። ይህም ሊሆን የሚችለው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ብቻ ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ኃይል እና ጥበብ ነው (1ኛ ቆሮ. 1:24) ። እግዚአብሔርን በእርሱ በኩል ስናውቅ መልካምነቱን አረጋገጥን ማለት ነው።

## የእግዚአብሔር ሁሉን አቀፍ (አጠቃላይ) ድንጋጌዎች

መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ስለ እግዚአብሔር ድንጋጌዎች እነርሱም - በፍጥረት፣ በታሪክ እና በድህነት ላይ ባለው፣ በነበረው እና በሚመጣዉ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እና ዘላለማዊ ውሳኔዎች ይናገራል።

ሆኖም ግን እነዚህ ድንጋጌዎች አስቀድመው *ሁሉን ነገር* ወስነዋል?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሁሉን ነገር መወሰኑን ይነገረናል

እርሱ የሚከተሉትን ደንግጓል።

- ምድር እና መሰረቱን (ምሳሌ 8:29) ።
- ባህርና ወሰኑን (ኢዮብ 38:8-11) ።
- ዝናብን (ኢዮብ 28:26) ።
- ፀሀይ፣ ጨረቃን እና ክዋክብትን (መዝ. 148:3-6) ።
- የታርክን ጊዜ እና ዘመናት (ኢሳ 46:9-10) ።
- የአንድ ሀገርን አካላዊ እና ባህላዊ ወሰን (ሐዋ. 17:26.
- ውልደታችን እና ባህሪያችንን (መዝ 139:15-16) ።

- የህይወት ዘይቤያችንን (ኤር.10:23) ሀሳባችንን እና ንግግራችንን ጭምር ወስኗል (ምሳሌ 16:1) ።
- የሰው ስልጣን እና ኃይል እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች ጭምር (ዘጽ. 9:16) ።
- የሰውን ክፋት (1ጴጥ. 2:28) ክርስቶስን የሰቀሉትን ሰዎችም ክፋት ጭምር (ሐዋ 4:24-28) ።
- የሀሰተኛው ክርስቶስ መንግስት መምጣት (ራዕይ 17:17) ።
- የክፉ ሰዎች ስለመጥፋት (ማቲ 26:24-25, ሮሜ 9:22) ።
- የወደቁ መላዕክት ፍርድ (ይሁዳ 6) ።
- የነገሮች ሁሉ ፍጻሜ (ኢሳ 46:10) ።
- የክርስቶስ መወለድ (መዝ 2:7-8) ፣ ህይወት (ሉቃስ 22:22)፣ እና ሞት(ራዕይ 13:8)።
- ከድህነት ጋር የተያያዙትን መጠራት (ሮሜ 8:28) ፣ ያመኑት ሰዎች እምነት (ሐዋ 13:48) መጽደቃቸው (ሮሜ 8:30)፣ መመረጣቸው (እንደ ልጅ መወሰዳቸው) (ኢፌ 1:5)፣ ጽድቅ እና መልካም ስራ (ኢፌ 1:3-4, ኢፌ 2:10) እና የክብሩ ወራሽነት (ኤፌ 1:11) ።
- በሰማይ፣ በምድር፣ በገሀነምም ያለውን ሁሉ (መዝ 135:6-12)።

አማኝ ይህንን ለመቀበል ሊቸገር አይገባም። ለሌሎች በብዙ መንገድ ቢተረጎምም ለአማኝ ግን የሁሉ ተቆጥጣሪ *እግዚአብሔር* እንጂ ክፉ ሰው፣ ወይንም ሰይጣን እንዳልሆነ ይረዳል።

ይህም ማለት የትኛውም ነገር እንዲሁ አይከሰትም። በተለይ በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ በሰማዩ አባታችን ያልተወሰነ ነገር በጭራሽ አይሆንም። ስለዚህም ሁሉ ነገር እግዚአብሔርን ለሚወዱት አንድላይ ለበጎ ይሆንላቸዋል ምክኒያቱ አባታቸው ሁሉ እንዲፈጸም በመወሰኑ ነው።

እግዚአብሔር በነገሮች ሁሉ ላይ ያለው ሉዓላዊ ውሰኔን መርሳት “ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና” የመሆኑ ምክንያት ነው (ሉቃስ 21፡26) ። ያለ ሉዓላዊ እና ሁሉን ወሳኝ አምላክ ተስፋ ቢሶች ናቸውና (ኤፌ 2:12)።

ስለዚህም “አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው፤ በሰማይም በምድርም የፈቀደውን ሁሉ አደረገ” በማለት ለዓለም እንመስክር (መዝ 115:3) ።

## የእግዚአብሔር አጥጋቢ ድንጋጌዎች

የእግዚአብሔር ውሳኔዎች በወረቀት ተጽፈው፤ የመቀነት ማህረብ ውስጥ በመንግስተ ሰማይ ተሸጉጠው የተቀመጡ ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ኃያል ፈቃድ ናቸው። ፈቃዱ እርሱ ከጊዜ ወደ ግዜ ወሳኔውን እና ያቀደውን እየተመለከተ የሚያስታውሰው አይደለም ነገር ግን ውሳኔዎቹ የማይለወጠው አእምሮው ሀሳብ ናቸው። ይህም ደግሞ የነገሮች ሁሉ ጅማሬ እና ምክንያት ነው።

እግዚአብሔር አንድን ነገር ሲፈቀድ (ያልፈቀደው አንዳች የለም) በፈቃዱ ያደርገው ነገር መፈጸም አለበት ደግሞም የእርሱ ፈቃድ በመሆኑም ይፈጸማል። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ በጣም በግልጽ ነው። በኢሳይያስ 46:9-10 እግዚአብሔር “እኔ አምላክ ነኝና፥ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም። በመጀመሪያ መጨረሻውን፥ ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ፤ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ” ይላል። በመዝሙር 73:23-28 ላይ ደግሞ አሳፍ በእግዚአብሔር ምክር እንደተመራ ይናገራል። የተመራው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አስቀድሞ ስላወቀው ሳይሆን የእግዚአብሔር ምክር ቀድሞ ህይወቱን እና በህይወቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉ አስቀድሞ ስለወሰነ ነው።

ሐዋ. 2:23 ይህንን እውነት መልሶ ከክርስቶስ ሞት ጋር በማያያዝ አጽንዖት ሲሰጥበት እንመለከታለን። “በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ” ወደ ጠላቶቹ የክፋት እጆች ታልፎ እንደተሰጠ ይናገራል። ለክርስቶስ ሞት እውነት የነበረው ለእኛም የዘላለምን ህይወትን ለማግኘት የሚሰራ እውነት ነው። ይህን የምናገኘውም “እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን” (ኤፌ 1:11)።

ስለዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አንዳንዶች መለወጥ እንደሚችሉ ቢያስቡም ማንም ፈቃዱን ሊቀይር ወይንም ሊለውጥ አይችልም። አንዳንዶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት ማስቀየር ፣በተደጋጋሚ በመጸለይ ወይንም በቂ ሰዎችን አሰባስበ በመጸለይ መለወጥ የሚችሉ ይመስላቸው። ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔርን መንፈሳዊ በሚመስሉ ማታለሎች ፈቃዳቸውን ማስፈጸም እንደሚችሉ ያስባሉ ነገር ግን ይህ ልክ አይደለም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉን ቻይ እና የማይለወጥ ነው።

ስለዚህም ነገር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይመሰክራል። በዳንኤል 4:35 ላይ ናቡከደነጾር (እግዚአብሔርን ማይፈራ ንጉስ) እግዚአብሔርን ማንም “ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?” በማለት ሊጠይቀው

እንደማይችል እንዲቀበል ሲማር እንመለከታለን። በሮሜ 9:19-20 ላይ ደግሞ ፈቃዱንም ማንም መቃወም እንደማይችል ይናገራል።

እግዚአብሄር በሚያስቡት እና ፍቃድ ባላቸው ፍጥረታት በሰው እና በመለዓክት ላይም ሳይቀር ሉዓላዊ ነው። ምሳሌ 16፡9 ላይ እኛ እንደምናቅድ እግዚአብሄር ደግሞ እርምጃችንን እንደሚመራ ይናናገራል። ቁጥር 1 ላይ የልብ መዘጋጀት እና የምላስ መልስ ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደሆነም እንረዳለን።ከዚህም ባለፈ የንጉስ ልብ በእጁ እንደሆነ እና ወደ ራሱ ፈቃድ ያዘነብላቸዋል (ምሳ 21:1)።

የእግዚአብሔር ውሳኔዎች በሀይል የተሞሉ እና የማይለወጡ በመሆናቸው ለሚያምኑቱ ታላቅ እረፍት ነው። ከምንም ማንም በላይ መዳናቸው እርግጥ የሆነበት ምክንያት ይህ ነው። የሰዎች ፈቃድ ይቀየራል ፤ ሃሳባቸውም ይወድቃል፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እና ሃሳብ ግን የማይለወጥ ነው። ለዚህም ነው ነገሮች ሁሉ ተያይዘው ለአማኞች ለመልካም የሚሆኑት (ሮሜ 8:28) ። እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ እና በአይለወጤነቱ ሁሉንም ነገሮች ወስኗቸዋል። ድነታቸውን ስለወሰነ ሞት ቢሆን ፥ ህይወት ቢሆን ፥ መላእክትም ቢሆን ፥ ግዛትም ቢሆን ፥ያለውም ቢሆን ፥ የሚመጣውም ቢሆን ፥ ሃይላትም ቢሆን ፈቃዱን ሊደናቀፍ ሆነ ሊከሽፍ አይችልም  (ሮሜ 8 ፡ 30-39)። ሁሉም ነገር ከእርሱ፣ በእርሱ እና ለእርሱ ነው ። ምን አይነት ታላቅ እና አዳኝ የሆነ አምላክ ነው።

## የእግዚአብሔር ቅድመ ሁኔታ የለሽ ፈቃድ

የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች በተለይም አስቀድሞ መወሰን፣ መመረጥ እና አለመመረጥ ፥ ቅድመ ሁኔታ የለሽ ድንጋጌዎች ናቸው። አዎን፤ ከአምስቱ የካልቪኒዝም ነጥቦች ውስጥ ሁለተኛው ያለቅድመ ሁኔታ መመረጥን ያመላክተናል።

ይህ ማለት ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት እግዚአብሔር ለውሳኔው ሌሎች ፍጥረታት ላይ እንደማይደገፍ፤ የሰው ፈቃድ ሳይሆን የእርሱ ፈቃድ የበላይ እንደሆነ ያመለክተናል። የእግዚአብሔር ድንጋጌ ፈቃዱ ነው። የእርሱ ፈቃድ ደግሞ በነገሮች ሁሉ ላይ ያለው ውሳኔ ነው። የእግዚአብሔር ድንጋጌ ቅድም ሁኔታ የለውም። ማለትም የእርሱ ፈቃድ ከሰዎች እና ከመላዕክት ፈቃድ በላይ ሲሆን ሰው ከፈቃዱ ጋር እስኪስማማ አይጠብቅም።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ቅድመ ሁኔታ የለውም ማለት በሰዎች ፈቃድ ጣልቃ ስለማይገባ ሰዎች ውሳኔያቸውን እስኪወስኑ አይጠብቅም። በአጭሩ ስናስቀምጠው የሰው ውሳኔ የእግዚአብሔር ውሳኔ ምክንያት ሳይሆን በተቃራኒው የእግዚአብሔር ውሳኔ ለሰው ውሳኔ ምክኒያት ነው። እንዲህ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ሉዓላዊ ይሆን ነበር።  የሰው ፈቃድ እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ የበላይ አይሆንም ነበር።

በሰው ነጻ ፈቃድ በሚያምኑ የእግዚአብሔርን ያለቅድመ ሁኔታ ድንጋጌ (ውሳኔ) ይክዳሉ። ድህነት የሰው ፈቃድ እንጂ የእግዚአብሔር አይደለም ብለው ይከራከራሉ ይሄም እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። የሰው ልጅ ክርስቶስን እና ወንጌልን ለመቀበል እስከሚወስን ድረስ እግዚአብሔር ምንም ማድረግ አይችልም ደግሞም አያደርግም ብለው ይናገራሉ። ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትን በግልጽ መካድ ነው። በየትኛውም መንገድ ከሉዓላዊነቱ አስተምህሮ ጋርም ሊሄድ አይችልም። ይህም ህያው እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ የሚደገፍ ያደርገዋል።

ታድያ መመረጥ ከሰዎች ፈቃድ ተነስቶ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነው ማለት ነው። ይህ የሀሰት አስተምህሮ እግዚአብሔር እርሱን አስቀድመው የመረጡትን ይመርጣል ብሎ ያስተምራል ፤ ደግሞም እርሱን የሚወዱትን ይወዳል ብሎ ያስተምራል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ “እርሱ ቀድሞ ሰለወደደን እኛ እንወደዋለን” የሚለውን አስተምህሮ መካድ ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ እና ቅድመ ሁኔታ የለሽ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫን ይቃወማል። በእንደዚህ አይነት አስተምህሮ እግዚአብሔርን እንደፈጣሪዎቻቸው ለሰዎች ስራ ምላሽ ከሚሰጡ ከአህዛብ አማልክት በጥቂት ብቻ ይለየዋል።

ሌሎች ደግሞ መመረጥ ዘላለማዊ መሆኑን ተረድተው በእግዚአብሔር አስቀድሞ እውቀት ላይ ትኩረት በማድረግ እግዚአብሔር ከጊዜ ቀድሞ በመሄድ አስቀድሞ ማን እንደሚያምን በማወቅ እና በማየት ስለስራቸው መረጣቸው ይላሉ። እንደዚህ አይነት ምርጫም እግዚአብሔርን በሰው ላይ እንዲደገፍ እና ከትንቢት በጥቂቱ የሚለይ ያደርገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ውሳኔዎች ቅደም ሁኔታ የለሽ መሆናቸውን ይነገረናል። ሮሜ 9:15-16 እግዚአብሔር ለፈቀደለት ብቻ ምህረት እንደሚያደርግ እንጂ ምህረቱን ለተቀበለው እንዳልሆነ ይናገራል። ስለዚህም ድህነት “ለወደደ (ለመረጠ) ወይም ለሮጠ (ለሰራ ፣ ለተጋ) አይደለም።” ኤፌሶን 1:5 እግዚአብሔር ከራሱ በጎ ፍቃድ የተነሳ ህዝቡን እንደሚመርጥ ያስተምረናል። በግልጽ አማርኛ እርሱ ስለፈለጋቸው እንጂ እነርሱ ስለፈለጉት አይደለም።

የእግዚአብሔር ውሳኔ ቅድመ ሁኔታ የለሽ እና በእኛ ድካም ወይም ተቀያያሪ ፈቃድ ላይ የተደገፈ እንዳልሆነ ስናውቅ እንዴት እግዚአብሔርን እናመሰግናለን!

## የእግዚአብሔር ጠቢብ ድንጋጌዎች

እግዚአብሔር ጠቢብ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቢያስተምርም ህዝቡ አብዛኛውን ጊዜ ፤ በተለይም በፈተና ሲያልፍ እና ነገሮች እንደእቅዱ ሳይሄድለት ሲቀር ይህንን እውነት ይረሳል ። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ጥበብ ለማየት ለሰው ይከብደዋል ሆኖም ግን ይህ ሰው በዚህ ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔርን ጠቢብ ድንጋጌ ባይረዳውም ሊያምነው ይገባል።

እግዚአብሔር በጥበቡ ሁሉን ነገር ወስኗል። ለዚህም ነው ነገር ሁሉ ለበጎ የሚሆነው። እንዲሁ የሚሆን ወይንም በራሱ ከሌሎች ሁኔታዎች ተነጥሎ የሚሆን ነገር የለም። ነገር ግን አብሮ እንደሚሰራ እና በስርዓት እንደሚገጣጠም ዘይት እንደተቀባ ጥሩ ማሽን ሁሉም ነገር አንድ ላይ ይስራል። ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር ጠቢብ በመሆኑ ነው። እርሱ ነገሮች ሁሉ ተጠቅልለው በፍጹም አንድነት ለራሱ ፈቃድ እንዴት ማድረግ እንዳለበት ያውቃል። ሁሉም ነገር ተጠቅልሎ የእግዚአብሔርን ክብር እና ታላቅነት ሊሆን ይገባዋል። ይህም ደግሞ የእርሱ ታላቅ አላማ ነው።

የእኛ ድህነትም በእርሱ ፈቃድ ውስጥ ተጠቃልሏል፤ ጸጋው በድህነት በኩል ለህዝቡ መገለጡ ታላቅ ክብር እና ሞገስ ወደ እርሱ ያመጣል እንደዚህም ታላቅ ክብር እና ሞገስ የሚያመጣ ብዙ ነገር የለም። ስለዚህም በእግዚአብሔር ጥበብ ውስጥ እርሱን ለውሚወዱት እና እንደሀሳቡ ለተጠሩት ነገር ሁሉ ተጠቀልሎ (ተያይዞ) ለበጎ ይሆንላቸዋል (ሮሜ 8:28) ።

ይህን በመከራችን እና በችግራችንም ጊዜ ልናምነው ይገባል። በነገሮች መካከል ሁሉ የማንረዳው አላማ እንዳለ መመልከት ብቻ ሳይሆን ይህ አላማ መልካም እና ጥበብ ያለበት እንደሆነ ማመን አለብን።

ይህንን ካመንን በሚሆነው ነገር ሁሉ አናጉረመርምም፣ አንፈራም፣ አንረበሽም ወይም አንሰናከልም። አምላካችን ጠቢብ ስለሆነ ለድህነታችንም ሆነ ለእኛ የሚሻለንንም እኛ ከምናውቀውም እጅግ አስበልጦ ያወቅልናል። በእውነትም በእምነታችን የእግዚአብሔርን ጥበብ ብናውቅ በእኛ ላይ ስለሚሆነው ነገር፣

መከራም ቢሆን በስተመጨረሻ እናመሰግናለን ። በለቅሶ ሸለቆ ውስጥ - ደረቅ እና የበረሃ ሸለቆ - በሆነው በታ የህይወት ወሃ እና ምንጭ እናገኛለን (መዝ 84:6)።

የመዝሙር 131 ቅኔ እንደሚገልጠው - የእግዚአብሔር ጥበብ ሰላም ያስተምራል

ልቤ አይተብትም

ክብሬም ከፍ ከፍ አይልም

የአምላክ ጥበብ ያልፈቀደውን

ላውቅ እኔ አልሻም

እንደ ልጅ እምነት ጌታዬ

ባንተ ተረጋግቼ አርፋለሁ

የእናት ጡት ለልጅ እንዲበቃው

ፈቃድህ እንዲሁ ይበቃል

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ

በእርሱ ብቻ ተሸሸፍ

ከጅማሬው ጀመሮ

ጥበቡ ብቻ ይምራህ[13]

## የእግዚአብሔር ፈቃድ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች *ፈቃዱ* ተብለው ሲገለጹ እናያለን። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙት እና በመንግስተ ሰማይ የሆነ ስፍራ ውስጥ የተቀመጠ ጥቅልል ሳይሆን የእግዚአብሔር ጥልቅ *ሀሳብ* እንደሆነ ይናገራል። ስለ ድንጋጌዎቹ ስናወራ ስለ *ቿራሱ* እያወራን ነው።

የእግዚአብሔር ፈቃድ የእርሱን ባህሪ የተላበሰ በመሆኑ ይህ እጅግ አስፈላጊ ነው። የእርሱ ፈቃድ ልክ እንደ እርሱ ዘላለማዊ፣ የማይለወጥ፣ ፍጹም እና ብቻውን ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲድን ፈቅዷል ወይንም ይፈልጋል በማለት  ድህነታቸው በፈቃዳቸው የተመሰረተ ነው ብለው የሚያስተምሩ በመኖራቸው ይህ አትኩሮት ሊሰጠው ያስፈልጋል ። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ሀሳብ ሉዓላዊ አይደለም ማለት ነው።

ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔር ሁለት ፈቃድ አለው ብለው ያስተምራሉ። የመጀመሪያው ዘላለማዊ ፣ የማይቀየር እና ሉዓላዊ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመጀመሪያውን ፈቃድ በመቃረን የሚለወጥ ፣ ሊቀየር የሚችል እና ቋሚ ያለሆነ ፈቃድ ነው ይላሉ። እግዚአብሔር አንዳንዶችን በክርስቶስ በኩል ለድህነት ጠርቷል ስለዚህም መዳናቸውን ፈቅዷል፤ ደግሞም እግዚአብሔር በስብከተ ወንጌሉ ውስጥ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ምኞቱን ስለግለጠ የሰዎችን ሁሉ መዳን ፈቅዷል ብለው ያምናሉ።

በዚህ አስተምህሮ መሰረት፣ እግዚአብሔር ለሁሉም መዳንን ይፈቅዳል (በወንጌል ውስጥ) ነገር ግን (በአስቀድሞ መወሰን) ለአንዳንዶች መዳንን አልፈቀደም ይላሉ። በዚህም በወንጌል አማካኝነት የወሰነው ፈቃድ ለአሁን እንጂ ለዘላለም የማይዘልቅ፣ አላማውንም የማይፈጽም ነው ማለት ነው።

ይህ አስተምህሮ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማለትም እግዚአብሔር ያልተሟላ፣ ያልተፈጸመ ፣ የሚለወጥ ፣ ሊሻር የሚችል (ሉዓላዊ ያልሆነ) እና ቋሚ ያልሆነ እንደሆነ በማስተማሩ እንቃወመዋለን። አስተምህሮው በእግዚአብሔር ውስጥ ተቃርኖ (ኢ-ፍጹማዊነት) አለ ይለናል። ከዚህም ባለፈ አንድ ሳይሆን ሁለት ሀሳብ ስላለው ሁለት አምላክ ነው የሚልን ምልከታ ይሰጣል ። ይህ ሁሉ እግዚአብሔር የእውነት እግዚአብሔር መሆኑን ይቃወማል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ ፈቃድ እንዳለው እና የሚፈቅደውን ሁሉ እንደሚያደርግ ያስተምረናል። መዝሙር 115:3 እና መዝሙር 135:5-6 ከጣዖት አምልኮ ጋር አያይዞ በአጽኖት ይህንን ሀሳብ ያነሳዋል። እግዚአብሔር ፈቃዱን ሁሉ አያደርግም (ፈቃዱ ሳይፈጸም እና ሳይሟላ ሊቀር ይችላል) ማለት እርሱ እግዚአብሔር አይደለም ማለት እና በአምልኮተ ጣዖት ሀጥያት ውስጥ መዘፈቅ ነው። የመዝሙር ክፍሉ የሚያስተምረን ይህንኑ ነው።

ምንድነው የምታምነው? እግዚአብሔር በሰዎች እና በድህነታቸው ላይ ሁለት ሀሳብ አለው የሚለውን ሃሳብ ትቀበላለህ? ፈቃዱ ከአንተ ሊበልጥ አይችልም ብለህ ወይንም ደግሞ ፈቃዱ ሊፈርስ ይቻላል በማለት በድፍረት መናገር ትችላለህ?

"በሰማያት ያለው አባታችን የፈቀደውን ሁሉ አደረገ" ማለታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ምቾት የሚሰጥ እምነት አይደለምን? እርሱ እግዚአብሔር ነውና።

## የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ፈቃድ እና የድንጋጌው ፈቃድ

እግዚአብሔር በድህነት ዙሪያ አንዲት ፈቃድ ብቻ አለው የሚለውን እውነት አስረድተናል። እርሱ የሰዎችን ድህነት (በወንጌል ውስጥ) ፈቅዷል (በአስቀድሞ መወሰን) ውስጥ አልፈቀደም ማለት አይቻልም።

ነገር ግን ስለእግዚአብሔር ፈቃድ ስናወራ ግልጽ የሆነ ልዩነት ልናስቀምት ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ፈቃድ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ስለእግዚአብሔር ድንጋጌ ብቻ ለማውራት ሳይሆን ስለ ትዕዛዛቱም ለመናገር ጭምር ነው። ሌላ ገጽታ ቢሆንም የእርሱ ትዕዛዛት ለህይወታችን ያለው ፈቃዱ ነው ።

እግዚአብሔር በሉዓላዊ ፈቃዱ አንዳንድ ጉዳዮችን ለህይወታችን *ወስኗል*። በህጉ በኩል ደግሞ አንዳንድ ነገሮችን ፈቅዷል ግን ይህ ፈቃድ በ*ትዕዛዝ* መልክ ነው ምክኒያቱም እርሱ ስለሚያዝዘን። ኢፌሶን 1:5 ስለ እግዚአብሔር የውሳኔ ፈቃድ ሲናገር ማቴዎስ 7:21 ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ትዕዛዛት ፈቃድ ይናገራል። ውሳኔዎች እርሱ ሊያደርግ ያሰበውን ሁሉ ይገልጻሉ ትዕዛዞቹ ደግሞ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ይገልጻሉ። የእርሱ የወሳኔ ፈቃድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሊያደርገው ያሰበውን ሲገልጥ የእርሱ የትዕዛዙ ፈቃድ ደግሞ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ያስረዳል። የፈቃዱ ትዕዛዛት ደግሞ የሰው ልጅ ሊያደርገው እና ሊሆነው የተገባውን ይገልጥልናል።

ይህንን ልዩነት እግዚአብሔር ሁለት የተለያዩ ፈቃዶች እንዳሉት ለማሰርዳት ብዙ ጊዜ ሰው ይጠቀምበታል። ይህም ሰዎች የጌታችን የኢየሱስ ክርቶስን አዳኝነት በወንጌሉ እንዲሰማ አዟል (ፈቅዷል) እና አንዳንዶች ወንጌሉን ሰምተው እንዳይድኑ ውስኗል (ፈቅዷል) ይላሉ። ትዕዛዝ እና ውሳኔ የተለያዩ ነገሮች በመሆናቸው ፈቃድ የሚለው ቃል በሁለቱም ቦታ ቢገባም እንኳን ይህ ምልከታ በቃላት ጨዋታ ላይ ተመስርቷል ብለን እናምናለን። ስለውሳኔ ስንነጋገር ፈቃድ የሚለው እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነውን ያመለክተናል። ሰለ

ትዕዛዙ ስንነጋገር ደግሞ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እና እርሱን የሚያስደስተውን ነገር ያመለክታል። እነዚህ ሁለት ነገሮች አንድ አይደሉም ፤በመካከላቸውም ምንም አይነት ተቃርኖ የለም። እግዚአብሔር የሚያዝዘውን አልወሰነም አሁንም ግን በመካከላቸው አሁንም ምንም ተቃርኖ የለም። ለምን? ምክኒያቱም ትዕዛዛቱ ባዶ ንግግር ሳይሆኑ  እግዚአብሔር ውሳኔውን ለመፈጸም የሚጠቀምባቸው መንገድ ናቸውና።

በግልጽ ለማስቀመጥ እግዚአብሔር አንድን ሰው እንዲያምን ሲያዝዘው፤ ይህ ትዕዛዝ ሊገፋ ወደ ማይችለው የሚያድን እምነት ወደ ክርስቶስ ይወስደዋል (ዩሀንስ 6:44) ወይንም ልቡን በማደንደን ወደ አለማመን ይወስደዋል (ሮሜ 9:18, 2ኛ ቆሮ 2:15-16)። በዚህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ይከናወናል። በመካከላቸው ምንም መቃረን የለም።

በተግባር ስንመለከታቸው ምንም ተቃርኖ የላቸውም። በወንጌል መነጽር የተመለከትነው እንደሆነ ደግሞ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው አንድ ጉዳይ እምነት መሆኑን እንመለከታለን። ልናምን ግድ ይለናል አልያም እንጠፋለን። የውሰነው ፈቃድ የጽድቅ ገዴታችንን ለመፈጸም የምንጠቀምበት ስላልሆነ በጽድቅ ለመኖር አንጠቀምበትም ምክኒያቱም የምንኖረው በትዕዛዛቱ እንጂ በውሳኔዎቹ ስላልሆነ።

ስለዚህም እረፍት እና ማረጋገጫ ስንሻ ወደ እግዚአብሔር ውሳኔዎች እንመለከታለን። እንግዲህ እምነት እና መታዘዝ የእግዚአብሔር የመመረጥ ውሳኔ መሆናቸውን እና እምነት፣ ንሰሀ፣ እና ቅድስና የመመረጣችን ማስረጃዎች እንደሆኑ እናስተውል።

## ክፍል ፩ - ማጣቀሻ


1. Belgic Confession of Faith, Article 2.
2. Ibid
3. Belgic Confession, Article 7.
4. The Confessions of St. Augustine, trans. E. B. Pusey, ed. and condensed David Otis Fullerfrom Book X (Grand Rapids,MI: Zondervan Publishing House Christian Life Library Selection series), 122.
5. Location of quotation in Charles Haddon Spurgeon’s writings is not known.

6. From the section“Translation Necessary,”originally in the preface to the King James (Authorized)Version of the Bible, 1611.Quoted here from the bookletwith modern spelling as “The Translations to the Reader” (London: Trinitarian Bible Society, 1998), 12.
7. Stanza 2 of hymn number 335, “Abide with Me,” in the Trinity Hymnal (Philadelphia: Great Commission Publications, 1974).
8. Arthur W. Pink, The Sovereignty of God (Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1970).
9. Homer C. Hoeksema, “God So Loved the World . . .” This pamphlet is available from its publisher, the Evangelism Committee, Crete Protestant Reformed Church, 1777 E. Richton Rd., Crete, IL 60417, www.prccrete.org.
10. Appendix III, “The Meaning of the ‘Kosmos’ in John 3:16,” in Pink’s Sovereignty of God (Baker Book House edition).
11. Canons of Dordrecht (Dordt), First Head of Doctrine, Articles 15–18. Summed up in the acronym TULIP, the five points of Calvinism are total depravity, unconditional election, limited atonement, irresistible grace, and the perseverance of the saints.
12. Westminster Confession of Faith, Chapter 3, Article 7.
13. Psalter 366, in The Psalter with Doctrinal Standards, Liturgy, Church Order, and Added Chorale Section (Grand Rapids,MI:William B.Eerdmans Publishing Company, 1927; repr. 1998).

**ክፍል ፪**

# ሰው እና የእርሱ አለም

## መላዕክት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንግስተ ሰማይ ከሚናገረው ባነሰ መልኩ ስለመላዕክት ይናገራል። ይህም በስህተት አይደለም ምክኒያቱም ስለ ድህነት ልናውቀው የተገባን ነገር ሁሉ ተነግሮናልና። ሆኖም ግን ጉጉታችንን ብቻ ለማርካት የሚጠቅም ጉዳይ አልተነገረነም። ስለዚህም ስለመላዕክት ሲነሳ በህይወታችን እና በድህነታችን ውስጥ ቦታ እንዳላቸው በመረዳት ተራ መላምቶችን ከመስጠት መጠንቀቅ አለብን።

መላዕክት መናፍስት እንደሆኑ እና መንግስተ ሰማይ ቤታቸው እንደሆነ እናውቃለን። ከመጽሐፍ ቅዱስም ገብራኤል እና ሚካኤል የተባሉትን ሁለት መላዕክቶች ስም እናውቃለን። የተለያዩ መላዕክት አሉ ለምሳሌ ሊቀመላዕክት፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌል . . . ፤*ሊቀመላዕክት* የሚለውም ስም የተለያዩ የመላዕክት ስልጣናት እንዳሉ ያመለክታል (ቆላ. 1:16 ይመ.) ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደገና ልዩ ልዩ መላዕክት ልዩ ልዩ የስራ ድርሻ እንዳላቸው ይገልጥልናል። ሚካኤል ልዑል፣ አለቃ፣ እና ተዋጊ እንደሆነ (ዳን.12:1, ይሁዳ 9, ራዕይ 12:7) ገብርኤልም ሁልጊዜ እንደ መልዕክተኛ ሲቀርብ እንመለከታለን (ሉቃስ 1:19,26) ፣ ሱራፌል ደግሞ እግዚአብሔርን በመገኘቱ ውስጥ የሚያመልኩ ሲሆኑ (ኢሳ 6:104) ፣ ኪሩቤል ደግሞ የእግዚአብሔር ግርማ እና ክብር ጠባቂዎች (ዘፍ 3:24, ዘጽ 25:18-22, ሕዝ. 10:1-20) እንደሆኑ ተጽፈውልናል።

መጽሐፍ ቅዱስም ብዙ መላዕክቶች እንዳሉ ይነግረናል። ዕብራውያን 12:22 ሊቆጠሩ ስለማይችሉ (አእላፍ) መላዕክቶች ይናገራል ሆኖም ግን አንዳንድ መላዕክት ከሰይጣን ጋር አብረው ወድቀዋል (ራዕይ 12:4) ። የአንዳንድ መላዕክት እና የሰዎች ሁሉ መወደቅ እንደ እግዚአብሔር ድንጋጌ እና አለመመረጥ ነው ። ስለተመረጡት መላዕክት ብቻ ሳይሆን (1ኛ ጢሞ.5:21) ለፍርድ ቀን ታስረው ስለ ተቀመጡት መላዕክት ጭምር መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምናገኝበት ምክኒያት ለዚህ ነው (ይሁዳ 6) ። ዕብራውያን 12:22 እንደሚያስተምረው የተመረጡት መላዕክቶች በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር የክብሩ ተካፋይ እንደሚሆኑ ይናገራል። የወደቁት መላዕክቶች ግን ከክፉ ሰዎች ጋር ወደ ገሀነም የሚጣሉ ይሆናል (ይሁዳ 6, ራዕይ 20:10) ።

ከእዚህ ውጪ የምናውቀው እጅግ ጥቂት ቢሆንም የምናውቀው የሚያጽናና ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለመላዕክት የሚናገረው በሙሉ ተጠቅልሎ በዕብራውያን 1:14 “ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው

ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" በሚለው መጠቃልል ይችላል።  እንዴት የሚደንቅ እውነት ነው!

ስለዚህ የመላዕክት ዋና ተግባር የእግዚአብሔርን ህዝቦች የሚያግዙ እና ድህነታቸውን የሚጠብቁላቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው (ዳን 10:13-14, ዳን 12:1, ራዕይ 12:7-10)። መላዕክቶች የመቤዠታችን ታላላቅ ክስተቶች ላይ የተገኙት ለዚሁ ነው። ለምሳሌ የክርስቶስ መወለድ (ሉቃስ 2:9-14) ፣ በበረሃው ሲፈተን (ማቲ 4:11) ፣ በጌተሰማኒ መከራ ሲያያሳልፍ (ሉቃስ 22:43) ፣ በትንሳኤው (ሉቃስ 24:4-7) ፣ ወደሰማይ ሲያርግ (ሕዋ 1:10-11) መጠቀስ ይችላሉ ። ዳግም ህዝቡን ወደ እራሱ ሊወስድ በሚመጣበት በዚያም ቀን ይኖራሉ (2ኛ ተሰ 1:7)።

በእኛ ድህነት እና የመጨረሻ ክብር ላይ የመላዕክቱ ጥልቅ ፍላጎት ምን እንደሆነም በ1ኛ ጴጥ 1:12 ላይ ተገልጾልናል። በዚያ ክፍል ላይ መላዕክት በነቢያቶች ስለክርስቶስ መከራ እና ከዚያ በኃላ የሚመጣውን ክብር ለማየት እንደሚሹ ይናገራል። ስለድህነታችን መጓጓታቸው እንዴት ደስ የሚል ምስክርነት ነው፤ በመላዕክት ማመንም እንዴት የሚያሳርፍ ነገር ነው።

እንደ ኤልሳዕ ባሪያ እነዚህን አገልጋይ መናፍስትን "እንድናይ" እና ፈረሶቻቸውን እና እሳት ሰረገሎቻቸውን በዙሪያችን እንድንመለከት አይናችን ሊከፈት አያስፈልገውም (2ኛ ነገ 6፡17) ። በአይነ ምናባችን ባናያቸውም እግዚአብሔር በቃሉ መኖራቸውን ስለነገረን እንዳሉ እናምናለን።

## **ጋኔኖች**

ስለመላዕክቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ሊመለሱልን ያልቻሉ ጥያቄዎች እንዳሉ ሁሉ ስለ ጋኔኖችም እንደዚሁ ብዙ የማይመለሱልን ጥያቄዎች አሉ ። ሆኖም ልናውቀው የተገባዉ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተሰጥቶናል።

ጋኔኖች የወደቁ መላዕክት እንደሆኑ እናውቃለን። በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ሰይጣን እና ጭፍሮቹ መላዕክት ተብለው ሲጠሩ እንመለከታለንና (2ኛ ቆሮ 11:14, ይሁዳ 6, ራዕይ 12:7-9) ። 2ኛ ጴጥሮስ 2:4 እና ይሁዳ 1፡6 ስለመውደቃቸው እና በሀጥያታቸው "የመጀመሪያ ስፍራቸውን ለቀቁ" በማለት ይነገሩናል። ኢሳይያስ 14:4-23 የሰይጣን ሀጥያት በእግዚአብሔር ላይ የማመጽ እና የኩራት እንደነበር ይናገራል።

በኢሳይያስ ላይ የነበረው ትንቢት ለባቢሎናዊያን ንጉስ የተጻፈ መልዕክት ቢሆንም ስለሰይጣን እንደሚናገር ተደርጎ በብዛት ይወሰዳል። የዚህም ምክኒያት ከባቢሎናዊያን ንጉስ ጀርባ እርሱ ስለነበረ እና በኢሳይያስ 14 ላይ ያለው አብዛኛው ታሪክ ከንጉስ ባቢሎን ይልቅ ስለሰይጣን በመናገሩ ነው። ይህ አረዳዳችን ትክክል ከሆነ ፤ በኢሳይያስ 14 ላይ ሰይጣን ከመውደቁ በፊት የነበረውን ስም “ሉሲፈር፣ የንጋት ኮከብ” መሆኑን ይነግረናል።

ሰይጣን የሰው ልጅ ውድቀት ዋና መሳሪያ ስለነበር የሰይጣን መውደቅ ከሰው መውደቅ በፊት እንደሆነ እናውቃለን (ዩሃንስ 8:44) ። በአብዛኛው ስለሰይጣን እና ስለመላዕክቱ መውደቅ የሚያወራ ክፍል አድርገን በምንረዳው በራዕይ 12:4 ላይ ሌሎች ብዙ መላዕክት አብረውት እንደወደቁ ተገልጧል። ነገር ግን በእርግጠኝነት ከመላዕክት አንድ ሶስተኛው በሙሉ አብሮ ከሰይጣን ጋር መውደቁን ማረጋገጥ እጅግ ከባድ ነው ምክንያቱም በራዕይ መጽሐፍ ላይ የምናገኘው ክፍል በአብዛኛው ምሳሌያዊ መሆኑ ነው።

ሰይጣንም እጅግ ታላቅ ሀይል እንዳለው እናውቃለን። እርሱ የዚህ ምድር *ገዥ* እና አምላክ ተብሎ ተጠርቷል (ዩሀንስ 12:31, 2ኛ ቆሮ. 4:4) ። ሀይሉ እጅግ ታላቅ በመሆኑም በራሳችን አቅም እርሱን ልንቋቋመው አንችልም (ከኤፌ 6:11 ጀምሮ) ። በ1ኛ ጴጥሮስ 5:8 ላይም የሚውጠውን ፈልጎ ከሚዞር አንበሳ ጋር ተነጻጽሯል።

የሰይጣን ሀይል በዋነኝነት የውሸት ፣ የማታለል እና የመፈተን ሀይል ነው (ዩሃንስ 8፡44, ራዕይ 13:14, ማቴ 4:11) ። በዚህ አማካኝነት የዚህን አለም ልጆችን ጠፍሮ በባርነት የሚይዝ (2ኛ ቆሮ 4:4) እና የአማኞች እና የቤተክርስቲያን ታላቁ ጠላት ነው። ስሙም ከዚህ ሀይሉ አንጻር የወጣ ነው፤ *ሰይጣን* “ጠላት” ወይንም “ከሳሽ” ማለት ሲሆን *ዲያቢሎስ* ደግሞ “ስም አጥፊ” ማለት ነው። በውሸቱ እና በስም ማጥፋቱም *አፖልዮን* በመባል ይታወቃል ትርጉሙም “አጥፊ” ማለት ነው (ራዕይ 9:11) ። በዚህ ውሸቱ ቀደምት ወላጆቻችንን ገደሏል (ዩሀንስ 8:44) አሁንም ወንዶችን እና ሴቶች እየገደለ ነው።

ክርስቲያኖች ሰይጣን ኃይል ቢኖረውም በጸጋ ልንቋቋመው እንደምንችል እና ልንቋቋመው እንደሚገባን ማወቅ አለባቸው ያኔም ከእነርሱ ይሸሻል። በያቆብ 4:7ም የክርስቶስ ኢየሱስ መፈተን እርሱን እንዴት መቃወም እንዳለብን መመሪያ ይሰጠናል ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ስናውቅ እና ስናውጅ በጾም እና በጸሎትም ስንተጋ ነው (ቁጥ 8ን ይመ) ።

ሰይጣን ታላቅ ኃይል ቢኖረውም በእግዚአብሔር ሉዓላዊ መሪነት እና አለቅነት ስር መሆኑን (ማት 12:29, ራዕይ 20:2) እና ከሌሎች የግፍ ሰራተኞች ጋር ወደ ዘላለማዊ የገሀነም እሳት እንደሚጣል ልናውቅ ይገባል (ራዕይ 20:20) ። ሉተር እንደጻፈው ዝማሬ "ታላቁ መጠጊያችን እግዚአብሔር ነው፣" "ለጨለማው ልዑል አጥፊ ለእርሱ አንቀጠቀቀጥም።"[1] እንላለን

የእግዚአብሔርን የጥሩር ልብስ ለብሰን ፈጥነን የእሳት ቀስቶቻቸውን እንድዋጋ ስለዳቢሎስ ልናውቀው የተገባን ሁሉ ተሰጥቶናል። ስለዚህ ይህንን እናድርግ ደግሞም አንፍራ።

## ፍጥረት በስድስት ቀናቶች

የዚህ ዘመን ብዙሃን በዘፍጥረት 1-3 የተጠቀሰውን የፍጥረት ታሪክ አይቀበሉም ይህም የሚያስገርም ጉዳይ አይደለም። አንዳንድ ክርስቲያኖች በዘፍጥረት 1-3 እንመን አልያም ደግሞ በዝግመታዊ ለውጥ እንመን ጉዳዩ ለውጥ አምጪ ክርክር እንዳልሆነ ማሰባቸው አስደናቂ ነው። እኛ ግን ስለፍጥረት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያወራውን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ትክክል እና የተፈጸመ ታሪክ ነው ብለን ማመናችን እጅግ ቁልፍ ነው ብለን እናምናለን። መጽሐፍ ቅዱስም ይህ ለምን እንደሆነ ይነግረናል።

በመጀመሪያ ዘፍጥረት 1-3ን ስንክድ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አልተቀበልንም ማለት ነው። 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ "መጽሐፍት ሁሉ በእግዚአብሔር አነሳሽነት ተጽፈዋል" የሚለውን ቃል እየካድን ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ክፍሎችንም እየካድን ነው። ይህንን በማድረጋችን ደግሞ እግዚአብሔርን እና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ውሸታም እያደረግን ነው ማለት ነው። ይህንን አስተውስ። በአራተኛው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ "ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው ፤ ........ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታል" ይህ ተቀምጦልናል (ዘጸ. 20:9-11) ። ታዲያ እግዚአብሔር ስለሚናገረው ነገር አያውቅም ነበር ማለት ነው?

ሰው በዝግመታዊ ለውጥ እንደመጣ ካመንክ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 19:4-5 ላይ “ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን (ዘፍ. 1:27ን እና ዘፍ. 2:24ን)?”

ማለቱን አስታውስ ። ኢየሱስ በእርግጠኝነት የመጀመሪያዎቹ ሁለት የዘፍጥረት ምዕራፎች ትክክል እንደሆኑ ያምን ነበር። ታዲያ እኛስ ማመን የለብንም?

የሰው ልጅ በዝግመታዊ ለውጥ እንደመጣ ካመንክ እና የእውነት አዳም የሚባል ሰው የለም ሚለውን ከተቀበልቅ በሮሜ 5 ላይ ስለመጀመሪያው ሀጥያት የተጻፈልንን እርሱም በመጀመሪያው ሰው በአዳም በኩል ሀጥያት እና ሞት ወደ ምድር ወደ ሰው ዘር በሙሉ ገብቷል የሚለውን እውነት አታምንም ማለት ነው። ዘፍጥረት 1-3 ላይ ያሉትን እውነታዎች መካድ ማለት ስለ ሀጥያት እና ስለ ሞት ምክንያት ወይንም ማብራሪያ የምናደርገው ሰው የለም ማለት ነው። ከዚህም በበለጠ የመጀመሪያው አዳም እንደሌለ ካመንን ክርስቶስ የመጨረሻው አዳም መሆኑን እና ድነት በእርሱ በኩል መምጣቱን በምን እንቀበላለን? (1ኛ ቆሮ 15:45, 47) ።

የዘፍጥረትን የፍጥረት ታሪክን ሳይቀበሉ በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት ማመን የማይቻል ነገር ነው። ክርስቶስ የመጨረሻው አዳም ስለሆነ ብቻ ሳይሆን የፍጥረት መውደቅ የእርሱ መምጣት ምክንያት በመሆኑ ነው። የመጀመሪያው አዳም የለም ማለት የሀጥያት ውድቀት የለም ማለት ነው። ስለዚህም ከአዳም የመጣ የመጀመሪያ ሀጥያት የለም ማለት ነው። ደግሞም ክርስቶስ አያስፈልግም ማለት ነው። በእርግጠኝነት እርሱ የመጣው በተራ አሟሟት ለመሞት እና በሰዎች ዝግመታዊ ለውጥ ውስጥ የተበላሸውን ነገር ለማስተካከል አይደለም።

በዝግመታዊ ለውጥ እና በፍጥረት ትሪክ ውስጥ ያለው ልዩነት *ወሳኝ* ነው። በትክክለኛው መንገድ ያልተማሩ እና ያልተመሩ ክርስቲያኖች ቢኖሩም ወደ ድህነት እምነት ለመምጣት ይህንን የፍጥረት እውነት ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። ስለዚህም የፍጥረትን ታሪክ ፣ ፈጣሪውን ፣ ስለፍጥረት የሚያወራውን ቃል፣ ፈጣሪ የሆነውን (ዩሀንስ 1:3) እና በእግዚአብሔር ጸጋ ታላቅ ጉድለታቸውን በፍጥረት ታሪክ ውስጥ ያወቁትን ሰዎች በሚያድነው በክርስቶስ እንመን።

## ዝግመታዊ ለውጥ

በተደጋጋሚ ዳርዊኒያን (Darwinian) ወይም ሌላ የዝግመታዊ ለውጥ ሀሳቦች ሳይንሳዊ ናቸው ተብሎ በመታሰቡ እነዚህ ሀሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በፍጥረት ጉዳይ ላይ ካልተስማሙ በፊት የነበረው

አመለካከት ወይንም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መቅረት አለበት ተብሎ ይታሰባል። ዝግመታዊ ለውጥ "*እውነታ*"፣ የመጽሐፍ ቅዱስ የፍጥረት ታሪክ ግን የእምነት ጉዳይ ብቻ ነው ተብሎ ይወሰዳል። ይህም ደግሞ ውሸት ነው።

የዝግመታዊ ለውጥ ዋና መርህ ሳይንሳዊ እውነታ ሳይሆን እምነት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አለም ጅማሬ እንደሚያስተምረው እንዲሁ ዝግመታዊ ለውጥም የሀይማኖት አስተምህሮ ነው ። የዝግመታዊ ለውጥ አስተምህሮ ምድርን ያለ እግዚአብሔር ለማሳየት የሚፈልጉ ሰዎች ሀይማኖት ነው። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት እና መጋቢነት ከፈጠራት አለም ውጪ ለማድረግ ይጥራሉ።

ስለዚህ ዝግመታዊ ለውጥ ኤቲይዝም ነው (እግዚአብሔርን እና በፍጥረታት ላይ ይለውን ስልጣን የሚክድ ሀይማኖት) ። ይህ ሀይማኖት የማያምን ሰው ነገሮችን ያለእግዚአብሔር ለማብራራት የሚጥረው ጥረት ነው። በዚህም ምክኒያት በመጽሐፍ ቅዱስ እና በሐሰት "ሳይንሳዊ" ተብሎ በተሰየመው ዝግመታዊ ለውጥ መካከል ምንም አይነት የማጣጣም ስራ ሊኖር አይገባም (1ኛ ጢሞ 6:20)።

እውነት ካልሆኑት እና ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ከሌላቸው የዝግመታዊ ለውጥ እውነታዎች መካከል የዩኒፎርሚተሪያንዝም መርህ አንዱ ነው ትርጉሙም - ነገሮች ሁሉ በቋሚ እና በማይለወጡ ተፈጥሯዊ ህጎች ይቆማሉ ማለት ነው። ዩኒፎርሚቴሪያኒዝም ትክክል ካልሆነ የዝግመታዊ ለውጥ አመለካከትም ትክክል ሊሆን አይችልም ማለት ነው ። ሳይንቲስቶችም ዝግመታዊ ለውጥ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችሉበት መንገድ በፍጹም ሊኖር አይችልም። እነዚህ "የተፈጥሮ ህጎች" አለመቀየራቸውን እንደ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለ ሰው ብቻ ማረጋገጥ ይችላልና።

መጽሐፍ ቅዱስ የዩኒፎርሚቴሪያኒዝም አስተምህሮ ስህተት እንደሆነ ያሳየናል። ዩኒፎርሚቴሪያኒዝም የነገሮች ጅማሬ መቸ እንደሆነ ባይናገርም ሁሉም ነገር ከመጀመሪያው ጀምሮ አልተለወጠም ብሎ ያስተምራል። የራዲዮ አክቲቭ ብስባሾች፣ የደለል መመስረት፣ የፎሲል መሰራት፣ የአፈር መሸርሸር እና የመሳሰሉት ነገሮች ወደ መሆን የመጡት በተፈጥሯዊ ህጎች መሰረት ነው ብለው ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እውነት እንዳልሆነ በግልጥ በ2ኛ ጴጥሮስ 3:3-7 ላይ ያሳየናል። ያለማመን ንድፈ ሀሳቦችን መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ስለሚያውቅ "ሁሉም ነገር እንደቀድሞ አይድለም" በማለት እነዚህን ክፍሎች አዘጋጀልን ። እግዚአብሔር በውኃ አለምን ከማጥፋቱ በፊት አለም ሌላ ነበረች ። በታላቁ የውኃ ጥፋት የጠፋው አለምም ተመልሶ ሊመጣ አይችልም። እግዚአብሔር እራሱ በአለም አቀፍ ዉሃ የአለምን ተፈጥሮ በአጠቃላይ ቀይሮታል፤

እንደገናም ደግሞ በአለም መጨረሻ ይህንኑ ያደርጋል ። ስለዚህ የሰዎች “ሳይንሳዊ” መላምት የማብራራት አቅም ካለው ከጥፋት ውሃ በኋላ ያለውን አለም ነው እንጂ ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረውን አለም ሊያብራራ አይችልም።

እኛ ለመጽሐፍ ቅዱስ የፍጥረት ታሪክ ማረጋገጫ አንፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት ታሪክ የሚናገረውን ማመን እግዚአብሔርን የማመን ጉዳይ እንጂ የማረጋገጥ ሆነ የማሳመን ጉዳይ አይደለም። “ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን” (ዕብ 11:3) ። ዝግመታዊ ለውጥ *ኣለማመን* ነው፤ እምነትም ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ይሰማል፣ ይታዘዛልም።

## ቴይስቲክ ዝግመታዊ ለውጥ

ከዳርዊን ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የተሳሳቱ ክርስቲያኖች ዝግመታዊ ለውጥን እና መጽሐፍ ቅዱስን አንድ ላይ በማምጣት ሁለቱን አብሮ ለማስኬድ በብዙ ሞክረዋል ። ይህ የማመቻመች ሙከራ “ቴይስቲክ ዝግመታዊ ለውጥ (Theistic Evolutionism/ *ቴይስቲክ ኢቮልዩሽኒዝም*)” ይባላል። አንዳንድ የቴይስቲክ ዝግመታዊ ለውጥ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።

*ጋፕ ቲዎሪ* (gap theory) የሚባለው ምልከታ ለዝግመታዊ ለውጥ የሚሆኑትን ቢሊየን አመታት እና ለለውጥ ሂደት ምክንያት የሆነውን ጊዜ ወይም ክፍተት በዘፍጥረት 1:1 እና በዘፍጥረት 1:2 መካከል ያስገባል። ለዝግመታዊ ለውጥም “ማስረጃ” ከጠፋው የመጀመሪያው አለም የተረፉ ጥቂት ቅሪታዎች ብቻ ናቸው ይላሉ፤ ሆኖም ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ካለፈው አለም ቅሬታ (የተረፈ ነገር) ስለመኖሩ የሚያወራው ምንም ፍንጭ የለም።

የ*ቀን-ኣመት* ወይንም *የክፍለ ግዜ ንድፈ ሀሳብ* (The day-age or period theory/ *ዴይ ኤጅ ኦር ፔሬድ ቲዎሪ*) የተመሰረተው ዘፍጥረት 1 እና 2 በእርግጥም ረጅም ዘመናት ነበሩ በሚለው አስተሳሰብ ላይ ነው። ነገር ግን ይህ ሙከራ በአጭሩ በዘጸአት 20:8-11 መልስን አግኝቷል ፤ መልሱም በዘፍጥረት 1 የነበሩት ቀናት ከ24 ሰዓት ቀን ጋር አንድ አይነት እንደነበሩ በግልጽ ያስቀምጣል ።

የ አፈ-ታሪክ ንድፈ ሀሳብ (the myth theory/ *ሚትዝ ቲዎሪ*) ደግሞ ዘፍጥረት 1-3 ታሪክ ሳይሆን እውነታ አድረገን በቀጥታ ልንወስደው የማንችለው ጥበባዊ አጻጻፍ ፣ አፈታሪክ ወይም እውነታን እንድንማርበት የተቀመጠ ምሳሌ ነው ብሎ ያምናል። የዚህ ንድፈ ሀሳብ ድካም ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ሐዋሪያቶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን በቀጥታው መቀበላቸው ነው (ማቴ 19:4, ሮሜ 5:12, 1ኛ ቆሮ 15:45-47)።

በመጨረሻም መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረት በስድስት ቀናቶች ውስጥ መፈጠራቸውን እና የዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች ታሪክ መሆናቸውን በመመስከሩ እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች በሙሉ ውድቅ ሆነዋል።

እግዚአብሔር እራሱ በዘጸአት 20:8-11 ላይ ፍጥረት በስድስት ቀን (እነዚህም ቀኖች ከእኛ የቀን አቆጣጠር ጋር ተመሳሳይ ናቸው) ውስጥ እንደ ተፈጠረ ይናገራል ። ኢየሱስ እና ጳውሎስም የሚያምኑት እግዚአብሔር በፈጠረው እውነተኛ እና ታርካዊው አዳም እንጂ በዝግመታዊ ለውጡ ሰው አይደለም (ማቴ 19:4-6, 1ኛ ቆሮ 15:45) ። ጴጥሮስም እንዲሁ በፍጥረት እንደሚያምን በዚህ ክፍል ውስጥ ስንመለከት (2ኛ ጴጥ. 3:5) ዩሀንስም ተመሳሳይ እምነት እንዳለው በዚህ ክፍል እናያለን (1ኛ ዩሀንስ 3:12) ።

እግዚአብሔር ትዕዛዙን ሲያወጣ ስለሚናገረው ጉዳይ አያውቅም ብለን በድፍረት መናገር እንችላለን? ክርስቶስ ኢየሱስ የአዳም እና የሄዋንን መፈጠር ለትዳር ምሳሌ ሲያቀርብ እየዘባረቀ ነበር? ጳውሎስ አዳምን “የመጀመሪያው ሰው” ብሎ ሲጠራው እየዋሸ ነበር?

ስለዚህም ስለፍጠረት አፈጣጠር ያለን የትኛውም አመለካከት ችግር አምጪ አይደለም የሚለው ሀሳብ ስህተት ነው። በዝግመታዊ ለውጥ እያመንን፣ በተለይም ደግሞ በክርስቶስ አዳኝነት ላይ ያለው እምነታችን አይነካም የሚለውም ሀሳብም እንዲሁ ስህተት ነው። በእነዚህ ሀሳቦች ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የእግዚአብሔር እውነተኛነት አደጋ ላይ ይወድቃልና ።

የዝግመታዊ ለውጥ ክርክር የእግዚአብሔር እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እውነተኛነት ላይ የተመሰረተ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ አስትመህሮዎች እውነተኛነትን የሚነካ ጉዳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የዘፍጥረት 1-11 ታሪካዊ ትክክለኛነትን በብዙ ቦታ ያስተምራል። ስለዚህም አልያም መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ሰው ደግሞ ሁሉ ውሸታም ነው ፤ አልያም ደግሞ ሰው ንድፈ ሀሳቡን ሲያቀርብ እውነታን እየተናገረ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በውሸት እና በሀሰት የተሞላ ነው። የትኛው ትክክል ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ዴይ-ኤጅ የፍጥረት ንድፈ ሀሳብ

የዴይ-ኤጅ ንድፈ ሀሳብ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የፔሬድ ንድፈ ሀሳብ ተብሎ የሚጠራው ምልከታ በዘፍጥረት 1 ላይ ያሉት ቀናቶች ረጅም ዘመናት ነበሩ ብሎ ይስተምራል ይህም ዝግመታዊ ለውጥን እና መጽሐፍ ቅዱስን ለማስታረቅ የሚሞክር ብቸኛው ንድፈ ሃሳብ ነው። ሀሳቡን የምንሞግተውም ይህንን መሰል ሙከራዎች እንዴት በቀላሉ ሀሰት መሆናቸው ሊረጋገጥ እንደሚቻል ለማሳየት ነው። በተጨማሪም ደግሞ እንደዚህ ያሉ ሀሳቦች ሀሰት መሆናቸውን ማርጋገጥ የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ በማጥናት ብቻ እንደሆነ ማሳየት እንፈልጋለን። መጽሐፍ ቅዱስም እራሱን በራሱ ስለሚተረጉም ለእኛ እውነተኛ እና የተረጋገጠ መመሪያ ነው።

ማንኝውም ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ “ቀን” የሚለውን ቃል ሲያጠና ሁለት ሀሳቦችን በፍጥነት ይረዳል። ይህንን መሰል ጥናት በመጽሐፍ ቅዱስ “ቀን” የሚለው ቃል ረጅም ዘምንን መወከል እንደሚችል ያመላክታል (2ኛ ጴጥ 3:8-10) ። በዚህም ጉዳይ ላይ ምንም ጥርጣሬ የለም።

ነገር ግን የበለጠ እና የጠለቀ ጥናት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ *ቀን* የሚለው ቃል በተራ ቁጥር ቃላቶች (መጀመሪያ፣ ሁሉተኛ፣ ሶስተኛ......... የመሰሰሉት) ሲገለጥ ረጅም ጊዜን ሊወክል እንደማይችል እንረዳለን ። *ቀን* የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተራ ቁጥር ቃላቶች ሲገለጽ የተለመደውን የ24 ሰዓት ቀን ያመለክታል። ስለዚህ በዘፍጥረት 1 ላይ *ቀን* የሚለው ቃል በተለምዶ የቁጥር አጠራር ተደግፎ በመጠራቱ የተለመዱትን ቀናቶች ይወክላል። መጽሐፍ ቅዱስም እራሱን በእራሱ አብራራ ማለት ነው።

እግዚአብሔርም የዘፍጥረት ቀኖች የተለመዱትን ቀናቶች እንደሚወክሉ በዘፍጥረት 1 ላይ ሰለ ንጋት እና ምሽት በመጥቀስ ፤ በዘጸአት 20:11 ላይ ደግሞ የፍጥረት ቀናቶች ለእኛ የስራ ቀንን የሚወክሉ ቀናቶች እንደሆኑ ይናገራል ። እግዚአብሔር የዘፍጥረት 1 ቀናቶች እኛ አሁን እንደምንሰራባቸው አይነት ቀናቶች ናቸው ይለናል ። በጥልቀት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሲተጠና “ምሽት እና ንጋት” አንድላይ ሲቀርቡ *ሁልጊዜ* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያላቸው ትርጉም አንድ ነው እርሱም እኛ አሁን ቀን ብለን የምንረዳውን ቀን ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንደገና እራሱን ሲያብራራ እንመለከታለን።

በዚህ ውስጥ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚማረው ማስጠንቀቂያ አለ። ይህም ደግሞ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመቅረብ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእራሱ ምን እንደሚል መረዳት አለብን የሚል ነው። የእራሳችንን አመልካከት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በማምጣት የእግዚአብሔርን ቃል መጋፋት የለብንም። የእኛ ድርሻ የሆነው የእራሳችንን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ መስጠት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት እና

በጥንቃቄ በማመሳከር እራሱን እንዲፈታ ማድረግ ነው። ይህንንም ካደረግን ወዲህ በአስተምህሮው ማመን እና መገዛት አለብን።

ቴይስቲክ ዝግመታዊ ለውጥ (Theistic evolutionism) መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 1-3 ላይ የሚናገረውን እውነት ብቻ ሳይሆን ክፍሉን የሚያብራሩትን እና በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሦስቱ ምዕራፎች ላይ ብርሃን የሚያበሩትን ክፍሎች እውነታ ለመቀበል አለመፈለግ ነው ። እንደገናም ቴይስቲክ ዝግመታዊ ለውጥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ጽሐፊነቱ እና እንደ ሉዓላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እና የእነዚህ ሦስት ምዕራፎች አብራሪነቱ የሚናገርውን አለመስማት ነው።

ጉዳዩ በፍጥረት እና በዝግመታዊ ለውጥ መካከል ብቻ ያለ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት፣በመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን እና ብቁነት መካከል ጭምር ነው። ይህ ደግሞ እውነት የሆነው ዝግመታዊ ለውጥን እና መጽሐፍ ቅዱስን ለማደባለቅ የሚደረግ የትኛውም ሙከራ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በመጣል ሳይንሳዊ ናቸው የሚባሉትን እምነት የለሽ የዝግመታዊ ለውጥ አስተምህሮ ስለሚቀይር ነው።

አንድ ሰው እንዲህ ብሏል “እግዚአብሔር ዮናስ አሳነባሪ ዋጠ ቢለኝ፣ ሳይንቲስት ደግሞ አሳ ሰውን ሊውጥ አይችልም ቢለኝ የመጀመሪያውን አምናለሁኝ።” እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ሰው ሁሉ ደግሞ ውሸታም ነው። እርሱ ሰለ ፍጥረት የሚናገረው ሀሰት ሊሆን አይችልም።

## የእግዚአብሔር መግቦት

መግቦት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም ። እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኝ የፍጥረታት ሁሉ ገዢ ነው የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ለመግለጽ የተሰጠ ስም ነው።

እግዚአብሔር እንደ ፍጥረት ሉዓላዊ ገዢ የፈጠረውን ሁሉ ይንከባከባል ፤ ለእነርሱም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ይሰጣቸዋል ። ማዘጋጀት (provide) የሚለው ቃል መግቦት (providence) የሚለው ቃል ውስጥ መገኘቱን አስተውሉ። ሆኖም ግን መግቦት ከአዘጋጅነቱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነት ፣ መሪነት እና ሁሉን ነገር ለአላማው መጠቀሙንም ያመላክታል። “በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቈጠራሉ ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል ፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም” (ዳን 4:35) ይህም የእግዚአብሔር መግቦት ምሳሌ ነው።

የእግዚአብሔር መግቦት ማለት ምንም ነገር እንዲሁ አይሆንም ማለት ነው። እድል ወይም እጣፈንታ የሚባል ነገር የለም (ማቲ 10:29-30) ። ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ስራ ነው። የክፉ ሰዎች የሀጥያት ስራ እና የዲያቢሎስ ስራ ሁሉ እንኳን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ውስጥ ነው (ዘጽ 4:21, 1ኛ ሳሙ 2:25, 2ኛ ሳሙ 17:10, 2ኛ ሳሙ 24:1, 1ኛ ነገስት 22:19-22, መዝ 139:1-6, ምሳሌ 16:1, 4, 9, ምሳሌ 21:1, ኢሳ 10:15, ኢሳ 45:7, ኢሳ 63:17, ኤር 10:23, ዳን 4:17, አሞጽ፣ 3:6, ማቴ 8:31, ሐዋ 2:23, ሐዋ 17:28, ሮሜ 9:18) ። ነገር ግን እግዚአብሔር ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ለየትኛውም ሰው የክፋት ድርጊት ኃላፊነት አይወስድም። በእውነትም መንገዱ እንደመንገዳችን ሀሳቡም እንደ ሀሳባችን አይደለም (ኢሳ 55:8) ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር መግቦት ሲናገር በብዛት ስለ "እጁ" ይናገራል (መዝ 109:27, 1ኛ ጴጥ 5:6) ። በእጁ ለፍጥረታት ነገሮችን ሁሉ ያዘጋጃል ህይወትን እና እስትንፋንም ይሰጣቸዋል ። በእጆቹ ነገሮችን ሁሉ እንዲያገለግሉት ወደ እራሱ ድንቅ አላማ ይመራል። የእርሱ እጆች ሉዓላዊ እና ኃያላን ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሰዎችን አላማውን መፈጸሚያ ሲያደርጋቸው (መዝ 17:13-14) ወይም ደግሞ የአላማው መሳሪያ አድርጓቸው (ዘፍ 49:24, መዝ 17:13, ኢሳ 10:15) "የእግዚአብሄር እጅ" ተብለው ሲጠሩ እንመለከታለን ። ከዚህም በላይ ደግሞ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር እየተጠቀመባቸውም ስራውን መጠየቅ እንደማይችሉ እንረዳለን (ኢሳ 45:9)።

እግዚአብሔርን ለማይፈሩት ሰዎች እንዴት የሚያስፈራ እውነት ይሆን? እነርሱ ምንም ቢያደርጉ ሆነ የትም ቢሄዱ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ናቸው፤ ያለእርሱም ምንም ማድረግ አይችሉም፤ እርሱም ዳኛቸው እና ቀጪያቸው ነው። ደግሞም በተመሳሳይ ልኬት ለአማኞች በእግዚአብሔር መግቦት ውስጥ የማይዘለቅ ማጽናናት አለ ምክንያቱም የያዛቸው እጅ ለዘላለም የወደዳቸው እና በምህረቱ የሚራራላቸው የአባታቸው እጅ በመሆኑ ነው(ዩሀንስ 10:28-29) ። መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ ስለመቀረጻቸው ጭምር ያወራል (ኢሳ 49:16) ።

ስለዚህም አማኞች ከመግቦቱ አስተምህሮ የሰማይ አባታቸው ሁሉን ቻይ መሆኑን ይረዳሉ። እርሱ ለድህነታቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላል። የህይወታቸውን እያንዳንዱን ሁኔታ ፤ እነርሱን የሚቃወሙ ነገሮችን ሁሉ ጭምር ይቆጣጠራል። ህመም፣ ሞት፣ ድህነት፣ መከራ፣ ስደት እንዲሁ በእጣፈንታ የሚመጣ ሳይሆን ሕዝቡን በሚወደው እና አንድያ ልጁን ለእነርሱ በሰጠው በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ቁጥጥር ስር የሆነ ነገር ነው ። በእርግጥም ሁሉም ነገር ተጠቅልሎ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ሁሉ ለመልካም

ይሆንላቸዋል (ሮሜ 8:28) ። ማንም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለያቸው አይችልም (ቁጥ 39) ።

## መጠበቅ እና መግቦት

የእግዚአብሔር መግቦት አንዱ ገጽታ "መጠበቅ" ነው። በዚህም ለፍጥረታት ሁሉ ህይወት እና መኖርን የሰጠው እግዚአብሔር እራሱ ራሳቸውን እና ህይወታቸውን ይጠብቃል ማለታችን ነው። ይህንን የሚያደርገው ለአውሬዎች እና ወፎች፣ ህዋ እና ክዋክብት፣ ሳር እና ዛፎች ለሆኑ ግዑዛን እና እንስሳት ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ፣ ለመላዕክቶች እና ለአጋንንቶችም ጭምር ነው (መዝ 104:10-24, ሉቃስ 8:26-33) ። በእርሱ ፍጥረታት ሁሉ ይኖራሉ ይንቀሳቀሳሉ አካልነትንም ተላብሰዋል (ሐዋ 17:28) ።

ይህ ታላቅ እውነት ነው። እግዚአብሔር በቋሚነት በሁሉን ቻይነቱ ሀይል ከእነርሱ ጋር እና በእነርሱ ውስጥ ካልተገኘ ፣ ሁሉንም ነገር ደግፎ ካልያዘ ምንም ነገር ሊኖር አይችልም ማለት ነው ። ነገሮች በእግዚአብሔር እንጂ በራሳቸው ህልውና (exist) ሊኖራቸው አይችልም ። ይህ እውነታ አሁን ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ የተቀመጥኩበትን ወንበር ፣ እንዲሁም ደግሞ ጸሐይን፣ ጨረቃን እና ሂደቶቻቸውን ጭምር ያካተተ ነው።

ይህ በፍጥረት ላይ ያለው አንድነት እና ስርዓት የተፈጥሮ ህግ ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የመገኘት እና የታላቅነቱ ሀይል ውጤት ነው። ጸደይ፣ በጋ፣ በልግ፣ እና ክረምት በየአመቱ በተመሳሳይ ጊዜ የሚመጡት "በተፈጥሮ ህግ" አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር በታማኝነቱ ስለሚልካቸው ነው። ጠፈር ምህዋሩን ለመከተል የተፈጥሮን ህግ አይታዘዝም ነገር ግን የሚያዘውን እና የሚመራውን እግዚአብሔርን ይታዘዛል።

በፍጥረት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ስራ ስለእራሱ ለሰዎች ሁሉ የሚመስክርበት አንዱ መንገድ ነው (ሐዋ 17:24-28, ሮሜ 1:18-20)። በፍርድ ቀን ማንም እግዚአብሔርን "አላወኩኽም" ሊል አይችልም። የእግዚአብሔር በፍጥረት ውስጥ መገለጥ ለሰው ልጅ የሚያድን መገለጥ ባይሆንም ሰዎችን ግን ያለማመካኛ ይተዋል።

እንዲህ ባለ የእግዚአብሔር ሀይል እና ታማኝነት ምስክርነት መካከል እየኖሩ ሰዎች እርሱን አለማምለካቸው ያሳፍራል(ሮሜ 1:21)። በተለይም ደግሞ እግዚአብሔር ስለሚያዘጋጅላቸው እና ስለሚጠብቃቸው እጅግ

አሳፋሪ ነው ። ጳውሎስ በሮሜ 1 ላይ እንደሚለው እርሱን ከማክበር እና ከማመስገን ይልቅ ወደ ጣዖት አምልኮ እና ወደ አለመንጻት ያዘነብላሉ።

ስለዚህም ጣዖትን ማምለክ እግዚአብሔርን ለማግኘት የሚደረግ ፍልጋ ሳይሆን ይልቁንም ከእሱ መሸሽ ነው። ይህም ደግሞ አህዛብ ጭምር ስለ እውነተኛው እግዚአብሔር የሚያወቁት አንዳች ነገር እንዳለ ያመላክታል። ከእሱ በመሸሻቸው እግዚአብሔር ለአሳፋሪ ሀጥያቶቻቸው በተለይም ለግብረሰዶማዊነት ሀጥያት አሳልፎ ይሰጣቸዋል (ቁጥ. 24-27) ። ይህ ደግሞ በተጨማሪ ደግሞ እርሱን ስለማወቃቸው ማመሳከሪያ ነው።

እነዚህ ሀጥያቶች ለማያመሰግኑ ሰዎች የተሰጡ ቅጣት ናቸው። እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አውሬዎች እየሆኑ ይልቁንም ደግሞ እግዚአብሔር ለሀጥያቶቻቸው አሳልፎ ስለሚሰጣቸው፣ አውሬዎች የማይፈጽሙትን ሀጥያት በመፈጸም ከአውሬም የባሱ ሆኑ ።

በፍጥረት ላይ ያለው የእግዚአብሔር የአብሮነት እና የመግቦት ኃይል በክርስቶስ ለታውቀ እና ለተወደደ አማኝ እጅግ ድንቅ ምስክርነት ነው። በእግዚአብሔር እንደሚኖር እንደሚንቀሳቀስ እናም አካልነትን የተላበሰ እንደሆነ በመረዳት ምንንም ነገር የማይፈራና ፣ ለዘላለም አመስጋኝ ይሆናል። ይህም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ህይወቱን ስለሚጠብቅለት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እለት በእለት፣ ህይወትን እስትንፋስን እና ሁሉን ስለሚጨምርለት ነው (ሐዋ 17:25)። ህይወትን በሚሰጠው እና በሚጠብቅለት ደግሞም ህይወትንም የመውሰድ መብት እንዳለው እና እግዚአብሔርም በሞት እንኳን ለልጆቹ እጅግ ታማኝ አባት መሆኑን እጅግ በመታመን በሙሉ ልብ በሰላም ሞቱን ይቀበላል።

**መንግስቱ እና መግቦቱ**

ሌላኛው የእግዚአብሔር መግቦት ገጽታ በነገሮች ሁሉ ላይ ያለው ገዢነት እና መንግስቱ ነው። እግዚአብሔር ገዢ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎ ያስተምረናል (መዝ 2:2-4) ። የነገሮች ገዢ እና የመግቦት አምላክ በመሆኑ እርሱ “ያም መገለጥ፣ የተባረከውና ብቻውን ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶችም ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚያሳየው ነው” (1ኛ ጢሞቴዎስ 6:15) ።

የእግዚአብሔር መግቦታዊ አስተዳዳሪነት

***ሁሉን አቀፍ ነው።*** የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የማይገዛው ነገር የለም፣ ሰይጣንም ቢሆን ሀጥያት (ኢዮብ 1:12, ኢዮብ 2:6) ።

***ሉዓላዊ ነው።*** እግዚአብሔር ሁሉን መግዛት ብቻ ሳይሆን ፈቃዱን እና አላማዉን በሚያገለግል እና በሚያስፈጽም መንገድ ሁሉን ይገዛል። ከሰዎች ፣ ከመላዕክት እና ከአጋንንት አንጻር እንኳን የእርሱ ገዢነት በጥያቄዎቻቸው ውስጥ አይገባም ወይም ገዢነቱ በፍጥረቱ ፈቃድ ላይ የተወሰነ አይደለም (ኢዮብ 9:12) ።

***ጻድቅ ነው።*** እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ የሚገዛው ሰዎች ፣ መላዕክት እና ጋኔኖች የእራሳቸውን ሀላፊነት እየወሰዱ ነው ። የሁሉ ነገር ተቆጣጣሪ እርሱ ቢሆንም ለክፉ ተግባራቸው እርሱ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም (ሮሜ 9:17-20) ።

***አላማ ያለው ነው።*** እግዚአብሔር መግዛት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ነገር ለፍጹም አላማው እንዲገዛ ያደርጋል። በእድል የሚሆን አንዳችም ነገር የለም። ለእግዚአብሔር አዲስ የሚሆንበት ሆነ ሃሳቡን የሚያስቀይር አንዳችም ነገር የለም (መዝ 115:3, መዝ 135:6, ሮሜ 9:21-22) ።

***ከመረዳት ያለፈ ነው።*** እግዚአብሔር ታላቅ መሪ በመሆኑ መንገዶቹ ከእኛ መረዳት በላይ ናቸው (ኢዮብ 9:10, ኢሳያስ 55:8) ። ነገሮች ሁሉ ተያይዘው ለህዝቡ ለመልካም ለተቀሩት ደግሞ ለመጥፍያቸው እንደሆነ ብናውቅም ይህንን ለማየት ግን ሁልጊዜ እንቸገራለን። በእምነት እንጂ በምናየው አንኖርምና (2ኛ ቆሮ 5:7) ።

***ባለጸጋ ነው።*** የእግዚአብሔር አገዛዝ ለህዝቡ የሚጠቅም ነው (ሮሜ 8:28) ። ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ለበጎ እንዲሁ አይሆኑም ሆኖም እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ስለሚቆጣጠር እና ስለሚመራቸው ለበጎ ይለወጣሉ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር መሪነት ለሁሉም በጸጋ የተሞላ ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን በማይፈሩት ላይ ያለው አመራር ህዝቦቹ ላይ ካለው አመራር በተለየ ነው። አመራሩ ፈራጅ ነው። ይህም የእሱን አመራር እና ስጦታውን በመቃወማቸው ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ወደ መጥፊያቸው እና ወደ መቀጫቸው ስለሚመራቸው ነው። እርሱ መልካም ነገርን እንደሚሰጥ ለመካድ ሳይሆን ። በእርግጥም ሕይወትን እና እስትንፋስን ፣ ምግብን እና መጠለያን ፣ የፍሬያማ አመታቶችን እና የቀረውን ሁሉ እጥቷቸውዋል። ነገር ግን እነዚህን ነገሮች የሰጣቸው ከፍቅር ወይንም ከጸጋ የተነሳ አይደለም።

የምናያቸው ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ጥብበዊ አመራር ውስጥ መሆናቸው በማይመስልበት በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን መግቦታዊ አመራር ልናምን ይገባል። በፍጥረት እና በማህበረሰብ ውስጥ ከስርዓት ይልቅ ስርዓት አልበኝነትን እና በታሪክ እና በፍጥረት ውስጥ ከፍትህ ይልቅ ኢ-ፍትሃዊነትን ፣ ረብሻን እና ትርምስን እንመለከታለን። ይህ ቢሆንም ግን እምነት እግዚአብሔር አሁንም ነገሮችን እየተቆጣጠረ እንዳለ ፣ በእድል የሚሆን አንዳች እንደሌለ እና በእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉም ለመልካም እንደሚሆን ያውጃል ። እምነት ነገሮች ሁሉ ለእግዚአብሔር ህዝቦች ለበጎ እንዲሆኑ ይደግፋል ፣ ነገሮች ሁሉም *ተሰብስበው* እግዚአብሔርን ለሚወዱ ሁሉ ለበጎ ሊሆንላቸው ግድ ነው ።

## የእግዚአብሔር ሁሉን አቀፍ መግቦት

የእግዚአብሔር መግቦት በምድር፣ በሰማይ እና በገሃነም ባሉ ነገሮች ሁሉ ላይ መሆኑ ሊደምቅ የሚገባ ዋና ጉዳይ ነው። በሌላ አማርኛ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው ማለታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ እነዚህን እንደሚመራ ይነግረናል፥

- መላዕክትን (መዝሙር 103:20-21) ።
- አጋንንትን (ኢዮብ 1:12, ኢዮብ 2:6) ።
- የሰው ልጅ በሙሉ (ኤር. 10:23, ሐዋ 17:28) ።
- የሰውን ልብ (ምሳሌ 21:1) ።
- የሰውን ስራ (ምሳሌ 16:9) ።
- የሰው ሀሳብ እና ንግግር (ምሳሌ 16:1) ።
- የሰው የሀጥያት ተግባራት (መዝ 33:10, ምሳሌ 16:4, አሞጽ 3:6, ሐዋ 2:23) ።
- በህዝቡ ሀጥያት ላይ (ኢሳ 63:17) ።
- በሀጥያት የደነደነው የሰው ልብን (ዘጽ 4:21, ሮሜ 9:18) ።
- አየር ንብረት እና ወቅቶችን (ሐዋ 14:17) ።
- ክዋክብት እና ጠፈርን (መዝ 104:19) ።
- የፍጥረት ታላላቅ ነገሮች ላይ ሁሉ (ኤር 5:24, ዳን 4:35) ።
- ጥቂት እና ትንንሽ የሚባሉትን ነገሮች ላይ ሁሉ (ማቴ 10:29-30) ።

- የተፈጥሮ አደጋዎች እና ደስ የማያሰኙ ክስተቶችን (መዝ 105:29, መዝ 148:8) ።
- ጦርነት እና ሰላምን (ኢሳ 45:7) ።
- ህይወት እና ሞትን (ዘፍ 4:1, መዝ 31:15, መዝ 104:28-29) ።
- ሁሉን ነገር (መዝ 103:19) በሉዓላዊነት እንደሚያስተዳድር ያስተምረናል ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር መግቦት የእርሱ ገዢነት ብቻ ነው ማለት አይደለም ። እርሱ ሁሉ ነገር እንዲከናወን እንደሚፈቅድ ፣ እንደሚመራ ፣ እንደሚቆጣጠር እና የሚሆነውን ሁሉ ደግሞም ለእራሱ አላማ እና ደስታ እንደሚያደርገው መርሳት የለብንም (ዘጽ 3:19-20, ኢሳ 44:28, ኢሳ 46:9-10, ኤፌ 1:5 ፊሊ 2:13) ።

ይህ የመግቦቱ ሚስጢር እና ተዓምር ነው። እግዚአብሔር ክፋትን እና ክፉ አድራጊዎችን ጨምሮ ሁሉን ነገር እርሱ ለክፋ ነገር ሁሉ ተጠያቂ ሳይሆን መጠቀሙ የመግቦቱ ሚስጥራዊነት ነው። በሉዓላዊነቱ ሁሉን ነገር ለህዝቡ ድኅነት የሚጠቀም እና እርሱን ለሚወዱት እና እንደሀሳቡ ለተጠሩለት ሁሉ ነገር ለበጎ እንዲሆን ማድረጉ ደግሞ የጸጋው ተዓምር ነው። ይህንንም የሚያደርገው ስለ ህዝቦቹ ሀጥያት ዋጋ ለከፈለው፣ ለሞተው እና ከሞትም ለተነሳው ለክርስቶስ ኢየሱስ ሲል ነው።

## መግቦቱ እና “የወል ጸጋ”

እግዚአብሔር በመግቦቱ ለፍጥረቱ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ይሰጣል (ሐዋ 17:25) ። ይህ ማለት እግዚአብሔር ለክፉዎች ጸሀይ እና ዝናብ ፣ ምግብን እና መጠለያን፣ ህይወትን እና እስትንፋስን ብቻ ሳይሆን የሚያመዛዝን አዕምሮ ፣ ፈቃድ እና መንፈስ ያሉ መልካም ስጦታዎችን ይሰጣል ማለት ነው።

ብዙዎች ከዚህ በመመነሳት እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደሚወድድ እና ለእነርሱ መልካም እንደሆነ ይናገራሉ። በእነርሱ አነጋገር እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው እና እንደሚያስብላቸው የሚመሰክር ወደ ድህነት የማያደርስ ለሁሉ የተሰጠ “የጋራ ጸጋ” ነው። ነገር ግን በጋራ የተሰጠን ነገር (የጋራ መግቦት) ሁሉ የጋራ ጸጋ ማለት ስላይደለ ሁለቱ ሀሳቦች ግራ ሊያጋቡን አይገባም። መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ለእነዚህ የእግዚአብሔር የጋራ መግቦቶች “ጸጋ” የሚለውን ቃል ሲጠቀም አንመለከትም።

ይህም እግዚአብሔር ለክፉዎች የሚሰጠው ስጦታ መልካም ስጦታ አይደለም ለማለት አይደለም (ያዕቆብ 1:17)። ነገር ግን እግዚአብሔር እነዚህን ስጦታዎች ስለሰጣቸው ይወዳቸዋል ወይንም ለእነርሱ ጸጋን ይሰጣል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር መልካም ስጦታዎችን ለክፉዎች መስጠቱ ስጦታውን የሰጠበትን *ምክኒያት* አይናገርም ። መጽሐፍ ቅዱስ ለክፉዎች መልካም ስጦታ መስጠቱ ከፍቅር ወይም ከምህረቱ ውጪ ሌላ ምክንያት እንዳለው ያስተምራል። እነዚህን ስጦታዎች የሰጣቸው የቁጣ ወጥመድ እንዲሆንባቸው (መዝ 11:5, ምሳ 14:35, ሮሜ 11:9) ፣ ለእርግማን (ምሳ. 3:33) እና ለመጥፊያቸው ነው (መዝ 92:7) ። ስለዚህ በእነዚህ ስጦታዎች *በሚያዳልጥ መንገድ* ወደ *ጥፋታቸው ይጥላቸዋል* (መዝ 73:18 በ ቁጥ 3-7 አውድ መሰረት) ። ይህ በግልጽ ክፉዎች ስጦታውን በእግዚአብሔር ፊት ሀጥያትን ለመስራት እና ለፍርዳቸው እራሳቸውን ሲይዘጋጁበት እንመለከታለን።

ይህ እውነት በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከጠላቶቻችን ጋር ባለን ግንኙነት እርሱን እንድንመስል እንማራለን። ለእነርሱ መልካም እንድናደርግ እና እነርሱ ባይመለሱ እና ንሰሀ ገብተው ባያምኑ እኛ ያደረግንላቸው መልካም ነገር ለእራሳቸው ጥፋት እና ፍርድ ይሆንባቸዋል (ሮሜ 12:20-21) ።

ስለዚህ ስጦታው መልካም ሆኖ ሳለ ይህንን ለሚመስል ምክንያት መሰጠቱ እኛን ሊያስገርመን አይገባም። አባት ለልጁ በኩሽና ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን የሥጋ ቢላዋ ቢሰጠው በእርግጥም ይህ አባት ለልጁ “መልካምን ስጦታ” ከፍቅር እና ከርህራሄ የተነሳ መስጠቱን እንድንጠይቅ ያደርገናል። ልጁ በእርግጠኝነት ለእራሱ መጥፋት ቢላዋውን ያለአግባብ እንደሚጠቀምበት እንደዚሁ ክፉዎች እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን መልካም ስጦታ ያለአግባብ ለእራሳቸው መጥፋት ይጠቀሙበታል።

የጋራ ጸጋን ማስተማር ትልቁ ጥፋት ምናልባትም በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እረፍት ማጥፋቱ ነው። ዝናብ እና ጸሐይ ፣ ጤንነት እና ህይወት የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታዎች ናቸው ካልን እግዚአብሔር  በተቃራኒ  ህመም ፣ ድህነት ፣ ድርቅ ወይም ሞትን ሲያመጣ መደምደሚያችን ምን ሊሆን ነው? እነዚህ ነገሮች የእርሱ እርግማን ናቸው? እነዚህን የሚልከው ስለሚጠላን ነው? ጸጋ “መልካም ነገር” ብቻ ከሆነ እነዚህን ነገሮች እግዚአብሔር ሳይሰጠን ሲቀር ጸጋ አልተሰጠንም ማለት ነው? ታዲያ እንዲህ ከሆነ እርሱ የሚልክልን ነገር ሁሉ ጤንነት ይሁን በሽታ ፣ ድህነት ይሁን ሀብት ፣ ህይወት ይሁን ሞት ፣ እርሱ ፍቅሩን ጸጋውን እና ነገርን ሁሉ ለበጎ ይልክልናል (ሮሜ 8:28) ብለን መደምደም አንችልም ማለት ነው? ነገር ግን ለክፉዎች ግን የሚልከው ነገር “መልካም” ቢሆን እንኳን ለጥፋታቸው አይደለምን? ታዲያ ከሀዘናችን እና ከመከራችን እንዴት እንጽናና?

## መግቦቱ እና የሀጥያት ገደብ

በመግቦቱ እግዚአብሔር የሚሆነውን ነገር ሁሉ ይመራል ፣ ይቆጣጠራል ። በሰዎች ህይወት ውስጥ የሚሆነው እያንዳንዱ ጥቃቅን ጉዳይ ጭምር በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ቁጥጥር ስር ነው። ናቡከደነጾር እንዳለው "በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል" (ዳን 4:35)። ስለዚህም ከናቡከደነጾር እና ከሌሎች ህይወት ምሳሌ እንደምንመለከተው በእርሱ መግቦት እግዚአብሔር የሰዎችን የሀጥያት ስራ ሁሉ ይቆጣጠራል ደግሞም ይመራል (1ኛ ሳሙ 2:25, 2ኛ ሳሙ 16:10, 2ኛ ሳሙ 24:1, 1ኛ ነገስት 22:29-22, ሐዋ 2:23, ሮሜ 9:18) ። በዚህ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ እና የመግቦት ስራ ውስጥ ሀጥያትን መገደብም የተጠቃለለ ነው ። እግዚአብሔር በመግቦቱ የሰዎችን ክፋት ይገድባል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሀጥያት መገደብ ብዙ ምሳሌን ያቀርብልናል ። ዘፍጥረት 6፡3 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያው ምሳሌ ነው ። በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር የሰውን እድሜ በማሳጠር ሀጥያትን ሲገድበው እንመለከታለን። በተጨማሪም የባቢሎን ግንብ ሲገነባ እግዚአብሔር የሰዎቹን ቋንቋ በመደበላለቅ ሀጥያትን ሲገድብ እንመለከታለ። በተጨማሪም እግዚአብሔር ሰዎችን ለሀጥያታቸው አሳልፎ መስጠጡ ሀጥያትን እንደሚገድብ ሌላ ማመላከቻ ነው (መዝ 81:11-12, ሐዋ 7:42, ሮሜ 1:24-28)።

እነዚህን ክፍሎች አብዛኞቹ ሰዎች የጋራ ጸጋን ለማመላከት እንደምሳሌ ይጠቀሙበታል ። እግዚአብሔር የሰውን ሀጥያት መገደቡ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያለውን ባለጸጋነት ይመሰክራል ይላሉ ። አንዳንዶች ደግሞ ይህ የጋራ ጸጋ የሰውን አጠቃላይ ውድቀት (*ቶታል ዲፐራቪቲን*) በመካድ ለመዳን የማያደርስ በሁሉም ሰው ልብ፣ ሀሳብ እና ፈቃድ ውስጥ ያለ ሆኖም ግን ለወንጌል መንገድን የሚያመቻች እና ወንጌሉን ለመቀበል እና ላለመቀበል በርን የሚከፍት የእግዚአብሔር ስራ ነው ይላሉ።

የሀጥያት መገደብ አለ ማለት ይህ ጉዳይ ስለጸጋ የሚናገር ጉዳይ ነው ማለት አይደለም አሁንም መጠየቅ ያለበት ጥያቄ "ለምን እና እንዴት ሀጥያት ተገደበ?" የሚል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሀጥያት መገደብ በእግዚአብሔር *ኃይል* እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የወደቀውን የሰውን ማንነት ለመቀልበስ የተሰራ የ*ጸጋ* ስራ እንዳይደለ ይናገራል ። ይህ ስራ እብድ ውሻ ላይ የአፍ ማሰሪያን እንደማሰር ነው፤ ከመናከስ ይገድበዋል እንጂ ከእብደቱ አይመልሰውም ። በተመሳሳይ እግዚአብሔር የሰዎችን

ልብ ሳይቀይር ብዙ መንገዶችን በመጠቀም በተለይም ደግሞ የተግባራችን ውጤት ፍራቻ በመጠቀም የሰውን የልብ ክፋት ይቆጣጠራል ። በኢሳይያስ 37:29 ላይ የምናገኘው ክፍል ሉዓላዊ እንጂ በጸጋ ያልሆነ የሀጥያት መገደብ አንዱ ምሳሌ ነው። በዚያ ክፍል እግዚአብሔር ስለ አሶር ንጉስ “ቍጣህና ትዕቢትህ ወደጆሮዬ ደርሶአልና ስለዚህ ስናጋዬን በአፍንጫህ ልጓሜንም በከንፈርህ አደርጋለሁ፥ በመጣህበትም መንገድ እመልስሃለሁ” በማለት ይናገራል፤ ንግግሩም በጭራሽ ጸጋ የተሞላ አይደለም።

እንደገና ደግሞ ይህ በኢሳይያስ ላይ የሚገኘው ክፍል የገደቡን አላማ ያስረዳናል ። አላማውም የእግዚአብሔር ህዝብ መጠበቅ እና ማስቀጠል ነው ።

የእግዚአብሔር የጋራ መግቦት ማለት የጋራ ጸጋ ማለት አይደለም። ጸጋ እግዚአብሔር ህዝቡን የሚያድነበት ሀይል ነው (ኤፌ 2:8-10) ። ከዚህ በስተቀር ሌላ አይነት አስገራሚ፣ አዳኝ እና ልዩ ጸጋ የለም ፤ስለዚህም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

## የሰው መፈጠር

ሰው በእግዚአብሔር መፈጠሩን እናምናለን ፤ ሰው በዝግመታዊ ለውጥ አልመጣም። የሰው መፈጠር በፍጥረት መጀመሪያ የእግዚአብሔር ስራ ዘውድ ሲሆን የእግዚአብሔርን ታላቅነት እና ሰው በእግዚአብሔር አለም ውስጥ ያለውን ግሩም ቦታ የሚያሳይ ታላቅ ምስክር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን የተለየ ፍጥረት በብዙ መንገድ ያሳየናል። ይህም

- ሌሎችን ሲፈጥር ያላደረገውን ምክር እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት እርስ በእራሱ ተማክሯል (ዘፍ 1:26) ።
- እግዚአብሔር ሰውን በእራሱ አምሳል ፈጥሮታል (ዘፍ 1:26-27) ።
- አራዊቶችን ፣ አእዋፋትን እና አሳዎችን ወደ መኖር እንደጠራው ስውን እንዲህ አልፈጠረውም ነገር ግን ሰውን ያበጀው በታላቅ ድርጊት ወይንም ተግባር ነው (ዘፍ 2:7) ።
- እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከእርሱ ጋር በህብረት እንዲኖር ነው (ዘፍ 2፡25-27) ።
- እግዚአብሔር ሰው መኖር የሚችልበትን ልዩ መኖሪያን አዘጋጅቶለታል (ዘፍ 2:8) ።

- እግዚአብሔር ከሰው ጋር በቀጥታ ይነጋገራል (ዘፍጥ 1፡28) ፡፡
- እግዚአብሔር በፍጥረታት ላይ ለሰው ልጅ ስልጣንን ስጥቶታል (ዘፍ 1:28) ፡፡

የሰው ልጅ ከአራዊት የሚለየው *በገዜ* (የኢንጊሊዘኛው ትርጓሜ ዲግሪ ብሎ አስቀምጦታል) ብቻ እንጂ በማንነቱ ፣ በአይነቱ ፣ ደግሞም እግዚአብሔርን የማወቅ እና ከእርሱ ጋር ህብረት በማድረግ ችሎታው መሆኑን የማያምነው የዝግመታዊ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ እና የመጽሐፍ ቅዱስ የሰው አፈጣጠር ታሪክ በጭራሽ አብረው አይሄዱም። በሰዎች እና በእንስሳት መካከል ልዩነት የለም በማለታቸውም የዝግመታዊ ለውጥ አስተምህሮ ተከታዮች የ"እንስሳት መብት"፣ ጽንስን በቀላሉ በማስወረድ፣ እና በዝግመታዊ ለውጥ የማያምኑ ሰዎችን "ኋላ ቀር" በማለት መሰል ተግባሮችን ያደርጋሉ ፡፡

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የሰው ልጅ ልዩ ሆኖ መፈጠሩ፣ ሰው በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ ምን ያህል ትልቅ ቦታ እንደነበረው እና በመውደቁ ምንን እንዳጣ ያስታውሰናል ፡፡ በመጀመሪያ የነበረበት የክብር ማንነት ብቻ አሁን ያለበትን የመከራ ማንነት ያስረዳዋልና። ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ህብረት እንዲያደርግ የተፈጠረው ሰው አሁን ግን ከሰይጣን ጋር ህብረት በማድረግ መኖር ጀመረ። ከፍታ ላይ ብቻ እንዲኖር የተፈጠረው እንደዚህ ዝቅታ ላይ ወደቀ። ለዘላለም ህይወት ብቻ የተፈጠረው ሰው በሀጥያቱ በራሱ ላይ ዘላለማዊ ሞትን አመጣ።

የዝግመታዊ ለውጥ አስተማሪዎች የሰውን ጊዜያዊ ጉዳይ መረዳት ስላልቻሉ ትምህርትን ፣ ማህበረሰባዊ ተሐድሶን (*ሶሻል ሪፎርም*) ፣ ፖለቲካን መድሀኒት አድርጎ በመውሰድ "መፍትሄዎች" ብለው አስቀምጠዋቸዋል ፡፡ የዝግመታዊ ለውጥ አማኝ ሰው እንደጠፋ ወይንም መንገዱን እንደሳተ ፣ ያለበት ሁናቲ የተመሰቃቀለ እና ለራሱ መፍትሄን ማበጀት የማይችልበት ደረጃ ላይ መሆኑን አይቀበልም ፡፡ ለሰው ልጅ ችግር ምድራዊ እና ጊዜያዊ መፍትሄዎች ተስፋ ቢስ መሆናቸውን አይመለከትም ፡፡ ስለ ሰው የመጀመሪያ ሁናቴ ደግሞም በእጅጉ የሚያስፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ትክክለኛ መረዳትን የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው።

የሰው ልጅ ምን እንደነበረ እና በሀጥያት በኩል አሁን ምን እንደሆነ ስንረዳ እራሱን በራሱ ማንሳት እንደማይችል እና ለችግሩ መፍትሄ በእራሱ ማግኘት እንደማይችል እንመለከታለን። እኛም ከሰው የሚመነጨን መፍትሄ ሳይሆን መለኮታዊ እና ለሰው ልጅ መጎሳቆል መፍትሄ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንመለከታለን።

## ሰው በእግዚአብሔር አምሳል

ስለሰው አፈጣጠር ከሚያስገርሙት ነገሮች መካከል ሰው ሲጀምር በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ነው። በዚያን ጊዜ በአንዳንድ ነገሮች ሰው እንደ እግዚአብሔር ነበር። ከዚህም በላይ የሚያስደንቅ ነገር የለም።

እግዚአብሔር ማንም ሰው ያላየው እና ሊያየው የማይችለው መንፈስ በመሆኑ ሰው በአካሉ እንደ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም (ዩሀንስ 4:24, 1ኛ ጢሞ 6:16) ። ስለዚህም በእግዚአብሔር አምሳል ስንል *በመንፈሳዊው* አምሳል ማለታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በኤፌሶን 4:24 እና በቆላሲያስ 3:10 ሰው እግዚአብሔርን በሦስት መንፈሳዊ መንገድ ይመስለው እንደነበር ይናገራል። እነዚህም ደግሞ በጽድቅ ፣ በቅድስና እና በእግዚአብሔር እውቀት ይመስለው ነበር ። ሰው ወደ ሀጥያት እና ፍርድ ከመውደቁ በፊት ይህንን ይመስል ነበር ማለት ነው ።

እግዚአብሔርን እንዲያውቅ እንዲወደው እና ከእርሱ ጋር በደስታ እንዲኖር እግዚአብሔረ አምሳል ነበረው። ይህ በእግዚአብሔር አምሳል ላልተፈጠሩ ለአውሬዎች እና ለግዑዛን ፍጥረት በጭራሽ መሆን አይደለም።

ሆኖም ግን በተደጋጋሚ የሚነሳው ጥያቄ የወደቀው እና ሀጥያትን የተላበሰው ሰው ከእግዚአብሔር አምሳልነት የቀረው ባህሪ አለ? የሚለው ጥያቄ ነው ። ይህ እጅግ ወሳኝ ጥያቄ ነው። እግዚአብሔር ሁሌም መልካም በመሆኑ ሰው ከእግዚአብሔር አምሳልነቱ የተረፈው ማንነት ካለው እንግዲህ በእርሱም ውስጥ መልካምነት ሊኖር ግድ ነው ። ነገር ግን ሰው ከእግዚአብሔር አምሳል ምንም የተረፈው ማንነት ከሌለ እግዚአብሔር ብቻ መልካም በመሆኑ በሰው ውስጥ ምንም መልካምነት እና ጠቃሚነት ሊኖር አይችልም።

ለዚህ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ የወደቀው ሰው ከእግዚአብሄር አምሳል የቀረው ምንም የለም በማለት በጣም ግልጽ ምላሽ ይሰጠናል። በሀጥያት ፍጹም የወደቀን ሰው እግዚአብሔር ሊመስል ይችላል ማለት ፍጹም ሊታሰብ የማይችል ነገር ነው። ኢየሱስ በዩሀንስ 8:44 ላላመኑት ፈሪሳውያን እና በእርሱ ለማያምኑ ሁሉ “እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።” በማለት ተናግሯል። በሌላ አማርኛ ሰዎች ያላቸው ብቸኛ መንፈሳዊ የመልክ ምሳሌ የሰይጣን ብቻ ነው። ይህንንም ደግሞ ስራቸውን ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ መልሶ ሰዎች የእግዚአብሔር አምሳል አሁንም አላቸው ወይ የሚለውን ጥያቄ ኤፌ 4:24 ላይ እና ቆላ 3:10 ላይ ድህነት የፈጣሪያችንን ምሳሌ እንደገና ማደስ ነው ይለናል ። በድህነት እግዚአብሔር በውስጣችን ያለውን የሰይጣንን መልክ በማስወገድ በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ወልዶን የእራሱን መልክ ፣ ጽድቅን ፣ ቅድስናን እና እውነተኛን እውቀት ሰጥቶናል። ኤፌ 4:24 እና ቆላ 3:10 የእግዚአብሄር መልክ ሶስቱን የጽድቅ ፣ የቅድስና እና የእውነተኛ እውቀት ስጦታ ያካተተ ነው። ይህ አምሳል እስካልታደሰ እና አዲስ ሆኖ እስካልተፈጠረ ድረስ የወደቀ እና መልካምን የመፈለግ ዝንባሌ የሌለው ሰው እንደዚህ አይነት ባህሪያት ሊኖሩት አይችሉም። እነዚህን ባህሪያት በክርስቶስ የታደሱት ብቻ አላቸው።

በእግዚአብሔር አምሳል ታደሰሃል? መልስህ አዎን ከሆነ ንግግርህ እና ስራህ እርሱን እንደምትመስል ያሳያል? የእርሱን ባህሪ ካልመሰለ እንዴት ያሳፍራል! ድነናል፣ እግዚአብሔርንም እንመስላለን እያለን እንደ ሰይጣን መኖራችን እንዴት አሳፋሪ ነው። በተቃራኒው እርሱን በመምሰል ስንመላለስ እና ልጆቹ ስንሆን ለእግዚአብሔር አዳኝ ጸጋ እንዴት ያለ ታላቅ ምስክር እንሆናለን (ኤፌ 5:1) ።

## አዳም እና የሰው ዘር ግንኙነቱ

ከሰው ዘር ጋር አዳም ግንኙነት ስላለው የድርጊቱ መዘዝ ለእኛም ሆነ። ታዲያ ይህ ግንኙነት ምን አይነት ነው?

አዳም የእኛ ተወካይ ወይንም ራስ ነበረ ። ይህንንም የምንረዳው ወላጆች ለልጆቻቸው ጥፋት ሀላፊነትን እንደሚወስዱ እና ልጆቻቸውን እንደሚወክሉ ሁሉ ስለአዳም ጥፋት እኛም ጥፋተኞች ሆነን በመቆጠራችን ነው (ሮሜ 5:12) ። በተጨማሪም 1ኛ ቆሮንቶስ 15:45 ላይ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ተወካያችን ሆኖ በመቅረብ “የመጨረሻው አዳም” በመባሉ የቀድሞው አዳም ተወካይነትን እንረዳለን ።

አዳም የእኛ ተወካይ ነበር ማለት በእኛ ቦታ በመቆም እርሱ ያደረገው ሁሉ ለእኛ ሆኗል ማለት ነው። ስለዚህም አዳም ላደረገው ነገር ሁሉ እኛ እራሳችን እንዳደረግነው ተጠያቂዎች ነን። በዚህም መንገድ የአዳም ሀጥያት እንደ እኛ ሀጥያት ተቆጥሯልና ስለሀጥያቱ እንከሰሳለን ወይንም ደግሞ እንቀጣለን።

ሰዎች በተደጋጋሚ ይህ ፍትሃዊ አይደለም ብለው ያጉረመርማሉ፤ ታዲያ በእውነት ይህ ፍትሃዊ አይደለም? ሆንም ግን አንድ በእርግጠኝነት የምንረዳው ጉዳይ ይህን መሰል ግንኙነት በምድር ላይ ባለን ምልልስ የሰረጸ መሆኑን ነው ። ወላጆች ልጆቻቸውን ይወክላሉ ለልጆቻውም ተግባርን ያከናውናሉ ። ጦርነት ሲነሳ ወይንም

በአንድ ሀገር ጦርነት ሲታወጅ የማይቀበሉት ሰዎች ቢኖርም ፖለቲከኛ የሀገሪቱን ህዝብ ይወክላል ። በተጨማሪም ደግሞ አዳም ተወካያችን ሊሆን አይገባውም የሚሉ ሰዎች ክርስቶስም የእኛ ተወካይ ሊሆን እንደማይገባ መቀበል አለባቸው። ደግሞም ክርስቶስ የአዳምን ቦታ እንደወሰደ እና ለህዝቡም ተወካይ እንደሆነ፣ የክርስቶስ ስራ ሁሉ ለእነርሱ ተቆጥሮ በእግዚአብሔር ፊት ስለእርሱ ሲል ጻድቅ እና እንከን የለሽ ሆነው እንደተገኙ መቼም ቢሆን ልንዘነጋ አይገባም።

ከዚያም ባሻገር የ አዳም ተፈጥሮ እኛ አለን ፤ ደግሞም አዳም ከውድቀት በስተቀር እኛ የነበረን ባህሪ ሁሉ አለው ። ስለዚህም ከአዳም ስራ የተሻለ ወይንም የተለየ ነገር እናደርግ ነበር ማለት አንችልም። እንደገናም አዳም ፍጹም እና ጻድቅ የነበረ በመሆኑ ያለምንም ጥርጥር የመረጠው ምርጫ የእኛም ምርጫ ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል ። አዳም በሀጥያት ሲወድቅ የእርሱ ሀጥያት በእኛ ላይ ፍርድን አስከተለ ብሎም በፍጹም ፍርድ የእርሱ ውድቀት የእኛም ውድቀት ሆነ።

አዳም አባታችን ስለነበር ከእርሱ - ምንም መልካም ማድረግ አለመቻል (ዲፕራቪቲ) ፣ *የተመረዘ* (ኮራፕት) እና *የወደቁ ሰውኛ ባህሪዎችን - ተቀበልን* ። አዳም በሀጥያት ከወደቀ በኋላ መንፈሳዊን ሞት በመሞቱ እኛ ከመወለዳችን በፊት በሀጥያት እና በመተላለፍ አስቀድመን ሞተናል ። እርሱም እራሱን የሚመስሉ ልጆችን ወልዷል (ዘፍ 5:3) ።

ክፋትን ከመስራታችን በፊት ስለሀጥያት መከራ እና ቅጣትን እርሱም ደግሞ በመተላለፋችን እና በሀጥያታችን ሞትን ተቀብለናል ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ለዚህም ምላሽ ከአዳም ጋር ያለን የተወካይነት ግንኙነት ነው። ከመወለዳችን በፊት ፣ መልካም ወይንም ክፉ ከማድረጋችንም በፊት፣ ስለእርሱ ሀጥያት ተጠያቂዎች ነን ። ስለዚህ እርሱ የተቀበለውን የሀጥያትን ቅጣት እና መከራ ተቀብለን እንወለዳለን ። እርሱ ስለ ሀጥያቱ ቅጣት አጠቅላይ ውድቀት (ቶታል ዲፕራቪቲ) እና መንፈሳዊ ሞትን ተቀበለ ። እኛም በእርሱ ሀጥያት ስለምንጠየቅ በተመሳሳይ ቅጣት ውስጥ ተወልደናል።

*ከዚህ እውነታ በተሻለ አሁን ያለንበትን ተስፋ የለሽ ሁኔታ የሚያስረዳ አንድም ነገር የለም። እኛ ምንም መልካም ወይንም ክፉ ከማድረጋችን እና ሀጥያተኞች ከመሆናችን በፊት የሀጥያትን ቅጣት ተቀብለናል። ይህንንም በመረዳት ብቻ የሀጥያት መድሀኒት ከእግዚአብሔር ብቻ ሊመጣ እንደሚችል እናስተውላለን። የዚህ እውነት ትክክለኛ ምልከታ ከሌለን ግን መድሃኒቱ የእራሳችን አቅም፣ ሀይል እና ፈቃድ እንደሆነ እናስባለን ማለት ነው።*

## መብት/ይገባኛል (ሜሪት)

ብዙዎች አዳም በገነት ውስጥ የሙከራ ጊዜ ላይ እንደነበር እና በመታዘዝ ቢቀጥል ኖሮ የዘላለም ህይወት የተገባው ይሆን ነበር ብለው ያምናሉ ። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ብለን እናምናለን ።

ከ1ኛ ቆሮንቶስ 15:47-48 ዘላለማዊ ፣ ሰማያዊ ህይወት የሚገኘው "ከሰማያት ጌታ" እርሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ እንደሆነ ይናገራል ። ከእርሱ ውጪ አዳም ምድራዊ ሆኖ ይቀር ነበር ማለት ነው።

ከዚህም በላይ የይገባኛል (ሜሪት) ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው። ሰው አሁን ባለበት የውድቀት ሁኔታ ላይም ሆነ በገነት ፍጽምና ውስጥ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ ለ "ይገባኛል (ሜሪት)" ቦታ የለውም።

ሰው እግዚአብሔርን ይገባኛል ሊል አይችልም ። ሰው ጻድቅ እንኳን ሆኖ ይህንን ጥያቄ ማቅረብ እንደማይችል መረዳት አለበት። ይህንን መሰል አስተሳሰብም ስሩ፣ ግንዱ እና ቅርንጫፎቹ ሁሉ መነቀል እና መወገድ አለበት።

ሀጥያት የሌለበት ሰው እንኳን አንዳች የሚገባው ነገር የለም ። አንድ ሰው የሚገባው ነገር እንዲኖረው በመጀመሪያ ይሃ ሰው የእራሱ ነገር ሊኖረው ይገባል ለምሳሌ - ጊዜ፣ ችሎታ ወይንም ጥንካሬ ሊኖረው ይገባል።

ነገር ግን የእራሱ የሆነ ነገር ያለው ሰው የለም። ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 4:7 እንዳለው "ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ?"። አዳም እንኳን ከውድቀቱ በፊት የሚመልሰው ምላሽ "ምንም የለም!" ነው ። እግዚአብሔር ራሱ በመዝሙር 50፡12 ላይ "ዓለምና ሞላው የእኔ ነውና" ብሎ ተናግሯል። እኛ ይገባናል ብለን ልናቀርበው የምንችለው ነገር ሁሉ አስቀድሞ የእርሱ ነው። ታዲያ የእራሱ የሆነውን ነገር ለይገባኛል ጥያቄ አቅርበንለት ልናስደስተው እንችላለን ብለን እናስባለን?

ሰው ከእግዚአብሔር ይገባኛል ብሎ መጠየቅ የሚችለው ነገር አለመኖሩ በሉቃስ 17:10 ላይ በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ ክፍል ላይ የእግዚአብሔር ቃል ሰውን የእራሱ የሆነ ህይወት ከሌለው እና ምንም ማግኘት ከማይችለው ባሪያ ጋር ሲያነጻጽረው እንመለከታለን። ከዚህም "የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ" እኛ አሁንም "*የማንጠቅም* ባሪያዎች ነን" ማለት እንዳለብን እንማራለን። ኢየሱስ በሰጠው በዚህች ትንሽ ምሳሌ መሰረት ባሪያው የጌታውን ፈቃድ ባከናወነ ጊዜ ካገኘው ምስጋና ጋር ስንወዳደር የእግዚአብሔርን ምስጋና የማይገባን ነን። ደግሞም ይህንን አስተውሉ - ቁጥር 10 የሚናገረው አሁን ስላለንበት የወደቀ ማንነት

ሳይሆን የታዘዝነውን ሁሉ ባደረግንበት በዚያ ሰዓት ነው። ለእኛ የማይታሰብ ጉዳይ ቢሆንም ለአዳም ግን ከውድቀቱ በፊት ይህንን ማድረግ ይቻለው ነበር ። በሌላ አማርኛ በሉቃስ ላይ ያለው ቃል ለእኛ ቢጻፍም ከእኛ ይልቅ ለአዳም የበለጠ ተግባራዊ ነበር ምክኒያቱም እሱ በጽድቅ ማንነት ውስጥ ስለነበረ! አዳም እግዚአብሔርን ይገባኛል ማለት ካልቻለ ታዲያ እኛ እንዴት እንችላለን?

ስለዚህም የሚገባን ነገር አለ ብለን እንድናስብ የሚያደርገንን ጠንቅ ሀሳብ ማስወገድ አለብን- ከአስተምህሮዋችን፣ ከተግባራችን እና ከአስተሳሰባችን ሁሉ ይህንን ልናወጣው ይገባል። ይህንንም ማድረግ የምንችለው የተፈጥሯዊ ባህሪያችንን ውድቀት ስንረዳ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ይገባናል ብለን የምንጠይቀው ምንም እንደሌለ ስንረዳ ብቻ በጸጋ ላይ ያለንን መደገፍ እና እምነታችንን በጥንካሪያችን ላይ ማደርግን እናቆማለን። ያኔ ብቻ “አሦር አያድነንም፤ በፈረስ ላይ አንቀመጥም፤ ድሀ አደጉም በአንተ ዘንድ ምሕረትን ያገኛልና ከእንግዲህ ወዲህ ለእጆቻችን ሥራ። አምላኮቻችን ናችሁ አንላቸውም በሉት” (ሆሴዕ 14:3)።

## የመጀመሪያው ገነት

አዳም የፍጥረት ዘውድ መሆኑ ሌላኛው አመልካች እግዚአብሔር በምድር ላይ ከሰራው ስራ ሁሉ የሚበልጠውን ገነት የተባለ የአትክልት ስፍራ በኤደን ውስጥ ለአዳም መስራቱ ነው። አዳም በዚያ ስፍራ ይኖርም ይሰራም ነበር። እስከሚወድቅበት ጊዜ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር በዚያ ይመላለስ ነበረ።

የመጀመሪያዋ ገነት ምን አይነት እንደነበረች ለማሰብ እጅግ ከባድ ነው። የት እንደነበር እና የተመሰረተበት ምድር ምን አይነት እንደነበር ምንም እውቀት የለንም። ሞት፣ መከራ ወይንም ህመም በዚያ አልነበረም። ሁሉም ነገር ፍጹም እና አሁን ከምንኖርበት አለም የተለየ ነበር። አዳምም ፍጹም እና ፍጹም በሆነ መኖሪያ የሚኖር ነበር።

አዳም በሀጥያት ሲወድቅ ይህንን ሁሉ አጣ ። የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ የሆነችውን ውብ ስፍራ እና ከየትኛውም ቦታ በተለየ መልኩ እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት፣ ከእርሱም ጋር ህብረት ማድረግ የሚችልበትን ስፍራ አጣ ። ይህ ባለመታዘዝ የመውደቁ አሳዛኝ ኩነት ነው። እግዚአብሔር ከገነት አዳምን

ያስወጣው ላለመታዘዙ እየቀጣው እና እንደ ሀጥያተኛነቱ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ሊኖረው እንደማይችል ሊያሳየው ፈልጎ ነው።

አዳም እና ሄዋን ሀጥያት ሰርተው የተባረሩት ከመጀመሪያው ገነት ነው (ዘፍ 3:23-24) ። ይህ ገነት በምድር ቢሆንም የእነርሱ መባረር በሰማያዊው ገነት ለሀጥያተኞች ምንም ቦታ እንደሌለ ያሳያል። በሀጥያታቸው ምክንያት እነርሱ እና ዘራቸው ከህይወት ሁሉ ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ህብረት ሁሉ እና እግዚአብሔርን ከማገልገል ሁሉ ተከለከሉ። የእግዚአብሔርም ጸጋ ብቻ ወደ ሰማያዊው ገነት መግቢያ መንገዱን ይከፍታል።

ጸጋን ለተቀበሉ ሁሉ የሚመጣው ገነት ምን እንደሚመስል በመጀመሪያው ገነት ተመስሏል። ሁለቱም በታዎች አንድ አይነት ስም አላቸው (ራዕይ 2:7)። አንዳይነት ዛፍ በሁለቱም ቦታ ያድጋል (ራዕይ 2:7, ራዕይ 22:2)። በሁለተኛው ገነት ውስጥን መከራ፣ ህመም፣ ለቅሶ ወይም ሞት የለም (ራዕይ 21:4)። የመጀመሪያው ገነት ሰማይ ምን ሊመስል እንደሚችል ጭላንጭሉን እያሳየን አዳም በሀጥያት ያጣውን እኛ በጌታችን እና በአዳኛችን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እንደምናገኘው ያረጋግጥልናል።

የመጀመሪያዋ ገነት መኖር እግዚአብሔር አስቀድሞ የኤደን ገነትን ሲሰራት ሌላ የተሻለ ነገር በሃሳቡ እንዳለ ያመላክተናል። በመጀመሪያው ገነት ውስጥ የተጀመረው የእግዚአብሔር አስቀድሞ የተወሰነ ታሪክ ፍጻሜውን የሚያገኘው በሁሉተኛው ሰማያዊ ገነት ብቻ ነው። የእግዚአብሔር እቅድ እራሱን በፍጥረት፣ በሀጥያት፣ በጸጋ እና በድህነት በኩል ማክበር ነው ምክኒያቱም ከአላማው ውጪ የሚሆን አንዳች የለምና። የመጀመሪያው ገነት የሁለተኛው ገነት ቃል ኪዳን እና ጥላ ነው።

በክርስቶስ ኢየሱስ እና ደግሞ እንደ ኃይሉ ምስክርነት የሚመጣው ገነት ከነበረው ገነት የሚበልጥ ነው ። በሚመጣው ሰማያዊ ገነት ሀጥያትን የመስራት እድል እንኳን የለም ። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ክብራቸው ሆኖ ከህዝቡ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራል (ራዕይ 21:3) ። በዛም የተወደደውን ክርስቶስ ያዩታል። ይህ ከማስተዋል በላይ የሆነ ደስታ እና ሀሴት ነው።

## ሁለት ዛፎች

እግዚአብሔር ለአዳም እና ለሄዋን መኖሪያ እንዲሆንላቸው የኤደን ገነትን ሲሰጣቸው በውስጡ የህይወት ዛፍን እና መልካሙን እና ከክፉ የሚያሳውቅ ሁለት የተለዩ ዛፎችን አስቀምጠላቸው ። እነዚህ ዛፎች በገነት መሃል ላይ መሆናቸው ዛፎች ምን ያህል አስፈላጊ እንደነበሩ ያመለክትልናል (ዘፍ 2፡9)።

የተሰጠን መረጃ በጣም ጥቂት በመሆኑ ስለዛፎቹ የሚነሱትን ጥያቄዎች ሁሉ መመለስ ያዳግታል ። ለምሳሌ የህይወት ዛፍ ለሚበሉት ሁሉ በህይወት የመኖርን አቅም የመስጠት ኃይል ነበረው? የሚለው ጥያቄ አለ ። ይህንን ጥያቄ በመከተል ደግሞ ይህ ፍሬ እንዲህ አይነት ሀይል ካለው አዳም እና ሄዋን የማያቋርጥ ህይወት እንዲኖራቸው ከዛፉ መብላት የሚጠበቅባቸው አንዴ ነው ወይንስ በተደጋጋሚ? ክፉውን እና መልካሙን የሚለዩበት ዛፍ አዳም እና ሄዋንን እንደ መርዝ በስጋ ካልገደላቸው (ዘፍ 3:6) የህይወት ዛፍ ፍሬ በቀጥታ ህይወትን እንደማይሰጥ አመላካች ሊሆን አይችልም? የሚሉ ጥያቄዎችም ይከተላሉ ። ነገር ግን ቁጥር 22 ልዩ የሆነን ምልስ ይሰጠናል ። የህይወት ዛፍ የማቆየት ወይም ለአዳም የማያልቅን ህይወት የመስጠት አቅም *ከነበረው* ህይወትን የማጥፋት አቅም ከሌለው መልካሙን እና ክፉውን ከሚለየው ዛፍ በእጅጉ የተለየ ነበር ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ የሚያወራው ጥቂት በመሆኑ ምናልባትም እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች መመለስ አንችልም ይሆናል። ነገር ግን በመጀመሪያው ገነት ውስጥ ስለሚገኙት ሁለት ዛፎች አንድ ግልጽ የሆነ ነገር አለ እርሱም ሁለቱ ዛፎች ለአዳም "*ተቃርኖን* (antithesis/አንቲቴሲስ)" መወከላቸው ነው ። ይህ ተቃርኖ ደግሞ በእግዚአብሔር እና በሰይጣን፣ በክፋት እና በመልካም፣ በቤተክርስቲያን እና በአለም፣ በአማኝ እና በማያምን መካከል ያለው መለየት እና መገፋፋት ነው።

የእግዚአብሔር ህዝቦችም ከተቃርኖው አንጻር ያላቸው ጥሪ ለእግዚአብሔር እና ለህጉ "እሺ" የማለት እና፤ ለዲያቢሎስ እና ለሀጥያት ደግሞ "እንቢ" የማለት ነው። እነርሱ ከሚኖሩበት አለም መለየት ዋናው ተግባር ይህ ነው (2ኛ ቆሮ 6:14-18) ። ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ያለው ጥሪ ነው ።

በገነት ያሉት ሁለት ዛፎች ለአዳም እና ለሄዋን ተመሳሳይ ጥሪን አቅርበው ነበር። ከህይወት ዛፍ በመብላት (እንዴት እና መቼ የሚለው ምንም ለውጥ አያመጣም) ለእግዚአብሔር እሺ ይላሉ ። መልካሙን እና ክፉውን የሚለየውን ዛፍ ባለመብላት ሰይጣንን፣ ሀጥያትን እና አለመታዘዝን እምቢ ይላሉ። የማይበሉበትም ምክኒያት ይህ ነው ። ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ በስተቀረ ከእውቀት ዛፍ የማይበሉበት ሌላ ምክኒያት አልነበራቸውም ምክኒያቱም ዛፉ "ለመብላት ያማረ" እና "ለዐይንም ለማየት የሚያስጎመጅ" ነበርና።

አዳም እና ሄዋንም ከዛፉ ፍሬ በሉ በሀጥያትም ወደቁ። እኛም ሰይጣንን እሺ ስንል እግዚአብሔርንም እምቢ ስንል የእነርሱን የሀጥያት መንገድ እንከተላለን። ሆኖም ግን በሁለቱ ዛፎች የተመሰለው እና ለእነርሱ የነበረው ያሀ ጥሪ ዛሬም አልተቀየረም። ባለመቀየሩም መቤዡት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፤ ህይወቱን እግዚአብሔርን እና ለህጎቹ ሁሉ እሺ በማለት በኖረ፣ ከዚህም ጋር ታክሎ ለሀጥያት እና ለሰይጣን እምቢ በማለት በበረሀው ስፍራ ተፈትኖ ባሳየው በእርሱ ብቻ ይሆናል ።

## የሰይጣን ውሸት

እግዚአብሔር በኤደን ገነት ካስቀመጣቸው ሁለት ዛፎች ውስጥ አንዱ ክፉን እና መልካሙን የሚለየው ዛፍ ነው። አዳም እና ሄዋንም ከዚያ ዛፍ እንዳይበሉ ታዝዘው ነበር ። ሆኖም ግን በመብላታቸው ከእግዚአብሔር ደስታ ወደ ሀጥያት እና ሞት ወድቁ።

ዛፉ “መልካሙን እና ክፉውን የሚለይ ዛፍ” የተባለው ለምንድን ነው? ሰይጣን በዋሸው ውሸት ምክኒያት ይህ ጥያቄ መልስ ሊያገኝ ግድ ነው (ዘፍ 3:5) ። ሰይጣን “.... እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ....” አላቸው፤ አዳም እና ሄዋንም ይህን ውሸት ታዘዙ።

ሰይጣን የተናገረው ውሸት ነበር፤ እርሱም ሁል ጊዜ ይዋሻል ። ክፉን “በመቅመስ” እና እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ መልካም እና ክፉውን *ማወቅ* አንችልም። ሆኖም ግን ሰይጣን ይህን ውሸት ዛሬም ይናገራል ፤ አሁንም ደግሞ ሰዎች ለዚህ ጆሮዎቻቸውን ይሰጣሉ ። ሰይጣን ሰዎች ክፉ ምን እንደሆነ ያውቁ ዘንድ ክፉውን “መሞከር” እንድለባቸው ይነግራቸዋል ሰዎችም ደግሞ ይህንን በደስታ ይሰማሉ።

ይህ ትምህርት ኤልዛቤል በትያጥሮን ቤተክርስቲያን ያስተማረችው አስተምህሮ ነው (ራዕይ. 2:20-24) ። እኛ እንደተረዳነው እርሷ እና ተከታዮቿ “የሰይጣንን ጥልቅ ነገር” ለማወቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንዲዘሙቱ እና ለጣዖት የተሰዉ ነገሮችን እንዲበሉ አስተምረዋል (ቁ 20 ፣ 24) ።

ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸውን ከዚህ አለም ክፋት ሊጠብቋቸው እንደማያስፈልግ በሚሰሙበት ወቅት ይህንኑ ውሸት ሰዎች ይነግሯቸዋል ። ልጆቻቸው ወደ አለም ወጥተው አለም ምን እንደምትመስል ማወቅ አለባቸው እየተባሉ ይመከራሉ ። ልጆቻቸው አለምን ለማወቅ የአለምን መልክ መሞከር ወይንም መቅመስ

አለባቸው ብለው ቢናገሩም እኛ ወይም ልጆቻችን ግን መልካሙን እና ክፉውን የምንማረው በዚህ መንገድ አይደለም ።

መልካም እና ክፉውን የምናውቅበት እውነተኛው መንገድ ክፉውን በመቅመስ ሳይሆን ክፉን በመተው እና ከእርሱ በመሸሽ ነው ። ስለወደቀው ሰው እስኪ እናስብ ፤ መልካም እና ክፉውን ከሚለየው የእውቀት ዛፍ በልቶ ክፉውን እና መልካሙን መለየት *አልቻለም*። እግዚአብሔር ግን ከክፉ ሙሉ በሙሉ ልዩ ሆኖ ክፉትን እንደሚያውቅ እኛም ደግሞ እንዲሁ ልንሆን ይገባል ።

እንደገናም ጠላት ለማለት የፈለገው ይህንን ብቻ ሳይሆን አዳም እና ሄዋን ለእራሳቸው መልካም እና ክፉውን የ*መወሰን* መብት አላቸው ለማለትም ጭምር ነው። በዚህም አባባል "ክፉውን እና መልካሙን" ከዛፉ በመብላት ይረዳሉ። ሰይጣንም እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ አላቸው። የወደቀው ሰውም ሰይጣንን በመታዘዝ ውሸቱን ሰማ አሁንም ደግሞ ለእራሱ መልካምን እና ክፉውን መወሰኑን ይቀጥላል።

እግዚአብሔርም "እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" ማለቱ ይህንን ማመላከቱ ነው። በዚህም ሰው ለእግዚአብሔር ብቻ የተገባውን ክፉውን እና መልካሙን የመለየትን መብት ለእራሱ እንደሚገባው ቆጥሯል የሚለው ተገለጠ ። ይህንንም በማድረጉ ሰው ከህይወት ዛፍ ከዚህ በኃላ ሊበላ አይገባውም ። ከዚህ በኃላ ወደ ህይወት ዛፍ እጁን ሊሰድድ እና በግልጽ በእግዚአብሔር ላይ አምጾ ለዘላለም ሊኖር አይችልም። ስለዚህም እግዚአብሔር ከገነት እና ከዚያ የህይወት ዛፍ አባረረው።

በሰው ዘር ላይ የመጣው ክፋት ሁሉ በመጀመሪያ ሄዋን እርሷንም ተከትሎ አዳም የሰይጣንን ውሸት በመስማቱ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እውነቱ ከተነገረን ወዲህ ከዚህ በኃላ የሰይጣንን ውሸት አንስማ ይልቁንም መልካሙን እና ክፉውን በትክክለኛው መንገድ ብቻ እርሱም እግዚአብሔር የሚለውን በመስማት እና እራሳችንን ከክፋት በሙሉ ልብ በመሸሽ እንለይ።

## መልካሙን እና ክፉውን የሚለይ ዛፍ

በአዳም እና ሄዋን የመጀመሪያ ቤት፣ ኤደን ገነት ውስጥ የተተከሉት ሁሉት ዛፎች የኖሩበትን ምክንያት አብራርተናል። አሁን ደግሞ መልካሙን እና ክፉውን የሚለየው ዛፍ አላማን ዘዳግም 8:2-3 ላይ ባለው የቃሉ ብርሀን መሰረት የተወሰነ ነገር እንበል። መልካሙን እና ክፉውን የሚለየው ዛፍ የተጻፈልን በዚህ ክፍል ውስጥ

የሚገኘውን መንፈሳዊ መርህ ለማስተማር ነው ብለን እናምናለን። *"አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ። ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳይኖር ያስታውቅህ ዘንድ አስጨነቀህ፥ አስራበህም፥ አንተም ያላወቅኸውን አባቶችህም ያላወቁትን መና አበላህ።"*

የዛፉ ፍሬ በእራሱ መልካም እንደነበር በማስታወስ እንጀምር። ሄዋን ዛፉን ስታየው የተመለከተችው ምልከታ እውነት አይደለም ብሎ ለማሰብ ምንም ምክንያት የለንም። "ለምግብነት ጥሩ" "ለአይንም የሚማርክ" እና "ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች" (ዘፍ 3:6) ስለዚህ አስቀድማ የእግዚአብሔርን ህግ በመቃረን ስትመኘው ነበር። *ታዲያ እግዚአብሔር ይህንን ዛፍ እንዳይበሉ ለምን አዘዘ?*

መልሱ በዘዳግም 8:2-3 ላይ ተቀምጦልናል። እግዚአብሔር አዳም እና ሄዋንን ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስተምራቸው ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር ህይወታችን በአካል ከመኖር በላይ ፣ በምግብ ከምንጠብቀው ሰውነታችን በላይ ነው የሚለውን ሊያስተምራቸው ፈልጎ ነበር። ለሰው ህይወት ማለት ከህያው እግዚአብሔር ጋር መኖር እና ለቃሉ መገዛት ነው።

ሆመር ሆክሴማ እንዳለው "ይሃ ዛፍ ለአዳም መብልን አቅረበለት። ይህም ያማረ፣ በምድር በእራሷ የተዘጋጀ ምግብ ነበር። ነገር ግን ይህንን ምግብ ሊመገበው የማይችለው ነበር! የእግዚአብሔርም ቃል አዘዘው ※※※ ከዚህች አንዲት ዛፍ ብቻ እንዲታቀብ። ይህንን መልካሙን እና ክፉውን ከሚለየው ዛፍ በመቆጠብ አዳም በህይወቱ የላቀ መንፈሳዊ ገጽታን ይለማመድ ነበር፤ ጌታው እና አምላኩ ለሆነው ለእርሱ በወዳጅነት እና በአገልጋይነት እንዲታዘዝ እና በዚህም ደግሞ በእውነት እንዲኖር ይሆንለት ነበር።"[2]

አዳም እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ የስጋን ምኞት ማርካት መረጠ። እርሱ (ከሄዋን) ጋር ሆዱ አምላኩ የነበረ እና "አሳባቸው ምድራዊ ነው" (ፊሊ 3:19) ከተባሉት ሰዎች ሁሉ የመጀመሪያው ነበር። ስለዚህም የሰው ልጅ እስካሁን ድረስ የሰጋውን እና የአእምሮውን ፈቃድ እያረካ በእግዚአብሔር የህይወት ስጦታ ላይ ባለመደገፍ ይኖራል ፤አሁንም ቢሆን ያለ እግዚአብሔር ቃል በምግብ ብቻ ለመኖር እየሞከረ አለ።

ነገር ግን አዳም በወደቀበት በዚያ ክርስቶስ አልወደቀም። ታዲያ አሁን ክርስቶስ ሰው በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር (ማቴ 4:4) ከመናገር አልፎ ለአርባ ቀን በበርሀ ውስጥ በርሃብ በመቀጣት በዚሁ መርህ ጸንቶ

አሳየን።  የበረሃውን ድንጋዮች በሙሉ ወደ እንጀራ ቀይሮ የአለምን ሁሉ ረሃብ ማጥገብ ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ አልበለጠበትም ። በአሁን ጊዜ የምትገኘው ቤተክርስቲያን ይህንን ታስብ ይሆን?

ነገር ግን በዚያ በርሃ ውስጥ የተከሰተው ታሪክ እውነተኛ የክርስቶስ ኢየሱስ ሙሉ አገልግሎት ነው። ሞቱ እንኳን እግዚአብሔርን መታዘዝ በምድር ላይ ህይወትን ከማስቀጠል እና ከምንም ነገር በላይ እንደሆነ ያሳየበት ምስክርነቱ ነው። እስከሞት ድረስ ታዘዘ። በዚህም ምርጦቹን ከወደቁት የአዳም ልጆች መካከል ተቤዠ።

## የህይወት ዛፍ

እግዚአብሔር በኤደን ገነት ውስጥ ከተከለው ልዩ ዛፍ መካከል ሌላኛው ደግሞ የህይወት ዛፍ ነው። ይህም ለአዳም እና ለሄዋን በእጅጉ ሊጠቅማቸው የሚችል ዛፍ ነበረ ።

ይህ ዛፍ ምድራዊ ህይወትን የመስጠት ኃይል ነበረው የሚል ጥያቄ አለ። እግዚአብሔር አዳም እና ሄዋንን እንዳይበሉ ሲዘጋባቸው ዛፉ በእውነትም ህይወትን የመስጠት ኃይል እንዳለው ሊያመላከት ይችላል (ዘፍ 3:22)። ሆኖም ግን ይህ የዛፉ ዋና አላማ አልነበረም።

ይህ ዛፍ ለአዳም እና ለሄዋን እግዚአብሔርን የመታዘዝ ህይወት ያዘለውን እውነት የሚያመላከት ነበር። ይህንንም ህጉ ይመሰክራል (ዛፉ በእራሱ ህይወትን መስጠት ባይችልም እንኳን) (ገላ 3:21) ። አዳም እና ሄዋን አለመታዘዝን ሲመርጡ “መኖር” የሚለው ቃል ትክክለኛውን ትርጉም መኖር አቆሙ። መሞት ስለነበረባቸው እግዚአብሔርም ከወሰደባቸው ሌሎች ነገሮች ጋር የህይወትን ዛፍ የሙብላት ሙብትን ነጠቃቸው።

የህይወት ዛፍ ለእኛም እጅግ ወሳኝ እና ጠቃሚ የሆነውን እውነታ ያመላክታል ፤ እርሱም መታዘዝ ክፉትን መተው ወይንም እግዚአብሔር የከለከለውን ነገር መተው ብቻ አለመሆኑ ነው። ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ ያልተለወጠ ግን መጠጥ ያቆመ ጠጪ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እየኖረ ባይሆንም እየኖረ ነው ማለት እንችላለን ማለት ነው።

መታዘዝ ሁልጊዜም አዎንታዊ ገጽታ አለው ይህንንም በቀደመው ክፍል ለእግዚአብሔር እሺ ማለት ብለን አብራርተነዋል። እግዚአብሔርን ሳንወድድ እና እርሱን ለማስደሰት ፍላጎት ሳይኖረን መታዘዝ እግዚአብሔርን

ማሳዘን ነው። እግዚአብሔርን ሳይወድዱ መስዋት ማቅረብ በእግዚአብሔር ፊት ሰውን እንደ መግደል ወይንም የውሻን ጭንቅላት እንደመቅላት መሆኑን ኢሳይያስ ይናገራል (ኢሳ 66፡3)። ጳውሎስም "በእምነት ያልሆነ ሁሉ ሀጥያት ነው" ሲል ይህንኑ ያስታውሰናል (ሮሜ 14:23)።

እግዚአብሔርን የማይወድዱት እና በሙሉ ልባቸው፣ ሀሳባቸው፣ ነፍሳቸው እና ኃይላቸው እሺ የማይሉት መልካምን ነገር አያደርጉም። ለእግዚአብሔር ህግ በውጫዊ ሁናቴዎቻቸው ብቻ ምላሽ መስጠታቸው ህጉን እንደሚያውቁ ነገር ግን እግዚአብሔርን እንደማያውቁ እና እንደማይወዱ ያሳያል። እንደዚህ በመታዘዛቸው ፍርዳቸውን ብቻ ይጨምራሉ። እውነተኛ መታዘዝ *ከሀጥያት* መራቅ ነው። ነገር ግን *ወደ* እግዚአብሔር በሙሉ ልባችን እና ኃይላችን መመለስም ነው።

በአዲሱ ፍጥረት ውስጥ ያለው የህይወት ዛፍ ብቻ ነው (ራዕይ 22:2) ። መልካሙን እና ክፉን የሚለየው ዛፍ በዚያ አይኖርም። ሀጥያት፣ ሞት እና ሰይጣን በዚያ አይኖሩም መታዘዛችንም ለእነርሱ እምቢ ማለትን የሚያጠቃልል አይሆንም ። መታዘዛችን በንጽሕና እና በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን የምንወድድበት እና የምናገለግልበት ነው።

የህይወት ዛፍ ለእኛ ታዲያ ክርስቶስን ይወክላል። ለአዳም እና ለሄዋን የህይወት ምንጫቸው እንደነበረው ዛፍ ለእኛም የዘላለም ህይወት ምንጫችን ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ያለን መታዘዝ ወደ ፍጻሜ የሚደርሰው በክርስቶስ በኩል ነው ። እኛን ወክሎ ለእግዚአብሔር እስከሞት ድረስ የታዘዘ እርሱ ነው። እርሱን እንመገባለን፣ ነፍሳችንም እስከ ዘላለም ህይወት ድረስ ያበለጽጋታል በዚህም እኛም ለእግዚአብሔር በሁለንተናችን ሁሉ እሺ ማለት እንችላለን። በአዲሱ ፍጥረት ከክርስቶስ ኢየሱስ በመመገብ እና በመርካት እግዚአብሔርን እምቢ የማለት እድልም አይኖርም።

አስገራሚ ነው፣ አይደል?

## የሰው ውድቀት

በአለም ታሪክ ውስጥ እጅግ አሳዛኝ የሆነው ታሪክ በጀርመን የተከሰተው የአይሁዶች እልቂት ፣ የአለም ጦርነት ፣ ታላቁ ዲፕረሽን ፣ አልያም ደግሞ ሰው ሰራሽ ወይንም የተፈጥሮ አደጋዎች ሳይሆን የሰው በሀጥያት መውደቅ ነው። ይህ አንድ ኹነት በአለም ውስጥ ላለው ችጋር፣ መከራ እና ጉስቁልና ምክንያት ነው። የሰው

ልጅ ባይወድቅ ኖሮ ሞት፣ በሽታ፣ ጦርነት፣ ሆስፒታል፣ ህመም፣ ወይንም ከእግዚአብሔር ጋር መለያየት አይኖርም ነበር።

የሰው ልጅ ውድቀት ይህንን ሁሉ እንዳመጣ እናስተውል። እግዚአብሔር የፍቅር እና የምህረት አምላክ ቢሆን ኖሮ እንደዚህ አይነት ችግር አይኖርም ብለን በእግዚአብሔር ላይ አናማርር። እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ብቻውን ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ሊወቀስ ይገባል።

ይህ ጉስቁልና ወደ እኛ የመጣው አዳም ሀጥያት ስለሰራ ብቻ ሳይሆን የእርሱ ሀጥያት የሁሉም ሀጥያት ስለሆነ ነው (ሮሜ 5:12)። እርሱ ሀጥያትን ስለሰራ እኛም አብረነው ሀጥያትን ስለሰራን ሞት እና ሌሎች የሀጥያት ውጤቶች ሁሉ ወደ እያንዳንዳችን መጣ "እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።"

በዘፍጥረት 3 ላይ የተጠቀሰው ክፍል ታሪካዊ እውነታ አይደለም በመባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት ሊሻር አይችልም። ይህንን ካደረግን ሰው እንዲህ የሆነበትን ፣ የሚኖርበት አለም ሁኔታ እና ክርስቶስ እንደ ሁለተኛ አዳም የመጣበትን ምክኒያት ማብራራት አንችልም።

ከዚህ በተጨማሪ ስለወድቀቱ ልናውቃቸው የሚገቡ ሌሎች ወሳኝነት ያላቸው ጉዳዮች አሉ።

አንደኛው በመጀመሪያ ሀጥያት የሰራችው ሄዋን በመሆኗ ምክኒያት ሴት በቤተክርስቲያን ውስጥ መገዛት (1ኛ ጢሞ 2:11-14) እና በወሊድ ወቅት እንድትሰቃይ ሆናለች (ዘፍ 3:16)።

ሁለተኛው ደግሞ የመጀመሪያው ሀጥያት የተፈጸመው በሰይጣን ጣልቃ ገብነት ነው። በውሸቱ እና በማታለሉ አዳም፣ ሄዋንን እና ትውልዳቸውን ገደለ (ዩሀንስ 8:44) ። የእርሱን ውሸት በፈቃዳቸው በመስማታቸው ለውድቀቱ እና ውድቀትን ለተከተለው ውጤት ተጠያቂ ናቸው።

ሦስተኛ የሰው ልጅ በመውደቁ ምክኒያት እግዚአብሔርን ስለመንፈሳዊ ሁኔታው ሊከሰው አይችልም። ሁሉም ሰው በሀጥያት ምክንያት "ሞቶ" ቢወለድም እግዚአብሔር ሰውን ፍጹም አድርጎ በመፍጠር ፍጹም የሆነ (እኛን ከመወከል አንጻር) ተወካያችንን አዳም ተሰጥቶናል። አዳምም በፈቃዱ እግዚአብሔርን በመቃረን እግዚአብሔር የሰጠውን መልካም ስጦታ ሁሉ አውጥቶ ወረወረ።

አራተኛ ሰው ዛሬም የሚሰማው እና የሚያምነው ቀድሞ የወደቀበትን "እንደ እግዚአብሄር እንድትሆኑ......" የሚለውን ያንኑ ውሸት ነው (ዘፍ 3:5) ። የእራሱን "ነጻ ፈቃድ" በማጉላት እና የህይወቱ ደራሲ እራሱ እንደሆነ

በእግዚአብሔር የለሽ አስተምህሮዎቹ ፣ አስተሳሰቦቹ ፣ እና የኑሮ ዘይቤዎቹ ውስጥ በማጽናት በራሱ ላይ የእራሱ ህግ እንደሆነ በማስመሰል የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት እና ገዢነት ይክዳል። ይህም ዛሪም የሰይጣንን ውሸት እንደሚሰማ ያሳያል።

ከአዳም ጋር እንደወደክ፣ የእርሱም ውድቀት የሰው ዘር በሙሉ ብቻ ሳይሆን የግልህም መውደቅ እንደሆነ ታምናለህ? ይህንን ካመንክ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻውን ሊያድነን እንደሚችልበትን ምክኒያት እና በእርሱም ማመን እንዳለብን ታውቃለህ።

## ሀጥያት እና መዘዙ

ብዙሀኑ አለም በአስፈሪ ሁኔታ እንዳለች ይስማማል። በአለም ላይም ብጥብጥ እና ውጊያ ሰፍኗል፤ ወንጀል እየጨመረ መጥቷል። በዕፅ ፣ በአሸባሪነት እና በብጥብጦች ጋርም “ጦርነት” ላይ ነን። ፍጥረት እራሱ እየተጎሳቆለ መጣ፣ የአለም አየር ንብረትም እንዲሁ መልኩን እየቀየረ ነው።

አንዳንዶች ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ የሚገኘው በመንግስታት ወይም በመንግስታዊ ፖሊሲ ላይ ፣ በተፈጥሮ እውቀት ዙሪያ እና በትምህርት ላይ ስር ነቀል ለውጥ ሲመጣ ነው ያላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ለውጡ እርግጥ እንዲሆን ሰዎች በቂ ትምህርት ፣ ቤት ፣ እና ለህይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንዲያገኙ ብዙ ገንዘብ መፍሰስ አለበት ይላሉ። ያኔ ብቻ የተሻለ ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብለው ያምናሉ።

አብዛኞቹ ሰዎች ሰው “የልብ ችግር” እንዳለበት ለማየት አይፈልጉም። ይህ የልብ ችግር ከወድቀት እና ከመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳም እና ሄዋን አለመታዘዝ የጀመረ ነው። እነዚህ ሁለት ሰዎችም የተፈጠሩት ፍጹም እና እግዚአብሔርን ያለሀጥያት የማገልገል እና የመውደድ አቅም የነበራቸው ሆነው ነበር።

ነገር ግን አዳም ከተከለከለው ዛፍ በመብላት ሀጥያትን ሰራ (ዘፍ 3) ። የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በእባብ ተመስሎ የመጣውን የሰይጣንን ውሸት አስተናገዱ (ዘፍ 3:1-5, ራዕይ 12:9) ። ሰውም እንደ እግዚአብሔርን መሆን እንደሚችል አመነ።

እግዚአብሔር አዳምን እንዳያደርግ ያስጠነቀቀውም ይሃ ቅጣት አዳም ሀጥያት በእርሱ ላይ ተፈጸመበት፥ አዳምም ሞተ። ይህ የአዳምን በስጋዊ ኑሮ ስለለወጠው መጨረሻው መቃብር ሆነ። ይህም የመዳን መንገድ እስካልተዘጋጀ ድረስ ለዘላለም በገሀንም ውስጥ መቃጠልን አመጣ ማለት ነው።

የአዳም የሀጥያት መዘዝ በሰው ልጅ ሁሉ ላይ ከባድ ውጤትን አስከትሏል ። አዳም የሁሉም ወኪል እና የመጀመሪያ አባት በመሆኑ የእርሱ አንድ ሀጥያት በሁሉም ላይ ሞትን አመጣ (ሮሜ 5:12)። እጅግ የሚያሳዝነውም ውጤት ሁሉም ሰው በመንፈሱ ሙት እና መልካምን ማድረግ የተሳነው ሆኖ መወለዱ ነው (ሮሜ 3:10-19) ።

የሰው ልጅ የልብ ችግር "አጠቃላይ (መላ) ብልሹነት" ይባላል። ይህም በእግዚአብሔር ፊት ምንም አይነት መልካም ለማድረግ አለመቻል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ "ድንጋይ ልብ" እና "ክፉ ልብ" ይናገራል (ህዝ 11፡19 ፣ ኤር 16:12) ። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉ የድንጋይ ልብ ስላለው ይህ የችግሮቹ ሁሉ መንሳኤ ነው።

ይህ የሀጥያት ውጤት በአለም ላይ ያለን ሰውን ብቻ ሳይሆን በሚመጣው ምድር ላይ ያለውን ተስፋም አብሮት ያጨልማል። ሰውም እንደገና ካልተወለደ በቀር ሰማያዊውን መንግሰት ሊያይ አይችልም (ዩሀንስ 3:3)። የሰው ልጅም ህይወት እንደገና እንዲባረክ ከእግዚአብሔር ብቻ ሊገኝ የሚችለው አዲስ ህይወት እና አዲስ ወይም "ንጹህ ልብ" ያስፈልገዋል (መዝ 51:10) ።

ለክፋት እና ለሃጥያት መዘዝ መገባደጃ የሚሆነው እግዚአብሔር ታላቅ የጸጋ ስራ እርሱም የህዝቡ መታደስ እና ዳግም መፈጠር ሲጠናቀቅ ብቻ ነው። በሀጥያት ምክንያት ይህቺ የምንኖርባት አለም እራሷ መንጻት ይኖርባታል ከዚያም ደግሞ ዘላለማዊው የክርስቶስ መንግስት ሊመጣ ያስፈልጋል። ፖለቲካ፣ ትምህርት፣ እና ማህበራዊ ታሃድሶ ይህንን ለውጥ ሊያመጣ በጭራሽ አይችልም።

## የመጀመሪያው (ዋናው) ሀጥያት

መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ሀጥያት ባንሰራ እና ምንም ትክክል ያልሆነ ነገርን ባናደርግ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ሀጥያተኞች መሆናችንን እንደማይቀር ያስተምረናል ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የ"*የመጀመሪያው ሀጥያት"* አስተምህሮ ነው።

ዋና ሀጥያት የሚለውን ስትሰማ የሚያመላክተው ወደ አዳም ሀጥያት እና ደግሞ እግዚአብሔር እኛን ለአዳም ሀጥያት ተጠያቂ እንዳደረገን ነው። እርሱ ባለመታዘዙ ሀጥያተኛ እንደነበረ ሁሉ እናም እንደርሱ ሀጥያተኞች

ነን ደግሞም ለዚህ እንቀጣለን። እግዚአብሔር በመጀመሪያው ሀጥያት እንደፈረደው ሁሉ በመተላለፋችን እና በሀጥያታችንም እየተቀጣን ሞተን ተወለድን (ዘፍ 2:17)።

የመጀመሪያው ሀጥያት አስተምህሮን በ ሮሜ 5:12 ታገኙታላችሁ። በክፍሉ አዳም እንዳጠፋ እና በእርሱም ምክንያት ሞት ወደ ሰው ልጅ ሁሉ እንደመጣ እንረዳለን። ይህ ክፍል ሁሉም ሀጥያትን ሲሰራ ሞት ይመጣል ሳይሆን ሁሉም ሀጥያተኛ ስለሆነ አስቀድሞ ሞት ወደ ሰው ልጅ መጥቷል እንደሚል አስተውል። አስቀድሞ፣ የሰው ልጅ ሳይወለድ በፊት ሀጥያትን ሰርቷል ስለዚህ ሲወለድም በመታለለፍ እና በሀጥያት ውስጥ ነው። ሰው ሁሉ በሀጥያት እንዲወለድ መቼ ሀጥያትን ሰራ? ያለው ብቸኛ መልስ በሮሜ 5:12 ላይ የሚገኘው መልስ ነው እርሱም ሁሉም በአዳም በኩል ሃጥያትን ሰርቷል የሚለው ነው።

*የመጀመሪያው ሀጥያት* ሁለት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው በአዳም በኩል ሁሉም ሰው ሀጥያት መስራቱ እና በእርሱ ሀጥያት ሁሉም ሀጥያተኛ መሆኑ ነው። ይህ ብዙውን ጊዜ "*የመጀመሪያው ጥፋት*" ይባላል። ይህም ደግሞ አዳም በእግዚአብሔር ፊት የሰው ሁሉ ወኪል ስለነበር ለሰው ልጅ ሁሉ ተላልፏል። ሁለተኛው ሰው ሳይወለድ በፊትም ጥፋተኛ ስለነበር ወደ ምድር ሲመጣ የሀጥያት ቅጣት የሆነውን ይህ የዘላለም ሞትን ሊቀበል ይመጣል ። በመተላለፍ እና በሀጥያት ሞተው ተወልደዋል (ኤፌ 2:1)። ሲወለዱ የሚቀበሉት ይሄ ቅጣት የመጀመሪያው ሀጥያት አካል ነው ። ይህም ደግሞ "የመጀመሪያው ብክለት" ወይንም "መላ ብልሹነት (ዲፕራቪቲ)" ይባላል።

ብዙ ሰዎች ይህ አስተምህሮ ፍትሀዊ አይድለም በማለት መቀበል አይፈልጉም። ነገር ግን ይህ በእውነት ፍትሃዊ አስተምህሮ ነው ። በሌሎች ብዙ የህይወታችን ጉዳዮች ላይ ፍትሃዊ አይደለም ሳንል ለሌሎች ኃላፊነትን እንወስዳለን። የፖለቲካ መሪዎቻችን ህግን ያወጣሉ እኛም ለእነዚህ ህጎች ኃላፊነቱን እንወስዳለን። ወላጆች ለልጆቻቸው በህሪ ሀላፊነቱን ይወስዳሉ። ኃላፊነትን መውሰድ የሰው ልጅ ህይወት አንድ አካል ነው። ይህ ደግሞ በደህንነትም ጭምር ይሰራል። ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ አዳኝነቱ የእኛን ኃላፊነት መቀበሉ ፍትሃዊ አይደለም ብለን ስናጉረመርም አንገኝም። ደህንነታችንም ሀጥያት በአዳም በኩል ወደ እኛ በመጣበት ተመሳሳይ መንገድ በክርስቶስ በኩል መጥቶልናል።

*የመጀመሪያ ሀጥያት* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ ወሳኝ አስተምህሮ ነው። ይህ አስተምህሮ በግላዊ ህይወት ውስጥም እጅግ አስፈላጊነት ያለው ነው። የመጀመሪያው ሀጥያት እንደሀጥያተኝነታችን ምን ያህል የጠፋን እንደሆንን እና ከክርስቶስ ኢየሱስ ውጪ መዳን በየትኛውም መንገድ ማግኘት እንደማንችል ያሳየናል።

በዚህ አስተምህሮ መሰረት አሁን ላይ ሀጥያትን ባንሰራ እንኳን እግዚአብሔር እንደሚቆጣን እና ለዘላለም እንደሚቀጣን እንረዳለን። ይህ ደግሞ ከክርስቶስ መስቀል ውጪ ለመዳን ሌላ የትም ልንሄድ የምንችልበት ቦታ እንደሌለ ያስተምረናል።

የመጀመሪያውን ሀጥያት ይዘህ እንደተወልድክ ታውቃለህ? ትንንሽ ልጆችህ እንኳን ከውልደታቸው ጀመሮ በዚህ እንደተበከሉ ታውቃለህ? ለዚህ አስከፊ በሽታ ብቸኛው ፈውስ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነስ ታውቃለህ? ድነትን ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ እና በእርሱ ብቻ እንድናምን የሚጣራው ለዚሁ ነው ።

## መላ ብሉሽነት

አብዛኞቹ አንባቢያኖቻችን አንዳንድ ጊዜ "የጸጋ አተምህሮት" ተብሎ የሚጠራውን የካልቪኒዝም አምስት ነጥቦችን ያውቃሉ ። እነዚህ አምስት እውነታዎች አንድላይ እግዚአብሔር በድነት ውስጥ ያለውን ሉዓላዊነትን፣ በሌላ አነጋገር ድነት ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር እንጂ በእኛ ፈቃድ ወይም ስራ ላይ የተደገፈ እንዳልሆነ ያስተምራሉ።

ከእነዚህ አምስት ነጥቦች የመጀመሪያው "መላ ብልሹነት" ነው። ይህም ድነት ከእግዚአብሔር እና ከጸጋው ብቻ የሆነበትን ምክንያት ያሳያል።

*ብልሹነት* የሚለው ቃል ሀጥያታችንን እና ክፋታችንን ይገልጽልናል። ይህንን ቃል የምንጠቀመው በእግዚአብሔር ፊት ክፉ መሆናችንን እና ከእርሱ ድነት እንደሚያስፈልገን አጽኖት ለመስጠት ነው።

ብልሹነት ሙሉ  በሙሉ ነው ስንል ሦስት ነገሮችን ማለታችን ነው።

የመጀመሪያው ከክርስቶስ በስተቀር ሁሉም ሰው ክፉ እና ነውር ያለበት ነው (መዝ 14፡2-3) ማለታችን ነው።

ሁለትኛ ሰው ሁሉ በሁሉም መንገድ ብልሹ ነው ። በእግዚአብሔር ፊት ስራቸው ብቻ ሳይሆን ሀሳባቸው ፣ ፈቃዳቸው (ምርጫቸው እና ፍላጎታቸው) ፣ ስሜቶቻቸው እና ልባቸውም ጭምር ክፉ ነው (ዘፍ 6:5 ፣ ኤፌ 2፡3 ፣ 4:22 ፣ ኤር 17:9) ። ፈቃዳቸው ብልሹ መሆኑም በጣም ዋና ነገር ነው ። ምክንያቱም ያለጸጋው ማንም መዳንን መምረጥ አለመቻሉ ነው። መዳንም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በሰው ፈቃድ ሊሆን አይችልም።

ሦስተኛ ሁሉም ሰው በሁሉም ረገድ ሙሉ በሙሉ ብልሹ (ዲፕሬቭድ) ናቸው። ፈቃዱ፣ ልቡ እና የተቀረው ማንነቱ ብልሹነት በገሚስ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ነው ። የሰው ልጅ መላ ባህሪው በየትኛውም መልኩ *መልካምነት* የለውም። ይህ እውነት ብዙ ጊዜ በመካድ እና በሰው ልብ ውስጥ ብዙ ክፋት ቢኖርም በውስጡ ጥቂት መልካምነት *"በብርታታችን ውስጥ ጥቂት ክፋት በክፋታችን ውስጥ ደግሞ ጥቂት መልካምነት"* አለ የሚል ምልከታ ይሰጣል። በተለይም ይህ ሀሳብ ከሰው መዳን ጋር ተያይዞ ይቀርባል። ሰው እራሱን ማዳን አይችልም ነገር ግን መዳንን *መምረጥ* የሚያስችለው በቂ መልካምነት በውስጡ አለ ይላሉ።

የሰዎች ብዙ ተግባር በሌሎች ሰዎች ግምገማ መልካም ተብሎ ሊቆጠር እንደሚችል አንክድም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ክፉ ነው ብሎ ፈርዶበታል። በእርሱ ፊት ማንም ሰው መልካም ሊያደርግ ሆነ ምንም አይነት መልካም የማድረግ ፍላጎት ሊኖረው አይችልም። እግዚአብሔር የሚፈርደው ከእኛ ከፍ ባለ መለኪያ ሲሆን የሚጠይቀውም ሁሉን ነገር በእምነት ለእርሱ ክብር እንዲደረግ ነው። እንዲህ ካልሆነ መልካም አይደለም ማለት ነው(ሮሜ 14:23, 1ኛ ቆሮ 10:31)።

በሰው ዘር ሁሉ ላይ ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ በመጽሐፍ ውስጥ በተደገመው ብቸኛው በመዝሙር ላይ ተጽፏል (መዝ 53 ይመ) ። መዝ 14 በግልጽ እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሚፈርደው እንዲህ እንደሆነ ይናገራል "የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ፤ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ" (ቁጥ 2) ። ፍርዱስ ምንድን ነው? "ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም" (ቁጥ 3) ።

ኤፌሶን 2:1 የመላ ብልሹነት *አስተምህሮ* በበደላችን እና በሀጥያታችን ሙታን ነበርን ብሎ ይጠቀልለዋል። የእኛ ሁኔታ ከዚህ የባሰ ሊሆን አይችልም። በሀጥያታችን ሞተናል በውስጣችንም ጥቂት የመንፈሳዊ መነሳሳት የለም በሀጥያታችን ሞተናልና። እኛ ሙሉ በሙሉ የተበላሸን (ዲፕሬቭድ) ነን።

በጸጋው ይህንን መረዳት ስንችል የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ምን ያህል እንደሚያስፈልገንም እናስተውላለንና ምክኒያቱም መላ ብልሹነት ያለባቸውን ሀጥያተኞች ማንም ሊያድን ስለማይችል ነው።

## የሰው ነጻ "ፈቃድ"

የፕሮቴስታንት ተሓድሶ በጀመረ ጊዜ ማርቲን ሉተር *"የፈቃድ እስራት (The bondage of the Will.)"* የሚል መጽሐፍን ጻፈ። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ኤራስመስን እና አስተምህሮውን ለመመከት ነው።

አስተምህሮውም ሰው መዳኑን የመምረጥ እና ያለመምረጥ መብት አለው ፤ የሰው ፈቃድ “ነጻ” ነው የሚል ነው ። ሉተር ለኤራስመስ በመጽሐፉ  የነጻ ፈቃድ ሀሳብ በተሓድሶ አስተምህሮ ውስጥ እጅግ ዋና ርዕስ እንደሆነ ያነሳለታል። ለኤራስመስም እንዲህ አለው ” አንተ ተጨማሪ በሆኑ እና ጥቃቅን በሆኑ ጉዳዮች እንደ ጳጳስነት፣ የንስሀ ስፍራ፣ የአመጋገብ ስርዓት እና በመሳሰሉት ተራ ጉዳዮች አላሳሰብከኝም። ሆኖም ግን ነገሮች ሁሉ የዞሩበትን ማጠፊያ አንተ ብቻ ተመለከትከው እርሱ ላይም አነጣጠርክ።”[3]

የኤራስመስን አስተምሀሮ በመቃወም ሉተር የወደቀው ሰው እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን እና የሚያረካውን ነገር ለማድረግ ነጻ አይደለም። ይልቁንም የመምረጥ ብቃቱ ከሀጥያት ጋር የታሰረ ነው ይላል። ሉተር የጻፈው ይህንን ቢሆንም ስለ ነጻ ፈቃድ የሚያወራው የኤራስመስ አስተምህሮ የአብዛኞች ፕሮቴስታንት አስተምህሮ ነው።

እኛም ከሉተር ጋር የሰው ፈቃድ ከሀጥያት ጋር የታሰረ ነው ደግሞም መልካም ነገር ማደረግ አይችልም ብቻ ሳይሆን መልካምን የማድረግ ፍላጎትም ሊኖረው አይችልም ብለን እናምናለን (ሮሜ 8:7-8) ። በተለይም ሰው ታላቁን መልካም ምርጫ እርሱም እግዚአብሔርን እና ክርስቶስን መምረጥ አይችልም። ስለዚህም ሰው ከላይ ካልተሰጠው በስተቀር በክርስቶስ ኢየሱስ ሊያምን አይችልም (ከ ዩሀ 6:44 ጋር ያነጻጽሩ) ።

የሰው ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአብሔር አስቀድሞ ወስኗቸው ለድህነት ያደርሳቸዋል ብለን እናምናለን (ሐዋ 13:48, ፊሊ 2:13) ። ሰው መዳኑን መምረጥ ካልቻለ እግዚአብሔር ለእርሱ ይመርጥለታል ማለት ነው። ይህ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ማን መዳን እንዳለበት እና ለሚድኑት ሰዎች ሁሉ በእራሱ ሉዓላዊ እና ኃያል ጸጋ ድህነትን እንደሚባርክላቸው እናያለን።

የነጻ ፈቃድ የሀሰት አስተምህሮ በርካታ እውነታዎችን ይክዳል። በመጀመሪያ አስቀድሞ መወሰንን ይክዳል። አስቀድሞ መወሰን ማለን የእግዚአብሔር ፈቃድ (የእግዚአብሔር ምርጫ) ሁሉን ነገር፣ የሚድኑትንም ሰዎች ጭምር ይወስናል ማለት ነው (ኤፌ 1:3-6)። የነጻ ፈቃድ አስተምህሮ የሰው ፈቃድ በድህነት ውስጥ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ያስተምራል።

ሁለትኛ የመዳን እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ይክዳል (ኤፌ 2:8-10) ። የነጻ ፈቃድ አስተምህሮ እምነት ሰው ክርስቶስን የሚመርጥበት የግሉ ውሳኔ ነው ይላል።

ሦስተኛ ክርስቶስ ለህዝቡ ብቻ የመሞቱን እውነታ ይክዳል (ማቴ 1:21) ። በነጻ ፈቃድ የሚያምኑ ክርስቶስ ያለምንም ልዩነት ለሁሉም ሰው እንደሞተ እና መዳናቸው እርሱ በመቀበል ነጻ ፈቃዳቸው ላይ እንደተመሰረተ ነው ይላሉ።

አራተኛ ደግሞ ድህነት በጸጋ ብቻ እንደሆነ የሚናገረውን አስገራሚ እውነት ይክዳሉ (ኤፌ 2:8-10) ። የነጻ ፈቃድ አስተምህሮ ሰው "አንዳች ነገር አርጎ" ይድናል የሚል ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ድህነት "እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም" በማለት ያስተምረናል (ሮሜ 9:16) ።

በሰው ነጻ ፈቃድ ማመን በስብከት እና በወንጌል ስርጭት ውስጥ በስፋት እየታየ ያለበት ዘመን ነው። ይህም ሀጥያተኞች ክርስቶስን እንዲቀበሉ በመለመን ፣ በመጣራት ፣ በመማጸን ፣ የመወሰኛ ጊዜ ፣ እጆችን በማስነሳት እና ሌሎችም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሰዎች ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው እንዲቀበሉ ለማሳመን በመሞከር ነው። እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሰው መዳን በፈቃዱ እንደሆነ አስቀድመው ያመለክታሉ።

ምናልባት አንዳንዶች ወንጌልን ታድያ ወንጌልን መስበክ ለምን ያስፈልጋል ሊሉ ይችላሉ። ነገር ግን ወንጌል "የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና" (ሮሜ 1:16) እግዚአብሔር እምነትን እና ንሰሐን ከዘላለም በፊት ለመረጣቸው እና በክርስቶስ በኩል ለዋጃቸው ሰዎች የሚሰጥበት መንገድ ነው። ለብዙዎችም ወደ ድህነት የሚያመጣ ሃይል ይሁንላቸው!

ክፍል ፱- ማጣቀሻዎች

1. Third stanza of "A Mighty Fortress Is Our God," hymn 81 in the Trinity Hymnal.

2. 2. Homer C. Hoeksema, From Creation to the Flood, Unfolding Covenant History: An Exposition of the Old Testament, vol. 1 (Grandville, MI.: Reformed Free Publishing Association, 2000), 119.
3. Martin Luther, The Bondage of the Will, trans. J. I. Packer and O. R. Johnston (London: James Clarke, 1957), 319 in “Conclusion.”

**ክፍል ፫**

# ክርስቶስ እና ስራው

## የአዳኛችን ስሞች

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ስሞችን እጅግ አስፈላጊ ጉዳዮች አድርጎ ያስቀምጣቸዋል ። እነዚህ ስሞች በጣም ወሳኝ በመሆናቸው በሥነ-መለኮት አስተምህሮ በአብዛኛው ብቻቸውን የተለየ ክፍል ይሰጣቸዋል።

ለምሳሌ *ኢየሱስ* የሚለው ስም ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በእግዚአብሔር መልዕክተኛ ለዮሴፍ የተሰጠው ስም በመሆኑ እጅግ ወሳኝ ነው። የዚህ ስም ትርጓሜ መላዕኩ እንደገለጠው ወንጌል በጥቂት ቃላቶች ተገልጦ ነው እያንዳንዱ ፊደልም ትልቅ ስብከት ሊወጣው ይችላል (ማቲ 1:21) ። በዚህም ስም ሰዎች ይድናሉ (ሐዋ 4:12)።

*"ክርስቶስ"* የሚለው ስም እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ ጴጥሮስ ይህንን ስም ሲጠራው ኢየሱስ ይህንን ሊያውቅ የሚችለው በሰማይ ያለው አባት (እግዚአብሔር) ሲገልጥለት ብቻ በመሆኑ ጴጥሮስን *"ብጹዕ "* ነህ አለው (ማቴ 16:17) ። የጠራው ይሃ ስም የቤተክርስቲያን የማይነቃነቅ መሰረት (ቁ.18) እና የአዲስ ልደት *ማረጋገጫ ነው* (1ኛ ዩሀንስ 5:1)። ስሙንም ደግሞ የማይጠራ ሁሉ በ1ኛ እና በ2ኛ ዩሀንስ እንደተገለጠው ሀሰተኛው ክርስቶስ እና አታላይ ነው (1ኛ ዩሀንስ 2:22, 1ኛ ዩሀንስ 4:3, 2ኛ ዩሀንስ 7)።

*"ጌታ"* የሚለው ስምም በጣም ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ማንም ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ኢየሱስ ጌታ ነው ማለት እንደማይችል ተነግሮናል (1ኛ ቆሮ 12:3)። *ጌታ* ለሚለው ስም እውነት የሆነው ሁሉ ለአዳኛችንም እውነት ነው።

የኢየሱስ ስሞች የእኛ አይነት ስሞች ባለመሆናቸው የእርሱን *ማንነት* እና *ምንነት* ይገልጹልናል በዚህም ምክኒያት እጅግ ወሳኝ ናቸው ። እነዚህ ስሞች እግዚአብሔር እራሱን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የመግለጡ አካል ናቸውና ለወንጌል መልዕክት እና ለድህነት አብሳሪነት እጅግ አስፈላጊ ናቸው። እነዚህን ስሞች ማወቅ እና መጥራት መዳን ነው።

ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የእግዚአብሔር (አብ) ፣ የኢየሱስ (የወልድ) እና የመንፈስ ቅዱስ በርካታ ስሞች የተሰጡን ። እንደ ተለያየ ሰው አቆጣጠር ቢለያይም ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 150 ስሞች አሉት ። እነዚህን ስሞች በሙሉ እና ትርጓሜዎቻቸውን ማወቅ እንዴት ያለ መባረክ ነው!

ሆኖም ግን ተራ ማነብነብ እና ትርጉም ሳይኖረው ይህንን ስም መደጋገም በረከትን አያመጣም በረከትም አይሆንም ። አስፈላጊው ነገር የስሞቹን ትርጓሜ *እውቀት* ከእግዚአብሔር ቃል መማር ነው። በዚህ እውቀት

እምነታችን ይበረታል፤ የምናውቀውን ያንኑ እናምነዋለን ደግሞም በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ሀይል እንማረካለን (2 ጢሞ 1:12) ። በእርግጥም በስሞቹ ላይ እምነት ያስፈልጋል ይህም እምነት ስሞቹ ነው የሚሉትን ሁሉ የሚያምን ነው። ነገር ግን እምነት ያለ እውቀት እጅግ ደካማ ነው።

ይህ ሊተኮርበት ይገባል። አንዳንዶች ስሙን ደጋግሞ ማነብነብ የሆነ ኃይል አለው ብለው ያስባሉ። እንዲህ አይነት እምነት ምንም አይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለውም። የክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ኃይል በእርሱ በማመን ፣ ስሙን ማወቅ እና መውደድ ሲሆን እምነትም ደግሞ ከስሙ እርሱ ማን እና ምን እንደሆነ ማወቅ ነው።

የኢየሱስን ስሞች ታውቃላችሁ? በ*ስሞቹስ* በግላችሁ አዳኝነቱን ታውቁታላችሁ? ስሙን በአለም ፊት እስክታውጁት ድረስ ትወዱታላቹ ፣ ታውቁታላችሁ? ይህን የምታደርጉ ከሆነ እንግዲያውስ እናንተም እንደ ጴጥሮስ ብጹዕ ናችሁ።

## ***ኢየሱስ* የሚለው ስም**

ከአዳኛችን ስሞች ሁሉ ኢየሱስ የሚለው ስም እጅግ ልዩ ነው። ይህ የእርሱ የግሉ *መጠሪያ* ነው። ሌሎች ስሞቹ ስራውን የሚገልጡ *ስሞች እንጂ* የግሉ መጠሪያዎች አይደሉም። *ክርስቶስ* እና *ጌታ* የሚሉትን መጠሪያዎችም እንደምሳሌ መጥቀስ እንችላለን ። ኢየሱስ የሚለው ስም ግን በአባቱ የተሰጠው ስም ሲሆን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የሚታወቅበት እና የሚወደድበት ስም ነው። እርሱን ስናናግረ እና ስለእርሱ ስናወራ የምንጠቀምበት ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም ነው።

የ*ኢየሱስን* ትርጉም ስናስታውስ ስሙ እንዴት ግሩም እንደሆነ እነርዳለን። በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የግል መጥሪያው ትርጉም "አዳኝ" ወይንም "ጅሆቫ ያድናል" የሚል ነው። አስተውሉት እስኪ ፤ ስለእርሱ ባወራን እና እርሱን በግሉ በጠራነው ቁጥር  እሱ እና እሱ ብቻ አዳኛችን ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠን አዳኛችን ነው እያልን ነው ማለት ነው።

ኢየሱስ የሚለው ስም መላዕኩ ገብርኤል የክርስቶስን መወለድ ለዮሴፍ ሲያበስረው የተገለጠ ስም ነው። ፥ "ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና" (ማቴ 1:21)። በዚህ አንድ ስም ውስጥ ምነኛ በርካታ ትርጉሞች ታጭቀዋል!

የኢየሱስ የግል ስም ጅሆቫ የሚለውን ስም ስለሚያመላክት (በኢንጊሊዘኛው ጄ (Je-) የጄሆቫ የሚለው ስም አጥሮ ሲጠራ ነው) *ኢየሱስ* በሚለው ስም መላዕኩ የገለጠው መልዕክት አዳኙ *ጅሆቫ* ነው የሚል ነው ። በእውነትም ሌላ ማንም ሊያድን አይችልም። ኢየሱስ የእግዚአብሔር አዳኝ የሆነው ከእግዚአብሔር ስለተላከ ብቻ ሳይሆን በእርሱ በኩል የሚያድነው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ድህነታቸው የተጠበቀ እንደሆነ የኢየሱስ ስም እራሱ ይናገራል። እርሱ ህዝቡን *ያድናል*! እርሱ ከእግዚአብሔር በመምጣቱ እና የእግዚአብሔርን ታላቅ ድነት በመያዙ አስተማማኝ እና የተረጋገጠ አዳኝ ነው።

በተጨማሪም ስሙ እራሱ ከአብ የተሰጡትን ብቻ ወይም ደግሞ *ህዝቦቹን* ብቻ እና ብቻ ሊያድን የመምጣቱን እውነታ ይናገራል ። እርሱ የሁሉም ሰው አዳኝ አይደለም። ለአንዳንዶች እጅግ አሳዛኝ እውነት ሆኖ ቢታይም ለተረዱት ሁሉ ግን የተባረከ እና የሚያስደንቅ እውነት ነው። አንዳንዶችን ብቻ ያድናል ማለት ሁሉን ሊያድን አቅዶ ነገር ግን ሊያድን አልቻለም ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጡትን ስጦታዎች ብቻ ግድፈት በሌለበት እና በተረጋገጠ መልኩ ያድናቸዋል ማለታችን ነው።

የኢየሱስ ስምም እርሱ ከ*ሀጥያት* አዳኝ እንደሆነ ያስታውሰናል። አንዳንዶች ሆዳቸውን የሚሞላ ፣ አካላቸውን የሚፈውስ እና አሁን ላሉበት ጊዜያዊ ችግራቸው መፍትሄ የሚሰጣቸውን አዳኝ ይፈልጋሉ። ነገር ግን በጸጋው ሀጥያተኛነታቸውን የተረዱቱ እና በእግዚብሔር ፊት በቤተመቅደሱ ውስጥ እንደዚያ ቀራጭ በማልቀስ እና አይኖቻቸውን ወደላይ ለማንሳት ሳይደፍሩ “አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ” እያሉ ለሚጸልዩት ሰዎች በክርስቶስ የልባቸው ፍላጎት የሆነውን እና የተረጋገጠ ይቅረታ፣ የማምለጫ መንገድ እና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆንን ያገኛሉ (ሉቃስ 18:13) ።

እርሱን እንደ ኢየሱስ ማወቃችን እንዴት ያለ በረከት ነው! በእውነትም “እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና” (ሐዋ 4:12) ። ይህንንም ስም ከብዙ ሽህ አመታት በፊት እንደኖረ ሰው ስም ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ልጅ ስም እና እንደ አዳኛቸው ስም ያውቁት ዘንድ ብዙዎች ይሁንላቸው።

## *ክርስቶስ* የሚለው ስም

*ክርስቶስ* የሚለው ስም ኢየሱስ እንደሚለው ስም አይነት አይደለም። ኢየሱስ የሚለው ስም የአዳኛችን የግል መጠሪያ ሲሆን ክርስቶስ የሚለው ስም ግን የተቀጽላ ስሙ ነው። ፕሪዝዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስተር፣ የፓርላማ አባል፣ እና የምክር ቤት አባል እንደሚሉት ስሞች ክርስቶስ የሚለውም ስም በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ የኢየሱስን *በታ ወይም ስራ* ያመለክታል።

በዚህም ምክንያት ሰዎች ፕሬዝዳንት ተብለው እንደሚጠሩት ኢየሱስም ክርስቶስ ተብሎ ይጠራል። ልዩነቱም ክርስቶስ ልዩ መሆኑ ነው። ሌላ ክርስቶስ ኖሮም አያውቅም ሊኖርም ደግሞ አይችልም።

ክርስቶስ ማለት "የተቀባው" ማለት ነው (*መሲህ* የሚለው የብሉይ ኪዳን ስም *ክርስቶስ* ከሚለው ስም *ጋር* ተመሳሳይ ትርጉም አለው) ። ይህም ክርስቶስ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ እንዲያከናውነው በእግዚአብሔር የተሰጠውን ልዩ ሹመት እና ጥሪ ያመለክታል። በማቲ 3:16 ላይ ክርስቶስ በሰው ሁሉ ፊት በመንፈስ ቅዱስ ሲቀባ በኢሳይያስ 61:1-3 አስቀድሞ ተገልጧል በዚህም ክፍል ደግሞ እንደተቀባ ሰውነቱ የሚሰራው ስራ ሁሉ ተካትቷል ።

በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ የክርስቶስ ቦታ እና ስራ ምንድን ነው?

ይህም ደግሞ *ነብይነት፣ ካህንነት* እና *ንጉስነት* ነው። የሂደልበርግ ካተኪዝም ከሪፎርሜሽን እምነት መግለጫዎች መካከል አንደኛው ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል "ክርስቶስ ተብሎ ለምን ተጠራ ይህም የተቀባ ሚል ትርጓሜ አለው?" መልሱም "በእግዚአብሔር አብ የተሾመበት(ordained) እና በመንፈስ ቅዱስ የተቀባው የእኛ ዋና ነብይ እና አስተማሪ ይሆን ዘንድ ነው፤ በእርሱም በኩል ስለመቤዠታችን የሥላሴው መማክርት እና የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ተገለጠልን። ደግሞም ሊቀካህናችን ይሆን ዘንድ ስጋውንም መስዋዕት በማድረግ እኛን ተቤዠን፤ በማያቋርጥም መማለድ ለእኛ እግዚአብሔር አብን ይለምንልናል። የዘላለም ንጉሳችንም ይሆን ዘንድ ተቀብቷል በቃሉ እና በመንፈሱ ይመራናል፣ በዋጀልንም በዚያ የድህነት ደስታ ውስጥ ይጠብቀናል ያጸናናልም።" [1]

ክርስቶስ የሚለው ስም ዋና የሆነበት ምክኒያት ክርስቶስ የሚለው ስም የትንቢት፣ የክህነት እና የንግስና ቢሮዎች በክርስቶስ ስም በመገለጣቸው ነው። ቤተክርስቲያንም ያለ ክርስቶስ የነብይነት፣ የክህነት እና የንግስና ስራ ልትኖር ባለመቻሏ ይህ ስም የቤተክርስቲያን መሰረት ነው (ማቴ 16:18) ። ክርስቶስ በነብይነቱ ካልነገረው በቀር ፣ እንደ ሊቀካህንነቱ ካልሞተላት በቀር እና እንደ ንጉስነቱ ደግሞ ከሰይጣን ካላዳነው በቀር ማንም በእርሱ ሊያምን አይችልም ስለዚህም ክርስቶስ የሚለውን ስም መጠራት የአዲስ ውልደት ምስክርነት ነው (1ኛ ዩሀንስ 5:1)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ መጥራት እንደ ተራ ነገር ስሙን መጥራት ብቻ ሳይሆን እርሱ ዋና ነብያችን እና አስተማሪያችን፣ ብቸኛው ሊቀካህናችን እና የእኛ ዘላለማዊ ንጉሳችን ነው ማለት ነው። በእርሱ ብቻ የምንማር ፣ በእርሱ ብቻ የምንመራ እና በእርሱ ብቻ የምንባረክ መሆኑን እውቅና የምንሰጥበት መንገድ ነው። ስለዚህም ከሰማይ ካልተሰጠው በስተቀር ማንም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሊል አለመቻሉ የሚገርም አይደለም።

ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት እርሱ ብቻውን እነዚህን ቢሮዎች የያዘ እና የተገባቸውን ስራ የሚሰራባቸው እርሱ ብቻ ነው ማለት ነው። የሚያስተምረን ማንም ሰው አያስፈልገንም (1ኛ ዩሀንስ 2:27)። ሌላ ሊቀካህን ወይንም መስዋት አያስፈልገንም! እርሱ የነገስታት ንጉስ እና የጌቶችም ጌታ ነውና ሌላ የምንቀበለው ንጉስ የለም። እርሱ ልዩ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በመመስከር ድህነትን በእርሱ በኩል ብቻ እንፈልጋለን።

## **“ጌታ” የሚለው ስም**

እጅግ ዋና የሆነው የአዳኛችን ድንቅ ስም *ጌታ* የሚለው ስም ነው። *ክርስቶስ* እንደሚለው ስም *ጌታ* የሚለውም ስም የግል ስሙ ሳይሆን የክብር ስሙ ነው።

ይህ የክብር ስም ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ስለሚገልጥልን አስፈላጊ የሆነ ስም ነው ። ለክርስቶስ አምላክነት ወይንም ጌታነት ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም ምክኒያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ ተብሎ ተጠርቷል ። “ጌታዬ” እና “አምላኬ” የሚሉት ሁለት ስሞችም ተመሳሳይ አዋጆች ናቸው (ዩሀንስ 20:28) ።

ጌታ የሚለው ስም በደማቁ የኢየሱስን ሉዓላዊ የሁሉ ነገር *ባለቤትነትን* ይገልጻል። እንደ ጌትነቱ ሁሉን ነገር በሉዓልዊ ስልጣኑ እና ኃይሉ መግዛት ብቻ ሳይሆን ነገር ሁሉ *ለእርሱ የተገባ* እና የእርሱ አገልጋይ ነው።

እግዚአብሔር በመዝሙር 50:12 ላይ እንደጌታነቱ "ዓለምና ሞላው የእኔ ነውና" ብሎ ተናግሯል። ይህ ማለት ዘማሪው በመዝሙር 119፡91 ላይ ለእግዚአብሔር "ሁሉም ባሪያዎችህ ናቸውና" ያለው ለእርሱ ነው ። ይህንን ጌትነት እግዚአብሔር ለኢየሱስ ሰጥቶታል (ሐዋ 2:36) ።

የኢየሱስ ጌትነት ሁለት ገጽታዎች አሉት። በአንድ በኩል እርሱ እንደፈጣሪ ነገሮች ሁሉ እንደራሱ አላማ በሉዓላዊ ኃይሉ ይገዛቸዋል። ይህ የክርስቶስ የጌትነቱ ገጽታ አንዳንድ ጊዜ "*የኃይሉ ገዥነት*" ተብሎ ይጠራል። በሁሉም ላይ እንዳለው ጌትነቱ እርሱ በሉዓላዊነቱ ነገሮችን ሁሉ ያለፈቃዳቸው እንኳን ቢሆን ለእራሱ አላማ ይጠቀምባቸዋል።

ነገር ግን "*የጸጋው ገዢነት"* የሚባልም ደግሞ ሌላ ገጽታ አለ። ከዚህ አኳያ በከፈለው ዋጋ ምክንያት ጌትነቱ በህዝቦቹ ላይ ብቻ ነው። ህዝቡ የእርሱ የሆኑት እንደ ጸሀይ ፣ ጨረቃ እና ክዋክብት ሳይሆን በዋጋ የገዛቸው እንቁዎቹ " እኔ በምሠራበት ቀን እነርሱ የእኔ ገንዘብ ይሆናሉ" ስለሆኑ ነው (ሚል 3:17)። ኢየሱስ በእነርሱ ላይ ጌታነቱን የሚገልጠው በኃይል ብቻ ሳይሆን በጣፋጭ ጸጋው ተጽዕኖም ጭመር ነው። እርሱ በብረት እና በኃይል ሳይሆን በእረኛ በተር ህዝቡን ይገዛቸዋል (መዝ 2፥9 ፣ መዝ 23:1)።

ይህ ጌትነቱ ገጽታ ሊመሰከር የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ብቻ (1ኛ ቆሮ 12:3)። በዚህ መልኩ ጌትነቱን ከመሰከርኩኝ እርሱ ጌታ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የእኔም ጌታ መሆኑን እመየመሰከርኩ ነው ማለት ነው። በዚህም እኔ በማንነቴ ፣ ባለኝ ነገር ወይም በሰራሁት ስራ ሳይሆን እርሱ ባፈሰሰው ደም ምክንያት የእርሱ እንደሆንኩኝ እና በእርሱ ዘንድ የተወደድኩ መሆኔን እመሰክራለሁኝ ማለት ነው።

ከዚህም ባለፈ እኔ ያለኝ ነገር ሁሉ የእርሱ እንደሆነ በዚሁ እየመሰከርኩ ነው። ያለኝ ሁሉ ቤተሰቤ፣ ጊዜዬ ፣ ንብረቴ ፣ ሰውነቴ እንኳን "ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" በፍጹም የእኔ አይደለም (1ኛ ቆሮ 6:20)። ባለኝ ነገር እና በሆንኩት ሁሉ የእርሱ በመሆኔ ሁሉን ነገር እርሱን ለማገልገል፣ ለክብሩ እና ለመንግስቱ ላደርግ ይገባኛል።

ኢየሱስ ጌታህ እንደሆነ ትመሰክራለን? ነገሮች ሁሉ ለእርሱ እንደሚገቡት እና ህይወትህን (ኑሮህ) ለእርሱ እንደሚገባው ትኖራልህ? እንግዲያወስ የእውነትም ጌታህ እና አምላክህ ነው።

## *የእግዚአብሔር አንዲያ ልጅ የሚለው ስም*

*የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ!* በአዳኛችን በዚህ ስም ውስጥ ያለው ምን አይነት ሀብት እና በክብር የተሞላ እውነት ነው። ስለ ስሙ የምናምነው ነገር ሁሉ በዚህ ስም እውነታነት ላይ የተመሰረተ ነው። የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ባይሆን ኖሮ ለእኛ ምናችንም አይሆንም ነበር።

ይህ ስም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ አንዱ አካል ነው ። በኢየሱስ ዘመን የነበሩት ያላመኑ አይሁዳውያን እንኳን የሚናገረውን ነገር ተረድተውት ቢሆንም በአሁን ጊዜ ብዙ ሰዎች ይህንን አይቀበሉትም። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ ሲነግራቸው ኢየሱስን ስም የእግዚአብሔርን ስም በማጥፋት ከሰውት ድንጋያቸውን አንስተውበታል (ዩሀንስ 8:59 ፣ ዩሀንስ 10:30-42)። በሚያስገርም መንገድ በዚህ ዘመን ካሉት ሰዎች በተሻለ መንገድ የተናገረውን ነገር ተረድተውት ነበር። አሁን ያሉት ሀይማኖቶች፣ የሥላሴ የለም የሚሉ አስተምህርቶች እና ሌሎች አንድ ብቻ ነው እግዚአብሔር ብለው የሚያስተምሩ ሁሉ የእግዚአብሔር አንዲያ ልጅ የሚለው ስም ትርጉሙ አልገባቸውም። ይህ ለእነርሱ እውነት አልያም ደግሞ ከባድ የእግዚአብሔርን ስም ማጥፋት ነው ሆኖም ግን "አንድያ ልጁ" የሚለው ስም "የእግዚአብሔር ልጅነት" ከሚለው ስም በላይ የእርሱን አምላክነት እና ኃያልነትን ይናገራል። እርሱ ከእግዚአብሔር ልጆች መካከል ልዩ ፣ ዘላለማዊ እና የባህሪ ልጅ መሆኑን ያመላክታል።

አንድያ ልጁ በሚለው ስም የተገለጸው እውነታ በዚህ ጊዜ ባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ውስጥ በብዛት አደጋ ላይ ሲጣል ይስተዋላል። እንደ 1ኛ ጢሞቲዎስ 3:16 ያሉ ክፍሎችን ስለ ክርስቶስ አምላክነት ምንም ሀሳብ እንዳይሰጡ ብቻ ሳይሆን ስሙን "ብቸኛ ልጁ (only son) " አድርገው (ረቫይዝድ ቨርዥን፣ ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን እና የኢንጊሊዘኛው መደበኛ ቨርዥን) ወይም ደግሞ "አንድ እና ብቸኛ ልጁ"( ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዢን) በማለት እውነት ባልሆነ መንገድ ተርጉመውታል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጁ አይደለም ነገር ግን "አንድያ ልጁ ፣ ከእርሱ የተወለደ ብቸኛ ልጁ (only begotten son) " ነው

(ዩሀንስ 3:16,18)። እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ብንሆንም ነገር ግን ከእርሱ “የተወለድን (begotten)” አይደለንም። እኛ ስለክርስቶስ በጸጋ “ጉዲፈቻነት” ልጆች የሆንን ነን።

ስለዚህም ይህ ስም ከግሪኩ ቀጥተኛ እና ትክክለኛ ትርጓሜ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ቤተክርስትያን እውነቱን እና የክርስቶስን መለኮትነት ለሚቃወሟት ሁሉ የምትከላከልበት መመከቻዋም ነው። ስለዚህም አላማቸው መልካም ነው ቢባልም (እኛ አይደለም ብለን እናምናለን) የእግዚአብሔርን ቃል እንተረጉማለን በሚሉት ሰዎች ሊነካካ እና ሊበለሽ የማይገባው ነገር ነው።

የክርስቶስ ኢየሱስ አንዲያ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ሌላኛው ገጽታ የእርሱ ልጅነት ለእኛ ልጅነት መሰረት እና ምክንያት መሆኑ ነው። ስለዚህም ምክኒያት እርሱ “በኩር (firstborn)” ወይም “አንዲያው (የተወለደው) ልጅ (first begotten)” ተብሎ ተጠርቷል ( ዕብ 12፡23 ፣ ዕብ 1:6)። በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ልጅ ማህጸንን የሚከፍት ነው (ዘጽ 13:2) ። ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቤተሰብ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኑ ለእኛ የሞትን እና የመቃብርን “ማህጸን” ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እንደ ሴት ልጆች እና እንደ ወንድ ልጆች ይቀላቀሉ ዘንድ ለወዳጆቹ ከፈተው ። ያለ እርሱ ለመወለድ የደረሱ ልጆች ግን ሊወለዱ የማይችሉ ልጆች ናቸው። የመጀመሪያ ልጅነት ስራውን የበለጠ ብንመለከት ደግሞ በብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ ልጅ በልዩነት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው።

ልክ እንደ ሌሎቹ የክርስቶስ ስሞች ሳይገባን የምንጠራው ስም አይደለም። ይህንን ስም ልጠራው ወይም ልንጠራው የምንችለው የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ አምላካችን ነው ማለት ስንችል ነው። እርሱ የእኔ አምላክ ነው ማለት ደግሞ በዚህ ስም ውስጥ በልዩነት እንደተገለጠው በመለኮትነቱ ውስጥ በእርሱ ለማመን እና በምህረቱ ተስፋ ለማድረግ ትልቅ መሰረት ነው።

## *የሰው ልጅ* የሚለው ስም

ኢየሱስ *የእግዚአብሔር ልጅ* ብቻ ሳይሆን *የሰው ልጅም* ነው። *የሰው ልጅ* የሚለው ስም አዳኛችን የእውነት ሰው እንደሆነ የሚያመላክት ስም ነው።

በሉቃስ ወንጌል ላይ በተደጋጋሚ እንደምናገኘው ይህን ስም ኢየሱስ እራሱን ለመጥራት ተጠቅሞበታል። ዩሀንስ ድንቅ የሆነው የክርስቶስ አምላክነት አጉልቶ ለማሳየት “*የእግዚአብሔር ልጅ*” የሚለውን ስም

እንደተጠቀመ ሉቃስም ኢየሱስ ከሀጥያት በቀር በሁሉ ነገር እንደኛ እንደነበረ አጉልቶ ለማሳየት *"የሰው ልጅ"* የሚለውን ስም ተጠቅሟል። ሉቃስ በኢየሱስ ሰውነት ላይ በማተኮሩም የክርስቶስ ውልደት እና የልጅነት ታሪክ በብዛት በሉቃስ ላይ እንድናገኘው ሆኗል።

ኢየሱስ የሰው ልጅ ነው ማለት እርሱ እኛ ወደዚህ ምድር እንደተወለድነው በመወለድ በዚህ ምድር ኖሮ ሞቷል ፤ ከእኛ ጋር "አንድ አጥንት እና አንድ ስጋ" ነው፤ እኛ የሰው ዘር አካል እንደሆንን እርሱም ከእኛ ጋር አንድ ነው ማለታችን ነው። ደግሞም "ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው...." (ዕብ 4:15) ።

ኢየሱስ የእውነት እና ፍጹም ሰው መሆኑ እንደ አምላክነቱ ወሳኝ እውነት ነው። እንደኛ ሰው ባሆን እና በሁሉ ነገር እኛን ባይመስል አዳኛችን ሊሆን ባልቻለ ነበር። እንደሰውነቱ የአዳምን ቦታ በመያዝ በእግዚአብሔር ፊት ወክሎናል (1ኛ ቆሮ 15:45-47) ። እንደ ተወካያችን ደግሞ የእኛን ሀጥያት በእራሱ ላይ አድርጎ ፤ ለሀጥያታችንም ሀላፊነት ተቀብሎ አስተሰረየልን።

እርሱ ሰው ባይሆን መከራን መቀበል እና መሞት አይችልም ነበር። እርሱ ፍጹም ሰው ባይሆን ለሀጥያታችን ሊቀጣ እንደሚገባው በፍትሃዊነት፣ በመስቀል ላይ የእኛን ቦታ ወስዶ መቀጣት አይችልም ነበር ምክኒያቱም ሰው ለሰው ሀጥያት ሊቀጣ ይገባልና ። እርሱ በሁሉ ነገር እኛን ባይመስል ኖሮ ባለ ምህረት እና ሩህሩህ "በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም" አይሆንም ነበር (ዕብ 4:15)።

እንደ ሰው ኢየሱስ ብቻ የእግዚአብሔር የመለኮት ሙላት በሰውነቱ ገልጧል (ቆላ 2:9) ። ስለዚህም ፊቱ "...... የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን......" የሚያበራውን ፣ የማይታየውን እና ሙሉ ክብር ያለውን እግዚአብሔር ያወቅነው በ*እርሱ* በኩል እና በእርሱ አማካኝነት ነው (2ኛ ቆሮ 4:6) ። ኢየሱስም "እኔን ያየ አብን አይቷል" ብሎናልና (ዩሀንስ 14:9) ።

ስለዚህም የሰው ልጅ በሚለው ስም ውስጥ ለአማኞች ትልቅ እረፍት አለ። ይህ ስም ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ እንደኖረ፣ እኛ በምንፈተንበት ሁሉ እንደተፈተነ፣ እኛም በምናልፍበት መከራ እንዳለፈ፣ ሞታችንን እንደሞተ እና በትንሳኤ ወደ ዘላለም ክብሩ እንደተነሳ ይነግረናል። እርሱ ሁሉን ነገር እንደማወቁ ችግሮቻችንን እንደሚያወቅ ሰው ብቻ ሳይሆን "በስጋው ወራት" እኛ ያስፈለገን ነገር ሁሉ እንዳስፈለገው ሰው ስለመመላለሱ ያስረግጥልናል (ዕብ 5፡7)። እርሱ ድካምን ሁሉ በመጀመሪያ *ስለሚያውቅ* በድካማችን እና በከበደንን ነገር ሁሉ እርሱ እንደሚረዳን ይህ ያሳምነናል። ይህ ሰው ለሰው ሀጥያት ቤዛ እንደሆነ እና

የክርስቶስ ሞት የማዳን ሀይል እንዳለው ያረጋግጥልናል። እንደ ሰው ልጅነቱ ኢየሱስ የእውነትም የበኩር ወንድማችን ነው።

### *አማኑኤል የሚለው ስም*

አማኑኤል የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለቴ ሲገኝ በኢሳ 7፡14 ላይ የተስፋው ቃል ሲሰጥ እና ማቴ 1፡23 ላይ የተስፋው ቃል ሲፈጸም ብቻ ተጠቅሷል።

በስሙ መጨረሻ ላይ ኤል- የሚለው ማለቂያ በዕብራይስጥ "እግዚአብሔር" ማለት ሲሆን የቀሩት ፊደላት ትርጉም ደግሞ "ከእኛ ጋር ነው" የሚል ነው በአንድ ላይ የስሙ ትርጉም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" ማለት ነው። ይህ በማቴ 1:23 እግዚአብሔር በመላዕኩ ገብርኤል በኩል የሰጠው ስም ቀጥተኛ ትርጉም ነው።

ይህ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ለንጉስ አካዝ በነብዩ ኢሳይያስ በኩል በኢሳይያስ 7:14 ላይ ተነገረ። ይህ የተነገረው እግዚአብሔር ንጉስ አካዝን በይሁዳ ለሚገኙት እግዚአብሔርን ለሚታመኑ ሰዎች እርሱ በዚያ ከባድ ጊዜ እንዳልጣላቸው እና መቼም እንደማይጥላቸው ካረጋገጠበት ምልክቶች ውስጥ አንዱ እንዲሆን ነው።

በኋላም የኢሳይያስ ትንቢት በክርስቶስ ኢየሱስ መወለድ ሲፈጽም እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር እንዴት እንደሚሆን እና ለምን እንደማይጥላቸው አሳይቷል። እርሱ በአማኑኤል ከእነርሱ ጋር ይሆናል። ስለ አማኑኤልም ሲል መቼም አይጥላቸውም።

ስለዚህ አማኑኤል የሚለው ስም ኢየሱስ በአንድ አካል እግዚአብሔርም ሰውም መሆኑን ያሳያል። የሰውንም ማንነት ከእራሱ ጋር አንድ አድርጎ በእርሱ እግዚአብሔር ሊቀርበን በሚችለው ቅርበት ቀረበን ። ስለዚህም አማኑኤል የሚለው ስም እግዚአብሔር እርሱ የህዝቡ አምላክ እንደሚሆን እና ከእነርሱ ጋር እንደሚኖር ያሳየበት የቃልኪዳኑ ሙላት ነው።

በእርግጥም ኢየሱስ አማኑኤል መሆኑ የጓደኝነት እና የህብረትን ኪዳን ያመላክታል። በዚህ የመለኮት እና የሰው አንድነትም ኢየሱስ እኛን የመለኮታዊ ባህሪ ተካፋይ አደረገን (2ኛ ጴጥ 1:4) ፣ እንደ አንድያ ልጁም

ደግሞ እርሱ ከእኛ ጋር እና በእኛ ውስጥ በማይሰበር አንድነት ይኖራል (ገላ 2:20) ። ስለዚህም እርሱ ከእኛ ጋር አንድ አጥንት እና አንድ ስጋ ነው (ኤፌ 5:30) ።

እንደ አማኑኤልነቱ ኢየሱስ ትክክለኛው የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ ወይም ማደሪያ እና በራዕይ 21:3 “ታላቅም ድምፅ ከሰማይ። እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤” የሚለውን የትንቢት ቃል የሚፈጽም ነው። በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ የሌለው ስለዝህ ነው ፤ ምክንያቱም “ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም።” (ቁጥ 22) ።

እግዚአብሔር ለሀጥያት የቤዝዎት ስራ ካልተሰራ በስተቀር ከሀጥያተኞች “ጋር” ሊሆን ስለማይችል አማኑኤል የሚለው ስም የክርስቶስንም ስራ ያመላክታል። ስለዚህም በስሙ “እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥” የሚለውን ያስታውሰናል (2ኛ ቆሮ 5:19)። እግዚአብሔር በአማኑኤል በኩል ከእኛ ጋር ሚሆነው ወደጠፋንበት በመምጣት ሀጥያታችንን በሙሉ በራሱ ላይ በማድረግ ከሃጥያታችን ሊያድነን ሀጥያታችንን ሁሉ በማስወገድ ነው።

ስለዚህም አማኑኤል በሚለው ስም ለሚያምኑ ሁሉ እንዴት ያለ በረከት ነው። ይህ ስለ አዳኙ እና በእርሱ በኩል ስለሚገኘው የድኅነት በረከትን የሚያስተምረን በአንድ ቃል የተጠቀለለ የወንጌሉ መልዕክት ነው።

## ከስሞች ሁሉ በላይ ስም

ለአዳኛችን በመጽሐፍ ቅዱስ የተቀመጡልን ብዙ ስሞች አሉ። ሁሉም ስሞች በእግዚአብሔር የኢየሱስን ሃይል እና የማዳኑን ክብር እንድንረዳበት የተሰጡን ስሞች ናቸው። እስካሁንም ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ጌታ ፣ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ፣ የሰው ልጅ እና አማኑኤል የተባሉትን በጣም ወሳኝ ስሞች አጥንተናል።

ሌሎች ስሞቹም እጅግ አስፈላጊ ናቸው ስለ እርሱ የተለያዩ ነገሮችን ያመላክቱናልና። ለምሳሌ *የሳሮን ጽጌሬዳ* እና *በእሾህ መካከል ያለ የሱፍ አበባ* የአዳኛችንን ውበት ያመላክታሉ (ማህለይ. 2:1) ። *የይሁዳ አንበሳ* (ራዕይ 5:5) እና *የምድር ነገስታት ገዢ* (ራዕይ 1:5) የእርሱን የንግስና እና ኃይል ይናገራል።

የዳዊት ልጅ (ማቴ 1:1) ፣ የዳዊት ዘር (ራዕይ 22:15) ፣ ራስ (ቆላ 2:19) እና ሙሽራው (9:15) በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም ከቤተክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያብራሩልን ስሞች ናቸው።

ከደረቅ መሬት ስር (ኢሳ 53:2) የሚለው ስም የአዳኛችንን መዋረድ ከሚናገሩ ስሞች መካከል ሲሆን የክብር ጌታ (1ኛ ቆሮ 2:8) የሚለው ስሙ ደግሞ የእርሱን ክብር ከሚናገሩ ስሞች መካከል አንዱ ምሳሌ ነው። የማይታየ አምላክ ምሳሌ (ቆላ 1:15) ፣ ድንቅ ፣ መካር ፣ ሀያል አምላክ ፣ የዘላለም አባት (ኢሳይያስ 9:6) ፣ ቃል (ዩሀንስ 1:1) ፣ አልፋ እና ኦሜጋ (ራዕይ 1:8) የሚሉት ስሞቹ ደግሞ መለኮትነቱን የሚናገሩ ስሞች ናቸው። እንደ የበኩር ልጅ (ቆላ 1:15) ፣ ከሙታን በኩር (ራዕይ 1:5)፣ የዳዊት ልጅ (ማቴ 21:9) የሚሉ ስሞቹ ደግሞ የእርሱን ሰው መሆን የሚገልጹ ስሞቹ ናቸው።

እንደ የእግዚአብሔር በግ (ዩሀንስ 1:29) ፣ የሰላም አለቃ (ኢሳ 9:6) ፣ መልካም እረኛ (ዩሀ 10:11) ፣ መስፍን (ማቴ 2:6) ያሉ ብዙዎቹ የአዳኛችን ስሞች ስራውን ያብራራሉ። አንዳንዶቹ እንደ የጽድቅ ጸሀይ (ሚል 4:2) ፣ የኪዳኑ መልዕክተኛ (ሚል 3:1) ፣ መንገድ ፣ እውነት እና ህይወት (ዩሀንስ 14:6) ፣ የህይወት እንጀራ (ዩሀንስ 6:18) ፣ ታማኝ ምስክር (ራዕይ 1:5) ያሉ ስሞቹ ደግሞ እርሱ በስራው ለእኛ ምን እንዳደረገ ያብራሩልናል።

ከእነዚህ ስሞች ኢየሱስ ዘላለማዊ ፣ ሁሉንቻይ ፣ ላይለወጥ የታመነ ፣ ባለሙሉ ክብር እንደሆነ እና ሁሉን ነገር እንደሚያይ ፣ እንደሚያውቅ እና እንደሚገዛ ፣ እርሱ የእግዚአብሔር በስጋ መገለጥ እንደሆነ (ሰውን እንደመሰለ) እና ብቸኛው የህዝቡ አዳኝ እርሱ እንደሆነ እነረዳለን። በእርግጥም ስለ እርሱ የምናውቀው ነገር ሁሉ በአንዱ ወይም በሌሎች ብዙ ስሞቹ ውስጥ የተጠቃለለ በመሆኑ ስሞቹ ለእኛ የተሰጡን እጅግ አስፈላጊ መገለጦች ናቸው።

በእያንዳንዱ ስም ውስጥ እርሱ “ከስሞች ሁሉ በላይ ስም የተሰጠው” መሆኑን እነረዳለን (ፊሊ 2:9)። በስሞቹ ከእርሱ ውጪ አዳኝ እንደሌለ በመረዳት በእርሱ ላይ ብቻ እምነታችንን እንድናደርግ እንበረታታለን። በዚህ መንገድም ስሞቹን የምናውቅ እኛ ስሙ መልካም እና ከአስር ሺህ ስሞች በላይ የተወደደ እንደሆነ አውቀን “ውዴ ይህ ነው፥ ባልንጀራዬም ይህ ነው” እንበለው (ማህለይ 5:16) እንላለን።

## የክርስቶስ *እውነተኛ* የሰውነት ባህሪ

ስለጌታችን ያለ በጣም የሚያስደንቅ እና ውድ እውነት እርሱ ከሀጥያት በቀር በሁሉም ረገድ እኛን መምሰሉ ነው (ዕብ 4:15) ። በሁሉ ነገር እኛን ይመስላል ማለታችን እርሱ ከመለኮትነቱ ባህሪ በተጨማሪ የሰውነትንም ባህሪ ይዟል ማለታችን ነው። እርሱ ሰውም አምላክም በአንድ አካል ውስጥ ነው።

ስለ ክርስቶስ የሰውነት ባህሪ ስናወራ የምናተኩርባቸው ብዙ አስፈላጊ እውነታዎች ቢኖሩም በተለየ መልኩ አምስት ነጥቦች ላይ እናተኩራለን። እርሱ *እውነተኛ ፣ ፍጹም ፣ ሀጥያት የለሽ* እና *ድካም አዘል የሰው ተፈጥሮ* ያለው እና ከኪዳን ውጪ የሆነ *ማዕከላዊ የሰውነት ተፈጥሮ (central human nature)* አለው። እነዚህ እውነታዎች በድኅነታችን ውስጥ ትልቅ ስፍራ እና አስፈላጊነት አላቸው።

በድሮ ጊዜ የነበሩ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት እና በአሁን ዘመን ያሉ አንዳንድ አምልኮዎች (cults) ክርስቶስ እንደሰው ተመስሎ መጣ እንጂ እኛ እንደምንለው በእርግጥም የሰው ስጋዊ ማንነት፣ ደም እና የሰው ነፍስ አልነበረውም የሚለውን አስተምህሮ ለመመከት ክርስቶስ እውነተኛ የሰው ባህሪ አለው የሚለው አስተምህሮ በተደጋጋሚ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል ። እንደ እነርሱ አስተምህሮ የእርሱ ሰውነት በመልክ ብቻ ነው ማለትም መላዕክ የሰውን መልክ ይዞ እንደሚመጣው አይነት ነው ይላሉ።

ነገር ግን ክርስቶስ የእውነት የሰውነት ባህሪን/ተፈጥሮን ካልያዘ የእኛም ድህነት እንደዚሁ የእውነት አልነበረም ማለት ነው። የእርሱ የሰውነት ተፈጥሮ እንዲሁ ውጫዊ ብቻ ቢሆን ኖሮ መከራው ፣ ሞቱ ፣ እና ድህነታችንም እውነት አይሆንም ነበር። የድህነታችን እውነታ በእርሱ የሰውነት ባህሪ ላይ የተደገፈ ነው። ዕብራውያን 2:14፣ 15 "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።" በማለት እውነተኛ ስጋን የለበሰ ነው እያለን ለምን በስጋ እንደተካፈለ ደግሞ "በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥" በማለት ያስቀምጥልናል።

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ኢየሱስ የሰውነት ባህሪ ላይ ትኩረት ሲያደርግ በሁሉ ረገድ፣ በመፈተን እንኳን እኛን ይመስለናል ብቻ አይደለም የሚለው ነገር ግን በሌሎች ብዙ መንገዶች ጭምር እንጂ (ዕብ 4:1) ። የእርሱ እውነተኛ ሰውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለመወለዱ ፣ ስለማደጉ ፣ ስለመማሩ ፣ ስለመታዘዙ ፣ ስለመብላቱ ፣ ስለመጠጣቱ ፣ ስለመድከሙ ፣ ስለማልቀሱ ፣ ስለመሰቃየቱ እና ስለሞቱ በተጻፉት ክፍሎች ሁሉ ላይ ተገልጧል። እነዚህ ሁሉ እርሱ የእውነትም እንደ እኛ ሰው እንደነበር ያስተምሩናል። በጌተሰማኒ ያሳለፈውን ጭንቀት ፣ ጴጥሮስ ሲክደው እና ይሁዳ አሳልፎ ሲሰጠው የተሰማውን ህመም ፣ በመስቀል ላይ በመተዉ የተሰበረውን መጠራጠር የእርሱን እውነተኛን መጠራጠር ብቻ ሳይሆን በእርሱ መከራ የተቀበልነውን ድሀንትም መካድ ነው።

ስለዚህም ክርስቶስ በአብ በፊት የሚወክለን እና ለሀጥያታችን ህይወቱን የሰዋልን የአጥንታችን አጥንት እና የስጋችን ስጋ ነው (ኤፌ 5:30) ። እርሱ ስለሰው ሀጥያት ዋጋ ለመክፈል እና በአብ ፊት እኛን በእራሱ ለማቅረብ ሲል ሰው ሆነ።

## የክርስቶስ ፍጹም የሰውነት ባህሪ

በክርስቶስ የሰውነት ባህሪ ውስጥ መታመን ያለባቸው - *እውነተኛ ፣ ፍጹም ፣ ሀጥያት የለሽ* እና *ድካም አዘል የሰው ተፈጥሮ* ያለው እና ከኪዳን ውጪ የሆነ *ማዕከላዊ የሰውነት ተፈጥሮ (central human nature)* - አምስት እውነታዎች አሉ ብለን ተነጋግረናል።

አሁን ደግሞ ክርስቶስ ስጋኝ ለብሶ ሲወለድ በስጋ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ክርስቶስ *ፍጹም* የሰውነት ባህሪ/ተፈጥሮ እንደነበረው የሚገልጠውን እውነት እንመለከታለን ። እርሱ እንደሰው መንፈስ ወይም ነፍስ (ሉቃ 23:46 ፣ ዩሀ 12:27) ፣ የሰው አእመሮ (ፊሊ 2:5) ፣ ፈቃድ (ዩሀ 6:38) ፣ ልብ (ማቴ 11:29) እና ለሰው ባህሪ የተገባው ነገር ሁሉ ነበረው።

እርሱ ግማሽ ሰው ግማሽ አምላክ አይደለም ነገር ግን ሙሉ ሰው እና ሙሉ አምላክ የሆነ አንድ ክርስቶስ ነው። ይህ ስጋን የመልበሱ (የተሰገዖው) ድንቅነት ፣ ሚስጥራዊነት እና ክብሩ ነው።

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ይህ እውነታ ተክዷል። አንዳንዶች የክርስቶስን ስጋ መልበስ (ተሰግዖ) ክርስቶስ የሰው አካል ብቻ ነበረው ፤ መለኮታዊ ማንነቱም የሰውን አእመሮ እና የሰውን ነፍስ ተክቶ ነበር ብለው ለማብራራት ሞክረዋል ። ለምሳሌ የሰው አእመሮ በእንስሳ አካል ውስጥ እንደ መክተት ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ሳይሆን በከፊል ሰው ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ፍጹም ሰው እንደነበር ማመን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፤ ድህነታችን በዚህ እውነት ላይ ይቆማልና!

*የሰውን "ሙሉ ማንነት"* ሊቤዥ ስላስፈለገው ክርስቶስ የሰውነትን እያንዳንዱን ባህሪ ሊወስድ ግድ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ የሰው መላ ብልሹነትን ሲያስተምር በሁሉም ነገሩ የተመረዘብ እና የወደቅን መሆናችንን ያስተምራል።

ሰውነታችን ርኩስ (ፊሊ 3፡21) ፣ ነፍስችንም የጠፋች (ማቴ 16:26) ፣ ፈቃዳችንም በሀጥያት የታሰረ (ሮሜ 6:16) ፣ አዕምሯችንም ምድራዊ እና ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ ነውና ለእግዚአብሔር ህግ ሊገዛ የማይችል (ሮሜ 8:7-8) ፣ ልባችንም ከሁሉም በላይ ሀሰተኛ እና እጅግ ክፉ ነው (ኤር 17:9) ። በሰው ፍጥረት ውስጥ አንድም መልካም የሆነ ነገር የለም።

ስለዚህም ክርስቶስ የእኛን ፍጹም (ሙሉ በሙሉ) የሰውነት ባህሪ እንደራሱ ውስዶ በእኛ ፈንታ ተኅሳቆለ፣ ለሀጥያታችንም በሁሉም ረገድ ቤዛነትን አደረገልን። በዚህ መልኩ እኛን በመቤዠት ልባችን ፣ አእምሯችን ፣ መንፈሳችን እና ኃይላችን ከሀጥያት ግዛት እና ባርነት አውጥቶ የህያው እግዚአብሔር ልጆች እና አገልጋዮች አድረገን።

ክርስቶስ ፍጹም አዳኛችን ነው። ስለእርሱም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ከእርሱ በቀር በእርግጥም ሊያድነን የሚችል አንድም የለም።

## የክርስቶስ ሀጥያት የለሽ የሰውነት ባህሪ

ስለክርስቶስ የሰውነት ባህሪ ከምናምናቸው አምስት እውነታዎች መካከል ሁለቱን አቅርበናል። እውነተኛ እና ፍጹም የሰውነት ባህሪ አለው የሚሉትን አስገራሚ ትምህርቶች ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ክርስቶስ ሀጥያት የሌለበት የሰውነት ባህሪ አለው የሚለውን ዋና እውነት እናነሳለን።

እርሱ ሀጥያት የለሽ ስለመሆኑ በዕብራውያን 4:15 ላይ በግልጽ ተቀምጧል። ኢሳ 53:9 ፣ ሉቃስ 1:35 ፣ እና በ2ኛ ቆሮንቶስ 5:21ም ይህንን እውነት ያስተምራሉ። ነገር ግን እርሱ እኛ በተፈተንበት ነገር ሁሉ በመፈተኑ ዕብራውያን 4:15 ክርስቶስ ሀጥያት መስራት ይችል ነበር? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል ። በሌላ አማርና ክርስቶስ ሀጥያት አልነበረበትም ስንል ሀጥያት *አልሰራም* ነው ወይንስ ሀጥያት መስራት *አይችልም* ነበር ማለታችን ነው?

አንዳንዶች የክርስቶስ ኢየሱስ መፈተን እውነት የሚሆነው እርሱ በሰውኛ (ሰው በሆነበት) ባህሪው ሀጥያት መስራት ቢችል ነው ብለው ያስባሉ። እርሱ ሀጥያት ያልሰራው እርሱ ሰውም አምላክም ስለነበር ነው ይላሉ። ይህንን መሰል አስተምህሮ ለመመከት ክርስቶስ ሀጥያት ሊሰራ የማይችል የመሆኑን እውነታ አስረግጠን ልንናገር ያስፈልጋል። *ተፈጥሮ* ሳይሆን ሰው *እራሱ* ሀጥያትን እንደሚሰራ ማስታወስ አለብን ክርስቶስም

ደግሞ *አንድ* ሰው *ብቻ* ነበር እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። መለኮታዊ በመሆኑ ሀጥያት መስራት አይችልም። እንደማንነቱ በእኛ የሰው ባህሪ ወይም ማንነት ቢሆንም እንኳን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ነውና እርሱ በሰውነት ባህሪው ሀጥያትን መስራት ይችላል ማለት እግዚአብሔር ሀጥያት ይሰራል ማለታችንም ነው። ስለዚህም በ2ኛ ቆሮንቶስ 5:21 ላይ "እርሱ ሀጥያትን አላወቀም" የሚለው እና ዕብራውያን 7:26 ደግሞ እርሱ "ቅዱስ፣ ያለተንኮል ፣ ነውርም የሌለበት፣ ከሀጥያተኞች የተለየ" የሚለው ይህንን እውነታ እንደሚያስተምረን እናምናለን።

ክርስቶስ ያለሀጥያት ነበር ማለት እርሱ እኛ ከአዳም የወረስነው የመጀመሪያው ሀጥያት በእርሱ አልነበረም ማለታችንም ነው (ሮሜ 5:12)። በዚህ መልኩ እርሱ ነውር የሌለበት ነበር። ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ እና እግዚአብሔር አብ አባቱ (የሰውነቱም አባት) መሆኑ ያለምንም ጥርጥር ከአዳም ዘሮች ውስጥ ክርስቶስ ብቻ ንጹህ እና ቅዱስ ስለመሆኑ ዋስትና ይሆናል።

እርሱ የመጀመሪያው ሀጥያት ብቻ ሳይሆን ከተወለደ በኋላም ምንም አይነት ሀጥያት አልነበረበትም። በእድሜው ሁሉ ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አልተላለፈም ፣ በጣም ጥቂት በሚባለው ነገርም ተሳስቶም አያውቅም ፣ እግዚአብሔርን የማያከበርም ንግግር ተናግሮ አያውቅም። እርሱ ፍጹም ነበር።

ስለዚህ በአጠቃላይ ሀጥያት የሌለበት ማለት እርሱ የመጀመሪያው/ የአዳም ሀጥያት የሌለበት ፤ በዘመኑም ሀጥያትን ያልሰራ እና ሀጥያትም መስራትም የማይችል ነበር። ስለዚህም ዕብራውያን እንደሚነግረን እርሱ አዳኛችን የመሆኑ ምክንያት ይህ ነው።

ሀጥያት ስለሌለበት መጀመሪያ ስለራሱ ሀጥያት መስዋዕትን አላቀረበም ። ይልቁንም ስለእኛ ፍጹም መስዋዕት ሆኖ እራሱን አቀረበ (ዕብ 7:27)። ስለዚህም እርሱም በእኛ ቦታ ሀጥያት ሆኖ እኛም ደሞ በእርሱ በኩል ለእግዚአብሔር ጽድቅ ሆንን (2ኛ ቆሮ 5:21)።

ስለዚህ የክርስቶስ ሀጥያት አልባነት ከተረጋገጠ የእርሱ ቅድስና ፍጹም መሆኑ የመረጋገጡ ዋስትና ነው።ይህ ለእኛም እውነት ነው። እርሱ በሞቱ ያደረገው ሁሉ ለእራሱ ሳይሆን በእጅጉ ለሚያስፈልገን ለእኛ ነው።

## የክርስቶስ ደካማ የሰውነት ባህሪ

አሁን አራተኛው የሆነውን የክርስቶስ የሰውነት ባህሪ ታላቅ እውነትን እንመለከታለን። እርሱ አሁን በከበረ በሰው ማንነት/ባህሪ/ ተፈጥሮ ያለ ቢሆንም በምድር ሳለ እንደ ሰው ደካማ የሰው ባህሪ ነበረው። የእርሱ የሰውነት ባህሪው የእውነት ፣ ፍጹም እና ሀጥያት የለሽ ከመሆኑም ባሻገር ደካማ ነበር።

ክርስቶስ በሰውነቱ ደካማ ስለነበር በምድር ህይወቱ ሀጥያት ከመስራት በስተቀር የሀጥያት ፍሬ ለሆኑት ክፋቶች ሁሉ የተጋለጠ ነበር። እርሱ ለበሽታ፣ ለርሃብ ፣ ለሀዘን ፣ ለህመም ፣ ለድካም ፣ እና ለሞት እንደኛው የተጋለጠ ነበር። እርሱ "......በነገር ሁሉ እንደኛው የተፈተነ ነው...." (ዕብ 4:15) ።

ሮሜ 8:3 ክርስቶስ የሀጥያተኛን ስጋ መልክ ይዞ መጣ ማለቱ ይህንኑ እውነታ ይናገራል። እርሱ ሀጥያተኛ ሆኖ መጣ ማለቱ ሳይሆን በሀጥያት ምክንያት በእኛ ላይ ለመጣብን ለሀጥያተኛው ስጋ ድካሞች ሁሉ የተጋለጠ ነበር።

ስለዚህ ክርስቶስ *የሀጥያተኛን* ስጋ ለብሶ አልመጣም። እርሱ እንደ በመጀመሪያው ክብሩ እና ውብ ግዛቱ ማንነት ውስጥ እንደነበረው አዳም አልነበረም። እርሱ እኛ ቦታችንን/ስፍራችንን እንዳጣነው እና በራሳችን ላይ ጥፋት እና ብልሹነት እንዳመጣነው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም የተረገምን እንደመሆናችን ባለፍንበት ሁሉ እንደኛ ሆነ።

ይህ እጅግ አስፈላጊ እውነት ነው። በሽታ ፣ ስቃይ ፣ ሀዘን ፣ እና ሞት የሀጥያታችን እና እግዚአብሔር በሀጥያት ላይ ባደረገው እርግማን ምክንያት የመጣ ነው። ክርስቶስ የእኛን ድካም መሸከሙ ለእኛ እርግማን የመሆኑ አንድ አካል ነው። በክርስቶስ ድካማነት ውስጥ ታዲያ ለእኛ እንዴት ያለ መጽናናት አለን!

ኢስይያስ ስለ ክርስቶስ በተናገረው ትንቢት ላት "የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው" (ኢሳ 53:3) ብሎ ጠርቶታል። የእርሱ ሀዘን ኢሳይያስ እንዳለው "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል.........እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ" በእርሱ ሕመም፣ ስቃይ እና ሀዘን "እኛ ተፈወስን" በማለት ያብራራዋል (ቁጥ 4-5)።

የመቤዠት አቅም ያለው የክርስቶስ ሞት ብቻ ሳይሆን በምድር ሁሉ ላይ ሲመላለስ ያለፈበት መከራም ጭምር ነው። ይህንን "ሕይወቴ በኀዘን አልቃለችና፥ ዓመታቴም በልቅሶ ጨኸት፤ ኃይሌ በችግር ደከመ፥ አጥንቶቼም ተነዋወጡ" በማለት ሲናገር መስክሮታል (መዝ 31:10)።

እርሱ የእኛን ፈተና እና መከራን ስላለፈበት ያውቀዋል ስለዚህም በክርስቶስ መከራ እና ፈተና ለእኛ የበለጠ መጽናናት አለልን። እርሱም እኛ ባለፍንበት አልፏል ስለዚህም ማንም እኛ ያለፍንበትን ፈተና አይረዳም ማለት አንችልም ክርስቶስ ይረዳናልና።

በዚህ መንገድ ታዲያ የክርስቶስ ድካም፣ ህመም፣ ሀዘን እና መከራ የድህነታችን አካል ናቸው። እኛ እንደ እርሱ አይነት ሀዘን አለ ብለን ማሰብ ሳይሆን ይህንንም እውነት እንመን (ሰቆቃቅ 1:12)።

## የክርስቶስ ፈተናዎች

ዕብራውያን 4:15 ክርስቶስ የደካማ የሰው ማንነት (በድካማችን ይራራልናል እና በሁሉም መልኩ ደግሞ እንደእኛ ተፈትኗል) እና ሀጥያት የለሽ ማንነት (ሀጥያት አልነበረውም) እንደነበረው ይናገራል። እነዚህን እውነታዎች አስቀድመን ተነጋግረንባቸዋል። እነዚህ ሁለት እውነታዎች በአንድ ላይ ስለክርስቶስ ፈተና ጥያቄን ያስነሳሉ። እርሱ ሀጥያት የሌለበት ከሆነ እንዴት ሊፈተን ይችላል? እርሱ ሀጥያት መስራት የማይችል ከነበር ታዲያ እንዴት ፈተናው እውነት መሆን ይችላል? ሀጥያት ደግሞ ካልሰራ የእውነት በሁሉም ነገር እንደኛ የተፈተነ ባህሪ አለው?

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው የክርስቶስ ፈተና እውነት ነበር። ፈተናዎቹ መላዕክት ሊያገለግሉት አስፈልጎታል (ማቴ 4:11)። እርሱ የደከመ የሰው ማንነት ሰለነበረው በፈተና ውስጥ እኛ እንደምንደክመው ደክሞ ነበር። ነገር ግን ይህ ሀጥያት መስራት ካልቻለ እንዴት ፈተናው እውነት ሊሆን ይችላል የሚለውን ጥያቄ ግን አይመልስም።

አንዳንዶች ክርስቶስ በመለኮትነቱ ሳይሆን በሰውነት ባህሪው ሀጥያትን መስራት ይችል ነበር ይላሉ። እኛ ይህንን ልንቀበለው የማይገባ መልስ ነው ብለን እናምናለን። ይህንን በማለት ማለት የሌለብንን እርሱም ፍጹም አልነበረም እንድንል ያደርገናል። በሰዋዊ ባህሪው/ማንነቱ ሀጥያት መስራት ይችላል የሚለው እውነት ቢሆን እንኳ እያልን ያለነው እርሱ የእግዚአብሔር አንዲያ ልጅ ሀጥያትን መስራት ይችላል ነው። እንደዚህ አይነት ንግግር ደግሞ የእግዚአብሔርን ስም ማጥፋት ነው።

“እግዚአብሔር በስጋ ተገለጠ” (1ኛ ጢሞ 3:16) የሚለውን ሚስጥር እንደተረዳን አስመስመስለን ከማብራራት ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን ፈተና መረዳት እንድንችል እንደሚረዳን እናምናለን። አዲስ

ኪዳን ይህንን ለመግለጽ የተጠቀመው አንድ ቃል ሆኖ ሳለ የኢንግሊዘኛው ግን “ፈተና” እና “ሙከራ(በአማርኛው ትርጉም ፈተና ተብሎ ተቀምጧል)” የሚሉትን ሁለት ቃላቶችን እንደሚጠቀም ልንረዳ ይገባል። አንድን ቃል ብቻ በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ትልቅ ልዩነት ያላቸው የሚመስሉን ሀሳቦች ምንም ልዩነት እንደሌላቸው እና ይህ በሰይጣን እና በሀጥያት ላይ የሚደረግ ሁለት ገጽታ ያለው ተመሳሳይ መንፈሳዊ ትግል እንደሆነ ያስተምረናል። ሰይጣን እኛን ሲፈትነን በተመሳሳይ እግዚአብሔርም እንደገና እየሞከረን(እየፈተነን) ነው።

ይህ እግዚአብሔር በሀጥያት እና በሰይጣን ላይ ያለውን ሉዓላዊነት ይገልጣል። ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ ሁልጊዜም “ወደ ፈተናም አታግባን” የሚለውን ጸሎት የምናቀርበው ለዚህም ነው። ይህም ደግሞ የክርስቶስን ፈተና እንደነረዳ በደንብ ይረዳናል።

ክርስቶስ በሰይጣን ሲፈተን (tempted) በእግዚአብሔርም እየተፈተነ (tested) ነበር። መፈተኑን (temptation) በዚህ መልክ ስናየው በመጡኑ ለመረዳት የሚቀልል እና ሀጥያት መስራት ሳይችል እንደተፈተነ እና የተፈተነበትን ምክንያት መረዳት እንችላለን።

ክርስቶስ የተፈተነበት ፈተና ከእግዚአብሔር የተላከ እና እርሱ የእውነትም ሀጥያት እንደሌለበት እንድናውቅ ከሰይጣን እና ከሀጥያት ጋር ያደረገው ከባድ መንፈሳዊ ውጊያ ነው ። በዚህ መሰረትም ሀጥያት የመስራት ሀሳብ ፈጽሞ ሊኖረው እንደማይችል እና ፈተናዎቹ እኛ እንደምንፈተነው የእውነት እና ከባድ እንደነበሩ እንመለከታለን።

ይህን መረዳታችን ለእኛ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር በተዋጋው ውጊያ ሀጥያት አልባ መሆኑ ለእኛም በምናልፍበት ውጊያ ማብረታቻ ይሆንልና። እርሱን እየተመለከትን “ዝላችሁ እንዳትደክሙ” እንደተባለነው በአእምሮዋችን ልንበረታ ይገባል (ዕብ 12:2-3)።

## የክርስቶስ *ማዕከላዊ* የሰውነት ባህሪ (Central Human Nature)

ክርስቶስ እውነተኛ ፣ ፍጹም ፣ ሀጥያት የለሽ እና ደካማ የሰው ባህሪይ እንዳለው ተመልክተናል። ከእነዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የሥነ-መለኮት አጥኚዎች አምስተኛ ሀሳብ እርሱም ማዕከላዊ የሰውነት ባህሪውን ይናገራሉ።

ይህም ክርስቶስ ከማሪያም ደም እና ስጋ የተወለደ ፣ የዳዊት ዘር የይሁዳም ነገድ የሆነ ፣ በስጋ የአብርሃም ዘር ነው ማለታችን ነው። ስለዚህ እርሱ የእኛ ስጋ እና ደም የሆነው የአዳም ልጅም ነው።

ይህ እራሱን በእራሱ የሚያብራራ ሀሳብ ቢሆንም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ግን ሲካድ የነበረ እውነት ነው።አንዳንዶች ክርስቶስ የሰውነት ባህሪውን ከመንግስተ ሰማይ እንደተቀበለው እና ቧንቧ ውሃን እንደሚያስተላልፍ ክርስቶስም ከማሪያም ማሕጸን ውስጥ እንዲሁ እንዳለፈ ይናገራሉ። አልያም ደግሞ የእርሱ የሰውነት ባህሪው በማህጸኗ ውስጥ ልዩ ሆኖ የተፈጠረ እንጂ በስጋ እና በዘረመል የእርሷ ልጅ አይደለም ይላሉ።

ይህ በአንዳንድ አናባፕቲስቶች (Anabaptists) በሬፎርሜሽን ጊዜ እና በጣም በቅርቡ ደግሞ በ ኒዮ ኦርቶዶክሳዊው (neo-orthodox) ካርል ባርዝ ይታምናል[2]። ሁለቱም ካርል ባርዝ እና አናባፕቲስቶች የክርስቶስን ሀጥያት የለሽነትን ለማስረዳት ይህንን አመለካከት ሲይዙ እናያለን። ኢየሱስ ከሰው ዘር ያልያዘ ካልሆነ ምንም አይነት የሰው ብልሹነት ወደ እርሱ ሊተላለፍ አይችልም ብለው ያስባሉ።

ነገር ግን ክርስቶስ ያለሀጥያት መሆኑን ለመቀበል እነዚህን አመለካከቶች መያዝ አያስፈልግም። ሉቃ 1፡35 እንደሚያስተምረን የእርሱ በመንፈስ ቅዱስ መጸነስ ሀጥያት የለሽ መሆኑን ያመላክታል።

አናባፕቲስቶች እና ባርዝ ያላቸውን አመለካከት መያዝ ማለት ክርስቶስ እንደ እኛ ከሀጥያት በስተቀር በሁሉም መምሰሉን ብሎም መጸነሱን እና መወለዱ መካድ ነው (ዕብ 2:14 ፣ ዕብ 4:15) ። ቤርክሆፍ እንዳለው “የክርስቶስ የሰውነት ባህሪ እንደ እኛ አይነት በእውነት ባይሆን እና የሚመስለን እንጂ እኛን የሆነ ባይሆን እርሱ አስታራቂ ሆኖ እንዲገባልን የሚያደርግ በእኛ እና በእርሱ በኩል ምንም አይነት ግንኙነት አይኖርም ነበር”[3]።

ክርስቶስ በእውነትም በዘረመል እና በፍጥረቱ በእውነት መጸነሱን እና መወለዱን ከአብርሃም የተስፋ ቃልኪዳን ቆርጦ ማውጣት ማለት ነው። እነዚህ ቃልኪዳኖቹም እርሱን የማያጠቃልሉ እና በእርሱ

የማይፈጸሙ ናቸው ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በእርሱ የታመኑ የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖችም ከዚህ ተስፋ ቃል የሚካፈሉት ምንም ነገር የለም ማለት ነው። ክርስቶስን ከአብርሃም እና ከዳዊት ቆርጦ ማውጣት ማለት ከብሉይ ኪዳን እና ከኪዳኑ ተስፋ እርሱ እና እኛን ቆርጦ ማውጣት ነው።

ስለዚህ ክርስቶስ ስጋን በመልበሱ (በተሰገያ)የእውነት የሰው ልጅ ዘር እንደሆነ እና በተፈጥሮ የዘር ሀረጉ የማሪያም እውነተኛ ልጅ እና በእርሷ በኩል የአብርሃም እና የዘሩ ልጅ የመሆኑን ውድ እውነት እንያዝ። የእኛ ድኅነት እና እንደ አብርሀም ልጆች በኪዳኑ ውስጥ ያለን ቦታ በዚህ እውነታ ላይ የተደገፈ ነውና።

## የክርስቶስ ዘላለማዊ መገኘት/ውልደት (The Eternal Generation of Christ)

ክርስቶስ ከአብ ጋር በሁሉ ረገድ እኩል በመሆኑ የእርሱ ሙሉ መለኮትነት ካብራራን ወዲህ የእርሱን ዘላለማዊ መገኘት ደግሞ ማብራራት አለብን።

“ማስገኘት (generates)” የሚለው ቃል አባት ልጅን ስለመውለዱ የሚያወራ ነው። እናት ስትጸንስ (conceives) አባት ደግሞ ያስገኛል ። የክርስቶስ መወለድ(generation) ማለት እርሱ እንደ ሁለተኛው የሥላሴ አካልነቱ የእግዚአብሔር ልጅ እና ለአባቱ ደግሞ የመጀመሪያ ልጅ ነው ማለት ነው። ስለዚህም “የመውለድ/ማምጣት (generates)” ሌላኛው ትርጉም ማግኘት ፣ አስገኘ (begotten) የሚል ነው። ከአባቱ ጋር ባለው ግንኙነት ክርስቶስ ብቸኛ ያስገኘው (የወለደው “begotten”) ልጁ ነው።

በእኛ ልማዳዊ አረዳድ ውልደት ልጅ ከአባቱ በኋላ የሚመጣ /የሚወለድ እና ጅማሬ ያለው ነው። ሆኖም ግን ዘላለማዊ መወለድ/መገኘት ማለት የሥላሴ ሁለተኛው አካል ክርስቶስ ከዘላለም ጀምሮ ማለትም ምንም መጀመሪያ ሳይኖረው በሥላሴ የመጀመሪያው አካል ተገኝቷል። ትውልዱም/መገኘቱም ዘላለማዊ በመሆኑ ሁለተኛው የሥላሴ አካል ከመጀመሪያው የሥላሴ አካል ጋር እኩል ነው አንዱም አንዱን አይቀድመውም።

የምንናገረው ክርስቶስ በስጋ ስለመወለዱ አይደለም። በስጋም በመወለዱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ምክኒያቱም በመንፈስ ቅዱስ የመጸለል ሀይል በሰው ባህሪ ተውልዷልና። በእኛ ስጋ እንደተወለደ ልጅ ጅማሬ ያለው እና ከአብ የሚያንስ ነው ። እንደ ሥላሴነቱ ግን የእርሱ ውልደት/መገኘት ዘላለማዊ ነው።

ይህንን የአትናሲያን እምነት አዋጅ እንዲህ አድርጎ አስቀምጦታል “ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ፤ አምላክም ሰውም መሆኑን ማመን እና ማወጅ ነው።

ከእግዚአብሔር አብ አንጻር ከአለማት በፊት የተገኘ/የተወለደ በዚህም አምላክ ነው ፤ በእናቱ ዘረመል፣ በአለም ውስጥ በመወለዱ ደግሞ ሰው ነው። በአምላክነቱም ከአብ ጋር እኩል በሰውነቱ ግን ከአብ ያነሰ ነው።"[4]

የክርስቶስ ኢየሱስ ውልደት ከዘላለም ስለመሆኑ በዚህ ጊዜ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እውነት ነው። አንዳንዶች ይህንን መካድ እንደ አዲስ ልማድ አድርገውታል። ምክንያታቸው ምንም ይሁን ሥላሴን ግን እየካዱ ነው ። ክርስቶስ እንደ ልጅ በዘላለም መገኘት/ውልደት ካልሆነ እርሱ ጅማሬ አለው ማለት ነው። እርሱ ደግሞ ጅማሬ ካለው ዘላለማዊ አይደለም። ዘላለማዊ ካለሆነ ደግሞ እርሱ በእውነት አምላክ አይደለም። እርሱ ደግሞ ሙሉ በሙሉ አምላክ ካልሆነ የእኛ አዳኝ አይደለም።

የክርስቶስን የዘላለም ትውልድን መካድ የአሪያኒዝም የጥንት ኑፋቄ ትምህርት ነው። በአሁኑ ዘመን ያሉ አንዳንድ አስተምህሮዎች እንደሚያስተምሩት በቤተክርስቲያን የጥንት ታሪክ ውስጥ ይህ ኑፋቄ ክርስቶስ *አምላክ* ቢሆንም ከአብ ጋር ግን እኩል አይደለም የሚል አስተምህሮ ነበር። የአርያኒዝም ተከታዮች አንዲያ ልጁ የሚለው ቃል ክርስቶስ መጀመሪያ እንደነበረው የሚያመለክት እና እንደ አብ ለዘላለም ያልነበረ መሆኑን የሚያመላክት ስለሆነ እርሱ ከአብ ጋር እኩል አይደለም ብሎ ያስተምራሉ።

ዘላለማዊ መገኘቱ/ውልደቱ በምሳሌ 8:22-20 ላይ በግልጽ ተቀምጦልናል፤ የሚናገረውም ጥበብ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነው። ክፍሉ "ከጥንቱ ከዘላለም ጀምሮ ተሾምሁ ፤ ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ.......... የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ ፤ ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ ፥ በፊቱም ሁልጊዜ ደስ ይለኝ ነበርሁ፥" ይለናል (ቁጥ 23 ፣ 30) ። ተመሳሳይ ሀሳቦች በሚኪያስ 5:2, በ1ኛ ቆሮንቶስ 1:24, እና በቆላሲያስ 1:15 ላይ ይገኛሉ። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስን አጥብቀን በመያዝ እናየእውነት ጠላቶች ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታችን እና አምላካችን የመሆኑን እምነታችንን (እወጃችንን) እንዲወስዱ አንፍቀድላቸው።

## የክርስቶስ ከድንግል መወለድ

ከእምነታችን አንዱ እና ወሳኙ ምሰሶ ክርስቶስ ከድንግል መውለዱ ነው። የክርስቶስ ኢየሱስ ሰውነት እውነታ እና መሰረታዊነት ከድንግል ከመወለዱ ጋር ሊነጣጠል የማይችል ግንኙነት አለው።

ይህ እውነታ መሰረታዊ በመሆኑ በብዙዎች ይካዳል። በጥንቷ ቤተክርስቲያን ጊዜ የነበሩ ግኖስቲክስ የሚባሉቱ የክርስቶስን ከድንግል መወለድ ይክዳሉ። ይህም አሁንም ብዙ ጊዜ ጥቃት የሚደርስበት እውነታ ነው።

እንደ ሪቫይዝድ ስታንዳድ (Revised Standard Version) ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አዳዲስ ትርጉሞች  በኢሳይያስ 7:14 ላይ ያለውን "ድንግል" የሚለውን ቃል "ልጅ አገረድ/ ወጣት ሴት" በሚለው ቃል በመተካት የክርስቶስን ከድንግል መወለድ ያጣሙታል። ሞርሞኖች ይህንን በአብ እና በማሪያም መካከል የግብረ ስጋዊ ግንኙነት በመፈጸም ያመጡት ነው ብለው የእግዚአብሔርን ስም ያቃልላሉ ። በዚህ ዘመን አብዛኞችም የክርስቶስ ከድንግል መወለዱ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ስለክርስቶስ ታምን የነበረው አፈታሪክ እንጂ በዚህ ዘመን የማይታመን እንደሆነ ይናገራሉ ። እነዚህ ሁሉ የሀሰት ትምህርቶች ምን ያህል ይህ አስተምህሮ (የክርስቶስ ከድንግል መወለዱ) እውነት እና ትክክል እንደሆነ ያመለክታል ። ሰይጣን ጊዜውን ምንም ጥቅም የሌላቸውን ነገሮች በመቃወም አያባክንምና።

ክርስቶስ ከድንግል መወለዱ እጅግ ዋና እና አስፈላጊ አስተምህሮ ነው። ምክንያቱም በመጀመሪያ የክርስቶስን ሰው መሆን የሚመሰክር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ክርስቶስ ሰው የሆነው እኛ በተወለድንበት መንገድ ስላልተወለደ ሰው የሆነ አባት የለውም። እንዲህ ባይሆን ኖሮ ከሀጥያት በስተቀር በሁሉም ነገር ባልመሰለን ነበር (ዕብ 2:27, ዕብ 4:15)።

በተጨማሪም ከድንግል መወለዱ ፣ በተለይም "ድንግል" የሚለው ቃል ላይ አጽንዖት በመስጠት ክርስቶስ ኢየሱስ የማርያምን ስጋን እና ደም ይዞ የተወለደ ቢሆንም እርሱ በዚህም መልኩ መወለዱ ይህንን ያመለክታል "………ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" (ዩሀ 1:13) ። ኢሳይያስ ከዘመናት በፊት እንደተናገረው ከድንግል መወለዱ ኢየሱስ አማኑኤል *እግዚአብሔር ከእኛ ጋር* የመሆኑም ምልክት ነው (ኢሳ 7:14)።

የድንግል መውለድን ለማመን ሮም ወይም የሲውዘርላንዱ ሃዳሽ ዚዊሊንግ እንደሚያስተምረው የማሪያምን ቋሚ/የማይሻር ድንግልናን እንድናምን አያስፈልገንም ። ከክርስቶስ መወለድ በፊትም ሆነ መወለድ በኋላ የእርሱን ሀጥያት የለሽነት ያረጋገጠው የማሪያም ድንግልና ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሀይል መጸነሱ ነው። ሉቃስ 1:35 በግልጽ ይህንን  "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" በማለት ያስተምራል።

የድንግል መውለድ ለመረዳት የሚያዳግት ሀሳብ መሆኑ ሊያስገርመን አይገባም። ይህ የጸጋው ድንቅ እና የታምራቱ አንዱ አካል ነው። የተራው ሰው ጽንስ እና መውለድ ሚስጥራዊ ከሆነ የክርስቶስን ወደ ምድር የመምጣት ታምር ሙሉ በሙሉ እንዴት መረዳት እንቻላለን? ይህንንም ባለመረዳታችን ሊገርመን አይገባም። የክርስቶስ በድንግል መወለድ እንደ አዳኝነቱ የእርሱ ስራ ነውና እርሱን እና ስለእርሱ የሆነውን እውነት ሁሉ በእምነት ብቻ ልንቀበል እንችላለን።

የክርስቶስ ከድንግል የመወለድ ታላቅ ታምር እጅግ ታላቅ ወደ ሆነው ከአባቱ ለተሰጡት ለእነርሱ ለሀጥያታቸው ሁሉ በስጋው በመሰቃየት ፣ በመድማት እና በመሞት ወደሰራው ከታምራቶችም ወደሚበልጠው ታምራት ይምራን።

## የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት አንድነት

የክርስቶስ ተሰገዖ ሚስጥር እውነተኛ አምላክ ወይንም ሰው መሆኑን ብቻ የሚያብራራ ሳይሆን እርሱ *ሁለቱንም* መሆኑን የሚያመላክት ነው። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 መሰረት የአምላክ በስጋ መገለጥ " እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር" እጅግ ታላቅ ነው። ይህም ሚስጥር በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ልንረዳው አንችልም።

ነገር ግን የክርስቶስ ሁለት ማንነቶች በአንድ አካል ውስጥ የተጣመሩ መሆናቸውን መረዳት እንድንችል ምንሳሌዎች ወይም ንጽጽሮችን መጠቀም እንችላለን። እነዚህ ማነጻጸሪያዎች ፍጹም አይደሉም ፤ መሆንም አይችሉም ። ነገር ግን ቻርለስ ሆጅ እንዳለው "እምነትን ለማጽናት እና አለማመንን ለመገጸጽ የሚበቃ አንድነት ወይንም ተመሳሳይነት አለ።"[5]

የስጋ እና የነፍስ አንድነት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። የአትናሲያኑ የእምነት አዋጅም ይህንን ይላል "ነፍስ እና ስጋ በአንድ አካል መሆናቸው ትርጉም እንደሚሰጠው ሁሉ ሰው እና አምላክ በአንዱ በክርስቶስ መሆናቸው ትርጉም ይሰጣል።"[6]

ይህ ምሳሌ ከክርስቶስ ሁለት ባህሪያት ጋር የሚመሳሰል የሚከተሉት ነጥቦች አሉት።

የመጀመሪያው ነፍስ እና ስጋ በአንድ ሰው ውስጥ ያሉ “አካላት (substance)” እና አንደኛው ረቂቅ ያልሆነ ሌላኛው ደግሞ ረቂቅ እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም ሁለት ባህሪ አለው - አንደኛው የተገደበ እና ፍጥረታዊ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ያልተገደበ እና መለኮታዊ ነው።

ሁለተኛው ነፍስ እና ስጋ የአንድን ሰው ማንነት እንደሚይዙ እነዚህ የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት በአንድ ማንነት ውስጥ ተጣምረው አሉ። በሁለቱ ማለትም በነፍስ እና በስጋ ተግባራት ሁሉ አንድ አድራጊ ፣ አንድ አሳቢ ፣ አንድ ፈቃጅ ሰው እንዳለ ሁሉ በክርስቶስ ሁለት ባህሪያት/ተፍጥሮ ውስጥም እንደዚሁ አንድ አድራጊ አካል።

ሦስተኛ ደግም ነፍስ እና ስጋ የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑት የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት/ማንነቶች ተዋህደው ሰውም አምላክም ያልሆነን አካል የሚፈጥሩ ሳይሆኑ እነዚህ ባህሪያት የተለያዩ ናቸው። መዳብ እና ዚንክ ቀላቅለን ሙሉ ለሙሉ አዲስ የሆነን ነሀስ የሚባል ንጥረ ነገር እንደምንሰራው እነዚህ ማንነቶች አይደባለቁም። ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ እና በእውነትም ሰው ፤ ሙሉ በሙሉ እና በእውነትም አምላክ ነው እንጂ ግማሽ አምላክ በግማሽ ሰው አይደለም።

አራተኛውም የነፍስ እና የስጋ ባህሪያት አንድን ሰው እንደሚወክሉት ሁሉ (ለምሳሌ አንድ ሰው ጠቢብ መንፈስ ያለው እና በቁመቱም ረጅም ሊሆን ይችላል) የክርስቶስ መለኮታዊ እና ሰዋዊ ባህሪያት እርሱን ይወክሉታል። አንድ ላይ የማይሄዱ ሀሳቦች ለሰው እንደሚባሉት ሁሉ ፣ ለምሳሌ - ሰው መንፈስ ነው፣ ሰው አፈር ነው - ለክርስቶስም በተመሳሳይ አገላለጥ የመለኮታዊ ባህሪይ ፍጹምነትን የተላበሰ እና የሰዋዊ ባህሪይ መገደብን የተላበሰ ነው እንላለን ። ሁሉን የሚያውቅ ሆኖም ግን የመምጫውን ቀን እና ሰዓት የማያውቅ፤ ዘላለማዊ ነገር ግን በጊዜ ውስጥ ጅማሬ ያለው፤ ሁሉን ቻይ የሆነ ነገር ግን ደክሞ የሚያውቅ ነው።

የአትናሲያኑ የእምነት አቃጅ የመጨረሻውን ሀሳብ እንዲህ አድርጎ ባማረ መንገድ አስቀምጦታል ክርስቶስ “ከእግዚአብሔር አብ አንጻር ከአለማት በፊት የተገኘ/የተወለደ በዚህም አምላክ ነው ፤ በእናቱ ዘረመል፣ በአለም ውስጥ በመወለዱ ደግሞ ሰው ነው። በአምላክነቱም ከአብ ጋር እኩል በሰውነቱ ግን ከአብ ያነሰ ነው። ሆኖም ግን አምላክ እና ሰው ቢሆንም እርሱ ሁለት ሳይሆን፣ አንድ ክርስቶስ ነው።”[7]ሊመለክ እና ሊወደስ የተገባው እርሱ አንድ ክርስቶስ ነው።

## የማይነጣጠል የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት አንድነት

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰገዖ ስንነጋገር እውነተኛ አምላክነቱ እና ሰውነቱ የማያቋርጥ መሆኑን ልብ ማለት አለብን። በመለኮታዊነቱ እና በሰውነቱ መካከል ያለው ጥምረት ሊለያይ የማይችል አንድነት ነው።

አንዳንድ ከልባቸው ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች ከትንሳኤው በኋላ ሰው አልነበረም የሚል ብዥታ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አመለካከት አላቸው። በቤተልሄም ሲወለድ የሰው ባህሪያችንን የለበሰ ቢሆንም ነገር ግን ከሞት ሲነሳ ይህንን ባህሪ ጥሎት ተነስቷል ብለው ያስባሉ። ሆኖም ግን ከሞት መነሳቱ እራሱ እንደ እኛ ሰው መሆኑን ያመላክትልናል። እስካሁን እንዳስተዋልነው እንደ አምላክነቱ ሊሞት ወይንም ከሞት መነሳት አያስፈልገውምና።

ስለዚህም በዚህ የሰውነት ባህሪው ወደ ሰማይ ሊያረግ አስፈለገ። እግዚአብሔር ማረግ አስፈልገውም ምክኒያቱም በሁሉም ቦታ ይገኛል። እንደ*ሰው* በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል ፣ በዚያም ሆኖ ይማልድልናል በሁሉም ነገር ላይ ደግሞ ሊፈርድ ዳግም ይምጣል።

እርሱ እንደ እኛ ሰው ካልሆነ ከእርሱ ጋር ምንም እንደማይኖረን ልናስታውስ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስም ስለእርሱ “ወንድማችን ሆነ” በዚህም ደግሞ “ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት” (ዕብ 2:17) ነው በማለት የሚናገረው ነገር ልክ አይደለም ማለት ነው ። በእርግጥም እርሱ እኛን ካልመሰለን የእኛ ወንድም ሊሆን አይችልም። የክርስቶስ የሰውነት ባህርሪም በትንሳኤው በኩል መለኮታዊም አልሆነም። እንደዚህ ከሆነ ለእኛ ለመማለድ ለዘላለም የሚኖር ታላቅ ወንድማችን አይሆንም ነበር። ድካማችንን የሚውቅ እና ድካማችን የሚሰማው እንደመሆኑ ሲያማልድልን ከሀጥያት በስተቀር ከእኛ እንደ አንዱ እንድሆነ አድርጎ ነው። እንደ ሰው በእግዚአብሔር ፊት እኛን ይወክለናል በረከታችንንም ይሰጠናል።

የእኛም ሰውነት በመጨረሻው ቀን እርሱን ለመገናኘት ከሞት ስንነሳ ሰውነታችን (ስጋችን) እንደሚከብረው የክርስቶስም የሰውነት ማንነቱ በትንሳኤው ከብሯል ደግሞም ተለውጧል። የሰውነት ባህሪው በሞቱ ወደ መለኮትነት አልተለወጠም አልያም በዛው አልቀረም ፤አሁንም እርሱ የሰው ልጅ ነው።

ክርስቶስ የሰውነት ባህሪ ስላለው ከእኛ ተለይቶ ወደ አባቱ እንዳረገው በአለም መጨረሻ ቀን እንደገና በዚያ የሰውነት ባህሪ ይመጣል።በእርግጥ እንደ አምላክነቱ ደግሞ በሁሉ ቦታ የሚገኝ በመሆኑ እስከ አለም መጨረሻም ከእኛ ጋር ነው። ነገር ግን ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ በሰውነቱ እርሱን ፊት ለፊት ልናየው አንችልም።

ይህን ሁሉ ለመረዳት የሚከብድ ነው? እንዴታ መሆንም አለበት። ነገር ግን ይህ የሆነው የክርስቶስ ስጋ መልበስ እና የእርሱ ሁለት ባህሪያት መጣመር መንገዱ ሁሌም ለእኛ በጣም ከፍ ያለው የእግዚአብሔር ስራ ስለሆነ ነው። ይህም በጸጋው የመዋጀታችን ታዕምራቱ አካል ነው።

በእርግጥ ለመረዳት የሚከብድ ቢሆንም እጅግ ክብር ያለበት ማጽናኛ ነው። ምክንያቱም "እውነተኛ ራስ የሆነ ፣ እንደራሱ የሚቀበለን እና ወደ ህብረቱ የሚያስገባን የእኛ ስጋ የሆነ በመንግስተ-ሰማይ አለን።"[8]

## የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት ህብረት

የክርስቶስ ሁለት ባህሪያት/ተፈጥሮዎች የግል ህብረት መገለጫ ናቸው (personal union) ። ይህም የጌታችን የክርስቶስ ኢየሱስ ሚስጥር አንድ አካል ነው።

የግል ህብረት ነው ማለታችን በመጀመሪያ እርሱ አንድ ብቻ ነው እያልን ነው። መለኮት እና ሰው የሆነ ሁለት ክርስቶስ ሳይሆን በቤተልሄም የተወለደ ፣ የተሰቃየ ፣ በመስቀል የሞተው እና በሶስተኛው ቀን የተነሳው አንድ ክርስቶስ ነው። ይህን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ በማንነቱ ብቸኛው (አንድያ) እና ዘላለውማዊው የእግዚአብሔር ልጅም ነው ማለታችን ነው። እርሱ ስጋዊ ሰው እና መለኮታዊ ሰው ሳይሆን አንዱ መለኮት በዘላለማዊ ማንነቱ የእኛ አይነት በሆነ ስጋ የሰውነትን ባህሪ እንደራሱ አድርጎ ወስዶታል። የሰውነት ባህሪያችንን እንደሰው ቢወስድም እርሱ በሥላሴ ውስጥ የመለኮት ሁለተኛ አካል በመሆኑ ደግሞ በሰው ማንነት ብቻ አይደለም። ይህ በተደጋጋሚ በተለይ እርሱ መለኮት *ሆነ* (ድማሬን የሚያመለክት የቃል አጠቃቀም ነው) ብለው በሚያስቡ ሰዎች የሚካድ እውነት ነው።

ይህ ከትምህርተ ክርስቶስ ውስጥ ለመረዳት የሚከብደው አስተምህሮ ነው። ይህ ማለት አንዲያ ልጅ የሆነው እርሱ በግል ማንነቱ በመስቀል ላይ መከራን በመቀበል የሞተው እና በመስቀሉ ላይም "አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውከኝ?" ያለው አምላክ እራሱ ነበር። እንዴት የሚገርም እውነት ነው!

እነዚህን ነገሮች ክርስቶስ ያደረገው በሰዋዊ ባህሪው ብቻ ነው ማለት ይህንን ሚስጥር አያብራራም ምክኒያቱም እርሱ የእግዚአብሔር ብቸኛው እና ዘላለማዊ ልጁ ነበርና። የእግዚአብሔር መንገድ እንዴት የማይመረመር እና ልንረዳው የማንችለው ነው!

ክርስቶስ በግላዊ ማንነቱ የሥላሴ ሁለተኛው አካል መሆኑን ማመን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ምክኒያቱም ለሀጥያታችን ማስተሰሪያን እንዲያደርግ እና ዘላለማዊ ጽድቅ ሊያመጣን የሚችለው እርሱ እንዲህ ከሆነ ብቻ ነው። ለህዝቡ ሁሉ ሀጥያት መስቀል ላይ በመሞት ዋጋ መክፈል የሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ነው። በሀጥያት ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ቁጣ በስድስት አጭር ሰዓት ውስጥ መቀጣት የሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ነው። ሊበላሽ ወይም ሊጠፋ የማይችለውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ጽድቅ ሊያመጣልን የሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ነው (ሮሜ 3:21-22)።

ክርስቶስም በግላዊ ማንነቱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ብቻ ስራው እና ሞቱ ለእኛ የማዳን አቅም አለው። ሰው ማድረግ ያልቻለውን እግዚአብሔር በልጁ ማንነት በኩል ማድረግ ቻለ።

በድንግል ማርያም ስጋን የተላበሰው ክርስቶስ በማንነቱ ሁለተኛ የሥላሴ አካል መሆኑን ማወቅ እጅግ ወሳኝ ነው። ሌላው ቢቀር የድህነታችን እና ስጋ መልበሱን ታምር ያስታውሰናል እርሱም አምላክ ሰው ሆነ እንጂ ሰው አምላክ አልሆነም የሚለው ነው።

የ1ኛ ቆሮንቶስ 8:6 ይህንን ሃሳብ ቆንጆ አድርጎ ይሰበስበዋል"ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።" እግዚአብሔር ይህንን አዋጅ ማወጅ እኝድንችል እና አጥብቀን ሁልጊዜ መያዝ እንድንችል ጸጋን ይስጠን።

## በክርስቶስ ሁለት ባህሪያት መካከል ያለው ልዩነት

ክርስቶስ አምላክ ነው፣ ክርስቶስ ሰው ነው ስን የክርስቶስን ሁለት ባህሪያት እንዳናምታታ መጠንቀቅ አለብን። እንዲህ አይነት ተግባር በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተደረገ ነገር ነው። ለምሳሌ አንዳንዶች ክርስቶስን አማላክ-ሰው (God-man) ብለውታል። በዚህም አስተምህሮታቸው እርሱ አሁን እውነተኛ አምላክም ሆነ ሰው አይደለም ፤ ነገር ግን ከሁለቱ የተደባለቀ አካል ነው ይላሉ። ለዚህ ምሳሌ ደግሞ ብረት የሆነውን ሶዲየም መርዛማ ጋዝ ከሆነው ክሎሪን ጋር ቀላቅሎ ብረትም ጋዝም ያልሆነውን ጭውን እንደ መፍጠር ማለት ነው።

የዚህ የጥንት የስህተት አስተምህሮ ችግር በሰው እና በመለኮት መካከል ያለውን ልዩነት መደምሰሱ ነው። በዚህም ዘመን ይህ አስተምህሮ በቀድሞው ስም ባይጠራም አሁንም ግን አለ። አብዛኞች ክርስቶስ አምላክ

የሆነው አንድ መልካም ሰው መለኮት እንደሆነ አድርገው በሰውነት እና በመለኮትነት መካከል ያለውን ልዩነት ያፈዛሉ። በዚህ ምልከታ መሰረት ክርስቶስ መለኮትነቱ ጋር የደረሰው የሰውነቱ አቅም በሙሉ በተረዳበት ጊዜ ነው ይላሉ። ብዙ መዝሙሮችን የደረሰው አይዛክ ዋትስ የተባለው ሰው ይህንኑ አመለካከት ያምን ነበር።

በሰውነት እና በመለኮትነት መካከል ያለውን ልዩነት ማፍዘዝ ስህተት ነው፤ ምክኒያቱም ሰዎች የጥፋተኝነት እና የሀጥያት ንግግራቸውን ወደ ጎን በመግፋት ስለራሳቸው አውንታዊ አስተሳሰብን መለማመድ አለባቸው የሚለውን የ"አውንታዊ አስተሳሰብ" ወንጌል እና ዘመናዊነትን ያስተዋውቃል። እንደ እነርሱም አስተምህሮ ክርስቶስ እንዳደረገው ሁሉ እነርሱም ሰዋዊ የሆነውን ሙሉ አቅማቸውን ማግኘት ይችላሉ። ስለዚህም የእነርሱ ድህነት የወንዶች እና የሴቶች ወደ ፍጹም ሰውነት ማደግ ሲሆን ይህም ፍጹምነት መለኮትን መሆን ነው ብለው ያምናሉ።

በክርስቶስ ሰውነት እና መለኮትነት መካከል ያለውን ልዩነት ስንጠብቅ ለቃላቶቻችን ልንጠነቀቅ እና መጽሐፍ ቅዱስም ስለክርስቶስ ሁለት ባህሪያት ከሚናገረው ላናልፍ ይገባል። ለምሳሌ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ ወይም "በሰውኛ ማንነቱ" ተሰቃየ እና ሞተ እንላለን ፤ አምላክ በመስቀል ላይ ሞተ አንልም። ወይንም ደግሞ ክርስቶስ "በሰውኛ ማንነቱ" በእግዚአብሔር ተተወ እንላለን ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እግዚአብሔርን ተወው አንልም።

ለእንደዚህ አይነት ንግግር መጽሐፍ ቅዱስ ላይም ማረጋገጫ አለን። ይህንንም በሮሜ 9:5 ላይ እናገኘዋለን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከአይሁዳዊያን የመጣ እንደሆነ ይነገረናል "ይህም የስጋዊ ማንነቱ ነው" ።

ስለዚህም ክርስቶስ ጌታችን እንደሆነ እና በአንድ ሰውነቱ እርሱ ዘላለማዊ፣ ሁሉን ቻይ፣ የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ፤ በተመሳሳይ ሙሉ በሙሉ የሰው ባህሪ እና ውስንነቶች ያሉበት ፍጹም እና እውነተኛ ሰው መሆኑን መጠበቅ አለብን። ይህ የተሰገየው አስገራሚነት ፣ እግዚአብሔርን ይመምሰል ታላቅ ሚስጥር እና የድህነታችን ተስፋ ነውና (ኤፌ 4:9-10)።

እነዚህን ሁለቱን ማንነቶቹን ቀላቅለን ሦስተኛ አካልን መፍጠር ለመረዳት የሚቀልል ሀሳብ ነው። ነገር ግን የክርስቶስ ሁለት ማንነቶች በአንድ አካል ውስጥ ለዘላለም ተጣምረው ግን ተለያይተው መኖራቸው ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ከአእምሯችን በላይ የሆነ ነገር ነው። ይህም የክርስቶስ ተሰገየ የእግዚአብሔር አስደናቂ ስራ ብቻ እንደሆነ ያሳየናል።

## በክርስቶስ በኩል ያለው የእግዚአብሔር ኪዳን

የክርስቶስ ኢየሱስ ሁለት ባህሪያቶች አንድነት/ህብረት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተጻፉት አንዳንድ ድንቅ ተስፋዎች መካከል እጅግ ወሳኝ ነው። ክርስቶስ የተስፋው ፍጻሜ ነው ፤እርሱ አማኑኤል "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" ነውና።

ለእነዚህ ተስፋዎች 2ኛ ጴጥሮስ 1:4 "ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ" ፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 6:16 "በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ" ፣ ኤፌሶን 3:19 "እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ" ፣ ኤፌሶን 5:30 "ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን" ፣ እና ገላቲያ 2:20 "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" የመሳሰሉትን ክፍሎች መጥቀስ እንችላለን።

እነዚህ ተስፋዎች ጆን ካልቪን ያለውን እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እና በህዝቡ መካከል ያደረገውን "ሚስጢራዊ አንድነት" ያመላክታሉ። በክፍሎቹ በግልጥ እንደተቀመጠው በተጨማሪም እምነት እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ካለው አገላለጥ አንጻር ይህ ከንግግር ዘዬ ያለፈ አገላለጥ ነው። እምነት በቀጥታ በክርስቶስ ማመን ወይንም የክርስቶስ አካል ወደመሆን ማመን ማለት ነው።

ስለዚህ እነዚህ ክፍሎች በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል ሊኖር ስለሚችለው ቅረቤታ ይናገራል። የእግዚአብሔርም ሰዎች ከእርሱ ጋር የተጣበቁበትን እና የእርሱን የተባረከ ህይወት የሚካፈሉበትን ህብረት ያመላክታል። ወደ ቤተሰቡ ከተቀላቀሉም ወዲህ በጸጋው የእርሱን መለኮታዊ ባህሪ ተካፋዮች ይሆናሉ። ይህ የሚያስገርም እውነት ነው!

ይህ አንድነት በክርስቶስ በእራሱ የምንረዳው ነው። እርሱ በአንድ በአካል ውስጥ የእኛ ስጋ እና ደም በሌላ ደግሞም ፍጹም እና እውነተኛ አምላክ ነው። በእርሱ በኩል አምላክ እና ሰው ይገናኛሉ ደግሞም አንድ ይሆናሉ ምክኒያቱም በእምነት እኛ በእርሱ አለን ፤ በእርሱ ሰውነትም የመለኮት ሙላት ሁሉ ተገልጦ ይኖራል (ቆላ 2:9-10)።

ክርስቶስም በተሰገዖው አማኑኤል የሆነው(እግዚአብሔር ከእኛ *ጋር* ነው) እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ስለሚጎበኘን ብቻ ሳይሆን በእርሱ በኩል ከእኛ *ጋር* ስለሚኖር እና ከእርሱ *ጋር* ባለንህብረት ስለሚያኖረን ነው።

የክርስቲያን *ጋ*ብቻ የዚህ ምሳሌ ነው ምክኒያቱም ወንድ እና ሴት "አንድ ስ*ጋ*" ይሆናሉና። በእርግጥም በኤፌሶን 5 ላይ ጳውሎስ ስለክርስቲያን *ጋ*ብቻ ወንድ እና ሴት አንድ ስ*ጋ* ይሆናሉ ካለ በኃላ ቁጥ 32 ላይ "ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።" በማለት አስቀምጦታል።

የእግዚአብሔር እና የህዝቡ በክርስቶስ በኩል አንድ ስ*ጋ* የሚሆኑበት እና የእግዚአብሔር የጸ*ጋ* ኪዳን የሚሟላበት ነው። የእግዚአብሔር ኪዳን የጓደኝነት እና የህብረት ኪዳን ሲሆን በዚህም እግዚአብሔር አምላካችን ሊሆን እና ህዝቡ ሊያደርገን ተስፋን ገብቶልናል። ይህም እውነት ከእግዚአብሔር *ጋ*ር በክርስቶስ በኩል አንድ ስንሆን የምንረዳው ነው።

ስለዚህም ለበጉ የሰርግ ድግስ እንጓጓለን ነገር ግን ይህ በመንግስተ ሰማይ ላለ ደስታ መጓጓት ሳይሆን ከእግዚአብሔር *ጋ*ር በክርስቶስ ኢየሱስ ላለን አንድነት ፍጻሜው (consummation) *ጋ*ር የምንደርስበት በመሆኑ ያሃ ቀን የተስፋችን መሟላት እና የደስታችን ሁሉ ጅማሬ ይሆናል።

## የክርስቶስ ሦስት ቢሮዎች

ስለክርስቶስ ሦስት ቢሮዎች በምንነ*ጋገ*ርበት ወቅት እርሱ ታላቁ *ነብርያችን* (ሐዋ 3:22-26) ፣ ብቸኛው *ሊቀ ካህናችን* (ዕብ 7:24-28) እና ዘላለማዊ *ንጉሳችን* ነው እያልን ነው (ራዕይ 17:14)።

እነዚህ ሦስት ቢሮዎች ክርስቶስን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ያደርጉታል። ከመልከጻዲቅ በስተቀር እነዚህን ሦስት ቢሮዎች የያዘ ማንም የለም (ዕብ 7)። በንጉስ አገዛዝ ዘመን የእስራኤል እና የይሁዳ ንጉሶች እንደ ካህንም እንደ ንጉስም ማገልገል አይችሉም ነበር። ንጉስ ዖዝያን በንግስናው ወቅት የካህንን ስራ ለመስራት በመሞከሩ በለምጽ ተመትቷል (2ኛ ዜና 26:16-21፡ ከ1ኛ ሳሙ 13:8-14) *ጋ*ር ያነጻጽሩ)።

ሰው እንደ ሳሙኤል ነብይ እና ካህን ሊሆን ወይም ደግሞ እንደ ዳዊት ንጉስ እና ነብይ ሊሆን ይችል ይሆናል ነገር ግን ንጉስም ካህንም ሊሆን አይችልም። መልከጻዲቅ ብቻ ሁለቱንም ቢሮዎች ሊይዝ ችሏል እርሱም ደግሞ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። እንደ ክርስቶስ ያለ ግን ማንም የለም።

ክርስቶስን የሚመስል ማንም ስለሌለ ከእርሱ ውጪ ምድራዊ ካህን ፣ ነብይ ወይም ንጉስ የለንም። የእርሱ ማንነት በዚህ ዘመን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሌላ ነብይ ፣ ካህን ወይንም የበላይ አስተዳዳሪ ነን የሚሉትን ሁሉ ያሳፍራቸዋል ። ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ውጪ ሌላ ራስ ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ሌላ ነብይ ፣ ለህዝቦቹ የሀጥያት ስርየት እራሱን መስዋዕት ካደረገው ከመሀረው የእግዚአብሔር ልጅ በስተቀረ ሌላ ካህን  የላትም። እነዚህን ሃሳቦች በሚቀጥሉት ክፍሎች እናነሳቸዋለን።

ግን ታዲያ ስለክርስቶስ የነብይነት፣ የክህነት እና የንግስና ቢሮዎች ከማውራታችን በፊት ቢሮ ምን እንደሆነ መረዳት አለብን። በመጀመሪያ ይህ ቢሮ *የአገልግሎት ወንበር* ነው። በእነዚህ ቢሮዎች ምክንያት ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይም ደግሞ በኢሳይያስ መጽሐፍ የጅሆቫ አገልጋይ እንደሆነ ተጠቅሷል (ኢሳ 52:13, ኢሳ 53:11)። እንደ ጅሆቫ አገልጋይነቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና ስራ ሊሰራ መጥቷል (ሉቃ 2:49 ፣ ዩሀ 4:34)።

ቢሮ *የስልጣን ወንበርም* መገለጫ ነው። በእነዚህ በሦስት ቢሮዎቹ ክርስቶስ በሰማይ እና በምድር ሙሉ ስልጣን አለው (ማቲ 28:18)። እንደ ነብይ የሚናገረው ቃል ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ እርሱን የማይሰሙ ስዎች ሁሉ ይጠፋሉ። እንደ ንጉስ ያለው ገዢነት ከሁሉም በላይ ነው። እግዚአብሔር ለእርሱ ለሰጠው ህዝብ ሀጥያት ስርየትን እንዲያቀርብ እና በድህነት በረከት እንዲባርክ ከእግዚአብሔር ስልጣን ተሰጥቶታልና እንደ ካህን መስዋቱን በማቅረብ እና እኛን በመባረክ የሰራው ስራ የድህነት ስራ ነው ።

በመጨረሻም ቢሮው *የመካከልነት ወንበር* ነው። እንደ ነብይ፣ እንደ ካህን፣ እና እንደ ንጉስ ክርስቶስ መካከለኛችን ነው። እርሱ በእግዚአብሔር እና በእኛ “በመካከል የሚቆምልን” እንደካህን የእግዚአብሔርን ፍትሃዊነትን የሚፈልግ የሀጥያት መስዋዕትን ለማቅረብ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ነብይነት ወደ እኛ ለማምጣት እና በእግዚአብሔር ስም እንደ ሉዓላዊ ንጉስ በእኛ ላይ መንገስም ጭምር ነው።

ክርስቶስ የሚለው ከብሉይ ኪዳን “መሲህ” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ይንንም ደግሞ ያመለክተናል ። ይህም ስም “የተቀባው” የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን የሚወክለውም ክርስቶስ በመንፈስ

ቅዱስ በኩል በእግዚአብሔር አብ  ነብያችን ፣ ካህናችን እና ንጉሳችን እንዲሆን የተቀባ እና የተሾመ መሆኑን ያመላክታል።

በእውነትም እርሱን የሚመስል የለም። ስለዚህም ከእርሱ ውጪ ማንንም አንስማ ፣ ለማንም አንስገድ ከእርሱ መስዋትም ውጪ ሌላ መስዋት አንፈልግ። ያኔ በእውነት እርሱ ክርስቶስ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት እንችላለን።

## ክርስቶስ ዋና ነብያችን

ክርስቶስ ለሀጥያታችን መስዋትን የሚያቀርብ ታላቅ ሊቀ ካህናችን ብቻ ሳይሆን የእኛ ንጉስ እና ነብይ መሆኑን እንረሳለን። እነዚህ ቢሮዎቹ ከካህንነቱ ጋር እኩል ዋናነት ያላቸው ነው።

እንደ ነብያችን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመጣልን ነብይ ነው። ይህንንም የሚያደርገው ህያው የእግዚአብሔር ቃል በ*መሆን* ነው (ዩሀ1:1 እና የሚቀጥሉትን ቁ. ይመ )። እንደ ህያው ቃልነቱ እግዚአብሔርን ለእኛ ይገልጥልናል (ዩሐ 1:14, ዩሐ 14:9)። ጸጋን ሁሉ ፣ ምህረት ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ደግሞም ቅድስናን ፣  ፍትህን ፣ እና የእግዚአብሔርን ቁጣ ያስተምረናል።

ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቃል ለእኛ በመናገርም እንደ ነብያችን ያገለግላል። ይህንንም ወንጌልን በመስበክ ተግብሮታል። ታማኝ ሰባኪዎችን በመጥራት እና በመላክ በህዝቡ ድምጹ እንዲሰማ አድርጓል (ዩሐ 5:25 ፣ ዩሐ 10:27)። በዚህም እርሱን ያላዩት እንዲወድዱት እና እንዲታዘዙት ያደርጋል (ዩሐ 20:29)። ይህም በስብከት የእግዚአብሔር ህዝቦች የክርስቶስን ድምጽ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሰሙ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንጌል ስብከት ከሚያወራው ዋና እውነት ውስጥ አንዱ ነው። ስብከት ወደ ድህነት የሚያመጣ የእግዚአብሔር ኃይል የሆነው እና(ሮሜ 1፡16) እምነትም ከመስማት የሚመጣበት ምክንያትም በዚሁ ነው (ሮሜ 10:17)።

ክርስቶስ ይህንን በመሰለ ኃይል ስለሚናገረ ሌላ ነብይ መፈለግ ወይም ከእርሱ ውጪ ሌላን መከተል አያስፈልግነም። በዚህ ዘመን ነብያት ነን ፤ የእግዚአብሔር የማይሻር ፈቃድንም እንናገራለን የሚሉ ሰዎች በክርስቶስ መገኘት ሊያፍሩ የሚገባቸው እና የእርሱን ብቸኛ የነብይነት ቢሮ መቃወም ነው። ክርስቶስ

ከመምጣቱ በፊት ሊሎች ነብያቶች ያስፈልጉ ነበር። ነገር ግ ን አሁን ክርስቶስ ህያው እና ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ለሆ ከእዚህም ውጪ ሌላ ሊኖር አይችልም።

የክርስቶስ የነብይነት ስራ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ሙሴ ከመወለዱ በፊት ስለመምጣቱ ተነበየ (ዘዳ 18:15, ሐዋ 3:22-25)። ሙሴ ስለክርስቶስ ነብይነት "ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት" በማለት ተናግሯል (ሐዋ 3:22)።

ሙሴ የተሻለ ነብይ እንደሚመጣ የተናገራቸው ሰዎቹ ሙሴን ሁልጊዜ ስለማይሰሙት እና ስለማይታዘዙት ነበር። የሚመጣው መሪ እራሱን እንዲሰማ የ*ሚያደርግ* መሪ ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ በሀይል ስለሚናገር ሀጥያተኛውን ሰው ሲጠራው ከመታዘዝ ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም። ወደ እምነት እና ንሰሓ ሲጠራን ሀያል የሆነው ድምጹ በሰዎች ልብ ውስጥ ታላቅ እምነትን እና ንስሃን ይፈጥራል። እርሱ ሲናገር ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምጽ በመስማት ህያዋን ይሆናሉ (ዩሀ 5:25)። ለዚህም ነው ሙሴ "*በሚነግራችሁ ሁሉ* እርሱን *ስሙት*" ያለው።

ሀጥያትተኞች "ሙታን" በመሆናቸው ክርስቶስ እነርሱን በዚህ ሀይል እስከሚናገራቸው ድረስ ሊሰሙት አይችሉም ይህ ያልዳኑት ሰዎች በሀጥያታቸው ምክንያት የመጥፋታቸውን ሀላፊነት አያጠፋውም "ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ" (ሐዋ 3:23)።

የክርስቶስን ድምጽ መስማት የምንችለው ኃያሉን እና የመፍጠር አቅም ያለው ያሃ ቃሉን በእኛ ልብ ሲናገር ብቻ ነው። በእርግጥም ካልሰማነው ስለምንጠፋ እርሱን መስማት አለብን። እንደ ነብይነቱም የእኛን ሙሉ ሀሳብ ይፈልጋል። "ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል" (ዕብ 2:1)።

## ክርስቶስ ብቸኛው ሊቀካህናችን

እንደ ብቸኛው ሊቀ ካህናችን የክርስቶስ ስራ ለሀጥያታችን እራሱን መስዋት አድርጎ የማቅረቡ ስራ ነው። እርሱ ሊቀካህናችን የሆነው መስዋቱን በማቅረብ እና መስዋትም እራሱ በመሆን ነው።

ክርስቶስ እንደ ካህንነቱ ስራው ለሀጥያታችን የሚሆንን መሰዋትን ብቻ ማቅረብ አይደለም። ይህ ብቻ  ቢሆን ኖሮ የእርሱ የክህነት ስራ አልቋል ማለት ነው። ነገር ግን ዕብራዊያን 7:28 ላይ እርሱ ለዘላለም ለእኛ ካህን ሊሆን እንደተሾመ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን ላይ እንዳሉት ካህናቶች የተቃጠለውን የማስተሰረያ መስዋት ካቀረቡ በኋላ ስራቸውን እንደሚጨርሱ ብቸኛውን የማስተሰርያ መስዋዕት ባቀረበ ጊዜ የእርሱም ሰራ የሚያበቃ አይደለም። ስለዚህም በራዕይ 1 ላይ ከብሮ እና ከማንም በላይ በላቀበት ሰዓት አሁንም የክህነት ስራውን እየሰራ ያለ መሆኑን ይናገራል። አለባበሱም እንዲሁ ነው፣ ያደረገው መደረቢያ፣ እና የታጠቀው የደረት ወርቅ ሁሉ የካህን ልብስ ነው።

የክርስቶስ የሊቀ ክህነት ስራ አሁንም በተለዩ ሁለት ረገዶች የሚቀጥል ነው። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል በሚሰራው የማስታረቅ ስራ ይቀጥላል። ይህም በብሉይ ኪዳን ካህኑ ከመሰዊያው እሳትን ወደ ቤተመቅደስ ወስዶ በመጋረጃው ፊት ለፊት ባለው የወርቅ መሰዊያ የእጣን ጭስ ያቀርባል ይህም ደግሞ ለክርስቶስ ስራ ምሳሌ ነው። ይህ መልካም መዓዛ ያለው እና ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ የሚያርግ ዕጣን የክርስቶስ ኢየሱስ ጣፋጭ ጸሎት ከእኛ ጸሎት ጋር ሆኖ ምላሽ እና ተቀባይነት ወደ ሚያገኝበት ወደ እግዚአብሔር መገኛ ሲገባ የሚመስል ነው።

እጣኑ የክርስቶስ አስታራቂነትን ስለሚያመላክት ካህኑ የእጣኑን እሳት የሚወስደው የማስተሰረያ መስዋዕት ከተከናወነበት ከታላቁ መሰዊያ ላይ ነው። ይህ እጣን የእግዚአብሔር ህዝብ በክርስቶስ አማላጅነት ጸሎቶቻቸው ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘቱን ያሳያል ። በሚቃጠል መስዋዕት ውስጥ ያለው ፍም ጸሎታችን ተቀባይነት ያገኘበት ብቸኛው ምክንያት እርሱም የክርስቶስ መስዋዕትነት ነው።

የክርስቶስ በክህነት የሰራው ስራ ዛሬም በህዝቦቹ ላይ በረከቱ በማፍሰስ ቀጥሎበታል። የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ እና የመንፈስ ቅዱስ ባርኮት የክርስቶስ የሰማያዊ ሊቀክህንነት ስራዎች ናቸው።

ይህ በብሉይ ኪዳን ካህኑ መስዋቱን የማቅረብ እና የማስተራረቅ ስራውን ሲጨርስ የተገኘውን የእግዚአብሔር በረከት ለህዝቡ በመባረክ ሲያቀርብ በምሳሌነት የተቀመጠልን ነው(ዘኊ 6:22-27)። ይህንንም በቤተ መቅደሱ ደጃፍ ላይ ቆሞ በጌታ ስም ህዝቡን በመባረክ ይፈጽማል (ሉቃስ 1:22)። ክርስቶስም ሰማያዊው ቤተመቅደስ ውስጥ ሆኖ በእግዚአብሔር ስም እኛን እንዲሁ ይባርከናል።

ይህን ለማድረግ ክርስቶስ በመጀመሪያ እራሱ መንግስተ ሰማይ መግባት ነበረበት። ይህም በብሉ ኪዳን በምሳሌነት ተቀምጦልናል - ሊቀ ካህኑ በአመት አንዴ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በስርየት መክደኛው ላይ

የማስተሰሪያ ደም ያቀርባል ። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ሕልውና ፊት ለፊት ለእኛ ሲቀርብ (ዕብ 9:24) ፣ ደሙን በእግዚአብሔር ፊት ይዞት ይመጣል። ይህ አሁንም መባረኩን እና በረከቱን ለህዝቡም በማምጣት የመማለዱ መሰረት ነው።

*በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ፍጹም የሆነ መስዋዕትን ያቀረበ ፣ ፍጹም የሆነ ምልጃን የሚያደርግ እና የእግዚብሔርን በረከት የሚያሰጠው ታላቅ ሊቀካህን አለው። ከእርሱ በቀር ሌላ ካህን አትመን!*

## ክርስቶስ ዘላለማዊ ንጉሳችን

የክርስቶስ ሦስተኛው ቢሮ የንግስናው ቢሮ ነው። ስለ ንግስናው ቢሮ እና ተግባራት ብዙ መማማር ያለብን ነገሮች አሉ።

የንግስናው ቢሮ ሁለት ግጽታ አለው እነርሱም በሀጥያተኛ አለም ላይ ያለው ገዢነት እና በህዝቡ ላይ ያለው ገዢነት ናቸው። የመጀመሪያው *የኃይሉ ገዢነት* ይባላል ሁለተኛው ደግሞ *የጸጋው ገዢነት* ይባላል።

በኃይሉ ገዢነት እርሱ በሉዓላዊነቱ የክፉዎችን ሀሳብ፣ ልብ እና ድርጊትን ሁሉ ለእራሱ አላማ እና ለመንግስቱ በመጠቀም ይቆጣጠራል። ይህንንም ኃይል በንግስና ስልጣኑ ለይሁዳ "የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ" ብሎ በመናገር ሲጠቀመው እናያለን (ዩሐ 13:17)። እንዲሰቀል እና ለህዝቡ ድህነት ደሙን ያፈስስ ዘንድ የጨለማን ስራ እንዲሰራ ይሁዳን ላከው። በፈቃዱ ወደ መስቀል እንደሄደ ሊያሳያቸው በአትክልት ስፍራ የያዙት ሰዎች እንዲወድቁ እና ወደኋላ እንዲሸሹ ሲያደርጋቸው ይህንኑ ተመሳሳይ ስልጣን ሲጠቀም እናየዋለን (ዩሐ 18:6)።

ይህ የንግስና ስልጣኑን በክርስቶስ ላይ *በሚያምጹ* ሰዎች እና ፈቃዱን *በሚጻረሩ* አመጸኞች ላይ ይጠቀማል። በእርሱ ላይ ተነስተው ይማከራሉ (መዝ 2) ነገር ግን እርሱ እነርሱ ላይ ሳቀባቸው ፣ አመጻቸውን እንኳን ለእርሱ መልካም ደስታ ተጠቀመበት።

ነገር ግን በጸጋም ይመራል። ይህ የጸጋው አገዛዝ ቤተክርስቲያንን እና በህዝቦቹ መካከል ያለ አገዛዝ ነው። ይህንንም ስልጣን በህዝቡ *ፈቃድ በኩል* እና *በፈቃዳቸው ውስጥ* ይጠቀማል። በጸጋው ፈቃዳቸውን ይለውጣል እርሱንም ደግሞ በፈቃዳቸው እንዲወዱት እና እንዲያገለግሉት ያደርጋቸዋል። የዚህ ገዢነቱ ውብ ገጽታ በመዝሙር 110:3 ላይ እንዲህ ተገልጧል "ሰራዊትህ በገዛ ፈቃዱ በጉንህ ይቆማል።"

በክርስቶስ ገዢነት ሁለት ገጽታዎች መካከል ያለው ልዩነት እርሱ ክፉዎችን በብረት በትር ሲገዛቸው እና ሲሰባብራቸው (መዝ 29) ፤ ህዝቡን ግን በእረኛ በትር በመግዛት ወደ ሰላም ሁሉ ይመራቸዋል (መዝ 23:4)።

እንደ ንጉስነቱ በህዝቡ ላይ መግዛት ብቻ ሳይሆን ለእነርሱም ይገዛላቸዋል ፣ በውጊያቸው ሁሉ እየመራቸው ለእነርሱ እንደሚዋጋላቸውም ጭምር ማስታወስ አለብን። እንደ ንጉስነቱ እርሱ የጠላቶቹ ሁሉ አሸናፊ ፣ የጨለማን ሙሉ ኃይል እና ግዛት ያስገዛ እና ድል የነሳ ደግሞም እኛ በእርሱ በኩል ከአሸናፊዎች ሁሉ የምንበልጥበት ንጉሳችን ነው (ሮሜ 8:37) ። ይህ ድሉ ገና የሚመጣ ድል ሳይሆን በመስቀሉ ሙሉ በሙሉ የተሟላ ድል ነው (ዩሐ 19:20 ፣ ቆላ 2:14-15)። "የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች ......." (ራዕይ 11:15) ። መንግስት፣ ሀይል፣ ክብር ለዘላለም እስከዘላለም ለእርሱ ነው (ማቲ 6:13)።

ድሉ የእኛም እንዲሆን ክርስቶስን እንደ ንጉስነቱ መቀበል አለብን። ይህንንም ደግሞ የጸጋውን መሪነት በልባችን በማክበር እናደርጋለን። ስለዚህም አብ ንጉሳችን ያደረገውን ልጁን እንውደድ አለዚያ ግን በእኛ ተቆጥቶ ከመንገዱ ያጠፋናል (መዝ 2:12)።

## የክርስቶስ አቋም ፤ ውረድቱ እና መክበሩ

ጥሩ የተሓድሶ ሥነ-መለኮት የመካከለኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አቋሞችን ያካተቱ ናቸው። የዌስትሚኒስተር አጭሩ የሀይማኖት ማስተማሪያ (Catechism) "ክርስቶስ እንደ ተቤዢያችን የነብይነት፣ የሊቀክህነት እና የንግስና ቢሮዎቹን *በውረድቱም በመክበሩም* አቋሞች ፈጽሞታል"[9] በማለት ይገልጽልናል። እነዚህ ውርደቱ እና የመክበሩ ሁናቴ የምንላቸው ምንድናቸው?

አቋም የሚለው ቃል በህግ ፊት ጥፋተኞች ወይም ንጹሐን የመሆናችንን ህጋዊ አቋም ያመላከታል ። አሁንም በዚህ ስፍራ የምንጠቀመው የክርስቶስ ስራ እንዲያመላክት ነው። በስራው የመጀመሪያው ክፍል እርሱም ደግሞ ውርደቱ በምንለው ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ለፊት የነበረው ህጋዊ አቋም የሀጥያተኛ እና የጥፋተኛ ሰው ነበር። በሁለተኛው ወይም በመክበሩ ጊዜ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት የጻድቅ የሆነበት አቋም ነበር።

በውርደቱ ጊዜ (ከውልደቱ እስከ ሞቱ ድረስ) ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ሀጥያተኛ የተቆጠረ ነበር። ትንሳኤውን፣ እርገቱን እና በአብ ቀኝ ያለውን ክብር ለፍርድም የሚመጣበትን ቀን በሚያካተው ከፍ ከፍ ባለበት ጊዜ ደግሞ እንደ ንጹህ ወይም ጻደቀ ተቆጥሯል።

ክርስቶስ በማንኛውም አይነት የሀጥያት ጥፋት የተገኘ ሰው አልነበረም ወይም ደግሞ በግሉ መጽደቅ አያስፈልገውም ነበር። ነገር ግን ሀጥያት ተሸካሚ እንዲሆን የሁሉንም ሀጥያት ጌታ በእርሱ ላይ እኖረው በዚህም እንደ ጥፋተኛ የሀጥያትን ቅጣት ሙሉ እንዲቀበል እና እንዲሰቃይ ከእኛ ተቆጠረ (ኢሳ 53:6) ። በተመሳሳይ ደግሞም በእኛ ምትክ ንጹህ እና ጻድቅ ሆኖ ተቆጥረ። ኢሳይያስ 53 ላይ ይህንን "ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ" በማለት ያመላክታል (ቁጥ 12) ። ክርስቶስ እራሱ በመዝሙር 69:5 ላይ "አቤቱ፥ አንተ ስንፍናዬን ታውቃለህ፥ ኃጢአቴም ከአንተ አልተሰወረም" የእራሱ ሀጥያት ስለነበር ሳይሆን የእኛን መተላለፍ እንደተሸከመ (እንደለበሰ) ሆኖ ሲናገር እንመለከታለን።

ክርስቶስ "ከህግ ተላላፊዎች" ጋር ስለተቆጠረ "በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም" ነበር (ኢሳ 53:4) ። ጌታን እንደ ፈራጅ ደስ እንዲለው "በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ" (ቁጥ 10)። በመከራው ፣ በፈተናው እና በመስቀል ሞቱ የተሸከመውን ሀጥያት እራሱ እንዳደረገው ሆኖ "አቤቱ አቤቱ ስለምን ተውከኝ?" ብሎ እስኪጸልይ ድረስ በገዛ አባቱ ተቀጣ።

ሀጥያታችንን እንደተሸከመው ሰው ክርስቶስ ለእኛ ሲል ደግሞ መጽድቅ ነበረበት። ስለዚህም ቃል ኢስይያስ 53:11 ላይ የእግዚአብሔር ጽድቅ አገልጋይ ብሎ ሲጠራው እንመለከታለን። "ጽድቅ........በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ" (1ኛ ቆሮ 1:30) ።

የእግዚአብሔር ልጅ ከተላላፊዎች እንደ አንዱ ስለእኛ ሲል መቆጠሩ የወንጌል ልብ (ማዕከል) እና የመጽሐፍ ቅዱስ አስገራሚ እውነታ ነው (ኢሳ 53:12) ። በዚህም የገዛ አባቱ እኛ ይቤዥ ዘንድ በዚህ መሰረት ፈረደበት። በእርግጥም እንዴት ግሩም አዳኝ አለን! እርሱንም የላከው ፍቅር እጅግ ድንቅ ነው!

## የክርስቶስ ዝቅ ብሎ መወለድ

ክርስቶስ ከአገልግሎቱ በፊት ስለነበረው ህይወቱ በደንብ የምናውቀው ስለ ውልደቱ ነው ይህም ደግሞ ድሃ ሆኖ መውለዱ፣ በመገፋቱ፣ በመከራ መምጣቱ እና በስደት መሆኑ ላይ አትኩሮት ይሰጣል።ቤተልሄም ፣ ግርግሙ ፣ መጠቅለያው ፣ እረኞቹ ፣ ወደ ግብጽ መሸሹ ሁሉም አንድን ታሪክ ይናገራል።

የውልደቱ ታሪክ ለምን በዚህ ጥልቀት ተነገረን፣ በዝቅታ መወለዱስ ለምን እንደዚህ አትኩሮት ተደረገበት? ይህ የሆነበት ምክኒያት የእርሱ የዝቅታ ውልደት የውርደቱ የመጀመሪያው ደረጃ በመሆኑ ነው። ስለ እኛ ፍርደኛ ሀጥያተኞች እግዚአብሔር ይከፍለው የጀመረው ከውልደቱ አንስቶ ነው።

ይህ ታሪክ የእኛን ሀዘን ለመቀስቀስ እና እርሱ ባለፈበት ድህነት እና መገፋት የተወለደ የለም የሚለውን ለመናገር አይደለም። ታሪኩ የማህበረሰብ ህሊና ጉዳይ ያለው ወይም በድህነት እና በመከራ ላይ ማህበራዊ ተሓድሶ ያስፈልጋል የሚል ጥሪም አይደለም። ይልቁንም የወንጌሉ አካል ስለሆነ እና ክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑ ይታይ ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎልናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ዝቅ ብሎ የመወለዱን ምክንያት ይነግረናል “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው” (2ኛ ቆሮ 5:21) ። የእርሱ ዝቅ ማለት ፣ መዋረድ እና መደህየት የህዝቡን ሀጥያት ተሸክሞ መሰቃየቱ እና ህዝቡን የመቤዠቱ አንዱ አካል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ በግልጽ 2ኛ ቆሮንቶስ 8:9 ላይ “የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ” ብሎ ይነግረናል። የእርሱ ድህነት ተሰገዖውን እና ከእርሱ ጋር የሚያያዙ ነገሮች ማሳያ እንዲሆን መሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለውም። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው ይህ የሆነው እኛ በድህነቱ በምድራዊ ሀብት ሳይሆን በሰማያዊው የማዳኑ ሀብት ሀብታም እንሆን ዘንድ ነው (ኤፌ 1:3) ።

ሁሉም የእርሱ መከራ ለእኛ ድህነት ነበር። የእርሱ መዋረድ ለእኛ ከፍ ከፍ ማለት ፣ የእርሱ ዝቅታውም ለእኛ ክብር ነው። እርሱ በመስቀል ብቻ ሳይሆን በኖረበት ዘመን ሁሉ አዳኛችን ነበር። እንዴት ያለ አዳኝ ነው!

እርሱ ከውልደቱ ጀምሮ አዳኛችን መሆኑ እጅግ አስፈላጊ ነበር። እኛ ሀጥያተኞች ፣ የተመረዝን እና ብልሹ ሆነን በመወለዳችን እርሱም የሀጥያትን መከራ እና ቅጣት ከውልደቱ ጀምሮ መቀበል ነበረበት (መዝ 51:5) ። ህይወታችን በሙሉ ከውልደታችን እስከ ሞታችን ድረስ በሀጥያት ግዛት ውስጥ እንደሆነ ሁሉ ህይወታችን በሙሉ ደግሞ በእርሱ የመከራ ህይወት ሊቤዥ ይገባል። ይህም ደግሞ የውርደትን፣ የሀዘኑን ጥግ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም ፈጸመው።

ስለዚህ የውልደቱ ታሪክ ስሜታችን የሚቆሰቆስበት እና የምናዝንበት ታሪክ ብቻ የምንዘጋው ጉዳይ ሳይሆን ወንጌል ነው። ስለ ውልደቱ ስንሰማ ሽማግሌው ስሞዖን ክርስቶስን በህጻንነቱ ሲያየው እንደተናገረ “ጌታ ሆይ፥

አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤ ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው" ማለት አለብን (ሉቃስ 2፡29-32)።

## የክርስቶስ የመከራ ህይወት

የክርስቶስ የመከራ ህይወት የውርደቱ ሁለተኛ ደረጃ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ነገሮችን ፤አንዳንድ ጊዜም ህይወቱ ከፈተና ውጪ ምንም ትርጉም ያለው እስከማይመስለን ድረስ በምድራዊ ህይወቱ ብዙ ፈተናዎችን አሳልፏል ። በእርግጥ "በመከራ አለፈ" ከሚለው ቃል ውጪ የተሻለ  ህይወቱን የሚገልጽ ንግግር የለም ።

እርሱ ደቀመዝሙር ሊሆነው ለፈለገው ሰው "ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው" እስከሚል ድረስ ድሃ ሆነ (ማቴ 8:20) ። በስተመጨረሻም የነበረውን አንድ ነገር ውስዱበት ልብሱንም ቀደዱት በጨርቁም ላይ እጣ ተጣጣሉበት።

እርሱ "የተናቀ ከሰውም የተጠላ"  (ኢሳ 53:3) ፣  "ያለ ምክኒያት የተጠላ" (ዩሀንስ 15:25)  ፣ ለገዛ ወንድሞቹ ባዳ (መዝ 69:8) ፣ በሀጥያተኞች ደግም የተሞገተ (ዕብ 12:3) ፣ በእራሱ ህዝብ የተገፋ (ዩሀንስ 1:11)፣ በደቀመዛሙርቱ የተሸጠ እና የተካደ (ማቴ 26:56, 74) ፣ ከአመጸኞችም ጋር የተቆጠረ (ኢሳ 53:12) ነበር።

የአለማዊያን እና የሀጥያተኞች ጓደኛ ፣ (የእግዚአብሔርን) ስም አጥፊ፣ ከሰይጣን ጋር አንድ መንግስት ያለው፣ ለሀገሩ ደህንነት ጠንቅ (ዩሀንስ 11:47-50) የተባለ ሰው ነበር። የንግስናው ንግግሮች የተናቁ ፣ ከእርሱ በላይ ቄሳር ተቀባይነት ያለው ንጉስ ነበረ ፣ ከእዚህም በላይ ወንበዴው ባርናባስ ከእርሱ ይልቅ ተመረጠ። በአይሁዳዊያን ለብዙ ጊዜ የግድያ ሙከራ ተደርጎበታል። በመጨረሻም ጠላቶቹ በፊቱ ላይ ተፉበት ፣ በጥፊ መቱት ፣ አፌዙበት ፣ ቀለዱበት ፣ ገረፉት ከዚያም ሰቀሉት። እንዴትስ ያለ መከራን ተቀበለ!

ከውርደቱ ፣ ከማፈሩ ፣ ከመገፋቱ ወይም ከህመሙ በላይ የሚበልጠው መከራ ግን ስለሀጥያታችን በእግዚአብሔር ቁጣ ውስጥ ማደሩ ነው። ይህንን ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በኢሳይያስ 53:3-6 ይናገራል።

ክርስቶስ የተጠላው እና የተገፋው ፣ በሀዘንም የተዋጠው እኛ ስላላከበርነው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር የተመታ እና የተቀሰፈም ሰለነበር ነው (ቁጥ 4)። ስለዚህ በዚህ ሁሉ መከራ "እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ።" በመከራውም ሁሉ እግዚአብሔር "የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" (ቁጥ 6)። ከዚህም አንጻር ስንመለከተው ማንም እንደ እርሱ በሀዘን የኖረ የለም (ሰቆ. ኤር 1:12) ።

ይህ ለቤዝዎታችን አስፈላጊ ነበር። በህይወታችን በሙሉ በሀጥያት ኖረናልና ክርስቶስ የሀጥያታችን ዋጋ በመስቀል ሞት ብቻ ሳይሆን ዘመኑን ሙሉ ስለሀጥያታችን በመሰቃየት መክፈል ነበረበት። በዚያ ሁሉ መከራ ያለ ሀጥያት በመታዘዙ እኛ ልንከፍል ያልቻልነውን የእግዚአብሔርን ታላቅ የመታዘዝ እዳ እርሱ በመታዘዝ ካሰልን ወይም ከፈለልን ። ክርስቶስም ስለዚህ በመዝሙር 69:4 "………በዚያን ጊዜ ያልቀማሁትን መለስሁ" በማለት ተናገረ።

ዕብራውያን 5:7-9 ይህንን ሁሉ አጠቃልሎ እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል "እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።"

## የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት

ሦስተኛው የክርስቶስ ውርደት ደረጃ ሞቱ ነው። የክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞት እና የደሙ መፍሰስ የታሪክ ሁሉ ማዕከል እና ለወንጌል የልብ ምት ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 2:2 ላይ "በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና" በማለት ይገልጸዋል። እንደገናም ደግሞ ገላቲያ 6:14 "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" ብሎ ተናግሯል።

መስቀሉ ብዙ ነገር ነው። የአለም ፍርድ ነበር። ኢየሱስ እራሱ ይህንን በዩሀ 12:31 ላይ ተናግሯል ፣ ጨለማው ፣ የመሬት መንቀጥቀጡ እና የመጋረጃውም መቀደድ ይህንን ይናገራል። በመስቀል ላይ የተገለጠው

የእግዚአብሔር ፍርድ እጅግ ግልጽ ከመሆኑ የተነሳ በስቅለቱ የነበሩ ሰዎች ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ደረታቸውን እየደቁ ነበር (ሉቃስ 23:48)።

መስቀሉም ለማያምኑ ሰዎች የመደናቀፊያ እና የመውጊያ ድንጋይ መሆኑን የሚቀጥል ነው። በመስቀል ላይ ክርስቶስ የማዕዘን ድንጋይ ብቻ ሳይሆን የመሰናከያም ድንጋይ ጭምር ሆነ (1ኛ ጴጥ 2:6-8) ።

ስለዚህም በእምነት እና ባለማመን መካከል፣ በመመረጥ እና በመተው መካከል ልዩነት የሚያመጣው መስቀሉ ነው። መስቀሉ እና “ኢየሱስንም በመካከላቸው” (ዩሀንስ 19:18) መሆኑ በግልጽ አንድ ሰው የሚያምነው እና የማያምነው በሰው ምክንያት ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል እና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በተገለጸው የእግዚአብሔር አላማ ምክኒያት ነው።

የመስቀሉ ደም በሰማይ እና በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ መታረቂያ ነው (ቆላ 1:20) ። ነገር ግን ከሁሉም በላይ የክርስቶስ መስቀል ከእግዚአብሔር ጋር መታረቂያችን እና ለሀጥያታችን ክፍያ ፣ ስርየታችን እና ቤዝዎት ነው (ቁጥ 21-22) ። በመስቀሉ በተለይም ደግሞ በሦስቱ የጨለማ ሰዓታት የክርስቶስ ኢየሱስ መከራ እና ውርደት የመጨረሻው ጫፍ ላይ እንደደረሰ እንመለከታለን። በዚያ ሰዓት ሀጥያታችንን ተሸክሞ ወደ ፈራጁ እግዚአብሔር ፊት ቀረበ። በእነዚያ ጥቂት ሰዓታትም የተፈጠረው ነገር ሁሉ ከመረዳታችን በላይ ነው።

በዚያ ጨለማ ሰዓት “አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?” የሚል አንድ አጭር እና ግልጽ ንግግር ወደ እኛ መጥቷል። የእግዚአብሔር ልጅ በአባቱ ተትቶ እኛ ለሀጥያታችን ይገባን የነበረውን ሁሉ ሲቀበል ነበር። እግዚአብሔር እኛን ይቀበለን ዘንድ እና ለዘላለም እንዳንተው ስለ እኛ ሲል እርሱ ተተወ። ለዘላለምም በእነዚያ ሦስት የጨለማ ሰዓታት የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ እንዳንቀበል ደግሞም እግዚአብሔር ሀይለኛ፣ ቁጡ እና የማይበርድ ዳኛ ሆኖ እንዳናየው ስለሀጥያታችን ሁሉ የእግዚአብሔርን ቁጣ ተቀብሎ እርሱ ከዚያ ቁጣ አተረፈን።

በመጨረሻም ጳውሎስ በገላቲያ 6:14 ላይ “ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት” በማለት እንደሚናገረው የክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል መሞት የጽድቃችን ሁሉ ምንጭ ነው። ስደት የሚደርስብንም ስለዚሁ ምክኒያት ነው (ገላ 6:12)። እራሳችንን መካዳችን ስለእርሱ የምናደርገው ምሳሌ ነው (ማቴ 10:38)። ይህም በዚህ እና በሚመጣው ምድር ለምንቀበለው በረከት ሁሉ ምንጭ ነው። ስለዚህ ከክርስቶስ እና ከመስቀሉ ውጪ የምናውቀው ሌላ ነገር አይኑር።

## የተወሰነ ስርየት

ካልቪኒስቶች ክርስቶስ ለሁሉም ሰው ሳይሆን ለተመረጡት ብቻ እንደሞተ በሚናገረው በተወሰነ ስርየት ያምናሉ። የተወሰነ ስርየት ማለት የክርስቶስ ሞት እና ደም የተወሰነ ነው ለማለት ሳይሆን የሞተው "የተወሰነ" ቁጥር ላላቸው ሰዎች ብቻ ነው ማለታችን ነው።

የተወሰነ ስረየት ከምንለው ለተመረጡት ስርየት ብንለው የተሻለ አገላለጽ ይሆናል። የተመረጠ የሚለው ሀሳብ ክርስቶስ ለተወሰኑ ስዎች ብቻ መሞቱን የሚናገረውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ይደግፋል።

በተወሰነ ወይንም ለተመረጡት ስርየት የምናምነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ክርስቶስ ለሁሉም ሳይሆን ለብዙዎች  እንደሞተ (ኢሳ 53:11, ማቲ 20:28, ማቲ 26፡28, ዕብ 9:28) ፣ ለህዝቡ እንደሞተ (ኢሳ 53:8)፣ ማቴ 1:21) ፣ ለበጎቹ እንደሞተ (ዩሐ 10:14-15 ፣ 26-28) እና ለቤተክርስቲያን እንደሞተ (ሐዋ 20:28) የሚያስተምሩ ክፍሎች በመኖራቸው ነው።

"አለምን" ወይንም "ሁሉንም" የሚሉ ክፍሎች የተወሰነ ቁጥር ነው ከሚለው ክፍል ጋር የሚጣረሱ ናቸው ብለን አናስብም። የእግዚአብሔር ቃል በፍጹም እራሱን አይቃረንም።  እነዚህን መሰል ክፍሎች የሚያስተምሩን ክርስቶስ በሰዎች መካከል ምንም መድልዎ ወይንም ልዩነት ሳይፈጠር እንደሞተ እንዲ ለሁሉም ሰው እንደሞተ ነው። በሌላ አማርኛ ክርስቶስ የሞተው ለሰው ልጆች ሁሉ (1ኛ ጢሞ 2:1-6 )  ፣ በእርሱ ላሉ ሁሉ (1ኛ ቆሮ 15:22) ወይም ለራሱ ህዝብ "አለም"  ብለው የሚያስተምሩ ክፍሎች  እርሱም ከነገድ እና ከቋንቋ የተዋጀውን ህዝብ መሆናቸውን የሚያስተምሩ ክፍሎች ናቸው (ዩሐ 3:16 ከ ዩሐ 17:9 ጋር አነጻጽሩ) ።

የተወሰነ ስረየት ብቻ የክርስቶስን አዳኝነት አጉልቶ ያሳየናል። ክርስቶስ ለሰው ሁሉ ሞቶ ነገር ግን ሁሉም ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ሰራ መዳን አልቻሉም የሚለው አስተሳሰብ የክርስቶስን የማዳን ስራ መሰረት ያናጋል። እንደዚህ አይነት አስተምህሮ የክርስቶስ መከራ እና ሞት ለድህነታችን በቂ ስላይደለ በተለምዶ የሰው ነጻ ፈቃድ የምንለው ያስፈልጋል ይላል። አስተምህሮው ክርስቶስ ለሁሉም ሞቷል ቢልም አሁንም ሰዎች ወደ ገሃነም ይገባሉ። ይህ እውነት ከሆነ የክርስቶስ ደም በከንቱ ለአንዳንዶች ፈሷል ፤ ሞቱም ደግሞ ለእነርሱ

እርባና ቢስ ነበር ማለት ነው። ስለዚህም ሞቱ የእውነትም ካሳ ፣ ስርየት ፣ ለሀጥያት በቂ ያልሆነ እና እኛን ከአብ ጋር ሊያስታርቀን ያልቻለ ነው ማለት ነው።

ክርስቶስ ለሰው ሁሉ ከሞተ ፣ አንዳንዶች ባይድኑ እና ልዩነቱ ነጻ ፈቃዳቸው ከሆነ በድነታችን ውስጥ ወሳኙ እና ዋናው ነገር ነጻ ፈቃዳችን እንጂ የክርስቶስ ሞት አይደለም ማለታችን ነው። ድህነታችን እርሱ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን እኛ ላይ የተመሰረተ ይሆናል ማለት ነው። በእንደዚህ አይነትን አመለካከት ስለክርስቶስ ሞትም ሆነ ስለእራሳችን እንዳናስብ እግዚአብሔር ይርዳን።

ክርስቶስ የሞተው አብ መርጦ ለሰጠው ልጆቹ ነው የሚለው አስተምህሮ እርሱ ለድህነታቸው የሚያስፈልገው ነገር በመከራው እና በሞቱ ስለጨረሰ ሌላ የሚያስፈልግ ነገር የለም ይላል። ስለዚህም ሞቱ የእውነት ማስተሰርያ ፣ ማስታረቂያ ፣ የሀጥያት ሙሉ ክፊያ ፣ ካሳ እና የሚያረካ ነው ማለት ነው። ስለዚህ እርሱ የእውነትም የሞተላቸውን ሁሉ ያድናቸዋል።

ውስን/የተወሰነ ስርየት ክርስቶስ እንዲሁ የድህነትን መንገድ ክፍት አላደረገውም በማለት ያስተምራል። እርሱ ልዑል እና አዳኝ ነው። ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን!

## የክርስቶስ ወደ ሲኦል መውረድ

የክርስቶስ ውርደት ሌላኛው ደረጃ ደግሞ ወደ ሲኦል መውረዱ ነው። በጥንቷ ቤተክርስቲያን በሐዋሪያት የእምነት መገለጫ  ክርስቶስ “ወደ ሲኦል ወርዷል” ብለው ያውጃሉ። በዚህም አዋጅ በተለይም ደግሞ  “ወደ ሲኦል ወርዷል” የሚለውን የእምነት አዋጅ “ተሰቅሏል፣ ሞቷል፣ ተቀብሯል” የሚለውን አዋጅ የሚከተል በመሆኑ ሁሌም ቢሆን ብዙ አለመግባባቶች እና ክርክሮች ይነሳበት ነበር ።

ብዙዎች ክርስቶስ ከሞተ በኋላ እና ከትንሳኤው በፊት በቀጥታ ሲኦል ወደሚባል ስፍራ እንደሄደ ያስተምራሉ። ይህንንም ለማረጋገጥ ወደ 1ኛ ጴጥሮስ 3:18-20 ይጠቁማሉ። ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች ከትንሳኤው በኋላ “በመንፈስ” ስለሆነ ነገር የሚናገሩ ናቸው። በተለይም ክርስቶስ ከሞቱ በኃላ ወደ ሲኦል ገብቷል ማለቱ በሉቃ 23፡43 ላይ ከመሞቱ በፊት ክርስቶስ “ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው” የሚለውን ክፍል ይቃወማል።

አንዳንዶች ወደ ሲኦል ወርዷል የሚለው ትርጉም ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ መሆኑን የሚያመላክት ነው ይላሉ። በእርግጥ ይህ ሀሳብ መዝ 16:10 ላይ ክርስቶስ በሲኦል እንዳለ “ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥

ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም" በማለት ከተናገረው ሃሳብ ጋር ይበልጥይስማማል። የቁጥር 10 ሁለተኛ ስንኝ ስለመበስበስ የሚያወራ ሲሆን የሚቀድመው ስንኝ ደግሞ ስለክርስቶስ ስጋ የሚናገር በመሆኑ መዝሙር 16:10 ስለክርስቶስ መቀበር የሚያወራ እንደሆነ እንድንገምት ያደርገናል።

የዌስትሚኒስተር ትልቁ የሀይማኖት ማስተማሪያ እንዲህ ይላል "የክርስቶስ ከሞቱ በኋላ ያለው ውርደት መቀበሩን እና በሞት ሀይል ውስጥ መሆኑን እና እስከ ሶስተኛው ቀን ድረስ መቆየቱን ያካተተ ነው ፤ በሌላ አገላለጽ ወደ ሲኦል ወረደ ተብሎ ተቀምጧል " [10] ።

ነገር ግን በሐዋ ስራ 2:31 ላይ ከመዝ 16፡10 ላይ የተወሰደው "ሲኦል" የሚለው ቃል ያለምንም ጥርጥር አዲስ ኪዳን ውስጥ ስለዘላለም የቅጣት ስፍራ የሚናገር ነው። ስለዚህም ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም በሲያል ውስጥ ነበር፣ ሆኖም ግን ይህ ስፍራ በእርግጥም ሲያል ላይሆን ይችላል።

መቼ እና እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ? እኛ ክርስቶስ ወደ ሲኦል የወረደው የሃይድልበርግ የእምነት አዋጅ በመመስረት "የሲያል ህመም እና ቅጣቶች" [11]በመስቀል ላይ ስለእኛ ራሱን አሳልፎ ሲሰጥ እንደሆነ እናምናለን።

ይህንንም ከመስቀሉ "አምላኬ አምላኬ፣ ስለምን ተውከኝ?" ብሎ ሲናገር በግልጽ አስረድቶናል አሳይቶናል (ማርቆስ 15:34)። ከእግዚአብሔር ህልውና መጣሉ እና በእርሱ መተው የሲያል ትርጉም ነው። በዚህም መልኩ ክርስቶስ በመከራ አለፈ።

ክርስቶስ ወደ ሲያል ወረደ የሚለው ቀብሩን ወይም በመስቀል ላይ ያሳልፈውን ወይም ደግሞ ሁለቱንም አንዳላይ ያመላክታል። ይህም ደግሞ የእርሱን ሊገለጥ ወይንም ሊብራራ በማይችለው መከራው እና ሞቱ ነፍሳችንን ከጥልቁ ሲያል ማስመለጡን ያስታውሰናል። በእንደዚህ ባለ መከራ በእግዚአብሔር አብ ህልውና እና በቅዱስ መላዕክቶቹ ባሉበት ለህዝቡ ሁሉ ዘላለማዊው የክብርን ቦታን ተቀብሏል። በዚያም እርሱ እና እኛም ከእርሱ ጋር ሆነን ዘላለማዊ በረከት እና ክብርን እንቀበላለን።

## የክርስቶስ መቀበር

የክርስቶስ ቀብር የወርደቱ አንድ አካል ነው ተብሎ ይታሰባል። የሐዋሪያት ስራ 2:24ም ይህ ለምን እንደሆነ ያብራራልናል። ከሙታን እስኪነሳ ድረስ “የሞት ጣር” አልተጠፋም ነበር። እስከ ትንሳኤው ቀን ድረስ “በሞት አለም ውስጥ ወይም በሞት ኃይል ውስጥ ነበር”[12] ማለት ነው።

እርሱ መከራ እንደተቀበለ እና ሞታችንን ድል እንደነሳ ስለሚያሳየን የእርሱ መቀበር አስፈላጊ እና የስራው ዋና አካል ነው። እርሱ ስለተቀበረ ብቻ እኛ “ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ?” ማለት እንደምንችል እና በመቃብር ውስጥ ተረስተን እንደማንቀር እናምናለን (1ቆሮ 15፡55 ፣ መዝ 31:12) ።

በክርስቶስ መቃብር ውስጥ በሀጥያት እና በሞት ላይ ያለው ድል ሲገለጥ እናያለን። የሐዋሪያት ሥራ 2:31 ይህንን “ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ” በማለት በግልጽ ይናገራል።

እነዚህ ቃላቶች ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ በነበረበት ጊዜ የእርሱ ስጋ የእኛ ስጋ እንደሚበሰብሰው እንዳልበሰበሰ የሚያመላክቱ ናቸው። የሐዋሪያት ሥራ 13:36-37 ክርስቶስን ከዳዊት ((እና ከሌሎቹ) ጋር በማነጻጸር እንዲህ ይላል “ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ፥ ከአባቶቹም ጋር ተጨምሮ መበስበስን አየ፤ ይህ እግዚአብሔር ያስነሣው ግን መበስበስን አላየም” በማለት ይናገራል።

ከዚህ አንጻር ክርስቶስ ሦስት ቀን በመቃብር ውስጥ መሆኑ ሞትን እና የሞትን ኃይል ሁሉ በመስቀሉ ሞት ድል እንደነሳው እንረዳለን። ይህንንም ያደርገው “የሞት መውጊያ” ስለተባለው ስለሀጥያት ዋጋ በመክፈል ነው (1ኛ ቆሮ 15:56) ። ከሀጥያት ውጪ ሞትም ሆነ መቃብር ሀይል የለውም። ሞትም ክርስቶስን ሊይዘው ያልቻለበት ምክንያት ይህ ነው (ሐዋ 2:24) ። ሞትን ፍጹም በማሸነፉ የተለመደውን መበስበስ እንኳን ሞት ሊያመጣበት አልቻለም።

በሐዋሪያት ሥራ 13:37-38 ሐዋሪያው ጳውሎስ ክርስቶስ መበስበስን አላየምና ለሀጥያታችን የምናገኘው ምህረት በእርሱ በኩል እንዳለ እንወቅ ብሏል። ስለዚህም ስራው የተሟላ ስለመሆኑ እና ለሀጥያታችን ፍጹም የሆነን ማስተሰርያን መቀበላችንን ለመረዳት እስከ ትንሳኤው ልንጠብቅ አይገባንም። ይልቅ መቃበሩ ስራውን ሁሉ ያረጋግጥልናል። ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ መበስበስን ባለማየቱ እኛም አንድ ቀን የማንበሰብስ እንደምንሆን “ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና” እርግጠኞች ነን። ይህም ሲሆን “ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ” የሚለው ንግግር ይፈጸማል (1ኛ ቆሮ 15:53-54)።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደሞተ እና በሦስተኛው ቀን ደግሞ ከሞት እንደተነሳ ልንረሳው አይገባም። ደግሞም ክርስቶስ "እንደተሰቀለ፣ እንደሞተ እና እንደተቀበረ" አንርሳ። በዚህም እርሱ አዳኛችን መሆኑን ያመለክተናልና። የመቃብር የመበስበስ ሃይል የሆኑት የሚያስጠላ ሽታ፣ የስጋ መበስበስ ፣ ወደ ሚያስጠላ መልክ መለወጥ እና የመሳሰሉት የመቃብር የመበስበስ ሃይልን ወካዮች ሁሉ በእርሱ ድል ተነስተዋል ። እርሱ መንፈሳዊ የሀጥያት መበስበስን ፈጽሞ ስላጠፋው ስንሞት እንኳን ሰውነታችን "በክርስቶስ እያንቀላፋ" ብቻ ይሆናል።

## የክርስቶስ ትንሳኤ

የክርስቶስ ትንሳኤ ከፍ ከፍ የማለቱ (የመክበሩ) የመጀመሪያ ደረጃ ነው። የመቤዠታችንም ታላቅ ስራ አንዱ አካል ነው። ያለ ትንሳኤው መስቀሉ እንኳን የተሟላ አይደለም። የእግዚአብሔርም ቃል ይህንን እውነት በ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:17 "ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ" በማለት ያስታውሰናል።

ያለትንሳኤው በሁለት መንገድ እና በሁለት ምክንያቶች አሁንም በሀጥያት ውስጥ እንቆያለን። እስካሁን በህግዊ መንገድ እና በእውነት በምልልሳችን በሀጥያት ውስጥ እንሆን ነበር።

*በመጀመሪያ በህግ ሀጥያተኞች እንሆን ነበረ ማለት ያለ ትንሳኤው ልንጸድቅ እና የሀጥያት ይቅርታን ልናገኝ አንችልም ነበር ማለታችን ነው።*

ለምን? ምክንያቱም ጽድቅ የእግዚአብሔር የዳኝነት ስራ ስለሆነ ነው። እርሱ እኛን ጻድቃን መሆናችንን የሚያሳይ ውሳኔ ማስተላለፍ (መወሰን) አለበት። ይህንንም የሚያደርገው ክርስቶስ በእኛ ፈንታ ሆኖ የፈጸመውን ስራ በመቀበል እና በመፍቀድ እርሱን ከሞት ሲያስነሳው ነው። ስለዚህም ትንሳኤው ዘላለማዊ እና የማይለወጥ የመንግስተ ሰማይ እና የምድር ዳኛ ጽድቃችንን ያተመበት መንገድ ነው።

እንደዚህ አስቡት ክርስቶስ በመስቀል ላይ "ተፈጸመ" ሲል ፤ አምላክም (እግዚብሔር አብ) ክርስቶስን ከሞት በማስነሳት "ተፈጸመ" አለ። ስለዚህም እግዚአብሔር በሕግ እኛን በፊቱ በሚያጸድቅበት ፍርድ ይህንን አስተላለፈልን።

ሮሜ 4:25 “እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ……” የሚለው ይህንኑ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ክፍሎች እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሞት ማስነሳቱ ላይ ትኩረት የሚሰጡት ለዚህ ነው።

ሁለተኛ ያለ ትንሳኤው እኛ የእውነት በተግባራችን ሀጥያተኞች ብቻ እንሆን ነበረ። ክርስቶስ ከሞት ያልተነሳ ቢሆን ኖሮ የእምነትን ስጦታ ፣ በእምነት በኩል የሀጥያት ይቅርታን እና ከሀጥያታችን ሊያድነን አይችልም ነበር። አሁንም በፊት እንኖርበት በነበረው የሀጥያት መንገድ እንኖር ነበር። እንደ ህያው ጌታችን ክርስቶስ ለሀጥያታችን ይቅርታ እና ከሀጥያታችንም ደግሞ ትድግናን ሰጥቶናል። እርሱ ሰላምንን እና ቅድስናን ሰጥቶናል።

ነገር ግን ይህ ሁሉ የክርስቶስን ትንሳኤ በበረከት የተትረፈረፈ መሆኑን አይገልጥልንም ። ትንሳኤው እኛ ወደ እግዚአብሔር መግቢያ ምክንያታችንም ነው። ከሙታን በኩር እንደመሆኑ ወደ እግዚአብሔር ህልውና እና ወደ እግዚአብሔር ስጦታ መግቢያ በሩን የከፈተልን ክርስቶስ ነው (ራዕይ 1:5) ። ለሌሎች ልጆች ሁሉ በር መክፈት የበኩር ልጅ የሁልጊዜ ስራ ነው  (ዘጽ 13:2, ኅዝ 20:26)። ክርስቶስ ከሞት ወደ ህይወት እና ወደ እግዚአብሔር ህልውና ለእኛ በሩን ከፍቶልናል።

ከዚያም ባሻገር የክርስቶስ ትንሳኤ እኛም አብረነው እንደምንነሳ የሚያሳይ ጽኑ አምድ ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:16 እንደሚያሰረዳው የእርሱ ትንሳኤ እና የእኛ ትንሳኤ የማይነጣጠሉ ናቸው። እርሱ ህያው ስለሆነ እኛም ህያዋን ነን።

እንግዲያስ የክርስቶስ ትንሳኤው የመቤዠታችን ሙሉ ውጥን በመሆኑ እና የእምነታችንን መሰረት ሳናናጋ እንዲሁ ሊካድ አይችልም ። ስለዚህም ለዘላለም በሚኖረው በእርሱ እመኑ በእርሱም ደስ ይበላቹ። በክርስቶስ ኢየሱስ መሰቀል እና ዳግም መነሳት የሚያምኑ ለዘላለም አይሞቱም።

## የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ

የክርስቶስ ማረግ ከፍ ከፍ የማለቱ (የመላቁ) አቋም ሁለተኛ ደረጃ ነው። በመቤዠት ስራው ውስጥ  የእርገቱ አስፈላጊነት በብሉይ ኪዳን እንደ ጥላ በገለጹት ክስተቶች ውስጥ በሚገባ ተንጸባርቋል። ይህም ጥላ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም የመመለሱ ተግባር ነው።

ቢያንስ አራት መዝሙራት ይህንን የእስራኤል ታላቅ ታሪክ በማክበር/ በማወደስ የክርስቶስን እርገት ጥላ ወካዮች አድርገው በግልጽ አመላክተዋል (መዝ 24, 47, 68 እና 132)። መዝሙራቶቹ በጣም በጥቂቱ ስለ ትንሳኤው በመናገራቸው በጣም የሚያስገርም ጉዳይ ነው ምክኒያቱም እኛ እንዲሁ ብንገምት ትንሳኤው ከእርገቱ በላይ ይልቃል ብለን ልንፈርድ እንችላለን።

በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ሲከበር የምናየው ክስተት ወይንም ቀን እርሱም የታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ የክርስቶስ እርገት ጥላ እንዴት ሊሆን ይቻላል? በአራት መንገድ ይህንን ያመለክተናል።

የመጀመሪያው ክርስቶስ ወደ ሰማይ እንዳረገ ሁሉ ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም “ወጣ” (2ኛ ሳሙ 6:12, መዝ 68:18, መዝ 132:8, ኤፌ 4:8) ።

ሁለተኛ በዳዊት ዘመን ታቦቱ (ታቦቱ ክርስቶስን የሚወክል እና እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የሚሆንበት እና ማንነቱን ለእነርሱ የሚገልጥበት ነበር) ከረጅም ጉዞ በኋላ ወደ መጨረሻው የማረፊያው ቦታ ገባ። እንዲሁ በእርገቱ ክርስቶስ በምድር የኖረው ህይወት እና ስራው ሲጠናቀቅ ውደ ሰማያዊው እረፍት ገባ (መዝ 132:8, 13-14, ዕብ 4:10)።

ሦስተኛ ዳዊት ታቦቱን ማምጣቱ የእስራኤል ጠላቶችን ድል መንሳቱን ስለሚያመላክት በመንግስቱ ተቀባይነት አግኝቷል። በተመሳሳይ ክርስቶስ በእርገቱ በክብር እና በግርማ ንግስናን በመቀበል የነገስታት ንጉስ እና የጌቶችን ጌታ ሆኖ ተገልጧል። በተማሪም ጠላቶቹ እና የእኛን ጠላት ድል ነስቷል (ፊሊ 2:9-11፣ መዝ 24:7-10 ፣ መዝ 68፡1 ፣ 18፣23) ።

አራተኛው በዳዊት ድል እና ሰላማዊው የሰለሞን መንግስት መከተል እግዚአብሔር ለአይሁዳዊን በብሉይ ኪዳን ስለ ከነዓን የገባውን ኪዳን ፈጸመላቸው (1ኛ ነገስት 8:56) ። በተመሳሳይ እግዚአብሔር ለእኛ የገባልንን ተስፋ በክርስቶስ እርገት ፈጽሞታል። በእርሱም በኩል ከሰማይ በመንፈሱ በኩል የተጠናቀቀውን የስራውን ትርፍ/ ጥቅም ሁሉ ሰጥቶናል (መዝ 68:19, መዝ 132:15-16)።

ስለዚህም እርገቱ ትንሳኤውን ይፈጽመዋል። ዳዊት ታቦቱን በሚመልስበት ሰዓት ለእስራኤላዊያን ሁሉ ስጦታን እንደሰጣቸው በእርገቱም ክርስቶስ በፈጸመው ስራ ጥቅምን እና ሽልማትን ያገኛል ከሙታን እንደተነሳው ጌታችን ደግሞ እርሱ የተቀበለውን መልካም በረከት ሁሉ በላያችን ላይ ያፈስልናል ማለት ነው (2ኛ ሳሙ 6:19, መዝ 68:18, ኤፌ 4:8-13)።

ስለዚህም እርገቱ እኛ ከእርሱ ጋር ወደ በሰማይ እንደምንሆን የሚያሳይ እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ ነው። ክርስቶስ ለእኛ ወደ ሰማይ በማረጉ ምክንያት እኛ አሁን በዚህ ሰዓት በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናል (ኤፌ 2:6) ።

የጌታችን እርገት የመቤዠታችን ስራ ቀላል እና አንድ ትንሽ አካል ሳይሆን የስራው ዋና እና አስፈላጊ አካል ሆኖ ተገልጧል ። ይህም ደግሞ በደስታ "አምላክ በእልልታ፥ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ። ዘምሩ፥ ለአምላካችን ዘምሩ፤ ዘምሩ፥ ለንጉሣችን ዘምሩ....... እርሱንም ከፍ ከፍ አደረጉት" እንድንል ያደርገናል (መዝ 47:5-6, 9) ።

## የክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጥ

የክርስቶስ ከፍ ከፍ ማለት (መላቅ) አቋም ሦስተኛው ደረጃ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእርገቱ ሰዓት ይህ እንደሆነ ይነግረናል (ኤፌ 1:20)። ይህ እንደ አዳኝ እና አስታራቂነቱ የማዳኑ ስራ አካል ነው።

ክርስቶስ በመለኮታዊ ባህሪው እግዚአብሔር ቢሆንም በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡ የእርሱን የሰውነት ባህሪ የሚያመላክት ነው። እንደኛ አይነት በሆነው ስጋው እና ሰዋዊነት (ሰው መሆኑ) ከሞት ተነሳ ፣ ወደ ሰማይ ያረገ እና አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል።

እግዚአብሔር "አካል፣ ሰውነት ሆነ ስሜት" [13] ሊኖረው እንደማይችል እናውቃለን። ስለዚህም እርሱ የሚታይ እና ስጋዊ "ቀኝ እጅ" እንደሌለው እናውቃለን። በአንድ ሰው በአንድ ሀያል እና ታላቅ ቀኝ እጅ በኩል መሆን ማለት በዚያ ሰው ፊት ታላቅ ክብር፣ ታላቅ ኃይል እና በረከት ማግኘት መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን (ዘፍጥ 48:8-22 ፣ 1ኛ ነገስት 2-29 ፣ ማቴ 25:33-34)። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ተቀምጧል ማለት የእርሱ ከፍ ከፍ ማለት (መላቅ) ለታላቅ ክብር፣ ስልጣን እና ኃይል መሆኑን ያመላክታል። በእግዚአብሔር ቀኝ እርሱ የጌቶች ጌታ እና የነገስታት ንጉስ ነው።

በዚያ *መቀመጡ* የንግስናውን ክብር እና ሀይል ያመላክታል።በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል ተቀምጦ በክብር እና ሞገስ ሁሉ *ነግሷል* ። በዚያ ስፍራ እንደ ንጉስ የተሾመው በእግዚአብሔር በእርሱ ሲሆን የንግስናው ኃይልም ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። በአንድ ክፍል ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል *ቆሟል*

ይላል (ሐዋ 7:55)። ይህም ደግሞ ወደ እኛ በክብሩ ሊመጣ እና የራሱ የሆኑትን ሊወስድ ለደማቸውም ሊበቀል እንደተዘጋጀ ያብራራልናል። ነገር ግን በተደጋጋሚ የምናነበው ተቀምጦ እንዳለ እናነባለን። ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለመምጣት እስከሚነሳበት ቀን ድረስ እንደተቀመጠ ይቆያል።

ይህንን ሁሉ ክብር እና ስልጣን ክርስቶስ የተሸለመው እግዚአብሔር አብ ከመጀመሪያው ጀምሮ የገባለት ተስፋ በመሆኑ ነው (ፊሊ 2:9, ዕብ 1:3) ። እነዚህን ሁሉ የሚቀበለው ፣ ከፍ ከፍ የሚለው እና የሚከብረው በሰውነት ማንነቱ መሆኑን ማስተዋል እጅግ ወሳኝ ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ ከፍ ከፍ ማለት አይችልምም አያስፈልገውም። ነገር ግን እንደ ሰው እኛን ወክሎ ከፍ ከፍ ብሏል።

እርሱ የሚቀበለውን ክብር፣ ስልጣን፣ ኃይል እና በረከት ለእኛ ለህዝቦቹ በመቀበል በመንፈሱ በኩል በእኛ ላይ ያፈስብናል ። ይህንን ጴጥሮስ በባለሀምሳ ቀን “ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው” በማለት ተናግሯል (ሐዋ 2:33) ።

በዚያው ክብር እና ሀይል እርሱ የተቀበለውን ማካፈል ብቻ ሳይሆን ልባች መቀበል እንዲችል ልባችንን ያዘጋጅልናል ፣ በቤተክርስቲያኑም ይሰበስበናል ፣ ብዙ መኖሪያ ባለበት በአባቱ ቤት ማረፊያን ያዘጋጅልናል ፣ ጠላቶቻችንንም ከእግሮቻችንን ስር ያደርግልናል። በአባቱም ቀኝ ሆኖ ለእኛ የማያቋርጥ መማለድን ከአባቱ ጋር ይማልድልናል። አባትም የተወደድው እና በቀኝ እጁ በኩል የተቀመጠውን ልጁን ካልሰማ ማንን ይሰማል?

## የክርስቶስ ዳግም መምጣት

ክርስቶስ ክፍ ከፍ የማለቱ (የመላቁ) የመጨረሻው ደረጃ ዳግም መምጣቱ ነው። የክርስቶስ መመለስ ጊዜው እና ሁኔታው በብዙ ክርስቲያኖች ውስጥ የማያግባባ የመነጋገሪይ ርዕስ ነው። ነገር ግን የመምጣቱ ጉዳይ ለሚወዱት እና ድህነታቸውን ከእርሱ ለተቀበሉት ሁሉ ተስፋ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም።

ይመጣል ማለት የምንወደውን እርሱን ፊት ለፊት እናየዋለን ማለት ነው። ከምድር ከሄደ ሁለት ሺህ አመታት ሆኖታል ሲመለስ ብቻም መልኩን እናየዋለን።

ክርስቶስ እንደገና ሲመጣ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ፍጻሜውን ያገኛል። በዚያም ቀን የበጉ እና ሙሽራዋ ቤተክርስቲያን ታላቅ የሰርግ ድግስ ይጀምራል ቤተክርስቲያንንም ወደ እራሱ ይወስዳታል (ራዕይ 19:6-9) ።

ያን ጊዜ ቤተክርስቲያንም ያለ ልዩነት አንድ ትሆናለች።  በመካከላችንም የሚለየን ባህር አይኖርም (ራዕይ 21:1) ። ነገሮችም ሁሉ በእርሱ አንድ ይሆናሉ (ኢፌ 1:10) ።

በዚያ ቀን ሁሉ ነገር ይታደሳል፤ ጽድቅ የሚሰፍንበት አዲስ ሰማይ እና ምድርም ይመጣል (2ኛ ጴጥ 3:13)። የሀጥያት ውጤት እና መርገም ይጠፋሉ በዚህ ጊዜ ሰማያዊዋ ገነትም የእኛ ትሆናለች።

በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የገባው ኪዳን ለዘላለም እና በስተመጨረሻ እንረዳዋለን። በክርስቶስ ይህ ይሆናል"የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤"  (ራዕይ 21:3) ። ይህ ፍጻሜ የኪዳን ህይወት ነው።

ክርስቶስም ሲመጣ የአሁኑ ሀዘናችን እና ፈተናችን ሁሉ ይፈጸማል። "እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም" (ራዕ 21፡4) ።

ከዚህ በተጨማሪም ክርስቶስ ሲመጣ ሀጥያት ሁሉ ይቀራል። ሰይጣን እና እርሱን የሚያገለግሉ ሁሉ ስለሚጣሉ የአሁኑ ሀጥያታችንን ሁሉ በዚያ ቀን ይቆማል። እንዴት ታላቅ ቀን ነው!

ደግሞም የሀጥያት ሀሳብ ሆነ እድል እራሱ ከእግዚአብሔር ህዝቦች ላይ ይነሳል። "ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።" (1ኛ ዩሀንስ 3:2) ። የእኛ ሀጥያተኛ ሰውነታችን እንኳን የእርሱን የክብር አካል ወደ መምሰል ይለወጣል (ፊሊ 3:21) ።

በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር በእጆቹ ስራ ሁሉ እራሱን የማክበሩ አላማ ይገለጣል። እግዚአብሔርን የሚወዱ የክርስቶስን መምጣት ሲያስቡ ስለእራሳቸው ክብር ብቻ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔርም መክበር ያስባሉ። ክርስቶስ ሲመጣ እና መንግስቱን ለአባቱ ሲያስረከብ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆናል።

እንዴት ያለ ተስፋ ነው! ይህ ተስፋ ያንተም ነው?

## ክፍል ፫ - ማጣቀሻዎች

1 .Heidelberg Catechism, Lord's Day 12, Q&A 31.

2. Karl Barth (1886–1968) was a modern Swiss theologian who worked in Germany over the period of the two world wars. His theology is known as dialectical or crisis theology and is characterized by paradoxes and reformulation of almost all fundamental Reformed doctrines. Notable among his heretical teachings are the notion that God is unknowable, the idea of "encounter" as the way in which God reveals himself, and a rejection of the historicity of Scripture.

3. Louis Berkhof, Systematic Theology, Part 3, "The Doctrine of the Person and Work of Christ," "New" Edition (Grand Rapids, MI: William B. Eerdmans Publishing Company, 1996), 334.

4. Athanasian Creed, verses 30–31, and 33.

5. Charles Hodge, Systematic Theology, vol. 2 (London: James Clarke, 1960), 380.

6. Athanasian Creed, verse 37.

7. Ibid., verses 31 and 33

8. Heidelberg Catechism, Lord's Day 18, Q&A 49.

9. The Westminster Shorter Catechism, Answer 23

10. The Westminster Larger Catechism, Answer 60.

11. Heidelberg Catechism, Lord's Day 16, Q&A 44.

12. The Westminster Larger Catechism, Answer 50.

13. Westminster Confession of Faith, Chapter 2, Article 1

ክፍል ፭

# ኪዳኑ እና ድህነት

## የኪዳኑ ባህሪ

ኪዳን ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ስለዚህ ጉዳይ ይናገራልና ይህ ጉዳይ ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።

ብዙዎች ኪዳንን በስምምነት ወይም ውል ብለው ይተረጉሙታል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር የገባው ኪዳን በአብርሃም እና በአቤሜለክ መካከል እንደተደረገው እንደ ሰው ኪዳን ብዙ ሃላፊነቶች ፣ ቃል ፣ እና ቅጣትን የሚያካትት አይነት ነው ብለው ያስባሉ (ዘፍ 21:27:32) ።

እንደዚህ አይነት ኪዳን  በሁለት አካላት ወይም ወገኖች መካከል የሚደረግ እና በተወሰነ መልኩ በእነዚያ ሰዎች ላይ የሚደገፍ እና ከሁለቱ በአንዱ መሰበር የሚችል የኪዳን አይነት ነው። እንደ እነርሱ አመለካከት ወይንም እምነት አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን የገባ የመጀመሪያው ሰው ሲሆን አሁን ግን አዳም በመውደቁ ክርስቶስ አዳምን ተክቶታል።

እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ያለው ኪዳን እንደዚህ *አይነት* ኪዳን አይደለም። ሰው ከህያው እግዚአብሔር ጋር እንደዚህ አይነት ኪዳን የሚገባ አካል ለመሆን በፍጹም የበቃ አይደለም። እግዚአብሔር አምላክ ነው፤ ሰው ደግሞ ህይወቱ ወይንም ኑሮው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ያለ ፍጡር ነውና ከእግዚአብሔር ጋር በልዩ መንገድ የሚፈጽመው ስምምነት እንዳለ ሰው ማሰብ የለበትም ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚያዝዘውን ሁሉ የማድረግ ግዴታ አለበትና። ፍጥረትም ከፈጣሪ ጋር ኪዳን ሊፈጽም አይችልም።

ኪዳንን ተመስርቶ እና አንዳንድ ሁኔታዎችን አሟልቶ በእግዚአብሔርም ፊት የይገባኛል ጥያቄ መጠየቅ አይችልም። ማድረግ የሚጠበቅበትን ነገር ሁሉ ካደረገ በኋላ እርሱ አሁንም *የማይጠቅም ባሪያ* ነው (ሉቃስ 17:10)። አንዳንዶች እንደህ አይነት አስተምህሮ ቢያስተምሩም በእርግጥም ሰው በኪዳኑ በኩል የዘላለም

ህይወት ሊገባው አይችልም። የዘላለም ህይወት የሚመጣው ከሰማያት ጌታ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ 15:47-48)።

መጽሐፍ ቅዱስ ኪዳኑ ስምምነት ሳይሆን በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በሉዓላዊነት የተመሰረተ *ትስስር* እንደሆነ ያስተምረናል ። ይህም በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚብሔር ኪዳኑን "ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላችኋለሁ፥ አምላክም እሆናችኋለሁ" በማለት በገለጠበት ክፍሎች ውስጥ ተገልጧል (ዘፍ 17:8, ዘጽ 6:7, 2ኛ ቆሮ 6:16, ራዕይ 21፡3) ።

እነዚህ ቃላቶች በጥቂቱ በተለያየ መንገድ ቢቀርቡም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኪዳንን ቀመርን የያዙ ይመስላሉ። እነዚህ ክፍሎች ስለ ኪዳን እንደሚናገሩ በግልጽ ያሳዩናል።

ሌሎች ክፍሎች ደግሞ በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል ስላለው እንዲህ አይነት ህብረት በደንብ ያስረዱናል ። ዘፍ 5:22-24 ፣ ዘፍ 6:9 ፣ ዘፍ 18:17-19 ፣ መዝ 25:14 ፣ ዩሐ 17:23 ፣ ያዕ 2:23 ፣ 1ኛ ዩሀ 1:3 ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው። ሁሉም ክፍሎች የእግዚአብሔር የተባረከው የወዳጅነት ወይም የህብረት ኪዳን ከህዝቡ ጋር በጸጋው እና በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ስራ ብቻ የሚመጣ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ይህ ግንኙነት በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የተመሰረተ እና እርሱ ብቻውን ለህብረቱ መተማመኛ ነው። በምንም አይነት መልኩ ኪዳኑ በሰው ወይም በሁለተኛ አካል የሚደገፍ አይድለም ሆኖም ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ስራ እና የጸጋው ስራ የሆነ የማይገባን ስጦታ ነው። ኪዳኑ ሁል ጊዜም የ*ጸጋ* ኪዳን ነውና።

## ከአዳም ጋር የነበረው ኪዳን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአዳም ጋር ስለነበረው ኪዳን በግልጽ የሚያወራው አንድ ክፍል ብቻ ነው እርሱም ሆሴዕ 6:7 "እነርሱ ግን እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላልፈዋል፤ በዚያም ላይ ወንጅለውኛል" ። ቁጥር 7 ላይ እነርሱ የሚለው "ሰው" ወይንም "አዳም" ማለት ነው (በዕብራይስጥ አንዳይነት ቃላቶች ናቸው)። ክፍሉን ስንተረጉመው የሚያወራው አዳም በግሉ የተላለፈውን ኪዳን ወይም የሰው ልጅ በእርሱ በኩል የተላለፈውን ኪዳን ያመላክታል።

ይህ ከአዳም ጋር የነበረው ኪዳን የተለየ ኪዳን ሳይሆን የአንዱ ዘላለማዊ የጸጋ ኪዳን የመጀመርያ መገለጥ እንደሆነ እናምናለን። በእርግጥም ኪዳኑ ዘላለማዊ ከሆነ ሊኖር የሚችለው አዳምንም የሚያጠቃልል አንድ ኪዳን ብቻ ነው።

የመጀመሪያው የኪዳን መገለጥ አጠቃላይ ኪዳኑ ስለምን እንደሆነ ያስረዳናል። በዚህ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር የሕዝቡ መለኮታዊ ወዳጅ እንደሆነ እና ከእነርሱ ጋር በተባረከ ጓደኝነት እንደሚኖር ተገልጧል። በመጅመሪያው የኪዳን መገለጥ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ጥሪ በኪዳኑ ገለጠ። ይህም ጥሪ ይገባኛል በሚል ህይወት ሳይሆን፣ በአመስጋኝነት እና በመታዘዝ ሰው እንዲኖር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው ከአዳም ውድቀት በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር *በመታረቃችን* ይህ ኪዳን የአንዱ ኪዳን መገለጥ እንደሆነ ያመለክታል (2ኛ ቆሮ 5:18-21)። *መታረቅ* የሚለው ቃል ኪዳናዊ ቃል ሲሆን የመጀመሪያው ግንኙነት እንደተበላሸ ሆኖም ግን ግንኙነቱ *ሙሉ በሙሉ እንዳልፈረሰም* የሚያመላክት ቃል ነው። ስለ እርቅ ማውራት የምንችለው የመጀመሪያ ግንኙነት ፈጽሞ ያልጠፋ እና በድጋሜ መመለስ *ወይም መታደስ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው።*

ይህ ያልሆነ እንደሆነ እግዚአብሔር ተቆጥቷል *ወይንም ተለውጧል ብለን እንናገር ነበር።* የመጀመሪያው ኪዳኑ እና አላማው ሙሉ በሙሉ ይበላሽ ነበር ፣ በዚህም እጅግ በመቆጣቱ አላማውን በመቀየር እንደገና በአዲስ ኪዳን ለመጀመር ግድ ብሎታል ማለት ነው።

አዳም በሀጥያት ከመውደቁ በፊት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የነበረው ኪዳን እንዴት የ*ጸጋ* ኪዳን ሊሆን ይችላል? *ጸጋ* ያልተገባን ስጦታ እንደሆነ ልናስታውስ ያስፈልጋል። የአዳም ማንነት እና የነበረው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር የማይገባ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ኪዳን እንዲያደርግ አዳምም እንዲገባው ምን የሰራው ስራ አለ? መኖሩ ሁሉ በእግዚአብሄር ሆኖ ሳለ ከእግዚአብሄር ምንም ነገር የተገባው እንዲሆን ያደረገ *አንዳች ነገር* ምንድነው?

ኪዳኑ በአዳም ውድቀት እንዳይበላሽ እና ኪዳኑ እንዲጠበቅ የሚያደርገው ጸጋው ነው። አዳም በሀጥያት ከወደቀ በኋላ ወደርሱ መጥቶ በሰይጣን እና በሴቲቷ መካከል ጠላትነትን በመፍጠር በአዳም እና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ጓደኝነት ማደስ ጀመረ (ዘፍ 3:15)። የእኛ “የመጀመሪያዎቹ መገኛዎቻችን” ከሰይጣን ጋር ህብረትን ማድረግ ቢመርጡም ፤ እግዚአብሔር የእራሱ በወዳጅነት እንዲሆኑ ስለመረጣቸው ከሰይጣን ጋር በወዳጅነት እንዲቀጥሉ አልፈቀደም። እርሱ ከእነርሱ ጋር ያለው ኪዳን ይቀጥል ዘንድ ሊመጣ

ላለው ክርስቶስ ምሳሌ የሆነውን የመጀመሪያውን መስዋዕት እራሱ በማቅረብ በእንስሳት ቆዳ ሸፈናቸው (ቁጥ 21)።

እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት ሁል ጊዜም የጸጋ ነው። ከዚህ ውጪ ዘላለማዊ አምላክ ከእኛ ጋር ግንኙነት ሊፈጥርበት የሚችልበት ሌላ መንገድ የለም።

## ከኖህ ጋር የነበረው ኪዳን

በብሉይ ኪዳን የነበሩት የተለያዩ ኪዳኖች በሙሉ የአንዱ ታላቅ የጸጋ ኪዳን የተለያዩ መገለጦች ናቸው ብለን እናምናለን። ኪዳኑ ዘላለማዊ ከሆነ ሊኖር የሚችለው አንድ ኪዳን ብቻ ነው (ዘፍ 17:7) ።

በእነዚህ የኪዳን መገለጦች እግዚአብሔር ስለ ጸጋውን ኪዳን አዳዲስ እና አስገራሚ የሆኑ ነገሮችን አሳይቶናል ። ለአዳም የመጀመሪያው የኪዳን መግለጥ እግዚአብሔር ኪዳኑ *የወዳጅነት* ኪዳን መሆኑን አሳይቷል።

ከአዳም በኃላ ታላቁ የኪዳኑ መገለጥ የሆነው ለኖህ ነው። በዚህ የኪዳኑ መገለጥ ኪዳኑ የፈጠረውን አለም ሁሉ እንደሚያካትት በማሳየት እግዚአብሔር የኪዳኑን አለም አቀፋዊነት አሳይቷል። አሁን የምታዩት ኪዳን ከሰው ጋር ብቻ የተገባ ኪዳን ሳይሆን "ሕያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን" ሁሉ ጋር ነው (ዘፍ 9:15) ። ኪዳኑ ከቀን እና ከማታም ጋር ያለ ታላቅ ኪዳን ነው (ኤር 33፡25)። ስለዚህም የእግዚአብሔር ኪዳን አለም አቀፋዊነት ሁሉንም ነገር ወይም ሁሉንም ሰው ያለ ምርጫ ያደርጋል(with out election) ማለት ሳይሆን የኪዳኑ አለማአቀፋዊነት በነገሮች መካከል ያለ ልዩነት (without distinction) ኪዳንን አድርጓል ለማለት ነው። ስለዚህም በመጨረሻው ጊዜ ፍጥረት ሁሉ በአዲሱ ሰማይ እና ምድር ይታደሳል ደግሞም ይወከላል።

ይህ ኪዳን በእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ላይ በቀሰተ ዳመና ተወክሏል። ይህ በአዲስ ምድር እና ሰማይ ፍጻሜውን የሚያገኝ ኪዳን ነው። ይህ ኪዳን ፍጥረት እንኳን "ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው" የሚያርፍበት ኪዳን ነው (ሮሜ 8:21)።

ኪዳኑ በኖህ ዘመን የተገለጠበት ምክንያት እግዚአብሔር ምድርን በዚያን ጊዜ ሊያጠፋ በመወሰኑ ነው። ነገር ግን በፍርዱ እና ከኖህ ጋር ባደረገው ኪዳን በእርሱ ጊዜ የነበረው የአለም መጥፋት የአለምመጨረሻ ሳይሆን

ምድርን የማደስ እና መጽዳት ሂደት መሆኑን ነግሮታል። እግዚአብሔርም ይህቺን ምድር በመጨረሻው ጊዜ በእሳት ሲያጠፋት እንዲሁ ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በአለማት ላይ ስላለው *የእግዚአብሔር አላማ አንስቶ የሚናገረው* በዚህ ምክንያት ነው ብለን እናምናለን (ዩሐ 1:29 ፣ ዩሐ 3:16-17) ። እያንዳንዱን ፍጥረት እና ሰው ባያጠቃልልም መላው የእግዚአብሔር አለም በስተመጨረሻ ቤዛነትን እና ድነትን ያገኛል።

ይህም ደግሞ መሆን አለበት ምክኒያቱም እግዚአብሔር አላማው ከንቱ እንዲሆን አይፈቅድም ። እግዚአብሔር ለራሱ ክብር የፈጠረውን የራሱን አለም ሰው በሀጥያቱ ምክኒያት ከእርሱ እንዲሰርቀው አይፈቅድም። የገዛ አለሙን ያድናል።

ይህ ሁሉ ኢሳይያስ 11 ላይ ያለውን ክፍል ለመረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው። ብዙዎች እንደዚህ አይነት ክፍለ ንባቦችን ሲያነቡ ከክርስቶስ *መመለስ በፊት የወደፊት ምድራዊ መንግስታት እንደሚኖሩ እና የሀጥያት ተጽዕኖ በተወሰነ መልኩም ቢሆን እንደሚቆም ይደመድማሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ረገድ ምንም ተስፋን አይሰጠንም።* ይልቅ በአዲስ ሰማይ እና ምድር ተኩላ እና በግ አንድላይ በሰላም አብረው በመሆን ጽድቅ ስለሚሰፍንበት መንግስት ይናገራል። “ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው” (ኢሳ 11:6, ሮሜ 8:21)። እንዴት ክብር ያለበት ቀን ነው!

## ከአብርሃም *ጋ*ር የነበረው ኪዳን

ከአብርሃም *ጋ*ር የነበረው ኪዳን ከእስራኤል *ጋ*ር ከነበረው ኪዳን *ጋ*ር ተመሳሳይ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳየናል። እግዚአብሔር ከአብርሃም *ጋ*ር ኪዳንን ሲገባ ኪዳኑ ከዘሩም *ጋ*ር በመሆኑ እግዚአብሔር ከእስራኤል *ጋ*ር ኪዳን ሲገባ ለአብርሃም፣ ለይሳሓቅ እና ለያዕቆብ የገባውን ኪዳን እየጠበቀ እንደሆነ ግልጽ አድርጓል (ዘፍ 17:7 ፣ ዘጽ 3:15-16)።

ይህም ደግሞ እጅግ አስፈላጊ እውነት ነው ምክኒያቱም በኪዳኑ ለአብርሃም እውነት የሆነው ሁሉ ለእስራኤልም ኪዳን እውነት ነው። *የሚያምኑ ሁሉ* የአብርሃም እውነተኛ ዘር እና ልጆች በመሆናቸውም ለአብርሃም እውነት የነበረው ሁሉ ለእኛም እውነት ነው።

ለአብርሀም ስለተገባለት ኪዳን ሊጠቀሱ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች አሉ። የመጀርመሪያው እና ዋናው ነገር ከአብርሃም ጋር ብሎም ከእስራኤል ጋር የተገባው ኪዳን የጸጋ ኪዳን መሆኑ ነው። በዘፍጥረት 15 ላይ የዚህ ታላቅ ኪዳን መገለጥ ይህንን ያመላክተናል።

ዘፍጥረት 15ን ለመረዳት በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ኪዳንን የሚገቡት ውል በመዋዋል እና በህጋዊ መንገድ አስመስክረው ሳይሆን ሰዎች በተከፈለ እንስሳት ወይም እንስሳቶች መካከል አንድላይ በመሄድ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። በኤርሚያስ 34:18 ይህ ከልብ የሆነ ስነ ስርዓት የሚከወነው እጅግ አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ብቻ እና ማንም ህጉን የተላለፈ ሰው እንደዚህ ሊከፋፈል እና አካላቱ ለአውሬ እና ለወፎች ሊሰጥ እንደሚገባ ለማስጠንቀቅ መሆኑን ይገልጻል። እስራኤላዊያን እርስ በእርስ ለገቡት ኪዳን ሳይታመኑ ሲቀሩ እግዚአብሔር በዚህ ያስጠነቅቃቸው ነበር (ኤር 34:19-10)።

የሰው ኪዳን በሁለት እኩያማቾች መካከል በመሆኑ ስምምነት ወይም በሁለት ወገን ያለ ኪዳን በመሆኑ ኪዳኑን የሚገቡ አንድ ላይ አብረው በእነዚያ የእንስሳት ቁርጥራጮች መካከል ያልፋሉ። በኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር እና ሰው  በፍጹም እንደ እኩያማቾች መቆም ስለማይችሉ የእግዚአብሔር ኪዳን ልዩ ነው። ዘፍጥረት 15 እንደሚለው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ኪዳን እግዚአብሔር ብቻ የመሰረተው በመሆኑ በአንድ ወገን ወይም በአንድ አካል ብቻ የተፈጸመ ኪዳን መሆኑን እንመለከታለን። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ኪዳኑን ሲፈጽም እና በእንስሳት ክፋዩ መካከል ሲያልፍ አብርሀም ተኝቶ ነበር። አብርሃም ይህንን ኪዳን ለመግባት ያደረገው ምንም ነገር አልነበረም። በየትኛውም ምልከታ ደግሞ አብርሃም ላይ የተደገፈ ኪዳን አይደለም። በእውነትም *የጸጋ* ኪዳን ብቻ ነው።

በእንስሳቶቹ ክፋይ መካከል እግዚአብሔር ብቻውን በማለፉ በልጁ ሞት በኩል እንዳደረገው ሁሉ ኪዳኑ ባይጠበቅ ሀላፊነቱን እርሱ እንደሚወስድ በምሳሌ እያሳየ ነበር (ኢሳ 53:8 ፣ ገላ 3:13) ። ከኪዳኑ አንጻር ላለብን ሀጥያት እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ቅጥታችንን በመቁረጥ እና በመጣል ተቀጣልን። ክርስቶስም እንዲህ ብሎ ሲጮህ "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ? " ይህንን መረዳት ችለናል። ስለዚህም ለአብርሃም የተገለጠው የጸጋ ኪዳን በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጽሟል።

## ኪዳኑ እና የርስት ተስፋው

ዘፍጥረት 15 እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ብሎም በአብርሃም በኩል ከእስራኤል ደግሞም ከእኛ ጋር አሁን ያለው ኪዳን የጸጋ ኪዳን መሆኑን ያሳያል። በዚሁ ክፍል ለአብርሃም በተገባለት ኪዳን ውስጥ ሊጠቀስ የሚችል ሌላም ገጽታ ወይንም ጉዳይ መኖሩን ያስታውሰናል። እርሱም ደግሞ የርስት ተስፋ ነው።

*ነገር ግን ይህ የርስቱ ተስፋ ብዙ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ በመረዳት አብዛኞችን ወደፊት ለእስራኤል ህዝብ በከነዓን ምድር የሚሆን ዳግም መሰባሰብ ወይንም መመለስ እንዳለ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ይህ ከንቱ ተስፋ እንደሆነ እናምናለን።*

ከአብርሃም ጋር የነበረው ኪዳን ከላይ የተጠቀሰው ተስፋ እንዴት ባዶ እንደሆነ ያሳየናል። ለአብርሃም የተገባለት ኪዳን ምድራዊ ተስፋ ያለው ከሆነ ይህ ተስፋ ለአብርሃም ለራሱ በጭራሽ አልተፈጸመለትም ማለት ነው።

በሐዋሪያት ሥራ 7:5 ቃሉ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ለአብርሃም እግሩን እንኳን የሚያሳርፍበትን የምድር በረከት እንዳልሰጠው ይናገራል። ነገር ግን ቁጥር 5 እግዚአብሔር ለዘሩም ብቻ ሳይሆን ለእራሱ አብርሃም ይህንን ኪዳን እንደገባለት ይናገራል። በእኛ ግምት በብሉይ ኪዳን የምናገኘው የርስት የተስፋ ቃል ወይም አጠቃላይ ተመሳሳይ ተስፋዎች መንፈሳዊ ፍጻሜ ያላቸው ስለመሆናቸው ከዚህ የበለጠ ግልጽ ማስረጃ ሊኖረን አይችልም ብለን እናምናለን ።ይህ የርስት ተስፋ ሁልጊዜም ሰማያዊ ርስት እንጂ ምድራዊ መሬት ወይንም ርስት አይደለም።

ዕብራዊያን 11:8-16 ይህንን ያረጋግጥልናል። አብርሃም በእምነት ኡር ከሚባል ምድር እግዚአብሔር ተስፋን ወደሰጠው ምድር ሲሄድ እርሱ "መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና" (ቁጥ 10)። ይሳሐቅ እና ያቆብም ሁሌም "በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ" (ቁጥ 13) ደግሞ "አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ"(ቁጥ 16)። በእርግጥም እነርሱ አለማዊ እርስትን ፈልገው ቢሆን ኖሮ ወደ ወጡበት ምድር የመመለስ እድል ነበራቸው (ቁጥ 15)፣ ነገር ግን የእነርሱ ተስፋ ይህ አልነበርም። ለእኛም ደግሞ ይህ ተስፋችን አይደለም።

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት የርስት መንፈሳዊ እና ሰማያዊ በመሆኑ በአብርሃም አምላክ የሚያምኑ አይሁዳዊያንም ሆኑ አህዛብ እውነተኛ የአብርሃም ልጆች የዚህን ኪዳን መፈጸም ሊደሰቱበት እና ሌሎቹንም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር በገባው ኪዳን የሰጥውን የተስፋዎች ፍጻሜ ይቀበላሉ (ሮሜ 3:28-29, ሮሜ 4:16-17, ገላ 3:29) ። ከዚህ ተስፋ ማንም አይጎድልም ፣ አብርሃምም ቢሆን ፣ አምነው በምርኮ የተበተኑት

እና ወደ ከነዓን ድጋሚ ያልተመለሱቱ አይሁዳዊያን ቢሆኑ ፣ በእምነት የአብርሃም ልጆች የሆኑ አህዛቦችም ቢሆኑ ከዚህ የተስፋ ቃል አይጎድሉም።

ስለዚህ ሁሉም የአብርሃም ልጆች ከአብርሃም ጋር ከተራራ፣ ከወንዞች እና ከምድራዊ ከተማዎች ሁሉ የሚበልጥን ነገር ይወርሳሉ። በዕብ 12:22-24 ወደሚናገረው ወደ ተባረከው ውርስ ይገባሉ። ከዚህም የሚበልጥ ምንም የለም።

## ከእስራኤል ጋር የነበርው ኪዳን

እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ኪዳን እንደነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎ ይናገራል። ሆኖም ግን ይህንን ኪዳን የምንረዳበት መንገድ ብዙ ክርክርን የሚያነሳ ነው።

ትልቁ ጥያቄ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረው ኪዳን በአዲስ ኪዳን ከነበረው ኪዳን የተለየ ነው ወይ እና አዲስ ኪዳን እና ብሉይ ኪዳን እንዴት እርስ በእርስ ይዛመዳሉ የሚለው ነው ። አዲስ እና አሮጌ *ኪዳንነታቸውስ ለተለያዩ ሰዎች የተሰጡ የተለያዩ ኪዳኖች* ከመሆናቸው አጻር ነው ወይስ ከአንዱ ኪዳን መገለጥ አንጻር ነው?

ዲስፐንሴሽናሊዝም የቀድሞውን እና የአዲሱ ኪዳን ፍጹም የተለያየ በማድረግ እና የሚመለከታቸውም የተለያየ ህዝቦችን ነው ደግሞም የተለያየ ተስፋ እና የተለያየ ፍጻሜን የያዙ ናቸው ብሎ ያስተምራል ። አስተምህሮቱ ዋልታ በረገጠው ጽንፉ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለነበሩ እስራኤላዊያን እና በአዲስ ኪዳን ለምትገኘው ቤተክርስቲያን የተለያየ የድነት መንገድ እንዳለ ጭምር ያስተምራል። የስኮፊልድ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ[1] ይህንን አስተምህሮ እንደ ምሳሌ አድርጎ ያቀርባል።

ደግሞ ዲስፐንሴሽናሊዝምን የሚቃወሙ ሆኖም ግን ሁለቱን ኪዳኖች ደግሞ ለመረዳት የሚያመነቱም አሉ። አንዳንዶች በአዲስ እና በብሉይ ኪዳን ያሉት ተስፋዎች እና አፈጻጸማቸው ላይ ልዩነትን

እንዳለ ይናገራሉ (ቅድመ ሚሊኒየሞች እና ድህረ ሚሊኒየሞች) ። ቢያንስ የተወሰኑት የብሉይ የኪዳን ተስፋዎች በአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ እና ሰማያዊ ከሆኑት ተስፋዎች በተለየ መልኩ ምድራዊ ፍጻሜ እንዳላቸው ያስተምራሉ።

ባፕቲስቶች ደግሞ በእስራኤል እና በቤተክርስቲያን መካከል በተለይም በኪዳኑ እና በምልክቶቹ ላይ ልዩነት አለ ብለው ያምናሉ። ለአብነትም ያህል እስራኤል እንደ ቤተክርስቲያን ናት እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም ብለው ሲያምኑ ግርዘት እና ጥምቀት የአዲስ እና የብሉይ ኪዳን ምልክት መሆናቸውን ይክዳሉ ። ሌሎች ደግሞ በጸጋ እና በህግ መካከል ልዩነት አለ ይላሉ። በአንድም ሆነ በሌላም ህግ በአዲስ ኪዳን አማኞች ህይወት ውስጥ ምንም ቦታ የለውም ብለው ያስተምራሉ። ይህም ስህተት አንቲኖሚናሊዝም (antinomianism) ይባላል።

ከዚህ ሁሉ በመቃረን የተሓድሶ እምነት አንድ ኪዳን ብቻ እና አንድ የኪዳኑ ህዝብ ብቻ እንዳለ ፣ እስራኤል የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን መሆኗን (ሐዋ 7:38) ፣ መገረዝ እና ጥምቀት በአላማቸው አንድ የሆኑ እና የሚምሳስሉ የኪዳኑ አንድ ምልክት መሆናቸውን (ቆላ 2:11-12) ፣ አንድ አዳኝ እና አንድ የድነት መንገድ እንዳለ (ሐዋ 4:12) ፣ በክርስቶስ የተሰጠ አንድ የዘላለማዊ ህይወት ተስፋ እንዳለ (ሐዋ 2:38-29) ፣ ለተስፋው ሁሉ አንድ መንፈሳዊ ፍጻሜ እንዳለው ያምናሉ (ዕብ 11:9-10, 13-16)። በሁለቱም ኪዳን ውስጥ በህግ እና በጸጋ ኪዳን መካከል አንድነት እንዳለም ጭምር ያምናሉ (ሮሜ 7:12)።

የተሓድሶ እምነት በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ሙሉ በሙሉ አንድነት እንዳለ እና ይህም አንድነት የእግዚአብሔርን አንድነት እንደሚያንጸባርቅ ያምናል። በእግዚአብሔር መካከል ልዩነት እንደሌለ እንዲሁ በአዲስ እና በብሉይ ኪዳንም ምንም አይነት መሰረታዊ ልዩነት የለም።

## አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ

ብዙዎች እስራኤል በብሉይ ኪዳን የነበረችው ቤተክርስቲያን ነች ስለዚህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከእስራኤላዊያን ጋር የነበረው ኪዳን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ላለችውም ቤተክርስቲያን ተመሳሳይ ነው የሚለውን አስተምህሮ በጽናት ይቃወሙታል። በዚህም ምክኒያት አስተምህሮዎቻችንን በጥንቃቄ በመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጥ አለብን።

እስራኤል እና ቤተክርስቲያን አንድ መሆናቸው ግልጽ ነው። በእርግጥም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኛዋ እስራኤል ምድራዊ ፣ምውት እና ስጋዊ ህዝብ ሳይሆን እንደ ቤተክርስቲያን *የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ህዝብ* ነበር።

በሮሜ 9:6-8 የእግዚአብሔር ቃል "እነዚህ ከእስራኤል የሚወለዱ ሁሉ እስራኤል አይደሉምና" በማለት ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤላዊያን እና እውነተኛ እስራኤላዊያን በሆኑት መካከል ግልጽ ልዩነት እንዳለ ያሳያል። በዘሩ ውስጥ የአብርሃም ልጆች እና የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የሚቆጠሩት ከእስራኤላዊ ወገን የሚወለዱ ሳይሆን በተስፋው ቃል ሀይል የሚወለዱ (በህያው የእግዚአብሔር ቃል ዳግም የተወለዱ) ናቸው። እነዚህ መንፈሳዊ ህዝቦች ናቸው።

ሮሜ 2:28-29 ይህንን በሚደንቅ መልኩ ያረጋግጥልናል። በግልጽ በውጫዊ ማንነታቸው አይሁዳዊ የሆኑት ሁሉ አይሁዳዊያን አይደሉም በማለት ይናገራል። አይሁዳዊ ማለት በውስጡ ማለትም ልቡ እና መንፈሱ የተገረዘለት ሰው ነው (ከቆላ 2:11 ጋር አነጻጽር) ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የአይሁዳዊ ትርጓሜ አንጻር ይህ ማለት የሚያምን አህዛብም እንደ አብርሃም ልጅ እና እንደ እስራኤላዊ ይቆጠራል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህንንም ነው። ሮሜ 4:11-16 አብርሃም ለሚያምኑ አይሁዳዊያን አባት ብቻ ሳይሆን የሚያምኑ አህዛቦችም አባት እንደሆነ ግልጽ አድርጎ አስቀምጧል። እርሱ የመንፈሳዊ ሰዎች "የሁላችንም" አባት ነው። ገላቲያ 3:7 በግልጽ እንዲህ ይላል "እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ።"

በእርግጥም አዲስ ኪዳን የሚያምኑ አህዛቦች ከማያምኑ የአብርሃም ዘሮች በላይ የተገረዙ እና እውነተኛ አይሁዳዊ እንደሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል። በስጋ አይሁዳዊ የሆኑት በፊሊጵስዮስ 3:2 ላይ "ክፉዎችም" እና ተራ "ሐሰተኛም" ተብለዋል። ምክንያቱም እነርሱ በውጪያዊ የተገረዙ እንጂ መንፈሳዊያን አይደሉምና። ኢየሱስም አንዳንድ አይሁዳዊያኖች የእውነተኛ የአብርሃም ልጆች አልያም የእግዚአብሔር ልጆች እንዳልነበሩ በግልጽ ተናግሯል (ዩሀ 8:33-41)። በተቃራኒው ደግሞ ፊሊጲስዮስ ውስጥ አህዛቦች "የተገረዙ" ተብለዋል። ምክንያቱም "በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና" (ቁጥ 3)።

ይህንን የሚያስተምሩ ተጨማሪ ክፍሎች አሉ። ገላቲያ 4:1-7 የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን እና የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን *ከአንድ ሰው ጋር* በማነጻጸር ከህጻንነት ወደ እድገት እንደሚሄድ ያሳይ።።

ገላቲያ 3:16 ፣ 29 አንድ ዘር ብቻ እንዳለ እርሱም ክርስቶስ እና በእርሱ ያሉቱ ብቻ እንደሆኑ ያሳየናል። ዕብ 12:22-23 ኢየሩሳሌምን፣ የጺሆን ተራራ እና የበኩር ልጁን ቤተክርስቲያን ይጠቅሳል። ወደ አንድ መምጣት ወደ ሁሉም መምጣት ነውና።

እስራኤልን የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሰዎች አድርጎ መለየት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። በኪዳኑ በረከት እና ቃል ኪዳን መሳተፋችን በዚህ መረዳት ላይ የተደገደ ነው። የተስፋው ምክኒያት እና ለተስፋው መብት ያላቸው እውነተኛ አይሁዶች ብቻ ናቸው። ማለትም ተስፋዎቹ አይሁድዊ ወይም ክርስቲያን የሚል ስም ላላቸው አይደለም። እውነተኛ አይሁዳዊ የሚያምን ሁሉ ነው። አንተስ ታምናለህ?

## ህጉ እና ኪዳኑ

ከእስራኤል ጋር የነበረው ኪዳን ልዩ ባህሪ በሲና ተራራ ህግ መሰጠቱ ነው። በህጉ እና በኪዳኑ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?

ይህንን ግንኙነት ለመረዳት ገላቲያ 3:17-21 ወሳኝ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በመጀመሪያ ህጉ ከመሰጠቱ ከአራት መቶ አመታት በፊት ለአብርሃም የተገባለት ኪዳን አንዱ እና ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ኪዳን መሆኑን እና ይህ ኪዳንም "በክርስቶስ መረጋገጡን" ይናገራል። ሁለተኛ ህጉ በመሰጠቱ ኪዳኑ እንደማይሰረዝ ይናገራል (ቁጥ 17)። ይህ ብቻ ሳይሆን ህጉም ከኪዳኑ ጋር አይቃረንም (ቁጥ 21)።

ዘጸ 24:7 ህጉን እግዚአብሔር ለህዝቡ ኪዳኑን ያሳወቀበት 'የኪዳን መጽሐፍ" ብሎ ይጠራዋል። ይህ ህግ በክርስቶስ በተረጋገጠው ኪዳን ውስጥ ያለ ከሆነ በዚህ ህግ ውስጥ ሌሎች ህጎች መጨመራቸው እንዳለ ሆኖ ህጉ አሁንም የኪዳን መጽሐፍነቱ ይቀጥላል።

በገላቲያ 3:19 መሰረት ህጉ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ በመተላለፋችን ምክኒያት ወደ ኪዳኑ የተጨመረ ነው። ህጉም ሀጥያተኝነታችንን በመግለጥ ክርስቶስ እንደሚያስፈልገን ያሳየናል ማለት ነው። ህጉ " ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል" (ቁጥ 24)።

ሮሜ 10:24 ተመሳሳይ ነገርን ይናገራል። ክርስቶስ የህግ መጨረሻ የሆነው ህጉን ስለሚያቆመው ሳይሆን እርሱ የህግ አላማ እና መዝጊያ እራሱ ስለነበር ነው። ህግ ክርስቶስን እንደ ዋና ግቡ በማድረግ አላማውም

ሀጥያትን በመግለጥ እና እውነተኛዋ እስራኤል በእምነት በክርስቶስ በኩል ትጸድቅ ዘንድ እንደሚያስፈልጋት ማሳየት ነው።

ጳውሎስ በሮሜ 7:7 “ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር” በማለት ይህ ህግ አሁንም እንደሚሰራ በግልጽ ይናገራል። ገላቲያ 3 ህግ የአይሁዳውያን ሞግዚት ብቻ ሳይሆን “የእኛም” ሞግዚት እንደሆነ በመናገር ይህንን ያረጋግጥልናል (ቁጥ 23-24)።

ስለዚህም ህግ የኪዳኑ አካል ነበር ለማለት አንቸገርም ። ገላቲያ 3:19 እንደሚያስታውሰን ይህ ህግ በእርግጥም የብሉይ ኪዳን አካል ነበረ። ህጉም አሁንም የኪዳኑ አካል መሆኑን የምናረጋግጠው አሁንም የእኛ ሞግዚት ሆኖ ወደ ክርስቶስ ስለሚመራን ነው የተቀየረው ግን እንደ ኪዳን ህዝቦች ከህግ ጋር ያለን ህብረት ነው ፤ ነገር ግን ይህ ሀሳብ በገላ 4፡1-7 ካለው ሃሳብ ጋር ፍጹም የተለያየ ነው።

ከህጉ ጋር የተጣበቁ “የዓለም መሰረታዊ ስርዓቶች” እና እንዲሁ የሚተገበሩ ተገባሮች እንደነበሩ አንክድም (ቆላ 2:20-23)። ሆኖም ግን ይህ ሁሉ አሁን ቆመዋል፤ በብሉይ ኪዳንም የእግዚአብሔር ኪዳን አካል የሆኑት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠቁሙ ሞግዚቶች በመሆናቸው ነው።

ዋናው ሀሳብ በክርስቶስ የእውነተኛ እስራኤላዊያን ሁሉ የሆነ የጸጋ ኪዳን፤ ይህም ደግሞ ከህጉ ጋር ፍጹም የማይቃረን አንድ ኪዳን ነው። የእግዚአብሔር ሕግ ከእግዚአብሔር ኪዳን ጋር የተጣረሰ ፣ አሁን ወይም ወደፊት የሚጣረስ በፍጹም አይደለም።

## በኪዳኑ ውስጥ የህጉ አገልግሎት

በገላቲያ 3:17-21 መሰረት ህግ የተሰጠው የእግዚአብሔር ኪዳን አካል ሆኖ እና አሁንም የኪዳኑ አካል እንደሆነ ተመልክተናል። በዚህም በእርግጥ ህግ እና ጸጋ  እርስ በእርስ አይቃረኑም ለማለት ነው። ህጉም ከኪዳኑ እና ከተስፋው የሚቃረን አይደለም (ቁጥ 21)። ጥቂቶች ባይስማሙበትም ህጉ በኪዳኑ ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ  ሀጥያትን የመግለጥ ስራ እንዳለው ተመልክተናል (ቁጥ 19:24)።

ነገር ግን ህጉ “የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ” እንደመሆኑ ስራው ይህ ብቻ አይደለም (ዘጽ 24:7) ። ህጉ በኪዳኑ ውስጥ ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር የኪዳን ሰዎች በምስጋና የሆነን የመታዘዝን ህይወት እንዲኖሩ በመመሪያነት ያገለግላል።

በዚህ የህጉ ስራ ምክንያት አማኞች ህጉን “ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሀን” (መዝ 119:105, ምሳሌ 6:23) ብለው ይጠሩታል። በህይወት መንገድ ላይ እርግጥ እና የሰላም መመሪያ ነው።

በዚህም ምክንያት ህጉ “ነጻ የሚያወጣው ፍጹሙ ህግ” እና “የንጉስ ህግ” ተብሎ ተጠቅሷል (ያዕ 1:25 ያዕ 2:8 ፣ 12) ። በያዕቆብ 2:8,11 ላይ እንደምንመለከተው ይህ ንጉሳዊ ህግ አዲስ ህግ ሳይሆን አስርቱ ትዕዛዛት ናቸው። ነጻ የሚያወጣ የንጉስ ህግ እና በነገስታት ንጉስ የተሰጠ እንደመሆኑ ይህ ህግ ለነጻነታችን ገደብ እና ብርሃን ያበራልናል በዚህም በክርስቶስ በኩል የተሰጠን ነጻነት ልቅ እንዳይሆነብን ይጠብቀዋል (ገላ 5:13-14)።

በብሉይ ኪዳን እንኳን እግዚአብሔር ህግን በመጀመሪያ የሰጠው አስቀድሞ ላዳናቸው እና ከግብጽ ባርነት ላወጣቸው ሰዎች ነው (ዘጽ 20:1-2) ። ይህንን ያደረገው ወደ ባርነት እንዲመለሱ ሳይሆን የእራሱ የኪዳን ህዝብ በመሆናቸው በህይወታቸው ገድብን ሊያበጅ እና ስለታላቅ ትድግናው ህይወታቸው እርሱን በይበልጥ እንዲያገለግል ለማስተካከል ነው።

ይህ ሁሌም እውነት ነው። በአንድ ነጻ ሀገር ነጻነት በህጉ የተገደበ ነው። ሁሉም ሰው እንደ እራሱ እይታ ትክክል የሆነውን በማድረግ ነጻነትን እንዳያጠፋ ህጉ ገደብን ያስቀምጣል። በዚህ ጊዜ እየተከሰተ እንዳለው ህጉ ሲተው እና ሁሉም ሰው ያስደሰተውን ነገር ሲያደርግ በመጨረሻም ሰዎች ከቤት ወጥተው በጎዳናዎች ላይ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ነጻነት አይኖራቸውም።

ለእግዚአብሔር የኪዳን ህዝቦች ህግ ትክክለኛ የህይወት መርህን እና ቅርጽ የሚሰጠው ለዚህ ነው።በእነርሱ ህይወት እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ ህጉ ከእርሱ ጋር ያላቸውን ህብረት ይወስናል። ህጉ ይህንን የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ባህሪ እና ማንነት ስለሚገልጥ እና ለእኛ እግዚአብሔርን የሚያስከብር የህይወት ባህሪ ስለሚያሳይ ነው።

ህጉ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳናዊ ህብረት እንዲገቡ አያደርጋቸውም ፤ እግዚአብሔርን የሚያከብር ህይወት ለመኖር የሚያስፈልገውን በቂ ጸጋም አይሰጥም። ይህንን ሰው የሚያገኘው ከክርስቶስ ነው (ገላ 3:24)። ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን የእግዚአብሄር የኪዳን ህዝቦች እንዴት መኖር እንዳለባቸው እና በቃልም ሆነ በድርጊት እንደት አመስጋኝ መሆን እንዳለባቸው የሚያመላክት የኪዳን መጽሐፍ ነው።

ይህ ማለት አማኝ ከህግ ጋር ያለው ግንኙነት ክርስቶስ ከመጣ ወዲህ መቀየሩ በፍጹም የሚካድ አይደለም። አሁን አማኝ *በህግ ስር* ሳይሆን *በጸጋ ስር* ነው።

## ከዳዊት ጋር የነበረው ኪዳን

የመጨረሻው በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው ታላቁ የእግዚአብሔር ኪዳን መገለጥ ለዳዊት የተሰጠው ኪነው (2ኛ ሳሙ 7)። የኪዳኑ መገለጥ እንደመሆኑ አንዳንድ ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህሪያት አሉት።

እንደገና ከዳዊት ጋር የነበረው ኪዳን አንዱ እና ዘላለማዊው ኪዳን በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ተገልጦ መሆኑን የሚያሳየውን የኪዳን ቀመር እንመለከታለን። በዚህ ኪዳን እግዚአብሔር የህዝቡ አምላክ እንደሚሆን እና የእንደራሱ ህዝብ እንደሚወስዳቸው ተስፋ (ቃል) ሰጣቸው (ቁጥ 24)። ይህ ሁልጊዜም የኪዳኑ አላማ ነው።

ሆኖም ግን ከዳዊት ጋር የተደረገው የኪዳኑ መገለጥ ከተለያዩ ነገሮች አንጻር ልዩ ነው። ልዩ የሚያደርገውም ኪዳኑን እና መንግስቱን አንድ ላይ በማቀራረብ ሁለቱ በእጅጉ የሚገናኙ ነገሮች መሆናቸውን ያሳያል። እግዚአብሔር የዳዊትን መንግስት ለመመስረት እና ንግስናውንም ለዘላለም ለማድረግ ቃል ገባለት ይህም ደግሞ የነገስታት ንጉስ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጸመ (2 ሳሙ 7፡12-13 ፣ ሉቃስ 1:32-33)።

ኪዳኑ እና መንግስቱ አንድላይ በመሆናቸው እግዚአብሔር ዳዊትን እና እኛን አንዳንድ ዋና እውነታዎችን ያስተምረናል። በኪዳኑ እና በመንግስቱ መካከል ያለው ግንኙነት የኪዳኑን ስርዓታዊ መዋቅር ያሳያል። በኪዳኑ የእግዚአብሔር ሰዎች በእግዚአብሔር አገዛዝ ስር እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ድርሻ ያላቸው የመንግስቱ ዜጎች ናቸው። ምንም እንደ ዳዊት አይነት ሰው ቢቀመጥበትም እንኳን በ2ኛ ሳሙ 7፡13 ላይ እግዚአብሔር የሚናገርለት "ዙፋን" የእራሱ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው።

በኪዳኑ እና በመንግስቱ መካከል ያለው ይህ ግንኙነት የመንግስቱን መንፈሳዊነት ይገልጣል። አሁንም ኢየሱስ ያስተምርበት በነበረ ጊዜ እንደነበሩ አይሁዳዊያን ምድራዊ እና ስጋዊ የመንግስቱ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ዛሬም አሉ። አለም ሁሉ የእግዚአብሔር መንግስት ነው ወይም ይሆናል ብለው ያስባሉ። በእነርሱ እይታ ይህ መንግስት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት በምድር ላይ የምትሆን እና ብዙሃኑ ክርስቲያን የሆነባት ማህበረሰብ እንደሚፈጠር ይናገራሉ። ወይም ደግሞ መንግስቱ እንደ ብሉይ ኪዳኑ የእስራኤል መንግስት በምድራዊ የአይሁድ ስርዓት የሚሆን እና ይህም መንግስት ክርስቶስ ከመምጣቱ ጥቂት ጊዜ በፊት ቀድሞ እንደሚገዛ ያስባሉ።

እነዚህ ሀሳቦች ስህተት እንደሆኑ እግዚአብሔር የመንግስቱ መምጣት ከኪዳኑ ተስፋ ጋር ኪዳን በማገናኘት ያሳያል። መንግስቱ የአይሁዳዊ መንግስት ወይም የክርስቲያን ማህብረሰብ ሳይሆን እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር በህብረት የሚኖርበት ስርዓት ነው። በብሉይ ኪዳኑ ምሳሌነት የመንግስቱ ማዕከል የእግዚአብሔር ቤት ወይም ቤተመቅደሱ ይሆናል(ቁ 13)። ይህም የዛሬዋን የክርስቶስ አካል ቤተክርስቲያንን ይወክላል (ዩሀንስ 2:18-21)።

ለዳዊት የተገባለት የኪዳኑ ተስፋ መፈጸም የክርስቶስ ስራ እንደሆነ እናያለን። እርሱ መንግስቱን የሚያፀናው እና ወደመንግስቱ የገባው በምድራዊ አገዛዝ ወይም አይሁዳዊ መንግስት በመመስረት ሳይሆን በአፍረት እና በመከራ ነው (2ኛ ሳሙ 7:14 ፣ መዝ 89:30)። መሸነፍ የሚገባው ጦር ፣ ተዋጊዎች እና መሳሪያዎች ወይም መንግስታት ሳይሆኑ ሀጥያት ነው።

የጻፉት ሰዎች ፌዝንን እና ማላገጥን አስበው ያስቀመጡት ቢሆንም በክርስቶስ መስቀል በላይ የተሰቀለው ጽሁፍ የዳዊት ቃልኪዳን መፈጸሙን ይገልጣል። ክርስቶስ በመከራው ለእውነተኛ የአብርሃም ልጆች የአሁዳዊያን ንጉስ ነበር። ክርስቶስም እነርሱን ከመንፈሳዊ ጠላቶቻቸው ሁሉ የሚታደጋቸው እና በሰማያዊው መንግስቱ በመንግስተ ሰማያት ቦታን የሚያሰጣቸው ነው።

## አዲሱ ኪዳን

አዲስ ኪዳን (New Testament) በዕብራውያን 8:6-13 ላይ አዲስ ኪዳን (new covenant) ተብሎ ተጠቅሷል። በእርግጥም ቴስታመንት (Testament) የሚለው ቃል ኪዳን ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። በዕብራዊያን 8 መሰረት አዲሱ ኪዳን የድሮውን ኪዳን ተክቶታል።

ከዕብራዊያን 8:6-13 በመነሳት አብዛኞች በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን መካከል ትልቅ መሰረታዊ ለውጥ አለና የተለያዩ ኪዳኖች ናቸው ብለው ይደመድማሉ። የባፕቲስት ተከታዮች የአማኝን መጠመቅ እንደ መከራርከሪያ ነጥብ በማድረግ በግርዘት የታሰረ ኪዳን እና በጥምቀት የታሰረ ኪዳን ልዩነት አለው ብለው ድምዳሜያቸውን ያቀርባሉ። የቅድመ ሚሊኒያሎቹም ለእስራኤል አሁንም ልዩ የሆነ ምድራዊ የተስፋ ፍጻሜ እንዳላቸው በማንሳት እምነታቸውን ለመደገፍ ከባብቲስቶች ጋር የሚመሳሰል ድምዳሜ ያቀርባሉ (ለእስራኤል አንድ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አማኞች ደግሞ ሌላ ኪዳን አለ ይላሉ) ።

 አዲሱ ኪዳን የቀድሞውን ኪዳን የተካው የበለጠ የተሟላ የአንዱ እግዚአብሔር ኪዳን መገለጥ በመሆኑ ነው። በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ያለው ልዩነት የአመራር ልዩነት ነው ስለዚህም ሀሳብ ደግሞ ዕብ 8 በግልጽ ይናገራል።

በመጀመሪያ ቁጥ 10 የተለመደውን የኪዳን አሰጣጥ (ቀመር) በመጠቀም አዲሱ ኪዳን ከድሮው የሚለይ እንዳልሆነ "አምላካቸው እሆናለው ህዝቤም ይሆናሉ" በማለት ያስቀምጠዋል። በአዲሱ ሆነ በአሮጌው ያለው ህብረት ተመሳሳይ ነው።

ሁለተኛው በቁጥር 10 "ህጎቼን" የሚለው አመላካች ይህንን ያረጋግጥላናል። በአዲሱ ኪዳን ህጉ አልቀረም እንደ አዲስ በሰዎች የሥጋ ልብ ላይ ተጻፈ እንጂ(2ኛ ቆሮ 3:3) ። ህግ እና ኪዳኑ አሁንም አንድ ላይ ይሄዳሉ። ይህ ህግ በአዲስ መንገድ ቢጻፍም ህግ መሰጠቱ ግን የኪዳኑ መሰጠት እና መታወጅ እንደሆነ ከዘዳ 4:13 እና ከዕብ 8:10 እንረዳለን።

ሦስተኛ ዕብ 8:11 መሰረት በአዲሱም ሆነ አሮጌው ኪዳን ዋናው ጉዳይ እግዚአብሔርን ማወቅ ቢሆንም ልዩነቱ እግዚአብሔርን የምናውቅበት መንገድ ነው። ይህ ክፍል ስለ አዲሱ ኪዳን በደንብ የምናውቅበት እና የመፈጸሚያ ጊዜ እንደሆነ ይናገረናል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ያለ ካህናት እና ሌዋዊያን መካከለኝነት በቀጥታ የሚያውቁበት ጊዜ ነው (ሚል 2:5-7)።

ታዲያ አዲሱ ኪዳን ሙሉ በሙሉ የተለየ ኪዳን ሳይሆን ክርስቶስ ሲመጣ ሰማይ እና ምድርም አዲስ እንደሚሆኑት ሁሉ ኪዳኑም አዲስ ሆኗል። ሰማይ እና ምድር ይታደሳሉ እንጂ ነገር አይጠፉምና።

ስለዚህም የቀድሞው ኪዳን ማለፍ ሙሉ በሙሉ አዲስ ኪዳንን ያመጣ ሳይሆን እግዚአብሔር የህዝቡ አምላክ እንደሆነ እና የእራሱ እንዲሆኑ እንደሚወስዳቸው የሚያሳይ የአንዱ ኪዳን የተሻለ መገለጥ ነው። ይህ እንደ ብሉይ ኪዳን የተስፋው ቃል በምሳሌ የሆነ መገለጥ ሳይሆን የመጨረሻው እና የተሟላ የኪዳኑ በአካል መገለጥ ነው። በአዲሱ ኪዳን ህጉ የተሰጠን ለባርነት ሳይሆን እግዚአብሔርን ስለድነታችን በተግባር እና በንግግር የበለጠ እንድናከብረው እና እንድናመሰግነው ያግዘን ዘንድ ነው።

አዲሱ ኪዳን በዕብ 8:6 ላይ እንደተገለጠው የክርስቶስ ተወካይ ሳይሆን ክርስቶስ እራሱ ስላመጣው የተሻለ እና እጅግ የከበረ ነው። የኪዳኑ ፍጻሜ ወይንም መጠናቀቅ (consummation) ብቻ ከዚህ ይልቅ የከበረ ይሆናል።

## የአዲሱ እና የድሮው ኪዳን ንጽጽር

ከዕብ 8:6-13 አዲሱ እና የድሮው ኪዳን ሁለት የተለያዩ ኪዳኖች እንዳልሆኑ ተመልክተናል። ወሳኝ በሆኑ ነጥቦች ሁሉ ሁለቱም *አንድ/ተመሳሳይ* ናቸው።

በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የአስተዳደር ወይም አስተዳደራዊ ነጥቦች ብቻ ነው። በዚህ መልኩ ብቻ አንደኛው "ብሉይ (የቀድሞ)" ሌላኛው ደግሞ "አዲስ" ኪዳን በመሆን የድሮው ኪዳን አለፈ። አዲሱ ፕሬዝዳንት ሲሾም የአመራር ለውጥ ነው ሰለዚህም በተገደበ መልኩ አዲስ መንግስት ነው። ነገር ግን የመንግስቱ አይነት ወይንም ህገመንግስቱ አልተለወጠም። ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ብቻ አንደኛው "አዲስ" ሌላኛው ደግሞ "አሮጌ" ተብሏል። አሁን አሮጌ የሚለው ተቅጥላ ሙሉ በሙሉ አልፏል። በአስተዳደሩ ላይ አዲስ ፕሬዝዳንት ተተካ እንጂ በመንግስቱ እና በመተዳደሪያው ላይ ምንም አይነት ለውጥ የለም።

ታዲያ እንዴት አዲስ እና ብሉይ ኪዳን ልዩነት አላቸው? ዕብራዊያን 8 እንደሚለው በሦስት መንገድ ልዩነት አላቸው።

የመጀመሪያው የመካከለኛው መቀየር ነው (ቁጥ 6) ። ክርስቶስ ሙሴን ይተካል። ነገር ግን ይህ መሰረታዊ ልዩነት አይደለም ምክኒያቱም ሙሴ ክርስቶስን ይወክል ነበር። በዕብራዊያን 3:5 ሙሴ "በኋላ ስለሚነገረው ነገር ምስክር" ተብሎ ሲጠራ እንመለከታለን። እንዲሁም በዘዳግም 18:15 ላይም ሙሴ እራሱ " እንደ እኔ ያለ ነብይ" በማለት ስለክርስቶስ ሲናገር እንመለከታለን። ስለዚህም ልዩነቱ በአስተዳደራዊ ብቻ ነው።

ሁለተኛው የልዩነት ነጥብ ደግሞ ህጉ የተጻፈበት መንገድ ነው (ዕብ 8:10) ። ቀድመን እንደጠቀስነው ህጉ አልተሻረም ሆኖም ግን በድንጋይ ላይ ሳይሆን በስጋ ልብ ላይ ተጻፈ። ይህም የአመራር ለውጥ ብቻ ቢሆንም ለአዲስ ኪዳን አማኝ ትልቅ ልዩነት አለው። እንደ አዲስ የተጻፈ ጽሑፍ በፊት ከነበረው የተለየ ወይም አዲስ ነገር አይደለም።

ሁለተኛው ነጥብ ይበልጥ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በዘዳ 4:13 እና በዕብ 8:10 የህጉ መሰጠት የኪዳኑ መሰጠት እንደሆነ በግልጽ በመቀመጡ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ህጉ አንድ፣ ኪዳኑ ግን የተለያየ ነው ብሎ ሊከራከር አይችልም። እነዚህ ሁለቱም በዘዳግም እና በዕብራዊያን ላይ *ተገልጸዋል* ።

ሦስተኛ አዲሱ ኪዳን የተሟላ እና ፍጹም የሆነ የኪዳኑን መገለጥ አምጥቷል። ዕብ 8:11 የሚናገረው ይህንኑ ነው። ይህ የተሟላ መገለጥ ከእንግዲህ ወዲህ ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከለኛቸውን (ክርስቶስን) በምድራዊ መካከለኞች ጣልቃ ገብነት ሳይሆን በ*ቀጥታ* እንዲያውቁቱ አድርጓል ። በአዲሱ ኪዳን ውስጥ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናቶች ወይም ሌዋዊያን አያስፈልጉም (ሚል 2:6-7 እንደ ማስረጃ ማቅረብ እንችላለን በተለይም ደግሞ በብሉይ ኪዳን የነበሩ አስተማሪዎች እንደሆኑ ያሳየናል) ።

ይህም አስተዳደራዊ ለውጥ ነው። አዲሱ ኪዳን ያመጣው አዲስን (ልዩ እና ብቻውን *የሆነ*) *ኪዳን ሳይሆን* ስለኪዳኑ በብሉይ ኪዳን የተተነበየው እውነታ እና የተሟላ መገለጥ መሆኑን ነው (ዕብ 8:6) ።

ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ኪዳን አንድ ኪዳን ብቻ ነው።

## የኪዳኑ ፍጻሜ

ኪዳኑ ድህነትን የሚያመጣ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች የተሰጠ ውል ወይም ስምምነት እንደሆነ የማናምንበት አንዱ ምክንያት ከኪዳኑ ፍጻሜ ጋር የተያያዘ ነው። የኪዳኑ ፍጻሜ በሰማያዊ እና ዘላለማዊ መንግስት የጌታችንን ክርስቶስን ክብር እና የመጨረሻ መረዳት የምናውቅበት ነው።

ኪዳኑ ድህነትን የሚያመጣ ውል ወይምም ስምምነት ቢሆን ኖሮ በፍጻሜው ቀን ድህነታችንን በሙላት ስንቀበል ኪዳኑ ይቆማል ወይም ደግሞ ሌሎች ስምምነቶች እንደሚያበቁት ስምምነቱ ሲያበቃ ጠቃሚ መሆኑን ያቆም ነበር።

ነገር ግን ይህ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም ኪዳኑ ዘላለማዊ ነው። ለውል ወይም ለስምምነት እንደሚደረገው ለትንሽ ጊዜ ብቻ አገልግሎን ወደጎን የሚጣል አይደለም። ስለዚህም ኪዳኑ በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል ያለ ግንኙነት ወይም ትስስር ነው ብለን እናምናለን። ይህ ግንኙነትም በመጽሐፍ ቅዱስ የኪዳን ቀመር ፡" እኔም አምላክ እሆናቹሀልው እናንተም ህዝቦቼ ትሆናላችሁ" በማለት ተገልጿል።

እግዚአብሔር የእኛ እኛም የእርሱ መሆናችን የኪዳኑ ዋና ባህሪ ከሆነ መንግስተ ሰማይ ውስጥ ኪዳኑ በሙላት ይታወቃል እንጂ የሚጣል ወይም ወደኋላ የሚቀር አይደለም። የመንግስተ ሰማይ ሙሉ አላማ "እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ሆነን እርሱን በክብሩ የምናውቅበት እና ለዘላለምም በእርሱ የምንደሰትበት ስፍራ"[2] ነው።

ራዕይ 21:3 የአዲሱን ሰማይ እና ምድርን ክብር በዚሁ መልክ ያስቀምጠዋል። ሁሉም ነገር አዲስ ሲሆን እንባ ፣ ሞት ፣ ማልቀስ ፣ ሀዘን ወይም ህመም አይኖርም። ይህ እንዴት ግሩም ነው!

ከዚህም በላይ የሚበልጠው ነገር ከመንግስተ ሰማይ የሆነ ድምጽ እንደነገረን ይህ ነው "እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው *ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል።"*

ይህ ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ" ከሚለው ኪዳናዊ ቀመር ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እንደተጠቀሰ እናስተውል። ከዚህ የሚበልጥ፣ የሚፈልግ ወይንም አስገራሚ ነገር ምን አለ!

ደግሞም ይህ ክፍል ሰለ እግዚአብሔር ማደሪያ እንደሚናገርም እናስተውል። ይህ ማደሪያ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የሚሆንበት እና እንደ አምላካቸው እራሱን የሚገልጥበት የኪዳኑ ስፍራ ነበር (ዘጽ 29:42-26)።

የብሉይ ኪዳኑ ድንኳን እግዚአብሔር በክርስቶስ ከእኛ ጋር ሆኖ አምላካችን የሚሆንበት ፣ በክብሩ ማንነቱን በሙላት ወደ ገለጠበት፣ የተሻለው እና የሚበልጠው ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠቁም ጥላ ነው። በክርስቶስ በኩል ከእኛ ጋር ይገናኛል ደግሞም ያናግረናል። በክርስቶስ በኩል ከእኛ ጋር አብሮ ይኖራል። ይህም የእግዚአብሔር ኪዳን ዘላለማዊ በረከት ነው።

## የኪዳኖቹ ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት የተለያዩ ኪዳኖች የተነጣጠሉ ኪዳኖች ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ዘላለማዊው አንድ ኪዳን መሆናቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ አስደግፈን ተመልክተናል። አሁን ደግሞ የተለያዩ ኪዳኖችን በመጥቀስ እና እያንዳንዳቸው የአንዱ ኪዳን መገለጥ ስለ መሆናቸው በዝርዝር ለጻፍነው ሁሉ ማጠቃለያ ለመስጠት እንወዳለን።

የመጀመሪያው የኪድኑ መገለጥ በገነት ውስጥ ለአዳም የተሰጠው ነው። ይህ የኪዳኑን መሰረታዊ ባህሪ ስለሚገልጥ *የሀይወት ኪዳን* ተብሎ ሊጠራ ይችላል። እግዚአብሔር የኪድኑ ሉዓላዊ ጌታ እንደሆነ እና ሰውም በግልጽ በኪዳኑ ውስጥ ያለውን ቦታ ገልጧል(ዘፍ 1 ፣ ዘፍ 2 ፣ ሆሴዕ 6:7)።

ሁለተኛው የኪዳኑ ታላቅ መገለጥ ከውድቀት በኋላ ለአዳም የተሰጠው መገለጥ ነው። ይህ ኪዳን *የተስፋ ኪዳን* ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ይህም የእግዚአብሔርን ታማኝነት ፣ ኪዳን ጠባቂውም አምላክ ከህዝቡ ጋር ያለውን ኪዳን በሉዓላዊነቱ እና በአዳኝ ጸጋው የሚያስተካክል እነደሆነ ገልጧል (ዘፍ 3: በተለይም ቁጥ 15)። በኪዳኑ ውስጥ ክርስቶስ ቃል የገባው ዘር እና ታላቅ መስዋት መሆኑ ተገልጧል (ቁጥ 15:21)።

ሦስተኛው ወሳኝ መገለጥ ለኖህ የተሰጠ። ይህ ኪዳን *የፍጥረት ኪዳን* በመባል በደንብ ይታወሳል። በዚህም እግዚአብሔር የኪዳኑን አለም አቀፋዊነት ሰውን ሁሉ ብቻ ሳይሆን ፍጥረትን ሁሉ እንደሚያካትት ገልጧል (ዘፍ 9:1-17)። በኪዳኑ ክርስቶስ አስታራቂ እና የፍጥረታት ሁሉ ጌታ መሆኑ ተገልጧል (ዘፍ 9:15-16, ቆላ 1:20)።

አራተኛው ለአብርሃም የተሰጠው መገለጥ ነው። ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ የእግዚአብሔር ኪዳን የቤተሰብ ኪዳን መሆኑ በደንብ በማስረዳቱ ኪዳኑ *የቤተሰብ ኪዳን* ተብሎ መጠራት ይችላል (ዘፍ 15, ዘፍ 17)። እግዚአብሔር አብ በልጁ በኩል ለአብርሃም የአማኞች እና የልጆቻቸው አምላክ እንደሚሆን ገልጠለት።

አምስተኛው ታላቅ መገለጥ ለእስራኤል የተሰጠው መገለጥ ነው። በመገለጡ ውስጥ የህጉ መሰጠት ዋናው ጉዳይ በመሆኑ ኪዳኑ *የህግ ኪዳን* ተብሎ ቢጠራ የበለጠ ይገልጠዋል። በዚህም እግዚአብሔር ሕጉ እና ኪዳኑ እንደማይጣረሱ እና አንድ ላይ የሚሄዱ እንደሆነ ይገልጥልናል (ዘጽ 19 ፣ ዘጽ 20 ፣ገላ 3፣ ገላ 4)። እስራኤል ለሆንነው ለእኛ እንደ እግዚአብሔር ህዝብነታችን ህጉ ህይወታችን የሚያስፈልገውን ገደብ እንደሚያሳየን እግዚአብሔር በዚህ ኪዳን ውስጥ ነገሮናል።

ስድስተኛው እና የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን መገለጥ ለዳዊት የተሰጠው መገለጥ ነው። ይህም ደግሞ የ*መንግስቱ ኪዳን* ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በዚህም እግዚአብሔር የኪዳኑን መዋቅር በተለየ መልኩ ገልጧል (2ኛ ሳሙ 7 ፣ መዝ 89)። ከዚያም በተጨማሪ የክርስቶስን ሉዓላዊ ራስነት እና የኪዳኑ ጌታ የመሆኑን ልዩ አድርጎ ይገልጣል።

አዲስ ኪዳን (Testament) በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *አድስ ኪዳን* (covenant) ተብሎ ተጠርቷል ። ይህም ፍጹም የተለየ ኪዳን ስለሆነ ሳይሆን የኪዳኑ አዲስ መገለጥ በመሆኑ እና ጥላ ከመሆን ይልቅ ጥላው የጠቆመው አካል ስለተገለጠበት ነው (ዕብ 8)። በዚህም በመጨረሻ ክርስቶስ ከበረከቶቹ ጋር መጥቶ ጥላን እና ምሳሌን ሁሉ ይፈጽማል።

ኪዳኑ በሙላት እንዲታወቅ አሁንም እስከ ኪዳኑን የፍጻሜ ቀን እንጠብቃለን። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ማደሪያ ከህዝቡ ጋር ይሆናል ፤ አምላካቸው ሆኖ ከእነርሱ ጋር ይኖራል ፣ እነርሱም ደግሞ ህዝቡ ይሆናሉ (ራዕይ 21:3)።

## የድነት ስርዓት

በሥነ-መለኮት ውስጥ ስለ "ድነት ቅደም ተከተል" ስናወራ የተለያዩ የድነት ክፍሎች አተገባበር እና እግዚአብሔርም እነዚህን ነገሮች እንዴት ለህዝቡ በመንፈስ ቅዱስ በኩል እንደሚሰጣቸው የምናብራራበት መንገድ ነው። በሌላ አማርኛ "የድነት ቅደም ተከተል" በእኛ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ስራን ያስረዳናል።

ከድነት ቅደም ተከተል ጋር በተቀራራቢ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ክፍል ሮሜ 8:30 ነው ነገር ግን ይህ ጠንካራ በሆነ ሥነ-መለኮታዊ እይታ ብዙም ቅደም ተከተልነት የለውም። ለአብነት ያህል ክፍሉ ስለ አስቀድሞ መወሰን በማንሳት እግዚአብሔር ምድር ከመመስረቱ በፊት ለእኛ የሰራው እንጂ በእኛ ውስጥ የሰራው ስራ እንዳለሆነ ይናገራል።

የተለመው የድነት ቅደም ተከተል የዌስትሚኒስተሩ ትልቁ የእምነት አስተምህሮ እንደሚገልጠው - ከክርስቶስ ጋር አንድነት ፣ ውጤታማ መጠራት ፣ መጽደቅ ፣ ጉዲፈቻ ፣ መቀደስ ፣ እና መክበር ነው። ሌሎች ሌላ አይነት ደረጃዎችን ሊጠቅሱ ይቻልሉ። አብዛኞቹ ለምሳሌ ዳግም ውልደትን እና እምነትን ያካትቱበታል። ሆኖም ግን እንደህ አይነት ደረጃዎች ዋና አላማቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን የተለያዩ የድነት ክፍሎች ለመረዳት መሞከር ነው።

እንደዚህ አይነት ቅደም ተከተል ስናነሳ መታወስ የሚገባቸው በርካታ ነገሮች አሉ።

ይህ ቅደም ተከተል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነጥቦችን ለመረዳት የሚደረግ ሙከራ እንጂ የተለያዩ ስርዓቶችን በመከተል አንደኛውን በረከት፣ ከዚያም ደግሞ ቀጣዩን በረከት መቀበል እንችላለን የሚል አይነት አስተምህሮ አይደለም። ግልጹ እውነታ እኛ ከልምምዳችን እንደተረዳነው እነዚህ በረከቶች በአብዛኛው በአንዴ የምንቀበላቸው ናቸው። ደግሞም የተቀሩት የአንድ ጊዜ የመንፈሳዊ ክስተቶች አይደሉም። ለምሳሌ መቀደስ ሰው ከዳነበት ቀን ጀምሮ  እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ የሚቀጥል ነው። የድነት ተግባር በአንዴ የሚያልቅ ሳይሆን የህይወት ዘመናችን የሚቀጥል እና ከክርስቶስ ጋር መንግስተ ሰማይ ስንገባ የሚፈጸም ጉዳይ ነው።

በእርግጥም ይህ  በፍጹምነት ደረጃ ላይ እንደርሳለን እና ቅድስናችን ተጠናቅቋል ብለው በሚያምኑ ሰዎች እና የድነትን ተግባር በአንዴ የሚፈጸም ነገር እንደሆነ ለመመልከት በሚፈልጉ የሚካድ ነው።

በተሓድሶ የድነት ደረጃዎች ውስጥ አትኩሮት ሊሰጣቸው የሚገቡ እና የማይቀየሩ ጉዳዮች አሉ። አዲስ ፍጥረት መሆን እና ውጤታማ ጥሪ ከእምነት በፊት ሊሆኑ ይገባል። አለበለዚያ እንደ አርሜኒያኒዝም እሳቤ በሰው ስራ የሆነ እምነት አለን ማለት ነው። የፕሮቴስታንት አስተምህሮ እውነት የሆነውን በእምነት ብቻ መጽደቅ የሚባለውን እውነታ ለመጠበቅ እምነት እራሱ ከመጽደቅ በፊት ሊመጣ ይገባዋል። በስተመጨረሻም መጽደቅ የግድ መቀደስን መቅደም ይኖርበታል አለበለዚያ የሮሚሽ አስተምህሮ እንደሚያስተምረው በስራ መጽደቅ ይሆንብናል።

ይህ ሁሉ ማንኛውም የድነት ደረጃዎች ድነት በመንፈስ ቅዱስ ሉዓላዊ ተግባር ሙሉ በሙሉ የእግዚአሔር ስራ የመሆኑንም ተግባራዊነት ማስተማር እንዳለበት ለመናገር ነው። ድነት የጸጋ ተግባር በመሆኑ "የጌታ ነው" (ዮናስ 2፥9)።

## ልንቋቋመው የማንችለው ጸጋ

የድነት ቅደም ተከተልን ስናጠና እንደ ወርቃማ ክር ጸጋ በቅደም ተከተሎቹ ሁሉ ላይ ተጠቅልሎ እናገኘዋለን። እያንዳንዱን የድነት ደረጃ የሚፈጥረው እና ዋስትናን የሚሰጠን ጸጋ *ልንቋቋመው የማንችለው ጸጋ* ነው።

ይህ ጉዳይ አትኩሮት ሊሰጠው ይገባል። የድነት የመጀመሪያው ደረጃ ጸጋ ነው ነገር ግን የድነት የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ ስራችን ነው የሚል አስተሳሰብ በፍጹም ሊኖረን አይገባንም። ዳግም ውልደት የእግዚአብሔር ስራ አይደለም ፤ መቀደስ *ደግሞ የእኛ ስራ ነው* ።

 የድነት ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ስራ የጸጋ ስራ ብቻ ሲሆን የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ የጸጋ እና የሰራ ነው የሚለው አስተምህሮ ትክክል አይደለም። በእምነታችን፣ በመለወጥ፣ እና በቅድስና ህይወት ብንነቃም እነዚህ ነገሮች በእኛ ላይ የተደገፉ ወይንም ደግሞ ከእግዚአብሔር ይገባናል ብለን የምንጠይቃቸው ነገሮች አይደሉም። እነዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚመጡ የእርሱ ጸጋ ናአው(ሮሜ 9፡16)። በእኛ ውስጥ መልካም የሆነውን ነገር ለእርሱ ደስታ የማድረግ ፈቃድ እና አቅም የሚሰጠን እርሱ ነው። (ፊሊ 2፡13)

ከድህነት ቅደም ተከተሎች መካከል *አንዳንዶቹ ብቻ* ልንቋቋመው በማንችለው ጸጋ የሚሆኑ እንደሆነ ማሰብ የለብንም። በመለወጣችን እና በመቀደሳችን ምክኒያት እንድንለወጥ እና እንድንቀደስ የሚያደርገንን የመንፈስ ቅዱስ ስራ እና ጸጋ ልንቋቋመው እንችላለን ማለት አይደለም። ድነት *በሙሉ* በማንቋቋመው ጸጋ የተፈጸመ ነው።

ጸጋ በባህሪው ልንቋቋመው የማንችለው ነው ፤ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጸጋ ነው ነውና። እርሱ ሁሉን ቻይ እንደመሆኑ ጸጋውም ሁሉን ቻይ ነው። ይህም ደግሞ በመግቦቱ ብቻ ሳይሆን በድነትም ጭምር ነው "እጁንም የሚከለክላት ወይም። ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም?" (ዳን 4:35) ።

አብዛኞቻችን ይህንን ታላቅ እውነት ችላ ብለነው ጥግ አስይዘነዋል። የተወሰነ ጸጋ ለሁሉም ሰዎች ተሰጥቷል የሚለው የጋር ጸጋ አስተምህሮ በግልጽ የሚያስተምረው ልንቋቋመው የምንችለው ጸጋ እንዳለ ነው። እንደዛውም በመልካም ልብ ወንጌልን የማቅረብ አስተምህሮ (doctrine of the well-meant offer of the gospel) *ጸጋው ብዙዎች ቢቃውሙትም እና ጸጋውን ቢቋቋሙትም* ወንጌልን ለሚሰሙ ሁሉ ድነትን

እንደሚሰጥ ያስተምራል። ውድ የሆነውን ጸጋን ልንቋቋመው አንችልም የሚለውን ይህንን አስተምህሮ ለመመከት ስንል ከእነዚህ ሁለት አስተምህሮዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ሊኖረን አይገባም።

ነገር ግን ይህ ማለት የማይቋቋሙት ጸጋ እግዚአብሔር ህዝቡን ወደ መንግስተ ሰማይ እያሰቃያቸው ፣ እየታገላቸው እና እያስገደዳቸው ያመጣቸዋል ማለት አይደለም። የማይቋቋም ጸጋ አስገድዶ የሚገፋ ሳይሆን የወዴታ ግፊት ነው። በሌላ አማርኛ እግዚአብሔር ልባችንን እና አእምሮዋችንን በመቀየር እርሱን እንድንወደው ፣ እንድንፈልገው እና እንድንከተለው ፣ በመታዘዝም ውስጥ እንድንጠበቅ እስከመጨረሻው ድረስ ያደርገናል ማለት ነው።

በመጀመሪያ የካልቪኒዝም አምስት ነጥቦች የነበሩት የዶርት ቀኖና ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ይህንን ይላሉ "ሰዎችን ሁሉ ስሜት እንደሌላቸው ነፍሳት የሚያደርግ ወይም ፈቃዳቸውን እና የመፍቀዳቸውን ባህሪ የሚወስድ ደግሞም ጉዳትን የሚፈጽም አይደለም። ነገር ግን መንፈስን የሚያፈጥን ፣ የሚፈውስ ፣ የሚያስተካክል እና ደስ በሚያሰኝ እና ኃያል በመሆነ መልኩ መንገዱን የሚቀይስ ነው፤ በዚህም የሥጋ አመጽ እና እብሪተኝነት አስቀድሞ በነገሰበት ስፍራ፣ ዝግጁ እና እውነተኛ መንፈሳዊ መታዘዝ መግዛት ይጀምራል"[3] ይህ ልንቋቋመው ስለማንችለው ጸጋ ውብ የሆነ አገላለጽ ነው።

ተፈጥሯዊ ብልሹነታችንን የሚያሸንፈው የማንቋቋመው ጸጋ ብቻ ነው። እንደዚህ አይነት ጸጋ ብቻ "በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል" የሚልን ዋስትና ይሰጠናል (1ኛ ጴጥ 1:5)። ስለዚህም ይህ የማንቋቋመው ጸጋ ብቻ በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን ምንም እንደሌለ አውቀን እንድንጽናና እና እንድናምን መልካም የሆነን ተስፋን ይሰጠናል።

**ዳግም ውልደት**

ዋና የሆነውን "የድነት ቅድመ ተከተል" ጥናት አሁን ዳግም ውልደት ምን እንደሆነ በመመልከት እንጀምራለን። "ዳግም ፍጥረት (regeneration)" ማለት "ዳግም ውልደት (rebirth)" *(በአማርኛው ዳግም ውልደት በሚለው ትርጓሜ ቀጥለናል)* ማለት በመሆኑ እንደ ክርስቲያን የአዲሱ ህይወታችን ጀማሬ እና የድነታችን የመጀመሪያው ደረጃ ነው ብለን እናምናለን።

የጸጋን የመጀመሪያ ተግባር ዳግም ውልደት(ዩሀንስ 3:3) ነው በማለታችን መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እውነት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ስራ እንደሆነ እና ያለእኛ እርዳታ የተፈጸመ ይልቁንም እኛ እራሳችን ሳናውቀው መሆኑን ያሳየናል። አዲስ የተወለደ ህጻን ወደዚህ አለም ለመምጣቱ ምንም የራሱ ድርሻ እንደሌለው ሁሉ እኛም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ዳግም ለመወለዳችን ያደረግነው አንዳች ነገር የለም።

ይልቁኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ማመላከት ብቻ ሳይሆን "እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" በማለት በስፋት ያስትምረዋል (ዩሀንስ 1:13)። የሀጥያትተኛ ፈቃድ (የስጋ ፈቃድ) ወይም ደግሞ የሰው ፈቃድ ሃይል (የሰው ፈቃድ) በየትኛውም መንገድ ከዳግም ውልደት ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ እናስተውል።

ዳግም ውልደት የመጀመሪያው የጸጋ ስራ ካልሆነ ማንም የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም (ዩሐ 3:3)። ኢየሱስ " ማንም አይችልም" ያለውን አስተውሉ። ስለዚህ አሳ በደረቅ መሬት ላይ (ከባህር ወጥቶ) መኖር እንደማይችለው አዲስ ፍጥረት ያልሆነ ሀጥያተኛ ከእግዚአብሔር መንግስት ጋር የሚያገናኘው ነገር ምንም የለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የመጀምሪያ የጸጋው ስራ እንደ ዳግም ልደት ብሎም *የአዲስ ልብ* ስጦታ (ሕዝ 36:25) ፣ *የልብ ግርዘት* ይህም ማለት ሀጥያትን ከልብ ቆርጦ መጣል (ቆላ 2:11-13) ፣ *ጥምቀት* ማለትም ደግሞ የሀጥያት መታጠብ (ቲቶ 3:5) *፣ የመንፈስ መንቃት/መፍጠን* ፣ ከመንፈሳዊ ሞት መንቃት ወይም መነሳት (ኤፌ 2:1) ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ *አዲስ ፍጥረት* መሆን (ቁጥ 10) እና *ከጨለማው መንግስት ወደ እግዚአብሔር ውድ ልጅ መንግስት* ሽግግር (ቆላ 1:13) በማለት ይገልጸዋል።

እያንዳንዱ አገላለጽ ዳግም ልደት የሁሉን ቻዩ እና የአስገራሚው አምላክ ሉዓላዊ ስራ እንደሆነ ያብራራልናል። ማን የሞተን ነገር ማስነሳት ይችላል? የዶርት ቀኖና ይህንን ሲገልጸው "ይህ በግልጽ ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ስራ ፣ ታላቅ ኃይል ያለው ደግሞም አስገራሚ፣ ሚስጥራዊ፣ እና ልንረዳው የማንችል እንጂ ከፍጥረት ስልጣን ያነሰ ወይንም ከሞትም ዝቅ ያለ አለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።"[4]

አስደናቂ የሆነው፣ ምናልባትም ከሌሎች አገላለጦች በላይ የሆነው የዳግም ልደት ማብራሪያ ኢየሱስ ህይወቱን ለጠፉ ሃጥያተኞች ሰጠ የሚለው ነው (ገላ 2:20 ፣ ቆላ 1:27)። በአዲስ ፍጥረትነት የተሰጠን የክርስቶስ የትንሳኤው ህይወት የሆነው አዲስ ህይወት ዳግም የሚሞት አይደለም (ዩሐ 11:25-26)።

ይህ *አዲስ* ህይወት ነው። አንድ ሰው በፊት ይናገር እና ይኖር እንደነበረው ዛሬም ሊናገር እና ሊኖር በፍጹም አይችልም። እርሱ ከዚህ በኋላ በመንፈሱ ሙውት ሳይሆን ህያው ነው። ሞት እዚያው ሆኖ ይበሰብሳል ህይወት ግን ይተነፍሳል ፣ ይንቀሳቀሳል ፣ ይናገራል። ዳግም የተፈጠርን እኛ በአሮጌው ማንነታችን እና ሃጥያታችን መኖር ከመቀጠል ይልቅ ከሞት ወደ ህይወት እንደተሻገርን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆነን ለእግዚአብሔር ህያዋን እንደሆንን እራሳችንን እንቆጥራለን (ሮሜ 6:11–13).

## መጠራት

አዲስ ፍጥረት (መንፈሳዊ ዳግም ልደት) በልባችን የክርስቶስ ኢየሱስ የትንሳኤው ህይወት መዘራት ከሆነ መጠራት ደግሞ እንዲያድግ እና እንዲያፈራ በዘሩ ላይ የሚሆን ዝናብ እና ጸሀይ ነው ማለት እንችላለን።

መጠራት አንዳንድ ጊዜ "ተግባራዊ ጥሪ (efficacious calling)" ተብሎ ይጠራል። ይህ ማለት መጠራት የተፈለገውን ውጤት የሆነውን ድነትን የሚያመጣ የእግዚአብሔር ኃያል ስራ ነው ማለት ነው። ውጤታማ ጥሪ የማንቋቋመው ጸጋ አካል ነው።

በድነት ቅደም ተከተል ውስጥ ስለመጠራት ስንነጋገር ስለሚጣራው ነገር ግን የማዳን ኃይል *ሳይኖረው* በሌሎች ሰዎች ጆሮ ውስጥ ስለሚገባው ጥሪ አይደለም። በማቴዎስ 22፡14 ላይ ክርስቶስ "የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና" በዚያ አውድ *መጠራት* የሚለውን ቃል ይጠቀመዋል ። እኛ የምንናገረው ግን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔር በመረጣቸው ህዝቦች ውስጥ የሚሰራው ስራ፣ በዚህም ደግሞ የወንጌል መሰበክ ድህነትን የሚያመጣላቸው እና ድህነታቸውንም የሚጠብቅላቸው እንደሆነ የሚያመለክተውን እውነት ነው።

ትልቅ አትኩሮት ለዚህ ሊሰጥ ይገባዋል። ውጤታማ ጥሪ በእኛ የሚያስጀምረው ድነትን ብቻ ሳይሆን የድነትን *ሙላትም* ጭምር ነው። እኛን በኃይሉ እና መቋቋም በማንችልው መንገድ ወደ ንሰሐ (ማት 9:13) ፣ እምነት (ሮሜ 10:17) ፣ ቅድስና (1ኛ ተሰ 4:7) ፣ ከክርስቶስ ጋር ህብረት (1ኛ ቆሮ 1:9) ፣ ነጻነት (ገላ 5:13) ፣ እርግጠኝነት (ኤፌ 4:4) እና በመጨረሻም ወደ ክርስቶስ ክብር ይጠራናል (1ኛ ጴጥ 5:10, ራዕይ 19:9) ። ስለዚህ ጥሪው ወደ ህይወታችን ዘመን ሁሉ መምጣቱን መቀጠል አለበት። ወደ እኛ የሚመጣው ወደ ቅድስና እና ወደ እርግጠኝነት (assurance) ሊጠራን ብቻ ሳይሆን ወደ ንሰሐ እና ወደ እምነትም ሊጠራን ጭምር ነው። ሀጥያተኞች እና በእምነታችን ደካሞች እስከሆንን ድረስ ወደ ንስሃ እና ወደ እምነት ልንጠራ ይገባል።

ይህንንም የምንለው ለተለመደው ሀሳብ የመልስ ምት ለመስጠት ነው። *በብዙዎች ዘንድ ይህ ጥሪ ላልዳኑት እንጂ ለዳኑት ሰዎች ሊደረግ አይገባውም ተብሎ ይታሰባል። በዚህም ብዙሃኑ አገልጋዮች እንደ ቀሪዎቹ (እንዳልዳኑት) ሁሉ በእጅጉ ለሚያስፈልጋቸው ለዳኑ ሰዎች ምንም አይነት ጥሪን አያቀርቡም።*

ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር ድምጽ የሚጣራው *ክርስቶስ* እንደሆነ አጽኖት ልንሰጥበት እንወዳለን (ሮሜ 4፡17 ፣ ዩሐ 10 :3 ፣ 16 ፣ 27) ። ይህም ጥሪ በመንፈስ ቅዱስ ስራ የክርስቶስን ጥሪ እንዲሰሙት ፣ ድምጹን እንዲያውቁት ፣ በጎች ወደ እረኛቸው እንደሚመጡ ወደ እርሱ እንዲመጡ በአንዳንድ ሰዎች ልብ ውስጥ የሚሰራ ሰራ ነው። ታዲያ ይህ አስደናቂ አይደል?

ዩሀንስ 10:3 "የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል" ይላል። ጥሪው ለሁሉም ሳይሆን ለተወሰኑት ነው። ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስ አስቀድሞ በጎቹን እንደሚያውቅ ነው። ከፍጥረታት በፊት ከአብ ለእርሱ የተሰጡ ናቸውና በእርግጥም ያውቃቸዋል (ኤፌ 1:4-6)።

ነገር ግን ክርስቶስ በጎቹን በስማቸው ሲጠራ እነርሱ ሜሪ ወይም ዊሊያም ብሎ በተለምዶ ስማቸውን አይጠራቸውም። የሚሰሙት መንፈሳዊ ሰማቸውን ነው፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በልባቸው ውስጥ አስቀድሞ ሲሰራ የተቀበሉትን ያንን ስም - ለምሳሌ የ *ተጠማችሁ* (ራዕይ 22:17)፣ የ *ተራባችሁ* (ኢሳ 55:1)፣ *ሸክማችሁ የከበደባችሁ*( ማቲ 11:28) የሚለውን ስም ነው።

በእርግጥም ጥሪው ሀጥያተኞችን የተራቡ ፣ የተጠሙ ፣ ሀጥያት እና ጥፋተኝነት የከበደባቸው እና በመጨረሻም ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ፈቃደኛ የሆኑ ያደርጋቸዋል። ስለዚህም ነው ጥሪው ተግባራዊ ጥሪ ይባላል።

የክርስቶስን የጥሪ ድምጽ መስማት እኛ ወደ እርሱ መጠራታችንን ማወቅ እንዴት ያለ በረከት እና ደስታ ነው።

## ጥሪ እና ስብከት

ተግባራዊ ጥሪ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ሉዓላዊ እና መቋቋም የማይቻለውን የመንፈስ ቅዱስ ስራ ስለሚያጠቃል አንዳንድ ጊዜ *ውስጣዊ ጥሪ* በመባል ይታወቃል ። ውጫዊ ጥሪ ከሆነው የቃሉ ስብከት የተለየ ጥሪ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን ጥሪ በወንጌል ስብከት በኩል የሚሰሙ ሁሉ በልባቸው ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ጥሪ እንደማይሰሙ ይናገራል። በዚህም ምክንያት በወንጌል ስብከት ሁሉም አይድኑም።

በሌላ አማርኛ በወንጌል ስብከቱ አንዳዶች የሚድኑት እና ሌሎቹ የማይድኑት የተለያዩ ሰዎች ስለሆኑ ሳይሆን በእነርሱ ላይ በተገለጠው የእግዚአብሔር ስራ ልዩነት ነው። ለዚህም ነው ማቴዎስ 20:16 እና ማቴዎስ 22:14 "የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና" የሚለን። ይህ ክፍል "ብዙዎች ተጠርተዋል ጥቂቶች ግን ምላሽ ይሰጣሉ" ሳይሆን የሚለን በእኛ መካከል ያለውን ልዩነት ግልጥ አድርጎ ያሳያል። ልዩነቱ እግዚአብሔር አንዳዶቹን መምረጡ እና አንዳንዶቹን ደግሞ አለመምረጡ ነው። ከዚያም ምርጫ አንጻር አንዳንዶቹን በውጫዊም በውስጣዊም መንገድ ይጠራቸዋል ሌሎችን ደግሞ አይጠራም።

መጽሐፍ ቅዱስ መጥራት የሚለውን ለውጫዊም ለውስጣዊም መጠራት ቢጠቀመውም ውስጣዊ መጥራት የሚመጣው *ውጫዊው መጠራት* በሆነው በስብከተ ወንጌል እንደሆነ መረዳት አለብን። ሁለቱንም ለመግለጽ ተመሳሳይ ቃል የምንጠቀመው ለዚህ ነው።

ይህንን በሮሜ 10:17 ላይ እንመለከታለን “እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው” ። ቁጥር 17 ከቁጥር 10 እስከ 14 ላይ የሚገኘውን ሃሳብ የሚጠቀልል ቁጥር ነው ነው። ለድነት ማመን እና ስብከትን መስማት የማይነጣጠል ግንኙነት አላቸው።

ቤተክርስቲያን ወንጌልን እስከ አለም መጨረሻ ሁሉ መስበክ ያለባት ለዚህ ነው። ይህ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሁሉ ወደ ድነት በመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ጥሪ እንዲያቀርብላቸው የሚያደርግበት መንገድ ነው።

ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ በስብከት ውስጥ ስለሚሰራ የወንጌል ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን ልናጸና እንወዳለን። ወንጌሉ “ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና” (ሮሜ 1:16,1ኛ ቆሮ 1:18, 24ንም ይመልከቱ)። ስብከቱም ውጤታማ ይሆን ዘንድ አንደበተ ርዕቱነት፣ ልመና ወይንም ሌሎች ሁኔታዎች አያስፈልጉትም።

ክርስቶስ በስብከት ውስጥ ያናገራል መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በስብከት ውስጥ ስለሚሰራ የወንጌል መሰበክ ሁልጊዜ ኃያል ነው፣ ነገር ግን ሁሌም ወደ ድነት ላያደርስ ይችላል ። ክርስቶስ ሲናገር እና መንፈስ ቅዱስ ሲሰራ አለመነካት አይቻልም። በወንጌል መሰበክ አንደኛው ይድናል ሌላኛው ግን ልቡ ይደነድናል (2ኛ ቆሮ 2:14-17)። ማንም ከሁለቱ መካከል ሊሆን አይችልም።

ስለዚህም በወንጌል መሰበክ የእግዚአብሔርን አላማ እንረዳለን ፤ የክርስቶስ ስራም ደግሞ ውጤታማ ይሆናል። ከተመረጡት አንዳቸውም አይጠፉም ወይንም ከክርስቶስ ደም አንዷቷ ጠብታ እንኳን አትባክንም። ስብከትም ባልዳኑት ላይ አይባክንም። ስለዚህ ከወንጌሉ ስር መሆን እጅግ ዋና እና አስፈላጊ ነገር ነው። በዚህ የዳንነው እኛ እንኳን “ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል” (ዕብ 2:1-3)። ወንጌል ሁል ጊዜም ህይወትን በህይወት ላይ የሚጨምር አልያም ደግሞ በሞት ላይ ሞትን የሚጨምር ነው።

## ግብዣ ሳይሆን ጥሪ ነው

ወንጌል ከጥሪ ይልቅ እንደ “ግብዣ” የሚቀርብ ነው ብለው የሚናገሩ ብዙዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ጊዜም እንኳን ቢሆን “ግብዣ” የሚለውን ቃል ሲጠቀም አንመለከትም ስለዚህ ይህንን መስማት እጅግ

የሚገርም ነገር ነው። “ግብዣ” ማቅረብ ከሚለው ቃል ጋር ምንም ችግር የለብንም። ነገር ግን በቀደመው አውድ መሰረት ወንጌል ማለት ክርስቶስን “አቅርቦ ማሳየት” ማለት ነው። የዌስትሚኒስተር ትልቁ የእምነት መግለጫ ለምሳሌ የክርስቶስን ግብዣ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ መዳን እንደሚችል *መመስከር*”[5] ነው በማለት ያስቀምጠዋል።

ነገር ግን በዘመናዊው አውድ “ግብዣ” የሚለው ሀሳብ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እንደሚወድድ ፤ በወንጌሉም በኩል ሁሉንም ለማዳን እንደሚሞክር እና ሀጥያተኛ ይዳን ወይንም አይዳን በሀጥያተኛው ፈቃድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው። እነዚህ አስተምህሮቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይጻረራሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እንደሚወድድ አያስተምርም (መዝ 11:5 ፣ ዩሀንስ 13:1 ፣ ሮሜ 9:13) ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉንም ለማዳን እየሞከረ ነው የሚል አስተምህሮ የለውም (ኢሳ 6:9-11 ፣ ሮሜ 9:18 ፣ 2ኛ ቆሮ 2:14-16) ። በእርግጠኝነትም እግዚአብሔር ሀጥያተኞችን ለማዳን በሚፈልግበት ጊዜ እነርሱ ድነትን ለመቀበል እምቢ በማለታቸው ይበሳጫል ወይንም ድነታቸውን እስኪቀበሉ ድረስ ይጠብቃቸዋል ብሎም አያስተምርም (መዝ 115:3 ፣ ዩሐ 6:44 ፣ ሮሜ 9:16 ፣ ኤፌ 2:8-9) ። በዚህም ምክንያት ወንጌልን “ግብዣ” ብለን መጥራት አንፈልግም።

ጥሪ ከግብዣ የተለየ ነው። ይህም ለእኛ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ያመላክተናል። እርሱ እንደ ንጉስነቱ ሀጥያተኞች በወንጌል እንዲያምኑ እና እንዲታዘዙ ይጠራቸዋል። እንዲሁም አንዳንዶችን በእራሱ ሉዓላዊ ጥሪ ወደ ድነት እንደሚያመጣ ይናገራል። ጠሪው እግዚአብሔር እንደሆነ ስናስታውስ ይህንን መረዳት ከባድ አይሆንብንም ። እርሱ “ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ” ነው (ሮሜ 4:17)።

ይህ ጥሪ የሚነገረው በወንጌል ስብከት ነው። አንዳንዶች እንዲሰሙ ብቻ ሳይሆን ለጥሪው እንዲታዘዙ እና ወደ ድነት እንዲደርሱ የመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ስራ ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል። በመንፈስ ቅዱስ ስራ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚጣራው እግዚአብሔር እንጂ ሰባኪው አይደለም። ሰባኪው መጠቀሚያ እቃ ብቻ ነው። ለዚህም ነው በማያምኑት ላይ ለጥሪው ባለመታዘዛቸው የሚፈረድባቸው። ባለማመናቸው የሚቃወሙት የሰውን ልመና ሳይሆን በአንድያ ልጁ በኩል እየተናገረ ያለውን የህያው እግዚአብሔርን ጥሪ ነው። ይህም ደግሞ እጅግ ዋና ነው።

ሰባኪ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ማቅረብ የሌለበትም ለዚህ ነው። የሚሰሙ ሁሉ ሊሰማ የተገባውን የእግዚአብሔርን ቃል እንጂ የሰባኪውን ስልት ፣ ፊልስፍና ፣ ወይም የፖለቲካ ሀሳቦቹን ወ.ዘ.ተ ሊሰማ አይገባውም። ሰባኪው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጥሪም አላስፈላጊ በሆኑ እና ለማሳመን በሚጠቀምባቸው ቃላቶች እና በልመና እንዳያበላሽ እና የሀጥያተኞችን ፈቃድ የሚጠብቅ አምላክ መሆኑን እንዲያስቡ እንዳያደርግ ሊጠነቀቅ ይገባል። በወንጌሉ ስብከት እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ እምነትን እና የሀጥያተኞችን ንስሃ ይፈልጋል። ታላቁ የምድሩ እና የሰማዩ ዳኛ መታዘዝን ይፈልጋል ፤ አለመታዘዝን ደግሞ ይቀጣዋል። በእንደዚህ አይነት ስብከት ሀጥያተኞች ይድናሉ እግዚአብሔርም ደግሞ ይከብርበታል። ወንጌል ሲሰብክ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ እምነትን እና ንስሀን ከሀጥያተኞች እንደሚፈልግ መታወቅ አለበት ። ሁሉን ቻዩ እና የሰማይ እና የምድር ዳኛ የሆነው እርሱ መታዘዝን የሚፈልግ እና አለመታዘዝን ደግሞ የሚቀጣ ነው። በእንደዚህ አይነት ስብከት ሀጥያተኞች ይድናሉ እግዚአብሔርም ደግሞ ይከብራል።

## የእምነት ባህሪ/ፍሬ ነገር (essence)

ስለ እምነት ስናስብ በተለምዶ እግዚአብሔርን እና ልጁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን የሚል *ክንዋኔን* እናስባለን። እምነት ማመን እና መታመን ነው ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ በፊት አንድ ነገር አለ። ይህም የእምነት ጠሊቁ እውነታ እና ባህሪ/ ፍሬ ነገር ነው እርሱም *ከክርስቶስ ጋር ያለ አንድነት* ነው።

ይህ በሀይድልበርግ የእምነት መግለጫ ተቀምጧል። እውነተኛ እምነት "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር መዳቀል/መጋባት/ መተከል" [6] ከመሆን አንስጻር እንደሆነ ያሳስባል። የዌስትሚኒስተር ትልቁ የእምነት መግለጫ ደግሞ እምነት ለእውነት እና ለወንጌል ተስፋዎች መስማማት ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ መታመን እና እርሱን ለድህነታችን መቀበልም እንደሆነ ይገልጽልናል[7]። ከእምነት ተግባር በተለየ መልክ ይህ ወደ ክርስቶስ መዳቀል(ingrafting) ፣ እርሱን መቀበል እና በእርሱ ማረፍ የሚለው አንዳንድ ጊዜም በሥነ መለኮት "የእምነት ሀይል" ወይም "የእምነት መርህ" ይባላል።

መጽሐፍ ቅዱስ እምነት ከክርስቶስ ጋር ያለ አንድነት እንደሆነ እንደ በዩሐ 17:20-21 ፣ ገላ 2:20 ፣ ኤፌ 3:17 ባሉ ክፍሎች ላይ ያስተምራል። ይህ አንድነትም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እምነት በሚያወራ ጊዜ ሁሉ ሲገለጥ እንመለከታለን። ለምሳሌ በአዲስ ኪዳን የግሪኩ ትርጉም በርካታ አገላለጾችን የሚጠቀም ሲሆን አብዛኞቹ እምነት ከክርስቶስ ጋር ወደሚኖረን ህያው መነካካት እና አንድነት እንደሚያመጣን የሚገልጹ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ “በክርስቶስ” ስለማመን ይናገራል። ታዲያ በእምነት በኩል፣ የአጥንቱ አጥንት፣ የስጋውም ስጋ እንደሆንን ከመናገር ውጪ ምን ማለት እንችላለን (ኤፌ 5:30)? መጽሐፍ ቅዱስም በግሪኩ “ወደ (into)” እርሱ ማመን (ዩሀ 3:16 ፣ 18 ፣ ቆል 2:5) ፣ ወይም እርሱ”ን (on)” ማመን (ሮሜ 9:23, ሮሜ 10:11) ወይንም ደግሞ “በእርሱ (upon)” ላይ ማመን ይለዋል (ሐዋ 11:17, ሐዋ 16:31)።

እነዚህ ክፍሎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ስላለን ቅርብ የሆነ እና ግላዊ አንድነት እና ህብረት ያመለክታሉ። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ በቀላሉ ስለ እምነት የሚናገሩ ክፍሎች ሳይቀር እርሱን እንደምንቀርብ፣ እርሱ ሲናገር መስማት እንደምንችል፣ እንደምናውቀው እና እርሱ የሚለውን ማመን እንደምንችል ይናገራል (ዩሀንስ 14:11, 2ኛ ጢሞ 1:12) ። ይህ የእውነተኛ እምነት ባህሪ ነው።

ታዲያ ይህ እውነተኛ እምነትን ከመሳዮቹ የምንለይበት መንገድ ነው። በብዙ መንገድ የውሸት እምነቶች እውነተኛ እምነትን ለመምሰል ይሞክራሉ ነገር ግን አንድ ተመሳስሎ መሰራት የማይችል ነገር አለ እርሱም ደግሞ በእምነት *በክርስቶስ* መሆን ነው።

እምነትን ከክርስቶስ ጋር ያለ አንድነት እንደሆነ መረዳት *ከ*እግዚአብሔር የ*ተሰጠ* ስጦታ እንደሆነ መረዳት ነው። እምነትን *ክንዋኔ* ብቻ አድርገን የተነጋገርን እንደሆነ እምነት ከእኛ የሚመነጭ እንደሆነ ልናስብ ነው፤ ነገር ግን እምነት በመጅመሪያ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን እንደሆነ ስንረዳ በግልጽ የእግዚአብሔር ስራ እና ስጦታ እንደሆነ እነረዳለን ። ቅርንጫፍ እራሱን ወደ ግንዱ ማዳቀል እንደማይችለው ሁሉ እኛስ ከክርስቶስ ጋር እራሳችንን አንድ ማድረግ እንችላለን?

እምነትን በዚህ መልኩ መረዳት ብዙ ነገሮችን እንድነረዳ ያደርገናል። እንዴት የክርስቶስ ኢየሱስ ጽድቅ *በእምነት በኩል* እንዴት የእኛ መጽደቅ እንደሚሆን ያብራራልናል። ይህ መረዳት እምነት አለምን የሚያሸንፍ ድል ነሺ እንዴት እንደሆነ ያስረዳናል። እንዲሁ የወረስነው ኃይል ስለሆነ ሳይሆን እምነት በክርስቶስ ውስጥ ስለሚጨምረን እና ሀጥያትን፣ ሞትን፣ አለምን እና ሰይጣንን አሸንፏን ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለሚያደርገን ነው።

ታዲያ እምነት አለን ማለት መቻል እንዴት ግሩም ነው። ይህንን ማለት በእግዚአብሔር አስገራሚ እና ሉዓላዊ ስራ ማመን እና በክርስቶስ እንደምንኖር እርሱም ደግሞ በእኛ እንደሚኖር፤ እርስ በእርስ ደግሞ ለዘላለም የማንለያይ መሆናችንን እናውቃለን።

## እምነት እና እውቀት

ስለእምነት ክንዋኔ ስንነጋገር እምነት *ማወቅን* እንደሚያካትት እናምናለን። ሁልጊዜም እምነትን እና እውቀትን ለመለያየት የሚፈልጉ እና እምነትን “በእውር” መቀበል ወይም መታመን አድርገው የሚቀበሉ ሰዎች አሉ። ይህ በተለይም ደግሞ በዚህ ዘመን የተለመደ እሳቤ ነው።

የሮማን ካቶሊክ አስተምህሮ ሁልጊዜ እምነትን እና እውቀት መለያየት እንደሚቻል ያስተምራሉ በተለይም ደግሞ ጥያቄ የሌለበት እምነት (እምነት ያለ ውስጣዊ እውቀት) አስተምህሮዋቸው ውስጥ ይህንን እንመለከታለን ። በሮማን ቤተክርስቲያን መሰረት የተራ ሰዎች ወይንም ያልተማሩ ሰዎች እምነት ነው።

የካርዝማቲክ፣ ጸረ-አስተምሮአዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሞደርኒዝም እና ኒዮ-ኦርቶዶክሲም ይህንን ያስተምራሉ ። እምነት እውቀትን የሚያካትት እንደሆነ የሚክዱ ሳይሆኑ እምነትን እና እውቀትን በመለያየት እና ዶክትሪን ወይንም አስተምህሮን በመናቅ ይናገራሉ።

በሚያሳዝን ሁኔታ ደግሞ እንደዚህ አይነት ዝንባሌ በአንዳንድ የተሓድሶ ሥነ-መለኮት አጥኚዎች እና አስተማሪዎችም ላይም ይስተዋላል። እነርሱም እምነት እውቀት እንደሆነ በግልጽ አይክዱም ነገር ግን በሥነ መለኮታቸው ተቃርኖ ያላቸው ነገሮች እና መጣረሶችን ሲያስተምሩ እንመለክታለን።

እነዚህ እግዚአብሔር በወንጌል ውስጥ ሁሉንም ሰው ይወድዳል ነገር ግን በመምረጥ ውስጥ ሁሉንም ሰው አይወድም የሚሉ ሰዎች ናቸው። ይህም በተገለጠው ፈቃድ መሰረት ሁሉንም ማዳን እንደሚፈልግ ነገር ግን ሁሉንም ሰው በእርሱ ሚስጥራዊ ፈቃድ መሰረት ማዳን እንደማይፈልግ እና ለሁሉም ድህነትን እንደሚያቀርብ ነገር ግን ለሁሉም ደግሞ እምነትን እንደማይሰጥ የሚናገሩ ሰዎች ናቸው። እንደዚህ አይነት ንግግር እወቀትን የሚጻረር እና መሠረተ ቢስ ነው። ማንም ሰው እንደዚህ አይነት ተቃርኖን *ሊረዳ* አይችልም። እነርሱ ሊቀበሉ የሚችሉት እንደዚሁ ግልጽ ባልሆነ መንገድ እምነት የእውር ዝላይ እንጂ የእውቀት ጉዳይ አይደለም የሚለውን ነው!

ይህ የእውቀት እና የአስተምህሮ *ታቃራኒ* የሆነ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስም ተቃራኒ ነው። በዩሐ 17:3 ኢየሱስ አዳኙን እምነት ክርስቶስን እግዚአብሔር እንደላከው “ማወቅ” ብሎ ይተረጉመዋል። ኢየሱስ ይህንን እውቀት በደፈናው ማመን ሳይሆን በማወቅ ማመን የዘላለም ህይወት ነው ብሎታል።

በ2ኛ ጢሞቲዎስ 1:12 ጳውሎስ ስለእራሱ እምነት “ተረድቻለሁኝ” ብሎ ይናገራል። ነገር ግን ይህንን የሚለው ያመነውን መጀመሪያ ስላወቀ ነው። በእርግጥም ክርስቶስ ኢየሱስን በስጋ እንደመጣ ፣ ለሀጥያታችን በመስቀል ተሰቃይቶ እንደሞተ እና እንደ እግዚአብሔር አንድያ ልጅነቱ ካላወቅነው እርሱን በመረዳት የሚያደርሰውን እምነት ማግኘት ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነው።

ስለዚህም እውቀትን ልንጠላ አይገባም። እውቀት በእራሱ ጥቅም ስለሌለው እምነት ሊኖረው ይገባል። ሆነም ቀረ መጽሐፍ ቅዱስ እውቀት መልካም ነገር እንደሆነ ይናገራል። በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6-7 “በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ” የእኛ ሀብት እንደሆነ ተጠቅሷል (ሉቃ 1:77, ኤፌ 1:17, ኤፈ 4:13, ፊሊ 3:8, ቆላ 2:3, 2ኛ ጴጥ 1:2-3)። *ባለማወቅ* ውስጥም ድፍረት አይኖርም።

እምነት ያለ እውቀት ወደ ጨለማ መዝለል ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ አይኖርም። በብርሀን ውስጥ ይኖራል። እንደዚሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን በጨለማ ውስጥ የእምነት ዝላይ እንደመዝለል አይደለም። እርሱን ማመን የግድ ወደ ብርሃን የምንመጣበት የአለም ብርሃን ነው። ይህም ብርሀን በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት ላይ ያለ የእግዚአብሔር ክብር የእውቀት ብርሀን ነው(2ኛ ቆሮ 4:6)።

## እምነት እና መታመን

በመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ከተገለጠባቸው የተለያዩ መንገዶች ውስጥ የመዳን እምነት ብዙ “ተግባሮችን” እንደሚያካትት ግልጽ ነው። በእነዚህ አገላለጾች ውስጥ በእርግጠኛነት ለአማኞች እምነት በተሰጣቸው እና በተለማመዱት ቁጥር የእምነት መጎልበት እና ማደግ እንደሚኖር እርግጥ ነው። ሉቃስ 17:5 ለምሳሌ “ሐዋርያትም ጌታን እምነት ጨምርልን አሉት” ይላል።

ክርስቶስ የእምነት መጀመሪያ ቢሆንም እምነት እርሱን መመልከት (ኢሳ 45:22) ፣ ወደ እርሱ መቅረብ (ማቲ 11:28) ፣ ወደ እርሱ እንደመጠጊያ መሸሽ (ዕብ 6:18) ፣ ከእርሱ መቀበል (ዩሀንስ 1:12) ፣ እርሱን መልበስ (ሮሜ 13:14) እና እራስን አሳልፎ ለእርሱ መስጠት (2ኛ ቆሮ 8:5) ሁሉ ያካትታል።

እነዚህ ሁሉ የአዳኙን እምነት ሁለተኛ ክንዋኔ እርሱም ክርስቶስን ስለ *መታመን* ይገልጻሉ። አስቀድመን አንዱ የሚያድን እምነት ተግባር መርህ እውቀት እንደሆነ ተናግረናል። መታመን ደግሞ ሁለተኛው ነው። እነዚህ

ሁለት የአዳኝ እምነት ክፍሎች በአንድነት 2ኛ ጢሞቴዎስ 1:12 ላይ “*ያመንሁትን አውቃለሁና፥* የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል *ተረድቼአለሁ*” በማለት ተጠቅሰዋል። ይህ ክፍል እንደሚናገረው መታመን ወይም መርዳት (ሀሳብን መቀየር - የኢንጊሊዘኛው ቃል ቀጥተኛ ትርጓሜ/ persuaded) በእውቀት ላይ የተመሰረተ ነው። ስለዚህ መረዳት/ ሀሳብን መሻር የሚለው ቃል ለዚህ አትኩሮትን ይሰጣል። አንድ ሰው በእውነታ ፣ በምክኒያታዊ እና በትክክለኛ ክርክሮች ሁሉ ሊያምን/ሊረዳ/ሀሳቡን ሊሽር ይችላልና።

ካላወቅን መታመን ወይም መረዳት አንችልም። እግዚአብሔር እራሱ በስጋ መገለጡን (1ኛ ጢሞ 3:16) ፣ ህይወቱን ለብዙዎች ካሳ አድርጎ መስጠቱን (ማቴ 20:28) ካላወቅን ልንታመንበት አንችልም።

ይህ የሚያድን እምነት ሁለተኛው ክፍል *የሆነው* በክርስቶስ *መታመን* የእምነት ግላዊ ባህሪ ላይ አትኩሮት ያደርጋል። ይህ መታመን የእምነትን እውቀት “ስለአንድ ነገር ማወቅ” የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን የእውነት እግዚአብሔር እርሱን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል መግለጡን መረዳትም ነው።

ያለዚህ የመታመን ተግባር በሚያድን እምነት እና በአጋንንት “እምነት” መካከል ምንም ልዩነት አይኖርም ምክንያቱም አጋንንቶችም አንድ አምላክ እንዳለ “ያምናሉ” ደግሞም ይንቀጠቀጡለታልና (ያዕ 2:19)። በዚህ መንገድ የሚያምኑ አጋንንቶች ብቻ አይደሉም። አብዛኞች የዚህን ቃል እውነት የተረዱ እና ምንም ተቃርኖ የላቸውም ነገር ግን እግዚአብሔርን ወይንም ክርስቶስን አልታመኑትም።

የአዳኙ እምነት ተግባር በሆነው መታመን ሰዎች የቃሉን እውነታነት መመልከት ብቻ ሳይሆን ለግላቸው እውነት መሆኑን እንዲረዱ ይረዳቸዋል። ስለዚህም እምነት አንድ ሰው እራሱን ለክርስቶስ በመስጠት ወይም በእርሱ በማረፍ ሊገለጽ ይችላል (ማቴ 11:28) ። ይህ ሙሉ በሙሉ እራስን መካድ እና ነፍስን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና ጸጋ ለእርሱ አሳልፎ መስጠትን ያካትታል።

አንዳንዶች ደግሞ እምነትን ከእውቀት እና ከአእምሮ ሀሳብ አንጻር ብቻ ለማስረዳት የሚፈልጉ ናቸው። እኛም በአሁኑ ጊዜ በተንሰራፋው እና እውነተኛውን አስተምህሮ የሚቃወመውን በ”ስሜት” ተደግፎ ማመንን አንቀበልም ነገር ግን እውቀት ላይ የተመሰረተ እምነት አስፈላጊነት ላይ አጽኖት ልንሰጥ እንወዳለን። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን በመመስረት፣ እምነትን በአእምሮ ክንዋኔ ብቻ ማስተማር በቂ ነው ብለን አናምንም። ይህም ደግሞ ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 1:12 አንድ ሰው እራሱን ወደ ክርስቶስ የሚያስገዛበት

እና ሰላምን እና እረፍትን በእርሱ በኩል የሚያገኝበት መንገድ እንደሆነ ይናገራል። ያለእዚህም እኛ ምንም ነን ደግሞም አንዳች ነገር ሊኖረን አይችልም።

**መጽደቅ**

መጽደቅ ምንድነው? በሚያሳዝን ሁኔታ የቃሉ ትርጉም ምን እንደሆነ የሚያውቁ እና መጽደቅ የክርስትና አንዱ አስፈላጊ አስተምህሮ እንደሆነ በማወቅ የመጽደቅን ብሩክነት የተረዱ እጅግ ጥቂቶች ናቸው።

መጽደቅ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት በመጀመሪያ ተመሳሳዩን የሆነውን *ጽድቅ* ምን እንደሆነ መረዳት አለብን። መጽደቅ እና ጻድቅነት አንዳይነት ናቸው።

ሁለትኛ መጽደቅ የህግ ንግግር እንደሆነ መረዳት አለብን። መጽደቃችን እግዚአብሔር ዳኛ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው (ዕብ 4:13) ። መጽደቅ ፍርዱ ይግባኝ የሌለበት የከፍተኛ ዳኛ *ፍርድ* ነው (ኢዮብ 40:8) ።

ሦስተኛ መጽደቅ የእኛን *ህጋዊ ሁናቴ* (ስፍራችንን) የሚያጠቃልል ነው። ይህም ደግሞ በህጉ እና በእግዚአብሔር ፊት ያለንን ቦታ ያመላክታል (መዝ 130:3) ። ይህ ህጋዊ ሁናቴያችን ደግሞ አንዳንድ ትክክል የሆኑ ነገሮችን መረዳት እንደምንችል ወይንም ደግሞ በዚህ ምክኒያት እንደምንቀጣ የሚወስን ነው።

ከዳኛ ፍርድ ሲተላለፍ ነጻ ወይንም ጥፋተኛ የሚል ሁለት የተለያዩ ፍርዶች ብቻ ነው ያሉት። በሀጥያተኞች መጽደቅ ውስጥ እግዚአብሔር ሀጥያተኞችን ከምንም አይነት የተሰሳሰተ ተግባር ወይም ወንጀል የመስራት ክስ ነጻ እንደሆኑ ነው የሚናገረው (ዘኊል 23:21, 2ኛ ቆሮ 5:19) ።

የመጽደቅ አስገራሚነት *ሀጥያተኞች* በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ሆነው መገኘታቸው ነው። የጻደቁ ሁሉ ሀጥያትን ሰርተዋል ደግሞም እነዚህ ሁሉ ሀጥያትን የሰሩት በዳኛው/በፈራጁ ላይ ነው (መዝ 51:4, ሮሜ 5:18, 21)።

እግዚአብሔር እነርሱን ጻድቅ የሚያደርገው እንደ ሜዶን እና ፋርስ ህግ በሆነ ህግ ነው። ፍርዱ መቼም ሊለወጥ አይችልም ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊለወጥ አይችልምና ነው። ደግሞም እግዚአብሔር ፍርድን ሲያስተላልፍ አይዋሽም (ዘኊ 23:29) የእርሱ ፍርድ ሁልጊዜም ትክክል እና እውነተኛ ነው።

ይህም ማለት ሀጥያተኛ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ እና ሀጥያት የሌለበት ለመሆን በእግዚአብሔር ፊት በስራው ስራ ሊቀርብ አይችልም ማለት ነው (ሮሜ 3፡38, ሮሜ 4:6) ። መጽደቅ ምክንያት ሊኖረው ግድ እንደመሆኑ ይህ ምክኒያት የክርስቶስ ኢየሱስ በመከራ እና እስከሞት ድረስ ፍጹም መታዘዝ ነው።

ክርስቶስ አብ ለሰጠው ሰዎች እንደ ምትክ ይቆማል። የእርሱ መከራ እና ሞት ለሀጥያታቸው ሁሉ የሆነ ቅጣት ነው (ኢሳ 52:5) ። በእርሱ ፍጹም መታዘዝ የእኛን ክፍያ እርሱ መለሰልን/ከፈለልን "በዚያን ጊዜ ያልቀማውን መለስኩ" (መዝ 69:4) ።

በመቀጣት ብቻ ሳይሆን ለሰረቀው በመተካትም ስለሀጥያቱ ሊያስተሰርይ ያለን ሌባ አስቡ። ክርስቶስ ለሀጥያታችን መቀጣት ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር እኛ ያልከፈልነውን አክብሮት እርሱ በመታዘዝ ሁሉ ከፍሎ መልሷል።

ክርስቶስ ይህንን ሁሉ የሚያደርገው ለእራሱ ለሆኑት ነው። የእርሱ መታዘዝ፣ መከራ፣ ሞት ሁሉ የሚገባው ወደ እነርሱ ሂሳብ ቁጥር ነው። ወይንም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ "ይቆጠርላቸዋል" ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው (2ኛ ቆሮ 5:19) ። በዚህም በእግዚአብሔር ፊት ሀጥያትን እንዳልሰሩ እና ምንም እንዳላደረጉ ይቆጠራሉ።

ታዲያ መጽደቅ እንዴት አስደናቂ ጉዳይ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ለሆንን ለእኛ ምንም "ኩነኔ እንደሌለብን" ከማወቅ ጋር ምን ይወዳደራል? በረከት ሁሉ ፣ መልካም መብት እና በእነዚህም መደሰት ሁሉ እዚህ ላይ የተመሰረተ ነው። ጳውሎስም እንዳለው "አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤" (ፊሊ 3:8-9)።

## በእምነት መጽደቅ

መጽሐፍ ቅዱስ በእምነት ስለመጽደቅ ሲናገር ብዙ እጅግ ወሳኝ እውነታዎችን ያስተምራል።

በእምነት መጽደቅ ሀጥያተኛ እንዴት በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅ እንደሚችል ያስረዳናል ። ይህ እግዚአብሔር እንደዳኝነቱ የመጽደቅን ፍርድ ለሀጥያተኛው እንዴት እንደሚፈርድ እና ይህም ሀጥያተኛ ከጥፋተኝነት ወደ ንጽሕና እንዴት እንደሚሸጋገር ያብራራልናል።

በእምነት ስንጸድቅ እምነታችን እንደ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርልናል (ዘፍ 15:6 ፣ ሮሜ 4:5) ። እግዚአብሔርም እንደ ዳኛነቱ እምነታችንን እንደ መጽደቃችን ወይንም ጥፋት የለሽነት ይቆጥረዋል።

ነገር ግን ይህንን የሚያደርገው እምነት በእራሱ በቂ ስለሆነ ወይንም እምነት እና የእምነት መታዘዝ ለህጉ የፍጹም መታዘዝ ምትክ መሆን ስለሚችሉ አይደለም። ይልቁን እምነት እንደ ጽድቅ የሚቆጠረው በእራሱ ባህሪ ምክንያት ነው። አስቀድመን እንደተመለከትነው እምነት *ከክርስቶስ ጋር አንድ* በመሆን የሚመጣ መሆኑ ጠሊቅ እውነታ ነው። በዚህም በእምነት እንዴት እንደምንጸድቅ እንረዳለን። እምነት እንደ ጽድቃችን የሚቆጠረው የስራ ምትክ ወይም በእራሱ በቂ የሆነ ነገር ስለሆነ ሳይሆን ነገር ግን ከክርስቶስ እና ከፍጹም ጽድቁ ጋር ስለሚያገናኘን ነው።

ስለዚህም የጸደቅነው *በእምነት* የእኛ በሆነው በክርስቶስ ጽድቅ ፣ መታዘዝ ፣ ቅድስና ፣ እና ስራ ሁሉ ነው። ደግሞም በእምነት በኩል ብቻ እንጸድቃለን። ከእምነት በስተቀረ ክርስቶስ እና ጽድቁን ሊሸከም የሚችል አንድም የለም። ከክርስቶስም ጽድቅ በቀር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አናገኝም።

እንዲሁም ደግሞ እምነት ሌላ ስራ አይደለም። በእምነት መጽደቅ ማለት አንዳንዶች እንደሚያስቡት እግዚአብሔር እንደ ዳኛነቱ ህግን ሁሉ ፍጽሙ ከማለቱ ይልቅ ለእኛ አንድን ስራ ብቻ ሰጥቶናል እርሱም እምነት ነው ማለት አይደለም።

እምነት እኛ የምናመጣው ፣ ብዙዎችም እንደሚያስተምሩት እኛ የምናፈራው አልያም ከእኛ የሚመነጭ አይደለም።ማመንም ሀጥያተኞች የሚወስኑት ውሳኔ አይደለም። ሀጥያተኛ በሀጥያቱ እስከጠፋ ድረስ ይህንን መሰል ውሳኔን ሊወስን አይችልም። የጸደቅንበት እምነት እርሱ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና። ለመዳን የሚያስፈልገንን ጽድቅ ብቻ ሳይሆን ጽድቁ የእኛ መሆን የሚችልበትን መንገድ እርሱ አዘጋጅቷል።

ስለዚህም መጽደቃችን ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ስራ ነው። ከእርሱ ዘንድ ለመጽደቃችን የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ይሰጠናል። እኛን የሚያጸድቀን ጽድቅ ፣ ጽድቃችንን የሚሰጠን ሰው እና ይህንን ጽድቅ የምንቀበልበትም መንገድ ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

ስለዚህ መጽደቅ *በእምነት ነው* ካልን *በስራ አይደለም* ማለት ነው። እኛ መልካም ስራ እንድንሰራ ተጠርተናል ደግሞም ተወስኖልናል (ኤፌ 2:10) ፤ ነገር ግን ይህንን የምናደርገው ላገኘነው መዳን እንደ ማረጋገጫ እና ማመስገኛ ነው እንጂ ድነት እንዲገባን ወይም ድነትን የምናገኝበት መንገድ አይደለም። ስራችን

በእግዚአብሔር ፊት ከመቅረባችን ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። የክርስቶስ ስራ ብቻ የእኛን በእግዚአብሔር ፊት መቆም እና መጽደቅ ይወስናል።

መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚለው "ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል" (ሮሜ 3:17)። "ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም (ጽድቃችንንም ጨምሮ) ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን" (ሮሜ 11:26 የተሰመረበት የተጨመረ ነው)። ነጻ እና በጸጋው የሆነ ጽድቅ በእምነት ስጦታ በኩል ተሰጥቶናል። እንዴት ያለ በረከት ነው! የማይገባቸውን ሀጥያተኞችም የሚያጸድቅ ጌታ እንዴት ያለ ባለጸጋ ነው።

## መጽደቅ እና መመረጥ

እኛ የእግዚአብሔር ህዝቦች ሙሉ በሙሉ እና በእርግጥም ከዘላለም በፊት (ምድር ከመመስረቷ በፊት) መጽደቃቸውን አናምንም ነገር ግን በመጽደቃቸው እና በመመረጣቸው ውስጥ የጠለቀ ግንኙነት መኖሩን እናምናለን። የእግዚአብሔር ህዝቦች *በእምነት* ይጸድቃሉ እንጂ *በመመረጣቸው* አይጸድቁም። ነገር ግን መጽደቃቸው ከመመረጣቸው ጋር ሊለያይ አይችልም።

በመጀመርያ ህዝቡን የራሱ እንዲሆኑ በመምረጡ እግዚአብሔር እነርሱን እና እነርሱን ብቻ *ለማጽደቅ ወስኗል።* የጽድቃቸው ውሳኔ የሆነውን ይህም ደግሞ *ያለነቀፋ* እና *ቅዱሳን* እንዲሆኑ ወስኗል (ኤፌ 1:4)።

ሁለተኛ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር ምክንያት በክርስቶስ ተመርጠዋልና እግዚአብሔር እነርሱን ሲመለከታቸው እና ለዘላለም ሲያያቸው የጸደቁ እና ጥፋት እንደሌለባቸው አድርጎ ነው። እርሱም

አስቀድሞ ያለሀጥያት ተመልክቷቸዋልና በዚህም እግዚአብሔር ፍቅሩን በእነርሱ ላይ ያኖራል። እነርሱን ለክርስቶስ ለዘላለም ሲሰጣቸው እግዚአብሔር ለዘላለም ያለሀጥያት አድርጎ ተመልክቷቸው ነው።

በተለይ በዚህ ቦታ ዘኁ 23:21 እጅግ አስፈላጊ ነው። "በያዕቆብ ላይ ክፉትን አልተመለከተም" ሲል የሚጠቀመው ቃል ስለ ትላንት የሚያወራ ግስ እንደሆነ አስተውሉ ። በተመሳሳይ ስለትላንት እንደሚያወራ የሚያለክት ክፍል በሮሜ 9:13 ላይ "ያዕቆብን ወደድኩ"ሲል እንመለከታለን። ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ አዋጅ (ውሳኔ) የሚያወራውን ይህ አገላለጽ ሁል ጊዜም በሉዓላዊ ጸጋ የሚያምኑ ሰዎች ይረዱታል።

ዘኁልቁ 23:21 የእግዚአብሔርን ህዝብ ለመርገም ለሞከሩት ለባላቅ እና ለበላዓም መልስ ይሰጣል። ክርስቶስ ገና ሳይመጣ እና የማስተሰርያ ደም ሳይፈስ የእግዚአብሔር ህዝቦች እርሱ በዘላለም ውስጥ በወሰነው ውሳኔ ምክንያት መርገም ሊሆንባቸው አይችልም።

ስለዚህም ስለ "ዘላለማዊ መጽደቅ" ወይም ደግሞ "ከዘላለም ጀምሮ ስለመጽደቅ" ልናወራ የምንወደው በዚህ አውድ ብቻ ነው። የመጽደቅ ዘላለማዊ ታሪካዊ ዳራ ላይ ትኩረት መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነውና።

መጽደቅን ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመምረጥ ውሳኔ ጋር መለያየት፣ ማንም ሰው ካመነ መጽደቅ ለሁሉም የተሰጠ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እንድነደርስ ያደርገናል። ይህ በአንድ ጎኑ ሀጥያተኛው ለወንጌል ባለው ምላሽ ላይ የተደገፈ እና ቅድመ ሁኔታ ያለው ጽድቅ ይሆንብናል ማለት ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርው በነጻ የሆነ እና በጸጋ የተሞላ መጽደቅ አይደለም።

ስለዚህ ከምርጫ ድንጋጌ አንጻር ፣ መጽደቅ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት በኩል ለተመረጡት እና ለእነርሱ ብቻ ነው። በተመሳሳይ በመመረጥ ድንጋጌ መሰረት መጽደቅ የራሳቸው እንዲሆን ለእነርሱ ብቻ የእምነት ስጦታ ተሰጥቷቸዋል።

ላልተመረጡት መጽደቅም ሆነ ጽድቅ መቼም ሊኖር አይችልም። ለእነርሱ ምንም አይነት ምህረት የለም። በእግዚአብሔር ድንጋጌ ወይም በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ላይ ያልተፈጸመ ስራ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እውነተኛነትን እና የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ባህሪን ሳይደመስስ ለእነርሱ ሊሰጥ አይችልም።

በመመረጥ እና በመጽደቅ መካከል ያለ እንደዚህ አይነት ጥብቅ ግንኙነት በመኖሩም መመረጣችንን በመጽደቃችን በኩል እናውቀዋለን። በእምነት በኩል ስለ ሀጥያታችንን ይቅር መባላችንን መለማመድ/ማወቅ

“በያዕቆብ ላይ ክፋትን አልተመለከተም፥በእስራኤልም ጠማምነትን” ባላየው በእርሱ ምህረትን እንደተቀበልን እናውቃለን (ዘኍል 23:21) ።

ህዝቡን በሉዓልዊነቱ ለሚያጸድቀው ለስሙ ክብር ይሁንለት።

## መጽደቅ እና ስርየት

ከላይ እንደተመለከትነው መጽደቅ ከመመረጥ ወይንም ከመስቀሉ ሊፋታ አይችልም። በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ላይ በተሰራው ማስተሰረያ ላይ በመመስረት መጽደቅ ከዘላለም በፊት የተወሰነውን ውሳኔ ይሰማል።

ይህ እጅፍ ዋና ጉዳይ ነው። በእግዚአብሔር ያልተደነገገ ነገር በጊዜ ውስጥ ሊፈጸም አይችልም፣ ያልተመረጡት ሰዎች መጽደቅ አንድ ምሳሌ ነው። በመስቀሉ ላይ፣ በክርስቶስ ሞት ያልተገዛ ወይም ያልተገኘ ጉዳይ ለሁሉም ሰው ሊሰጥ አይችልም።

ስለዚህም ላልተመረጡት የሚቀርብ መጽደቅ የሚባል (ቅድስናም ወይም ምህረትም) የለም ። የእግዚአብሔርም ጽድቅ ለሁሉም ሊታወጅ ስለሚገባው ወንጌሉ ለሁሉም ሊሰበክ ይገባል (ሮሜ 3:25-26) ። የሚሰሙትም ሁሉ ለሚያምኑ በእግዚአብሄር ፊት እንደሚጸድቁ እርግጠኛ በሆነ ተስፋ በእምነት ሊጠሩ ይገባል። ነገር ግን ይህ ተስፋ በጊዜ ውስጥ ግልጽ የሚሆነው ክርስቶስ ለሞተላቸው እና እግዚአብሔር ለመረጣቸው ብቻ ነው። ስለዚህም የመጽደቅ ተስፋ ለተመረጡት እና እግዚአብሔርም በምሕረቱ ለጽድቅ የሚሆንን እምነት ለሰጣቸው ብቻ የሚፈጸም ይሆናል (ኢፌ 2:8-9)።

ክርስቶስ ለተመረጡት ብቻ ሞቷል የሚለው አስተምህሮ የተገደበ ስርየት የሚለው አስተምህሮ ነው። ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽ ሆኖ እናገኘዋለን። የክርስቶስ ኢየሱስ መሞት በእግዚአብሔር ለተመረጡት መጽደቅን ያሰጣቸዋል (ኢሳ 53:11, ሮሜ 3:24, ሮሜ 5:9,19)። ይህንንም የሚያደርገው ክርስቶስ በመከራው እና በሞቱ የእነርሱን አለመታዘዝ በእርሱን ፍጹም መታዘዝ ስለተካ እና ለእነርሱ ጥፋት ስለተቀጣ ነው።

በዚህ መልኩ ክርስቶስ ዳኛ በሆነው በእግዚአብሔር፣ ተቀባይነት ያለው ፍጹም የሆነ ጽድቅ (ያለጥፋት መሆንን) አስገኝቶላቸዋል። ይህ ጽድቅ በእምነት በኩል የእነርሱ ይሆናል፤ እንዲሁም ደግሞ ጥፋተኝነታቸው

ተነስቶ እንደገና የእግዚአብሔርን ስጦታ እና መገኘት ተቀብለዋል። ስለዚህ የክርስቶስ ስራ የመጽደቃቸው መሰረት ነው።

እንዲሁ ስናስበውም የክርስቶስ ሞት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መጽደቅ እንደሆነ መናገር እንችላለን (ሮሜ 5:19)። በሞቱ ከእግዚአብሔር የለያያቸውን ነገር ሁሉ ከመንገዳቸው ተጠርጎ  እግዚአብሔር የሚቀበለው እና የፈቀደው ጽድቅ ተሰጥቷቸዋል (ኢሳ 53:11)።

ስለዚህም ክርስቶስ የተቀበለው ወይንም ያገኘው አጠቃላይ የሆነን ጽድቅ ሳይሆን ለተመረጡ እና ለተወሰነላቸው ሰዎች ብቻ የሚሆንን ጽድቅ ነው። ይህ ለእነርሱ የተሰጠ ጽድቅ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በከፈለው ዋጋ የተገኘ ነው። ከዚህም ውጪ ሌላ ጽድቅ የለም (ሮሜ 10:14)።

ሉዓላዊ ፣ ጸጋ የተሞላ፣ የተወሰነ ምርጫ እና የተወሰነ ስርየት በአንድነት የዋነኛውን መጽደቅ እርሱም በእምነት በኩል አብ ለክርስቶስ ለሰጣቸው ሁሉ የተረጋገጠ ነው። በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ለሁሉም የሚሰጥ ጽድቅ  ከመስቀሉ እና ከመመረጥ የራቀ ወይም የተፋታ እና ማንንም ሊያጸድቅ የማይችል ነው።

## ጉዲፈቻ/ አዶፕሽን

ብዙውን ጊዜ ጉዲፈቻ በድነት ቅደም ተከተል ውስጥ አይጠቃለልም። ለዚህም ምክንያቱ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዲፈቻ ወይንም ስለ አዶፕሽን ስለማይናገር ሳይሆን ልጅነት ወይንም ጉዲፈቻ የመጽደቅ ጥቅም በመሆኑ ነው። ልጅነት በመጽደቅ ውስጥ ተጠቃልሏል ብለን እንረዳለን ማለት ነው።

በእርግጥም ጉዲፈቻ ወይንም ልጅነት የመጀመሪያው እና ትልቁ የመጽደቅ ጥቅም ነው። ሀጥያታችን በነጻ ይቅር በመባሉ እና በክርስቶስ ጻድቅ በመሆናችን እግዚአብሔርም እኛን እንዲሁ መቀበል ብቻ ሳይሆን እንደ እርሱ ውድ ልጆች ተቀብሎናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ስለ ጉዲፈቻነት ወይንም ልጅነት ሲያወራ እኛ በእግዚአብሔር ጸጋ ልጅ ስለመሆናችን እና እርሱም ደግሞ አባታችን የመሆኑን እውነታ ይናገራል። ስለዚህም ስለጉዲፈቻ/ ልጅነት ርዕስ አንስተን ማውራታችን አግባብነት የሌለው አይሆንብንም።

ጉዲፈቻ ወይንም ልጅነት እንደ መጽድቅ የተለያዩ ቅድመ ተከተሎች አሉት። መነሻውን ከዘላለማዊው ምክር አድርጎ በአዲሱ ሰማይ ምድር ፍጻሜውን ያገኛል። እነዚህም ቅደም ተከተሎች እንደሚከትሉት ናቸው።

የመጀመሪያው እግዚአብሔር ፍቅሩን በእኛ ላይ በማኖር ከዘላለምም በፊት የእርሱ ልጆች እንድንሆን መረጠን (ሮሜ 8:29, ኤፌ 1:5)። አስታውሱ እግዚአብሔር የመረጠን የእርሱ ልጆች ለመሆን የተገባን ስለሆንን ወይም ስለምንሆን ሳይሆን  እንዲሁ ልጆቹ እንድንሆን በመፈለጉ ብቻ ነው።  እኛ ልጆቹ እንድንሆን አስቀድሞ ወስኗል።

ሁለትኛው በክርስቶስ መከራ እና ሞት በኩል የአባትነት ፍቅሩ ለማይገባን እና በቤቱ ለመገኘት ምንም አይነት ህጋዊ መሰረት ለሌለን ለእኛ እግዚአብሔር ልጅ እንሆነው ዘንድ የሚያስፈልገውን መሰረታዊ ነገር ሁሉ አቅርቦልናል (ገላ 4:4-5 ፣ ኤፌ 2:13)። ይህ የልጅነት ወረቀታችን የተጻፈው እና የታተመው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ነው ብለን ማሰብ እንችላለን።

ሦስተኛ፣ በእግዚአብሔር ህብረት እና ቤተሰብ ውስጥ መግባት የቻልነው በመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው፤ እርሱም በሰራው ስራ የእግዚአብሔርን ፍቅር እና እንክብካቤ መቅመስ/ማወቅ ችለናል (ገላ 4:6-7)። ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት ስንነጋገር ዩሀንስ 14:18 በቀጥታ “ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ” ይለናል።

ስለዚህም በልጅነታችን ተግባር ውስጥ እግዚአብሔር ከምድራዊው ልጆችን የመቀበል/ የጉዲፈቻ ስራ ያለፈ ነገርን አደረገ። እግዚአብሔር በምድራዊው የማደጎ ሁኔታ ፈጽሞ እውነት ሊሆን በማይችል በልኩ በመንፈስ ቅዱስ በኩል እኛ የእርሱን መልክ ይዘን እርሱን እንመስል ዘንድ እንደገና እንድንወለድ አደረገ  (ኤፌ 4:24 ፣ 1ዩሐ 3:1-2)።

አራተኛ “ምንም እንደምንሆን ገና ስላልተገለጠ” (1ኛ ዩሐ3:2) መጽሐፍ ቅዱስ “የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ” ብሎ የሚጠራው የፍርድ ቀን አለ (ሮሜ 8:19)። በዚህም ቀን ፍጥረት ሁሉ በክርስቶስ ምን እንደምንመስል ይመለከታል ፤ በዘላለም ቤታችንም ከአባታችን ጋር ለዘላለም ልንኖር እንወሰዳለን። በዚያ ቀን አሁን ካለው ከሀጥያት ባርነት እና ኃይል ተላቀን ስጋችንም ወደ ልጅ ስጋ ይቀየራል (ቁጥ 23)። ይህንንም ቀን እንጠብቃለን።

ለዘላለም አስቀድሞ መወሰን ፣ በክርስቶስ መዘጋጀት ፣ በመንፈስ ቁጥጥር ውስጥ መሆን እና በዘላለም ውስጥ ፍጹም መሆን፣ እግዚአብሔር እኛን ልጆቹ ያደረገበት ተግባራት ምነኛ የሚያስገርሙ እና የሚያስደንቁ ናቸው። ዩሀንስ ካለው ጋር እኛም እንስማማለን “የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ” (1ኛ ዩሀንስ 3:1)።

## ሰላም

የምንኖርበት እግዚአብሔራዊ ያልሆነ አለም በመካከለኛው ምስራቅ ሰላም ይሁን ፣ ጦርነት ባለበት ስፍራ ሁሉ ሰላም ይሁን በማለት ብዙ ጊዜ ስለ ሰላም ይናገራል። ማንም ስላምን ይመርጣል፣ በደም መቃባት ፣ በመገዳደል እና በብጥብጥም ደስ የሚሰኝ የለም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስም ስለ ሰላም የሚናገረው ነገር እንዳለ መርሳት አይገባንም። እውነተኛ ሰላም የመጽደቃችን ፍሬ ነው (ሮሜ 5:1)።

መጽሐፍ ቅዱስ ለክፉዎች ሰላም እንደሌለ ይነገረናል (ኢሳ 57:21) ። እነርሱም “ሰላም ሳይሆን ሰላም ሰላም ይላሉ” (ኤር 6:14) ። እነርሱ “......ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው፤ ጸጥ ይል ዘንድ አይችልምና፥ ውኆቹም ጭቃና ጉድፍ ያወጣሉና” (ኢሳ 57:20)። በእነርሱ ዘንድ የሰላም መንገድ እንኳን አይታወቅም (ኢሳ 59:8)።

ይሄ ሁሉ እውነት የሚሆነው ትክክለኛው ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በኩል የሚፈጸም ሰላም ስለሆነ ነው። እርሱ የሰላም ንጉስ ነው (ኢሳ 9:6) ። የእርሱ ስላም ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል የመሆን ሰላም ነው። በዚህም እግዚአብሔር እንደማይኮንነን እናውቃለን፣ የእርሱ ሰላም በእርሱ መስዋዕትነት እና በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ ባገኘነው የሀጥያት ይቅርታ ያገኘነው ሰላም ነው።

እውነተኛ ሰላም እግዚአብሔር እኛ ላይ ቁጣ እንደሌለበት ፣ ክርስቶስ ሀጥያታችንን እንደወሰደ እና ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን አንዳች ነገር እንደሌለ ከማወቅ የሚመነጭ የልብ ፣ የነፍስ እና የአእምሮ መረጋጋት ነው፥ “የጽድቅም ሥራ ሰላም፥ የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል” (ኢሳ 32:17)።

ይህ ሰላም የሚመጣው ክርስቶስ እንደሚያጸድቅ በማመን ነው “በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ” (ሮሜ 5:1)። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር አብረው ትዕዛዙ በሚያዘው መታዘዝ ለሚሄዱ ሁሉ የተገባ ነው

“ስለዚህ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ” (2ኛ ጴጥ 3:14)።:

ያለ እውነተኛ መንፈሳዊ ሰላም ምንም ትርጉም ያለው ነገር የለም። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሳይሆኑ በሰዎች ዘንድ ያለ ሰላም ማታለል ወይንም ውሸት ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እስካልሆኑ ድረስ በእውነት እርስ በእርስ ሰላም ሊሆኑ አይችሉም።

ፖለቲከኞች ፣ ተደራዳሪዎች ፣ እና ተኩስ አቁም አዋጆች አላማቸውን ቢያሳኩ እንኳን የሰውን ልብ መቀየር ስለማይችሉ መቼም ቢሆን እውነተኛ እና ዘላቂ ሰላም ሊያመጡ አይችሉም። በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ እነርሱ እስከሚመጣ ድረስ ሰዎች “በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ የምንጣላ” ነን (ቲቶ 3:3)።

ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ሰላም ከሌለ ዘላቂ የጥል እና የብጥብጥ መቋጫ ሊኖር አይችልምና ክርስቲያኖች በሰዎች ጥረት ፣ ተስፋዎች ፣ በሰዋዊ ድርጅት ሁሉ ላይ ባለመታመን በራዕ 21 ላይ እንደተገለጸው የዚህ አለም ማብቂያ እና የአዲሱን ሰማይ እና ምድር መምጣት በመጠባበቅ ወደ ክርስቶስ መምጣት ይመልከቱ። ለቤተክርስቲያን ሲባል ወይም ደግሞ ስለቤተሰቦቹ ሲል ክርስቲያን ለጊዜያዊ የጦርነት እና የብጥብጥ ፍጻሜ ሊጸልይ ይችላል። ነገር ግን የሚፈልገው እውነተኛ ሰላም በዚህ አለም ሳይሆን በሚመጣው አለም ብቻ ያለ ነው።

ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም” ያለው ለዚህ ነው (ዪሀንስ 14:27) ።

እግዚአብሔር እውነተኛ ሰላም ለእኔ እና ለእናንተ ይስጠን። ለብዙዎችም ይህንን ሰላም ይስጣቸው!

## መለወጥ

የመለወጥ ጅማሬ ከአዲስ ፍጥረት ስለሚነሳ መለወጥ እና አዲስ ፍጥረት ግንኙነት አላቸው። በእርግጥም ብዙ ክርስቲያኖች ስለመለወጥ በሚነጋገሩበት ወቅት ወይንም “መች ነው ጌታን የተቀበልከው (የተለወጥከው)?” ብለው ሲጠያየቁ ጥያቄያቸው *የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ጸጋ* በዚያ ሰው ላይ መቼ መጣ ለማለት ነው። ሆኖም ግን እኛ ስለመለወጥ ስንነጋገር ከቅድስና ጋር በማያያዝ የክርስቲያኖች የእለተ

እለት ህይወት ላይ ማተኮር እንፈልጋለን። መለወጥ “መመለስ” እንደሆነ ስናስተውል እነዚህ ሁለት ሀሳቦች ተያያዥ እንደሆኑ እንረዳለን።

የምንመለሰው ከ*ሀጥያት* (ሕዝ 33:11) *ወደ እግዚአብሔር* እንደሆነ በቃሉ ተቀምጦልናል (ሕዝ 33፡11 ፣ ሉቃ 1:16) ። እነዚህ ሁለቱ አንድላይ መሆን አለባቸው ። አንዳንዶች ከተወሰነ ሀጥያት ሊመለሱ ይችላሉ ለምሳሌ ከሰካራምነት ይመለሳሉ፤ ሆኖም ግን ወደ እግዚአብሔር አይመለሱም። እነዚህ ሰዎች አልተለወጡም ማለት ነው። አንዳንዶችም ከሀጥያቶቻቸው ሳይመለሱ ወደ እግዚአብሔር እንደተመለሱ የሚናገሩ አሉ፤ እነዚህም አልተለወጡም።

ከሀጥያት መመለስ ንሰሃን እና ቋሚ የሆነ ከሀጥያት፣ ከሰይጣን እና ከስጋ ጋር የሚደረግ ትግልን - መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚለው *አሮጌውን ሰውነት ማውለቅ* ያካተተ ነው (ቆላ 3፡9 ፣ ሐዋ 26:20 ፣ 1ኛ ቆሮ 9:26-27 ፣ ገላ 5:17) ። ወደ እግዚአብሔር መመለስ ደግሞ የህይወት ቅድስናን - መጽሐፍ ቅዱስም *አዲሱን ሰው መልበስ* ብሎ ያስቀመጠውን ያካተተ ነው (ቆላ 3፡10 ፣ ሐዋ 26:18) ።

በዚህ ቦታ ላይ ብዙዎች ይሳሳታሉ። በህብረቶች ላይ እጆቻቸውን ማንሳታቸው ወይም “ክርስቶስን ለመቀበል ያደረጉት ውሳኔ” ለራሳቸውም ብሎም ለሌሎች የመለወጣቸው ምልክት ነው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ያለ ንስሐ እና መቀደስ ይህ ማታለልእና አሁንም ሰዎችም ከእግዚአብሔር መንግስት የራቁ ሆነው ይቀጥላሉ (ማቴ 18:3)።

ይህ በመለወጥ ውስጥ የሚሆነው መመለስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ በህይወታችን ውስጥ ሉዓላዊ ጸጋውን ሲገልጥ ይፈጸማል። ነገር ግን በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። በእየለቱ ከሃጥያታችን ልንመለስ (ዘወር ልንል) ይገባናል። ሀጥያትን እስከሰራን ድረስ ንስሐ መግባት እና ሁልጊዜም “በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን” ልንመላለስ ይገባል (1ኛ ዩሀንስ 1:8-9 ፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 7:1)።

ይህ የእለተ እለት ንግግር ላይ አትኩሮት ያደርጋል። ነገር ግን ዋናው ጥያቄ “መቼ ተለወጥክ ?” ሳይሆን “አሁን ተለውጠሃል?” የሚለው ነው። “ለክርስቶስ ውስኛለው” ማለታችን ወይም አንዳንዶች ከብዙ አመት በፊት ጌታን መቀበላቸው አሁን በምድር ላይ በሀጥያት የሚራመድ እና በድሮ ኑሮው ለሚመላለስ ሰው ምንም ማለት አይድለም። ይህ ፍጹም በመረሳት በአንዳንድ ቦታዎች የእምነት ለውጥ ያደርገ ነገር ግን ሳይለወጥ በሀጥያተኛ ኑሮ የሚኖርበት “ስጋዊ ክርስትና” የሚባል አዲስ ክርስቲያንነት መጥቷል።

አንዳንዶች ለድህነታቸው ቀን እና ሰዓት መጥራት አለመቻላቸው ምንም ለውጥ አያመጣም። ጳውሎስ እንደዳነው ሁሉም አይድንም (2ኛ ጢሞ 3:15) ። ክርስቲያኖች አሁን በእግዚአብሔር ግሩም ጸጋ የተለወጠን ህይወት እየኖሩ ከሆነ እና በእግዚአብሔር ኃይል እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ከተለወጡ እነርሱ የእውነት የተለወጡ ሰዎች ናቸው።

ስለዚህ መለወጣችንም ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስራ መሆኑን አንርሳ። በእኛ ውሳኔ ወይም ምርጫ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ነብዩ እንደሚለው "እግዚአብሔር አምላኬ ነህና መልሰኝ እኔም እመለሳለሁ" (ኤር 31:18) ።

## መቀደስ

መቀደስ ከድህነት ቅደም ተከተሎች/ደረጃዎች ውስጥ የመጨረሻው እርምጃ ቢሆንም በአስፈላጊነቱ ከሌሎቹ የሚያንስ ነው ማለት አይደለም።

በመቀደስ ውስጥ የድነታችን መለኮታዊ አላማ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር መፈጸም ይጀምራል። መቀደስ ከቅድስና ጋር የተያያዘ ነው፤ ቃሉም በቀጥታ "ቅዱስ ማድረግ" የሚል ትርጉም አለው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በቅድስና ኑሮዋቸው የእግዚአብሔርን ክብር እና ጸጋውን ማሳየት ይጀምራሉ።

ስለዚህም መቀደስ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ልብ እና ህይወት *በዘመናቸው ሁሉ* የሚሰራው ስራ ነው። በስራውም ከሀጥያት መጨማለቅ እና ኃይል ነጻ በመሆን ለእግዚአብሔር እና ለቃሉ በመታዘዝ መኖር ይችላሉ። ይህም ደግሞ ከዳግም ልደት ይጀምራል በሞታችን እና ወደፊት በምናገኘው ክብር ደግሞ ይጠናቀቃል።

መቀደስ የክርስቶስ በእኛ ውስጥ የሚሰራው ስራ ሲሆን መጽደቅ ደግሞ ክርስቶስ ለእኛ የሰራው ስራ ነው የመጽደቅ እና የመቀደስ ልዩነት ይህ ነው። መንጻት/መቀደስ የህይወት ዘመን ስራ ነው ፤ መጽደቅ ግን የአንድ ጊዜ ስራ ነው። በመንጻት/በመቀደስ የተነቃቃን እና የምንሰራ እንሆናለን ፤ በመጽደቅ ውስጥ ግን የእኛ ዋና አከናዋኞች አይደለንም ። መንጻት ሀጥያታችን የበከለውን ማንነት የሚያነጻ ስራ ነው ፤ መጽደቅ ግን ጥፋተኝነትን ከእኛ ያስወግዳል።

መጽደቅ ማለት ስደተኛ በህግ በኩል ወደ አዲስ ሀገር ዜጋ ሲሆን እንደ ማለት ነው። ነገር ግን ዜጋ ከሆነ በኃላ እንደ ዜጋ ለመኖር ቋንቋውን ፣ የአለባበስ ስርዓቱን ፣ ምግቡን ፣ እና የሀገሩን አዲስ ህጎች ሁሉ ይለምዳል። መንጻትም እንዲሁ የእግዚአብሔር ህዝቦች የመንግስተ ሰማይ ህይወት ኑሮን የሚማሩበት መንገድ ነው።

መንጻት ሙሉ በሙሉ በጸጋ ይከናወናል። መንጻታችንን"ከእግዚአብሔር ከእራሱ እንማራለን" እንጂ በእራሳችን የምንማረው አንዳች የለም ። እኛ በቅድስናችን እና በመልካም ስራችን ተሳታፊዎች እንሆን ዘንድ በእኛ ውስጥ የሚሰራው እግዚአብሔር ነው "ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" (ፊሊ 2:13)።

በመቅደስ ወይንም በመንጻት ተግባር ውስጥ የድነታችንን ሀላፊነት እኛ እንወስደዋለን ማለት አይድለም ። እንደገናም በመቀደስ ተግባር ውስጥ በራሳችን ከእግዚአብሔር ጋር "በመስማማት" ድነታችን የጸጋ መሆኑ ይቀራል ማለት አይደለም ። ይህ ቢሆን ኖሮ ድነታችን በጸጋ መሆኑ ይቀር ነበር።

በመቀደሳችን ውስጥ መልካምን ስራ እናደርጋለን ነገር ግን ለዚህ ስራችን የሚገባን አንድም ነገር የለም (ኤፌ 2:8-10)። ብንታዘዝም ደግሞ የምንመካበት አንዳች ነገር የለም። ቅድስናችን የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና የመንጻታችን ክብር ፣ ምስጋና ፣ እና አምልኮ እርሱ ብቻውን ይገባዋል።

አንዳንዶች እንደሚያስቡት መንጻት/መቀደስ ምርጫ አይደለም። እነርሱ "ስለሥጋዊ ክርስትና" ይናገራሉ ይህም ደግሞ በክርስቲያን ህይወት ውስጥ የክርስቶስ ኢየሱስ ጌታነትን የሚክድ በመሆኑ ምልከታቸው ትክክል አይደለም።

መንጻት ከመጽደቅ የተለየ ቢሆንም መጽደቅን የሚከተል አስፈላጊ ተግባር ነው። አንድ ሰው ወንጀልን ሰርተሃል ተብሎ ታስሮ ጥፋተኛ አለመሆኑ ከታወቀ ከእስር ቤት መፈታት አለበት። በእግዚአብሔር ፊት በመጽደቃችን ሀጥያት የሌለብን ሆነን ስለተገኘን በፍርዱ መሰረት ከሀጥያት እና ከብልሹነት ልንላቀቅ ይገባል። በመቀደስም/በመንጻትም ደግሞ ነጻ እንወጣለን።

ዕብራዊያን 12:15 ክርስቲያን ሳይነጻ መኖር እንደማይችል ያስተመራል። ያለ *ቅድስና* "ማንም ሰው እግዚአብሔርን ሊያይ አይችልም!" ስለዚህም ቅድስና ምርጫ ወይንም አላስፈላጊ ነገር እንደሆነ ልናስብ አይገባም። ይህ እግዚአብሔር በህዝቡ የሚከብርበት የጸጋው ስራ ነው። በኢሳይያስ 43:21 ላይ ይህንን እናነባለን "ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ"። ጸጋም ይህ እንዲፈጸም ያደርጋል።

## ቅድስና

መንጻት የሚለው ቃል "ቅዱስ መሆን" ማለት ነው። ትርጉሙ በእራሱ እንደሚያመለክተው መንጻት የእኛ ስራ እንዳልሆነ እና በመንጻት ስራ ተካፋዮች ብንሆንም መንጻት ግን የእግዚአብሔር ስራ በእኛ ውስጥ እንደሆነ ግልጽ ነው ።እኛን *ቅዱሳን* አደረገን።

አስቀድመን እንደተነጋገርነው ይህ ቅድስና አማራጭ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ያለ ቅድስና ማንም እግዚአብሔርን ማየት አይችልምና (ዕብ 12:14)። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው (ኢሳ 40:25 ፣ ኢሳ 41:14) ስለዚህም ማንም ቅዱስ ሳይሆን በእርሱ ቅዱስ ህልውና ውስጥ መቆም አይችልም (መዝ 24:3-5)።

ታዲያ ቅድስና ምንድነው?

ቅድስና የሚለው ቃል ዋና ሀሳብ "መለየት" ነው። ቅዱስ መሆን ማለት መለየት ማለት ነው። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን እስራኤል ከሌሎች ህዝቦች የተለየ ቅዱስ ህዝብ ነበረ (ዘሌ 20:24-26)። ከእስራኤላውያን መካከልም ካህናቶች ሙሉ ህይወታቸው በቤተመቅደሱ ላለ አገልግሎት የተለዩ ስለሆኑ "ለጌታ ቅድስና ነበሩ" (1ኛ ዜና 23:13 ፣ ዘጽ 28:36-38) ።

ዛሬ ቤተክርስቲያን የተለየች ፣ ቅዱስ ህዝብ እና የንጉስ ካህን (1ኛ ጴጥ 2:9) ናት። ስለዚህም አባሎቿም ቅዱስ መሆን አለባቸው (1ኛ ጴጥ 1:15-16)።

ነገር ግን ቅድስና ሁለት ክፍል አለው። እነርሱም *ከየሆነ* ነገር መለየት እና *ለአንድ* ነገር መለየት ናቸው ነው። እነዚህ ሁለቱም ደግሞ እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

አማኞች በመጀመሪያ ከክፋታቸው እና ከክፉ ሰዎች እንዲለዩ ተጠርተዋል (2ኛ ቆሮ 6:14-18, ኤፌ 5:11-12) ። አማኞች ከአለም ሊወጡ አይችሉም (1ኛ ቆሮ 5:9-11) ነገር ግን በአቅማቸው ሁሉ እራሳቸውን እግዚአብሔራዊ ካልሆነ ህይወት ፣ ህብረት ፣ ስራ እና ህይወት ሊለዩ ይገባቸዋል። ከምንም በላይ ደግሞ እራሳቸውን "ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት" ማድረግ ይኖርባቸዋል (ያዕቆብ 1:27) ።

በ2 ቆሮ 6፤14-15 ላይ እንደተገለጸው በቤተክርስቲያን እና በአለም መካከል ፣ በአማኝ እና በማያምን መካከል ፣ በጨለማ እና በብርሀን መካከል ያለው ልዩነት አንዳንድ ጊዜ "አንቲ ቴሲስ" ተብሎ ይጠራል።

ይህ ክፍል በተጨማሪ ለእግዚአብሔር የተለየን ስለመሆናችን ይናገራል (ቁጥ 16-18) ። ያለዚህ ቅድስና ሙሉ መሆን አይችልም። ለእግዚአብሔር መለየት ማለት በብሉይ ኪዳን ካህናቶች እንደሆኑት ለእርሱ የተሰጠን እና የምንታዘዝ መሆን አለብን ማለት ነው። ለእግዚአብሔር አገልግሎት በህይወታችን በሰዓታችን ፣ በአካላችንም ጭምር እንኳን የተለየን ልንሆንለት ይገባል።

ይህ መለየት የትርፍ ጊዜ ጉዳይ አይደለም። ቅዱስ መሆን ፣ መለየት እና ለእግዚአብሔር መሰጠት በጌታ ቀን ሙሉ ለሙሉ ወይም ለጥቂት ሰዓታት ብቻ መሆን ማለት አይደለም። ነገር ግን ሙሉ ህይወታችንን በክርስቶስ የተገዛ በመሆኑ ለእግዚአብሔር ስለሚገባው ለእግዚአብሔር የተሰጠ እና በቅድስና የሚኖር ህይወት ሊሆን ይገባዋል።

ለዚህም *ተጠርተናል*። እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና እኛም ለቅድስና ስለተመርጥን እና መቤዠትን ስላገኘን፤ ብሎም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ስለላከልን ቅድስና ከእኛ ይጠበቃል (1ጴጥ 1፡15-16 ፣ ኤፌ 1:4 ፣ 1ኛ ጴጥ 1:18-19። ይህ የቅድስና ጥሪ በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። የዊልያም ህግ እንደሚለው ይህ በሀላፊነት ልንወስደው የተገባመጠራት ነው[8]።

ይህንን ጥሪ *አዳምጣችኋል*?

ለጥሪው *ትታዘዛላችሁ*?

## ተቃርኖ (አንቲ ቴሲስ)

አልፎ አልፎ አንዳንድ የተሓድሶ ሥነ መለኮታዊያን ስለ አንቲቴሲስ ይጽፋሉ። ይህ ሀሳብ በጨለማ እና በብርሀን መካከል ፣ በአማኝ እና በማያምን መካከል ፣ እና በአለም እና በምድር መካከል ስላለው *ልዩነት* እና *ተቃርኖ* የሚናገር ነው።

ይህ ተቃርኖ/አንቲ ቴሲስ ቃሉ በቀጥታ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተቀምጦ ባናገኘውም በእግዚአብሔር የማዳን ጸጋ ምክኒያት የሚመጣ ውጤት ሆኖ ሲንጸባረቅ እንመለከታለን። ስለ ተቃርኖ/አንቲ ቴሲስ በግልጽ የሚያወራው 2ኛ ቆሮንቶስ 6:14-18 ላይ የተጠቀሰው ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ላይ ያለው ቃል ተቃርኖን የሚገልጽ ብቻ ሳይሆን በጽድቅ እና በእርኩሰት (ባለመጽደቅ) ፣ በጨለማ እና በብርሀን ፣ በክርስቶስ እና በሌሎች አማልክቶች ፣ በእምነት እና ባለማመን ፣ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እና በጣዖታት ቤተመቅደስ

መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራልናል ። ወደ ተግባር ስንተረጉመው ይህ ማለት እኛ “ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁነ” እንደሚለው የተለየን መሆን አለብን ማለት ነው (ቁጥ 17)።

ይህ መለያየት መንፈሳዊ ነው። እኛ ከአለም በስጋችን ተለይተን እንድንወጣ አልተጠራንም (1ኛ ቆሮ 5:10)። ይህ በሚመንኩሱ እና በገዳም በሚቆዩ ፣ ትዳርን ወይም አንዳንድ ምግቦችን መብላት በሚከለክሉ ሰዎች የሚደረግ ስህተት ነው። ተቃርኖ ማለት በአካላዊ ሁኔታ እራሳችንን በዙሪያችን ካለው አለም ለይተን ወይም ከአለም ነገሮች አግልለን እንኑር ማለት አይደለም። ነገር ግን ከክፉዎች *ተግባር ጋር* ምንም አይነት ህብረት የለንም ማለት ነው (ኤፌ 5:11-12) ይህ ብቻ ሳይሆን ከክፉዎች ጋር ጓደኝነት እንድንመሰረት ሆነ ህብረት እንድናደርግ አያስፈልግም ማለት ነው (2ኛ ቆሮ 6:17 ፣ ያዕቆብ 4:4 ) ። ስራ መስራት እና በዚህ አለም መኖር ስላለብን ከእነርሱ ጋር ልንሰራ እንችል ይሆናል ነገር ግን እንደዚያም ቢሆን ቅዱስ በመሆን መለየት አለብን (1ኛ ቆሮ 5:9-11)።

በዚህ ሀሳብ ውስጥ የጋራ ጸጋ የሚለው አስተምህሯችን ላይ ተቃውሟችንን እናንሳ። እግዚአብሔር ለክፉዎች እና ላልመረጣቸው ሁሉ የጋራ ጸጋን ይሰጣል ማለት በእግዚአብሔር ህዝብ እና በአለም በኩል አንድ የሚያደርግ መሰረት አለ እንደማለት ነው። ስለዚህ ቢያንስ በአንዳንድ መንገድ አማኞች ከክፉዎች ጋር የጋራ ተግባር ሊኖራቸው ፣ ከእነርሱ ጋር ህብረት ሊኖረን እና ጓዳኞቻችን ልናረጋቸው እንችላለን። ይህንንም ህብረታችንን ለመደገፍ የጋራ ጸጋ አለን ብለን መከራከር እንችላለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን እና ለእግዚአብሔር ሰዎች ደህንነት እና ጤነኝነት ከክፉዎች መለየት ሊኖር እንደሚገባ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦልናል ። ይህም በብሉይ ኪዳን ጭምር ግልጽ ነበር። ዘዳግም 33:28 “እስራኤልም ተማምኖ ይኖራል” ተብሎ ተጽፏል። በአዲስ ኪዳንም ይህ እውነት ነው። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል “እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል” የእግዚአብሔር የሆኑ እና ትዕዛዙን ለሚፈጽሙ ሁሉ “ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኵስንም አትንኩ ይላል” (2ኛ ቆሮ 6:17-18)። ታዲያ በተለይም በዚህ ጊዜ ይህንን ቃል አብልጠን መስማት አለብን!

እያንዳንዳችን የተለየን ልንሆን ይገባል። ስለ እግዚአብሔር ስንል እና ስለቤተክርስቲያን ስንል የተለየን ልንሆን ይገባል። እኛ ካልተለየን እግዚአብሔር በእኛ አይከብርም። ቤተክርስቲያንም አለምን የምትመስል ትሆናለች።

**መጽናት**

ከድነት ቅድመ ተከተል/ ደረጃዎች የመጨረሻ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ መጽናት ነው። መጽናት የሚለው ቃል በእግዚአብሔር ኃይል እና ጸጋ ምክንያት አማኞች እምነታቸውን አያጡም የሚለውን ሀሳብ ይገልጣል። እግዚአብሔር ሕዝቡን *ያጸናል* (መዝ 37:28, ኤር 32:40, 1ኛ ጴጥ 1:5) ። ይህም ቃል ድነት በጸጋ ብቻ እንደሆነ ያስታውሰናል። አማኞች ድነታቸውን የማያጡት በመታዘዛቸው ፣ በታማኝነታቸው እና በጥረታቸው ሳይሆን ከመጥፋት በሚያጸናቸው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

ታዲያ እግዚአብሔር የሚያጸናው ምንድን ነው? እርሱ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ለድነት ዘር የሚሆነውን የዳግም ውልደት ህይወት ያጸናላቸዋል (1ኛ ዩሀንስ 3:9)። በዚህም እርሱን ማመን እና እግዚአብሔርን ፍጹም ባልሆነ መንገድ ቢሆንም እንኳን መታዘዛቸውን እንዲቀጥሉ እምነታቸውን እና መታዘዛቸውን ያጸናል (መዝ 90:17, መዝ 138:8, ፊሊ 1:6)።

እግዚአብሔር ስጋን እና የስጋን ስራ *አያጸናም*! በአማኝ ውስጥ ስጋው፣ ስራው፣ እና ግዛቱ የሚጠፉ ናቸው (ገላ 5:24)። አማኞች ይህ እንዲጸናለት ሊፈልግ ፣ ወይንም ደግሞ ለማጽናት ሊተጋ አይገባም።

እኛም ይህንን ከዚህ አስተምህሮ አንጻር የእግዚአብሔር ምርጦች የጸኑ መሆናቸውን ልናስታውስ እንወዳለን። የሚያጸናቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ስለመረጣቸው ነው (ኤፌ 1:3-4, 11)።

ነገር ግን የተመረጡት ከእምነት ተለይተው አይጸኑም። እምነት ለድነት ምክንያት ባይሆንም የድህነት መንገድ ግን ነው። 1ኛ ጴጥሮስ 1:5 ስለ አማኝ  እንዲህ ብሎ ያስተምራል “በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ”

ታድያ አማኞች ከምን ይጠበቃሉ? የሚጠበቁት ከፈተና ፣ ከድካም ፣ ወይም በሀጥያት ከመውደቅ አይደለም።

ይህንን ማስታወስ እጅግ ወሳኝ ነው! አማኞች ከመውደቅ ሳይሆን ወድቀው ከመቅረት ፣ ከፈተና ሳይሆን በፈተና ከመጥፋት ፤ ከሀጥያት ሳይሆን በሀጥያት ከመሞት የተጠበቁ ናቸው። በእራሳቸው ድክመት እና ሀጥያተኝነት አማኞች በፈተና እና በሀጥያት ሊወድቁ ይችላሉ። ነገር ግን መዝሙር 37:24 መጠበቃችንን ያረጋግጥልናል “ቢወድቅም ለድንጋጤ አይጣልም፥ እግዚአብሔር እጁን ይዞ ይደግፈዋልና”

አማኝ ሊወድቅ እንደሚችል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዳዊት እና በጴጥሮስ መውደቅ በግልጽ እንመለከታለን። እነርሱ ወድቀው እንደማይቀሩ በመመለሳቸው እንረዳለን። በእርግጥም በጴጥሮስ መውደቅ ጊዜ ጌታ አስቀድሞ ጴጥሮስ እንደማይጠፋ “ጌታም። ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ” በማለት ማረጋገጫ ሰጥቶት ነበር (ሉቃስ 22:31-31)። መጠበቅ እንዴት ያለ የጸጋው ድንቅ ስራ ነው።

## የቅዱሳን ጽናት

*የቅዱሳን ጽናት* በተለምዶ ከአምስቱ የካልቪኒዝም ነጥቦች ውስጥ አምስተኛው ነው።  ከእግዚአብሔር ስራ እና የጸጋው አቅም በላይ ስለእኛ ድርሻ የሚያወራ በመምሰሉ ከሌሎቹ አራት የካልቪኒዝም ስሞች የተለየ ይመስላል። በዚህም ምክንያት አንዳንዶች *የቅዱሳን መጽናት* የሚለውን ስም ይመርጣሉ። የቀድሞው ስም የእግዚአሔርን ሉዓላዊ ጸጋ አያሳላምና።

ስለመጠበቅ ሳይሆን ስለመጽናት ማወራታችን በድነት መንገድ መቀጠል የምንችለው “በጸጋ ብቻ ነው” የሚለውን የሚክድ አይደለም። ከጸጋው ውጪ መጽናት የምንችልበት ሌላ መንገድ የለም።

መጠበቅ እንደሚለው ስም መጽናትም የሚያስተምረው የእግዚአብሔር ሕዝቦች አንዴ ከዳኑ ድነታቸውን ሊያጡ እንደማይችሉ፣ ደግሞም እንደማያጡ ነው። እነርሱ በድነት መንገድ እስከመጨረሻው *ይጸናሉ*።

ነገር ግን ይህ የድነት መንገድ በፈተና እና በከባድ ነገሮች ሁሉ የተሞላ መሆኑንም ያመላክታል። ቀላል መንገድ ከመሆን ይልቅ  መስቀሉን የመሸከም ፣ ስለክርስቶስ መከራን የመቀበል ፣ ክፉን ፣ አለምን እና ስጋን የመቃወም እና በመከራ ጊዜ መጽናትን ሁሉ የሚያካትት ጉዞ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ህዝቦች በሰላም በእነዚህ ፈተናዎች ሁሉ በማለፍ ከክርስቶስ ጋር ወደ ክብር ይገባሉ።

*መጽናት* የሚለውን ቃል የምንጠቀመው የእግዚአብሔር ህዝቦች ድነታቸውን ሊያጡ ይችላሉ የሚሉትን ለመቃወም ነው። እነርሱ የመጽናት አስተምህሮ አለማዊነት ፣ ግድ የለሽነትን እና እግዚአብሔርን ለመምሰል ያለውን ትጋት ሁሉ ይወስዳል ብለው ያስባሉ።

ሁለቱም መጽናት እና ጻድቃን የሚለው ስም እንዲህ አለመሆኑን ይናገራል። የእግዚአብሔር ህዝቦች ጻድቃን ሆነዋል ማለትም በጸጋው ኃይል ቅዱስ ሆነዋል ፤ በዚህም የቅድስና መንገድ በመጓዝ ወደ መንግስተሰማይ ይገሰግሳሉ እንጂ ወደ እርኩሰት አይሄዱም ማለት ነው(ዕብ 12:14)። የድነት መንገድ የቅድስና መንገድ ነው ስለዚህም ወደ ክብር የሚያስኬድ ሌላ መንገድ የለም። ደግሞም በክርስቶስ ደም የተገዛ ፣ አዲስ ፍጥረት የሆነ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ታድሶ መንፈስ በውስጡ የሚያድርበት ሰው በጥፋት ጎዳና ይቀጥላል ማለት የማይታሰብ ነገር ነው (ሮሜ 6:1-2)።

ነገር ግን ይህንን የሚክዱ አንዳንድ ሰዎች አሉ። አንድ ሰው ድኖ ነገር ግን የህይወት ለውጥ ላያሳይ እና በዚያው የሀጥያት መንገድ ከመዳኑ በፊት ይኖር የነበረውን ኑሮ ይኖራል ብለው የሚያስቡ አሉ። በዚህ አስተምህሮ መሰረት ለምሳሌ ሙሉ ህይወቱን በክርስቶስ ግዛት ውስጥ ሳያደርግ እና በጌትነቱ ሳይገዛ ኢየሱስ አዳኙ ሆኖ ጌታው ግን ያልሆነ ሰው አለ ማለት ነው።

በዚህም ምክንያት “ዘላለማዊ ደህንነት” የሚለውን ስም አንወደውም። ይህም ደግሞ ስሙ በእራሱ መጥፎ ስለሆነ አይደለም። ነገር ግን ይህንን ስም የሚጠቀሙ ሰዎች አኗኗርህ ምንም ለውጥ አያመጣም በማለት “አንዴ የዳነ፣ ለዘላለም ድኗል” የሚለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ስለሆኑ ነው።*ነገር ግን ኑሮአችን እጅግ ወሳኝ ነው፤ በጣም ወሳኝ ነው።*

የጻድቃን መጽናት እጅግ እረፍት የሚሰጥ ነው። የእግዚአብሔር ህዝቦች ከክርስቶስ ጋት በክብር ወደ ህይወት እንደሚመጡ ብቻ ሳይሆን የሚያረጋግጠው በዚኛውም ህይወት ቅዱሳን እንደሚሆኑ የሚናገረው ነው። የትኛውም አማኝ ሀጥያቱን መውደድ እና መጠበቅ አይፈልግም ። እርሱ ሀጥያቱን መጥላት እና ከዚህም ሀጥያቱ ሙሉ በሙሉ ለመዳን መሻቱ ሊኖረው ይገባል። ስለዚህም የቅዱሳን መጽናት አስተምህሮ የዳነ ከሀጥያት ነጻ ወጥቷል ደግሞም ይወጣል የሚለውን አስተምህሮ ያስተምራል።

## ቅዱሳን

የቅዱሳን ጽናት አስተምህሮን እየተነጋገርን ነበር። ከመጨረሳችን በፊት በዚህ አስተምህሮ *ቅዱሳን* ከሚለው ቃል ጋር በተገናኘ መናገር የምንፈልገው ነገር አለ። ቃሉ በቀጥተኛ ትርጉሙ “የተቀደሱ” ማለት ነው ደግሞም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሰዎችን መንጻት ነው።

*ቅዱሳን* የሚለው ቃል ትክክለኛ መረዳት አስፈላጊ ነው። ቅዱሳን አንዳንዶች እንደሚሉት በመንፈሳዊ ህይወታቸው እራሳቸውን የሰሩ ሰዎች ቢሆኑ ወይንም ደግሞ በፈቃዳቸው እና በስራቸው ቅዱሳን የሆኑ ሰዎች ቢሆኑ በእርግጠኝነት መጽናት የሚባለው ነገር አይኖርም። ቅዱሳን እራሳቸውን ቅዱስ ካደረጉ እራሳቸውን ርኩስ ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው።

ይህ ሰው የሚድነው በእራሱ ፈቃድ ነው፤ መንጻቱ እና በጸጋ ማደጉም በእርሱ ላይ የሚደገፍ ነው የሚል እሳቤ *"የነጻ ፈቃድ"* አስተምህሮ ነው። ስለዚህም ለእርሱ ቅዱስ እንዲሆን የተዘጋጀለትን ጸጋ ለመጠቀም መምረጥ አለበት። ነገር ግን በዚህ እሳቤ መሰረት ማንም ቅዱስ አይሆንም ነበር።

እኛ ግን ቅዱሳን ቅዱሳን የሆኑት እና ያላቸው የትኛውንም አይነት ቅድስና በጸጋው ብቻ እንደሆነ እናምናለን። በሌላ አማርኛ እነርሱ ቅዱሳን እና ለክርስቶስ ኢየሱስ ታማኝ አገልጋይ ናቸው (ኤፌ 1:1, ፊሊ 1:1, ቆላ 1፡1-2)።

የቅዱሳን ቅድስና የእራሳቸው ነጻ ፈቃድ ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እና ምርጫ ውጤት ነው። በኤፌሶን 1:4ም ይህንን እንመለከታለን "ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን" ። የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ የቅድስናቸው ምንጭ ነው።

ከዚህም በላይ የቅዱሳን ቅድስና የተገዛው በእራሳቸው ስራ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ነው። ስለዚህም ደግሞ በቆላ 1:21-22 ይህንን እንመለከታለን "እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።" የክርስቶስ ኢየሱስ ደም መፍሰስ ለቅድስናቸው መሰረት ነው።

እግዚአብሔርም "ሁሉን ነገር ሰጥቻችኋለው እናንተም እንደ ትዕዛዜ ነገሮችን እንድታደርጉ የእራሳችሁ ድርሻ ነው" እንደሚለው የቅዱሳን ቅድስና በእነርሱ ላይ አይደገፍም። ቅዱሳን በባህሪያቸው እና በንግግራቸው በመንፈስ ቅዱስ ስራ ቅዱስ ይሆናሉ። መንጻትም ደግሞ "በመንፈስ መንጻት ነው" (1ኛ ጴጥ 1:2)። ስለዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች "ቅዱሳን ሊሆኑ የተጠሩት" ናቸው በማለት ይናገራል (ሮሜ 1:7, 1ኛ ቆሮ 1:2)። ስለዚህም የእግዚአብሔር ኃያል ቃል እነርሱን ወደ ቅድስና ያመጣቸዋል።

መንፈስ ቅዱሳንን የመስራት ስራ ጀመሮ እስከመጨረሻው በቅድስና እንዲኖሩ ለእነርሱ ሁሉንም ኃላፊነት ሰጥቶ አይሄድም። የእነርሱ በቅድስና መቀጠል ሙሉ በሙሉ የሚደገፈው በመንፈስ ቅዱስ አብሮነት እና ኃይል ነው። ቅዱሳን ለመሆን በእራሳችን ጥረት አንማርም። ድነትን የሚያመጣልን የእግዚአብሔር ጸጋ ነው "ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል" (ቲቶ 2:11-13)። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የቅድስና ሀይል ነው።

ስለዚህም ቅዱሳን ብቻ ጌታን እንደሚያዩት መርሳት የለብንም (ዕብ 12:14)። እግዚአብሔር እርሱን በክብሩ እንድናየው የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሚሰጠን ማወቅ እንዴት ግሩም ነው!

## መክበር

በድህነት ደረጃ ውስጥ የመጨረሻው ክፍል የእግዚአብሔር ምርጦች ወደ መንግስተ ሰማይ የሚገቡበት ጊዜ እርሱም *መክበር* ነው። በእኛ መክበር እግዚአብሔር በዳግም ውልደት የጀመረውን የድህነታችንን ስራ ይጨርሰዋል። ህዝቡን ከመከራ እና ከሞት ብቻ ሳይሆን ከሀጥያታቸው ሁሉ ያድናቸዋል።

*ስለመክበር የምናደረገው ንግግር ለመጨረሻው አስተምህሮ የተገባው ነው። ነገር ግን በጠለቀ መልኩ ስለነዚህ ጉዳዮች እንደመካከለኛ ሁነት እና የዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ስለሆነው ስለ ትንሳኤ ጸፈናል። ቢሆንም ስለመክበር እዚህ ቦታ ላይ ማንሳት አስፈላጊ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ታላቅ ስራ የሚጠናቀቅበት እና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር የምንበቃው በመክበራችን ውስጥ ነው።*

በመክበራችን ውስጥ ሦስት ደረጃዎች አሉ። የመጀመሪያው አዲስ ፍጥረት ስንሆን የዘላለም ህይወት ስጦታ እንቀበላለን። በዚህ ስጦታ ምክንያት ከክርስቶስ ጋር አብረን ተነስተን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጠናል (ኤፌ 2:5-6) ፣ የእኛ "ንግግር" ( የህይወት ዘይቤያችን) በመንግስተ ሰማይ ነው (ፊሊ 3:20) ፣ እና የክርስቶስ አዲስ ህይወት በእኛ ውስጥ ይኖራል (ገላ 2:20)።

ሁለተኛ ደግሞ ነፍሳችን ከሞት በኃላ በቀጥታ ወደ ክብር እና የመንግስተ ሰማይ በረከት ይገባል ይህም ደግሞ የዘላለም ህይወት ስጦታን ነው (2ኛ ቆሮ 5:1-8)።

ሦስተኛ ሰውነታችን ከሞት ሲነሳ እና እንደ ክርስቶስ የክብር ሰውነትን ተላብሰን ወደ አዲሱ ሰማይ እና ምድር ስናርግ የምንቀበለው የዘላለም ህይወት ስጦታ ነው (ፊሊ 3:21)።

ስለዚህም የዘላለም ክብር ጅማሬ በመጨረሻው ቀን እንደምንቀበለው ሁሉ አሁንም ደግሞ እንዳለን አጥብቀን መናገር እንፈልጋለን። በመንግስተ ሰማይ እንደምንሆነው አሁን በከፊል መሆናችን ለመታዘዛችን ካለን ታላቅ መነሳሳት ውስጥ አንዱ ነው። በቆላስያስ 3:1-4 ጳውሎስ ስለዚህ ይናገራል። እኛ ከክርስቶስ ጋር ስለተነሳን እና በእግዚአብሔር ህይወታችን በእርሱ ስላለች፤ ሰማያዊውን ነገር ልንሻ እና አይናችንን እዚያ ላይ ልናደርግ ይገባናል።

የዘላለም ህይወት አሁን በእኛ ውስጥ በመጀመሩ ምክኒያት ነው አንዳንድ ጊዜ መንግስተ ሰማይን የምንናፍቀው እና ከአለም መላቀቅ፣ ከስጋችን እና ከአለም መዳን የምንፈልገው። ጳውሎስ እንዳለው እዚህ ከመቆየት እጅግ የተሻለ ነውና (ፊሊ 1:21-24)።

ሰማያዊ ክብራችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምሳሌዎች እና በአይነቶች እንደ አንጸባራቂ ወይንም አብሪ ነገር ተገለጧል። በተደጋጋሚም ደግሞ በዚህ መልክ የተገለጠው፣ አይን ያላየው፣ ጆሮ ያልሰማው እና በሰው ልብ ከቶ ያልታሰበ በመሆኑ ነው (1ኛ ቆሮ 2:9)። እግዚአብሔርንም ለሚወዱት ለእነርሱ የተዘጋጀላቸው ነገር ነው።

እኛ በሚያስደንቅ መልኩ ከሀጥያት እና መዘዙ በመላቀቅ ብንለወጥም፤ እግዚአብሔር ቃል የገባልንን ያንኑ ብንቀበልም፤ የመንግስተ ሰማይ ኑሮ አስገራሚው ክብር እግዚአብሔር እና ክርስቶስ በዚያ መኖራቸው ነው። ይህ የመንግስተ ሰማይ ብጹህነት፣ ደስታ፣ ክብር እና ሰላም ነው (ራዕ 21:3, 7, 22-23 ፥ ራዕ 22:3)። ስለዚህም የመክበር ተስፋ ያላቸው እነርሱ እራሳቸውን ለማንጻት እና ለሰማያዊው መንግስት አለምን ሁሉ ለማጣት እና ለመተው የተዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል። እነርሱም ይህንን ክብር በሚጠባበቁበት ጊዜ በእምነት እንጂ በሚያዩት ነገር አይራመዱም።

# ክፍል ፬ - ማጣቀሻዎች

1. C. I. Scofield (1843–1921), orig. editor, and Doris W. Rikkers, cont. editor, Scofield Study Bible, King James Version (New York: Oxford University Press, 2003). Scofield’s work was first published in 1909.
2. Answer 1 of the Westminster Shorter Catechism is“Man’s chief end isto glorify God and to enjoy him for ever.
3. Canons of Dordt, Heads of Doctrine 3 and 4, Article 16.
4. Ibid.
5. The Westminster Larger Catechism, Q&A 65.
6. Heidelberg Catechism, Lord’s Day 7, Q&A 20.
7. The Westminster Larger Catechism, Q&A 72.
8. William Law, A Serious Call to a Devout and Holy Life (Grand Rapids, MI: William B. Eerdmans Publishing Company, 1966). Original first published in 1728.

ክፍል ፭

# ቤተክርስቲያን እና ስርዓቶቿ

## ቤተክርስቲያን

መጽሐፍ ቅዱስ ስለቤተክርስቲያን ብዙ ከመናገሩ የተነሳ በሥነ-መለኮት ቤተክርስቲያንን የሚመለከት አስተምህሮ ሁሉ ብቻውን ይጠናል። ብዙ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍቶች ቤተክርስቲያን ዋና ትኩረታቸው ናት። የሐዋሪያት ስራ ለመጀመሪያ ጊዜ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን እንዴት እንደተመሰረተች ይናገራል ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ስላለው ታማኝነትን ይናገራል (1:9) ፣ ኤፌሶን ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት የሚለውን አስተምህሮ የያዘ ነው(1:22-23, 5:30-32) ፣ ቆላስያስ ደግሞ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ መሆኑን ለሚያመለክተው ታላቅ እውነት አትኩሮት ይሰጣል (1:18, 2:10) ፣ 1ኛ ጢሞቴዎስም የቤተክርስቲያንን ትክክለኛ ባህሪ ወይንም ተግባር ያስተምረናል (3:15) ፣ ቲቶ ደግሞ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትክክለኛ ስርዓትን ያስተምራል (1:5)።

የቤተክርስቲያን አስተምህሮ የሚገፋ ወይም አትኩሮት የሚነፈገው መሆን የለበትም። ነገር ግን በዚህ ዘመን ስለቤተክርስቲያን አስተምህሮ የሚያውቁ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለቤተክርስቲያን የሚለውን የሚያስተውሉ እና ለምን አስፈላጊ እንድሆነ የተረዱ ጥቂቶች ናቸው።

ቤተክርስቲያን ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል "የተጠሩ" የሚል ነው። ስለዚህም *ቤተክርስቲያን* የሚለው ስም የዳኑትን ሰዎች ብቻ ይመለከታል ማለት ነው። ይህ ስም እውነተኛ የቤተክርስቲያን አካላቶች "ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሀን የተጠሩ" ሰዎች መሆናቸውን ያስታውሰናል (1ኛ ጴጥ 2:9) ። ይህም ብቻ ሳይሆን የዳኑት ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ቦታ የጸጋ መሆኑንም ያስታውሰናል ። አባላት የሆኑት በራሳቸው ምርጫ ሳይሆን በእግዚአብሄር *ጥሪ* ነው።

የቤተክርስቲያን አባላቶች የተጠሩ መሆናቸው የሚያሳየው ከሀጥያት መዳናቸውን (ከጨለማ መጠራታቸውን) ብቻ ሳይሆን ከአለም እና ከክፋት መለየታቸውንም ጭምር ነው (2ኛ ቆሮ 6:14-18) ። ስለዚህም *ቤተክርስቲያን* የሚለው ስም የቤተክርስቲያን አባላት ቅድስናን እና መታዘዝም ያመለክታል ማለት ነው። ምዕመናኖቿ ቅዱሳን ያልሆኑበት ቤተክርስቲያን *ቤተክርስቲያን* የሚለው ስም አይገባትም።

ቅድስና ለቤተክርስቲያን መኖር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። አባላቶቿ የተጠሩት የተመረጡት እና ቤዛነትን ያገኙት ወደ ቅድስና ነው (ኤፌ 1:4 ፣ ቆላ 1:21-22)። እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ ካለው አላማ አንጻር የቤተክርስቲያን ቅድስና እጅግ አስፈላጊ ነው። የቤተክርስቲያን ህልውናዋ የእግዚአብሔር ክብር ነው

(ኤፌ 1:6, 12)። ይህም አላማ የሚፈጸመው በቤተክርስቲያን እና በአባላቶቿ ቅድስና ነው። አባላቶቿ ቅዱሳን ያልሆኑባት እና ያልተቀደሰች ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን የማያከብር እና ሊያከብር የማትችል ቤተክርስቲያን ናት። በቤተክርስቲያን መቀደስ ግን የእግዚአብሔር ክብር ይገለጣል።

በአሁኑ ዘመን ባለችው ቤተክርስቲያን አባላቶቿ እንደ ተጠሩት በቅድስና አለመኖራቸው ለቤተክርስቲያን እፍረት እና መጎዳት ሆኗል። ቤተክርስቲያን ከአለም በአስተምሮዋ ፣ የአባላቶቿ ባህሪ እና በተግባር የተለየች ካልሆነች ምስክርነቷ ሁሉ ትርጉም አልባም ነው። የቤተክርስቲያን ክብር እና ለዚህ ለጠፋ አለም ያላት ምስክርነት ክብር የሚደገፈው ከዚህ ክፉ አለም በመጠራቷ ፣ በልዩነቷ እና በመቀደሷ ነው።

ስለዚህም የቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ “.........የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ......... በፊቱ ቅዱሳን እና ያለነቀፋ” (ኤፌ 1:4,6) ሆነው መቆም እንዲችሉ ልትጸልዩ ይገባል። የቤተክርስቲያን ስራ እና ምስክርነት የሚበለጽግበት ብቸኛው መንገድ ይህ ብቻ ነውና።

## ጉባዬ እና አካል

ስለ ቤተክርስቲያን ስንነጋገር መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ *ቤተክርስቲያን* የሚለውን ቃል በተመሳሳይ መንገድ እንደማይገልጠው እንረዳለን። ቃሉንም የሚጠቀመው ጉባዬ የሚሰበሰብበትን ህንጻ ለመወከል ሳይሆን ስለቀጠናዊ በቤትክርስቲያኖች ለመናገር (1ኛ ቆሮ 1:2, ራዕይ 2:1, 8:12) ወይም ደግም ስለተመረጡት እና በዘመናት ውስጥ ስለዳኑት ሁሉ ለመናገር ነው (ኤፌ 1:23)።

ቤተክርስቲያን በ*ክርስቶስ አካልነቷ* እና ቤተክርስቲያን የ*ሰዎች ስብስብ በመሆኗ* መካከል ያለው ልዩነት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጥ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ቤተክርስቲያን እንደ ቀጠናዊ ስብስብነቷ *የቤተክርስቲያን ተቋም* ወይንም *የምትታየው ቤተክርስቲያን* ተብላ ልትጠራ ትችላለች ምክኒያቱም በምድር ላይ የተቋም መልክ ያላት እና የተገለጠች ናት። እንደዚሁ ደግሞ የተቤዡት ሰዎች ሁሉ ስብስብ *ቤተክርስቲያን፣ አካል፣ የማትታየው ቤተክርስቲያን* ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ ምክኒያቱም ይህች አካል በክርስቶስ ኢየሱስ ህያው የሆነች ናትና (“አካል” ነፍስ ያለው ፍጥረት እንደማለት ነው) ደግሞም ይህች አካል መንፈሳዊ እና የማይትታይ ናት (በምድር ላይ የሚታይ ወይንም የምንመለከተው አይደለም)።

ቤተክርስቲያን እንደ አካነቷ የምታካትተው የእግዚአብሔርን ምርጦች እና የተቤዣቸውን ሰዎች ብቻ ሲሆን (1ኛ ጴጥ 2:9) ፣ በቀጠናዊ ጉባዬ ሁልጊዜም ግብዞች ሊገኙ ይችላሉ(ራዕ 2:14-15 ፣ ራዕ 3:17-18)። ቤተክርስቲያን እንደ አካልነቷ የሞቱትን ፣ በህይወት ያሉትን እና በክርስቶስ ተመርጠው ገና ያልተወለዱትን ወይንም ወደዚህ ምድር ያልመጡትን ታካትታለች። ቤተክርስቲያን እንደ ጉባዬነቷ ግን የምታጠቃልለው አሁን በህይወት ያሉትን እና በዘመናት መካከል በተገደበ ጊዜ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ነው።

በአካል እና በጉባዬ መካከል ያለው ልዩነት አስፈላጊ ነው። ብዙ ጉባዬዎች ቢኖሩም (ራዕይ 2 እና 3) አንድ የክርስቶስ አካል ብቻ አለ (1ኛ ቆሮ 12:12)። አካሉም ሊጎዳ ወይም በጠላቶቹ ሊጠፋ አይችልም (ማቴ 16:18) ነገር ግን አንዳንድ ጉባዬዎች ሊታጡ ይችላሉ ደግሞም ይታጣሉ (1ኛ ቆሮ 1:11 ፣ ራዕ 3:1, 16)። እንደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አንድ ጉባዬ “ከመቅረዙ መካከል” በታውን ሊያጣ ይችላል (ራዕይ 2:5)። በዚህ ሁለት አውዶች መሰረት ግራ እንዳንጋባ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሁለት ትርጉሞች እና ልዩነቶች ማስታወስ ይኖርብናል።

ከቤተክርስቲያን አባልነት ጋር በተያያዘ በቤተክርስቲያን እና በአካሉ መካከል ያለው ልዩነትም እጅግ አስፈላጊ ነው። እኛ በሚታየው አካባቢያዊ ጉባኤ ውስጥ እራሳችንን እንድናሳትፍ ግዴታ አለብን (ዕብ 10:25) ። ነገር ግን እኛን በመምረጥ እና በጎልጎታ ላይ በፈሰሰው ደም አማካኝነት ከክርስቶስ ጋር የሚያጣብቀን እግዚአብሔር ነው (ቆላ 1:12-14)።

ሆኖም ግን ለቤተክርስቲያን የተጠቀምናቸው እነዚህ ሁለት ትርጉሞች ልዩነት ቢኖራቸውም እርስ በእርስ ይወራረሳሉ ። የክርስቶስ አካል በአጥቢያ ጉባዬ ውስጥ ይገኛል። የአጥቢያው ጉባኤ ቤተክርስቲያን ተብሎ የሚጠራበት ምክንያትም የክርስቶስ አካል በአጥቢያ ጉባኤ ውስጥ በመገኘቱ ነው።

ለማለት የፈለግነው ቤተክርስቲያን በእውነተኛ እና ትክክለኛ ትርጉሟ የዳኑት ሰዎች ስብስብ እና አካል *ብቻ* ናት። አንዳንድ ጉባኤዎች “ቤተክርስቲያን” በመባል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት በእውነት የተቤዡት ሰዎች በዚያ ስፍራ ስለሚገኙ ነው። እንደዚሁም ደግሞ የብሉይ ኪዳን ህዝብ እስራኤል የተባለው እውነተኛ እስራኤላዊያን በመካከሉ ስለተገኘ ነው (ሮሜ 2:28-29, ሮሜ 9:6, ገላ 3:29)።

ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ስለቤተክርስቲያን የሚያስተምረውን እንማር። በዚህም ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ አካልነቷ እና ተቋምነቷ መውደድ እና ማክበር እንማራለን።

## የቤተክርስቲያን ስሞች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለቤተክርስቲያን የተለያዩ ስሞች ተሰጥተዋት እንመለከታለን። እነዚህ ስሞች እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን በተመለከተ የገለጣቸው ስሞች ናቸው። እያንዳንዳቸውም ስለቤተክርስቲያን ቁልፍ የሆነን ጉዳይ ይነግሩናል።

ቤተክርስቲያን የሚለው ስም "የተጠራ" ማለት እንደሆነ ቀድመን ተመልክተናል። ይህ ስም እግዚአብሔር ህዝቡን ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሀን የጠራበትን ደግሞም ልዩ ሰዎች እንዲሆኑ የሚሰራበትን ቃል እና ተግባር ይወክላል (1ኛ ጴጥ 2:9)። *ቤተክርስቲያን* የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ መጠቀሱ የሚያስገርም አይደለም። የቤተክርስቲያን መገለጥ እና መባረክ የእግዚአብሔር ጥሪ እና ሉዓላዊ ጸጋ ስጦታ መሆኑን ያሳየናል።

ቤተክርስቲያን *የክርስቶስ አካል* ተብላ ተጠርታለች (1ኛ ቆሮ 12:12-27) ። ይህ ስም ክርስቶስ እንደ ቤተክርስቲያን ራስነቱ ያለውን ክብር ፣ ቤተርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላትን ህያው ህብረት እና የቤተክርስቲያን አባላት ያላቸውን የእርስ በእርስ ህብረት የሚገለጥ ነው። በአካሉ ውስጥ ክርስቲያኖች እርስ በእርስ ደግሞም ከክርስቶስ ጋር አካል ናቸው።

ደብዳቤዎቹ በጥቂቱ አትኩሮታቸው የተለያየ ቢሆንም የክርስቶስ አካል የሚለው ስም በኤፌሶን እና በቆላሲያስ ተጠቅሷል። ኤፌሶን በራሱ በቤተክርስቲያን ላይ የሚያተኩር እና ክርስቶስ በዚህ ቦታ ላይ ያለውን ክብር በደንብ የሚገልጽ ነው። ቆላስያስ ደግሞ ክርስቶስ  የቤተክርስቲያን የክብር ራስ መሆኑ ላይ የሚያተኩር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም ቤተክርስቲያንን ከወይን ግንድ ጋር (ዩሀንስ 15:1-6) ወይም ደግሞ ከዛፍ ጋር (ሮሜ 11:16-24) ያነጻጽራታል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እስራኤል እና ቤተክርስቲያን የሚያነጻጸር ክፍል እንመለከታለን (መዝ 80:8, ኢሳ 5:1-7) እነዚህ ክፍሎች እስራኤል እና ቤተክርስቲያን አንድ መሆናቸውን ያረጋግጡልናል። ይህ ንጽጽር በቤተክርስቲያን እና በክርስቶስ በኩል ያለውን ጥብቅ ትስስር እና የቤተክርስቲያን ፍጹም በክርስቶስ መደገፍን ያሳየናል ። እርሱ የወይን ግንድ ነው እኛም ደግሞ ቅርንጫፎቹ ነን።

*የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ* (1ኛ ቆሮ 3:16-17, 2ኛ ቆሮ 6:16, ኤፌ 2:20-21) ወይም ደግሞ *የእግዚአብሔር ቤት* በጥቂቱ ለየት ስም ነው (1ኛ ጢሞ 3:15, ዕብ 3:6, 1ኛ ጴጥ 2:4-9)። የሚያወራው *አካል ስለሆነቻው ቤተክርስቲያን* እንጂ አካሏ ስለምትሰበሰብበት ህንጻ እንዳልሆነ አስተውሉ። ቤተክርስቲያን ከህንጻ ወይንም ከማደሪያ *ጋር* ሲወዳደር ውበትን ፣ ስርዓትን ፣ እና አንድነትን ያመለክተናል። በዚህ መንፈሳዊ ህንጻ ውስጥ እያንዳንዱ አካል የእራሱን ቦታ ይይዛል። አካል የሚለው ስም የቤተክርስቲያንን ልዩነት ወይም ደግሞ እያንዳንዱ ምዕመን የተለያየ ቦታ እና ስፍራ እንዳለው ያሳያል (1ኛ ቆሮ 12)። ነገር ግን ሁሉም አካሎች አንድ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ህንጻ ናጸው።

መቅደስ ፣ ቤት፣ ህንጻ የሚሉት ቃላቶች ዋና አትኩሮት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ከህዝቡ *ጋር* የሚያድርበት ቦታ እንደሆነች የሚናገረውን የተባረከ እውነት ይገልጣሉ። እርሱ በክርስቶስ ራስነት ከእነርሱ *ጋር* በአንድ ጣራ ስር እንደ አንድ ቤተሰብ ይኖራል። ። በዚያ እግዚአብሔር እና ህዝቡ እርስ በእርስ ይነ*ጋገ*ራሉ ፤ እርሱም የገባላቸውን ኪዳን ይጠብቅላቸዋል ለዘላለምም ይባርካቸዋል።.

## የቤተክርስቲያን ሌሎች ስሞች

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች እንድናውቅ እና እንድንወዳት ብዙ ስሞችን እና አገላለጾችን ተጠቀሟል። ከእነዚህ ስሞች ብዛት እና አገላለጽ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር እይታ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነች እና በእኛም እይታ እንደዚሁ መሆን እንዳለባት እንረዳለን።

የቤተክርስቲያን ስሞች ዝርዝር በዕብራዊያን 12:22-24 ላይ ተጠቅሷል። በዚህ ክፍል ቤተክርስቲያን *የፂሆን ተራራ* ፣ *የህያው የእግዚአብሔር ከተማ* ፣ *ሰማያዊት ኢየሩሳሌም* ፣ *በሰማያት የተጻፉ የበኩራን ማህበር* ተብለው ተጠቅሰዋል። ቤተክርስቲያንም የአዲስ ኪዳን *ቅዱስ ህዝብ* ተብላ ተጠርታለች (1ኛ ጴጥ 2:9)።

ከዚህም እስራኤል እና ቤተክርስቲያን አንድ እንደሆኑ እንረዳለን። እስራኤል የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስቲያን ደግሞ የአዲስ ኪዳን እስራኤል ናት። የእስራኤልን ዋና ከተማ እግዚአብሔር እንደራሱ የመረጠው እና የእርሱን መኖሪያ ስፍራ እና መቅደስ ያበጀበት ስፍራ መሆኑን ለመግለጥ(መዝ 68:16, መዝ 132:13-14) የተቀመባቸውን ስሞች በአዲስ ኪዳን ለቤተክርስቲያን ሲጠቀምባቸው እንመለከታለን። ይህም

በራዕይ 21 ላይ መላዕኩ ለዩሐንስ እንዲህ ብሎ ሲገልጣት እንመለከታለን - *የእግዚአብሔርን ከተማ፣ አዲሲቷን ኢየሩሳሌም፣ ሙሽሪት፣ የበጉ ሚስት* (ቁጥ 9-10, ከኤፌ 5:32 ጋር ያነጻጽሩ) ።

በዚህ ውስጥ ብዙ ምስክርነቶች አሉ። ቤተክርስቲያን ወይን መሆኗ (ከዩሀንስ 15:1-6, መዝ 80:8 ጋር ያነጻጽሩ) ፣ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እና ማደሪያ መሆኗ (ኤፌ 2:20-22, 1ኛ ጢሞ 3:15) ፣ የፂሆን ተራራ፣ ኢየሩሳሌም፣ እናም ደግሞ የህያው እግዚአብሔር ከተማ ተብላ መጠራቷ እስራኤል በብሉይ ኪዳን የነብረችውን ነገር ሁሉ የአዲስ ኪዳኗን ቤተክርስቲያን እንደሚወክላት እንረዳለን።

የበለጠ በዚህ ጉዳይ ላይ ከመናገራችን በፊት የስሞቹን አስፈላጊነት ለማብራራት እንሞክራለን። ቤተክርስቲያን እንደ ከተማ ፣ ሀገር ወይም መንግስት ተብላ መጠራቷ ንጉሷ ጋር የራሷ መንፈሳዊ ሀብት፣ ህግ፣ ባህል እና ቋንቋ እንዳላት ያመላክታል። የቤተክርስቲያን አባላቶች የዚህ መንግስት ዜጎች በመሆናቸው እንደ ዜጋ ሙሉ መብት እና ጥቅም ያገኛሉ። በዚያ መንግስት እነርሱ ከጠላቶቻቸው ሁሉ የተጠበቁ እና በነገስታቱ ንጉስ በመልካም ይተዳደራሉ።

ሆኖም ግን ቤተክርስቲያን *መንፈሳዊ* መንግስት፣ ህዝብ እና ከተማ ነበረች ደግሞም ነች። ግድግዳዎቿ ድነት መግቢያዋም ምስጋና ነው (ኢሳ 60:18)። ቁልፏም የወንጌል መሰበክ እና የክርስቲያን ምግባራዊ ልምምድ ነው (ማቴ 16:19, ማቲ 18:15-20)። የቤተክርቲያን መሰረቶች ሐዋሪያዊ እና ትንቢታዊ አስተምህሮዎች ሲሆኑ እነዚህም ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ አይደሉም (ኤፌ 2:20-22, ራዕይ 22፡14)።

ቤተክርስቲያን *የጺሆን* ተራራ ማረፊያ መባሏ እኛ በቤተክርስቲያን ንጉስ ግዛት ስር ያለን መሆናችንን ያመለክተናል ።ደግሞም ይህ ግዛት የማይሻር እና ጠንካራ ነው (መዝ 48:12-14)። ስለዚህ ከዚህ ውጪ ሌላ ግድግዳ፣ መግቢያ፣ መሰረት እና ቁልፍ ከወዴት ይመጣል? የገሀነም ደጆች ሊቋቋማት አለመቻላቸው የሚያስደንቅም አይደለም (ማቴ 16:18)።

ነገር ግን ይህንን ሁሉ ልንረዳ የምንችለው በእምነት ብቻ ነው። በአለም እይታ ቤተክርስቲያን ትንሽ እና የተገፉች ቅሬታ ፣ ጥቂት ህዝብ ያላት (ሉቃስ 12:32)፣ ትንሽ የወይን እርሻ፣ በታላላቅ ፍሬዎች መካከል የተቀበረች፣ የተከበበች ከተማ ትመስላለች (ኢሳ 1:8)። ቤተክርስቲያን “እንደ ኢየሩሳሌምም ያማርሽ ነሽ፤ ዓላማ ይዞ እንደ ተሰለፈ ሠራዊት ታስፈሪያለሽ” መሆኗን የምንመለከተው በእምነት ብቻ ነው (ማህ 6:4, 10) ። ስለዚህም በእምነት በጺሆን እንመላለስ ደግሞም ለትውልድ ሁሉ እንናገር ደግሞም ማረፊያዎቹን ሁሉ እናስተውል ። ሁል ጊዜም እግዚአብሔር እግዚአብሔሯ መሆኑ የተገለጠ ይሆናል (መዝ 48:12-14) ።

## ቤተክርስቲያን እና እስራኤል

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ብዙ ማብራሪያዎችን እና መግለጫዎችን ተጠቅመን ቤተክርስቲያን እና እስራኤል አንድ እንደሆኑ አመላክተናል። ቤተክርስቲያን የጺሆን ተራራ፣ የእግዚአብሔር ከተማ፣ ሰማያዊ እና ቅዱስ ኢየሩሳሌም (ዕብ 12:22-24, ራዕይ 21:9-10)፣ የተቀደሰች ከተማ (1ኛ ጴጥ 2:9)፣ ወይን (ዩሀንስ 15:1-6, መዝ 80:8) ፣ የእግዚአብሔር ሙሽራ (ኤፌ 5:31-32, ራዕይ 21:9-10) ነች። ቤተክርስቲያን እስራኤል በብሉይ ኪዳን የነበረችውን ሁሉ ነች።

ይህ የቤተክርስቲያን ማንነት እና እስራኤልነት የበለጠ በሐዋ 7፡38 ላይ “በበርሀ ያለች ቤተክርስቲያን” ተብላ በመጠራቷ ተረጋግጧል።

በተመሳሳይ ከሁሉም ወገን የተውጣጡት የእግዚአብሔር ምርጦች  እውነትኛ እስራኤላዊያን እና እውነተኛ አይሁዳዊያን ተብለው ተጠርተዋል (ሮሜ 2:28-29, ሮሜ 9:8, ገላ 3:29, ፊሊ 3:3)። በእርግጥም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ትንቢቶች የእስራኤል ህዝብ መንፈሳዊያን እና በአዲስ ኪዳኑ ቤተክርስቲያን የሚተረጎሙ እንደሆኑ ይናገራል (ሆሴ 1:10 እና ሮሜ 9:24-26 ላይ ያለውን የትንቢትን ፍጻሜ ከአሞጽ 9:11-15 እና በሐዋ 15:13-17 ካለው የትንቢት ፍጻሜ ጋር ያነጻጽሩ)።

በተለይም የቤተክርስቲያንን ዶክትሪን በተመለከተ ይህ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው ። በዚህ ብርሃን ብቻ ብሉይ ኪዳን ከታሪኩ፣ ከማስጠንቀቂያው እና ተስፋው ለቤተክርስቲያን መሆን ይችላል። ብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን ስላልሆኑ ህዝቦች ብቻ የሚያወራ ከሆነ ብሉይ ኪዳን ለእኛ በዚህ ዘመን *የሚናገረን ነገር የለውም* ማለት ነው። ስለዚህም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍቶችን ማንበብ የእኛን የማወቅ ፍላጎት ከማርካት በዘለለ የሚያደርገው ነገር የለም ማለት ነው።

እስኪ አስቡት፤ እስራኤል እና አዲሲቷ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ናቸው ብለው የሚያምኑ ሰዎች በአስተምህሮ እና በስብከታቸው ለብሉይ ኪዳን ፍትሀዊ ሆነው አያስተምሩም። ብሉይ ኪዳን ከእነርሱ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም ይላሉ። ነገር ግን እስራኤል እና ቤተክርስቲያን አንዳይነት ከሆኑ የብሉይ ኪዳን ታሪክ እንደ ቤተክርስቲያን ታሪክ ተደርጎ ሊሰበክ እና ተስፋዎቹ እና ማስጠንቀቂያዎቹ ለቤተክርስቲያን በሚገባ ሊነገራት ይገባል።

ይህ የእስራኤል እና የቤተክርስቲያን አንድነት ጥምቀትን ለመረዳት መሰረታዊ የሆነ ነገር ነው።ይህም ደግሞ ኪዳኑ ፣ ተስፋዎቹ እና እስራኤል እና ቤተክርስቲያን ህጻናትን የማጠመቅን ስርዓት ተመሳሳይ መሰረትን ስለሚጋሩ ነው። “የአማኝን ጥምቀት” ይዞ የህጻናትን ጥምቀት ለመተው አንድ ሰው ብሉይ እና አዲስ ኪዳንን ፤ ኪዳናቸውን እና ተስፋቸውን መለየት አለበት። በዚህም በቤተክርስቲያን እና በእስራኤል መካከል ልዩነት ይፈጠራል።

እስካሁን የተነጋገርንበትን ስናስታውስ፤ በቃሉ እውነተኛ ትርጉም መሰረት የተመረጡት ብቻ እስራኤል (የእግዚአብሔር ልዑል) ወይም ቤተክርስቲያን (የተጠሩ) ተብለው ተጠርተዋል። የተቀሩት እውነተኛ እስራኤል ወይም ቤተክርስቲያን አይደሉም (ሮም 2:28-29, ሮሜ 9:6-8)። እነርሱ እስራኤል ወይም ቤተክርስቲያን የሚለው ስም የኖራቸው በውጪያዊ ማንነታቸው ከትውልዳቸው ጀምሮ ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር በመሆናቸው ነው።

ተፈጥሯዊ ውልደት እውነተኛ አይሁዳዊ ወይም የቤተክርስቲያን አባል አያደርግም። መጥምቁ ዩሀንስ እንዳለው “እግዚአብሔር ለአብርሀም ልጆች ከእነዚህ ድንጋዮች ማስነሳት አይችልምን” (ማቴ 3:9)። ስለዚህ አንድ ሰው እውነተኛ እስራኤላዊ ለመሆን ከተስፋው ቃል መወለድ እና ከእግዚአብሔር መወለድ ይኖርበታል። ከእውነተኛ እስራኤላዊያንም፤ አይሁዳዊም ሆነ አህዛብ መንፈሳዊ የአብርሃም ዘርን በተስፋው ሃይል እግዚአብሔር አስነስቷል ።አንተ የአብርሀም ዘር ነህ?

## ቤተክርስቲያን እና መንግስት

አሁን አሁን ስለክርስቶስ መንግስት ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ንግግር በዝቷል። በተደጋጋሚ የክርስቶስን ዳግም መምጣት ከምድር ጋር የተያይዘ አድርገው ይናገራሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚመጣው መንግስት ይህንን ይመስላል ብሎ አያስተምርም። የክርስቶስ መንግስት ከምንም በላይ *ሰማያዊ* መንግስት ነው (ማቴ 26:29, ዩሀንስ 6:15, ዩሀንስ 18:36) ። ባህሪው መንፈሳዊ እና ሰማያዊ ነው (ዩሀንስ 3:3, 5: ሉቃስ 17:20-21)። መረዳቱም ሰማያዊ ነው (ራዕ 12:10)።

ስለክርስቶስ መንግስት ስንነጋገር ስለጸጋው መንግስት እየተነጋገርን ነው፣ ነገሮች ሁሉ የሚታዘዙት እና የሚተዳደሩት በእርሱ ባለጸጋ እና አዳኝ ኃይል ነው። በእርግጥም ሁሉም ነገር በሉዓልዊነቱ እና በሁሉን ቻይ

ኃይሉ ለሚመራው ለክርስቶስ መንግስት የተገባ ነው (ማቴ 28:28, ፊሊ 2:9-11)። መንግስቱ የጸጋ ስፍራ ነው፤ የጸጋ ስፍራ ብለን የምንጠራውም መንግስት አሁን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው። መንግስቱ ከቤተክርስቲያን የተለየ አይደለም ነገር ግን ቤተክርስቲያን እራሷ መንግስቱ ነች። በእርሷ ብቻ ጸጋ መሪ ነው። ጸጋ ከቤተክርስቲያን ገደብ ውጪ ወዴትም ሊፈስ አይችልም ፤ የጋራ ጸጋም የሚባል ነገር የለም።

በቤተክርስቲያን ውስጥ በጸጋው አማካኝነት የክርስቶስ መንግስት ዜግነት ይገኛል። በዚህ መንግስት ስዎች የሚሰበሰቡት በእግዚአብሔር ጸጋ እና መንፈስ ነው (ቆላ 1:13)። በዚህም መንግስት በእርሱ የጸጋ ኃይል ይጠበቃሉ። እንደ መንግስቱ አካልነታቸው የክርስቶስ መንግስት ሙሉ በሙሉ ወደፍጻሜው ሲደረስ ያኔ ወደ መንግስተ ሰማይ እና ክብሩ ይለወጣሉ። እኛም ስለሚመጣው መንግስት የጌታችንን ጸሎት ስንጸልይ እናገኘዋለን ። በማቴዎስ 16:19 ላይ ክርስቶስ የሚናገረው ስለዚህ መንግስት ነው። ይህ መንግስት ቅጥሩ መዳን መግቢያውም ምስጋና ነው። ይህንንም ኢሳይያስ አስቀድሞ ተንብዮታል (ኢሳ 60:18) ።

ይህ መንግስት በዚህ አለም ውስጥ ይገኛል ነገር ግን በጠላት የተያዘ ግዛት ላይ ያለ ምሽግ በመሆኑ መንግስቱ በጦርነት ውስጥ ያለ ሠራዊትን እና የተከበበች ከተማን ይመስላል (ኢሳ 1:8, ማቴ 16:18, ራዕ 20:9) ። በዚህ አለም ያለችው ቤተክርስቲያን ጦርነት ላይ በመሆኗ ሁልጊዜም ተዋጊ ቤተክርስቲያን መሆኗን ትቀጥላለች።

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መንግስት ስለሆነች መንግቷም ሰማያዊ እና መንፈሳዊ ስለሆነ የዚህ አለም የጦር መሳሪያዎች አያስፈልጓትም (መጠቀምም የለባትም)። አንዳንዶች እንደሚመኙት ቤተክርስቲያን የአለምን ግዛት ሁሉ መቆጣጠር ብትችል እንኳን የክርስቶስን መንግስት በጥቂቱ እንኳን ማስፋት አትችልም። መንግስቱ የሚሰፋው በተረጋጋ እና በጥቂት የወንጌል ቃል ነው። አስቀድሞው የዚህ አለም እና የሰይጣን አገልጋይ የነበሩ ሰዎች በጣፋጭ ንግግር ወደ ክርስቶስ ህብረት ይጠራሉ። ከጻድቃንም ጋር ዜግነትን በማግኘት የእምነት ቤተሰብ አባል ይሆናሉ (ኤፌ 2:19)። ይህ በመስቀሉ አስቀድሞ የተገኘ የክርስቶስ መንግስት ታላቅ ድል ነው (ቆላ 2:15)። የትኛውም የምድር ኃይል፣ በሀጥያት ያሉ የዚህ መንግስት ዜጎች እንኳን፣ የክርስቶስን መንግስቱ ድልነሺነት ሊቋቋሙ አይችሉም (ማቴ 16:18)።

እንደዚህ አይነት የክርስቶስ መንግስት ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ ባህሪ ስላለው ማንም እንደ አዲስ ካልተወለደ በቀር ሊያየው አይችልም። ይህ መንግስት በጸጋ እና በወንጌል ለተጠሩት ነገር ግን ገና ላልከበሩት ሁሉ የተዘጋጀ ነው። በዚህ መንግስት በክርስቶስ በኩል እነርሱ ከአሸናፊዎች ይበልጣሉ።

ስለዚህ የዚህ ታላቅ መንግስት ዜጋ ናችሁ?

## የቤተክርስቲያን ተዋጊዎች

የእግዚአብሔር ምርጦች ቤተክርስቲያን ሦስት የተለያዩ የህዝብ ቡድኖች አሏት፤ በመጨረሻም እነዚህ ሁሉ በክርስቶስ አንድ ወደ መሆን ይመጣሉ። የመጀመሪያው በዘመናት መካከል በምድር ያሉ የተመረጡት ህዝቦች ናቸው (ኤፌ 1:10)። እነርሱ *የቤተክርስቲያን ተዋጊዎች* ይባላሉ።

ሁለተኛ መልካሙን ገድል የተጋደሉ እና ድርሻቸውን ጨርሰው ወደ ክብር የሄዱት ናቸው። እነርሱ *ድል ነሺ* ቤተክርስቲያኖች ይባላሉ (2ኛ ጢሞ 4:7-8, ራዕይ 6:10) ።

በመጨረሻ ለቤተክርስቲያን በመመረጥ የተወሰኑት አሉ እነርሱም ደግሞ ገና ያልተወለዱ እና ወደ ንሰሐ እና እምነት ገና ያልመጡት ናቸው። እነርሱን ደግሞ *የተደበቁ ወይም የሚመጡ* ቤተክርስቲያን ብለን እንጠራቸዋለን (2ኛ ጴጥ 3:9) ።

በምድር ያለው ቤተክርስቲያን ተዋጊዋ ቤተክርስቲያን የሚልው ስም በትክክል ይወክለዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዋጊ ተብሎ ተጠቅሷል (ሙን 6:4, 10, ራዕይ 19:11-16)። ጥሪውም ውጊያ ነው (2ኛ ቆሮ 10:3-4, 1ኛ ጢሞ 1:18, 2ኛ ጢሞ 2:4)። አባላቱም የእግዚአብሔርን የጦር እቃ ለብሰዋል (ኤፌ 6:10-18)። መሪውም ክርስቶስ ነው (ዕብ 2:10, ራዕይ 19:11-16)።

የጦር *ተዋጊ* የሚለው ስም ቤተክርስቲያን ለመዋጋት የተዘጋጀች መሆኑን ብቻ ሳይሆን ሁልግዜም ውጊያ ውስጥ እንዳለች ያመለክታል። ይህም ደግሞ የቤተክርስቲያን ሙሉ ጥሪ እና ህይወት ነው (2ኛ ጢሞ 2:4) ። ይህ ውጊያ እኛ ይህንን ህይወት እስከምንጨርስ እና ወደ ክርስቶስ ለክብር እስከምንሄድ ድረስ አይቆምም (ቁጥ 7-8)።

የቤተክርስቲያን ውጊያ መመከት ብቻ አይደለም። ቤተክርስቲያን እና ምዕመኗ ወደ ውጊያው የተጠሩት ወደ ጠላት ሰፈር እንዲሄዱ እና እንድያጠቁም ጭምር ነው። በ2ኛ ቆሮንቶስ 10:4-5 “(የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን” የሚለው በእርግጥም ስለዚህ ይናገራል። ይህ ክፍል ውጊያው መንፈሳዊ እንደሆነ ይናገራል።

ጠላት ወይም ክፉ (ኤፌ 6:12)፣ የጦር እቃ (ቁጥ 13-17)፣ እና ውጊያው መንፈሳዊ መሆኑ የውጊያው ፈተና ቀላል ወይንም እንዲሁ መፈጸም የሚችል እንደሆነ አያመላክትም።

ጠላቶቻችን ሰይጣን ፣ አለም እና የገዛ ሀጥያተኛ ስጋችን ናቸው። ሀጥያት እና ፈተና ሁሉ በእነዚህ ውስጥ ተሸፍነው እናገኛቸዋለን አንዳንድ ጊዜ በእራሳችን ውስጥ ሀጥያት ይደበቃል። ይህ ውጊያ ከፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያው ወይም ወታደራዊ ኃይል ጋር የምንዋጋው አይደለም። ውጊያውን የምንዋጋው በእምነት እና በእግዚአብሔር ቃል ነው (ኤፌ 6:13-17, 1ኛ ዩሀንስ 5:4)።

ይህ ውጊያ ሀሰት ከሆኑ ሀሳቦች እና ከስህተት ትምህርቶች ብሎም ከክፋት እና ከፈተና በመጻረር የሚደረግ የአእምሮ እና የነፍስ ውጊያ ነው (2ኛ ቆሮ 10:4-5, ያዕቆብ 4:7)። ይህ ውጊያ ከእግዚአብሔር እና እግዚአብሔርን ከማወቅ ጋር የማይስማማ ማንኛውም ነገር ላይ የሚደረግ ውጊያ ነው።

ነገር ግን በውጊያ ውስጥ *ለድል* አንዋጋም። የምንዋጋው ድሉን በክርስቶስ ኢየሱስ መከራ፣ ሞት፣ ትንሳኤ እና እርገት *እንደተቀበለ* ሰው እና አስቀድሞ *በእጁ እንደያዘ* ሰው ነው። በሚወደን በእርሱ ደግሞ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን (ሮሜ 8:17) ። ግን መዋጋታችን እንዳለ ነው። በዚህ ስፍራ ያለነው እራሳችንን ለማስደሰት ሳይሆን ወታደሮች ልንሆን ነው (2ኛ ጢሞ 2:3-4)።

ስለዚህ እየተዋጋህ ነው ወይንስ እየተጫወትክ ነው?

## ድልነሺ ቤተክርስቲያን

*ድል ነሺ ቤተክርስቲያን* የሚለው ስም ከመከራው እና ከስራው ጨርሶ በክብር ውስጥ እያረፈ ያለውን ቤተክርስቲያን ይወክላል። በድል ነሺው ቤተክርስቲያን ውስጥ የተካተቱት ሰዎች መልካሙን ገድል ተጋድሏል ፣ ውጊያውን ጨርሷል ደግሞም ከጌታ የጽድቅን አክሊል የተቀበሉ ናቸው (2ኛ ጢሞ 4:7-8)።

ስለ *ድል ነሺዋ ቤተክርስቲያን* በመነጋገራችን በምድር በእምነት ጦርሜዳ ላይ ያለችው ቤተክርስቲያን ድል ነሺ አይደለችም ለማለት እንዳልሆነ መረዳት አለብን። አሁንም ቢሆን በውጊያው ውስጥ የሚገኙት፣ መከራ እና ችግር የሚቀበሉት ሁሉ በወደዳቸው በእርሱ ከአሸናፊዎች ሁሉ ይበልጣሉ (ሮሜ 8: 37)። *ክርስቶስ* በጠላቶቹ ሞት ፣ ሀጥያት፣ እና ሰይጣን ላይ ሙሉ በሙሉም ድል ነስቷል (ሉቃስ 10:17-18, ኤፌ 4:8, ቆላ 2:15)። እኛም በክርስቶስ ድል ነሺዎች *ነን*።

ይህ አትኩሮት ሊሰጠው ይገባል። ክርስቶስ የነገስታት ንጉስ ተብሎ እስኪከብር *እየጠበቀ* አይደለም። እርሱ በአብ ቀኝ በክብር እና በግርማ ነግሷልና (ዕብ 2:9) በጠላቶቹም መካከል ሆኖ ይገዛል (መዝ 110:2) ። ውጊያውን እየተዋጋን ቢሆንም ከእርሱ ጋር ድሉን በማግኘታችን የምንዋጋው የተሸነፈውን ጠላታችን ነው። የቀረን ነገር ቢኖር በወታደራዊ ቋንቋ “ነገሮችን ማጠናቀቅ (mopping up operations)” ነው። መንግስታችን አሸንፏል። ስለዚህ የቀረን በአብ መሰብሰብ ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ 15:24)።

የክርስቶስ ድል መንሳት ክፉ ሰዎች የበለጠ እየከፉ በመጡበት እና አለም ሁሉ በጨለማ በተጣለችበት ጊዜ እንኳን ይቀጥላል ። ክፉዎችም ፍጹም የተሸነፉ ከመሆናቸው የተነሳ ክርስቶስ እነርሱን መግዛት ብቻ ሳይሆን በሉዓላዊነቱ ለእራሱ አላማ ያጠቀምባቸዋል።

በክብር ያሉትን ጻድቃን ድልነሺ ቤተክርስቲያን ብለን የምንጠራው ድሉን *ማጣጣም/ የድሉን ሀሴት* ስለጀመሩት ነው። በምድር ያሉ ቅዱሳን አሁንም በፈተና እያለፉ ቢሆንም እነዚያ ግን ከስራቸው ሁሉ አርፈዋል (ራዕይ 14:13) ፤ ደግሞ “ከዚያ ከቶ አይወጣም” (ራዕይ 3:12) ተብሎ እንደተጻፈ ከዚያም ከቶ አይወጡም። ምድራዊ ተዋጊዎች ግን አሁንም የእምነትን የጦር እቃ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በመንግስተ ሰማይ ያሉት ቅዱሳን ደግሞ ይህንን አውልቀውት ነጭ ልብስን ለብሰዋል (ቁጥ 5)። እነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ የጠላቶቻቸውን ፊት አያዩም፤ የበጉን መልክ ብቻ ያያሉ (ራዕ 22:4)። እምባቸው ታብሷል ከእንግዲህም ወዲህ ሞት ወይንም ሀዘን ወይንም ለቅሶ ወይንም ህመም በዚያ የለባቸውም (ራዕይ 21:4)።

ቤተክርስቲያን በመንግስተ ሰማይ ያለች ድልነሺ መሆኗን ማሰባችን መልካም ነው። የእነርሱ ክብር ድል ነሺነቱ የእኛም እንደሆነ ያመላክተናል። ከጥቂት ጊዜ በኃላ እነርሱ ባሉበት እንኖራለን ከእነርሱ ጋርም እናርፋለን። ያሃ ቀን እንዴተ ታላቅ ነው! እኛም እዚህ ስንጠብቅ እነርሱ በመንግስተ ሰማይ እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን እንዲበቀልልን ይለምናሉ እግዚአብሔርም ይህንን ጸሎት ይሰማል (ራዕ 6:9-11) ።

በሁለት ረገዶች ብቻ በመንግስተሰማይ ያሉ ቅዱሳን ድል ነሺነታቸው አልተጠናቀቀም። የመጀመሪያው አካላቸው ገና ከሞት አልመነሳቱ ነው። ስለዚህም መንግስተ ሰማያዊ ክብርን በነፍስ እና በከበረ ስጋ ገና አላጣጣሙትም። ሁለተኛ የተቀረችው ቤተክርስቲያን ገና አልከበረችም ቁጥር 9-11 ክብሩ ያለእኛ የተሟላ እንዳልሆነ ይናገራል። የክርስቶስ ሙሉ ሰውነት በአንድ ተጠቅልሎ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይሆናል ይህም ቀን እስከሚመጣ ድረስ ድልነሺዋ ቤተክርስቲያን መጠበቅ አለባት።

በእግዚአብሔር ድንጋጌ ወይንም ውሳኔ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም እና ግዛት፣ ደግሞ በመንፈስ ሉዓላዊ ስራ የዚህ ቀን መምጣት የተረጋገጠ ተስፋ ነው። የቤተክርስቲያንም ተዋጊዎች ይጠብቃሉ ደግሞም ይጸልያሉ ድልነሺ ቤተክርስቲያንም ደግሞ ታርፋለች፣ ትጠብቃለች፣ ድግሞ ትጸልያለች በቅርብም ሁላችን አንድ እንሆናለን።

## ያልተወለደችው ቤተክርስቲያን

የክርስቶስ አካል እና የማትታየው ቤተክርስቲያን አባል የሆኑት በመንግስተ ሰማይ የከበሩት እና በዚህ ምድር የሚኖሩት እና የዳኑት ብቻ አይደሉም። በእግዚአብሔር የተመረጡ ገና ያልተወለዱ እና ያልዳኑ ሰዎችም አሉ። እነርሱም በመመረጥ እና በመስቀል ላይ በፈሰሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የቤተክርስቲያን ናቸው ነገር ግን በአዲስ ውልደት እና በእምነት ግን ገና አካል አልሆኑም።

ክርስቶስ አብ ስለሰጠው ሰዎች ብዙ ጊዜ ሲናገር እንመለከታለን። እነዚህም ደግሞ ገና ያልዳኑት ናቸው (ዩሀንስ 6:37, 39, ዩሀንስ 10:16, 29, ዩሀንስ 17:2) ። እነርሱ አለም ከመፈጠሯ በፊት ለእርሱ የተሰጡ ናቸው (ዩሀንስ 17:6, ኤፌ 1:4) ፣እርሱም ስለእነርሱ ይጸልያል (ዩሀንስ 17:9) ደግሞም ሞቶላቸዋል (ቁጥ 13:19) ። ስለዚህም ድነታቸው እና በቤተክርስቲያን ያላቸው ስፍራ የተረጋገጠ ነው።

ስለእነዚህ ሰዎች ሲባል ክርስቶስ መምጣቱን ያዘገየዋል ። በእግዚአብሔርም ፈቃድ እንደገና እስከሚመጣ ድረስ ሁሉም መዳን እና እንደ አዲስ መወለድ አለባቸው። በ2ኛ ጴጥሮስ 3:9 ይህንን እንመለከታለን። አብዛኞቹ አንዳቸውም እንዳይጠፉ የሚለውን ሀሳብ እግዚአብሔር ድነቱን ለሁሉም ሰው ያለምንም ምርጫ እንዳዘጋጀ ለማስረዳት ይጠቀሙበታል ። ነገር ግን ይህ ክፍል እግዚአብሔር ስለ ሰዎች ሁሉ ድነት ያለውን ፈቃድ የሚናገር ክፍል አይደለም።

ዘጠነኛው ቁጥር በግልጽ ስለ*እኛ* ይናገራል። የክርስቶስ ታላቅ መከራ (ምህረቱ) *ለእኛ*ነው። የእርሱ ምህረት ለእኛ ነው ማለት አንዳችንም እንዳንጠፋ እና ወደ ንሰሀ እንድመጣ ይፈልጋል ማለት ነው። እኛ የሚለው ቃል በግልጽ በሁለቱ ክፍሎች ላይ ተቀምጧል እጅግ የሚገርመው ነገር ደግሞ እኛ የሚለውን ቃል ያስገባው ወደ ንስሐ ገና ያልመጡትን ሰዎች ያካተተ ነው። እነርሱ አካላችን ናቸው ማለትም "በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ" (2ኛ ጴጥ 1:1) ደግሞም "ለሕይወት

እና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነው ነገር ሁሉ” የተሰጣቸው እና “እነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋ” የተሰጣቸው ናቸው (ቁጥ 3-4)።

እነዚህ ሰዎች ይህ ሁሉ በረከት በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ስለተመረጡ እና በእርሱ በኩል በዋጋ ስለተገዙ እንጂ በንስሀ እና በእምነት እነዚህን ነገሮች ስለተቀበሉ እንዳልሆነ እናውቃለን። ሆኖም ግን መመረጥ እና የክርስቶስ ደም እጅግ ታላቅ ማረጋገጫ ናቸው እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ አሏቸው ብንል እና የእኛ አካል እንደሆኑ እንረዳለን።

በእርግጥም በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ይህንን ክፍል መረዳት እንችላለን። ይህ ክፍል እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲድን ስላለው ፍላጎት ይናገራል በማለት ክፍሉን ትርጉም የለሽ ወይንም አወዛጋቢ ማድረግ የለብንም። ክርስቶስ እንደሚመጣ ቃል ገብቶልናል (2ኛ ጴጥ 3:4, 10) ደግሞም ሁሉም ወደ ድህነት እስከሚመጡ ድረስ ይጠብቃል (ቁጥ 9)። በዚህም ምክኒያት እግዚአብሔር እና ምህረቱ ይጠብቋቸዋል።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለሁሉም ድህነት ያለምንም ምርጫ የሚጠብቅ ከሆነ ክርስቶስ መቼም አይመጣ ሰው ሁሉም ያለምንም ቀሪ መቼም ወደ ንሰሀ ሊመጣ አይችልም። የሚጠፉ አሉ ደግሞም ሁሌ ይኖራሉ።

ስለዚህ የክርስቶስ መምጣት ከተመረጠችው ቤተክርስቲያን መዳን “ሌሎች በጎች” ከመምጣት ጋር የተያያዘ ነው። ሁሉም ወደ ንሰሀ በእግዚአብሔር ጸጋ ከመጡ በኋላ በእርግጠኝነት ክርስቶስ እንደሚመጣ እናውቃለን።

እስከዚያ መጨረሻ ድረስ በሰማይ ያለችው ቤተክርስቲያን በጸሎት ትተጋለች (ራዕይ 6:10-11) በምድር ያለችው ቤተክርስቲያንም ከእነርሱ ጋር ትተባበራለች (ራዕይ 22፡20) በዚህም እግዚአብሔር የመረጣቸውን ነገር ግን ባለማመን እና በጨለማ ያሉትን ህዝቦቹን እንዲሰበስብ ትለምናለች።

## የቤተክርስቲያን መመረጥ

በመመረጥ እግዚአብሔር ግለሰብን ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያንን፣ ማለትም የቤተክርስቲያን እና የክርስቶስ አካል ይሆን አንድ እንዳንዱ ሰው ተመርጧል (መዝ 132:13 ከዕብ 12:22, 1ኛ ጴጥ 2:9 ጋር ያነጻጽሩ) ። እንዴት የከበረ እውነት ነው!

መመረጥ አምባ ገነናዊ ወይንም ደግሞ እንደ ሎቶሪ እጣ አይደለም። አላማ ያለው እና በቤተክርስቲያን መመረጥ ውስጥም ይህ አላማ በግልጽ የሚታይ ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተክርስቲያን እንደ ህንጻ ወይም ቤት መመሰሏ ይህንን እንድንረዳ የበለጠ ይጠቅመናል። እርሱ እንደ አናጺ የሚጠቀማቸውን

እቃዎች ይመርጣል። ስለዚህም እግዚአብሔር ለዚያ መንፈሳዊ ስፍራ እና ለክርስቶስ ኢየሱስ አካል እንዲስማማ አድርጎ እያንዳንዱን ሰው መርጧል(ኤፌ 2:20-22, 1ኛ ጴጥ 2:5)።

አናጢ አስቀድሞ ሳያቅድ ቤቱን እንደማይሰራ እንደዚሁም እግዚአብሔር  በዚሁ መልክ ቤተክርስቲያን ይገነባታል ። በዚያ ቤት ውስጥ ማን ቦታ ሊኖረው እንደሚገባ እና ምን አይነት ቦታ ሊኖረው እንደሚችል የሚወስነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው እንጂ የሰው ፈቃድ አይደለም። ድንጋይ እና ጣውላ ህንጻው ላይ የሚኖራቸው ስፍራ ምን እንደሆነ እንደማይወስኑ ሰዎችም በእራሳቸው ምርጫ በእግዚአብሔር ቤት ምን አይነት ቦታ ሊኖራቸው እንደሚችል መወሰን አይችሉም።

እግዚአብሔር ለቤቱ መሳሪያን እየፈለገ አያሰበስብም ነገር ግን በጥንቃቄ መንፈሳዊ መኖሪያውን ከዘላለም ጀምሮ በመወሰን ቤቱን ለመስራት የሚፈልገውን ነገር “ያዝዛል”። በሰው ግላዊ ህይወት ውስጥ የሚፈጠሩ ክንዋኔዎች ሁሉ አስቀድሞ በመወሰን፤ እግዚአብሔር በምርጫ እያንዳንዱ ሰው እንዴት እንደሚቀረጽ እና እርሱ ያዘጋጀለትን ትክክለኛ ቦታ እንዴት ማግኘት እንዳለበት ይወስናል (ኤር 1:5)።

ደግሞም ይህ ቤት በተረጋገጠ እና ጽኑ መሰረት ላይ የሚገነባ፣ ለዘመናትም የሚዘልቅ መሆን ስላለበት እግዚአብሔር ክርስቶስን መሰረት እና የማዕዘን ድንጋይ አድርጎ አቁሞታል (1ኛ ጴጥ 2:6)። እያንዳንዱ ቤትም ከክርስቶስ ጋር እንዲጣበቅ ተቀርጾ ተሰርቷል።

የተመረጡት ሁሉ ሲሰበሰቡ እና ሲከብሩ ይህ መንፈሳዊ ቤት የእግዚአብሔር የእራሱ ማደሪያ ይሆናል (ኤፌ 2:22)። ሁሉም ክብር እና ውበት የእርሱ ይሆናል። እርሱም ብቻውን የቤቱ አናጺ፣ ቀራጺ እና ዋና ነዋሪም ነው።

ከዚህም በላይ የቤተክርስቲያን መመረጥ የቤተክርስቲያንን አንድነት ይወስናል ደግሞም ያረጋግጣል (ዩሀንስ 10:16, ኤፌ 1:9-10)። የተመረጡት ሰዎች በእርሱ በኩል ተመርጠዋልና ክርስቶስ እነርሱን ሁሉ አንድ ያደርጋቸዋል (ቁጥ. 4)። ጳውሎስም ኤፌ 4:3 ላይ አንድነት እንዲኖረን እና አንድነታችንንም እንድንጠብቀው ይነግረናል ። ይህ አንድነት በክርስቶስ ኢየሱስ መመረጣችን ላይ እና በእርሱ መሰብሰባችን ላይ ያተኮረ ነው።

መመረጣችንም ደግሞ የቤተክርስቲያንን ቅድስና ያመላክታል (ኤፌ 1:4)። እኛ የተመረጥነው *ቅዱስ ስለሆንን* ሳይሆን *ቅዱስ እንድንሆን* ነው። ቅድስና አስፈላጊ የሆነው ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ በመሆኗ

ነው። እግዚአብሔር በመንፈሱ በቆሸሸ እና ቅዱስ ባልሆነ ስፍራ አይኖርም። ስለዚህም የህንጻውን ምሳሌ አንድ ጊዜ በመጠቀም መመረጥ (እቅዱ) የህንጻው ውበት እንደሆነ ያረጋግጥልናል።

ቤተክርስቲያንን የመሰብሰብ እና የመገንባት ስራ አላለቀም። የመጨረሻው ክብር የተሰጠው አሁንም ለማናያቸው ነገሮች ነው። አሁን የምናያት ቤተክርስቲያን ነገ ላይ ይህንን አትመስልም። ቤተክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ከተገነባች ወዲህ የተመረጡትን ከጨለማ ያወጣው እና ወደ ታላቅ ብርሀን ያመጣውን የእርሱን ምስጋናዎች ትገልጣለች። ይህም ደግሞ እንደ ዘላለማዊ ቅርስ ለክብሩ፣ ለጥበቡ እና ለጸጋው ይቀርባል።

## የቤተክርስቲያን ቅድስና

ስለቤተክርስቲያን ቅድስና ስናነሳ ስለቤተክርስቲያን አንድ ባህሪ እየተነጋገርን ነው። አንድነቷ ፣ አጥቃላይነቷ ፣ እና ተልኮአዊነቷም ሌሎች ባህሪያቶቿ ናቸው።

የቤተክርስቲያን ቅድስና ማለት እንደ ክርስቶስ አካልነቷ ከክርስቶስ ጋር ባላት ህብረት የተቀበለችው ቅድስና ማለታችን ነው። ቤተክርስቲያን የእራሷ ቅድስና የላትምና የቤተክርስቲያን ቅድስና የክርስቶስ የእራሱ ቅድስና ነው (1ኛ ቆሮ 1:2, 1ኛ ቆሮ 3:16-17, 1ኛ ጴጥ 2:9)።

ይህ ቅድስና የቤተክርስቲያን መርህ መሰረት ሲሆን ቅድስናም ለቤተክርስቲያን የተገባው ለእያንዳንዱ የተመረጠ አካል በክርስቶስ ሞት የተገዛ በመሆኑ ነው። ማለትም እያንዳንዱ ሰው ክርስቶስ አካሉ እንዲሆን በእምነት ወደ እራሱ ሲያመጣው እና ሲያነጻው ቅድስና ተሰጦታል።

ይህንን የቤተክርስቲያን ቅድስና በተለያዩ መንገዶች እንመለከታለን። ቅድስና ማለት “መለየት” እንደሆነ በመረዳት የቤተክርስቲያን ቅድስና የሚገለጠው ቤተክርስቲያን ከዚህ አለም በመለየቷ ነው።የተለየ መንግስት ፣ ንጉስ፣ ህግ ፣ ባህል እና ተስፋ ያለባት ናት (1ኛ ጴጥ 2:9)።

በእርግጥም ቅድስና ቤተክርስቲያን በአለም ያላት ድንበር ነው። ቤተክርስቲያን ምንም አይነት ፖለቲካዊ ፣ የዘር ወይንም የቋንቋም ገደብ የላትም። ቅድስና ቤተክርስቲያንን ከአለም የሚለያት ብቸኛ ገደብ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ያልሆኑን ሁሉ ከምናያት ቤተክርስቲያን ማስወጣት ደግሞም በውጪ እንዲቀሩ መሆን አለባቸው።

ቅድስናም ቤተክርስቲያን በተቃርኖ የምትቀጥልበት ምክኒያት ነው። ሁልጊዜም ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ ከእራሷን አባላቶች  (በቤተክርስቲያን) ውስጥ ካሉት ግብዞች እና ስጋዊያንን በመኮነን ክፋትን እና ሀጥያት ለተላበሰው ምድር ትመሰክራለች።

ቤተክርስቲያን እና አባሎቿ ለመቀደስ ሲጥሩ በአለም እና በቤተክርስቲያን መካከል ሁልጊዜም ተቃርኖ ይኖራል (ዩሀንስ 15:18-20)። ቤተክርስቲያንም የእራሷ ቅድስና የላትም። ቤተክርስቲያን ላይ የሚያበራው ቅድስና የእራሱ የእግዚአብሔር ቅድስና ነው (1ኛ ጴጥ 1:15-16)። እግዚአብሔርን የማይፈሩ የሚጠሉት እና የሚቃወሙት ይህንን ነው (ዩሀንስ 3:19, ሮሜ 8:7)።

ይህ የእግዚአብሔር ቅድስና በበአባሎቿ መቀደስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይገለጣል። እነርሱ "ቅዱሳን" የሆኑት በጸጋ ሲሆን የእግዚአብሔርም ቅድስና በጸጋ ስለተሰጣቸው እርሱ ቅዱስ እንደሆነ እነርሱም ቅዱስ ይባላሉ። ቅድስና ግልጽ የሚሆነው ከክፉዎች እና ከክፋት ሲለዩ ነው (2ኛ ቆሮ 6:14-7:1)።

በዚህም በአማኞች እና በምትታየው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሀጥያት የለም ለማለት አይደለም። እንዲያውም በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሥጋዊነት እና የላቀ ሀጥያት በምዕመኗ ውስጥ አለ። በዚህም ልባችን በጥልቁ ያዝናል (መዝ 51:3, መዝ 119:53, 136)። ስለዚህም ነው የቤተክርስቲያን ቅድስና የእምነት እንጂ የእይታ ያልሆነው። ምንም ያህል በዚህ አለም ብትሆንም ቤተክርስቲያን ቅዱስ እንደሆነች እናምናለን ።

የምናየውን ብቻ ከሄድን በምዕመኗ ውስጥ ብዙ ሀጥያትን ስለምንመለከት በእርግጠኝነት በቤተክርስቲያን ተስፋ እንቆርጣለን። ነገር ግን የጻድቃን ቅዱስ ህብረት እንደሆነ በማመን በክርስቶስ ፊት "እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት" ሆና ትቀርባለች (ኤፌ 5:27)።

ስለዚህም ደግሞ ያለቅድስና አንድም ሰው ጌታን ማየት አይችልምና በጸሎት እና በተግባራችን እንደ ቤተክርስቲያን አባላቶች ቅድስናን እንከታተል (ዕብ 12:14)።

## የቤተክርስቲያን አለማቀፋዊነት

የሐዋሪያቱ የእምነት አዋጅ "ቅዱስ አለማቀፋዊ ቤተክርስቲያን" ሲል ስለ ሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እየተናገረ አይደለም። ሮም ቅዱስ አለማቀፍ ቤተክርስቲያን እንደሆነች ብታምንም ቤተክርስቲያኗ ቅዱስም ፣ አለማቀፋዊም ፣ የክርስቶስ ኢየሱስም ቤተክርስቲያን ያልሆነ የሀሰት ቤተክርስቲያን ነው።

*ካቶሊክ* የሚለው ስም "አለም አቀፋዊ" የሚል እውነተኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን መገለጫ ትርጉም ነው። ይህንን ቃል ለሮማዊያኖች ብለን አንተወውም።

ቤተክርስቲያን አለማቀፋዊ መሆኗ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ክፍሎች ላይ ተጽፏል። ራዕይ ምዕራፍ 7 ቁጥር 9 ቤተክርስቲያን አለማቀፋዊ መሆኗን ይናገራል። እጅግ ብዙ ክፍሎችም ማንም በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የምትቀርበውን ቤተክርስቲያን የህዝቧን ፣ ሀገሯን ፣ ቋንቋዋን እና ትውልዷን ቁጥር እንደማያውቅ ይናገራሉ።

የቤተክርስቲያን አለማቀፋዊነት ከብዙ ህዝቦች መካከል በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ የተመረጡ ህዝቦች መሆናቸውን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ህዝቡን እንደሚሰበስብ ያመላክታል። ስለዚህም ካቶሊካዊነት እኛ ከአብርሐም ከይሳሐቅ እና ከያዕቆብ ጋር በእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግስት ውስጥ እንደምንሆን ያረጋግጥልናል (ማቴ 8:11)። በራዕይ 6:11 ላይ እንደተገለጸው  አማኞች፣ ጓድ አገልጋዮች እና የሰማዕታት ወንድሞች ተብለው ይቆጠራሉ።

በስተመጨረሻም የቤተክርስቲያን አለማቀፋዊነት ብዙ አይነት ህዝቦች የቤተክርስቲያን አባል እንደሆኑ ያሳያል። ሀብታም ወይንም ደሀ ፣ ታላቅ እና ታናሽ ፣ ወጣት እና ሽማግሌ ፣ አገልጋይ እና ገዢ ፣ ወንድ እና ሴት ሁሉ አባል ነው። ቤተክርስቲያንም ለእነዚህ ሁሉ ስፍራ አላት።

ቃሉም በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2 ስለሰው ሁሉ እንድንጸልይ ሲያዝዘን ይህንን ይነግረናል (ቁጥ 1-2)። ሁሉም የሚለው ቃል "ያለ ምንም ልዩነት" ማለት አይደለም። እንደዚያ ቢሆን ስለሁሉም ሰው በዚያ መንገድ መጸለይ ከባድ ይሆን ነበር። ነገር ግን ቃሉ በተለያየ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች "ለሁሉም አይነት ሰው" በማለት አመላክቷል። እኛ ለሁሉም አይነት ሰው ልንጸልይ ተጠርተናል ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው በመሞቱ ሁሉን ሊያድን ፈቅዷል (ቁጥ 4-6)።

ያዕቆብ ቤተክርስቲያን ለሃብታሙ አድሎ በማድረግ ድሃውን መግፋቷን ሲወቅስ በአዕምሮው ውስጥ የቤተክርስቲያን አለማቀፋዊነትን አስቦ ነው (2:1-9)። እኛም በውጫዊ ማንነታቸው ሌሎችን ክርስቲያኖች ስንገፋ ተመሳሳይ ነገር እናደርጋለን ።

በስረዓት ከተተረጎመ ገላ 3:28 ስለ ካቶሊካዊነት በዚህ መልኩ ይናገራል "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።" ይህ ክፍል ወንድ በሴት ላይ ያለውን ራስነት ወይም ደግሞ ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠውን ስጦታ አይክድም። ነገር ግን ወንድም ሆነ ሴት፣ አይሁዳዊም ሆነ አህዛብ፣ ባሪያም ቢሆን ነጻ በክርስቶስ ኢየሱስ ስላሉ እኩል ክርስቲያኖች እንደሆኑ ለማሳየት ነው ።እነርሱ ሁሉ የአብርሀም መንፈሳዊ ልጆች ናቸው።

የክርስትናን እምነት አንድ ቋንቋ የበለጠ ይገልጠዋል የሚለው እሳቤ ወይንም አንዳንድ ዘሮች ትክክለኛ ክርስትናን አይኖሩም የሚለው እምነት የቤተክርስቲያንን ካቶሊካዊነት ይቃወማል። በተመሳሳይ ዲስፔንሴሽናሊዝም (dispensationalism) *እና የእንግሊዝ እስራኤላዊያን እንደሚያስተምሩት* አንድ ሀገር ወይንም ህዝብ በተለየ መልኩ የእግዚአብሔርን መንግስት ይወክላል ማለትም ትክክል አይደለም።

ስለዚህ በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የትኛውም አይነት መድሎ ወይም ግትርነት አይኑር። እነዚህ ነገሮች ለውጥ አያመጡምና ሰዎች በቆዳቸው ቀለም፣ በቋንቋቸው፣ በዜግነታቸው እና በባህላቸው ምክኒያት መድሎ አይደረግባቸው።

የቤተክርስቲያንን አለማቀፋዊነት በማመን እኛ "አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው" እንላለን (ሮሜ 10:12-13)።

## ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን

የሐዋሪያት የእምነት አዋጅ ስለ "ሐዋሪያዊ" ቤተክርስቲያን ባይናገርም የጥንት የቤተክርስቲያን አዋጆች ስለዚህ ይናገሩ ነበር ። ለምሳሌ የኒቺኒ የእምነት አዋጅ "በአንድ ቅዱስ ካቶሊክ እና ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን አምናለሁ" ይላል። ይህንን ሲል ምን ማለቱ ነው?

የሮም ቤተክርስቲያን እራሱን እንደ ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን የሚቆጥረው ጳጳሳቱ የሐዋሪያቶቹ ተከታይ እንደሆኑ እና ያልተሰበረ የትውልድ ተዋረድ እንዳላቸው ስለሚያምኑ ነው። ነገር ግን እነዚህ ትሩፋቶች እንዳለ እውነተኛ አይደሉም።

አንዳንዶች የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያኖች ደግሞ ሐዋሪያዊ ነን የሚሉት እነርሱ ወደ ሐዋሪያዊ ልምምድ ወይም አስተምህሮ የተመለሱ ስለሆኑ ነው። ይህ እውነት ቢሆንም የኒቅኒ የእምነት አዋጅ ግን ይህንን አይነግረንም።

የኒቂኒ የእምነት አዋጅ እና የተሓድሶ ሥነ መለኮት ወደ ኤፌሶን 2:20 ይመለከታሉ ቤተክርስቲያንን እንዲህ ይገልጣታል “በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው”። ይህ ክፍል በግልጥ በማቴዎስ 16:18 ኢየሱስ ካለው ጋር የገናኛል “በዚች አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለው የገሀነም ደጆችም አይችሏትም።”

የሮም ቤተክርስቲያን ይህ አለት ጴጥሮስ እራሱ ነው ብላ ትወስደዋለች። ስለዚህም ስማቸውን ከ“ጴጥሮስ” (በግሪኩ ፔትሮስ ሲሆን) ትርጓሜውም “አለት” (በግሪክ ፔትራ) - ጋር በማመሳሰል ጳጳሳቱ ሁሉ የጴጥሮስ ተከታይ (ወራሾች) እንደሆኑ ያስባሉ። ነገር ግን የጽሁፉ አገባብ ለእንደዚህ አይነት አፈታት የሚመች እንኳን አይደለም። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ቃላቶች ናቸው። በግሪኩ ጴጥሮስ የሚለው ቃል የተለየ እና ብቻውን የሆነ ትንሺዬ አለት ሲሆን ፔትራ የሚለው ደግሞ ትልቅ ተራራ እና የተራራዎች ሰንሰለት ነው። በእርግጥም ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን በእራሱ በጴጥሮስ ላይ እገነባለሁ እያለ አይደለም (እርሱ የቤተክርስቲያን መሰረት ለመሆን በቂ አይደለም)። ነገር ግን እርሱ ቤተክርስቲያኑን ጴጥሮስ ኢየሱስ ጌታ ነው እና የእግዚአብሔር ልጅ ነው ባለበት ትርጓሜ ላይ መስርቶታል ማለቱ ነው (ማቲ 16:16) ። ይህም ደግሞ ጠንካራ እና የማይሻር መሰረት ነው።

በዚህም አብርሆት ኤፌ 2፡20 በሐዋሪያዊ እና (ትንቢታዊ) አስተምህሮ መሰረት መተርጎም አለበት በሌላ ቋንቋ በመንፈስ አነሳሽነት በተጻፉት የብሉይ እና አዲስ ኪዳን መጽሐፍቶችን በመመስረት ሊተረጎም ይገባል። እነርሱ የቤተክርስቲያን መሰረት ናቸው።

በሐዋሪያት ትምህርት እና አስተምህሮ የተገነባች እንደመሆኗ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ላይ የተመሰረተች ናት። ስለዚህም እርሱ ብቻውን ዋና የማዕዘን ድንጋይ ነው “በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል” (ቁጥ 21)።

በእርግጥም ሁሉም የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ከክርስቶስ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይህ ያመላክታል። ክርስቶስም “መጽሐፍትን መርምሩ” ...... “እነርሱ ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው” ይላል (ዩሀንስ 5:39)። ስለ

ሐዋሪያትም ሁሉ ጠቅልሎ ጳውሎስ “በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና” ይናገራል (1ኛ ቆሮ 2:2)።

ታዲያ እውነተኝእ ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናት። በዚህ መሰረት ላይ የተመሰረተች ቤተክርስቲያን በእርግጥም ትጸናለች የገሀነም ደጆችም አይችሏትም ( ማቴ 16:18)።

ጥቂት ቤተክርስቲያናት ብቻ እውነተኛ ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን ናቸው። አብዛኞቹ የሐዋሪያት ሆነ የነቢያት አስተምህሮ ስለሌላቸው ለገሀንም ኃይል ጥቃት ተጋላጭ ናቸው። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑ በጠንካራ መሰረት ላይ የተመሰረተች እንዲትሆን ይርዳት።

## የቤተክርስቲያን አንድነት

ስለቤተክርስቲያን ቅድስና፣ ካቶሊካዊነት እና ሐዋሪያነት ተነጋገረናል። በተጨማሪ የቤተክርስቲያን ሌላ ባህሪ አለ እርሱም አንድነት ነው።

ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት ስናወራ በዋነኝነት አንድ ቤተክርስቲያን እና አንድ የክርስቶስ ኢየሱስ አካል አለ ማለታችን ነው። ክርስቶስ ከአንድ አካል በላይ የለውምና።

ይህ የቤተክርስቲያን አንድነት ብዙ የሀይማኖት ወገን (ዲኖሚኔሽን)፣ ህብረት እና ቤተክርስቲያናት ስላሉ በግልጽ ሊታይ አይችልም። በተወሰነ መጠን ይህ መለያየት የመጣው በቤተክርስቲያን እና በምዕመኗ ሀጥያተኛነት እና በደካማነቷ ምክኒያት ሲሆን ደግሞም ሌሎች ምክኒያቶች አሉ።

የመልካ ምድራዊ እና የቋንቋ ልዩነቶች በምትታየው ቤተክርስቲያን ውስጥ ፍጹም የሆነ አንድነት እንዳይታይ ያደርጋል። እነዚህ ልዩነቶችም በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር “ባህርም የለም” የሚወገዱ ይሆናል (ራዕይ 21:1)። በአዲሱ ሰማይ የርቀት፣ የቋንቋ ልዩነት ወይንም ሌሎች ነገሮች አይኖሩም በዚህም ደግሞ አማኞችን እርስ በእርስ ሊለያየ የሚችል ነገር የለም።

ነገር ግን በዚህ ምድር የቤተክርስቲያን ሀጥያት እና አባሎቿ በተቋም መልክ አንድነትን ለመፍጠር እንድትችል ከባድ ያደርጉታል። በአስተምህሮ እና በልምድ ያለው ልዩነት የእግዚአብሔርን ቃል ባለመታዘዝ እና መረዳት ባለመቻላችን በሀጥያት ውድቀት የሚመጣ ሲሆን አማኞች እርስ በእርስ እንዲለያዩ ያደርጋል።

ሀጥያት የቤተክርስቲያንን አንድነት ስለሚያጠፋ እና አማኞችን ስለሚከፋፈል እነዚህን ልዩነቶች ክርስቲያኖች ቃሉን በማጥናት እና እርስ በእርስ ሰለሚያምኑባቸው ነገሮች በመነጋገር ማጥበብ አለባቸው። እነርሱ በልዩነት መቻቻል የሚለውን ሀሳብ መቀበል የላቸውም። የቤተክርስቲያንን አንድነት መፍጠር የማይታሰብ በሚሆንበት ሰዓት እንኳን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያላቸውን ህብረት መቼም መልቀቅ የለባቸውም። ከእራሳቸው ብድን ወይንም ወገን ውጪ ሌላ ክርስቲያን እንደሌለ በማሰብ ሌሎችን መግፋት የለባቸውም።

ሆኖም ግን አማኞች እውነትን በመግፋት አንድነትን መፈለግ የለባቸውም። እነርሱ እውነትን ሊገዟት እንጂ እውነትን ሊሸጡ አልቆሙምና (ምሳኤ 23:23)። ኢኪዩሚኒዝምም በዚህ ዙሪያ ይሳሳታል። ይህ አስተሳሰብ እውነታን ሀሰተኛ አንድነትን በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚያመጣዝብርቅርቅ ስሌት ይሸጣል።

ስለ አንድነት መጸለይ እና አንድነትን በመፈለግ ቅዱሳን ይህ አንድነት በልዩነት ውስጥ መሆኑን መርሳት የለባቸውም። የቤተክርስቲያን አንድነት ማለት እያንዳንዱ አማኝ አንድ መሆን አለበት ማለት አይደለም። ደግሞም እያንዳንዱ አባል እና ቤተክርስቲያን እርስ በእርስ በካርቦን ኮፒ የተገለበጠ መሆን አለበት ማለት አይደለም።

ጳውሎስም ይህንን በ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ላይ በግልጽ ያስቀምጠዋል። በዚህም በአባላቶች እና በስጦታዎቻቸው መካከል ልዩነት እንዳለ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ አባል አሰፈላጊ እንደሆነ ይናገራል በሚያሳዝን መንገድ ይህንን እውነታ በተደጋጋሚ እነረሳለን። ሆኖም ግን በዚህ ምክኒያት ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ኢየሱስ አካል ብቻ ትሆናለች።

ሀጥያት እስከሚጠፋ ድረስ ሁሌም ልዩነት በመኖሩ የቤተክርስቲያን አንድነት የእምነት ጉዳይ ነው። የኒቒኒ የእምነት አዋጅ “አንድ ቅዱስ ካቶሊክ እና ሐዋሪያዊ ቤተክርስቲያን አለ” በማለት እንደሚያስተምረን እኛ ክርስቲያኖች እናምናለን።

ስለዚህም አማኞች የቤተክርስቲያን አንድነትን በእምነት እንጂ በእይታ ባለመንቀሳቀስ መረዳት አለባቸው (2ኛ ቆሮ 5:7)። ይህ እንዴት ታላቅ እውነት ነው! እምነት ስህተቶች፣ ሀጥያት እና ልዩነት በመካከሏ ያለባትን ቤተክርስቲያን ሰዎች እያዩ እርሷን ከመሸሽ ታስቆማለች።

ደግሞም እንደዚህ አይነት እምነት በከንቱ አይደለም። ክርስቶስ ሲመለስ “ሁሉን በክርስቶስ አንድ ያደርጋል” (ኤፌ 1:10) ሀጥያትንም ደብዛውን ያጠፋል በዚህም የልዩነት መንገድ ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳል።

## ቤተክርስቲያን በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን

አንድ እጅግ አስፈላጊ የቤተክርስቲያን አንድነት ገጽታ *በአዲስ* እና *በብሉይ* ኪዳን ያለው አንድነት ነው። ይህም ማለት እስራኤል እንደ ብሉይ ኪዳን *ቤተክርስቲያን* እና የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን እንደ እውነተኛ የእግዚአብሔር *እስራኤል* ናት። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ግልጥ ቢሆንም ይህንን ጥቂጦች ብቻ አስተውለውታል።

እስራኤል ቤተክርስቲያን፣ ቤተክርስቲያንም እስራኤል መሆኗ የህጻናት ጥምቀትን ለመደገፍ የምንጠቀምበት ሀሳብ ውስጥ መሰረቱ ይገኛል (አንድ ቤተክርስቲያን፣ ስለዚህም አንድ ኪዳን አንድም የኪዳን ምልክት)። ደግሞም እስራኤል እና ቤተክርስቲያን ሁለት የተለያዩ አካሎች እና የተለያየ ተስፋ አላቸው የሚለውን የዲስፔንሽናሊዝም አስተምህሮ ለመመከት እንደዚህ አይነት መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።

የሐዋሪያት *ሥራ* 7:38 በግልጽ እስራኤል እና ቤተክርስቲያን አንድ እንደሆኑ ይናገራል። በዚህም እስራኤል "በምድረበዳ ያለች ቤተክርስቲያን" ተብላ ተጠርታለች። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተክርስቲያን ስም የሚለው ቃል በቃል ነው።

ፊሊጲስዮስ 3:3 ደግሞ ሌላው ማረጋገጫ ነው። በዚህ ክፍል ጳውሎስ ስለ አህዛብ ቤተክርስቲያን "እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና" በማለት ተናግሯል (ሮሜ 3፡28-29, ገላ 3:29)። እግዚአብሔርን በመንፈስ የሚያመልኩት እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወድዱት እውነተኛ አይሁዳዊ እና የእግዚአብሔር እስራኤል ናቸው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር እውነተኛ አይሁዳዊ መሆን ከአብርሃም ወገንነት፣ ከዘር ሀረግ እና ከተፈጥሯዊ ውልደት ጋር የሚያያዘው ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ "ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና" ብሏልና (ሉቃስ 3:8)።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት እውነተኛ አይሁዳዊ በተስፋው ቃል ኃይል የተወለደ (ሮሜ 9:8) ፣ የአብርሃም አይነት የሚያጸድቅ እምነት ያለው (ገላ 3:8-9) ፣ እንደ አብርሀም የክርስቶስ የሆነ (ቁጥ 29) እና ደግሞም በልቡ የተገረዘ ሰው ነው (ሮሜ 2:28)። የቀሩት አይሁዳዊ አይባሉም (ሮሜ 2:28)። ከኪዳኑ ጋር የሚያገናኛቸው ምንም ነገር የለም (ሮሜ 2:39)።

የእስራኤል እና የቤተክርስቲያን አንድነት በሮሜ 9:24-26 ላይ የተጠቀሰው ሆሴዕ 1:10-11 እና ሐዋ 15፡13-17 ላይ እንደገና የተጠቀሰው አሞጽ 9:11-15 ግልጽ ያደርገዋል። በሆሴዕ ክፍል ላይ የእግዚአብሔር ቃል አስርቱን ነገዶች በመጠቆም (ይህ ደግሞ ይሁዳን እና ብንያምን ሳያጠቃልል) ስለ ወደ ፊት ተሓድሶአቸው ያወራል ። ሮሜ 9:24-26 ይህ ትንቢት በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን መሰብሰብ እንደተሟላ ያሳየናል።

በአሞጽ 9:11-15 ላይ ስለእስራኤል መንግስት መታደስ እና ወደ ቀድሞ በታቸው ተመልሰው ቤተ መቅደሱን እንደሚገነቡ እናነባለን። ነገር ግን ሐዋሪያት ስራ 15 በግልጽ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የዚህን ተስፋ ፍጻሜ የአህዛብ መሰብሰብ እንደሆነ ያሳየናል ። በዳዊት ዳግም የተገነባው ቤተመቅድስ መወደቁ እና መበላሸቱ (ቁጥ 16) በተስፋው ቃሉ "እግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን ተርኮአል" እግዚአብሔር አህዛብን መጎብኘቱን ያሳየናል (ቁጥ 14)።

ስለዚህም እነዚህን እውነታዎች መረዳት ስንችል ብቻ ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን ለእኛ ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች እንደተጻፈልን እንረዳለን። ተስፋው እና ማስጠንቀቂያዎቹ ሁሉ ለሌሎች እኛ ለማናቃቸው እና ከእኛ ጋር ምንም ግንኙነት ለሌላቸው ህዝቦች ሳይሆን ለእኛ ለልጆቹ ተሰጥቶናል። ብሉይ ኪዳንን በምናነብበት ወቀት ይሄ ሀሳብ ትልቅ ልዩነትን ያመጣል ምክኒያቱም የምናነበው አይናችን ላይ ልባስን ለብሰን ሳይሆን በመረዳት እና በማስተዋል ይሆናል።

## የቤተክርስቲያን ቢሮዎች

ወደሰማይ ካረገ ወዲህ ጌታችን የተለያዩ ቢሮዎችን ለቤተክርስቲያን አቋቁሟል (ኢፌ 4:11)። እነዚህን ቢሮዎች ያዘጋጀው አገልጋዮች እርሱን ይወክሉት ዘንድ እና ቤተክርስቲያንን በእነዚህ ቢሮዎች ያገለግሉ ዘንድ ነው። እርሱ ብቸኛው የቤተክርስቲያን ራስ እና ንጉስ ነው። እነዚህ ቢሮዎችም ለቤተክርስቲያን ጤናማነት እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው።

በእነዚህ ቢሮዎች ቁጥር እና ባህሪ ላይ ብዙ ክርክር አለ። ወደዚያ ክርክር ሳንገባ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት ቢሮዎች እንደ መጀመሪያው ሦስት እንደሆኑ እናምናለን። እነርሱም ሽማግሌ፣ ዲያቆን እና የወንጌል አገልጋይ ናቸው።

እኛ እነዚህ ቢሮዎች ሁልጊዜም “ቋሚ፥ ናቸው የምንለው አንዳንድ እንደ ሐዋሪያት፣ ወንጌላዊያን እና ነብያት ያሉ ጊዜያዊ ቢሮዎች ስላሉ ነው። እነዚህ ቢሮዎች የመጽሐፍ ቅዱስ *በመንፈስ አነሳሽነት* መጻፉን እና *ግድፈት የለሽ መሆኑን* ለሰሚዎች የሚያስተላልፉ ቢሆንም (ሐዋ 21:10-11, ዕብ 2:3-4, 2ኛ ጴጥ 3:15-16) መጽሐፍ ቅዱስ በመጠናቀቁ የሚያስፈልጉ ቢሮዎች አይደሉም (2ኛ ጴጥ 1:19-21) ።

የመሪ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆኖች እና የወንጌል አገልጋዮች ቢሮ ብቻ የማይሻር መሆኑ በጳውሎስ ለቀደሙት ሐዋሪያቶች ትዕዛዝን በሚሰጥበት በመጨረሻ ላይ በጻፈው መልክቶቹ ላይ በተለይም በቲቶ እና በጢሞቴዎስ ላይ  በግልጽ ተጽፈው እናገኛቸዋልን። ከዚህ በተጨማሪ ደብዳቤዎቹ ከቤተክርስቲያን ስርዓት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው (1ኛ ጢሞ 3:15) እና በቤተክርስቲያን ያሉትን ነገሮች በስርዓት ከማድረግ ጋር የተያያዙ መሆናቸው (ቲቶ 1:5) ይህንን ሀሳብ የበለጠ ያረጋግጥልናል።

የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እና ሽማግሌዎች በአዲስ ኪዳን በአንድነት ሽማግሌዎች ተብለው መጠራታቸው አሳሳቢ ጉዳይ ባለመሆኑ ስለዚህ ጉዳይ መከራከር አንፈልግም። ግልጽ የሆነው ነገር እነዚህ ቢሮዎች የተለያዩ ድርሻዎች የነበራቸው እና በአዲስ ኪዳን ደግሞ የተለያዩ ቢሮ ሆነው መገለጣቸው ነው (1ኛ ጢሞ 3:4)።

እኛን የሚያሳስበን እነዚህ ሦስት ቢሮዎች በዚህ ዘመን በቤተክርስቲያን የተረሱ እና የተገፉ መሆናቸው ነው። በዚህ ዘመን በጣም ጥቂት አብያተክርስቲያናት ብቻ ሦስቱም ቢሮዎች አሏት። እነዚህም ሦስት ቢሮዎች በተሰበሰቡበት ቦታ አንዳንድ ጊዜ ዲያቆን የሽማግሌን ቦታ ወይም በግልባጩ በመቀያየር ሲሰሩ አልያም ደግሞ አገልጋዮች የሦስቱንም ስራ ሲሰሩ እናይ ይሆናል። እንደዚሁም ብዙውን ጊዜ እነዚህ ቢሮዎች ከሹመትነት ባለፈ ተራ ነገር እየሆኑ እና የሚመርጧቸውም ሰዎች ከመንፈሳዊ ብቁነታቸው ተነስተው ሳይሆን ከሀብት እና ከታዋቂነታቸው ጋር በተያያዘ ሲሆን እንመለከታለን።

ይህ ለቤተክርስቲያን መጥፋት ምክንያት ብቻ ይሆናል።  በእርግጥም እነዚህ ቢሮዎች የክርስቶስ ተወካዮች ከሆኑ በቤተክርስቲያን ውስጥ እነርሱን ማጣት ክርስቶስ እራሱ በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል መገኘት እያለበት አለመገኘቱን የሚያመላክቱ ናቸው።

እነዚህ ቢሮዎች የክርስቶስ ሦስት ቢሮዎች ይሆኑት የነብይነት፣ የካህንነት፣ እና የንጉስነት ገጽታዎች ናቸው። በቢሮዎችም የሽማግሌዎች እና የአገልጋዮች መሪነት ግልጽ የሆነ ነገር ነው። እነዚህ ቢሮዎች የክርስቶስ ንግስና

እና የነብይነት ቢሮዎች ተቀጣይ መሆናቸውን አለማየት ከባድ ነው። የዲያቆን ቢሮ በደንብ ብንረዳው የክርስቶስ የክህነት ቢሮው ወይም ደግሞ የክህነት አንድ ገጽታ እንደሆነ እናስተውላለን።

ይህ እውነት ከሆነ የቤተክርስቲያን ቢሮዎች የክርስቶስን ቢሮዎች ያንጸባርቃሉ ለቤተክርስቲያንም እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው በዚህም ዘመን መረሳት የለባቸውም። ቢሮዎቹ ወደ ተገቢው ስፍራቸው እና ስራቸው እንዲመለሱ የእኛ ተስፋ እና ጸሎት ነው።

## የሽማግሌዎች ቢሮ

መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት የተለያዩ ቃላቶችን ለሽማግሌ ይጠቀማል። የመጀመሪያው ቃል "ሽማግሌ" ተብሎ ሲተረጎም (ሐዋ 14:23, ሐዋ 15:2, 6ff፣ 1ኛ ጢሞ 5:1, 17, 19፡ ቲቶ 1፡5, ያዕቆብ 5:14, 1ኛ ጴጥ 5:1)፣ ይህ በግሪክ ቃሉ "ፕሬስብተር" ሲሆን ትርጉሙም "በእድሜ የገፋ ሰው" ማለት ነው። በሌላው ትርጉም ደግሞ ሲተረጎም "ቢሾፕ" ወይንም "ተቆጣጣሪ" (ሐዋ 20:28, ፊሊ 1:1 1ኛ ጢሞ 3:1-2, ቲቶ 1:7) የሚለው ሲሆን ይህ ደግሞ ሌሎችን የመግዛት ስልጣን ያለው ሰው ማለት ነው።

እነዚህ ሁለት ቃላቶች አንድ አይነት ቢሮን እንደሚወክሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው። በሐዋሪያት ሥራ 20 ጳውሎስ የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን አስጠርቶ "ጠብቋት" ይላቸዋል (ቁጥ 28)። በሌላ ቦታ ደግሞ "ኤጲስ ቆጶስነት (ቢሾፕ)" (1ኛ ጢሞ 3:1,2 ) ተብለው ሲጠሩ እንመለከታለን። በቲቶ 1:5-7 ጳውሎስ "ሽማግሌ" እና "ኤጲስ ቆጶስ" አንድላይ ስለአንድ ሰው ለመናገር ይጠቀማል። ይህም ደግሞ የሮማን ካቶሊካዊነት እና የኤጲስ ቆጶስነትን ስርዓት ይቃወማል። እነዚህ ሁለቱም የኤጲስ ቆጶስነት ስፍራ የተለየ ፣ ከፍ ካሉት ቢሮዎች እና ከሌሎች ቢሮዎች ልዩ መሆኑን ያስተምራል።

መጽሐፍ ቅዱስ በመሪ ሽማግሌዎች (1ኛ ጢሞ 3:4-5, 1ኛ ጢሞ 5:17) እና በአስተማሪ ሽማግሌዎች (1ኛ ጴጥ 5፡1) መካከል ልዩነት ያደርጋል። ነገር ግን ይህ አንዱ ቢሮ ከአንደኛው በላይ ነው የሚልን ምልከታ የለውም። እነዚህ ክፍሎች በእነዚህ ቢሮዎች መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ያሳያሉ። መሪ ሽማግሌዎች ማስተማር አለባቸው (1ኛ ጢሞ 3:2) እና ደግሞ "በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት" አስተማሪ ሽማግሌዎችም ደግሞ ይመራሉ (1ኛ ጢሞ 5:17)።

ስለዚህ በእነርሱ መካከል ያለው ልዩነት የተግባር ብቻ ነው። አስተማሪ ሽማግሌዎች በተለየ ሁኔታ ባይሆንም ቃሉን እና አስተምህሮውን በማስተማር ከሌሎች ሽማግሌዎች አንጻር ይደክማሉ። ኤፌሶን 4:11 ደግሞም እነዚህን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች መጋቢ እና አስተማሪ ብሎ ይጠራቸዋል።

የእኛ ንግግር በመሪ ሽማግሌዎች ላይ ሲሆን የተለያዩ ነጥቦችን ስለዚህ ቢሮ ማንሳት አለብን። እነዚህ የመሪዎች ዋና ቢሮ ሲሆኑ ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በረከት እንጂ መርገም መሆን የለባቸውም።

በመጀመሪያ ብዙ ሽማግሌዎች ሊኖሩ ይገባል። አገልጋይ ቢሆንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሽማግሌ ብቻውን ሲመራ ተናገሮ አያውቅም። በአንድ አምባገነናዊ አመራር መምራት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አብሮ የሚሄድ አመራር አይደለም። ይህም ደግሞ በምሳ 11:14, በምሳሌ 15:22, እና በምሳሌ 24: 6 ላይ ተጠቅሷል።

ሁለተኛ ደግሞ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር ህዝቦች አገልጋይ ናቸው (ማቴ 23:11, 1ኛ ቆሮ 9:19, 2ኛ ቆሮ 4:5) ። ይህም በቆላስያስ 4:17 ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል። በዚህም ክፍል ጳውሎስ ቤተክርስቲያን አገልጋዮቿን እንድታስጠነቅቅ እና ለሙሉ አገልግሎቱ ታላቅ ክብርን እንድተሰጥ ይነግራታል። ሽማግሌዎችም እራሳቸውን እንደ አገልጋይ በማየት አምባ ገነናዊነትን እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ጌታ መሆንን ማቆም አለባቸው።

ሦስተኛ የሽማግሌዎች ገዢነት ማለት እነርሱ በቤተክርቲያን ህይወት በሁሉም አይነት መንገድ መምራት አለባቸው ማለት ነው። ይህም ደግሞ ስብከትን ፣ የሌሎች ቢሮዎች እና አገልጋዮች ባህሪን ያካትታል (ሐዋ 20:28-31) ።ቤተክርስቲያንን "ከቀማኞች" እና "ከተኩላዎች" መታደግ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሁሉ ድርሻ ነው። ማንም ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ እራሱ ገዢ ሊሆን አይችልምና።

አራተኛ ከክርስቶስ በተሰጣቸው በገዢነት ስልጣን ሽማግሌዎች ቤተክርስቲያን ይመራሉ (ሐዋ 20:28)፣ ይህም ደግሞ ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሲሆን (ማቲ 28:28) ፣ እርሱን በመታዘዝ የሚፈጸም ተግባር ነው (1ኛ ጴጥ 5:4)። ይህ ማለት በተግባር የእነርሱ ስልጣን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ነው። እነርሱ ወደ አገልጋዮቻቸው ሲያመጡት ከእራሳቸው አመለካከት ውጪ በዚህ መልኩ መምራት ፣ መገሰጽ እና ይህንን ብቻ ማስተማር አለባቸው።

እንደዚህ አይነት ሽማግሌዎች ለክርስቶስ ቤተክርቲያን በረከት ይሆናሉ።

## የዲያቆን ቢሮ

የዲያቆን ቢሮ በክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ውስጥ እጅግ የተረሳ ነው። አብዛኞቹ ቤተክርስቲያኖች ዲያቆናት የሏቸውም ደግሞም ቢኖራቸውም እንኳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርሻቸውን አይወጡም።

ዲያቆን ባላቸው ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ዲያቆኖች የሽማግሌዎችን ድርሻ በመውሰድ ቤተክርስቲያንን ይመራሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንዲሁ የቤተክርስቲያንን የገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ይቆጣጠራሉ። ይህ ደግሞ ቢሮ ወይንም ሹመት የማያስፈልገው ጉዳይ ነው። የዲያቆንን ቢሮ ለመረዳት ሐዋሪያት 6ን ማስተዋል እና ማጤን ያስፈልጋል። ይህ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹን ዲያቆናት ታሪክ ይነገራል። "ዲያቆን" የሚለው ቃል ቀጥተኛ የግሪክ ትርጉም በቀላሉ "አገልጋይ" ማለት ነው።ይህንን መጽሐፍ ቅዱስም ቤተክርስቲያንን እና አማኞችን በየትኛውም የሚያገለግልን ሰው ለመግለጽ ይጠቀመዋል (ዩሀንስ 12:26, ሮሜ 16:1)። ሆኖም ግን ሐዋርያት *ሥራ* 6 አንዳንዶች በተለየ መልኩ "አገልጋዮች" እንደሆኑ ያስቀምጣል።

የሐዋሪያት ስራ 6 እንደሚያስተምረን የእነዚህ ልዩ አገልጋዮች ቢሮ፣ እርሱም የዲያቆናት ቢሮ፣ አንድ ሰው ሊጠራበት የሚያስፈልገው ቢሮ ነው (ቁጥ 3, 6 ፡ ልክ እንደዚሁ ፊሊ 1:1, እና 1ኛ ጢሞ 3:10, 13ን ተመልከቱ)። ይህም ደግሞ ቢሮው የቤተክርስቲያንን መጽሐፍት ከመጠበቅ በላይ እንደሆነ ያመላክትልናል ። እንዲሁም አንዳንድ የመንፈሳዊ ብቁነቶች ለዚህ ሹመት አስፈላጊ እንደሆኑ እንረዳለን (ሐዋ 6:3, ደግሞም 1ኛ ጢሞ 3:8-13ን ይመልከቱ)።

ሐዋሪያት *ሥራ* 6:3 ይህንን ሲናገር 1ኛ ጢሞቴዎስ 3:8-13 ደግሞ ሀሳቡን ያረጋግጣል። ይህም ደግሞ ዲያቆኖች እንደ ሽማግሌዎች እና እንደ አገልጋዮች *ወንዶች* መሆን እንዳለባቸው ነው። ለዚህም ምክኒያቱ የተጠራው ይህ ቢሮ በቤተክርስቲያን ውስጥ *ስልጣንን* ስለሚጠቀም ነው፣ ስልጣኑ ግን እንደ ሽማግሌዎች አይነት ይደለም። ሴቶች ዲያቆን የሆኑበት ቤተክርስቲያኖች ሴት የቤተክርስቲያን መሪዎች እና ሰባኪዎች እንዳሉበት ቤተክርስቲያናት የእግዚአብሔርን ቃል የማይታዘዙ ናቸው።

ከሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 6 የግሪካዊ መበለቶችን በማንሳት የዲያቆናት የስራ ድርሻ ምን እንደሆነ እነረዳለን። ይህ ስራ ወይም ተግባር ብዙውን ጊዜ የተቸገሩ ሰዎችን ከመርዳት ጋር የተያያዘ ነው። ነገር ግን ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች መርዳት እና ማገዝ ብቻ እንዳልሆነ ከሐዋሪያት *ሥራ* 4:35 በግልጽ እነርዳለን። በዚህ ስፍራ ሐዋሪያቶች ወደ ዲያቆንነት ያስተላለፉት "ተግባር" ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ገንዘብን በመሰብሰብ እና ገንዘብን በመስጠት የሚካሄድ ነው።

ይህንን ተግባር በመፈጸማቸው ለዚህ ስራ የተሾሙት ሰዎች በክርስቶስ በእራሱ የተጠሩ መሆናቸውን እና ከበጎ አድራጎት የዘለለ ስራ እንዳላቸው ማስተዋል ያስፈልጋል። ለአገልግሎቱ እና ስራው በክርስቶስ እንደመመረጣቸው፣ ዲያቆናቶች ክርስቶስ እና ስሙን ለማገልገል ተጠርተዋል "ድሀዎችን ለማሳረፍ እና ትርፍ ስጦታን ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚገኙ አጽናኝ ንግግሮች ሊያጽናኑ ተጠርተዋል።"[1]

ይህንን በማድረጋቸው ዲያቆናት የክህነትን ተግባር በጥቂቱ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይፈጽማሉ። እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናቶች የእነርሱ የምህረት ቢሮ ሲሆን ክርስቶስን እና ህዝቡን በማገልገላቸው የሚገኙትን ስጦታዎች ይቀበላሉ ።

ይህ ቢሮ በመጀመሪያ እና በልዩነት ለቤተክርስቲያን እንዲሆን በገላቲያ 6:10 የተጠቀሰውን ህግ በስራቸው መከተል አለባቸው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ይህ ቢሮ ሲታደስ በመዝሙር 37:25 " ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም" የሚለው ቃል ይፈጸማል።

## የመጋቢ እና የአስተማሪ ቢሮ

የመጋቢ እና የአስተማሪ ቢሮ (ኤፌ 4:11) ሦስተኛው የቤተክርስቲያን ቋሚ ቢሮ ነው። ይህም ደግሞ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4:14 እና በሮሜ 10:15 ላይ የምንመለከተው ጥሪ ያስፈልገዋል። ቢሮውን የሚቀበሉ ወይም የሚወስዱ ሰዎች ዋና ስራ "በመስበክ እና በማስተማር" መድከም ነው(1ኛ ጢሞ 5:17) ። ይህም ደግሞ ወንጌልን በመስበክ ነው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5:17 እንደሚያስረዳው በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እና ቃል የሚደክሙት እነርሱ ቤተክርስቲያንን ከሚመሩት ሽማግሌዎች ጋር ይቆጠራሉ። ሽማግሌዎች መጋቢያን እንደሆኑ ሁሉ የወንጌል አገልጋዮችም የቤተክርስቲያን መሪዎች መሆናቸውን ይህ ክፍል ያሳየናል (ሐዋ 10:28)። መጽሐፍ ቅዱስ አገልጋይ እና መሪ ሽማግሌ የተለያዩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነገር የለውም።

"በቃሉ እና በአስትምህሮ" የሚደክሙ ሽማግሌዎች ዋነኛ ስራ ወንጌልን መስበክ ነው። ይህም  በ2ኛ ጢሞቴዎስ 4:2 እና በሌሎች ብዙ ክፍሎች ተጠቅሶ እናገኘዋለን። ኤፌሶን 4:11 እንደሚያስታውሰን ይህ ቢሮ የአስተማሪነት ቢሮ ነው። ስለዚህም የሰባኪ ስራ ሰዎችን ማስደሰት አይደለም። ዋና ስራውም በተለመደው መልኩ "ወንጌልን መስበክ" ብቻ አይደለም። ስራው ማስተማር ነው።

እዚህ ሀሳብ ላይ ትንሽ ጫና ማሳደር እንፈልጋለን። ምክንያቱም አብዛኞች የወንጌል ሰባኪያን ይህንን ረስተውታል። የፈለጉትን ነገር ሁሉ እየሰሩ ይህን ውድ የሆነ የማስተማር ተግባር ጥቂት ብቻ ያከናውናሉ። ምዕመናንም ለአመታት ከእነዚህ አስተማሪዎች ስር ቢማሩም አንድ እልፍ የሚያደርግ ነገርን ሳያገኙ ይቀራሉ። ይህም ደግሞ ሁልጊዜ የሰባኪው ጥፋት ባይሆንም አብዛኛውን ጊዜ ግን ነው።

ሰባኪ እንዲያስተምር የተጠራው ትልልቅ የቤተክርስቲያን ምዕመናን ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸውንም ጭምር ነው (ዩሀንስ 21:15)። ስለዚህም ሰባኪው ለቤተክርስቲያን ልጆች በተደጋጋሚ ምክርን መስጠት አለብት። ነገር ግን ተራ የሆኑ እና ምንም ጥቅም የሌላቸውን “የህጻናት ስብከቶች” ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን እና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ሊያስተምራቸው ይገባዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ሰባኪው ወጣቶችን ቃሉን በማስተማር ለመልካም ስራ ሊያዘጋጃቸው ይገባል (2ኛ ጢሞ 2:2)። ከዚህ ጋር በመስማማት የተሓድሶ ቤተክርስቲያናት የወንጌል ሰባኪዎችን ለዚህ ስራ ሁሌም ይጠራቸዋል። በዚህ ሁሉ ሰባኪ መጋቢ የመሆን፥ የእግዚአብሔር ህዝቦች ጠባቂ እና እነርሱን የመንከባከብ ትልቅ ድርሻ አለበት (ሕዝ 34:1-6)።

ሰባኪ ለማስተማር እንደተጠራ ሁሉ ለማንበብ እና ለማጥናትም (1ኛ ጢሞ 4:13) ደግሞም አስተምህሮን/ዶክትሪንን እንዲያከብር ማለትም እንዲማር እና እንዲያውቅ ተጠርቷል (ቁጥ 16)። ቢሮውን በያዙት ሰዎች ብዙውን ጊዜ ይህ ሀላፊነት ይዘነጋል። በዚህም ምክኒያት ቢሮውን የተቀበሉት ሰዎች ሀላፊነታቸውን ከመሸከማቸው በፊት አስተምህሮን መማር ይችሉ ዘንድ፣ የሰለጥኑ እና መመሪያ ያገኙ ዘንድ አስፈላጊ ነው። ታዲያ ይህ *እንዴት ይፈጸም* የሚለው ጉዳይ ከ*መፈጸሙ* አንጻር አሳሳቢ አይደለም።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ምዕመናንም ሀላፊነት አለባቸው። በቆላሲያስ እንደነበረችው ቤተክርስቲያን ሰባኪዎቻቸውን “በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽሙው ተጠንቀቅ” (ቆላ 4:17) ማለት አለባቸው። ምዕመናን ይህንን ማለት *አለባቸው*። ይልቁንም ደግሞ አገልጋዩ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀላፊነቶቹ ትክክለኛ ክብርን ከመስጠት ሲገደብ ይህንን ማለት ይጠበቅባቸዋል።

የመጋቢ ወይም የአስተማሪነት ቢሮ ለተሰጣቸው ሰዎች ቀላል ነው ማለት አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ለህዝቡ ድነት ሲል የሾመው ኃላፊነት ነው። መንጋውን የማይመግቡ እረኞች ወዮላቸው (ሕዝ 34:2)!

## የቤተክርስቲያን መንግስት

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የከፋፈለው አንድ ነገር የቤተክርስቲያን መንግስት በተለይም ደግሞ ወገን (ዲኖሚኔሽን) እና ለብቻ መቆም የሚባሉት ነገሮች ናቸው። በፍርሀት እና በመንቀጥቀት ስለዚህ ሀሳብ እንነጋገራለን።

በእራስ መቆም ትክክል ያልሆነ ብቻ ሳሆን ለቤተክርስቲያን ገዳይ የሆነ ነገር ነው። ይህንንም ቤተክርስቲያን በብዙ ቦታዎች የመውደቋ ምክንያት አድርገን እንመለከተዋለን።

በራስ መቆም አባላቶቹን እና ቤተክርስቲያንን ችግር ሲፈጠር ያለ አጋዥ እና ያለ እርዳታ ይተዋቸዋል። ይህም እንደ ምሳሌ 24:6 ያሉ ተመሳሳይ ክፍሎች ላይ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ማለት ነው። ሐዋ 15 ላይ የተጠቀሰውንም ስራ ወይም መንገድ አይከተልም። እንዲሁም ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጋር በሚያስማሙ መሰረት ህብረት እንዳናደርግ ይከለክላል።

ሆኖም ግን በሌላኛውም ወገን በኩል ችግሮች አሉ። ምንም አይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስደገፊያ ሳይኖር ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያን “ከላይ ወደ ታች” በኮሚቴዎች እና በቦርዶች ስለምትመራ አጥቢያ ቤተክርስቲያንም ሆነች አባላቶቿ በቤተክርስቲያን ላይ ሀሳብ መስጠት አይችሉም። በዚህም ምክንያት ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች ለአባላት (ለማንኛውም ሰው) ለስራቸው ወይም ለባህሪያቸው ምላሽን መስጠት አይፈለጉም።

በፕሬስበተሪያን እና በተሓድሶ የሀይማኖት ወገን (ዲኖምኔን) ኮሚቴዎች እና ተወካዮች ክርስቶስ ብቻ ሊኖረው የተገባውን ስልጣን የሚያስይዝ የስልጣን ተዋረድ አለ። ይህንንም ደግሞ አንቀበልም።

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለቱም ወገን ያለውን ችግር የሚቀርፍ መልስ እንደሚሰጠን እናምናለን። የመጀመሪያው መልስ ክርስቶስ እንዲሰሩ የሰጥቸው ስራ ስለሆነ ምዕመናን ለጋራ መረዳዳት እና ቁጥጥር አንድላይ በጋራ መቆም *አለባቸው* (ሐዋ 15)። “የመንፈስን አንድነት መጠበቅ” እጅግ አስፈላጊ ነው (ኢፌ 4:3)።

ሁለተኛ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ራስን በእራስ የመምራት ስልጣን መጠበቅ አለበት። በዚህም ደግሞ ቤተክርስቲያን የኮሚቴዎች እና የሰብሳቢዎች ቤተክርስቲያን እንዳትሆን እና የወንጌል ስብከት ስራ ፣ ስርዓቶቿን ማስተዳደር እና የክርስትናን ተግባራት መከታተል ወይም ማድረግ የእነርሱ ስራ እንዳይሆን ነው (ሐዋ 13:1-4, 1ኛ ቆሮ 5:4-5)። ክርስቶስ የሚሰጠው ስልጣን እነዚህ ነገሮች በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ

እንዲፈጸሙ ነው። ቤተክርስቲያን ከላይ ወደ ታች የምትመራ አይደለችም። ይህም ማለት ተወካዮቹ ሁልጊዜም በተግባራቸው ብቻ የተገደቡ መሆን አለባቸው። ሐዋ 15 እንደሚለው እነርሱም ለጋራ እርዳታ እና ምክር ሊኖሩ ይገባል። እነዚህ ተወካዮች ወደ እነርሱ የሚቀርብላቸውን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ውሳኔዎች ሲወስኑ ውሳኔዎቹ ሊከበሩ ይገባል (ቁጥ 23-29)። ይህም ደግሞ አንድ ከፍ ያለው ባለስልጣን ስላዘዘው ሳይሆን ቤተክርስቲያን እራሷ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በህብረት ለመኖር ስለወሰነች ነው።

ሦስተኛ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ቢሮዎች በመጽሐፍ ቅዱስ በተሰጠን እና በተጠቀሰልን መንገድ የሚመሩ ሊሆኑ እና የቤተክርስቲያን ቢሮዎች በሙሉ ለቤተክርስቲያን ማለትም ለአማኞች አካል የሚጠየቁ መሆን አለባቸው ። ክርስቶስ ለእነርሱ የሰጣቸው ስልጣን በቤተክርስቲያን ላይ አገልጋይ እንዲሆኑ እንጂ ጌታ ሊሆኑ አይደለም (2ኛ ቆሮ 4:5, ቆላ 4:17)።

እነዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ነግሮች ሁሉ በጨዋነት እና በመልካም አስተዳደር እየተደረጉ እንዳለ የምንመለከትበት የመጀመሪያ ደረጃዎች ናቸው። እንደዚህ ያለ መልካም ስርዓት ደግሞ ለቤተክርስቲያን ደህንነት እና ጤንነት እጅግ አስፈላጊ ነው።

## እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን

እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ምንድነው? የትስ ይገኛል? የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል የምንሆን ከሆነ ይህ መጠየቅ ያለበት ከባድ ነገር ግን እጅግ አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ብዙውን ጊዜ ለመመለስ ቀላል የሆነ ጥያቄ አይደለም።

ይህንን ጥያቄ ከባድ የሚያደርገው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የነበረች ቤተክርስቲያን ሀሰተኛ ቤተክርስቲያን ወደ መሆን የመለወጥ እድል ስላላት ነው። ክርስቶስም የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን ስለዚህ ሁኔታ በራዕይ 2:5 ላይ ያሳስባታል።

የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሀሰተኛ ቤተክርስቲያን ወደ መሆን እየተጠጋች ለመሆኗ ክርስቶስ ሻማዋን እንደሚወስድ ሲያስጠነቅቃት ማየታችን ማስረጃ ነው። እነዚያ ሻማዎች በመንፈስ ቅዱስ ዘይት በመንደድ በአለም የሚያበሩ የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው (ዘካ 4:1-6 ፣ ዕብ 1:9 ፣ ማቴዎስ 5:14)። የኤፌሶን ቤተክርስቲያን መንፈሱን እና ብርሀኑን የማጣት ከባድ ችግር ላይ ነበረች። ይህች ቤተክርስቲያን

ሻማዋን እንደምትነጠቅ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ትርጉሙ ከእንግዲህ ወዲህ የክርስቶስ እንደማትሆን የሚያመላክት ነው። እርሱም በዚያች ቤተክርስቲያን ውስጥ አይመላለስም (ራዕይ 1:12-13)። በተመሳሳይ መልኩ ክርስቶስ የሎደቂያን ቤተክርሲያን ከአፉ እንደሚተፋት ያስጠነቅቃታል (ራዕይ 3:16)።

ለእነዚህ ሁለት ቤተክርስቲያናት ክርስቶስ በፍርድ ማስጠንቀቂያ የሰጠበት ምክንያት የቀድሞውን ፍቅር ትታቿሀል (ራዕይ 2:4) ፣ ለብ ብላችኋል እና በሥጋዊ ነገር ላይ በሚያተኩር ኑሮ ውስጥ ኖራቿል በማለቱ ነው (ራዕይ 3:16-17)። በእርግጠኝነትም በዚህ ዘመን በተመሳሳይ ፍርድ እና በተመሳሳይ ምክኒያት የሚወድቁ እንዳሉ ግልጽ ነው።

ስለዚህ እውነተኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያውን ፍቅር የማይለቅ ቤተክርስቲያን (ራዕይ 2:4) ፣ ክርስቶስ የሚያዘዘውን (ቁ 5) የማይተው ፣ ደግሞም ታማኝ (ቁ 10) ፣ ከሀጥያቱ ንሰሀ የሚገባ (ቁጥ 16) ፣ ያለውን አጥብቆ የሚይዝ (ቁጥ 25) ፣ የሚያስተውል (ራዕይ 3:3) ፣ አባላቶቹ ልብሳቸውን የማያቆሽሹ እንዲሆኑ የሚያደርግ (ቁጥ 4) ፣ የክርስቶስን ቃል የሚጠብቅ እና ስሙን የማይክዱ (ቁጥ 8) መሆን አለባቸው። እንዲህ አይነት ቤተክርስቲያናት በዚህ ዘመን ጥቂት ናቸው።

ቤተክርስቲያናት በእኩል ደረጃ ንጹሐን እንዳልሆኑ ከእነዚህ ክፍሎች መመልከት እንችላለን። ክርስቶስ በራዕይ 2 እና 3 የጠቀሳቸው ምንም ችግር ካልተገኘባቸው ቤተክርስቲያናት አንስቶ እንደሚጠፉ የተዛተባቸውን ቤተክርስቲያናት ሁሉ ያጠቃለለ ነው። ሆኖም የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ከነችግሯ ቤተ ክርስቲያን እንደተባለችው በዚህ ስፍራ ያሉትም ሁሉ ከነጥፋታቸው ቤተክርስቲያን ተብለዋል።

እውነተኛዋን ቤተክርስቲያን በምንፈልግበት ጊዜ በፍለጋችን ፍጹሟን ቤተክርስቲያን ለማግኘት እንዳንደክም ይህንንም በአእምሮዋችን መያዝ አለብን። በምድር እና በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል ሀጥያት እስካለ ድረስ ፍጹም ቤተክርስቲያን ለትኖር አትችልም።

የሮም እና አንዳንድ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያናት እንደሚሉት የክርስቶስ ብቸኛ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ነን ማለት የሚችል ቤተክርስቲያን የለም። በተለያየ መጠን ንጹህ እና እውነተኛ የሆኑ እና በተወሰነ ደረጃ ቢሆንም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሆኑ በጣም ብዙ አይነት ቤተክርስቲያኖች አሉ። በምድር ባለችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ፍጹምነት ሊኖር እንደማይችል ከረሳን ቤተክርስቲያንን ላንቀላቀል እንችላለን። ይህ ደግሞ በዕብ 10:24-25 “ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ በአንዳንዶችም

ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ" የሚለውን ክፍል መጻረር ነው።

ሆኖም ግን በራዕይ 2 እና 3 ላይ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የተናገረው ቃል የቤተክርስቲያን አባልነትን እና የቤተክርስቲያን አባል ሀላፊነቶችን በምንፈጽምበት ጊዜ ንጽህናን ፣ እውነትን ፣ እና ታማኝነትን ለእርሱ ስንል መከታተል እንዳለብን ግልጽ ያደርገዋል።

## የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች

እውነተኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በአለም እንደምትገኝ ይህ ክፍል ያረጋግጥልናል "በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም" (ማቴ 16:18)። ነገር ግን ዕብራውያን 10:25ን በመታዘዝ እንድንቀላቀላት እውነተኛዋን ቤተክርስቲያን የት ማግኘት እንዳለብን እና እንዴት እርሷን መቀላቀል እንዳለብን እናውቃለን?

ከላይ እንደተመለከትነው እውነተኛ ቤተክርስቲያን በአንድ ቤተክርስቲያን ሆነ ወገን (ዲኖሚኔሽን) ብቻ የምትወከል ባለመሆኑ የአባልነት ጥያቄ  እጅግ አስቸኳይ መሆኑ ግልጽ ነው። የተለያዩ ቤተክርስቲያን እና የሀይማኖት ወገን (ዲኖሚኔሽን) በመኖራቸው የትኛውን እንቀላቀል? መልሱም ደግሞ ለክርስቶስ ኢየሱስ የበለጠ ታማኝ የሆነችውን እና ፍጹም ባትሆንም በአስተምህሮ፣ በህይወት እና በተግባር ወይንም በልምምድ ንጽሁ የሆነችውን ቤተክርስቲያን መምረጥ አለብን።

ለዚህም እንዲሆን የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶችን እንነጋገራለን። እነዚህ ምልክቶች ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እና ለቃሉ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነች የሚያመሰክሩ ናቸው። ምልክቶቹም ያሏት ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ኢየሱስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን አካል ናት  የሌሏት ደግሞ ቤተክርስቲያን የተባለች ነገር ግን "የሰይጣንም ማኅበር" ናት (ራዕይ 2:9)።

አንዳንዶች "የምልክቶቹ" ቁጥር እና ባህሪያቶች ላይ ክርክርን ያነሳሉ። የቤልጂየሙ የእምነት አዋጅ ንጹህ የቃሉን ስብከት ፣ እንደ ክርስቶስ ትዕዛዝ ስርዓቶቿን የምትጠብቅ እና በታማኝነት የክርስትያን ምግባርን በቤተክርስቲያን ውስጥ የምትፈጽም መሆን አልባት[2] ይላል(ማቲ 16:18-19, ማቲ 28:19-20, 1ኛ ቆሮ

11:23-24)። አንዳንዶች ደግሞ  ለሦስተኛው ምልክት ተጨማሪ ወይም በእርሱ ምትክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምልኮን ያካትቱበታል።

ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ አንድ ምልክት ሆነው መጠቃለል እንደሚችሉ ግልጽ ነው፤ እርሱም ደግሞ ቤተክርስቲያን *የምታደርገው ነገር ሁሉ* ክርስቶስን በመታዘዝ መሆን አለበት የሚለው ነው። የቤልጅየሙ የእምነት አዋጅ እውነተኛ ቤተክርስቲያን "ነገሮች ሁሉ ከንጹህ የእግዚአብሔር ቃል አንጻር ይተዳደራሉ፤ ቃሉንም የሚቃረኑትን ሁሉ አይተገበሩም፤ ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ብቸኛ ራስ መሆኑ ይታወቃል"[3] ይላል ።

ስለ አንድ ሆነ ብዙ ምልክቶች ብናውራም አንዳንድ ምልክቶች የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክት የሆኑት ክርስቶስ በቤተክርስቲያን መገኘቱን የሚያመላክቱ በመሆናቸው ነው። ይህም እጅግ ዋና ነገር ነው። ክርስቶስ ካልተገኘ ቤተክርስቲያን የምታደርገው ነገር ሁሉ ከንቱ እና አባልነትም ደግሞ ግብ የለሽ ነው ፣ ክርስቶስም የሌለበት ስብስብ ቤተክርስቲያን ሊባልም አይችልም (ራዕይ 1:12-13, ራዕይ 2:5) ።

ስለዚህ ልጆቻችንን ስናሳድግ ይህንን እውነት ማስታወስ አለብን። የክርስቶስ መኖር ምልክቶች በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ የማይታይ ከሆነ ለልጆቻችን ምን ተስፋ አለን? እነርሱን ሊያድናቸው እና በመንገዳቸውም ሊመራቸው የሚችለው ክርስቶስ በመገኘቱ ብቻ ነው።

የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች የክርስቶስ ኢየሱስን መገኘት በተለይም ደግሞ በወንጌል ስብከት የሚያሳዩ መሆናቸው ግልጽ ነው። በስርዓት የተሰበከ ስብከት *ክርስቶስ እራሱ በቤተክርስቲያን* እየተናገረ ማለት ነው (ዩሀንስ 10:27, 1ኛ ቆሮ 1:23-24, ኤፌ 2:17)። ስለዚህ ንጹህ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የክርስቶስ መኖር ማረጋገጫ ነው።  የስርዓቶቿ እና ክርስቲያናዊ ምግባር መገኘትም ይህንኑ ያመላክታል።

እነዚህ የክርስቶስ መገኘት ምልክቶች መሆናቸው ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባ ነገር ነው። እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ ቢሆኑም ቤተክርስቲያንን የምንቀላቀለው በአባላቶቿ ምክኒያት፣ በእነርሱ እግዚአብሔርን መምሰል ሆነ ጓደኝነት አይደለም። ቤተክርስቲያንን የምንቀላቀለው የነፍሳችን ብቸኛ አዳኝ እና ኤጲስ ቆጶስ የሆነውን ክርስቶስ ለመከተል ነው።

**ወንጌል**

የቤተክርስቲያን ታላቅ እና *ብቸኛ* ጥሪ ወንጌልን መስበክ ነው። በእርግጥም በማቴዎስ 28:19 ላይ የተጠቀሰው የ"ታላቁ ተልዕኮ" ዋና አላማ ነው። ነገር ግን ወንጌል ምን እንደሆነ ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚያውቁ ይመስላል።

ወንጌል የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉም "መልካም ዜና" ወይም ደግሞ የክርስቶስን መወለድ ያበሰረው መላዕክ እንዳለው "የምስራች" ማለት ነው። በእርግጥም ይዘቱ በዚህ ሀጥያት በተሞላች ምድር ውስጥ ተሰምቶ ከሚያውቁ ነገሮች ሁሉ በላይ የሚያስደስት እና መልካም ዜና ነው። መልካም ዜና የሆነውም የእግዚአብሔርን ነጻ እና ሉዓላዊ ጸጋ ስለሚናገር ነው።

ነገር ግን የወንጌልን መልዕክት የሚቀይሩ እና *መልካም ዜና*ነቱን የሚያበላሹ ብዙ ናቸው። በእነርሱ ስህተት ወንጌል እለተ እለት ከምናነበው ጋዜጣ ምንም የተሻለ ዜና አይሆንም። በተለይ ደግሞ ድነት በሰው ስራ ላይ የተደገፈ እንደሆነ በሚናገሩ ሰዎች ወንጌል መበላሸቱ እርግጥ ነው። በስራ የሆነ ድነት የምስራች ሳይሆን መርዶ ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ስራችን በሙሉ ክፉ እንደሆነ እና ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ መሆኑን ስለሚያረጋግጥልን ነው (መዝ 14:1 ፣ ኢሳ 64:6)።

ወንጌል ድነትን በሀጥያተኛው ፈቃድ፣ ምርጫ እና ውሳኔ ላይ የሚደገፍ አድርጎ ሲያቀርብ ወይንም መልዕክቱ ይህንን መሰል ዝንባሌ ሲኖረው መልካም ዜና አይደለም። ይህም ደግሞ ለእንደ እኛ አይነቱ ተለዋዋጭ፣ ጠንካራ ውሳኔ የለሽ፣ ፈቃደኛ ያለሆነ፣ እና የማይታዘዝ ፍጥረት የበለጠ ከባድ ዜና ነው (ዩሐ 5:40, ዩሐ 6:44, ዩሐ 8:44)።

እንደዚሁ ደግሞ ሌላ በእኩል ሚዛን የሚረብሸው ዜና ክርስቶስ ለሁሉም ሰው መሞቱን የሚናገር እና እግዚአብሔር ሁሉንም ያለምንም ምርጫ ማዳን እንደሚፈልግ የሚነዛው ወንጌል መሰል አስተምህሮ ነው። ክርስቶስ ለሁሉም ሰው ሞቷል የሚለው አስተምህሮ ክርስቶስ ሞቶላቸው ወደ ገሀንም ለሚገቡት ሰዎች መልካም ዜና አይደለም። እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እንደሚወድድ እና ሁሉንም ሰው ማዳን እንደሚፈልግ የሚያወራ ወንጌል፤ እርሱን ማድረግ የሚፈልገውን የማያደርግ እና ማድረግ የማይችል አምላክ አድርጎ ስለሚያቀርበው የምስራችነቱ ይቀራል። ክርስቶስ ከሞተላቸው መካከል ወደ ገሀነም የሚገቡ ካሉ ይህ በክርስቶስ ላይ ያለንን መደገፍ ሁሉ ይወስዳል። እግዚአብሔር ሁሉንም ለማዳን ፈልጎ ነገር ግን ሁሉንም ማዳን ባይችል እኛ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ያጠፋብን ነበር።

ደግሞም ወንጌሉን ለመስበክ የሚገቡ አይደሉም ተብለው የተወሰኑ እውነታዎችን በወንጌል ውስጥ አለማንሳት ስህተት ነው ። በዚህ ልማድ ውስጥ የተለያዩ ችግሮች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ *ሙሉ በሙሉ* ወንጌል ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በመናገር እና ወንጌልን በመስበክ መካከል ምንም ልዩነት የለም። በማቴዎስ 28:19 “ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” ለሚለው ቃል የሐዋሪያት *ሥራ* 2, 7, 13, እና 17 ጥሩ ምሳሌ ነው። በዚህ ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፣ አስተምህሮ፣ ስነጽሁፍ ሁሉ ፤ ደግሞም እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ሉዓላዊ መሆኑን ከሚናገረው አስተምህሮ ጀምሮ እስከ ፍጥረት እና የእግዚአብሔር ሁሉን ገዢነት አስተምህሮ ድረስ የተለያዩ አስተምህሮዎች ተጠቃለዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ የትኛውም አስተምህሮ ለእግዚአብሔር ህዝብ እጅግ መልካም ዜና ነው ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔርና ስለድነታቸው ይናገራልና።

ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ ወንጌልን በጥቂት እውነቶች ብቻ አጠቃልሎ ይህንኑ ሀሳብ በተደጋጋሚ በወንጌል ስርጭት ፕሮግራሞች ላይ መስበክ፣ ደግሞም የተለያዩ ክፍሎችን በመጥቀስ ያልዳኑ ሰዎች ይኑሩ አይኑሩ ሳይታወቅ ይህንኑ መስበክ በጣም የሚረብሽ ነገር ነው።

ስብከትን ሙሉ በሙሉ ላልዳኑ ሰዎች ማዘጋጀት ትክክል አይደለም። የእግዚአብሔር ህዝቦች ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ እውነት መስማት አለባቸው። በዚህ ምድር እስካሉ ድረስ፣ አማኞች ላላመኑት ሰዎች በሚነገርበት መጠን ወደ ንሰሀ እና ወደ እምነት መጠራት አለባቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ኪዳን ሊጽናኑ፣ በማስጠንቀቂያዎቹም ሊገሰጹ እና በውድ እውነታዎቹ ሊመሩ ይገባል። እግዚአብሔር እንደዚህ አይነት ስብከትን ለቤተክርስቲያን ይመልስላት።

## ስብከት

ስብከት ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስን ሌሎች ትምህርቶችን እንደምናስተምረው ማስተማር ነው? የትምህርት አይነት ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊነቱን ለምን አጉልቶ ይናገራል? በእውነትም ስብከት እጅግ ልዩ  የሆነ ነገር ነው።

ስብከት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት ምን እንደሆነ እና እንዴት ልዩ እንደሆነ መረዳት አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ በተለይ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስብከትን የሚተኩት የግሪክ ቃላቶች ስለ ስብከት ብዙ ነገር ያስተምሩናል።

አንደኛው ቃል ስብከት በውስጡ ምን ምን *እንደያዘ* ይነገረናል። ይህ ቃል በኢንጊሊዘኛው *"ኢቫንጀላይዝ"* የሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም ደግሞ "መልካም ዜናን ለሰዎች መውሰድ" ማለት ነው። አትኩሮትን አሁን የምንሰጠው ሌላኛው ቃል ደግሞ ስብከት ስለምን እንደሆነ ያሳየናል። ይህ ቃል ሲተረጎም "መልዕከተኛ" ማለት ነው። ነገር ግን ይህንን ስንል እንዲሁ ዝም ብሎ መልክተኛ ሳይሆን "አብሳሪ" የሆነ መልክተኛ ማለታችን ነው። አብሳሪ ማለት ደግሞ በንጉስ እና በታላቅ መሪ የተላከ ሰው እና አንድን መልዕክት የንጉሱን ቀጥተኛ ቅላቶች ይዞ ወደ ህዝቡ የሚያመጣ ነው። አብሳሪ ምንም ነገር እንዲጨምር ፣ አንድንም መልዕክት እንዲያወጣ እና መልዕክቱን እንዲተረጉም አልተፈቀደለትም። እርሱ ማለት ያለበት "ንጉሱ እንዲህ ይላል!" ብቻ ነው። በዚህም መልኩ የንጉስ አምባሳደር መሆን ይችላል (2ኛ ቆሮ 5:20, ኤፌ 6:20) ።

ይህንኑ ስብከት ላይ ስንተገብረው አብሳሪ የሚለው ቃል ወንጌልን ሊሰብክ የሚወጣ ሰው ሁሉ በነገስታት ንጉስ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠራ ወይም የተላከ መሆን አለበት ማለት ነው። ማንም እራሱን እንደ ሰባኪ መሾም ሆነ ስራውን በእራሱ ለመስራት መሮጥ አይችልም። ክርስቶስ እንኳን ይህንን አላደረገም (ዕብ 5:5)። ሰው እራሱን ሰባኪ ካደረገ መልዕክቱ ምንም ክብደት የለውም ደግሞም ማንም ሊሰማው አይገደድም።

ምናልባት ምሳሌ ይህንን ሀሳብ እንድንረዳው ያግዘን ይሆናል። ለምሳሌ እንደ ዜጋ የምኖርበት መንግስት ምን እያቀደ እንዳለ በጥቂቱም ቢሆን እውቀቱ ሊኖረኝ ይችላል። ስለዚህም ሌላ ሀገርን ለመጎበኘት ስሄድ ለዚያ ሀገር መንግስት ስለ ሀገሬ መንግስት እቅዶች ለመናገር እራሴን ልሾም እችላለው። ሆኖም ግን የምናገረው መልዕክት በየትኛውም መልኩ ትክክል ቢሆን እንኳን ንግግሬ ስልጣን የለውም ደግሞም ማንም ይህንን ንግግር ሊሰማ ግዴታ የለበትም። መልዕክተኛ ወይም ሌሎች የመንግስቴ ትክክለኛ ተወካዮች ግን መልዕክቱን ቢያመጡ የሀገሩ መንግስት የግዴታ መስማት ይኖርበታል።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰብኩ ሁሉ መላክ እንዳለባቸው ይነግረናል (ሮሜ 10:15)። እነርሱ ካልተላኩ ማንም ለሚናገሩት ነገር ክብር ሊሰጣቸው አይችልም። ይህም መላክ በራሱ ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደሆነው መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን በኩል ለዚህ ተግባር ሰዎችን በመሾም ወይም እጅ በመጫን ይፈጸማል(ሐዋ 13:1-3)።

ይህም አገልጋይ በአገልግሎቱ ተጠያቂ የሆነው ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለቤተክርስቲያናት እና ለሚላክለትም ቤተክርስቲያን ጭምር መሆኑን ያመላክታል (ሐዋ 14:27)። መጠራት ማለት ሁልጊዜ ተጠያቂ መሆን ማለት ነው። ክርስቶስ እንኳን አገልጋዮችን ቤተክርስቲያን እንድትልክ ይናገራል። በዚህም ክርስቶስ ላመጣው መልዕክት ተጠያቂ የሚሆኑ አገልጋዮችን በቤተክርስቲያን በኩል ይጠራል።

ስለ እነዚህ ምክንያቶች በተልኮ አገልግሎት እናምናለን። "እንደመጣልን መስበክ" መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ብለን አናምንም። በማንም ያልተላኩ እና ለማንም ምላሽ የማይሰጡ ሰዎች እውነተኛ አምባሳደሮች እና የክርስቶስ አብሳሪዎች አይደሉም።

## ክርስቶስ እና ስብከት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስብከት የሚናገረው ዋና ነገር የእግዚአብሔር ህዝቦች የክርስቶስን ድምጽ በስብከት ውስጥ መስማታቸውን ነው። በዩሐ 10:27 ኢየሱስ ድምጹን መስማት እንዳለብን ይነግረናል።

በ*ስብከቱም* ውስጥ ድምጹን መስማታችን ከሌሎች ክፍሎች በግልጽ የምንረዳው ነገር ነው (ሮሜ 1:16-17, ሮሜ 10:13-14, 1ኛ ቆሮ 1:18, 23-24, ኤፌ 2፡17)። ለምሳሌ በኤፌ 2:17 ላይ ክርስቶስ እራሱ መጥቶ ሰላምን ለአይሁዳዊያንም ለአህዛብም እንደሚሰብክ የሚናገረውን ክፍል ተመልከቱ። በብሉይ ኪዳንም እንኳን በነብያት በኩል ይሰበክ የነበረው የክርስቶስ መንፈስ ነው (1ኛ ጴጥ 1:10-11)።

ይህ እጅግ አስፈላጊ ነጥብ ነው። ክርስቶስ በስብከት የማይናገር ከሆነ ማንም በወንጌል ስብከት አይድንም። የየትኛውም ሰው ድምጽ ሀጥያተኞችን ሊኮንን እና ወደ ድነት ሊያመጣቸው አይችልም። ይህንን ማድረግ የሚችለው የክርስቶስ ድምጽ ብቻ ነው ። ማንም ሀጥያትተኞችን ሊቀይር እና ወደ እግዚአብሔር ወይም ወደ ክርስቶስ ሊያመጣ አይችልም። ማንም ሀጥያተኞችን ለውጦ በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ሊወስዳቸው አይችልም (ዩሐ 10:27)።

ክርስቶስ በስብከት በኩል በመናገሩ እና ድምጹም ስለሚሰማ ወንጌል "ወደ ድነት የሚያመጣ የእግዚአብሔር ኃይል ነው" (ሮሜ 1:16)። በእርግጥም ወንጌል "ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኃይል እና የእግዚአብሔር ጥበብ" እንደሆነ ያመለከታል (1ኛ 1:23-24)።

ክርስቶስ በወንጌል በኩል መናገሩ ወንጌል የሁለት ገጽታ ያለው ተጽዕኖ እንዳለው ያመላክታል። ያድናል ደግሞም ልብንም ያደነድናል። የህይወት ሽታ ነው ፤ ደግሞም የሞትም ሽታ ነው (2ኛ ቆሮ 2:14-16)። ማንም ወደ ክርስቶስ መጥቶ ድምጹን ሰምቶ ምንም አለመሆን አይችልም። በእግዚአብሔር ጸጋ ድምጹን ለመስማት የሚወድ እና ድምጹን ለመስማት እለተ እለት ያለው ፍላጎት ይጨምራል አልያም ደግሞ እያንዳንዱን ድምጽ ይጠላዋል ደግሞ ጆሮውን እና ልቡንም ያደነድናል (ኢሳ 6:9-10)።

ስለዚህ ሰዎች ባለማመን ውስጥ ሲወድቁ በክርስቶስ ይደናቀፋሉ። እርሱ ወደ ጥፋት የሚወስድ የማደናቀፊያ ድንጋይ ነው። ይህም ደግሞ ሰባኪው የእራሱን ድርሻ በድንብ ከተወጣ በሰባኪው ምክንያት አይደለም።

ይህም ሆኖ ክርስቶስ በወንጌል ስብከት በኩል እንዲሰማ አንዳንድ ነገሮች እውነት መሆን አለባቸው። የመጀመሪያው *መጽሐፍ ቅዱስ* ብቻ መሰበክ አለበት። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ብቻውን ክርስቶስ ለህዝቡ የላከው መልዕክት ነው። ተረት ፣ ቀልድ፣ መዝናኛ፣ እና የሰባኪው ሀሳብ ምንም ያህል ጠቃሚ ቢሆንም ለስብከት ግን አያስፈልግም። ቃሉ ብቻውን መሰበክ አለበት።

ሁለተኛ ስብከት *መብራራት* አለበት። ይህም ቃሉ ብቻ መሰበክ አለበት የሚል ሌላኛው አገላለጽ ነው። በዚህ ዘመን ብዙ ስብከቶች አይብራሩም። አንዳንድ ደስ የሚሉ ሀሳቦች ብቻ ስብከት ላይ ይንጠለጠላሉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ሲብራራ ወይም በድንብ ሲብላላ አናይም።

ሦስተኛ ሰባኪው አስቀድመን እንዳልነው *የታላከ* መሆን አለበት (ሮሜ 10:15)። በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተፍቅዶለት እና ታዝዞ መውጣት አለበት (ሐዋ 13:1-4. ቤተክርስቲያን መላኳ በመንፈስ ቅዱስ እንደመላክ ነው ቁጥ 4)። ሰባኪ ካልተላከ እርሱም ሆነ ሰሚዎቹ ክርስቶስ እርሱን ሊጠቀምበት የሚችልበት እና በእርሱ በኩል እየተናገረ ለመሆኑ ማረጋገጫ የላቸውም። ታዲያ ስብከቱ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው?

እግዚአብሔር የክርስቶስ ድምጽ አሁንም በቤተክርስቲያኖች እንዲሰማ ይፍቀድልን።

## ይየክርስቲያናዊ ቅጣት አስፈላጊነት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተክርስቲያን ቅጣቶች ከአሁኗ ቤተክርስቲያን ላይ ፍጹም ጠፍቷል። በጣም ከባድ ሀጥያት ካልሆነ በቀር በቤተክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ሲታገዱ አንሰማም። አንዳንዴ ከባድ ለሆነ ሀጥያት እንኳን ሳይታገዱ ይቀራሉ። ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች በቤተክርስቲያን አባልነት እንዲቀጥሉ ተትተዋል። የማያምኑ ሰዎች በቤተክርስቲያን ቢሮዎች ያገለግላሉ። አገልጋዮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያለሆነ ነገር

ቢሆንም እንኳን ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸዋል ። ኃጢያት ፣ አለማመን ፣ ወደ ኋላ መመለስ እና አለመታዘዝ ሲገሰጹ አንመለከትም።

በተለይ ብዙ ነገሮች እንደ "ትንሽ" ኃጢያቶች ተቆጥረው ሳይገሰጹ እና ሳይፈተሹ የተተዉ እንደሆነ እጅግ አጥፊዎች ናቸው። ስለ ሌሎች ክፉ መናገር፣ ሐሜት፣ ጥላቻ፣ ወይንም ደግሞ ጸብ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሀጥያት ተብለው ቢሰየሙ ያልተለመደ ነገር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ሀጥያቶች ለቤተክርስቲያንም ሆነ ለእግዚአብሔር አገልግሎት እጅግ አጥፊዎች ናቸው (ምሳሌ. 26፥17–28፤ ማቴ. 5፥21–24)። እነዚህ ወይኑን የሚያበላሹ ትናንሾቹ ቀበሮዎች ናቸው (መኃ 2፥15)።

የቅጣት ማነስ ውጤት ሀጥያት በአጥፊነት ሃይሉ በቤተክርስቲያን ላይ እየበለጸገ እና እያደገ በመሄድ ቤተክርስቲያንን የማጥፋት ደረጃ ላይ መድረሱ ነው ። "ጥቂቷ እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደምታቦካ" በማለት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ኃጢአት የተነገረው ቃል ይህንን ያስታውሰናል (1ቆሮ. 5፥6)። ሁሉ ነገር በቦታው እያለ የመጀመርያን ፍቅር ማጣቷ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሻማዋ እንደሚወገድ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳት አደረገ (ራዕ. 2፥1–7)።

ክርስቲያናዊ ቅጣት የሚፈጸመው በማውገዝ እና በመታገድ ነው። በእውነቱ እነዚህ ድርጊቶች የሚያስደስቱ ባይሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ አብዝቶ እንደሚናገረው ለቤተክርስቲያን ደህና መሆን እና ጤንነት እጅግ ወሳኝ ነገር ነው (ማቴ. 18 17፣ 1ቆሮ 5፡1-13 2ተሰ 3፡14-15 1ጢሞ 1፡19-20 ፣ ራዕ 2፡2)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድን ሰው ማገድ ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት እንደሆነ (1 ቆሮ. 5፡5 ፣ 1 ጤሞ 1፡20) እና ከህብረት ማግለል እንደሆነ ተገልጿል (ማቴ 18:17 ; 2 ተሰ 3:14) በተለይ ደግሞ ከጌታ እራት ህብረት ማግለል አንዱ ነው (1 ቆሮ 5:11 ፣ 13)። በተወሰነ መልኩ ሀጥያትን የሰሩት አካሎች እንዲፈተኑ የሚያደርግ ነው (ራዕ 2:2)።

ክርስቲያናዊ ቅጣት ከባድ እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ በመሆኑ የማይፈጸምበት ዋናው ምክኒያት ይህ ሳይሆን አይቀርም። ቢሆንም ለቤተክርስቲያን ደህንነት ብቻ ሳይሆን ለሀጥያተኞች መዳንም በጣም አስፈላጊ ነው። 1 ቆሮንቶስ 5፡5 የቅጣት ዋነኛ ዓላማ “የሥጋ መጥፋት" እና በጌታ በኢየሱስ ቀን የመንፈስ መዳን እንደሆነ ጠንከር ባለ አገላለጽ ይሞግተናል (2 ተሰ 3፥14 ይመልከቱ)። ከተሓድሶ የእምነት አዋጆች አንዱ መታገድን “የመጨረሻው መፍትሄ”[4] በማለት ይገልጸዋል።

ይሁን እንጂ ቅጣት ሲባል መታገድ ማለት ብቻ አይደለም ።*ሁሉንም* አባላት *መከታተል* እና *መገሰጽንም* ያካትታል። ማቴዎስ 18 ኃጢአተኛው ንሰሀ ለመግባት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ቤተክርስቲያን በአጠቃላይ ወደ ጉዳዩ እንኳ እንደምትገባ ያስተምራል። አማኞች በታማኝነት እነዚህን ሃላፊነቶቹን ከተወጣ መደበኛ ቅጣት እና ከቤተክርቲያን መታገድ ያን ያህል እንደማያስፈልግ እኛ አምነንበታል።

## ክርስቲያናዊ የቅጣት/ተግሳጽ መንገድ

ክርስቲያናዊ ቅጣት በጣም ከባድ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በማቴዎስ 18 በጥንቃቄ የሚተገበሩ ህጎች ተሰጥተውታል። እነዚህም ህጎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

እንደተመለከትነው ቅጣት በተለምዶ ከግል ምክር ወይንም ንግግር ይጀምራል ። አንድ ሰው ሲበድለን ወይም ሲያስቀይመን ጉዳዩን ወደ ቤተክርስቲያን ከማምጣት በፊት ወደ እርሱ በመሄድ ሀጥያቱን ለራሱ መጠቆም አለብን።

የግል ተግሳጽ የተለያዩ ገጽታዎች ትኩረታችንን ያሻሉ ። በመጀመሪያ ከሀጥያት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ከሆነ ለ*ሀጥያተኛው* ለእራሱ እንጂ *ለሌሎች ሰዎች መነገር* የለበትም። የሌሎችን ሃጢያት ለሌሎች ሁሉ መናገር እራሱ በቤተክርስቲያን ውስጥ ገዳይ ክፋት የሆነው ሐሜት ወይም ሚስጥርን የማውጣት ሀጥያት ነው (ምሳ 26:20–26) ። ኢየሱስ በማቴዎስ 18፡15 ".......አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ንገረው......" ያለው ለዚህ ነው።

ሁለተኛ ኃጢአት ወደ ሰራው ሰው የመሄድ ዋና ግዴታ ያለበት *ሀጥያት የተተገበረበት* ሰው ነው(ቁ. 15)። ብዙ ጊዜ በኩራታችን እና በንዴታችን ምክኒያት የበደለን ሰው ወደ እኛ እስኪመጣ እንጠብቃለን። በዚህም ምክንያት ከእሱ ጋር አንታረቅም።'

ሦስተኛ ኃጢአትን ስንገስጽ በትሕትና እና በፍቅር መሆን አለበት ። በማቴዎስ 18 ኢየሱስ ኃጢአተኛ ባልንጀሮቻችንን "ወንድሞች" በማለት ጠርሯቸዋል። በ2 ተሰሎንቄ 3፡15 ስለ አንድ ከቤተክርስቲያን የተገለለ ሰው ስንናገር እንኳን እርሱን"እንደ ወንድም" መምከር አለብን። ብዙውን ጊዜ ወንድምን የማናገኘው ሀጥያቱን በምንገልጥበት ምክኒያት ነው።

ጉዳዩ ወደሌሎች የሚቀርበው (ሌሎች እንዲሳተፉበት የሚደረገው) ኃጢአተኛው ምክር/ ተግሳጽን ካልተቀበለና ካልተጸጸተ ብቻ ነው። ያኔም ቢሆን ሚስጥርን በሚያጋልጥ መልኩ ወይንም እንደ ወሬ ለሌሎች መነገር የለበትም ። ኃጢአተኛው የግድ በምስክር ፊት መቅረብ አለበት (ማቴ. 18፥16፤ ዘኁ. 35፥30)፣ ሃጥያትን እንደሰራ ካመኑ ምስክሮቹ ሃጥያተኛውን ሊመክሩት/ ሊገስጹት ግዴታ አለባቸው (ማቴ.18:17)።

ጉዳዩ በቤተክርስቲያን ወደ ተሾሙት ሽማግሌዎች ፊት የሚቀርበው ኃጢአተኛው ንስሐ ሳይገባ ከቀጠለ ብቻ ነው ። ያንግዜ ለሠራው ኃጢያት እና ንስሃ ለመግባት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይታገዳል ። ቃሉ እንደሚያመለክተው ይህ ከጌታ ማዕድ እና በመጨረሻም በቤተክርስቲያን ውስጥ ከአባልነትና ከአብሮነት መገለልን ያጠቃልላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ *ምክሮች* እንጂ ስለ ምክር እንደማይናገር ልብ ማለት ጥሩ ነው። ፍቅር ለንስሃ እያንዳንዱ እድል እንዲሰጠው ይጠይቃል። መምከር በተቻለ መጠን ኃጢአተኛውን በተለይ ንስሐ ከገባ ሊታለፍ ይገባል (2 ቆሮ 2፥5–8)። በዚህ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ፍቅር ኃጢአትን ይሸፍናል ይላል። ይህም እንዳይታይ ለመደበቅ ሳይሆን ኃጢአተኛውን ከአላስፈላጊ እፍረትና ነቀፋ ለመታደግ ነው (ያዕቆብ 5:19–20)።

ይህ ቢሆንም  መጽሐፍ ቅዱስ በተሰወኑ ጉዳዮች ላይ ኃጢአት ወዲያውኑ እና በሕዝብ ፊት መገሠጽ እንዳለበት ይጠቁማሉ ። ምናልባትም ጴጥሮስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ስፍራን የያዘ ሰው በመሆኑ ይሆናል ጳውሎስ ከጴጥሮስ ጋር እንዲህ ዓይነት ንግግር ያደረገው (ገላ. 2፥11-14) ። በ1ጢሞ 5:20 ላይ ሁለት ጉዳዮች ማለትም አንድ ሰው በአደባባይ ሲሳሳት እና ሰውየው በቤተክርስቲያን ውስጥ መሪ ሆኖ የተገኘ እንደሆን የሚል ጉዳዮች ተነስተዋል (ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው በተለይ ስለ ሽማግሌዎች ነው) ።

ቤተክርስቲያን ውስጥ ጥፋትን እንዳያስከትል ሀጥያት በዚህ መንገድ ሊስተናገድ ይገባል። በዚህ ጊዜ የእኛ ቅዱስ አምላክ ላይ ዘበት ሳይሆን እርሱ ይከብራል ሀጥያተኞችም ይድናሉ።

### ቁርባን

ስለ ስብከት እና ቅጣት ከተናገርን ወዲህ አሁን ወደ ከባዱ ጉዳይ ወደ ቁርባን እንመጣለን። በአንድ በኩል ለቤተክርስቲያን አንድነት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተሰጠን ቁርባን ለመለያየታችን መሆኑ እጅግ የሚያሳዝን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያን የምታምነው ነገር በአብዛኛው ወደ ቁርባናት ላይ የሚያተኩር ነው

ስለዚህ ለቤተክርስቲያን እና ለክርስቲያኖች መለያየት ምክኒያት ቢሆን አይገርምም ነገር በእውነት ላይ አንድነትን ማግኘት እንዲሆንልን ተስፋ እናደርጋለን ደግሞም እንጸልያለን።

ቁርባን ምንድነው? ቁርባን የሚለው ቃል የመጣው “ማህላ” የሚል ትርጉም ካለው የላቲን ቃል ነው። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይገኝም (በአማርኛው ትርጓሜ ይገኛል) እያንዳንዱ ቁርባን ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሰጠው የሚታይ እና የሚዳሰስ ተስፋ እና ማህላ ነው።

*ቁርባን* የሚለው ቃል በተለይም ደግሞ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ለሰጠው ተስፋ ማረጋገጫ እንዲሆን በክርስቶስ የተሰጡትን የተለያዩ የአምልኮ ስርዓቶችን ለማመልከት እንጠቀምበታለን። እነዚህ የአምልኮ ስርዓቶች ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ በቤተክርስቲያን ውስጥ በጥቅም ላይ ይውላሉ (ማቴ. 28፥19–20፤1 ቆሮ. 11 26)።

የአምልኮ ስርዓት ውይም በዓል ምሳሌዎች ወይም ምልክቶች ናቸው። ይህ ኢየሱስ የጌታን እራት ቂጣው "*ሥጋዬ*" ብሎ ሲጠራው እና ጽዋውንም "በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን" ብሎ ሲጠራው በግልጽ የምናስተውለው ነው(ሉቃ. 22፥20)። ቂጣው እና ጽዋ በቀጥታ ስጋ እና ደም ነው ማለት ሳይሆን የክርስቶስ ስጋ እና ደም *ምልክቶች* ናቸው።

ተመሳሳይ ነገርን በጥምቀት ውስጥ እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ የውሃ ጥምቀትን እና በክርስቶስ ደም ከሃጥያት መንጻትን በተመሳሳይ ስም ይጠራቸዋል። ሁለቱም ምልክትና መንፈሳዊ እውነታ አንድ ስም አላቸው። ጥምቀት (ከሐዋ 2፡41 እና 1 ጴጥ 3፡21 ጋር አነጻጽር)።

እነዚህ ምልክቾ እና ምሳሌዎች እምነታችንን ለማገዝ ተሰጥተውናል (መሳ 6፥36– 40 ፣ ሉቃስ 1 18–20 ፣ ሉቃ 2፡12)። በሁለት መንገዶች እምነታችንን ያግዛሉ፡ የመጀመሪያው የማይታዩ መንገስው እውነታዎችን እንድንረዳ በምናባችን ምስል እንዲፈጠር ያግዙናል ሁለተኛው ደግሞ ሙሉ አዳኛችን ክርስቶስ እንደሆነ እንድንረዳ ወደ እርሱ ይጠቁሙናል። አብዛኛውን ጊዜ እምነታችን ደካማ ስለሆነ እና ሳናይ ማመን እንድንችል እነዚህ ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው (ዮሐ. 20፥29፤ 2 ቆሮ. 5፥7)።

በግርዛትና በጥምቀት መካከል ፣ በፋሲካ እና በጌታ እራት መካከል ቀጣይነት እንዳለ በማመን ቁርባኑ *ማህተም* እንደሆነም እንመለከታለን (ሮሜ 4፡11) በእርግጥ ምልክቶች ከሆኑ ማኅተሞችም መሆን አለባቸው ምክኒያቱም ምልክቶች አንድን ነገር ያረጋግጣሉ ወይንም ደግሞ ያትማሉ።

እንደ ማህተምነታቸው ቁርባናት ለአማኞች መንፈሳዊ እውነታዎችን በማሳየት እና አንዳንድ ነገሮችን በማስተማር ብቻ ሳይሆን እምነታችንን በማጠናከር እና በማረጋገጥ ይጠቅሙናል። በጥምቀት ውስጥ ውኃ ሰውነታችንን እንደሚያጥበው ሁሉ እኛም እንዲሁ የክርስቶስ ደም ነፍሳችንን እንደሚያጥብልን እና በእውነትም ቂጣው እና ወይኑ ሰውነታችንን እንደሚያበለጽገው ክርስቶስ ለነፍሳችን ምግብ የሆነውን የዕለት ተዕለት መብል እና መጠጥና በመስጠት እንደሚመግበን በማረጋገጥ እምነታችንን ያጠነክሩታል።

ስለዚህ እነዚህ ቁርባናት ለማያጠፉን፣ ይልቁኑ በድክመታችን ሁሉ ለሚደግፈን ለእግዚአብሔር መልካምነት እና ምህረት አስደናቂ ምስክሮች ናቸው። በዚህም ምክንያት ቁርባናት አስፈላጊ እና በመተግበራችንም በእግዚአብሔር ላይ እንደምንታመን የምናመለክትበት ነው።

## ሁለቱ ቁርባናት

ለምን ሁለት እና ሁለት ብቻ ቁርባናት ኖሩ? ይህ ጥያቄ መልስ የሚያስፈልገው ሮማኒዝም ሰባቱ ቁርባናት በማለት በሠራው ስህተት እና አንዳንድ የፕሮቴስታንት ቡድኖች የእግር መታጠብ ፣ እባብ መያዝና ሌሎች የስርዓቶችን ከፍ የማድረግ ዝንባሌ ስላላቸው እና ስርዓቶቹን ከቁርባናት ጋር እኩል እያደረጉ በመሆናቸው ነው።

አንድ ነገር ቁርባን እንደሆነ እንዴት እናውቃለን? መልሱም ክርስቶስ ራሱ ያዘዘውና በሐዋርያት ትእዛዝ ወይም ተግባር የተረጋገጠ ምሳሌያዊ የአምልኮ ሥርዓት ሲሆን ብቻ ነው ። ይህንን የቁርባናት "ተቋም" እንለዋለን። ይህ እግር ማጠብን ከቁርባንነት ተርታ ያወጣዋል። ምንም ያህል ክርስቶስ የደቀመዝሙርቶቹን እግር ቢያጥብም፣ ትዕዛዝ እና የቤተክርስቲያን አምልኮተ ስርዓት እንዲሆን አልታዘዘም ደግሞም በሐዋሪያት ምሳሌነት ሲረጋገጥ አንመለከትም።

በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተጨመሩት ነገሮች እነዚህን መመዘኛዎች እንደማያሟሉ ግልጽ ነው (እንደ እግር ማጠብ ስርዓት)። የልጆች አዋጅ፣ ንሰሀ መግባት፣ እና ደግሞ ሌሎች ሀይማኖታዊ ተግባራት ለየትኛውም ነገር ምልክቶች አይደሉም፤ ለምሳሌ (extreme uniction) ወይንም በጠና የታመመ ወይንም ሊሞት ያለን ሰው ለመንግስተ ሰማይ እንዲዘጋጅ ዘይትን መቀባት እና የመሳሰሉት ነገሮች በክርስቶስ ሆነ በሐዋሪያት

የታዘዙ አይደሉም። ጋብቻም ምልክት ቢሆንም በክርስቶስ እና በሐዋሪያቶች እንድንፈጽመው የምንገደደው ተግባራት አይደሉም (1ኛ ቆሮ 7:1, 6-8, 25-27, 32-24)።

ሆኖም ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ ጥያቄያችንን አይመልሱም። ለምን ሁለት ቁርባናች ብቻ ኖሩ? ለምን የጌታ እራት እና ጥምቀት ብቻ ቁርባን ሆኑ? ቁርባናትን የበለጠ እናከብር እና እንጠቀምበት ዘንድ ይህ ለምን እንደሆነ መናገር አለብን።

ለምን ሁለት ቁርባናት ብቻ እንደሆኑ በራሳቸው ውስጥ ተገልጿል። ሁለቱ በአንድነት የእኛን አጠቃላይ የክርስትና ህይወት ይወክላሉ። ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን መግባትን ፣ መዳንን እና የምንገባበት መንገድ የሚያመላክት ነው ። የጌታ እራት የሚያመለክተው በዚያ ቃል ኪዳን ውስጥ ክርስቶስ በነጻነት የሰጠውን ማዳን እና በመደሰት ስንኖር ያለውን ህይወታችንን ይወክላል።  ስለዚህ ሌሎቹ ቁርባናት የሚባሉት ነገሮች ምንም ምልክት ስለሌላቸው ቁርባን ሊሆኑ አይችሉም።

የቁርባናት አስደናቂ ነገር የእኛን የክርስትና ህይወት በሁለት ገጽታ በምሳሌንት ማሳየታቸው ነው ስለክርስቶስ ድምር ምስክርነትን ይሰጣሉ። አንድ ላይ ሆነው እኛ ከእርሱ፣ በእርሱ፣ እና በእርሱ በኩል እንደሆነ እና ያለ እርሱ ምንም ነገር እንደሌለን ያመላክቱናል። ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 4፡12 ላይ  "መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች የለምና" ያለውን ይህንን ያረጋግጡልናል። ምስክርነታቸው በኤፌሶን 1፡3 ላይ የጳውሎስ እንደመሰክረው አይነት ናቸው እርሱም "መንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ"  በክርስቶስ አለን የሚል ነው።

ቁርባን የክርስቶስ ሞት እና ደምን ማዕከላዊነት ይናገራል ። ጥምቀት በደሙ እና በመስዋዕትነት ወደ ክርስትና ሕይወት እንደምንገባ ያስታውሰና። የጌታ እራት ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ህብረት ከገባን በኋላ የምንኖረው ፣ የምንቀሳቀሰው ፣ መንፈሳዊ ማንነታችንን ፣ ጥንካሬያችንን እና ለነፍሳችን ብልጽና የሚያስፈልገንን ነገሮች ሁሉ በክርስቶስ ደም እና መስዋዕትነት እንዳገኘን ያስረዳናል። የክርስቶስ መስዋዕትነት ለኛ ሁሉ ነገራችን ነው።

 እግዚአብሔር እንዴት ያሉ ድንቅ ስጦታዎች በቁርባኑ በኩል ሰጥቶናል ! እምነት በሌለው እና በግዴለሽነት አንጠቀምባቸው።

**የጥምቀት ተምሳሌት**

ይህ ዋና ጉዳይ በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳት ጥናታችንን የምንጀምረው በፍርሀት እና በጥንቃቄ ነው ። በጥምቀት የሚያምኑን (በፕቲስቶችን) ማስቀየም ሆነ የማስቀየም ፍላጎት የለንም ሆኖም ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ግልጽ እንደሆነ እናምናለን። የምንለውን እንዲያደምጡን ብቻ እንጠይቃለን።

የመጀመሪያው ጉዳይ የጥምቀት *ምሳሌ* ነው ። እኛ ሮማኒዝም ፣ አንጊሊካኖች እና ሉተራኖች እንደሚያስተምሩት የጥምቀት ውኃ በራሱ ምንም ዓይነት ውጤታማነትም ወይም ኃይል አለው ብለን አናምንም። የጥምቀት ዋጋ ያለው *ምሳሌ* መሆኑ ላይ ነው።

የጥምቀት ውሃ የክርስቶስ ኢየሱስን ደም እንደሚወክል እና በሰው ላይ ውሃው መደረጉ (በምን አይነት መልኩ ይደረጋል የሚለውን ክርክር ለጊዜው ትተነው) በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የሀጥያትን መታጠብ ይወክላል።

በሌላ አነጋገር ጥምቀት የመዳንን ተግባራዊነት በመጽደቅ (የኃጢአታችንን ጥፋተኝነት ማስወገድ) እና በመንጻት (የኃጢአታችንን ቆሻሻ እና ብክለት) ይወክላል። ስለዚህ ጥምቀት ይቅርታችንን ይወክላል ይህም ይቅርታ በእምነት በኩል በመጽደቃችን የምናገኘው እና እግዚአብሔር በዳግም ልደት እና በመንጻት እኛን ቅዱስ ሲያደርግ የምንቀበለው ነው።

ከዚህም ባለፈ ጥምቀት በመጽደቅ እና በመቀደስ ሀጥያታችን ታጥቦ በመወገድ የድነትን ተግባራዊነት እንደሚወክል በመሆኑ ተስማምተናል። እንደገና ደግሞ ውሃው የክርስቶስን ደም የሚወክል ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን መንፈስም ይወክላል። በመንፈስ ቅዱስ ታጥበናል ደግሞም እንታጠባለን (እንጠመቃለን) በዝህም ሀጥያት ይነጻል ክስም ይደመሰሳል።

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስን ስጦታ እንደ ጥምቀት የሚገልጽው በዚህ ምክንያት ነው (ማቴ. 3፥11 ፣ ሐዋ 1 5 ፣ ሐዋ 11 16፤ 1 ቆሮ. 12 13)። በሀጥያት መንጻት ውስጥ መንፈስ ታላቁ ስራው ጥምቀት ነው። እርሱ ለመጽደቃችን እና ለመንጻታችን ይሆን ዘንድ በእኛ ላይ የክርስቶስ ኢየሱስን ደም ይረጫል። ይህንንም የሚያደርገው እራሱን ለእኛ በመስጠት ስለሆነ ድነትን ስናገኝ *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም* ብቻ ሳይሆን *በመንፈስም ተጠምቀናል* ማለት እንችላለን።

ይህ ብዙ አስፈላጊ ውጤቶች አሉት ። የመጀመሪያው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለድነት ተጨማሪ ነው የሚለውን የጴንጤቆስጤ ስህተትን ለመመከት ይረዳል። በመንፈስ መጠመቅ እራሱ ድነት ነው። ይህም ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ተቀምጦልናል (የሐዋ 2:38፧39, ሮሜ 5:1፣5, ሮም 8:9, 1ኛ ቆሮ 12:13ን ከዩሀ 7:37፧39, ገላ 3:2, ኤፌ 1:13.14

ይህ ሁሉ ደግሞ ጥምቀት *እንዴት መሆን* እንዳለበት ይወስናል። ጥምቀት የክርስቶስን ደም እና መንፈስ የሚወክል ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ክንዋኔውን በመረጨት ወይንም ደግሞ በማፍሰስ እንደገለጠው ማስተዋል አለብን። ይህንን ነጥብ "የጥምቀት መንገዶች" በሚለው ርዕስ ሥር እናብራራለን። እዚህ ርዕስ ላይ ያለው ቁም ነገር ጥምቀት ውብ መሆኑ ነው። በደምና በመንፈስ መታጠብን እና የሀጥያት መወገድን ያመለክታል። በኢየሱስ ክርስቶስ እና በዚህም ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንዴት እንደገባን ያሳያል፤ እርሱም በጸጋው እና በክርስቶስ ብቻ ነው።

## የጥምቀት ምልክት እና እውነታነት

ስለጥምቀት በምናነሳበት ጊዜ አዲስ ኪዳን *ጥምቀትን* በሁለት መንገድ መጠቀሙ ልናስተውለው የተገባ ቁልፍ ነገር ነው። ይህንን አለማስተዋል ወደ ግራ መጋባት እና ስህተት ይመራል።

አዲስ ኪዳን *ጥምቀት* የሚለውን ቃል ሲጠቀም አንዳንድ ጊዜ ሚስጥርን ወይንም ስርዓትን እየወከለ ነው። ይህንንም ስርዓት እኛ *የውሃ ጥምቀት* እንለዋለን (ማቴ 3:7 ፣ ማቴ 28:19; ሐዋ 2:38, 41; 1 ቆሮ. 10:2)። የውሃ ጥምቀት ዋናው ጥምቀት አይደለም ነገር ግን የጥምቀት *ምልክት* ሲሆን የሚወክለውም መንፈሳዊ እና የማይታየውን እውነታ ነው።

ከምሳሌነቱ በመነጠል *የጥምቀት እውነታ* በክርስቶስ ደም እና በመንፈስ ቅዱስ ከሀጥያታችን መታጠብ ነው። የውሃ ጥምቀት የሚወክለው እውነታ ይህንን ብቻ ነው። ስለጥምቀት በመንፈሳዊው አውድ ያወራን እንደሆነ ጥምቀት ያድናል ማለታችን ትክክል ነው (1 ጴጥ 3:21)።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የውሃው ጥምቀት ምሳሌ ሳይሆን በመንፈሳዊ አውድ የምንመለከተው ጥምቀት እንደሚያድን ይናገራሉ (ሮሜ 6:3–6 ፣ 1 ቆሮ 12:13 ፣ ገላ 3:27፣ ኤፌ 4:5 ፣ ቆላ  2:12)። እነዚህ ክፍሎች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ (ከመንፈስ ቅዱስ) ስለመጠመቅ ይናገራሉ።

አንዳቸውም ስለ ውሃ ጥምቀት የሚያወሩ አይደሉም። ይህን ያልተረዳን እንደሆነ ወደተለያዩ ስህተቶች ውስጥ የምንወድቅ እና ውሃ ያድናል ወይም ውሃ ወደ ክርስቶስ ህያው ህብረት ያቀርበናል ወደሚል የተሳሳተ ድምዳሜ እንደርሳለን (1 ጴጥ 3:21 ፣ 1 ቆሮ 12:13)።

በምልክቱ እና በእውነታው ላይ ያለው ልዩነት በውሃ የተጠመቁ ሁሉ እውነተኛውን ጥምቀት የተቀበሉ አለመሆናቸው እና በእውነተኛ ጥምቀት የተጠመቁ ነገር ግን በውሃ ጥምቀት ያልተጠመቁ የድነት ጥምቀት የላቸውም ማለት አይደለም።

ነገር ግን እነዚህ ሁለት ነገሮች የተያያዙ ናቸው። አንደኛው የሌላኛው ምልክት ወይም ምሳሌ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ወደ "ቺካጎ" የሚል ነገር ግን ወደ ሂዩስተን አቅጣጫን የሚሰጥ ምልክት በተሳሳተ መንገድ ይመራል። እኛን ለመርዳት እንደመቀመጡ ምልክት ሁልጊዜም ወደ እውነታው መምራት አለበት። እንዲሁም እውነታው ከምልክቱ ጋር ምልክቱም ከእውነታው ጋር አንድ ሊሆኑ ይገባል።

ለምሳሌ *የውሃ ጥምቀት* አተገባበር ጥያቄዎች *መንፈሳዊውን ጥምቀት* በመመርመር ሊመለሱ ይችላሉ። ምናልባት "በክርስቶስ ደም እና በመንፈሱ እንዴት እንጠመቃለን?" ብለን የጠየቅን እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መልሱ "በመረጨት ወይም በማፍሰስ" የሚል ይሆናል። ምልክቱ እና እውነታው የማይገናኝ ቢሆን እንግዳ ነገር እና ወደ ስህተት የሚመራን ይሆን ነበረ።

በተመሳሳይ መልኩ እውነታው ከምልክቱ ጋር መመሳሰል አለበት።ይህ ባይሆን የክርስቶስን ሞት በመወከል፣ በክርስቶስ መስዋዕትነት የሆነልንን የሀጥያት መንጻት የሚወክሉትን ቂጣውን መብላት እና ጽዋውን መጠጣት ባላስፈለገን ነበረ።

በእርግጥ እውነታውን እንድንረዳ እና እንድናምን ክርስቶስ ይህን ምልክት ለእኛ ሰጥቶናል። እኔ ምናልባት "ማንኛውም ነገር ሃጥያቴን ፈጽሞ ሊያጥብልኝ ይችላል? ይህ ከማመን በላይ ነው። ሃጥያቶቼ ብዙ እና ከባባድ ናቸው" ብዬ ልናገር እችላለው። ከዚያም የጥምቀት ምልክቱ "ውሃ የሰውነትን ቆሻሻ ማንጻቱ እውነት እንደሆነ የክርስቶስም ደም ሃጥያትን ሁሉ ያጥባል" በማለት በክርስቶስ እና በመስዋዕቱ ላይ እምነት እንዲኖረኝ ያበረታታኛል።

## የጥምቀት ትርጉም

በአዲስ ኪዳን *ጥምቀት* የሚለው ቃል ትርጉም “ማጥለቅ (immerse)” ወይንም “ሙሉ በሙሉ ውሃ ውስጥ ማጥለቅ (submerse)” ነው የሚል ሀሳብ አለ። ጥምቀት እንዴት ይተገበራል ወደሚለው ጥያቄ ሳንገባ ይህ አስተሳስብ ግን ትክክል እንዳልሆነ በጥቂት ጥናት እንመልከት።

እንደዚህ አይነት ጥናት በአዲስ ኪዳን ጥምቀት የሚለው ቃል “ማጥለቅ” የሚል ትርጉም እንደሌለው የሚያመላክቱ በርካታ ክፍሎችን ያሳየናል። ስለዚህ በዚህ እምነት ውስጥ ያሉት ሰዎች የሌሎችን ልማድ በመከተል ጥምቀትን “ሰዎችን በውሃ ውስጥ በማጥለቅ” እየከወኑ በእኛ ላይ እንዳይፈርዱ ሀሳባችንን እንዲያዳምጡ ልመናችንን እናቀርባለን ። ከታች የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በምንም አይነት ሁኔታ ጥምቀት ማለት “መጥለቅ” መሆኑን አይናገሩም።

ማርቆስ 10:38–39 “ ኢየሱስ ግን :- የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ ፥ እኔ የምቀምሰውንም ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን አላቸው?” ስለ ጥምቀት ሲነሳ በዚህ ክፍል ውስጥ ጥምቀትን እንደ መጥለቅ/ማጥለቅ መረዳት ትርጉም የለሽ ነው። በርግጥ በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለመከራው እና ስለሞቱ ነው ( ሉቃ 12:50 ተመልከት)። በመከራው እና በሞቱ ተውጧል/ ጠልቋል ማለት ትርጉም የማይሰጥ ነው።

1 ቆሮንቶስ 10:2 “ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመና እና በባህር ተጠመቁ” ። ይህ ቁጥር እስራኤላዊያን ከሙሴ ጋር በባህር እንደተጠመቁ ይናገራል። በደመና እና በባህር የሚሉት ቃሎች በቀጥተኛ ትርጉማቸው አልተቀመጡም። ነገር ግን የግሪኩን መጽሐፍ ስንመለከት “በሙሴ በኩል” በደመናና በባህር ተጠመቁ የሚልን ትርጉም እናገኛለን። ቁጥሩ በሙሴ ውስጥ ጠልቀዋል እንዴት ሊለን ይችላል? ስለዚህ ጥምቀት የሚለው ቃል ሌላ ትርጉም ሊኖረው ይገባል።

1 ቆሮ 1:13: “ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቅሏልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁ?”። በዚህ ክፍል ጳውሎስ እንደ 1ቆሮ 10፡2 ተመሳሳይ ቋንቋን ይጠቀማል። እንዲሁ ኢየሱስ በማቴ 28:19 ላይ ተመሳሳይ ነገርን ይናገራል። በአብ ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ወይም በሌላ ስም *ውሃ ውስጥ መጥለቅ* ምን አይነት ትርጉም ሊኖረው ይችላል?

1 ቆሮ 12:13: “የግሪክ ሰዎች ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል። ሁላችን አንዱን መንፈስ ጠጥተናል”። የእግዚአብሔር ቃል በአንድ አካል

*ጠልቀዋል* እያለ ነው? ይህ ትክክለኛው ትርጉም ይሆናል ብሎ ማሰብ የሚከብድ ነገር ነው። እንደ እውነታው በዚህ ክፍል ቃሉ እየተናገረ ያለው ስለመጥለቅ ሳይሆን ስለመጠጣት ነው!

ከመንፈስ ቅዱስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ስለመጠመቅ የሚያወሩ ጥቅሶች ስለማፍሰስ ወይም ስለመንፈስ መረጨት እንጂ ለመጥለቅ አይናገሩም (ሐዋ 1:5 ፣ ሐዋ 2:17–18)።

ታዲያ *ጥምቀት* ምን ማለት ነው? ጥምቀት "ሁለት ነገሮች በመነካካታቸው ምክኒያት የአንዱ ሁናቴ በሌላኛው ይቀየራል" ማለት ነው። ይህ ቃል ንክኪው ምን አይነት እንደሆነ አያብራራልንም፤ በመረጨት፣ በማፍሰስ፣ በማጥለቅ ይሆን በሌላ መንገድ የሚናገረው ነገር የለም።

ስለዚህ 1ቆሮ 10፡2 እንደሚያስቀምጥልን ከሙሴ ጋር መጠመቅ ማለት እግዚአብሄር ሲሾመው እና መካከለኛቸው ሲያደርገ እስራኤላዊያን ከእርሱ ጋር መነካካት ችለዋል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ሁኔታቸው ከባርነት ወደ ነጻነት ተለውጧል። ክርስቶስ በሞቱ ተጠምቋል ማለት ተውጠዋል ማለት ሳይሆን በእኛ ምትክ የጸደቀ እንዲሆን በእኛ ምትክ የእርሱ ሁኔታ በእግዚአብሄር ፊት የጥፋተኝነቱ ሁኔታ እንዲቀየር ከሞቱ ጋር በተቀራረበ መነካካት ተነካክቱል ማለት ነው።

ሮሜ 6:1–6 በክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ ተጠምቀናል ብሎ ሲናገር በድርጊቶቹ ላይ ተውጠዋል እያለን አይደለም (ክፍሉ ምንም ማለት ቢሆን)። ክፍሉ በእምነት በኩል ከሞቱ እና ከትንሳኤው ጋር ተገናኝተን ሁኔታችን ሙሉ ለሙሉ እና ለዘላለም የመቀየሩን እውነታ እየተናገረ ነው። የአማኝ የመጠመቁ እውነታ ትርጉም ይህ ነው።

## የጥምቀት መንገዶች

ስለ ጥምቀት መንገዶች ስንነጋገር የትኛውንም ሰው ልናናድድ ሆነ በክርስቶስ ቤተክርስቲያን መካከል መከፋፈልን ልናጎላ አንፈል። በእነዚህ ጉዳዮች በተለይም ከዚህ ርዕስ በቀር በሌሎች ጉዳዮች ከምንስማማቸው ሰዎች ስምምነትን እንድናገኝ ጥልቅ ፍላጎታችን ነው ።

ይሁን እንጂ ሕፃናትን ውሃ መርጨት የሚያስችል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንደሌለና እንዲህ ዓይነቱ ልማድ ከሮማውያን የተወሰደ እንደሆነ ብዙ ጊዜ እንሰማለን።በእርግጥ ቤተክርስቲያን ህጻናትን የምታጠምቅ

ከሆነ በሌሎች ነገሮች ላይም ችግር እንዳለባት የሚናገሩ የካልቪኒዝም አስተምህሮችን ተቃዋሚ በርካታ መጽሐፍት በገበያ ላይ አሉ።

ስለጥምቀት መንገዶች ሲነሳ መረጨት/ውሃን ማርከፍከፍ ትክክለኛ ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለው ብቻ ሳይሆን *ብቸኛው* የጥምቀት መንገድ ነው ብለን እናምናለን። እስኪ ጉዳዩን በጥልቀት እንመልከት።

መረጨት በሮማዊያንም የሚደረግ ተግባር መሆኑ ምንም ክርክር እንደማያስነሳ እርግጥ ነው። ሆኖም ግን አንድ ነገር የሮማዊያን አስተምህሮ በመሆኑ ሊወገድ ካስፈልገው እንግዲ ሥላሴም ጭምር ሊወገድ ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪም በRomish liturgy ላይ ስለህጻናት ጥምቀት በተሰጠው ትዕዛዝ ለአጥማቂው የተቀመጠ "እርሱ ህጻናቱን *እንዲጠልቁ* ያደርጋቸዋል ወይም *ውሃ በላዩ ላይ* ያፈሳል" ይላል።ይህ ማለት ሮማናዊያንም በማጥለቅ ያምናሉ ማለት ነው። ስለዚህ ከሮማኒዝም ጋር የሚደረግ ክርክር ወደጎን መተው አለበት።

መረጨት ወይም ማፍሰስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረትን የያዘ በመሆኑ ልንሳሳትበት የማንችልበት ጉዳይ ነው። ከታች ያስቀመጥናቸውን እውነታዎች ለመጥቀስ እንወዳለን።

ሁሉም የብሉይ ኪዳን የጥምቀት ስነስርዓቶች በመረጨት ወይም በማፍሰስ የሚከወኑ ናቸው። በዚህም በአዲስ ኪዳን ጥምቀት የሚለው ቃል በንጉስ ያዕቆብ እትሙ ላይ "ማጠብ" የሚለውን ቃል የሚጥቀመው። ዕብ 9፡10 ላይ እውነተኛው ጥምቀት በግልጽ ተቀምጧል (በተጨ. ቁጥር 13, 19, 21 ይመልከቱ)።

በውሃ ጥምቀት የተመሰለው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁልጊዜ በመረጨት ወይም በማፍሰስ ተገልጿል (ኢሳ 44:3 ፣ ህዝ 36:25 ፣ ኢዩ 2:28–29 ፣ ሚል 3:10 ፣ ሐዋ 2:17 ፣ 18 ፣ ሐዋ 10:44–45)።

በተመሳሳይ በውሃ የተወከለው የክርስቶስ ደም ተግባር በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ሁልጊዜ በመረጨት ተገልጿል (ኢሳ 52:15 ፣ ዕብ 10:22 ፣ ዕብ 12:24 ፣ 1 ጴጥ 1:2)።

የብሉይ ኪዳኑ የነበሩ ታላላቅ ጥምቀቶች በማጥለቅ የተፈጸሙ አልነበሩ፣ (1 ቆሮ 10:2 ፣ 1 ጴጥ 3:20–21)። በዚህ አይነተኛ ጥምቀት የጠለቁር ፈርዖን ከወታደሮቹ ጋር እና በኖህ ጊዜ የነበረው እግዚአብሔራዊ ያልሆነው አለም ነው። በተመሳሳይ ክፉው በእሳት ባህር ሊጠልቅ/ሊዋጥ ይገባዋል። ስለዚህም መጥለቅ/መዋጥ የፍርድ እንጂ የጥምቀት ምሳሌ እንዳልሆነ እናምናለን።

## የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እና የኢየሱስ ጥምቀት

ስለጥምቀት መንገዶች ጥናታችንን በመቀጠል ስለ ኢቶጵያዊው ጃንደረባ እና ስለኢየሱስ ጥምቀት ልንመለከት እንወዳለን (ሐዋ 8 ፣ማቴ 3 ፣ ማር 1)። እነዚህ ክፍሎች ስለመጥለቅ የሚናገሩ ግልጽ ምሳሌዎች ናቸው።

*የጃንደረባው ጥምቀት*። በተለምዶ "ከውሃ ውስጥ መውጣት" የሚለው ጥምቀትን የመጥለቅ ትርጉም ይሰጠዋል። በሐዋ 8፡38-39 ላይ የጃንደረባው ጥምቀት መጥለቅ ነው ተብሎ እንዲብራራ ሆኗል። ሆኖም ግን ይህ ምልከታ ውስጥ ሁለት ስህተቶች አሉት።

የመጀመሪያው "ወደ/ ወደ ውስጥ/ into " (eis in Greek) እና " ወደ ውጪ መውጣት/ out of" (ek) የሚሉት የግሪክ ቅጥያዎች መጥለቅን አያመላክትም። ይህ ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው ውሃ ውስጥ መግባቱን እንኳን የሚያመላክቱ ቃላቶች አይደሉም። በአዲስ ኪዳን "into ወደ/ወደ ውስጥ" የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ ተተርጉሟል ለምሳሌ "at/ስፍራን በመጠቆም" (20 ጊዜ), "in/ ውስጥ" (131), "into/ ወደ ወደውስጥ" (571), "to/ለ" (282), "toward/ወደ እርሱ/እርሷ/እነርሱ" (32), and "unto/በእርሱ/እርሷ/እነርሱ ላይ" (208)። እነዚህ ሁሉ በጥሩ ጥናት መረጋገጥ የሚችሉ ናቸው። ደግሞም out of/ መውጣት የሚለው ቃል በብዙ መልኩ ተተርጉሟል ለምሳሌ "from/ከ" (182 ጊዜ), "up from/ከሆነ ነገር መነሳት" (2), and "out of/ ከሆነ ነገር መውጣት" (131) የሚሉትን ያጠቃልላል። የተለያየ ትርጉምን በሁለቱ ክፍሎች ውስጥ በመተካት የሚያመጣውን ልዩነት መመልከት ይቻላል። ነጥቡ እነዚህ ሁለት ቃላት ጥምቀቱን ሳይሆን ከጥምቀቱ በፊት ነና በኋላ የሆነውን ነገር የሚያመላክቱ መሆኑ ነው።

በሐዋ 8 ከጥቅምቀት ጋር የተቀመጡት እነዚህ ቃላት ጥምቀትን ሊያብራሩ አይችሉም ምክኒያቱም ግስነታቸው ለፊሊጶስ እና ለጃንደረባው ነው። በመጥለቅ የሚሆንን ጥምቀት የሚወክሉ ከሆነ ፊሊጶስ እራሱ እራሱን በማጥለቅ አጥምቋል ማለት ነው። ፊሊጶስ እራሱ "ወደ ውሃው ወረዱ" እና "ከውሃው ወጡ" ተብሏል። ቃሉ የሁለቱንም ጥምቀት በመጥለቅ እንዳከናወኑት እየነገርን ነው ወይም ደግሞ ስለጥምቀቱ ምንም እየተናገሩ አይደለም።

የመጨረሻው እና በጣም አስፈላጊው የኢየሱስን ጥምቀት በቃሉ ብርሃን ከተመለከትን በመጥለቅ እንደማይሆን እንረዳለን። በማቴ 3 እና በማር 1 ላይ ስለኢየሱስ ጥምቀት የተገለጸውን እውነታ እንመልከት።

በማር 1 ላይ በሐዋ 8 ላይ የተጠቀሰው ተመሳሳይ የግሪክ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል። በማቴ 3፡16 ላይ apo/አፖ የሚል የተለየ የግሪክ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ቃል "from" 372 ጊዜ እና "out of" 27 ጊዜ ብቻ ተብሎ ተተርጉሟል።

በኢየሱስ የጥምቀት ትርክት ላይ የሚስተዋል ተጨማሪ ነገር አለ። በሰላሳ አመቱ፣ በካህን፣ በውሃ መጠመቁ እንዲሁ የምናልፈው ጉዳይ አይደለም (ሉቃ 3:23 ፣ መጥምቁ ዩሐንስ እንደ አባቱ ዘካሪያስ ካህን ነበረ ፣ ሉቃ 1:5, 13)። በሚጠመቅበት ጊዜ ኢየሱስ "ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና" ብሎ ተናግሯል (ማቴ 3:15)።

ኢየሱስ "ጽድቅን ሁሉ" በጥምቀት መፈጸሙ የሚያመላክተው ህጉ የሚጠይቀውን ጽድቅ ሁሉ ማሟላቱን ነው። ህግ ምንድነው? ካህን የሚሾምበት ህግ ነው። ካህን ሰላሳ አመት እስኪሞላው ድረስ አይሾምም (ዘኍ 4:3 ፣ 47)። ይህን ማሟላት ሲችል በሌላ ካህን ውሃውን በመርጨት የሚሾም ይሆናል (ዘጸ 29:9 ፣ ዘኍ 25:13 ፣ ዘኍ 8:6–7)። ስለዚህ ህጉን በመፈጸም ረገድ ኢየሱስ ሊጠመቅ የሚችለው በመረጨት ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ህጉን እየፈጸመ ሳይሆን እየጣሰ ነው። የክርስቶስ ጥምቀት የጥምቀት ዘዴ በመጥለቅ መሆኑን ለማመላከት የሚቀርብ ምሳሌ ሳይሆን በተቃራኒው ጥምቀት በመጥለቅ የሚያመላክት ነው። ጥምቀትን ከዚህ በተለየ መልኩ የሚመለከቱት ይህንን እንዲያጤኑበት እንለምናለን።

## የሕጻናት ጥምቀት በአዲስ ኪዳን

ስለ ህጻናት ጥምቀት የሚነሳው የተለመደ ተቃውሞ በአዲስ ኪዳን አንድም ህጻን ስለመጠመቁ የሚያመላክት የመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ የለም የሚል ነው። ይህ በቀላሉ ትክክል አይደለም። ይልቁንም ሁለት የህጻናት ጥምቀቶች በአዲስ ኪዳን አሉ።

የመጀመሪያው ቀድመን ለሌላ ሀሳብ የተመለከትነው "ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመና እና በባህር ተጠመቁ" የሚለው የ1 ቆሮንቶስ 10:2 ክፍል ነው። የእስራኤላዊያን በቀይ ባህር መሻገር በጥምቀት መልኩ ተገልጧል ይህም ጥምቀት ህጻናትን ያካተተ ነው (ዘጸ 10:9 ፣ ዘጸ 12:37)። ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚቆጠሩ እስራኤላዊያን ከግብጽ ሲወጡ በመካከላቸው ህጻን አልነበረም ብሎ መካድ እጅግ የሚከብድ ጉዳይ ነው (ዘጸ 12:37–38)።

ሀሳቡ ቀይ ባህርን መሻገር በአዲስ ኪዳን አገላለጽ እና ቃል አጠቃቀም ጥምቀትን የሚያመላክት ነው። ይህንን ሁነት ለመግለጽ በ1ቆሮንቶስ 10፡2 ላይ ጥምቀት የሚል የአዲስ ኪዳን ቃል ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ በብሉይ ኪዳን መፈጥሩ ባፕቲስቶስ የሚያነሱት የመከራከሪያ ሀሳብ ነው። የጥምቀት ግሪክ አቻ ቃሉ አስቀድመን እንደተመለከትነው ሁሌም መጥለቅን እንደማያመለክት ተነጋግረናል። እስራኤላዊያኖች በቀይ ባህር ውስጥ አልሰመጡም።

ከዚህም በተጨማሪ በብሉይ ኪዳን ቀይ ባህርን መሻገር ጥምቀት በአዲስ ኪዳን የመጣ አዲስ ነገር አለመሆኑን ያሰምርበታል። ዕብራዊያን 9፡10 “.....ስለ ምግብ እና ስለ መጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠብ የሚሆኑ የስጋ ስርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን ህሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም።” በማለት በግልጽ እንደሚያስቀምጠው በብሉይ ኪዳን በርካታ ጥምቀቶች ነበሩ። *መታጠብ* የሚለው ቃል በቀጥታ *መጠመቅ* የሚለው ቃል ነው። ይህም እውነተኛ ጥምቀት መሆኑ በአዲስ ኪዳን ስለተጠቀሰ የተረጋገጠ ነው። ቁጥር 19 ላይ ጥምቀቱ በ“ሁሉም ህዝብ” ላይ በመከናወኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ህጻናትንም እንደሚያጠቃልል እንረዳለን (ዘጸ 20:12)።

ባፕቲስቶች እንደሚቃወሙት *የተለመዱ* የጥምቀት ስርዓት መሆናቸው የሚለውጠው ነገር የለም። *ሁሉም* የውሃ ጥምቀቶች ምሳሌያዊ እና ወደ አንድ ነገር የሚያመላክቱ ናቸው። የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን ጥምቀቶች *ተመሳሳይ ነገርን ይመስላሉ* - እርሱም በክርስቶስ ደም እና በመንፈሱ የሀጥያት መታጠብ ነው (1 ቆሮ 10:2 ፣ በተለይ ዕብ 9:13–14 ፣ 22፣ እና 1 ጴጥ. 3:21)።

ጥቅሶቹ የብሉይ ኪዳኑ ጥምቀት ከአዲሱ ኪዳን ጥምቀት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ስለሚያመላክቱ እጅግ ወሳኝ ናቸው። ሁለቱም በክርስቶስ ደም የሀጥያት መንጻትን እና ክስ መደምሰስ ያመላክቱናል (ዕብ 10:22–23)። በብሉይ ኪዳን መጠመቅ በአዲስ ኪዳን ከመጠመቅ ጋር እኩል አስፈላጊነት አለው። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት አንደኛው የክርስቶስን ሞት በመጠባበቅ የሚደረግ ምሳሌ ነው ሌላኛው ደግሞ ይህ ከተፈጸመ ብኋላ የሚደረግ ምሳሌ ነው።

በሁለቱ ኪዳናት መካከል መሰረታዊ የሆነ ልዩነት ባለመኖሩ በጥምቀትም ዙሪያ ምንም አይነት ልዩነት የለም። ከዚህ በተለየ መልኩ ማሰብ ብሉይ ኪዳን ከአዲስ ኪዳን ወደ ሚለየው የዲስፔንሽናሊዝም አስተምህሮ ማቅናት ነው።

መጥምቁ ዩሀንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ማጥመቅ ሲጀምር ጥምቀት በእስራኤላዊያን ዘንድ ያልተሰማ እና የማይታወቅ አዲስ ነገር አልነበረም። እንዲሁም በብሉይ ኪዳን የህጻናት መጠመቅ ሊያስደንቀንም አይገባም። ነገር ግን በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን አንድ የእግዚአብሄር ህዝብ ፣ አንድ ኪዳን ፣ አንድ የድነት መንገድ አለ።

## የቤተሰብ ጥምቀት

የ"ህጻናት" ጥምቀት ከማለት ይልቅ "የቤተሰብ" ጥምቀት ብለን ለመጥራት እንወዳለን። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉን።

የመጀመሪያው ማንም ህጻናትን ብቻ አያጠምቅም። በእድሜያቸው የገፉ እና ከዚያ ቀደም ተጠምቀው የማያውቁ ሰዎች ህጻናትን በምታጠምቅ ቤተክርስቲያን እንኳን በሙሉ በወጣትነታቸው ይጠመቃሉ።

ሁለተኛው መጽሐፍ ቅዱስ መጠመቅን አስፈላጊ ሲያደርግ የቤተሰብ ጥምቀትን ወክሎ ነው።

ሶስተኛ "የቤተሰብ ጥምቀት" እንደ ሐዋ 16 ያሉ ክፍሎች ህጻናትንም ሆነ ትላልቆችን ለምን እና እንዴት ልናጠምቃቸው እንደሚገባ ያስታውሰናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለቤተሰብ ጥምቀት መናገሩ በጣም ግልጽ የሆነ ነገር ነው። በሐዋሪያት ስራ 16 ሊዲያ እና ፊሊጲያዊው የእስር ቤት ጠባቂ በጳውሎስ መጠመቃቸውን ይናገራል(ቁጥር 15, 33)። ጳውሎስ  በ1 ቆሮንቶስ 1:16 ላይ የእስጢፋኖስን ቤተሰብ እንዳጠመቀ ይናገራል።  በሐዋ 10:48 ላይ ጴጥሮስ የቆርኖሊዎስን ቤተሰብ እንዳጠመቀ እናነባለን። ስለዚህ ይህ የአዲስ ኪዳን የጥምቀት ስርዓት ነው።

እነዚህ ክፍለ ምንባቦች የአማኝ ልጆችን ማጥመቅ እንደሚገባ የሚያግዙ ናቸው። በቤተሰቡ ውስጥ ትንሽ ህጻን ስለመኖሩ እርግጠኞች መሆን አንችልም ነገር ግን በአራቱም ቤተሰብ ውስጥ ምንም አይነት ህጻናት አልነበሩም ማለት አንችልም። ቢሆንም የቤተሰብ ጥምቀት የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በመሆኑ ቤተሰባችን ሊጠመቅ ከተገባው ህጻናትን አለማጥመቅ ከባድ ነው ምክኒያቱም አብዛኛው ቤተሰብ ህጻናትን ያካትታል።

የ "አማኞች ጥምቀት" የመጽሐፍ ቅዱስ ደንብ ከሆነ ባፕቲስቶች እንደሚያስተምሩት የቤተሰብን ጥምቀት የማይቻል ያደርገዋል። ምናልባትም በባፕቲስት ቤተክርስቲያን የተለያዩ የቤተሰብ አባላት ቢያምኑ እና

ቢጠመቁ የሚጠመቁት በአንድ ላይ ሳይሆን ለየግል ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ የእምነት ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነውና።

የቤተሰብ ጥምቀት የሚፈጸመው እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ፣ በሙላተ ጸጋው እና በአይለወጤነቱ ለቤተሰባቸው እና ለልጆቻቸው አምላካቸው እንደሚሆን የሰጠውን ተስፋ በማመን ነው (ዘፍ 17:7 ፣ ሐዋ 2:39)።

ይህ ድርጊት የግድ ቤተሰቡ ሁሉ መዳን አለበት የሚል አይደለም። ጥምቀት በትልቅነታቸው ለሚያውጁት እምነት እንኳን ዋስትና አይሰጥም። ጥምቀት አንድ የተጠመቀ ሰው ይድናል ብሎም አያመላክተንም።

ቤተሰብን የማጥመቅ ስርዓት የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ አስተምህሮን በመከተል፤ እግዚአብሔር እራሱ - አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ - የሆነ እና ለቤተሰቦች ድነቱን በመላክ ጸጋውን እንደሚያጎላ እና እንደሚገልጥ የሚያስታውሰን ነው። እሱ በእርግጥም የቤተሰብ አምላክ ነው (መዝ 107:41)

## ጥምቀት እና የመንግስቱ መግቢያ

ብዙውን ጊዜ በህጻናት ጥምቀት የሚያምኑ ሰዎች ለዚህ ማስረጃ እንዲሆን ማርቆስ 10:13-16ን ይጠቅሳሉ። ይህም ክፍል ኢየሱስ ህጻናትን የባረከበት ክፍል ነው። በአማኞች ጥምቀት የሚያምኑቱ ደግሞ በክፍሉ ላይ ምንም የጥምቀትን ርዕስ ባለማገኘቱ መከራከሪያ ነጥባቸው ላይ ያፌዛሉ።

ሆኖም ግን ማርቆስ 10 የህጻናትን ጥምቀት ለመደገፍ ልንጠቀምበት እንችላለን። ይህ በተለያየ ምክኒያት ሊሆን ይችላል ሆኖ ግን ማስተዋል ያለብን እነዚህ ልጆች በእርግጥም ህጻናት መሆናቸውን ነው(ሉቃ 18:15)።

በመጀመሪያ በክፍሉ ላይ የሚገኙ ህጻናትን ኢየሱስ ወደ እቅፉ በማስገባት ባርኳቸዋል።ወደ ክርስቶስ እቅፍ መወሰዳቸው እና በእርሱ መባረካቸው ከድነት የሚያንስ አይደለም። እነዚህ ህጻናት በኢየሱስ የዳኑ ስለመሆናቸው በቁጥር 14 እና 15 ላይ መንግስቱን ስለመቀበላቸው የተናገረው ክፍል ማስረጃ ነው።

ድነት እና መንግስቱን መቀበል ጥምቀት መንግስቱን እንዴት እንደምንገባ የሚያሳይ ምሳሌ ወይም ምልክት ነው። እነዚህ ህጻናት ጥምቀት የሚያመላክተውን *እውነታ ከተቀበሉ* ለምን *ምልክቱን* አይቀበሉም? በተለየ መልኩ ለመግለጽ ትልቁን ነገር *ከተቀበሉ* ለምን ትንሹ *ቀረባቸው?* እውነተኛውን ከተቀበሉ እና መቀበል ከቻሉ

ምልክቱንም መቀበል ይችላሉ ብለን እናምናለን። ድነት ለእነርሱም ሆነ ለትልልቆች በጸጋው ኪዳን ተስፋ ተሰጥቷቸዋል።

ሁለተኛው በቁጥር 15 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነዚህ ህጻናት ካልሆኑ በስተቀር መንግስቱን ማንም እንደማይቀበል ተናግሯል። ማለትም ህጻናት ሳይረዱት፣ በጸጋ ኃይል ብቻ ድነትን እንዳገኙ ማለት ነው። ስለዚህ እንደ ህጻናት መንግስቱን መቀበል ማለት ያለምንም ስራ እና ያለምንም ጥረት መቀበል ማለት ነው። ህጻናትም መንግስቱን መቀበል የሚችሉት *በዚህ መንገድ* ብቻ ነው።

እንደ እውነታው ከሆነ ይህ ማንኛውም ሰው መንግስቱን ሊቀበል የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ነው። ድነት በመጀመሪያ ሲመጣ እኛ ዘንድ ፍላጎትም ሆነ ምኞት አልነበረም። በሀጥያታችን እና በበደላችን ሙታን ስለነበርን እግዚአብሔር በሙላተ ጸጋው በዳግም ልደት አማካኝነት ድነትን እና መንግስቱን ሲሰጠን እርሱ የሰራልንን ማወቅ እና መፈለግ ጀመርን። ስለዚህም ኢየሱስ መንግስቱን የመቀበያ ብቸኛው መንገድ እንደ ህጻናት በመሆን እንደሆነ ይነግረናል። በዚህ መንገድ ካልተቀበልነው ሲጀመርም አልተቀበልነውም ማለት ነው።

የተጠመቀ ህጻን ሁሉ መዳን አለበት ብለን አናምንም። ነገር ግን በእያንዳንዱ ህጻን ጥምቀት ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ኪዳን በሉዓላዊው የጸጋ ሃይል እንዴት መዳን እንደሚቻል ያመላክተናል

በእርግጥም በሚጠመቁ ህጻናት ምሳሌነት እንዴት እያንዳንዳችን እንደምንድን ምሳሌ እናገኛለን ይህም ደግሞ በእራሳችን ብርታት እና ፈቃድ ሳይሆን በሁሉን ቻዩ ሉዓላዊ ጸጋ ነው። በዚህም ሰው ሳያውቀው እና ሳይፈልገው እግዚአብሔር አገኘው፣ አዲስም ልደት እና ህይወትን ሰጠው።

የህጻናት ጥምቀት አላማ የህጻናት ድነት መጠመቃቸው ላይ ይመሰረታል ለማለት ሳይሆን (የውሃ ጥምቀት ብቻውን ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም) እኛ እንዴት እንደምንድን ያሳየናል። ጥምቀት የድነትን ብቸኛውን መንገድ እና እግዚአብሄር ወላጆቻቸውን ባዳነበት በሉዓላዊ ጸጋው ልጆቻቸውን ለማዳን ተስፋ እንደሰጠ ያመላክተናል። ረዳት በሌላቸው ህጻናት ጥምቀት ውስጥ ይህንን ምስክርነት ብዙዎች ማየት አለመቻላቸው እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው።

## ጥምቀት እና መገረዝ

ለቤተሰብ ወይም ለህጻናት ጥምቀት የሚነሳው ተቃውሞ በመገረዝ እና በጥምቀት መካከል ያለው ግንኙነት ነው። ውጫዊ ምልክትነታቸው ፍጹም የተለያየ በመሆኑ ይህንን ለመመልከት ቀላል አይደለም።

ጥምቀትን እና መገረዝን እንደምልክት መጥቀሳችን ሊስተዋል ይገባል። የእነዚህ ምልክቶች ትርጉም ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው። የመገረዝ እውነታው ከመጠመቅ እውነታ ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው።

ይህም በክርስቶስ የመስቀል መሰዋት የሀጥያት መወገድ ነው። ለመገረዝ ይህ እውነታ በዘዳ 30:6 እና ቆላ 2:11 ላይ ግልጽ ሲሆን ለመጠመቅ ጊዜ ደሞ ሮሜ 6:1–6 እና 1 ጴጥ 3:21 ግልጽ ነው። ምልክቶቹ ስለመንፈሳዊ እውነታ በማንሳታቸው ረገድ ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው። ምንም እንኳን ፍጹም የተለያዩ ቢሆኑም ተመሳሳይ መንፈሳዊ እውነታን ይወክላሉ።

ሁለቱ የተለያዩ ናቸው ማለት በዲስፔንሽናል ስህተት ውስጥ መውደቅ እና ሁለት አይነት ድነት- ለብሉይ ኪዳን ሌላ ድነት ለአዲስ ኪዳን ደግሞ ሌላ ድነት አለ ወደሚለው ድምዳሜ ደርሰናል ማለት ነው።. ወደዚህ ስህተት ላለመግባት አንዳንዶች ደፍሞ በዘዳ 30:6 እና ቆላ 2:11 መሰረት በብሉይ ኪዳን መገረዝ የድነት ምልክት ሳይሆን እስራኤላዊያንን ለመለየት የተቀመጠ ምልክት ነው የሚል ሃሳብ ያስቀምጣሉ።

ይህንን ጳውሎስ በሮሜ 2:28 ላይ ውጫዊ መገረዝ እውነተኛ ነገር አይደለም እንዲሁ በውጫዊ ማንነት አይሁዳዊ መሆንም ምንም አይደለም በማለት ይቃወመዋል። ልዩነት የሚፈጥረው መገረዝ የ*ልብ* መገረዝ እንደሆነ እና አይሁዳዊ መሆን *በውስጣዊ ማንነት* እንደሆነ ይናገራል። የአብርሃም ተፈጥሯዊ ዘር በመሆናቸ አንዳች የተለዩ እንደሆኑ የሚሰማቸው ሰዎች ይህንን ክፍል ሊያነቡ ይገባቸዋል።

ለምን በጥምቀት እና በመገረዝ መካከል ውጫዊ የምልክት ልዩነቶች ኖሩ? ይህንን በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መካከል ባለው ትልቅ የልዩነት ብርሃን መመልከት ይቻላል። በብሉይ ኪዳን እነዚህ ሁሉ የሚያመላክቱት ደሙን ያፈሰሰው ክርስቶስን ነው (ዕብ 9:22) ነገር ግን አንዴ የክርስቶስ ደም ከፈሰሰ በኋላ ሌላ የሚፈስ ደም በመገረዝም እንኳን ቢሆን የለም (ዕብ 10:12)።

ይህ በመገረዝ እና በጥምቀት መካከል ያለ እውነተኛ ልዩነት ነው። በእውነታቸው እና በትርጉማቸው ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ በ ቆላስያስ 2፡11-12 ሁለቱን ይተረጉማቸዋል። ምናልባት በእነዚህ

ሁለት ቁጥሮች የምናገኘው ረጅም አረፍተነገር በመሆኑ ጳውሎስ እየተናገረ ያለውን ጭብት ልናጣው እንችል ይሆናል። በክፍሉ ላይ የተገረዘ መጠመቅ እንደሚገባው ይናገራል። ይህ የቆላስያስ 2 ዋና ሃሳብ ነው። ለአህዛብ አማኞች ሲናገር ጳውሎስ በክርስቶስ ሁሉ ነገር፣ መገረዝም ጭምር እንዳላቸው ይነግራቸዋል (ቁጥር 10–11)። የመለኮት ሙላት በሰውነቱ በተገለጠበት በክርስቶስ የሚያጡት አንዳች ነገር አይኖርም (ቁጥር 9)

መገረዝ እና መጠመቅ ተመሳሳይ ትርጉም እንዳላቸው ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ እውነታቸው ተመሳሳይ በመሆኑ ምክኒያት የህጻናትም ጥምቀት መተግበር እንዳለበት ለእግዚአብሔር ህዝቦች ሊነገር ይገባል።

## አማኝ ያልሆኑ እና ኪዳኑ

በህጽናት ጥምቀት ላይ የሚነሳው አንዱ መቃወሚያ የሚጠመቁት ያልዳኑ እና በዚህ ድርጊት ፈጽመው የማይድኑ ናቸው የሚል ነው። ህጻናትን የሚያጠምቁ ሰዎችን በተደጋጋሚ ያላመነ እና ሃጥያቱን ያልተናዘዘን ሰው እያጠመቁ እንደሆነ ያስታውሳሉ። ለባብቲስቶች ይህ ሙሉ በሙሉ በግምት የሚደረግ ይመስላል።

ለዚህ ተቃውሞ ስንመልስ በባብቲስትም ሆነ በተሓድሶ ቤተክርስቲያናት የ*ዳኑትን* ብቻ ልናጠምቅ *አንችልም*። ምክንያቱም የልብን ሚስጥር እኛ አናውቅም። የባብቲስት ቤተክርስቲያን ንስሃ የገቡትን እና እምነታቸውን የሚያውጁትን ብታጠምቅም እንኳን ይህ ከእርሷም የተሰወረ ነው።

ይህንን ለበርካታ ባፕቲስት ጓደኞቻችን ስናቀርብላቸው የሚሰጡን መልስ "ቢያንስ እኛ ከእናንተ ያነሰ ቁጥር ያለው ያላመኑ ሰዎችን እናጠምቃለን" የሚል የተለመደ መልስ ነው። ባፕቲስቶች አንድ ያልዳነን ሰው ያጠመቁ እንደሆነ ተጠማቂው የተጠመቀው "የአማኞችን ጥምቀት" ሳይሆን "የአዋጆችን ጥምቀት" ነው።

በዚህ ነጥብ ላይ ለመጨመር በመጽሐፍ ቅዱስ መገረዝ እና ጥምቀት ለማያምኑ ሰዎች ሲደረግ እናያለን። አብርሃም እስማኤልን የገረዘው እስማኤል በኪዳኑ ውስጥ ምንም ተስፋ እንዳልተሰጠው ከተነገረው በኋላ ነው (ዘፍ 17:18–19)። እንዲሁ ይስሃቅ ኤሳውን የገረዘው ኤሳው ከተተወ/ ከተጠላ በኋላ ነው (ዘፍ 25:23–24)።

ከዚህ ነጥብ በመነሳት ባፕቲስቶች መገረዝ ለህዝብ ልዩነት የተደረገ ምልክት እንደሆነ ይሞግታሉ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመገረዝ በሚናገረው እውነት መሰረት ትክክል አይደለም። "ሰውነት በመገፈፍ በክርስቶስ

መገረዝ ፣ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ” (ቆላ 2:11 ፣ ዘዳ 10:16; ዘዳ 30:6; ኤር 4:4)።

ለጥምቀትም ተመሳሳይ ነው። በቀይ ባህር (በ1ቆሮ 10፡1 ፣ 2 ጥምቀት ተብሎ ተገልጿል) በእግዚአብሔር “እርሱን ላላስደሰቱቱ” እና በኋላ ላይ በሰይጣን ለወደቁ የተደረገው ጥምቀት ነው (ቁጥ 5-10)። ካም ከቀሪው የኖህ ቤተሰብ ጋር “ተጠምቋል” (1 ጴጥ 3:20–21)።

ስለዚህ ሊነሳ የሚችለው ብቸኛው ጥያቄ “እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን ለኪዳኑ እና ለድነት ምልክት የሚሆነውን ለዳነውም ላልዳነውም እንዲተገበር ለምን ፈቀደ?” ትልቅ ሰዎች ሆኑ ህጻናት ምንም ልዩነት የለም ስለዚህ ባፕቲስቶችም ይህንን ጥያቄ ሊመልሱ ይገባል።

የዚህ ጥያቄ መልስ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ አላማ ላይ ይወድቃል። እግዚአብሔር ከዘላለም በፊት የአንዳንዶችን መዳን እና የሌሎችን አለመዳንን ጭምሮ ነገሮችን ሁሉ እንደወሰነ በጽኑ የሚያምን ሰው ብቻ ለዚህ ጥያቄ ግልጽ እና ጠንካራ መልስ ይኖረዋል።

መልሱ መሆን የሚችለው የብሉይ ኪዳን ግርዘት እና የአዲስ ኪዳን ጥምቀት፤ እንደ ወንጌል ስብከት ለድነት እና *ልብን ለማደንደን/ ኩነኔ* የሚሆኑ ኃይል እና ምስክርነቶች ናቸው። ይህንንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይከውናሉ (2 ቆሮ 2:14 –16) ። አዋቂዎችንም ሆነ ህጻናትን የምናጠምቀው የእግዚአብሔር አላማ ለአንዳንዶች ድነት እና አንዳንዶችን ልክ እንደ ኤሳው እስማኤል እና ካም ለጥፋት ይጠቀምባቸዋል።

## እምነት እና ጥምቀት

አሁን ደግሞ እምነት ጥምቀትን የግዴታ መቅደም አለበት የሚለውን የባፕቲስት መከራከሪያን ልናነሳ እንወዳለን። ባፕቲስቶች ጥምቀትን “የአማኞች ጥምቀት” ይሉታል።

በመጀመሪያ ይህ ሁኔታ የማይቻል መሆኑን ልንናገር እንወዳለን። ለማንሳት እንደሞከርነው ባፕቲስቶች ማጥመቅ የሚችሉት እምነትን *ያወጇቱን* ብቻ ናቸው። ማንም ልብን ማወቅ ስለማይችል የተጠመቀ ሁሉ አማኝ መሆኑን ማረጋገጥ አይቻልም።

የተለመደው የባፕቲስቶች ምላሽ ቤተሰብን ወይም ህጻናትን ከሚያጠምቁት ያነሱ የማያምኑ ሰዎችን እናጠምቃለን የሚል ነው። ይህ በእርግጥም እውነት ነው ነገር ግን የባፕቲስት ቤተክርስቲያን አንድ ግብዝ የማያምን ሰው ካጠመቀች በእውነትም "የአማኝን ጥምቀት" እየተገበረች አይደለም።

ነገር ግን ዋናው ጉዳይ ይህ አይደለም። በማርቆስ 16:16 ላይ ኢየሱስ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ብሎ ተናግሯል። ይህ ቃል በተለይም የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን እንድታጠምቅ የተሰጣት ፈቃድ እና ትዕዛዝ በመሆኑ ሊብራራ ይገባዋል።

በመጀመሪያ ሁሉም ባፕቲስቶች በሚያነቡት መንገድ ክፍሉ "በመጀመሪያ ያመነ ከዛያም የተጠመቀ ይድናል" አይልም። የሚለው ለድነት ጥምቀት እና እምነት አስፈላጊ ናቸው ብቻ ነው።

ሁለተኛ እምነት እና ጥምቀት በዚህ ቅደም ተከተል መቀመጣቸው በዚህ ቅደም ተከተል ሊከሰቱ ይገባል ማለት አይደለም። በ2 ጴጥ 1፡10 መጠራት ከመመረጥ በፊት ቢጠቀስም ሁሉም ካልቪኒስት እንደሚያውቀው መጠራት ከመመረጥ በፊት ሊሆን አይችልም።

በማርቆስ 16፡16 ላይ የተቀመጠው ቅደመ ተከተል የአስፈላጊነት ብቻ ነው። እምነት ከጥምቀት ቀድሞ የተጠቀሰው የበለጠ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ይህንንም በክፍሉ መጨረሻ ላይ እምነት ሲጠቀስ ጥምቀት ግን ባለመጠቀሱ የምናስተውለው ነው።

የማርቆስ 16፡16 አቀማመጥ አንዱ አንዱን መቅደም የሚል አይነት ከሆነ ቅደም ተከተሉ የሚሆነው "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" በሚለው መሰረት እምነት - ጥምቀት - ድነት የሚል ይሆናል። ማንም በዚህ ቅደም ተከተል አይስማማም!

ከዚህ በተጨማሪም በተወሰነ ደረጃ እምነት ጥምቀትን እንደማይቀድም የሚናገሩ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች አሉ። የሐዋሪያት ስራ 19፡4 ስለመጥምቁ ዩሀንስ ሲናገር መጥምቁ ዩሃንስ  ከእኔ ኋላ በሚመጣው ልታምኑ ይገባል በማለት ለህዝቡ ሲናገር ነበር። በክርስቶስ ቀድመው በማመናቸው አይደለም *የተጠመቁት*።

ከቁጥር 4 አንጻር ባፕቲስት ሁለት አማራጭ አለው። የመጀመሪያው የመጥምቁ ዩሃንስ ጥምቀት የአዲስ ኪዳን እውነተኛ ጥምቀት አይደለም ማለት ነው፤ ሆኖም ግን በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥምቀቶች የዩሃንስ ጥምቀቶች ናቸው (ስለዚህ ስለጥምቀት ከአዲስ ኪዳን የምንወስደው ምንም

አይነት አስተምህሮ አይኖርም) አልያም ደግሞ እምነት ሁሌም ጥምቀትን ሊቀድም እንደማይችል መቀበል ነው።

## ንስሐ መግባትና መጠመቅ

ባፕቲስቶች "ለአማኞች ጥምቀት" የሚያቀርቡት ሌላ መከራከሪያ የእምነት ብቻ ሳይሆን ንሰሓም ጥምቀትን መቅደም አለበት የሚል ነው። በጥቂቱ ይህንን መከራከሪያ ምላሽ ሰጥተነዋል ነገር ግን ሊጠቀሱ የሚገባቸው የተወሰኑ ነገሮች አሁንም አሉ።

በመጀመሪያ "ዩሃንስ በምደረ በዳ የንስሃንም ጥምቀት ለሃጥያት ስርየት እየሰበከ መጣ" በማለት ስለንስሃ ጥምቀት የሚያወራውን ማርቆስ 1፡4 እንመልከት። ብዙዎች ከዚህ ክፍል ንስሃ ጥምቀትን መቅደም አለበት የሚል መደምደሚያ ይወስዳሉ።

ነገር ግን ይህ በምንም አይነት መንገድ ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። ቃሉ "ጥምቀት የንስሃ ምንጭ ነው" የሚል በመሆኑ ጥምቀት ንስሃን *ሊከተል* ይገባዋል እንድንል ሊያደርገን ነው። ይህ ንግግር ጥምቀት እና ንስሀ አንድ ላይ የሚሄዱ እንደሆነ ነገር ግን ስለቅደም ተከተላቸው የማያወራ ሊሆን እንደሚችል መታሰብ አለበት።

ክፍሉ ስለተቀመጡብት ቅደም ተከተል የሚለን ነገር ምንም እንደሌለ እናምናለን ፣ ነገር ግን ንስሃ እና ጥምቀት የሚደጋገፉ ማለትም ጥምቀት ንስሃን ይጠይቃል (ከጥምቀትም ቀድሞ ወይም ከጥምቀት ቀጥሎ ወይም ሁለቱንም ሊሆን ይችላል)።

በጥምቀት እና በንሰሃ መካከል ቅደም ተከተል ቢኖር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ንሰሃ ጥምቀትን እንደሚከተል ይናገራል። በማቴዎስ 3፡11 ላይ የሚገኝ ተመሳሳይ ንባብ ይህንን ያመላክተናል። በክፍሉ ውስጥ "ለ" ንሰሃ አጠምቃችኋለው ሲል እንመለከታለን። ለ የምትለው ቅጥያ "ወደ አንድ ነገር ማምራትን ታመላክታለች። ሀሳቡ ጥምቀት የሚከናወነው ንስሃ ይከተለዋል በሚል ምልከታ ነው፣ ወይንም ደግሞ ጥምቀት የንስሃ ጥሪ ነው ማለት እንችላለን።

ጥምቀት ንስሃን ወደኋላ ሳይሆን ወደፊት እንደሚመለከት ያቀረብነው ምክረ ሃሳብ ማቴ 3፡11 በባፕቲስት እና በተሓድሶ ዘንድ በጥምቀት ምልከታ ላይ ያለውን ወሳኝ የሆነ ልዩነት ያሳየናል። በባፕቲስቶች እይታ

ጥምቀት ማለት በንስሃ እና በማመን *ያደረግነው ድርጊት* ምልክት ወይም ምሳሌ ነው። በተሓድሶአዊያን ጎን ደግሞ ጥምቀት ማለት በእኛ ውስጥ እግዚአብሔር በዳግም ውልደት ለሰራው ስራ ምልክት ወይም ማሳያ ነው። ለጸጋው የሰጠነውን ምላሽ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ የጸጋው ስራ መሆኑን ያመላክተናል።

ጥምቀት በስርዓታዊነት ባህሪው በኢየሱስ ክርስቶስ የሀጥያት መታጠብን ያመላክታል። ይህ እግዚአብሄር እኛን በማዳን ውስጥ ቀድሞ የሰራው ስራ ነው። ይህንን የሰራልን ለጸጋው ስራ ምላሽ መስጠት በማንችልበት ጊዜ ነው። ንስሃም ይህንን ይከተላል።

ይህንን ከተረዳን፣ የህጻናት ጥምቀት አዲስ እና ልዩ ነገር ሳይሆን ትክክለኛ እንደሆነ እንረዳለን። በመጨረሻም በልጅነታችን ሆነ አድገን የዳንን ብንሆን እንኳን እንደ ህጻናት ሳንሆን ወደ መንግስተ ሰማይ ልንገባ ከቶ አንችልም። ማለትም ስራን እና ምላሽን ሁሉ በሚያልፍ ንጹህ ጸጋ ብቻ መግባት እንችላለን። የህጻናት ጥምቀትም ይህንን የጸጋ ስራ ያመላክታል ደግሞም ያከብራል።

## ቅጣት/ተግሳጽ እና ህዝብን ማጥመቅ

ማቴዎስ 28፥19 ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ጥምቀትን እንድታከናውን ስልጣን የሰጠበት ክፍል ነው “እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።” ክፍሉ ጥምቀት አለም አቀፋዊ እንጂ የአይሁድ ስርዓት ብቻ እንዳልሆነ ያስተምራል።

ስለዚህ ወሳኝ ጥቅስ ልንናገረው የምንወደው ሁለት ነጥቦች አሉን። ክፍሉ ስለህጻናት ጥምቀት የሚቃረን ሳይሆን ይልቁኑም ጠንካራ ማስረጃ የሚሰጥ ክፍል ነው። ባፕቲስቶች ኢየሱስ ቀድመን አህዛብን እንድናስተምር (ደቀመዝሙርነት) ከዚያም ቀጥሎ እንድናጠምቅ ነው ያዘዘን ብለው ይከራከራሉ። ህጻናት ሊነገራቸው ወይም ደቀመመዝሙር ለማድረግ እድሚያቸው ስለማይፈቅድ ሊጠመቁ አይገባም ይላሉ። ነገር ግን ይህ በርካታ ነጥቦችን ይስታል።

በመጀመሪያ በማርቆስ 16፥16 ላይ እንዳመላከትነው የሚሉት ቃል በጥቅሱ ውስጥ የለም። ኢየሱስ “አህዛብን ሁሉ አስተምሩና አጥምቋቸው” አላለንም። ይህን ያለ እንደሆነ የአማኞች ጥምቀት ብለው የሚያስተምሩት ባፕቲስቶች ትክክል ናቸው ማለት ነው።

ሁለተኛው ክፍሉ ስለህዝቦች እንጂ ስለግለሰብ የሚናገር አይደለም። ከጥቅሱ ባህሪ አንጻር ሁለቱ ደቀመዝሙር የማድረግ እና የማጥመቅ ተግባር አንድላይ ሊከናወኑ ይገባል። አንድ ሰው ማጥመቅ ከመጀመሩ በፊት አለም ሁሉ ወንጌልን እስኪሰማ መጠበቅ የለበትም። አለዚያ ምቀት የሚባል ነገር አይኖርም።

የሰዋሰው አውዱ የባፕቲስት እይታን የሚቃረን ነው። ክፍሉ በቀጥታ "እያጠመቃቹኋቸው ህዝብን ሁሉ አስተምሩ" ወይም "ሁሉንም ህዝብ ካጠመቃችሁ በሁላ አስተምሯቸው" በሚል መልኩ ልንረዳው ይገባል። "ከማጥመቃችሁ በፊት ህዝብን ሁሉ አስተምሩ" ማለት አይደለም። ክፍሉ ጥምቀት ወይስ ማስተማር ይቅደም በሚለው ቅደም ተከተል ላይ ምንም የሚናገረው *ነገር የለውም።*

ከዚህ በተጨማሪ ህዝብ ህጻናትንም ያጠቃልላል። የህዝቡ አካል የሆኑትን ህጻናትን ሳናካትት ህዝብን ማስተማር እና ማጥመቅ የማይቻል ነገር ነው።

በማቴዎስ 28፡19 "እንዲሁ ብዙ ህዝብን ያስደንቃል" የተባለው የኢሳይያስ 52:15 ፍጻሜ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ሁልጊዜም ቢሆን ስለተፈጸሙት የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መመልከት አለብን። የማቴዎስ ወንጌል ዋና ጭብጥ ይህ ነው። ማቴዎስ ሁሌም ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ መሆኑን ያሳያል (በተለይ ምዕ 1 እና 2 ይመልከቱ)። በዚህ ሁኔታ ተመራጩ የሚሆነው የትንቢት ፍጻሜ ኢሳያይስ 52:15 ነው።

በኢሳይያስ ላይ የተጠቀሰው የህዝብ ሁሉ መረጨት (የኢንጊሊዘኛው ትርጉም መደነቅን sprinkle ብሎ ያስቀምጠዋል) ለሀጥያት የክርስቶስ መከራን መቀበል እና መሞትን ይከተላል። "ከሰው ልጆች ይልቅ ተጎሳቁሏል" መባሉ በዚህ መንገድ ህዝብን ሁሉ ይረጫል (ቁ.14)። በአዲስ ኪዳን በማቴዎስ 28፡19 ላይ ያለውን የክርስቶስ ትዛዝ በመታዘዝ እንመለከተዋለን።

ኢሳይያስ 52፡14 የህዝብ ሁሉ ጥምቀት በማስደነቅ (sprinkling) መሆኑን ብቻ ሳይሆን የነብዩ መጽሐፍ ለዚህ መደነቅ(sprinkling) ህዝቡ ከልጆቻቸው ጋር መሰብሰቡን ይነግረናል። ወደ ክርስቶስ ለመደነቅ(sprinkling) እና ለድነት ሲመጡ ሴት እና ወንድ ልጆቻቸውን ምናልባትም የሚንከባከቡትንም ህጻን ሳይቀር ይዘው መጥተዋል (ኢሳ 49:22 ኢሳ 60:4)። ይህ የህዝብ መደነቅ ተስፋ በጥምቀት ተመስሎ እና

ታውሶ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ስራ ፍጻሜውን አግኝቷል። ከሮማ ካቶሊክ በመቅዳት ወይም ልማዳቸውን በመውሰድ ሳይሆን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ተሓድሶ ህጻናትን ያጠምቃል።

## የጌታ እራት

"ሁለቱ ቁርባናት" በሚል ርዕስ ስር በሁለቱ ቁርባናት መካከል ያለው ልዩነት ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን እና ማህበር መግቢያችንን በመሆኑ እና የጌታ እራት ደግሞ አንድ ጊዜ ከገባን በኋላ በዚያ ቃል ኪዳን ውስጥ ያለውን ኑሯችንን የሚያሳይ መሆኑ እንደሆነ ተነጋግረናል። ስለዚህ ሁለቱም አንድ ላይ ሆነው መላውን የክርስትና ሕይወታችንን በጸጋ ብቻ መሆኑን በዓይነ ሕሊናችን ያሳዩናል።

የሁለቱ ቁርባናት ልዩ ምስክርነት ክርስቶስ እና የእርሱ መስዋዕትነት ሁሉም ነገር መሆኑን ነው። የጥምቀት ውኃ በክርስቶስ ሞትና ደም ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውስጥ እንደገባን ያሳያል። የጌታ እራት ደግሞ አንድ ጊዜ ወደ ቃል ኪዳንና መንግሥት ከገባን በኋላ የክርስቶስ እራሱ ሞቱ ፣ አካሉ እና ደሙ ህይወታችን፣ ምግባችንና ኃይላችን ነው።

የጌታ እራት ተስፋ በእግዚአብሔር ኪዳን ውስጥ መኖር ምን እንደሆነ ያመለክታል። በጌታ ማዕድ ላይ እንደ ቤተሰቡ አባላት ተቀምጠን እግዚአብሔር አባታችን ስለእኛ እንደሚጠነቀቅ እና የሚያስፈልገንን ነገር እንደሚያቀርብልን በምስል ያሳየናል። የጌታ እራት የሚያመላክተን ይህን ብቻ ሳይሆን እንክብካቤውን እና ህብረቱን እንደምናጣጥምም ጭምር ነው።

የጌታ እራት ተምሳሌትነት የተለያዩ ምልከታዎች ያሉት ሲሆን ሁሉም የእግዚአብሔርን ኅብረት እና መግቦት ብሎም በእግዚአብሔር ኪዳን ውስጥ መኖር ምን ማለት እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። በመጀመሪያ የጌታ እራት የሚቀርብበትን *ጠረጴዛውን* እንመልከት። በውስጡ የሚገኙ ነገሮች በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ይህም ቁርባን "የጌታ ማዕድ" ተብሎ ተጠርቷል (1 ቆሮ. 10፥21)። ገበታው በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያለንን ቦታ እና ጌታ እንደ አባት እንደሚወደን እና የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሚሰጠን ያመላክታል።

ሁለተኛ *ህብስት/ቂጣና* ወይን አለ። መሰበሩ እና መቀዳቱ፤ የተሰበረውን *ሥጋ* ና የፈሰሰውን የክርስቶስ ደም የዕለት ተዕለት መንፈሳዊ መብላችንና መጠጣችን፣ ምግብና እረፍት ፣ መንፈሳዊ ሕይወታችን የሚበቅልበትና የሚደገፍበት፣ የሚያድግበትና የሚፋፋበት፣ ወደ ዘላለም ሕይወት ተጠብቆ የሚቆይበት መሆኑን ያሳያል።

ስለዚህ ይህንን ልብ እንበል። የክርስቶስ መስዋዕትነት ለሀጢያታችን እና ወደ እግዚአብሔር ሞገስና አብሮነት ለምንመለስበት መንገድ የተከፈለ ክፍያ ብቻ ሳይሆን ይህንን ህይወት ጥለን ወደዘላለሙ ቤታችን እስክንሄድ ድረስ የእለት ተእለት ኃይላችን እና የሚያስፈልገን ምግባችን ነው ።

ሦስተኛው *መብላትና መጠጣት* ነው። ይህ እምነታችንን ከማሳየት በተጨማሪ አስፈላጊነቱን እና ወሳኝነቱን ያሳየናል ። ካልበላን እና ካልጠጣን፤ ምግብና መጠጥ ምንም ጥቅም የላቸውም። የክርስቶስ የተሰበረው አካል እና የፈሰሰው ደም ለእኛ ያለ እምነት ምንም ጥቅም የለውም። የሮማ ካቶሊኮች እንደሚያስተምሩቱ የጌታ እራት ቂጣ እና ጽዋን በመውሰድ ቅጽበታዊ የሆነ በረከት የለም። እምነትን ከተሓድሶው አዋጆች መካከል አንዱ የሆነው የቤልጂየሙ አዋጅ "የነፍሳችን እጅና አፍ"[5] በማለት ይጠራዋል።

በዚህ መንገድ የጌታን እራት መብላት እና መጠጣት የዕለት እንጀራችንን እንደምንወስድ እና እንደምንበላው እንዲሁም ወደ ሰውነታችን እንደምንቀበለው ያመለከታል። ስለዚህ በእኛ ውስጥ የሚኖረውን ሀይላችን እና ህይወታችን ክርስቶስን በእምነት እንቀበላለን።

ይህ በጣም የማረ ምስል ነው!

## በጌታ እራት የክርስቶስ መገኘት

የጌታ እራት በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የሚያመለክት ሆኖ ሳለ በቤተክርስቲያን ውስጥ የመከፋፈል እና የክርክር ርዕስ መሆኑ እጅግ ያሳዝናል። ሆኖም ግን ለክርክር የሚነሱት ሀሳቦች እንዲሁ ቀላል አይደሉም።

ዋናው ጥያቄ ክርስቶስ በጌታ እራት ውስጥ ይገኛል፣ ከተገኘስ እንዴት ነው የሚገኘው የሚለው ጥያቄ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ያለን አመለካከት የጌታን እራት እንዴት እንደምንተገብረው በእጅጉ የቀልሳል - እየተጠራጠርን ወይንም እያመንን፣ ተራ አድርገን ወይም ደግሞ በጥንቃቄ እንድንወስደው ያደርገናል።

የተለያዩ ምልከታዎች እንደሚከተሉት ናቸው

ትራንሰብስታንቴሽን (transubstantiation) የሮማ ካቶሊክ እምነት ሲሆን የጌታ እራት ህብስት እና ወይን በቄስ ሲባረክ ወደ ክርስቶስ ስጋ እና ደም “ይለወጣል” የሚል እምነት ነው። ምልከታው እምነትን በመግፋት፣ አንድ ሰው ክርስቶስን ለመቀበል የሚያስፈልገው ህብስቱን እና ወይኑን መጠጣት ብቻ ነው ይላል።

በተጨማሪም ህብስቱ፣ ማለትም ስጋ የሆነው ህብስት ሲቆረስ የክርስቶስ መስዋትነት እንደገና እየተካሄደ ነው የሚለው እምነታቸው ለቅዳሴ (mass) አስተምህሯቸው መሰረት ሆኖ እናገኘዋለን።

የ*ሉተራን* አስተምህሮ ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስ *ሥጋ* እና ደም በህብስት እና በወይኑ ውስጥ ይገኛል ብለው ያምናሉ። ይህ አመለካከት ኮንሰብስታንቲዬሽን (consubstantiation) በመባል ይታወቃል። አስተምሮውም በሮማ ካቶሊክ አስተምህሮ ላይ እንዳለው አይነት ኑፋቄ አለበት። ሆኖም ግን ይህ አስተምህሮ ቅዳሴ (mass) ባይኖረውም ሁለቱም አስተምህሮች ክርስቶስ በ*አካል* መገኘቱን ያስተምራሉ።

የአብዛኞች ወንጌላዊያን አስተምህሮ በአስራ ስድስተኛው ክፍለዘመን የነበረ የተሓድሶ ለውጥ አምጪ ኡልሪች ዝዊንግሊ አስተምህሮ ነው። ይህ አስተምህሮ በጌታ እራት ላይ ክርስቶስ በአካል እንደማይገኝ የሚያስተምር ነገር ግን የጌታ እራት የክርስቶስ ኢየሱስ ሞት *ማስታወሻ እና መታሰቢያ* ነው የሚል ነው። በግልጥ የሮማኒዝምን እና የሉተራን አስተምህሮ ስህተቶችን ባይዝም ይህ አስተምህሮ አሁንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። አሁን እንደምንመለከተው ይህ አስተምህሮ የጌታ እራት ለምን በጥንቃቄ እና ማስተዋል መተግበር እንዳለበት አያስተምርም። የጌታ እራት መታሰቢያ ብቻ ከሆነ እራስን መገምገም እና "ፍርድ"ን መፍራት ለምን እንደሚያስፈልግ አያስተምርም (1ኛ ቆሮ 11:29)።

የተሓድሶ አስተምህሮ የጌታ እራት ላይ ክርስቶስ *በእውነት እንደሚገኝ፣* እርሱም *በመንፈስ* እንጂ *በስጋ* እንዳልሆነ ያስተምራል። በሌላ አማርኛ እርሱ ለእግዚአብሔር ህዝቦች እምነት ይገኛል ደግሞም ከእነርሱ ጋር ህብረት በማድረግ በእምነት በኩል ይመግባቸዋል። እርሱ እምነታቸውን ወደ እርሱ እንዲያደርጉ ህብስት እና ወይንን ይጠቀማል።

ይህ የተሓድሶ አስተምህሮ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11:29 ላይ በግልጥ እንመለከተዋለን፣ የሚናገረውም በጌታ እራት ላይ "ማንም የጌታን *ሥጋ* ሳይገባው ቢበላና ቢጠጣ ፍርድ የሚያመጣበትን ይበላል"። ይህ ብቻ ሳይሆን የጌታ እራት በሚፈጸምበት ወቅት  ክርስቶስ እራሱ እንዲህ ብሎ ይነገረናል፡ "ይህ ስለ እናንተ የሚሆን *ሥጋ*ዬ ነው።" ክርስቶስ በጌታ እራት ወቅት በመኖሩ ምክኒያት ሰው እራሱን በስርዓት ሳይገመግም ቢበላ እና ቢጠጣ ፍርድ ይሆንበታል። ክርስቶስ በመኖሩ ብቻ በጌታ እራት ውስጥ በረከት ይኖራል። የተሓድሶ ምልከታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሲሆን ለጌታ እራት የበለጠ ትርጉምን እና ትርፍን ይሰጣል። ስለዚህ በቅዱስ ቁርባን ከክርስቶስ ጋር እንገናኛለን ደግሞም በሙላቱ እንደ አዳኛችን እና ተቤዢያችን በእርሱ እንደሰታለን። ታዲያ ይህንን በስርዓት እንድንጠቀመው ይሁንልን።

## ቂጣና ወይን በጌታ እራት

ከጌታ እራት ጋር በተያያዘ ልንጠይቀው የምንችለው አንዱ ጥያቄ፣ "በዚህ ቅዱስ ቁርባን ውስጥ ሁለት ንጥረ ነገሮች (ቂጣ እና ወይን) ለምን አሉ? በጥምቀት ቅዱስ ቁርባን ውስጥ አንድ (ውሃ) ብቻ አለ?" ይህ በጣም ጥሩ ነው ከጌታ እራት ትርጉም ጋር በተሳሰረ ጉዳይ ላይ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጥያቄ አለ ።

ቅዱሳት መጻህፍትን ካጠናን ቂጣ/እንጀራ መሰረታዊ ተምሳሌት ሆኖ እናገኘዋለን ለሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮች ። በዚህም ምክንያት ቂጣ/ እንጀራን “የህይወት በትሮች" እና በጌታ ጸሎት ውስጥ "የዕለት እንጀራችንን" ለማግኘት መጸለይ፣ በዚህም ለምድራዊ ፍላጎታችን ሁሉ መጸለይ። ስለዚህ የጌታ እራት ዳቦ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የግድ አስፈላጊ እንደሆነ የክርስቶስን መሥዋዕት ያመለክታል ። ያለ "የቀን እንጀራ" መኖር ከምንችለው በላይ መኖር አንችልም ያለ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ።

ይሁን እንጂ የወይን ጠጅ ለምን? ወይን ጠጅ በቅዱሳት መጻሕፍት ቅንጦትን፣ ብዛትን፣ ስብነትን፣ ብልጽግናን፣ ደስታንና ድግስን ያመለክታል( ዘዳ. 28፥51፤ መዝ. 104፥15፤ ኢሳ. 55፥1፤ ኢዩኤል 3፥18) ከሕይወት ከሚያስፈልጉ ነገሮች በላይና በላይ የሆነ ሕይወትን ከሕልውና የበለጠ የሚያደርገው ደስታንና ደስታን የሚሰጥ።

ስለዚህ የጌታ እራት የወይን ጠጅ ክርስቶስ መሆኑን ያመለክታል የመንፈሳዊ ሕይወታችንን መሰረታዊ አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን የስብሃትና ብልፅግናና ደስታም ጭምር ነው። ወይ በተለየ መልኩ ለማስቀመጥ ወይኑ ያስታውሰናል በክርስቶስ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ይሰጠናል፤ ከዚህም በተጨማሪ ሁልጊዜ ይሰጠናል እኛ "ከምንለምነውወይም ከምናስበው ሁሉ እጅግ አብልጠን" (ኤፌ. 3፥20)። በእርግጥም አምላክ በምሕረቱ እጅግ ባለጸጋ ነው ፤ ለሕዝቡም ቸርነት የሞላበት ነው ። እነዚህ ሁለት የጌታ እራት ነገሮች አንድ ላይ ተወስደው ያስታውሱናል አሁንም ክርስቶስ ሁሉንም ነገር ነው። ዋና ምስክርነት ክርስቶስ የእኛ መድኃኒት አልፋና ኦሜጋ ነው፤ ያለ እርሱ ምንም የሌለን ከእርሱ ጋር ሁሉን ምናምን፤ እርሱና እርሱ ብቻ ሊመኝ፣ ሊፈልግ፣ ሊወደውና ሊያገለግለው እንደሚገባ

በእግዚአብሔር የጌታ እራት ስጦታ በመደሰታችን ባልተከፋፈለ ልብ እንሻውና በሞላው ሁሉ ደስ ይበለን እንጂ በራሳችን ሳንታመን ወይም ከርሱ ሌላ ምንም ነገር ከመፈለግ በቀር በሙላትና በኾነ በጸጋው ታደሰ፣ በመጨረሻ ይህንን ህይወት ትተን በአብ ቤት ባዘጋጀልን ቤት ከእርሱ ጋር ለመሆን ስንሄድ የሚኖረንን ጣዕም በመቅመስ።

የእግዚአብሄር ቤተሰብን አንድነት የሚገልጸው ይህ የጌታ እራት በብዙ ቤተክርስቲያናት ዘንድ የመከፋፈያ እና የመከራከሪያ ምክንያት መሆኑ እጅግ የሚያሳዝን ነገር ነው። ቢሆንም ጉዳዩ አስፈላጊ ያልሆነ ጉዳይ አይደለም።

በእርግጥ ዋናው ጥያቄ በጌታ እራት ውስጥ እና ላይ ክርስቶስ እንዴት ይገኛል የሚለው ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ያለን እይታ በእራቱ አወሳሰድ የምንወስደው በአጉል እምነት ወይም በማመን ፣ በጥንቃቄ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን እና አለመሆኑን ያመላክታል።

የተለያዩ እይታዎች የሚከተሉት ናቸው።

የሮማ ካቶሊኪስም እይታ  ትራንሰብስታንሽን (transubstantiation) የሚባል ሲሆን የጌታ እራት ዳቦው እና ወይኑ በካህኑ ሲባረክ ወደ ክርስቶስ ደምነት እና ስጋነት ይለወጣል ብሎ ያስተምራል። ለሁሉም ክርስቶስን ለመቀበል ዳቦውን መብላት እና ጽዋውን መጠጣት በመሆኑ እነትን ወደጎን ይገፋል። የሚቆረሰው ዳቦው የእውነትም ዳቦ ሳይሆን ስጋው ከሆነ የክርስቶስን መስዋዕትነት በተደጋጋሚ ስለሚያደርገው ምልከታው ለተደጋጋሚ መስዋዕት አስተምህሮ (doctrine of the mass) መሰረት ይጥላል።

የሉተራኖች ምልከታ አካላዊ የክርስቶስ ደም እና ስጋ በዳቦው እና በወይኑ ውስጥ ይገኛል ብሎ ያስተምራል። ይህ እይታ ኮንሰብስታንሽን የሚባል እና የተደጋጋሚ መስዋዕት አስተምህሮን በውስጡ የሚያቅፍ በመሆኑ ለሮማ ካቶሊኪስም አይነት ትችት ክፍት ነው።

የአብዛኞቹ የፕሮቴስታንቶች ያላቸው እይታ የአስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን የሲዊዙ ሃዳሽ ዑርሊች ዝዊንግሊ እይታ ነው። በየትኛውም አይነት መንገድ በጌታ እራት ውስጥ የክርስቶስ መገኘት የሌለበት ሲሆን እራቱ የክርስቶስ ሞቱ ማስታወሻ ብቻ ነው ሚወክለው የሚል ነው። የሮማኒዝምን እና የሉተራኒዝምን ስህተቶች በግልጽ የተከላከለ ቢሆንም ነገር ግ ን ይህ እይታ እራሱ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ እና የጌታ እራት በዚህ ያህል

ጥንቃቄ ለምን መወሰድ እንደሚገባው የሚያብራራ አይደለም። እራቱ ማስታወሻ ብቻ ከሆነ እራስን መመዘን እና "የመጥፋት" ፍራቻ አያስፈልግም  (1 Cor. 11:29)።

 በጌታ እራት ላይ የተሃድሶዎች እይታ ክርስቶስ በእርግጥም ይገኝበታል ነገር ግ ን በአካል ሳይሆን በመንፈስ በሆነ መገኘት ይገኝበታል የሚል ነው። በሌላ አነጋገር እርሱ ለእግዚአብሄር ህዝብ እምነት ተገኝቶ ከእነርሱ ጋር ህብረት በማድረግ በእምነት ከእርሱ ጋር ይመግባቸዋል። እርሱ ዳቦውን እና ወይኑን እምነታቸውን ወደ እርሱ ሊመራው ይጠቀምበታል።

የተሃድሶዎች እይታ በግልጽ በ1ቆሮ 11:29 ስለጌታ እራት "የጌታን ስጋ ስለማይለይ" በሚለው ክፍል ተገልጿል።እንዲሁም ይህ "ይህ ስጋዬ ነው" በሚለው የኢየሱስ የራሱ ቃል ላይ የተመሰረተ ነው። አንድ ሰው እራሱን ሳይፈትሽ መብላቱ እና መጠጣቱ ሊያስፈርድበት የሚችለው በእራቱ ላይ ክርስቶስ በመገኘቱ ብቻ ነው። በእራቱ ላይ ያለው ማንኛውም በረከት ከክርስቶስ መገኘት የተነሳ ነው። መጽሃፍ ቅዱሳዊ የሆነው የተሃድሶዎች እይታ ለጌታ እራት እጅግ ብዙ የሆነን ትርጉም እና ትርፍ ይሰጣል።በዚህም በሚስጢሩ በኩል ክርስቶስን እንደ አዳኛችን እና ታዳጊያችን በሙላቱ ተገናኝተን እንደሰትበታለን። ስለዚህ እንጠቀምበት።

## የጌታ እራት ህብስት እና ወይን

ከጌታ እራት ጋር በተያያዘ የምንጠይቀው ጥያቄ ቢኖር "በጥምቀት ቁርባን አንድ ነገር (ውሃ) ብቻ ኖሮ ሳለ ለምን በጌታ እራት ጥምቀት ሁለት ነገሮች ይኖራሉ እነርሱም (ስጋ እና ወይን)?

መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ህብስት እንደ ህይወት መሰረታዊ ነገር ተመስሎ እናገኘዋለን። በዚህም ምክኒያት ብዙውን ጊዜ "የህይወት ርዳታ" እንለዋለን ደግሞም ለ"እለት እንጀራችን" በጌታችን ጸሎት ውስጥ ስንጸልይ ለምድራዊ ችግሮቻችን ሁሉ እንለምናለን። ስለዚህ ህብስቱ የክርስቶስ ኢየሱስ መስዋትነት ለመንፈሳዊ ህይወታችን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ወካይ ነው። የ"እለት እንጀራችን"ን ሳናገኝ መኖር እንደማንችለው ሁሉ ያለ ክርስቶስ መኖር አንችልም።

ታዲያ ወይንስ ለምን ተመረጠ?

ወይን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅንጦትን ፣ መትረፍረፍን ፣ መስባትን ፣ብልጽግናን እና ግብዣን ይወክላል (ዘዳ 28:51 ፣ መዝ 104:15 ኢሳ 55:1 ፣ ኢዩ 3:18)። ለህይወት ከሚያስፈልጉን መሰረታዊ ነገሮች ያለፈን፣ ህልውናን ከተራ ህይወት ከፍ የሚይያደርግ፣ እና ደስታ ወይም ሀሴትን ይወክላል።

ስለዚህ የጌታ እራት ወይን ክርስቶስ ለመንፈሳዊ ህይወታችን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ለመስባቱ ፣ ለብልጽኛው እና ለደስታውም ጭምር እንደሚሆን ያመለክታል። በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሰጠን ያስታውሰናል። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ “ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ይልቅ እጅግ አብልጦ” (ኤፌ 3:20) ይሰጠናል። በእርግጥም በምህረቱ ፣ በፍቅሩ እና በደግነቱ እጅግ ባለጠጋ ነው።

እነዚህን ሁለት የጌታ እራት አካሎችን አንድ ላይ መውሰድ አሁንም ክርስቶስ ሁሉ ነገር እንደሆነ ያስታውሰናል። የጌታ እራት ዋነኛ ምስክርነቱ ክርስቶስ የድነታችን አልፋ እና ኦሜጋ ፣ ከእርሱ ውጪ ምንም ነገር የሌለን ፣ በእርሱ ሁሉ ነገር ያለን እና እርሱ እና እርሱ ብቻ ልንመኝ ፣ ልንፈልግ ፣ ልንወድድ እና ልናገለግል የተገባው መሆኑን ያሳየናል።

የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በጌታ እራት እየተደሰትን ባልተከፋፈለ ልብ አንፈልገው፣ በሙላቱ እንደሰት፣ በእራሳችን እየተማመንን እና ከእርሱ ውጪ ያሉ ነገሮችን በመሻት ሳይሆን፤ ከሙላቱ በመመገብ፣ በጸጋው በመታደስ፣ ይህንን አለም ትተን እርሱ በአባቱ ቤት ባዘጋጀልን መኖርያ አብረነው ስንሆን ሊኖረን የሚችለውን ደስታ ጣዕም እናጣጥም።

## እራስን መመርመር እና የጌታ እራት

መጽሐፍ ቅዱስ ከጌታ እራት ጋር በተያያዘ በትጋት ራሳችንን እንድንፈትሽ ያዘናል “ሰው ግን ራሱን ይፈትን ፥ እንዲሁ ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ ፤ ሳይገባው የሚበላ እና የሚጠጣ የጌታን ስጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድን ይቀበላልና ፥ይጠጣልምና” (1 ቆሮ 11:28–29)። በእርግጥ ይህ ለጌታ እራት የሚተገበር ብቻ ሳይሆን የሁል ጊዜ ተግባራችን ስለሆነ ራሳችንን መመርመር ያለብን ለምን እንደሆነ ልናውቅ ይገባል (ሰቆ 3:40፣ 2 ቆሮ 13:5)።

በመጀመሪያ እራስን ስለ መመርመር እያወራ መሆኑን እንወቅ። ጥሪው የሌሎችን ህይወት እንድንመረምር ሳይሆን የራሳችንን ህይወት እንድንመረምር ነው። ሌሎችን መመርመር እራስን ወደማጽደቅ ይመራናል። እራሳችንን መመርመር ግን ወደ እውነተኛ ንስሃ እና በእግዚአብሔር ላይ ወደመታመን ይመራናል። ሌሎችን መመርመር ብዙውን ጊዜ እራስን ከመመርመር የሚደረግ ሽሽት ነው።

ሁለተኛ *እራስን* መመርመር እንጂ በራስ መመርመር አይደለም። እራሳችን ላይ የምንፈርድ ከሆነ አይፈረድብንም ማለት ነው (1 ቆሮ 11:31)። ሊመረምሩን እና ሊመዝኑን የሚገባቸው እግዚአብሔር እና ቃሉ ናቸው(1 ዜና 28:9 ፣ መዝ 26:2 መዝ 44:21)። ጸሎታችን መሆን የሚገባው "አቤቱ ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፤ ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ ፤ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ ፤ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ" መዝ 139:23–24። ራስን መመርመር ማለት እራስን ለእግዚአብሔር ምርመራ ማቅረብ ማለት ነው።

ሰስተኛው- እራስን የመመርመር አላማ *ድነታችንን* ወይም እምነት እንዳለን ማያ *አይደለም*። ይህ የማይቻል ነገር ነው። እምነት የሌላቸው እራስን የመመርመር ጸባይ የላቸውም። እራስን መመርመር ያላቸው ሰዎች ድነታቸውን ጥያቄ ውስጥ በማስገባት መጠራጠር ወይም ለመጠራጠር ሊነሳሱ አይገባም። ጥርጣሬ ሃጥያት ነው። ይልቅ እራስን የመመርመር አላማ በእምነት እንዳለን ለማረጋገጥ ማለትም ህይወታችን እግዚአብሔራዊ ፣ ታማኝ እና በእምነት እየተመላለሰ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው (2 ቆሮ 13:5) ።

ይህንን ካልን ወዲህ፤ እራስን መመርመር ሦስት ነገሮችን ያቀፈ ነው- እነርሱም ሀጥያተኛነታችንን፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እና ለእኛ የሰራው የጸጋ ስራ ፣ እና ለእርሱ በመታዘዝ እና ቅዱስ ምስጋና እንድንኖር የተጠራነውን መጠራት ያካተተ ነው። የራሳችንን ሃጥያተኝነት የምንመለከተው የመላ ብልሹነታችንን ጥልቀት እንድንረዳ እና የራሳችን ልብ ሀጥያታችንን በመሰወር እንዳያታልለን ብሎም ሃጥያታችንን በደንብ ባወቅነው እና በገለጥነው ቁጥር ወደመስቀሉ እንሮጥ ዘንድ ነው (ምሳ 28:13)። በእኛ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስራ የምንመረምረው፣ መንፈሳዊነታችንን ያገኘነው ፣ የምንኖር እና የምንቀሳቀሰው በጸጋው ብቻ መሆኑን በተረዳን ቁጥር እግዚአብሔር ለእኛ ላደረገው ሁሉ እጅግ አመስጋኞች እና በጸጋው ላይ ይልቁኑ የምንደገፍ እንድንሆን ያደርገናል። ጥሪያችንን የምንመረምርበት ምክንያት ጥሪያችንን እንድንረዳ ፣ ጥሪያችንን ለመፈጸም በትጋት እንድንታገል እና በእግዚአብሔር መንገድ መዓዝ እንዲሆንልን ነው። ስለዚህ ክርስቲያናዊ ኑሯችንን፣ ጸባይ፣ እና ልምምዳችንን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን እንድንመረመር ተጠርተናል።

የእግዚአብሔር ቃል ካስቀመጠልን መስመር ጋር ህይወታችን እና ምልልሳችን አንድ ካልሆነ ንስሃ እንድንገባ ፣ ወደ ክርስቶስ እንድንሮጥ እና ለጸጋው እንድንለምን ይጠበቅብናል። የዛን ጊዜ ራስን መመርመር ማለት እራስን ማደስ እና በጸጋው እና በእውቀቱ ለእግዚአብሔር ክብር በሙላት ፍሬያማነት ይሆናል።

## ክፍል ፫ - ማጣቀሻዎች


1. Form of Ordination of Elders and Deacons, in The Confessions and the Church Order of the Protestant Reformed Churches (Grandville, MI: Protestant Reformed Churces in America, 2005), 292.
2. Belgic Confession, Article 29.
3. Ibid.
4. Form for Excommunication, in Confessions and Church Order, 276.
5. Belgic Confession, Article 35.

ክፍል ፯

# የክርስቶስ መመለስ እና ነገረ ፍጻሜ

**የመጨረሻው ቀን**

መጽሐፍ ቅዱስ ስለመጨረሻው ቀን (ቀኖች) እና ስለመጨረሻው ጊዜ ሁነት በተደጋጋሚ ይናገራል ( ዘፍ 49፡1 ፣ ኢሳ 2፡2 ሚል 4፡1 ፣ ዩሃ 6፡39 ፣ ሐዋ 2፡17 ጢሞ 3፡1 ዕብ 1፡2 ፣ ያዕ 5፡3 ፣ 1ጴጥ 5፡3 ፣ 1ዩሃ 2፡18 ፣ ይሁ 18)። ይህም ብቻ ሳይሆን ስለ አለም መጨረሻ እና ስለዘመን ፍጻሜም አክሎ በርካታ ቦታዎች ላይ ያነሳል (ማቴ 13፡39-40 ፣ 1ቆሮ 15፡24 ፣ 1ጴጥ 4፡7 ፣ ራዕ 2፡26)።

ይህ የመጨረሻው ጊዜ እና የመጨረሻው ቀኖች መቼ ናቸው? እንደ እውነቱ እና ብዙ እንደሚወራው የቀረቡ ወይስ ፍጹም የራቁ ናቸው? በዚህ ዘመን ስለእነርሱ ማወቅ ይጠቅመናል?"አለም ያበቃለታል" ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? እነዚህ መመለስ የሚገባቸው ጥያቄዎች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ የአዲስ ኪዳንን ዘመን ሙሉ በሙሉ የመጨረሻው ጊዜ እንደሆነ ግልጽ ያደርግልናል። ይህንንም በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡11 ጳውሎስ ትምህርቱን ለቆሮንቶስ አማኞች እና ለእኛ የአለም ፍጻሜ እንደመጣብን እና እንደደረሰብን በመናገር ሲያስተምር እንመለከታለን። በተመሳሳይ ዕብ 9፡26 ክርስቶስ ሀጥያትን ሊያርቅ እራሱን መስዋዕት ማድረጉ የዘመን መጨረሻ እንደሆነ ያመላክተናል (. ዕብ 1፡2 ፣ 1ጴጥ 1፡5 ፣ 20 1ጴጥ 4፡7 ፣ 1ዩሃ 2፡18)።

የክርስቶስን ዳግም መምጣትን እና ታላቁን የፍርድ ቀን የአለም "ፍጻሜ" ((ማር 13፡7 ) እና ከመምጣቱ በፊት ያሉትን ጊዜ "የመጨረሻው ቀን" (2ጢሞ 3፡1) ብሎ መጥራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አይደለም ይህ የተለየ ዘመን ሳይሆን የአዲሱ ኪዳን ዘመን አካል ነው።የምንኖርበት ዘመን ይህ "ቀን"፣ ይህ ጊዜ የመጨረሻው ነው። ከዚህ በኋላ ከአዲስ ሰማይ እና ምድር ውጪ የሚመጣ ሌላ ምንም ነገር የለም።

የዘመን ፍጻሜ አሁን ከሆነ ፣ አንዳንዶች እንደሚሉት ፣ ጌታ ከመመለሱ በፊት አለም ለብዙ ሺህ ዓመታት ሊቆይ እንደሚችል ማመን ይከብዳል ። እንግዲያው መጨረሻው ከመጀመሪያው እና ከበፊቱ ታሪክ ሁሉ ይረዝማል? በእርግጥም መጨረሻው እንደዚያ ቢሆን እንግዳነቱ አያጠራጥርም።

መጽሐፍ ቅዱሳችን ይህንን ጠቅላላ ዘመን የመጨረሻው ዘመን እና የሁሉ ነገር ፍጻሜ አድርጎ ይመለከተዋል። ምክንያቱም ደግሞ የክርስቶስ መምጣት በቶሎ እንደሆነ ቃል ስለተገባልን እና እግዚአብሄር ስራውን

የሚጨርስበት እና “ፈጽሞ እና ቆርጦ” የሚያደርግበት ስለሆነ ነው (ሮሜ 9፡28)። ሁለቱ ነገሮች የተያያዙ ናቸው። የክርስቶስ በቶሎ መምጣት በብዙ አመታት ብዛት አይለካም ፣ ይልቁንም እግዚአብሄር የፈቃዱስን ስራ እየጨረሰ ነው እና በሙሉ በሙሉ እንደተጠናቀቀ ክርስሮስን ይልካል።

የአሁኑ ያለው ዘመን በጠቅላላው የዘመን ፍጻሜ ነው የሚለው እውነታ እጅግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ይህም ማለት እኛ ሁላችን እየኖርን ያለነው በመጨረሻው ዘመን ላይ በመሆኑ በጥቂቱም ቢሆን የመጨረሻው ዘመን ክስተቶችን መካፈላችን አይቀሬ ነው (ማቴ 24፡34) ፣ ይህም ሁላችንም ፍጻሜውን ከእኛ እጅግ በራቀ ሁኔታ ወደፊት እንደሆነ ሳይሆን ወደ እኛ በእጅጉ የቀረበ እንደሆነ በማሰብ (በመጠባበቅ) እንድንመላለስ እና በተጨማሪ ተስፋችን በሚመጣው በክርስቶስ ላይ እንጂ ከዚህ ምድር ወይም በምድር ካሉት ነገሮች አይደለም። እነርሱ አስቀድመው ወደ ፍጻሜያቸው እየመጡ ነው።

በዘመን ፍጻሜ እንደምንኖር ማወቅ እንዴት የሚያስፈራ ነገር ግን አስድናቂ ነገር ነው። በየዕለቱ እንቅስቃሴያችን የመጨረሻው ፍርድ እና የአዳኛችንን መምጣት እየተመለከትን እንኖራለን። አገልጋዮች የጌታን ፍርሃት በማወቅ ይሰብካሉ። እኛ ሁላችንም እንደ መጻተኞች እና ጉዞአችን በጣም በቅርቡ እንደሚጠናቀቅ ተጓዦች ፤ የዘላለሟን ከተማ በቅርብ ለመጀመሪያ ጊዜያችንን እንደምናያት በማወቅ እንኖራለን። የምንኖረው በአስጨናቂ ጊዜ ውስጥ መሆኑን እንገነዘባለን። ፍጻሜው በጣም ቅርባችን እንደሆነ እናውቃለን ፣ ነገር ግን  አንፈራም ፣ ምክንያቱም የመቤዛችን ቀን ቀርቧል።

## ልዩ ልዩ የክርስቶስ መምጣቶች

በመጽሃፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሰረት አዲስ ኪዳን በሙሉ የዘመን ፍጻሜ መሆኑን ተመልክተናል። የመጨረሻው ቀን ወይም የመጨረሻው ጊዜ -ፍጻሜው ወደፊት ብቻ ሳይሆን በአሁን ያለ ነገር ነው ፣ በየትኛውም ጊዜ ቢኖር  እያንዳንዳችንን የሚነካ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን።

የክርስቶስ መምጣት ከዚህ በእውነታ ብርሀን አንጻር ልንረዳው ይገባል። በእርግጥ ሁሉም ነገሮች ወደ ፍጻሜያቸው የሚደርሱበት ታላቅ የታሪክ ክስተት ነው።ወደፊት ብቻ ሳይሆን አሁን እየሆነ ያለ ነገር ነው።

የክርስቶስ መምጣት በቤተልሄም መወለዱን ፣ ለፍርድ መመለሱን እና በመካከላቸው የተከሰተውን ሁሉ ጨምሮ እንደ አንድ ክስተት በቅዱሳት መጽሃፍ ተገልጧል። ስለዚህም ነው የብሉይ ኪዳን ነብያት በሺህ

አመታት ታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ሁነት ቀላቅለው የሚያቀርቡልን። በእነርሱ ሁሉንም እንደ አንድ ክስተት ያዩታል  በእይታቸውም አልተሳሳቱም ።

ከእግዚአብሄር አላማ አንጻር እና ከዘላለም እይታ አንጻር (2ጴጥ 3፡8) የክርስቶች ዳግም መምጣት ታሪክን የሚቋጭ ፣ የእግዚአብሄርን ሉዓላዊ አላማ የሚያሳካ ፣ የዘላለሙን እና ሰማያዊውን መንግስት የሚያመጣ አንድ ስተት ነው (ዳን 9፡24)። በመንፈስ መሪነት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ያዩት ይህንን ነው ።

ይህ ሁሉ አንድ ክስተት ነው የመባሉ እውነታ ክርስቶስን ሊመጣ ዝግጁ ነው ማለት  ነው። ቅዱሳት መጽሃፍ የሚናገሩት እንዲህ ነው ። ምንም እንኳን ስለ ግላዊ እና አካላዊ መምጣቱን ወደፊት በመመልከት እንደ ወደፊቱ ክስተት ቢናገርም በታሪክ ሁሉ እየመጣ መሆኑን ለማሳየት አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይናገራል። እርሱ በመንገድ ላይ ነው፣ እና በመጨረሻው ላይ ያለው የግል ገጽታ በቤተልሄም የጀመረው ነገር የመጨረሻው ደረጃ ብቻ ነው።

ስለዚህ ቅዱሳት መጽሃፍ የክርስቶስን መወለድ "የመምጣቱ" አንዱ አካል ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎች የተለያዩ ክንውኖች የክርስቶስ "ምጽዓት" አካል አድርጎ ያቀርባሉ።

ክርስቶስ በመንፈስ (ዩሃ 14፡16-18)። ምክንያቱም የመንፈስ መፍሰስ የክርስቶስ የመምጣቱ አካል ስለሆነ፣ ሃዋሪያው ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ስብከቱ ላይ በመንፈስ መፍሰስ እና ከአለም ፍጻሜ ጋር በምንገናኛቸው ነገሮች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አላደረገም - ደም እና እሳት ፣ ጢስ እና ጭለማ (ሐዋ 2፡16-21)።

ክርስቶስ ለአማኞች በሞ መጣል። እርሱ እራሱ ይመጣል፣ ምንም እንኳን በግል እና በአካል የሆነ መምጣት ባይሆንም ። ይህንን በዩሐ 14፡2-3 ባለ ክፍል ውስጥ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራን አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ ፥ እኔ ባልሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁና ወደ እኔም እወስዳችኋልሁ።" በማለት አረጋግጦልናል። ይህ በርግጥም እኛን በመሞት መጽናኛችን ነው። ክርስቶስ በህይወታችን በግል እና በግልጽ ባይመጣም በወንጌል ድምጹን ሰምተን እንከተለዋለን (ዩሐ 10፡27)። ክርስቶስ በሚያጽናናው መንፈሱ በኩል ወደ እኛ እንደመጣ እና ንሞት እርሱ መጥቶ ወደ እራሱ እንደሚቀበለን እናምናለን(ዩሐ 14፡3)። በዚህም ምክንያት እርሱን በአካል አግኝተነው እና ለዘላለም በደስታ ከእርሱ ጋር እንሆናለን።

ክርስቶስ በስብከተ ወንጌል በኩል መጥቱል። ክርስቶስ በወንጌሉ በኩል የተናገረው ማስረጃ ነው (ዩሃ 10፡27 ፣ ኤፌ 2፡17)። ይህ ነጥብ በማቴ 28፡19-20 ያለው ክፍል በሚገባ ያነሳልናል። ይህ የማቴ 28:19–20 ሃሳብ ነው። በወንጌሉ ስብከት ከክርስቶስ መምጣት ማስተዋል አለብን ።

ይህ ሁሉ ማለት የክርስቶስ መምጣት እኛ ላይ ፈጣን ተጽዕኖ የሌለበት የወደፊት ክስተት ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ልንቆጥረው የሚገባን ወቅታዊ ንገር ነው። በርግጥም በአንድም ሆነ በሌላ ኢየሱስ ክርስቶስ በየዕለቱ ይመጣል እና ወደ ራሱ ሊወስደን ሲመጣ በራሳችን ህይወት በእርግጥ ይመጣል።

**የክርስቶስ ዳግም መምጣት**

የክርስቶስ መምጣት የተለያዩ ገጽታዎች እንዳሉት ተናግረናል። በልደቱ፣ በመንፈስ ስጦታው፣ በወንጌል ስብከት እና በእኛ ሞት መጣትን ይጨምራል። እነዚህ ሁሉ ለፍርድ እና ለድነት ስለክርስቶስ መምታት የተለያዩ ገጽታዎች መሆናቸውን አሳይተናል።

ያም ማለት ኝ፣ የክርስቶስ መምጣት በአለም ፍጻሜ ልዩ በሆነ መንገድ መናገር እና ሁለተኛ ወይም የመጨረሻ ምጻቱ ብለን መጥራት አንልም ማለት አይደለም። ይህ የመጨረሻው ምጻት እና እንደ ልደቱ እና ስቅለቱ ካሉ የታሪክ ታላላቅ ክንውኖች አንዱ ይሆናል ምክኛቱም አሁን እንደምናውቃቸው የታሪክ ፍጻሜ እና የነገር ፍጻሜ ነው።

በተለያዩ መንገዶች ይህ መምጣት ልዩ እና የተስፋችን ሁሉ ትኩረት ነው።

የክርስቶስ የመጨረሻው መምጣት የሚሆነው ግለሰባዊ ነው (ማቴ 24፡30 ፣ 1ተሰ 4፡16)። በመንፈስ ቅዱስ በኩል ወይም በስብከተ ወንጌል በእንደራሴዎቹ (በውክልና) በኩል የሚመጣ ሳይሆን እራሱ ማንንም ሳይወክል በአካል የሚመለስ ይሆናል። አይኖች ሁሉ ይመለከቱታል (ራዕ 1፡17) ፣ በእርሱም የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል ይገለጣል (ቆላ 2፡9) ፣ ክርስቶስም በአለሙ ላይ በጽድቅ ይፍርዳል (ሐዋ 17፡31) እንዲሁም የእርሱ የሆኑትን ህዝቦቹን ወደ ዘላለማዊው ክብር ይቀበላቸዋል (ያስገባቸዋል)። ይህ ግለሰብ ነክ (ግለሰባዊ) የሆነ የክርስቶስ መምጣት የእኛ (የአማኞች) የተስፋችን ማዕከላዊ በመሆኑም እርሱን ለማየት እንጠባበቃለን።

የክርስቶስ የመጨረሻው መምጣት የሚታይ ነው (ሐዋ 1፡11)። በርግጥም በዚህ የመጨረሻው መምጣቱ አይን ሁሉ የወጉትም ያዩታል (ራዕ 1፡7)። ስለዚህ መጽሃፍ ቅዱሳችን የክርስቶስን የመጨረሻ መምጣትን እንደ መገለጥ ወይም በአካል ስለመምጣቱ እንደሆነ ይገልጹልናል (2ተሰ 1፡7 ፣ 1ጢሞ 6፡14 ፣ 1ጴጥ 1፡7)። ያለ እርሱ በእጊዝብሄር ፊት ለመቆም ምንም አይነት ትምክህት ሊኖረን ስለማይችል ኢየሱስ ለእኛ ሊታይ ይገባዋል። እንደ ሰቀሉት እና እንደገደሉት ለአለም መታየት አለበት። መጽሃፍ ቅዱሳችን የክርስቶስን የመጨረሻ መገለጥ የክርስቶስ ዳግም ምጻት ብለው ይገልጹታል (ዕብ 9፡28) ምክኛቱም የመምታቱ ሌሎች ገጽታዎች ስለሌሊ ሳይሆንይህ ሁለተኛ መምጣቱ የተባለበት ምክንያት በአካል ወደዚህ ምድር መምጣቱ ህጻን ሆኖ በቤተልሄም መምጣቱን ተከትሎ በአለም መጨረሻ ላይም በአካል በመጣበት ሁነት ለሁሉም ሊታይ ሆኖ ስለሚገለጥ ነው።

በመጨረሻም የፍጻሜው የክርስቶስ መምጣት በክብር እና በሃይል ይሆናል (ማቴ 24፡30 ፣ ማቴ 25፡31)። ዳግም ምጽዓቱ ከፊተኛው የተለየ ነው ምክንያቱም በመጀመሪያ ጊዜ በባሪያው መልክ በሃጥያተኛ ስጋ ምሳሌ መጥቷል (ሮሜ 8፡3 ፣ ፊሊ 2፡7)። በዚያን ጊዜ በአባቱ ክብር የሚገለጥበት ልዩ የሆነ መገለጥ ነው (ማቴ 16፤ 27)። ሃይሉ እና ክብሩ በነገሮች ፍጻሜ ላይ የሚገለጠው ለሃጥያተኞች ፍርሃት ይሆናል (ራዕ 1፡7 ፣ ራዕ 6፡15-17) ፤ የእርሱ ለሆኑቱ ደግሞ የደስታ እና የናፍቆታቸው የማክተሚያ ምክንያት ይሆንላቸዋል (ራዕ 1፡3 ፣ ራዕ 22፡20 )።

የክርስቶስ መመለሻ ቀኑ እና ሰዓቱ ፤ ወሩ እና አመቱም ጭምር በእኛ ዘንድ የሚታውቅ አይደለም። የማወቅ እድሉ ተሰቶንም ብናውቀው እንኳን ይጠቅመንም። ምክንያቱም ያኔ ወይ ግድየለሾች እና አለማዊያን እንሆናለን ወይም ተስፋ እንቆርጣለን። ነገር ግን ይህን ቀን ባለማወቃችን አይኖቻችንን በመመለሱ ላይ በማቅናት በአስተውሎት በሆነ ህይወት እና በጸሎት ፤ በመጠን እና በትጋት በመኖር የቅድስና እና ግዚአብሄርን የመምሰል ህይወታችንን እንድንቀጥል ያግዘናል (ማቴ 24፡42-51 ፣ 1ተሰ 5፡1-8 ፣ 2ጴጥ 3፡10-12)። ስለዚህም ቃል እንደገባው ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ እናምናለን። ምንም እንኳን በእኛ የህይወት ዘመን በአካል ተገልጦ ባናየውም እንኳን በወንጌሉ በኩል ድምጹን ለመስማት እና ለመከተል እንናፍቃለን (ዩሃ 10፡27)።

### አንድ የክርስቶስ የመጨረሻ መምጣት

ከዓለም ፍጻሜ በፊት ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በግል እና በሚታይ ምጽዓት የሚያምኑ አሉ። ሁለቱም ቅድመ ሺ አመት እና ዲስፔንሺናሊዝም ከመጽሃፍ ቅዱሳዊ ምስክርነት በተቃረነ መልኩ ክርስቶስ ከአንድ ጊዜ በሆነ መገለጥ እንደሚመጣ ያስተምራሉ። እነዚህን አመለካከቶች በኋላ በዝርዝር እናብራራቸዋለን።

የቅድመ ሺ አመት አስተምህሮ የክርስቶስ ተመልሶ መምጣት ከሺው አመት መንግስት ምስረታ በፊት ይህም ከአለም ፍጻሜ ሺህ አመታት በፊት እንደሚሆን ያስተምራል። አስተምህሮቱ ስያሜውን ያገኘው በዚህም ምክንያት ነው። ይህ መምጣቱ "ንጥቀት (መነጠቅ)" ተብሎ ተገልጿል። የሺው አመት መምጣት ክርስቶስ ለፍርድ ከመጣ ከአንድ ሺ አመት በኋላ የሚሆን ሲሆን በዚህ መምጣቱም ክርስቶስ አዲስ ሰማይ እና ምድርን የሚፈጥር ይሆናል።

ዲስፔንሽናሊስዝም (Dispensationalism) በመነጠቅ የሚያምን ብቻ ሳይሆን፣ "መገለጡ" የተባለውን ሶስተኛውን ግላዊ እና የሚታይ የክርስቶስን መምጣት ይይዛል። እንደ አማኞቹ ይህ መምጣት "ከቅዱሳኑ ጋር የሆነ መምጣት" ነው። ዲስፔንሽናሊስቶሽ ይህንን አስተምህሮ 1ተሰ 3፡13 እና በ ይሁ 14ን እንደ ማስረጃ ይጠቀማሉ። በዚህ ትምህርት መሰረት፣ ክርስቶስ፣ በመገለጥ ጊዜ በኢየሩሳሌም ከአይሁዶች ጋር መንግስቱን ይመሰርታል።

በእኛ ዘንድ መጽሃፍ ቅዱሳችን የሚያስተምረን ከክርስቶስ ስጋ መልበስ በኋላ እና ከአለም ፍጻሜው በፊት ክርስቶስ አካላዊ እና በሚታይ መልኩ የሚገለጠው አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ እናምናለን። የቅድመ ሺህውን "መነጠቅ" እና የዲስፔንሽናል "መገለጥ" የሚሉትን ሁለት ሃሳቦች እንዲያጸና የተጠቀሱት የመጽሃፍ ቅዱስ ምንባባት ስለተነሱት ሃሳብ ከማውራት ይልቅ ግልጽ በሆነ መልኩ የሚያብራሩልን በአለሙ መጨረሻ ክርስቶስ ስለመምጣቱ እና ስለመምጣቱ ብቻ ነው።

ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ተመልሶ እንደሚመጣ የሚናገረው የይሁዳ 14 እና 15 ክፍለ ምንባብ አስረግጦ የሚናገረው በዘመን ፍጻሜ ክርስቶስ ለፍርድ ተመልሶ ስለመምጣቱ ነው። በክፍሉ ውስጥ እንደምናነበው "ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ..........ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቷል" ይለናል። በንባቡ ውስጥ ይሁዳ ፍርድ ብሎ የጠቀሰው ከቁጥር 6 እና 7 ላይ እንደምንረዳው በፍጥረት ሁሉ ላይ ስለሚሆነው የመጨረሻው ፍርድ ነው። በቁጥር 6 እና 7 ላይ ባለው አውድ ንባብ ይሁዳ "ስለ ታላቁ የፍርድ ቀን" እና ስለ ሰዶም እና ገሞራ በእሳት መጥፋት ነው እርሱም የመጨረሻው ፍርድ ምስል ነው (2ጴ 2፡6 ይመልከቱ)።

ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ተመልሶ ስለመምጣቱ የሚያነሳልን ሌላው ክፍል 1ተሰ 3፡13 እና "መነጠቅ" ለሚለው አስተምህሮ መሰረት ሆኖ የሚጠቀሰው ደግሞ 1 ተሰ 4፡15-18 ያለው ክፍል ነው። ክፍሉ ግን ግልጽ በሆነ መልኩ ስለ ሁሉም ፍጻሜ በግልጽ እየተናገር ነው። በእነዚህ ክፍሎች እንደተገለጸው የክርስቶስ መምጣት በብዙ መላዕክት እና በእግዚአብሄር መለከት ይታጀባል፣ በሌላ ቦታ ደግሞ "የመጨረሻው መለከት" ተብሎ ተገልጿል (1ቆሮ 15፡52)። በሺ አመታት የታሪክ ሁኔት ፣ በሌላ የመለከት ድምጽ አልያም ደግሞ በሌላ መጨረሻ መታጀቡን አንመለከትም።

ስለዚህ ሁለቱም ክፍሎች ማለትም 1ተሰ 3 እና 4 መሰረት የጌታችን መምጣት ግልጽ በሆነ መልኩ የቅዱሳንን ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም መክበር ያመላክታሉ "....እንዲሁም ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንሆናለን" (1ተሰ 4፡17 በተጨማሪ ራዕ 21፡3 ፣ ራዕ 22፡4 ይመል)። በ1ተሰ 3 እና 4 ላይ በተጠቀሰው አውደ ንባብ የክርስቶስ መምጣት የሺ አመታት አገዛዝ በምድር ላይ መሆኑን የሚከተል እና ከዚህም ቀጥሎ በሰማያዊ ህይወት ይጠቃለላል።

በመጨረሻም በመጽሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከመጨረሻው ፍርድ ቀድሞ በሺው አመታት ውስጥ ስለሚሆኑ ክስተቶች ሳይሆን መነጠቅን ከመጨረሻው ፍርድ ጋር የሚያይዙ በርካታ ክፍለ ንባባት አሉ። ለዚህም እንደማሳያ የሉቃ 17፡28-37 ያለውን ክፍል በዋናነት መትቀስ ይቻላል። ስለሰዶም ማጣቀሻ በሚያዝ የሉቃስን እና ማጣቀሻውን ከይሁዳ 7 ጋር አነጻጽሯቸው። ይህም የሰዶም ክስተት የመጨረሻው ፍርድ አይነተኛ ምሳሌ መሆኑን ይህም "የዘላለሙ እሳት" ያጠራልናል። በተጨማሪም ከማቴ 24፡37-41 ጋር ያነጻትሩ።

ያለው አንድ መምጣት ብቻ ሲሆን እርሱም ለፍርድ እና ለድነታችን የሆነ መምጣት ብቻ ነው። ይህም እጅግ በቅርቡ ይሆናል።

## የክርስቶስ የመምጣቱ ምልክቶች

መጽሃፍ ቅዱሳችን የክርስቶስ መምጣቱ ሁሌም በምልክቶች የታጀበ መሆኑን ያመላክተናል። ይህም ስጋ ለብሶ መምጣቱ በምልክት ነበረ (ሉቃ 1፡18-20 41-45 ፣ ሉቃ 2፡12)። እንዲሁም መምጣቱም በምልክት

የታጀበ ይሆናል (ማቴ 24፡3 ፣ 30 ፣ ሉቃ 21፡11 ፣25)። መምጣቱን ተከትሎ የተጠቀሱ ምልክቶች ወሳኝ እና በትክክለኛው ምስለታቸው ልንረዳቸው ይገባል።

መምጣቱን ተከትሎ የሚታዩት ምልክቶች በተለያዩ ምድቦች የምንመድባቸው ናቸው። ይህም በፍጥረት ላይ የሚሆኑ ምልክቶች (ማቴ 24፡7 ፣ 29) ፣ በታሪክ ላይ የሚሆኑ ምልክቶች (vv 6-7) ፣ በቤተክርስቲያን ላይ የሚሆኑ ምልክቶች (vv 10-16) በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል። አንዳንዶቹ “የምጥ ጣር መጀመሪያዎች” ሲሆኑ (vv 5-8) ፣ ሌሎቹ ደግሞ  ግልጽ በሆነ መልኩ ስለመጨረሻው የሚናገሩ ናቸው (vv 14-16)። ጥቂቶቹ ደግሞ ስለ ክርስቶስ የሚታይ ሆኖ ስለመምጣቱ accompany የሚያደርጉ ናቸው (vv 29-31)።

ከክርስቶስ መምጣት ጋር ስለሚቆራኙቱ ምልክቶች እና ድንቅ ስለሆኑት መጽሃፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ጋር ስላላቸው ግንኙነት በብዙ መልኩ ትኩረት ማድረግ የምንወድባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ። አስተውሎ መጽሃፍ ቅዱሳችን ስለ ክርስቶስ መምጣቱ የሚያወሳን እየሆነ ያለ ሁነት አድርጎት ነው። እርሱ በመምጣቱ መንገድ ላይ ነው።

ክርስቶስ እየምጣ ነው ስንል የመምጣቱ ምልክቶች ሁሉ በአውራ ጎዳና ላይ እንዳሉ ምልክቶች አይደሉም፣ ይህ በቀላሉ ማስታወቂያ ወይም በሩቅ የሆነን ነገር ያመላክታሉ። እነዚህ የክርስቶስ መምጣት ምልክቶች እንደ ባቡር ፊሽካ ድምጽ እና የሃዲድ ጩኸት ናቸው። እንደዚህ አይነት ድምጾች የባቡሩ መምጣት አካል ሲሆን የሚፈጠሩትም በባቡሩ መምጣት ነው።

ስለዚህ እነዚህን የክርስቶስ መምጣት ምልክቶች እርሱ ሲቃረብ የእግሩ ድምጽ አድርገን ልንገልጸው እንችላለን። ልክ አንድ ሰው የእግሩ ዱካ ድምጽ እና በግልጽ እንደሚሰማው ሁሉ፣ ወደፊት እንደሚመታ እንዲሁ የክርስቶስ መምጣት መምጣት ምልክቶች የሚታዩት እና የሚሰሙት ይመጨረሻው መልክ ሲቃረብ ነው።

ይህ በራዕይ ውስጥ የምናገኘው የመለወጥ ትርጉም ነው ብለን እናምናለን። ።ማህተሞች ፣ መለከቶች እና ጸዋዎች ደረጃ በደረጃ  ፣ የምድር አንድ አራተኛው ክፍል  (ራዕ 6፡8) ፣ ከዚያም የምድር አንድ ሶስተኛ (ራዕ 8፡ 7-12 ፣ ራዕ 9፡18) በመጨረሻም ምድድ በጠቅላላ (ራዕ 16፡3- 4 , 17) ። በሌላ አገላለጽ በራዕይ መጽሃፍ ውስጥ የተገለጹት the አህተሞች ፣ መለከቶች ፣ እና ጽዋዎች  ተመሳሳይ ምልክቶችን እና የፍርድን

ያመላክታሉ። ነገር ግን እነዚህ ምልክቶች እና ፍርዶች እየጠነከሩ ይሄዳሉ። ታሪክ እየገፋ ሲሄድ እና ክርስቶስ ሲቃረብ በግልስት ይታያሉ።

ነገር ግን ምናልባት ምልክቶቹ ከክርስቶስ የእግሮቹ ዱካ ድምጸት የበለጠ ምስለት ይኖራቸዋል። በባቡሩ መምጣት የፉጨት እና የመንኩራኩሪች  ድምጽ እንዲሰማ እንደሚያደርግ ሁሉ እነዚህ ምልክቶች በክርስቶስ መምጣት የተከሰቱ ናቸው። እነዚህ ምልክቶች የሚከሰቱት በክርስቶስ መምጣት ነው ምክኛቱም በመምጣቱ ታሪክን እና ፍጥረትን ቤ/ክንም ጨምሮ ስለሚገዛ ነው።

እንደ ሉዓላዊ ንጉስነቱ እና ጌታነቱ በምድር ሆነ በሰማይ ነገሮች ሁሉ እንዲያበቃላቸው ብሎም ነገሮች ሁሉ እንዲከሰቱ የሚያደርገው ክርስቶስ ብቻ ነው (ማቴ 28፡18)። ይህ ምንም ነገር ከእርሱ ፈቃድ ውጪ በሆነ ሁኔታ በእድል አለመሆናቸው የአማኞች መጽናኛችን ነው።

እነዚህን ምልክቶች በፍጥረት እና በታሪክ ውስጥ የክርስቶስ የእጁ ስራዎች መሆናቸውን እናስብ ይሆናል። በርግጥም ምልክቶቹ እርሱ (ክርስቶስ) ነገሮችን እንዲው በአቦ ሰጥ እንደማይሰራቸው ፣ ይልቁንም እለት በእለት ነገሮችን ወደ ታየላቸው ፍጻሜ እንደሚያመጣቸው ማሳያም ነው።

በዙሪያችን በሚሆኑት ነገሮች ከመፍራት እና ከመደንገጥ ይልቅ ነገሮች ሁሉ የእርሱን ሃይል እና መምጣት ስለሚናገሩን መምጣቱን ተስፋ በማድረግ እንጠባበቃለን። በጦርነት እና በአደጋዎች ብሎም በክህደት መካከል ቆመን ፤ የሰው ልጆች ልብ በፍርሃት ሲሞላ እና የሰማይ ሃይላት ሲናወጡ መዳናችን ከምንም ጊዜ በበለጠ ወደእኛ መቃረቡን አስተውለን አይናችንን በማቅናት ከአንገታችን ቀና እንላለን (ሉቃ 21፡25-28)።

**መነጠቅ**

መነጠቅ የሚለው ቃል በመጽሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ የምናገኘው ቃል አይደለም። ቃሉ ግን ያለምንም ተቃውሞ የክርስቶስን ድንገተኛ እና የሚታይ ሆኖ በሰማይ መገለጡን እና ቅዱሳንም ክርስቶስን በደመና ለመቀበል በአየር ላይ መሆናቸውን ለመግለጽ መጠቀም እንችላለን። ስለዚህ የእግዚአብሄር ቃል በ1ተሰ 4፡ 15-17 ላይ ይናገረናል። ይህ መነጠቅ ሚስጢር ነው የሚለውን ትምህርት ከመጨረሻው ታላቁ መከራ በፊት የሚፈጸመው የእግዚአብሄር ህዝብ በመከራ ውስጥ እንዳያልፉ መጽሃፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ እንቃወማለን።

መከራ እና የሚመታው አለም ፍጻሜ አንድ ሺህ ዓመት ሲቀረው (የቅድመ ሺው ዝመን መነጠቅ ) ነው። እነዚህ ሃሳቦች  በ1ተሰ 4 ብሎም በመጽሃፍ ቅዱስ አስተምህሮ ውስጥ ምንም መሰረት የለውም።

መነጠቅ ሚስጥራዊ አይደለም። በተሰሎቄ መጽሃፍ ላይ የተገለጸው ሁኔታ ምንም አይነት ነገር ቢሆንም አንድ የምናውቀው ነገር ቢኖር አንዳች ሚስጥራኢ የሆነ ነገር መሆኑን ነው። በክሉ ላይ እንደምናነበው ሁነቱ በመላዕክት አለቃ ድምጽ እና በእግዚአብሄር መለከት እንደሚሆን እናነባለን። ከክፍሉ እንደምንረዳው ይህ ሁነት አንዳች ኮሽታ ሳይሰማ የሚሆን ሳይሆን በታሪክ ውስጥ ከሆነው ይልቅ በጣም በድምጽ የተሞላ እና በጣም ሚስጢራዊ የሆነ ክስተት ነው የሚሆነው።

በሌላ ክፍል ላይ የምናገኘውም ምንባብ ከላይ ያነሳነውን ተመሳሳይ ሃሳብ የሚደግፍልን ነው። ማቴ 24፡30-31 ላይ የምናነበው ሃሳብ በ1 ተሰሎ 4 ላይ ካለው ክፍል ጋር በእጅጉን የሚመሳሰል ነው። ሁለቱም ክፍላተ ምንባባት መላዕክትን ፣ የመለከት ድምጽን እና ምርጦቹ (አማኞች) ወደ ክርስቶስ መሰብሰባቸውን ይጠቅሳሉ። በማቴዎስ ዘገባ ላይ ተጨምሮ የምናገኘው የሰው ልጅ በአካል መገልጡን (የናዝሬቱ ኢየሱ) ተከትሎ የምድር ነገዶች ሁሉ ዋይ ዋይ እንደሚሉ የተገለጸው ነው። እንግዲህ ይህ ሁሉ ክስተት ግልጽ ሆኖ ተጽፎ እያለ ማንም ሳያውቅ በሚስጥር ይሆናል ማለት አንችልም። በዚህ ጉዳይ ላይ ሚስትር ሊሆንበት የሚችል ነገር አይታይም።

በ1ቆሮ 15፡51-52 ባለው ክፍል ውስጥ ያለምንም መጠራጠር በ 1ቆላ 4፡15-17 ከተገለጸው ክፍል ጋር ፍጹም የሆነ ተመሳሳይነት ያለውን ሃሳብ ይነግረናል። በክፍሉ ውስጥ ሁለት ቡድኖች ማለትም ቀድሞውኑ ከሁነቱ በፊት ያንቀላፉቱ እና በአጸደ ስጋ ያሉቱ እንደሚነጠቁ እናነባለን። በቆሮንቶስ መልዕክት ላይ “ያላንቀላፉት” የሚላቸው እና በተሰሎንቄ ምልዕክት ላይ “በህይወት ያሉቱ” የሚላቸው የክርስቶስን መምጣት በህይወት እያሉ ስለሚከናወንባቸው ሰዎች ነው። ከላይ እንዳወሳነው የቆሮንቶስ መልዕክት ላይ የምናገኘው አውደ ንባብ መነጠቅ አንዳች በሚስጥር የሚከናወን ሳይሆን ይበልጡኑ በግልጽ እንደሚሆን ያመላክተናል።

በተመሳሳይ መልኩ መነጠቅ ከሁሉም ነገሮች ማብቂያ እና ከመጨረሻው መከራ (tribulation) በኋላ እንደሚከናወን አጠናክሮ የሚገልጽልን የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ማቴ 24፡29 ላይ “ከዚያች ወራት መከራም በኋላ........” የሚል ቃል እናገኛለን። የምድር ነገዶች ዋይ ዋይ ይላሉ የሚለውን ሃሳብ ከራዕ 1፡7 እና

ራዕ 6፡12-17 ካለው ክፍል ጋር አጣምረን ያየነው እንደሆነ የሚያመላክተው በአለም ፍጻሜ የክርስቶስን ለፍርድ ዳግም (ሁለተኛ) መምጣት ነው።

ማቴ 24፡ 37-41 እና ሉቃ 17፡26-37 በተመሳሳይ መልኩ ይህንን መነጠቅ ከምመጨረሻው ፍርድ በፊት እንደተፈጸመ ይገልጹታል። በእነዚህ ምንባባት ውስጥ የተገለጹት የሰዎች መወሰድ እና መውጣት ከኖህ እና ከሰዶም ዘመን ጋር ተነጻጽሯል። በሌላ አገላለጽ በኖህ ዘመን ሳይወሰዱ የቀሩት ልክ እንደ ሰዶም እና ገሞራ ለፍርድ የተጠበቁ ናቸው (ይሁ 7 ፣ 2ጴጥ 3፡3- 7 ይመልከቱ) ።

ከዚህ በተጨማሪም 1ተሰ 4 ስለ ሰውነታችን ትንሳኤ ይናገራል፣ ቅዱሳት መጽሃፍት በሁሉም ቦታ በመጨረሻው ቀን እንደሚፈጸሙ ይናገራል (ዩሐ 6፡39-40 ፣ 44-54 ፣ ዩሐ 11፡24)። በእርግጥ የመጨረሻው ቀን ከ 365 000 ሌሎች ቀናት አይከተልም። ስለዚህ በተለይ በዩሐ 12፡48 ላይ ያለምንም ማምታታት የመጨረሻው ቀን የፍርድ ቀን እንደሆነ ተነግሯል።

ስለዚህ የምንጠብቀው ከመጨረሻው እና ታላቁን መከራ በፊት አንድ ሺህ አመት በሚስጥር መነጠቅ ሳይሆን ሳይሆን በሁሉም ነገር መጨረሻ ላይ ቅዱሳንንበአደባባይ መነጠቅ፣ ውጤቱም ቀጣይ በክብር መኖራችን ከጌታ ጋር ይሆናል (1ተሰ 4፡17)።

## **የክርስቶስ በድንገት እና ሳይጠበቅ መምጣት**

መነጠቅ በአደባባይ የሚሆን ክስተት ከሆነ ክርስቶስ ባልተጠበቀ እና ድንገተኛ በሆነ ሁኔታ እንደሚመጣ ለምን እናነባለን (1ተሰ 5፡1-9)? መጽሃፍ የክርስቶስ መምጣት “ሌባ በምሽት እንደሚመጣ” ያስቀምጠዋል (ማቴ 24፡43 ፣ 2ጴጥ 3፡3 ፣ ራዕ 16፡15)።

እውነቱ ግን የክርስቶስ ባልተጠበቀ እና ድንገተኛ በሆነ ሁኔታ መምጣት ለማያምኑቱ ነው። ይህ በ1ተሰ 5፡1-9 ባለው ክፍል ላይ በሰፊው ተብራርቷል። በክፍሉ ውስጥ ጳውሎስ በጌታ የማያምኑትን “እነርሱ (they and them)” በማለት ከ “እናንተ ye and you” ከሚለው ቃል ለይቶ አቅርቧቸዋል።በተሰሎንቄ ላሉ አማንኞች የማይታበል ጥፋት “በእነርሱ” ላይ እንደሚመጣ ነግሯቸዋል (ቁ 3) ። “እናንተ ግን ፥ ወንድሞች ሆይ ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥” በማለት ልዩነታቸውን ያስቀምጥላቸዋል (ቁ 4)።

ክፉዎች የክርስቶስን መምጣት እና የመጨረሻውን የፍርድ ቀን የሚተባበቁ አይደሉም። ብዙዎች እንደሚመጣ እና እንደሚያውቅ ቢሰሙም ይህን እውነት በልባቸው እንደ እውነታነቱ አልተቀበሉትም (ሮሜ 1፡18)። እነዚህ ጴጥሮስ ዘባቾች ብሎ የሚጠራቸው ሰዎች ናቸው (2ጴጥ 3፡1-8)። በሚያደርጉት ስራቸው ላይ የእግዚአብሄር ቁጣ ፈጥኖ ባለመገለጡ እግዚአብሄር የማይቀጣ እንደሆነ ደምድመዋል። አሁን በምድር ላይ የላካቸው ፍርዶቹንም (ኤድስ  የመሬት መንቀጥቀጥ ፣ ድርቅ እና ረሃብ ፣ ጦርነት) ይገነዘቡም።

እንደነዚህ አይነት ሰውች ቤ/ክ ውስጥም ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ አምስቱ ሞኝ ደናግላን ተመስለዋል (ማቴ 25፡1-13)። ሙሽራው በሚመጣበት ሰዓት መብራታቸው ዘይት አልቆበት ተኝተው ነበር። በዚህም ምክንያት ከሰርጉ ግብዣ እከልክለዋል። እነዚህ ዝንጉዎች በቤ/ክ ውስጥ ያሉ እና አማኝ (ደናግላን) የሚል ስያሜ ያላቸው ቢሆኑም ማንነታቸው ግን የግብዞች እና የኢ-አማንያን ናቸው።

በክፍሉ ውስጥ አምስቱ ብልህ ደናግላን የተወከሉት የእግዚአብሄር ሰዎች ሙሉ በሙሉ ሳያውቁ አልተወሰዱም (ተጨማሪ ማስረጃ መነጠቅ ሚስጥር አይደለም)። ምንም እንኳን በድካምም  ቢሆን ክርስቶስ እንደ ተስፋ ቃሉ በእርግጥም ተመልሶ እንደሚመጣ በማመን ከእንቅልፋቸው ነቅተው እየጠበቁት ነው። በ1 ተሰ 5፡4 ላይ እንደሚያስረዳን የእግዚአብሄር ህዝቦች ባለማመን እና በሃጥያት ጨለማ ውስጥ ያሉ አይደሉም።በክርስቶስ መምጣት ሳያውቁ መወሰድ ባለማመን መወሰድ ነው። ምንም እንኳን አማኞች የክርስቶስን ተመልሶ መምጫ ሰዓቱን እና ጊዜውን ባያውቁም (ማቴ 24፡36 ፣ 42 ማቴ 25፡13 ፣ ማር 13፡ 32) ክርስቶስ በማያምኑት ላይ በድንገት እንደሚመጣው አይመጣባቸውም። የተስፋ ቃሉን በየዕለተ ዕለት ህይወታቸው ነቅተው መመልከታቸው ከኢአማኒያን የሚለያቸው ነው። ክርስቶስ እንደተናገረው “የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና” (ማቴ 24፡44)።

በዚህም ምክንያት ሁኔታዎችን እንድናስተውል እና በጸሎት እንድንጠባበቅ አስቸኳይ ጥሪ ተሰጥቶናል። ይህንን ጥሪ በማቴ 25፡13 ላይ እናገኛለን። በተመሳሳይ መልኩ 1ተሰ 5 “እንግዲአስ እንንቃ በመጠን እንኑር እንጂ እንደሌሎቹ አናንቀላፋ.......እኛ ኝ ከቀን ስለሆንን ፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤” (ቁ6 እና 8)።

ይህ ማስጠንቀቂያ አሁንም እጅጉን አስፈላጊ ነው። ሙሽራው ሲመጣ አምስቱ ደናግላን ተኝተው ነበር (ማቴ 25፡5)። ደናግላኑ በመብራታቸው ውስጥ ዘይት ይዘው ነበር (ዘይት የመንፈስ ቅዱስ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ነው) ግን ነቅተው አልጠበቁትም ። ይህንን በማሰብም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሌላ ክፍል ላይ “የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆን?” በማለት የተናገረው (ሉቃ 18፡8)። ይህ የተነገረው አስቸኳይ እና ተደጋጋሚነትን በሚጠይቅ ጸሎት ነው።

ይህ ማስጠንቀቂያ ያስፈለገበት ምክንያት በምድር ላይ በሚኖረን የቆይታ ህይወት ክርስቶስ እንደማይመጣ እና ቸልተኝነት በተሞላበት ህይወት እንዳንኖር ነው።(የቀረ)  ስለዚህም ወደፈተና እንዳንገባ አይኖቻችንን በማቅናት በጸሎት ልንተጋ ይገባናል።

## የክርስቶስ በቶሎ መምጣት

ክርስቶስ “እነሆ በቶሎ እመጣለው” ሲል ምን ማለቱ ነው (ራዕ 22፡7 ፣ 12 ፣ 20)? ይህ ጥያቄ ክርስቶስ የተስፋውን ቃል ከሰጠን ሁለት ሺ አመታትን እንዳስቆተረ ስናስብ ምላሽ እንዲያገኝልን መጓጓታችን አይቀሬ ነው።

ፈርሃ እግዚአብሄር የሌላቸው እና ዘበኞች ይህንን እውነታ ክርስቶስ ፈጽሞ እንደማይመጣ ማስረጃው አድርገው ያቀርቡታል (2ጴጥ 3፡3)። ቢሆን መዋሸት የማይችለው የእግዚአብሄር ልጅ ማመናችን በእያንዳንዱ ቅጽበት መምጣቱን ነቅተን በጸሎት እየተጋን እንጠባበቃለን። ሆኖም ተስፋ እንዳንቆርጥ ቶሎ ስለመምታቱ ሲናገሩ ምን ማለቱ እንደሆነ መመርመሩ ጠቃሚ ነው ።

ከላይ እንደተመለከትነው የክርስቶስን መምጣት በተለያየ ምልከታ አንስተን ሁሌም እየመጣ እንደሆነ ተመልክተናል። ይህም ክርስቶስ በፍርዱ ፣ በስብከተ ወንጌሉ ፣ በመንፈስ ቅዱስ እና በስጦታዎቹ ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ግሉ በሞቱ በኩል በየእለቱ እየመጣ ነው። በዚህ ሁሉ የተለያየ የመምጣቱ ሁኔታ ውስጥ ዋጋው በእጁ ነው ፤ ለእያንዳንዱም እንደየስራው የሚከፍለው ይሆናል (ራዕ 20፡12 ፣ ራዕ 22፡12)።

የሆነው ሆኖ፣ ራዕይ 22 በግልጽ እንደሚያስቀምጠው ክርስቶስ በቶሎ እንደሚመጣ ሲናገር በተለይ የመጨረሻውን ግላዊ እና የሚታየውን መምጣቱን እየተናገረ ነው።  ከዚህም አንጻር እርሱ ቃሉን ይጠብቅልናል።

በመጀመሪያ ደረጃ በቶሎ እመጣለው ብሎ ቃል መግባቱ ህዝቦችሁ ወደ እርሱ መውሰድ ካለበት ጊዜ አንዳች ቅጽበት የሚያህል መዘግየት (tarry) ወይም መዘናጋት (linger) አይኖርም። ወሰኙ ጊዜ ስለተዘጋጀ ሁሉንም ነገር አዲስ ለማድረግ በአባቱ ክብር ሁሉ ይመለሳል።

ይህ የጊዜ ቀጠሮ በእግዚአብሄር የፈቃዱ ብርሃን ልናየው የሚገባ ነው። እግዚአብሄር በሉዓላዊነቱ የክርስቶስንም መምጣት ጨምሮ ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ወስኗል ። ከዚህም ጋር በተቀናጀ ሁኔታ በታቀደላቸው ጊዜ ሁሉም ነገር ወደተወሰነላቸው ማብቂያ እንዲመጡ ወስኖላቸዋል። በዚህ ጊዜ የታሪክ ውስጥ እግዚአብሄር በምርጦቹ ላይ ያለውን አላማ ይፈጽማል ሁሉም ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ (2ጴጥ 3፡9)። ከሃጥያተኞች እና ከማያምኑ ጋር ያለውን አላማ በዚያን ጊዜ ይፈጽማል። በዚያን ጊዜ የተመረጡቱ ሁሉ ሲድኑ በእርሱ ላይ በማያሙቱ ላይ ደግሞ እንደየስራቸው እና እንደአመጻቸው የእግዚአብሄርን የቁጣ ፍርድ ያጭዳሉ። (ዘፍ 15:16 ፣ መዝ 75:8  ራዕ 14:10 ፥ 15–20)።

በዚያን ጊዜ ክርስቶስ ይመጣል። ከጊዜው የተወሰነ ጊዜ (እጅግ በጣም የተወሰነ የምንለውን ጊዜ እንኳን) ቀድሞ አይመጣም። እንዲሁም ደግሞ ከተቀጠረው ጊዜ የተወሰነ ዘግይቶም አይመጣም። በነገር ሁሉ የሰማይ አባቱን (የእግዚአብሄርን) ፈቃድ የተከተለ ነው።

ከዚህ አንጻርም ክርስቶስ በቶሎ ይመጣል። እርሱ በታሪክ መጨረሻ  ይመጣል። ስለዚህም የአለም ታሪክ በተለይም ደግሞ ከእግዚአብሄር ዘላለማዊ አመታቶች ጋር ሲነጻጸር ረጅም የሚሆን አይደለም። እግዚአብሄራዊ ያልሆኑቱ ቢልየን አመታት እንዳለፉ እና እንደሚመጡ ይናገራሉ። ነገር ግን ለዚህ አለም ጥቂት ሺ አመታት ብቻ እንዳለፉት እናውቃለን።

በመጨረሻም ክርስቶስ በቅርቡ ይመጣል ምክንያቱም ክፉዎችን ክፉ እቅዳቸውን ለመፈጸም ፈጥኖ ይመጣል። በታሪክ ሁሉ ውስጥ ሁልጊዜ ስራቸው በሚመጣው የእግዚአብሄር ፍርድ ጣልቃ እየተገባበት እና እየተሸነፈ ነው። ይህ ደግሞ በፍጻሜው እውነት ይሆናል። የእርሱ መምጣት ለእኛ ቶሎ አይሁን!

### አስደናቂው የክርስቶስ መምጣት

የክርስቶስ መምጣት በዓለም ፍጻሜ አስደናቂ እና ተአምር መሆኑን ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም-ይህ አለም የሚያየው በመጨረሻ ነው። በአይኖቻችን ድንቅ የሆነና እና ከማስተዋል በላይ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሄር ስራ

ነው። እንደ እውነታው በዘመኑ መጨረሻ ዘመን የሚሆነው ነገር ሁሉ በጠቅላላ የእግዚአብሄር ድንቅ ስራ ፥ ተአምራቱ ነው።

በክርስቶስ መምጫ ጊዜ የሚሆኑት ምልክቶች ፣ የሙታን መነሳት ፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር መገናኘታቸው ፣ አሮጌው ምድር እና ሰማይ በእሳት መጥፋታቸው ፣ የመጨረሻው ፍርድ እና የአማኞች መክበር በጠቅላላ ተፈጥሮአዊ እና ምድራዊ በሆነ ምልከታ ቢብራራ የማይገልጸው ነገር ነው። ነገሮቹ በጠቅላላው የዚህ አለም ያልሆኑ የመንፈሳዊው አለም ስለሆኑ የምንቀበላቸው በእምነት ብቻ ነው።

ይህ የክርስቶስ መምጣት እውነታ መሆኑን የሚገልጹ የተለያዩ  የመጽሃፍ ቅዱስ አሉ። አንደኛ ነገር፣ የራዕ 1፡7 “አይን ሁሉ የወጉትም ያዩታል” በማለት ይመሰክርልናል (ተጨ ማቴ 24፡27 ፣30)። ይህ ብቻ ሳይሆን አጠቃላዩ ትንሳኤ እንደሚፈጸም የሚጠቁም ነው። ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣል፣ ነገር ግን የክርስቶስ መምጣት የእግዚአብሄር ተአምራዊ መሆኑን ያሳያል።

ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ አይኖች ሁሉ እንደት እንደሚያዩት ለመናገር ይከብዳል። ነገር ግን ያለምንም መጠራጠር የእግዚአብሄር ቃል እውነት እንደሚናገር እናምናለን። በእርግጥ አይን ሁሉ ሊያየው ይገባል፣እርሱ እንደ እግዚአብሄር መገለጥ ይመጣልና፣ ሁለቱም ህያውም ሆነ ሙታን ፍጥረት ሁሉ ይፈረድበታል ከእርሱ ጋር እንዳላቸው ግንኙነት ድነት ወይም ጥፋት ይፈረድባቸዋል።

የክርስቶስ መምጣት የታላቁ የእግዚአብሄር ተዓምራት እና ድንቅ ስራ እንደሆነ የሚመሰክርልን ሌላኛው ይመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል 2ተሰ 2፡8 ነው። ይህ ክፍል የሃጥያት ሰው “አመጸኛው” በሚገለጠው በክርስቶስ ብርሃን ምክንያት እንደሚጠፋ ይነግረናል። ይህንን በእኛ አቅም መረዳት ቢከብድም መምጣቱ ተፈጥሮአዊ የሆነ ሁነት አይደለም።

የክርስቶስ መምጣት የእኛ ተስፋ ነው። ምክንያቱም በፍርድ ቀን ስለስራችን በዙፋኑ ፊት መልስ ልመስጠት በምንቆምበት ጊዜ ከጎናችን የሚቆመው እርሱ ብቻ ነውና። እርሱ የእኛ ፈራጃችን ይሆንልናል። የፍርዱ ንግግር እንኳን በእርሱ ላይ ያለንን ድንቅ ተስፋ አያጠፋውም።ድነታችን በፍርዱ ውስጥ እና በፍርዱ ላይ መሆኑ የማዳኑ ስራ አካል ነው።

ስለዚህም መምጣቱን በተስፋ ነቅተን እንጠባበቃለን። እንደ አማኞች ህይወታችን በጠቅላላ ከዚህ እይታ አንጻር የሚመዘን ነው። ህይወታችን ግቡ እና አላማው የሚመሰረተው በክርስቶስ መገለጥ ላይ ነው። ከዚህ ጉዳይ በበለጠ በህይወታችን ላይ ሚዛን የሚደፋ ነገር ለእኛ ለአማኞች የለንም።

ይህ ሁሉ ሲደመሩ የሚያመላከትው የክርስቶስ ተመልሶ መምጣት አስደናቂው እና ተዓምራዊው የድነት አንዱ ክፍል ነው። ከጥረት ታሪክ አንስቶ እግዚአብሄር እራሱን ከሰው ልጆች የአስተሳሰብ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ብቸኛው አዳኝ እንደሆነ እየገለጠ ነው። እግዚአብሄር እኛን ተዓምራዊ ሆኖ በክርስቶስ በተገለጠው ጸጋው አድኖናል። የክርስቶስ ተመልሶ መምጣት እንዲሁ የመጨረሻው እና ታላቁ የጸጋው እና የምህረቱ መገለጫ ይሆናል።

## የሺህ ዘመን

ስለ ክርስቶስ መምጣት የቅዱሳን መጽሃፍት ምስክርነት “መቼ እና እንዴት ይመጣል?” የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። ይህን ጥያቄ ለመመለስ በምንነሳበት ጊዜ በራዕይ 20 ላይ የተገለጸውን የሺውን ዘመን የምናገኘው። የሺውን ዘመን ተከትሎ የተለያዩ ምልከታዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ቅድመ ሺው አመት ፣ ድህረ ሺው አመት እና አሚሌኒያሊዝም ማንሳት ይቻላል። ሁሉም ምልከታዎች መሰረት የሚያደርጉት ክርስቶስ የሚመጣበትን ጊዜ እና ሁኔታ ላይ መሰረት ባደረገ መልኩ ነው።

በመጽሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከባዱ እና ምሳሌያዊ በሆነ አገላለጽ በተጻፈው የራዕይ አንድ ምዕራፍ ላይ ብቻ የምናገኘው ይህ የሺው ዘመን ሃሳብ በክርቲያኖች መካከል የክርክር እና ያለመጋባብት ምክንያት መሆኑ የሚያሳዝን ነገር ነው። ቢሆንም የሺው ዘመን ልዩ ልዩ ምልከታዎች ምንም የማይጠቅሙ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ለመረዳታችን የራሳቸው የሆነ ፋይዳ አላቸው። የክርስቶስ የመምጣቱ ጊዜ እና ሁኔታ ማወቃችን ፋይዳ ያለው ጉዳይ ነው።

የሺው ዘመን የተለያዩ አመለካከቶች ስለክርስቶስ መንግስት ምንነት ጥያቄ ያስነሳል - ምድራዊ ወይስ ሰማያዊ ፣ የአሁን ወይስ የወደፊት ፣ አይሁዳዊት ወይስ አማናዊት የሚሉትን የተለያዩ ጥያቄዎች እንዲነሱ ያደርጋል። እነዚህ ጥያቄዎች ክብደት ያላቸው ናቸው። የተጠራነው መንግስቱን እንድንፈልግ እና እንዲመጣ እንድንጸልይ ነው ፣ ጥሪያችን እንድንፈጽም የምንፈልገውን ማወቅ አለብን።

ከዚህም የተነሳ የሺው ዘመን ጉዳይን መረዳት ምንም ለክርስቲያን ምንም የማይጠቅም አድርገን ከማሰብ ይልቅ ምልከታዎችን በመጽሃፍ ቅዱስ እውነታ በመፈተሽ እንደ ክርስቲያን ምኑን ማመን እንዳለብን ለማመላከት እንወዳለን። ይህንን ሃሳብ ለማብራራት የወደድነው በወንድሞች (በክርስቲያኖች) መካከል ያሉትን ልዩነቶች ለማስፋት አልያም ደግሞ በጉዳዩ ላይ የተለያየ ምልከታ ያላቸውን አማኞች ለማግለል ያሰበ ሳይሆን ከዚህ በተቃራኒ እውነታውን መጽሃፍ ቅዱሳችን ምን እና ለምን እንደሚያስተምረው በመጽሃፍ ቅዱስ ብርሃን ፈትሾ ለማቅረብ ነው።

ሚሊንየም የሚለው ቃል “አንድ ሺህ አመት” ማለት ሲሆን በራዕይ 20 ላይ ስድስት ጊዜ የተሰጠውን ሺህ አመትያመላክታል። በዚህ የሺው ዘመን ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል ሰይጣን የታሰርበት እና በመጀመሪያው ትንሳኤ ተካፋይ የሆኑ አማኞች ከክርስቶስ ጋር የሚኖሩበት እና የሚገዙበት ዘመን ነው። ይህ የሺው ዘመን ማብቂያ ላይ ሰይታን “ለጥቂት ጊዜ” መፈታቱን ተከትሎ የምድርን ህዝብ በማሳት በአማኞች ከተማ ላይ ጦርነት ለማድረግ ያዘምታቸዋል። በዚህም እግዚአብሄር ጣልቃ በመግባት የመጨረሸው የፍርድ ጊዜ ይከተላል።

አንዳንዶች ሺውን ዘመንም ጨምሮ ይህ በወደፊት እንደሚሆን ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ እኛ አሁን ያለንበት ዘመን እራሱ የሺ አመታት አካላት ነን እና ጀምሯል ብለው ያምናሉ (amillennialism)። አሁን ያለንበት ጊዜ የሺው አመት ውስጥ ቢሆንም ፍጻሜው ግን ወደፊት እና የሚታየውም ልንገልጽው የማንችለው ሰላም ፣ በረከት እና ብልጽኛ በቤተክርስቲያን ላይ ሲሆን ነው ብለው የሚያስተምሩ አሉ (ድህር ሺው ዘመን)።

ቅድመ ሺስቶች ቀጣዩ የክርስቶስ መምጣት ከፊተኛው ሺ ዘመን ቀድሞ እንደሆነ እና ወደፊት ከአንድ በላይ የሆነ የክርስቶስ መምጣት እንዳለ ያስተምራሉ። ድህረ ሺስቶች (Postmillennialists) ደግሞ የክርስቶስ መምጣት ከሺው ዘመን በኋል እንደሆነ እና ከሺው ዘመን በኋላ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚሆን ያስተምራሉ። በቅድመ እና በድህረ ሺው አመታት መካከል ያለው ሚሊየም የሚለውን በቀጥታ እንደ አንድ ሺ አመታት አለመውሰዳቸው ነው። አሚለኒአሊስቶች (amillennialists) ከዚህ በተቀራኒው ሺውን አመት የሚመለከቱት ከክርስቶስ ሞት አንስቶ ለወንጌላት ዘመን በሙሉ የቆመ ተምሳሌት እንደሆነ ነው።

## የዲስፔንሸናሊዝም እና የቅድመ ሺ አመት ንጽጽር

በክክል ለመናገር የክርስቶስ በአካል እና በሚታይ መልኩ መምጣት ከክርስቶስ አገዛዝ ከሺው ዘመን መንግስት ቀድሞ እንደሚመጣ ባላቸው ትምህርት የቅድመ ሺ አመት እና የዲስፔንሽናሊዝም ለአንድ አስተምህሮ የቆሙ ናቸው። እይታዎቹ መካከል በርካታ ተመሳሳይነት አለ። ሁለቱም ቃል በቃል የሺ አመት መንግስት መሆኑን ይናገራል። ሁለቱም ይህ ሺው አመት እና መንግስቱ የወደፊት እንደሆነ ያስተምራሉ። ሁለቱም የክርስቶስ መንግስት ማዕከላዊነቱን በኢየሩሳሌም የሚያደርግ ምድራዊ መንግስት እንደሆነ እና ኢየሱስም በአካል እና በሚታይ ሁኔታ እንደሚያስተዳድር ያስተምራሉ። ሁለቱም እግዚአብሄር ለአብርሃም እና ለአይሁዳዊያን ስለ መሬት የገባላቸው የተስፋ ቃል ለህዝቡ የወደፊት ፣ ቀጥተኛ እና ምድራዊ ምድራዊ መፈጸም እንዳላቸው ያስተምራሉ። ሁለቱም በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ "እስራኤል" ሁልጊዜም የሚወክለው የአብርሃም አካላዊ የዘር ሃረግ የሆኑትን አይሁዳዊያንን ብቻ እንደሆነ ያስተምራሉ። እንዲሁም ሁለቱም ከአንድ በላይ የሆነ ትንሳኤ እና ፍርድ እንዳለ ያስተምራሉ።

ቢሆንም በቅድመ ሺው አመት እና በዲስፔንሽናሊዝም መካከል ወሳኝ የሆነ ልዩነቶች አሉ። ዲስፔንሽናሊዝም ከሺው አመት ቀድሞ የክርስቶስ መምጣት ሁለት ጊዜ በመነጠቅ (ከሺው አመት ቀድሞ በነገሮች ወይም በታሪክ ፍጻሜ) እና በመገለጥ (ክርስቶስ ለቅዱሳኑ እና ከቅዱሳኑ ጋር መምጣት) እንደሚመጣ ያስተምራል። ከዚህም በተጨማሪ ዲስፔንሽናሊዝም ከታላቁ መከራ በፊት ሚስጢራዊ እና በየትኛውም ሰዓት የሆነ መነጠቅ እንደሚሆን ያስተምራል። ይህም ማለት ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር እንጂ በታላቁ መከራ ውስጥ አታልፍም ማለት ነው።

ዲስፔንሽናሊዝም የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን በታሪክ ውስጥ "አቅጣጫ (parenthesis)" እንደሆነች እና የእግዚአብሄርን መንግስት እና ህዝብ የሚመሰርቱት አይሁዳዊያን ብሄር ብቻ እንደሆኑ ያስተምራሉ። በተመሳሳይ የዲስፔንሽናሊስት ጠበብቶች አመለካከት የክርስቶስ የሺው ዘመን መንግስት የሚያቅፈው አይሁዳዊያን ብቻ ናቸው ይላሉ። ይህም ማለት የመንግስቱ ህዝቦች የሚሆኑት አይሁዳዊያን ብቻ ናቸው ማለት ነው። ከእዚህም ሌላ ዲስፔንሽናሊዝም የክርስቶስ መምጣት በሆኑት በንጥቀት እና በመገለጡ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከምድር እንደሚወሰድ ያስተምራል።

ሁሉንም ግርታዎች ለመጨመቅ በስኮፊልድ መጽሃፍ ቅዱስ ማጥኛ [1] ላይ የምናገኘው የድሮው ዲስፔንሽናሊዝም በብሉይ ኪዳን ድነት በክርስቶስ ደም እና መስዋዕትነት በእምነት በኩል ብቻ መሆኑን በመካድ ለአይሁዳዊያን እና ለአህዛቦች ሁለት የተለያየ የድነት መንገድ እንዳለ ያስተምራል። በተቃራኒው

የታሪካዊው ቅድመ ሺው ዘመን አስተምህሮ በትክክለኛ ሁኔታ መነጠቅ እና መገለጥ ሁለት የተለያዩ ሁነቶች ሳይሆኑ አንድ መሆናቸውን ያስተምራል። ታሪካዊው ቅድመ ሺው አመት ሚስጢራዊ እና በማንኛውም ሰዓት የሚሆን ንጥቀት እንደሌለ እና ቤተክርስቲያን በመጨረሻው ቀን ባለው ታላቁ መከራ ውስጥ እንደምታልፍ ይሞግታል። ታሪካዊው ቅድመ ሺው አመት ከዲስፔንሽናሊዝም በመቃረን ቤተክርስቲያ በክርስቶስን መንግስት ውስጥ ስፍራ እና ድርሻ እንዳላት እና አይሁዳዊያንን የሚመለከትበት የእግዚአብሄር የበፊቱ እና የወደፊቱ በታሪክ ውስጥ "አቅታጫ" እንዳልሆነች ያስተምራል። በመጨረሻም ታሪካዊው ቅድመ ሺ አመት በስኮፊልድ መጽሃፍ ቅዱስ ማጥኛ ላይ ያለውን በተለያየ ጊዜ (ዲስፔንሽንስ) የተለያየ የድነት መንገድ እንዳለ የሚያስተምረውን የስህተት ትምህርት እና መጽሃፍ ቅዱሳዊ ያልሆነው እና እንግዳ የሆነው ለተወሰነ ጊዜ በሁሉም ቦታ የሚገኘው የመንፈስ ቅዱስ ከምድር ላይ ይወሰዳል የሚለውን አስተምህሮ አያውቀውም።

ታሪካዊው ቅድመ ሺው አስተምህሮ ከዲስፔንሽናሊዝም በርካታ ስህተቶች የጸዳ እና እሩቅ እንደማይሄድ እናምናለን። ለማብራራት ተስፋ እንደምናደርገው የቀድሞውም ሆነ የአሁኑ ቅድመ ሺው መጽሃፍ ቅዱሳዊ አይደሉም።

## የቅድመ ሺህ ዘመን ስህተቶች

ቅድመ ሺው ዘመን የክርስቶስ መምጣት ግላዊ ፣ በሚታይ ሁኔታ ከአለም ፍጻሜ በፊት እንደሚሆን ስለሚያስተምር አንዳንዴ "ቺልያዚም" ተብሎ ይጠራል። ክህደቱ እና ክፋቱ በመጨመር በውጤቱም የመጨረሻ የክርስቶስ ተቃዋሚ ይገለጣል ይላል።በዚያን ጊዜ በማቴ 24፡21 ላይ "ታላቁ መከራ" ተብሎ የተገለጸው ከባድ የስደት ጊዜ ይጀምራል። ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ እና የስደት ጊዜ የሚያበቃው ቅዱሳንን በሚያስነሳው ፣ በህይወት የሚገኙትን ሰውነት በሚቀይረው ፣ በሚፈርድላቸው እና በኢየሩሳሌም ለአንድ ሺ አመት የሚቆይን መንግስት በሚመሰርተው በክርስቶስ መምጣት ነው።

ቅድመ ሺው ዘመን እንደሚለው የዚህ መንግስ ወደ ገዛ መሬታቸው በሚመለሱ የጅምላ (የብዙሃን) አይሁዳዊያን መለወጥ ውጤት ነው ይለናል። ከአህዛብ ክርስቲያኖች ጋር በአንድነት በኢየሩሳሌም ከተማ ማዕከላዊነት የክርስቶስን መንግስ የሚመሰርቱ ሲሆን አይሁዳዊያን ቅድሚያ የሚኖራቸው ይሆናል። ይህ መንግስት ለአንድ ሺ አመት የሚቆይ እና በምድር ላይ በጽድቅ ፣ በሰላም እና በብልጽግና የሚታወቅ ነው።

በዚህ የክርስቶስ በምድር ላይ የሚገዛበት ግዜ ማብቂያ ላይ የተቀሩት ሙታን የሚነሱበት ፣ የመጨረሻው ፍርድ እና የአዲስ ሰማይ እና ምድር መፈጠር የሚከተል ይሆናል።

አንዳንድ የዚህ ቅድመ ሺው ዘመን አመለካከቶች በጣም እንግዳዎች ናቸው። ለምሳሌ ያህል የሺው ዘመን መንግስት ነዋሪዎች ከሞት ተነስተው የከበሩት እና በምድር ላይ በህይወት የሚገኙት ቅልቅል ሲሆን ይህም ከ 1ቆሮ 15፡50 ጋር የሚቃረን ነው። ከዚህም ሌላ መንግስቱ የሚሆነው እርግባም በተወገደለት ምድር የሚሆን ሲሆን ነገር ግን ፈጽሞ ከሃጥያት ፣ ከበሽታ እና ከሞት ባልተገላገለ ምድር ላይ ነው። በምድር ላይ በትንሳኤን ያገኙ ቅዱሳን ለሃጥያት እና ለሞት ከተጋለጡ ሰዎች ጋር ለረጅም ጊዜ ይኖራሉ።

ነገር ግ ን በአስተምህሮቱ ላይ ከዚህ የሚበልጥ መቃወሚያ አለ።

የመጀመሪያው መጽሃፍ ቅዱስ የክርስቶስ መምጣት ከአለም ፍጻሜ አንድ ሺ አመት ይቀድማል የሚለውን አስተምህሮ ይቃወማል።ከዚህ ይልቅ የክርስቶስ መምጣት (1 ቆሮ 15:23–24) ፣ የአዲስ ሰማይ እና ምድር መፈጠር (2 ጴጥ 3:9–10) ፣ የሙታን ሁሉ ትንሳኤ (ራዕ 20:12–13) እና የመጨረሻው ፍርድ (ማቴ 24:37–41; ሉቃ 17:28–37; ያዕ 6–7, 14–15) ከአለም ፍጻሜ ጋር በትይዩ የሚሆን ጉዳይ እንደሆነ ያስተምረናል።

ሁለተኛው መጽሃፍ ቅዱስ ከአንድ በላይ የሆነን ትንሳኤ እና ፍርድ (ዩሐ 5:25–29) አልያም የአለም ፍጻሜን በአንድ ሺ አመት የሚቀድም ትንሳኤ እና ፍርድ እንደሚሆን አያስተምርም (ዩሐ 6:39–40, 44–45; ዩሐ 11:24; 1ቆሮ 15:51–52 1ቆሮ 15:51–52 ላይ “መጨረሻ” የሚለውን አጽንዖት ይመልከቱ)።

ሰስተኛው መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ከምድራዊ መንግስትነቱ በተቃረነ መልኩ መንግስቱ ሰማያዊ እንደሆነ ይናገራል (ዩሐ 18:36; ዕብ 12:22–23)።

አራተኛ መጽሃፍ ቅዱስ የክርስቶስ መንግስት የአንድ ሺ አመት ዕድሜ ያለው ሳይሆን የዘላለም እንደሆነ ያስተምራል (ዳን 4:34; ዳን 7:27; 2 ጴጥ 1:11)።

አምስተኛ መጽሃፍ ቅዱስ አይሁዳዊያን የአብርሃም አካላዊ ዘሮች ብቻ እንደሆኑ አያስተምርም። ከዚህ ይልቅ አማኞች ሁሉ አይሁዳዊ ሆነ አህዛብ እውነተኛ አይሁዳዊያን እውነተኛ የእግዚአብሄር እስራኤል እንደሆነ ያስተምራል (ሮሜ 2:28–29; ገላ 3:29; ፊሊ 3:3)። እስራኤል ቤተክርስቲያን ፤ ቤተክርስቲያንም እስራኤል ነች። እንዲሁም መንግስቱ ቤተክርስቲያን ፣ ቤተክርስቲያንም መንግስ ነች።

በዚህም ምክኛት በተለይ ቅድመ ሺው ዘመን አስተምህሮን እንቃወማለን።

## የዲስፔንሽናሊዝም ስህተቶች

ከቅድመ ሺው ዘመን በላይ ከባድ ስህተቶችን የያዘው ዲስፔንሽናሊዝም የድስፔንሽናሊዝም እና ብራዘርኒስም አምንጪ በሆነው ጆን ኔልሰን ዳርብይ (1800-1882) ዳእቢይዝም ተብሎ ይታወቅ ነበር። ችግሩ ስለወደፊቱ እና ስለሚሊኘም የተወሰኑ አስተምህሮቱ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በጠቅላላ erroneous ስነመለኮታዊ ዘዴው ላይ ነው።

ዲስፔንሽናሊዝም የሚለው ስያሜውን ያገኘው ታሪክን በተለያየ የጊዜ ክፍፍል “dispensations” በሚከፋፍለው ንድፈ ሃሳቦቹ ላይ በመነሳት ነው። በእያንዳንዱ የጊዜ ክፍፍል “dispensations” ውስጥ እግዚአብሄር በሰው መፈጸም አለመቻል የሚተናቀቅ የተለያየ የኪዳን ግንኙነት አለው የሚል ነው። በዳርብይ ክላሲክ ዲስፔንሽናሊስም መሰረት አሁን ያለውነ “በቤተክርስቲያን ዘመን” ወይም በጸጋ የጊዜ ክፍለት “dispensation of grace” ሲሆን ከዚህ በኋላ የሚመጣው አንድ ዘመን ብቻ እርሱም የመንግስቱ የጊዜ ጅፍለት “dispensation of the kingdom” ብቻ ነው።

የዲስፔንሽናሊዝም የተወሰኑ ስህት የሆኑ አስተምህሮዎችን ስለ ሚስጢራዊ ፣ ቅድመ ሺው አመት ፣ ቅድመ ታላቁ መከራ መነጠቅ እና ብዙ ጊዜ ስለሚሆነው የክርስቶስ መምጣት ባነሳን ጊዜ አውርተናቸዋል።

በመቀጠል የምናነሳው የዲስፔንሽናሊዝም ሌላኛው አስተምህሮ ከአንድ በላይ የሆነ ትንሳኤ እና ፍርድ እንዳለ ማመኑ እና መጽሃፍ ቅዱስን በተለይም ራዕይ 20 በቀጥታ መተርጎሙ ነው።

የዲስፔንሽናሊስት ጥቂቶቹ በጣም ግልጽ ስህተቶቹ (more flagrant errors) መጽሃፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ ከመጠቀም ጋር ይያያዛል።

የመጀመሪያ ስህተታዊው የመጽሃፍ ቅዱስ አተረጓገም መንገድ (ዘዴ) ነው። ብሉይ ኪዳን በጠቅላላ እና የተወሰነው አዲስ ኪዳን object of curiosity ካልሆነ በስተቀር ተግባራዊነታቸው ለአይሁዳዊያን እንጂ ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ምንም ተግባራዊነት የላቸውም የሚለው የዚህ መንገድ (ዘዴ) ውጤት ነው። ለምሳሌ የስኮፊልድ መጽሃፍ ቅዱስ ማጥኛ ማስታወሻ የተራራው ስብከት የአይሁዳዊያን እንጂ የክርስቲያኖች አይደለም ብሎ ያስተምራል። መጽሃፍ ቅዱስ ከዚህ በተቃራኒ ሁሉም ቅዱሳት መጽሃፍት ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የሚጠቅሙ (እና ተግባራዊያን) እንደሆኑ ያስተምራል (ዩሐ 10:35; 2 ጢሞ 3:16–17)።

ዲስፔንሽናሊዝም ይንን ስለሚክደው በተቃራኒው ቢናገር እንኳን የእውነትን ቃል በስህተት በመከፋፈል ይከሰሳል።

ሁለተኛው ዲስፔንሽናሊዝም ጽንፈኛ የሆነ ቀጥተኛነት (strict literalism) ይከተላሉ። አንዱ እንዳለው ክርስቶስን እንደ መንፈሳዊ ንጉስ እና ለእነርሱ እንደሞተ ፈሪሳዊያን መመልከት ያልቻሉበት ምክኛት የፈሪሳዊያን ቀጥተኝነት ነው። ይህ ጽንፈኛ የሆነ ቀጥተኝነት (ብዙ ጊዜ ባይተገበርም) እና ዲስፔንሽናሊስቶች "ማመናፈስ" ከሚሉት ተቃራኒ የሆነ ከመጽሃፍ ቅዱስ ተጻራሪ ነው (1 ቆሮ 2:12–15)። መጽሃፍ ቅዱስ እራሱ በብዙ ምንባባቱ የብሉይ ኪዳን ነገሮችን "የሚያመናፍስ (spiritualizes)" መሆኑን በ 1 ጴጥ 2:5–9 እና በእብራዊያን ሙሉ መጽሃፍ የምናገኘው ነገር ነው። በራዕ 2፡17 ላይ ነጩ ድንጋይ እንደሚለው አይነት በርካታ በቀጥታ ሊወሰዱ የማይችሉ ነገሮች ላሉ መጽሃፍ ቅዱስ በጥንቃቄ እና በትህትና (soberly) መተርጎም እንዳለበት እንመክራለን።

ሰማያዊውን እና መንፈሳዊውን የክርስቶስን መንግስት ወደ መካድ የመራው የዲስፔንሽናሊዝም የማመናፈስ መቃረን ነው። የነዚህ ሁሉ ስህተቶች ስር የዲስፔንሽናሊዝም erroneous የሆነ መጽሃፍ ቅዱሳዊ እይታ ነው።

**የዲስፔንሽናሊዝም ተጨማሪ ስህተቶች**

ስለ ዲስፔንሺናሊዝም ዋና ዋና ስህተቶች የምናምነውን አስፍረናል። ሌሎች ስህተቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ዲስፔንሽናሊዝም እስራኤልን እና ቤተክርስቲያንን ይነጣጥላቸዋል። ከዲስፔንሽናሊዝም ወሳኞች መካከል እስራኤል እስራኤል ናት ፤ ቤተክርስቲያንም ቤተክርስቲያን ናት ሁለቱ በፍጹም ሊያወዛግቡን አይገባም የሚለው ነው። ይህ መጽሃፍ ቅዱስ የብሉይ ኪዳኑ እስራኤል እንደ ህዝብም ሆነ በመንፈሳዊው ቤተክርስቲያን መሆኗን ያስተምራል (ሮሜ 2:28–29). በሐዋ 7:38 ላይ እስራኤል "በምድረ በዳ በማህበር (ቤተክርስቲያን)" ተብላ ተጠርታለጭ በዕብ 12:22–24 ደግሞ ኢየሩሳሌም እና ጺዮን እንደ ቤተክርስቲያን ተገልጸዋል (በተጨ ገላ. 3:29 እና ፊሊ 3:3 ይመልከቱ)። በራዕ 21:9–10 ሙሽራዋ ፣ የበጉ ሚስት ቅድስቲቷ ኢየሩሳሌም ተብላ ተገልጻልች።

የዲስፔንሽናሊዝሙ ይህ ልዩነት በአይሁዳዊያን እና በእነርሱ ምትክ የተሰራውን ስራ ፤ በአይሁዳዊያን እና በቤየክርስቲያን ምትክ የተሰራውን የእርሱን ስራ መካከል ነው። ዲስፔንሽናሊዝም የእስራኤላዊያን ንጉስ የቤተክርስቲያን ደግሞ ራስ እንደሆነ ያስተምራል። የስኮፊልድ የመጽሃፍ ቅዱስ ማጥኛ ማስታወሻ የብሉይ

ኪዳን ህዝቦች በክርስቶስ የቤዝዎት ስራ በማመን ሳይሆን በሌላ መንገድ እንደዳኑ እና እግዚአብሄር ከአንድ በላይ የሆነ የድነት እቅድ እንዳለው እንኳን ያስተምራል። መጽሃፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሁለቱም ኪዳናት ተመሳሳይ አዳኝ እንደሆነ በግልጽ የሚያስተምረውን አስተምህሮ ይጻረራል

ዲስፔንሽናሊዝም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳንን ከክርስቶስ አካል እና ከሙሽሻነት ውጪ ያደርጋቸዋል። በእርግጥ ይህ የመጣው እስራኤልን እና ቤተክርስቲያንን ፤ ክርስቶስ ለእስራኤላዊያን ንጉስ ለቤተክርስቲያን ደግሞ ራስ በሚለው መከፋፈል ነው። እንዲሁም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን “በእምነት ቤት” የሚያጠቃልለውን እና በክርስቶስ ሙሽራነት እና አካሉ ውስጥ መቆጠራቸውን (መካተታቸውን) ይቃረናል (ኤፌ 2:11–18, በተለይ አይሁድ እና አህዛብ በአንድ አካል ያስታርቅ የሚለውን ቁ. 16 ፣ ሙሽሪቷ እና የበጉ ሚስት ቅድስቲቷ ኢየሩሳሌም ተብሎ የተገለስተበት ራዕ 21:9–10)።

ዲስፔንሽናሊዝም መንፈስ ቅዱስ ከመነጠቁ እና ከመገለጡ ሰባት አመትን ቀደም ብሎ መንፈስ ቅዱስ ከምድር ላይ እንደሚወስድ ያስተምራል። በእነዚህ ጊዜያት ያለ ሉዓላዊ እና ምህረታዊ የመንፈስ ቅዱስ ስራ እስራኤላዊያን ወደ ድነት ይመጣሉ። ይህ መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እምነት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ የእግዚአብሄር ስጦታ መሆኑን እና ለድነት አስፈላጊ የሆኑቱ ዳግም ፍጥረት ወይም ልደት የመንንፈሱ ልዩ ስጦታ የመሆናቸውን አስተምህሮ ይጻረራል (ዩሐ 3:3–8 ፣ ኤፌ 2:8)።

ዲስፔንሽናሊዝም ስለ “ሚስጢራዊ” ቤተክርስቲያን ያስተምራል። ክላሲካል ዲስፔንሽናሊዝም በአዲስ ኪዳን የቤተክርስቲያን ታሪክ “parenthesis” እንደሆነች እና ቤተክርስቲያን እራሷ በብሉይ ኪዳን ምንም ያልተነገረላት ሚስጢራዊ እንደነበረች ያስተምራል። ይህ መጽሃፍ ቅዱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ትንቢት የተነገረ መሆኑን ብቻ ሳይሆን እውነተኛ እስራኤልን እንደ ቤተክርስቲያን ፤ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ እንደ እስራኤል የሚመለከትበትን አስተምህሮ ይጻረራል። በሐዋ 15:13-41 ላይ ያዕቆብ ስለ እስራኤል የተነገረውን የብሉይ ኪዳኑን ትንቢት ለአዲስ ኪዳኑ የአህዛብ ቤተክርስቲያን መመስረት ተጠቅሞበታል (ከሐዋ 7:38 አነጻጽር)። በተመሳሳይ ቤተክርስቲያ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ “parenthesis” አልተመላከተችም ነገር ግን በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሄር የስራው ግብ እና አላማ መሆኑናን እንመለከታለን። እርሷ “አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላት ሙላቱ ናት” (ኤፌ 1:22–23) ፣ በስራው ሁሉ ለእራሱ የሚያቀርባት “ባለ ክብሯ ቤተክርስቲያን” ነች (ኤፌ 5:25–27)። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ዲስፔንሽናሊዝም ሊወገድ ይገባዋል።

**ድህረ ሺህ ዘመን**

ድህረ ሺው ዘመን የሺው ዘመን የጀመረ ቢሆንም ዋናው ፍጻሜ ወደፊታዊ እና ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሰላም ፣ በረከት እና ብልጽግና በወንጌሉ እና በቤተክርስቲያን ላይ ሲመጣ የሚታይ ሲሆን ነው ብሎ እንደሚያስተምር ቀደም ብለን አብራርተነዋል። ሺውን ዘመንን የሚተረጉሙበት ራሳቸው መንገድ ያላቸው የተለያዩ አይነት ድህረ ሺው ዘመን አሉ።

ከሁሉም በፊት የብዙ አናጺያን (Puritans ) እና ዘመናዊ ጸሃፊያን እይታ የሆነው የቀድሞው ድህረ ሺው ዘመን ብዙ አይሁዳዊያንን እንደሁም አብዛኞቹን ወደመለወጥ የሚመራ ወደፊት ታላቅ የሆነን የእግዚአብሄርን ስራ ይጠባበቃል። በተመሳሳይ ምልከታ አንዳንዶች በሃዋሪያት ዘመን ወንጌሉ በድጋሚ ተብኮ እንደ ሃዋሪያቱ ዘመን ፍሬ የሚያፈራበትን እና በአስራስድስተኛ ክፍለ ዘመን እንደሆነው ታላቁ የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አይነት ከክርስቶስ መምጣት ቀድሞ በቤተክርስቲያን የፍጻሜው ጊዜ የሚሆንን ታላቅ ተሃድሶን ይጠባበቃሉ።

አንዳንድ ጊዜ የክርስቲያን ተሃድሶ ወይም የግዛት ስነመለኮት አካል የሆነ በአሁኑ ጊዜ ስር ነቀል ድህረ ሺው ዘመን እምነት ተከስቷል። ይህ ድህረ ሺው ዘመን ወደፊት ለቤተክርስቲያንን አስደሳች የወደፊት ጊዜን ብቻ ሳይሆ መላው ህብረተሰብ እና የሰው ህይወት በክርስቶስ አገዛዝ ውስጥ የሚሆንበት ጊዜ እንደሚመጣ እና ይህ “ክርስቲያናዊ” ማህበረሰብ ስለክርስቶስ መንግስት የተሰጠው ቅዱስ ተስፋ ፍጻሜ እንደሚሆን ያስተምርሉ።

ይህ የቅርብ ጊዜ ድህረ ሺው ዘመን የክርስቶስ መንግስት በዚህ ምድር በዋናነት የሚታወቅበት የወንጌሉ መሰበክ እና የቤተክርቲያን እድገት ብሎም በተለያዩ የህይወት አካባቢዎች ላይ የክርስቲያኖችን ድርጊት ይጠባበቃል።

ይህ አመለካከት ያላቸው አብዛኞቹ በተለያዩ ማህበረሰባዊ ቦታዎች ላይ ክርስቲያኖች እንዲሳተፉ እንደውም በታውን እንዲቆጣጠሩት እና እንደሚሉት እያንዳንዱ የህይወት ቦታዎች ላይ ክርስቶስን እንዲሾሙት በታዎችን ለክርስቶስ እንዲናጠቁ ይሞግታሉ። ይህን ምልከታ የሚይዙት አብዛኞቹ ፕሪተሪስት ናቸው (የግሪኩ preterite የሚለው ቃል ትርጉም “በፊት ፣ ያለፈ”)። እነዚህ ማቴ 24:1–35 አብዛኛው የራዕይ መጽሃፍ ፍጻሜውን ያገኘ ወይም ያለፉ ነው ብለው ያምናሉ። የተገለጹት ክንውኖች በ70 AD በሮማዊያን ወታደሮች የኢየሩሳሌም በጠፋበት ወቅት ነው። አብዝዛኞቹ ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ እና ስለ ታላቁ መከራ የሚናገሩት መጽሃፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች እንደተጠናቀቁ ይናገራሉ። ስለ ቤተ ክርስቲያን እና የህብረተሰቡ

የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያላቸው ብሩህ አመለካከት በመጨረሻው ጊዜ መከራ እና የክርስቶስ ተቃዋሚ ላይ ማንኛውንም እምነት ይከለክላል።

እነዚህ ሰዎች ሁል ጊዜም ህግ አጥባቂዎች (ቲዎኒስቶች) ናቸው (theonomy ማለት "የእግዚአብሄር ህግ")። የብሉይ ኪዳኑን የማህበረሰብ ህግ ጨምሮ የእግዚአብሄር ህግ በምድር ላይ ለሚሆነው የክርስቶስ መንግስት መሰረት እንደሆነ ያምናሉ። በዚህ መንግስት ውስጥ ዋናው ሃይል ወንጌል ሳይሆን ህግ ይሆናል፣ ምክንያቱም ሁሉም የማይለወጡ ሲሆን ሁሉም በእግዚአብሄር ህግ እና በህግ "መገዛት" ስር ይሆናሉ።

እንግዲህ በዚህ ዘመናዊው ልዩ ድህረ ሺው ዘመን (modern radical postmillennialis) በርካታ ስህተቶች ስላሉበት የአናጺያን እና የአዲሱ አመለካከት አካል በሆነው በቀድሞው ድህረ ሺው ዘመን አንስማማም። ይህንን አስተምህሮ ዲስፔንሽናሊዝም ከባድ ስህተት የመሆኑን ያህል ከባድ ነው።

## የድህረ ሺህ ዘመን ስህተቶች

አሮጌውን የድህረ-ሺህ አመታትን ከቅርብ ጊዜ የድህረ-ሺህ አመታት ጋር አነጻጸረነዋል ፣ ይህም የኋለኛው የክርስቲያን ተሃድሶ እንቅስቃሴ ዋና አካል ነው። ይህ አይነት ድህረ ሺው ዘመን ከአናጺያኑ (Puritans) የድሮው ድህረ ሺው ዘመን የተለየ እና በእጅጉ አደገኛ ነው።

የመጀመሪያው ይህ አይነቱ ድህረ ሺው ዘመን ወንጌል መስበክን ዋጋ ያሳጣዋል። በተከታዮቹ ዘንድ በኢኮኖሚው እና በፖለቲካው ውስጥ ያለው እርምጃ ቢያንስ ለመንግስቱ መምጣት የወንጌሉን ያህል አስፈላጊ ነው። ለእነርሱ መንግስቱ በወንጌሉ በኩል በሰዎች ድነት ውስጥ የሚኖረው ድል ክርስቲያኖች በመላ ማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው ገዢነት የሚበልጥ አይደለም።

ሁለተኛው ይህ ድህረ ሺው ዘመን ቤተክርስቲያንን ትርጉም የለሽ እና ቀላል ያደርጋታል። መንግስቱ ከቤተክርስቲያን የሚያልፍ እና በላይ እንደሆነ በማሰብ ቤተክርስቲያንን ከክርስቶስ በመቀጠል ለክርስቲያኖች የፍቅራቸው ዋና ጉዳይ መሆኗን አይመለከቱትም። ነገር ግን ይህ በመዝ 122:6 እና በኤፌ 1:17–23 ውድቅ ተደርጓል። መዝ 122:9 እና ኤፌ 1:17–23 የቤተክርስቲያን መጠበቅ እና መሰባሰብ የክርስቲያን የህይወታቸው ዋና አላማ እና ስራ እንደሆነ ቢያመላክትም በተቃራኒው ድህረ ሺው ዘመን በዚህ መልኩ

አይመለከተውም። ለብዙሃን ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች በፖለቲካው ፣ በኢኮኖሚው እና በሌሎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ላላቸው ተሳትፎ የስልጠና መድረክ ብቻ ነች።

ቤተክርስቲያንን የቀልድ (trivializing) ማድረጉ በቤተክርስትቲያን አስተዳደር ፣ አምልኮ እና አስተምህሮቶች ላይ ፍላጎትን በማሳጣት አስተምህሯቸው መጽሃፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ ወገኖች ጋር የመቀላቀል ኢኩሚኒቻሊዝም ዝንባለ እንዲኖር ያደርጋል። በስተመጨረሻም በእነርሱ ምልከታ ዋናው ነገር ቤተክርስቲያን ሳይሆን መንግስቱ ነው።

ስለዚህ ይህን አይነቱን ድህረ ሺው ዘመንን የሚከተሉ ቤተክርስቲያን በታማኝነት ወንጌሉን በመስበክ እና sought the salvation ብታደርግም ቤተክርስቲያን ከመጀመሪያውኑ በታሪክ ውስጥ በሙሉ ማህበረሰብ ውስጥ የገዢነቱን ስፍራ ለመውሰድ ወድቃለች (አልተሳካላትም) በማለት ይከሷታል። በዚህም ቤተክርስቲያን ውጥንቅጥ በሆነ መልኩ አልተሳካላትም ይላሉ።

ሶስተኛው ይህ አይነቱ ድህረ ሺው ዘመን ታማኝ የክርስቶስ ምስክሮችን ያዳክማል። የፖለቲካ እና በተለያዩ ማህበረሰባዊ አካባቢዎች ላይ መሳተፍን ትኩረት ስለሚሰጥ እንደ ግለሰብ አንድን ተራ ክርስቲያን (በአሉታዊ መረዳት እንዳይፈጥር) እግዚአብሄር በሰጠው ቦታ ላይ የሚኖረውን የታማኝነት እና የአማኝነት የህይወት ምስክር ዋጋ ያሳጣዋል። ዋና ነገሩ ለሌሎች መዳን እግዚአብሄር እንዲጠቀምብን መልካም ምስክር መሆኑ ሳይሆን ማህበረሰብን መውረስ ላይ ነው

አራተኛ የዚህ ድህረ ሺ ዘመን አቀንቃኞች ህግ ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ አዲሱን አይነት ሌጋሊዝም (legalism) ይወክላሉ። መንግስቱ ሁሉንም ከህጉ ስር ተገዢ እንዲሆኑ በማድረግ መንግስቱ እንዲታወቅ የሚተባበቁ ህጉ ወንጌሉ ማድረግ የከበደውን ነገር ያደርጋል በልው ያስባሉ። በሮሜ 8:3: “ከስጋ የተነሳ ስለ ደከመ ለህግ ያልተቻለውን እግዚአብሄር የገዛ ልጁን በጻጥያተኛ ምሳሌ በሃጥያትም ምክ ኛት ልኮ አድርጓል እና እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ስጋ ፈቃድ በማንመላለስ እኛ የህግ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ ሃጥያትን በስጋ ኮነነ።” ተብሎ ስለ ህግ ደካማነት የተጻፈውን ይዘነጋሉ።

በስተመጨረሻም ይህ አይነቱ ድህረ ሺው ዘመን ተቀዳሚ ተግባሩ በምድር ላይ የሺው ዘመን መንግስት እንዲታወቅ ትኩረት የሚሰጠው “ሃሳባችን ምድራዊ ነገሮች” ላይ ወደሚያስደርግ ሃይማኖት ያዘነብላል። ይህ ደግሞ ጳውሎስ በፊሊ 3፡19 ላይ መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ነው ክብራቸው

በነውራቸው ነው ሃሳባቸው ምድርዊ ነው" ብሎ ያስጠነቀቀን ማስጠንቀቂያ ነው። በዚህ ውስጥ ተከታዮቹ (adherents) የአካልን ትንሳኤ ፣ ሰማይ የአማኞች እውነተኛ እና የመጨረሻ መኖሪያቸው መሆኑን እና የአማኞች ሰማያዊ ተስፋ ማረጋገጫ የሆነውን የክርስቶስን ማረ'ግ ሲክዱ ልንመለከት እንችላለን።

**አሜሊኒያሊዝም**

አሜሊኒያሊዝም የሚለው ቃል በቀጥታ "ሺው ዘመን የለም " ማለት ነው። በትክክል ለመናገር አሚሊኒያሊዝም ሺው ዘመን የለም ብሎ ጭራሹኑ አያስተምርም ። እውነታው አሚሊኒያሊዝም በቃል በቃል እና የወደፊቱ ሺው ዘመን አያምንም።

አሜሊኒያሊዝም የራዕይ 20ው ሺህ ዘመን ከመጀመሪያው የክርስቶስ መምጣት ጀምሮ እስከ አለም ፍጻሜ ያለው ሙሉ የአዲስ ኪዳን ዘመን እንደሆነ ያስተምራል። ስለዚህ የራዕይ 20ው ሺው ዘመን ቃል በቃል ትርጓሜው ሳይሆን በምሳሌነት ልንረዳው ይገባል።

ይህ ትምህርት የተመሰረተው በመጀመሪያ ብዙውን ጊዜ በመጽሃፍ ቅዱስ የሚገኙ ቁጥሮች አንድ ሺን ጨምሮ ከቃል በቃል ትርጓሜ ይልቅ ምሳሌያዊያን የመሆናቸው እውነታ ላይ ነው። ለዚህ መጽሃፍ ቅዱስ ቃል በቃል "በሺህ ተራራዎች" ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ተራሮች ያመላከተበት መዝ 50፡10 ጥሩ ምሳሌ ነው።

በዚህ ሺው አመት ጊዜ የሰይጣን መታሰር ዋና ጉዳይ በመሆኑ አሜሊኒያሊዝም ሰይጣን የአዲስ ኪዳን ዘመን በሙሉ እንደታገደ ያስተምራል (ራዕ 20:1–3)። እርሱ የታገደው ሙሉ ለሙሉ ሳይሆን "ህዝብንም ወደፊት እንዳያስት" ነው (ራዕ 20:3)።በሌላ አነጋገር ወንጌሉ እንዳይሰበክ እና በአህዛብ መካከል በመለወጥ ፍሬ እንዳይኖር መከልከል በማይችልበት መንገድ ታግዷል።

ሰይጣን የታሰረው በመጀመሪያው የክርስቶስ መምጣት ጊዜ መሆኑ በማቴ 12:29 ላይ ግልጽ ነው። በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ በራዕይ 20፡2 ላይ እንደተጠቀሰው ሰይጣንን ለመግለጽ የተለመደውን የግሪክ ተመሳሳይ ቃል ተጠቅሟል። ለፈሪሳዊያን "ሃይለኛው ሰው (ሰይጣን)" ሊታሰር ይገባል በማለት ነግሯቸዋል። ከክፍሉ አውድ አንጻር ኢየሱስ በወንጌሉ ስብከት በኩል በአህዛቦች መሰብሰብ ስለመንግስቱ መምጣት እየተናገረ ነው (ማቴ 12:14- 21, 28–30)። የማቴ 12:29 ክፍል ራዕ 20:2 በመተርጎም በአዲስ ኪዳን ውስጥ የታየው የወንጌል ስኬት የሰይጣን መታሰር ውጤት እንደሆነ ያመላክተናል።

ስለዚህ አሚሊኒያሊዝም የሚመለከተው ገና ያልመጣን ሺህ ዘመን ሳይሆን ነገር ግን አሁን እኛ ያለነው በሺው ዘመን መካከል እንደሆነ እና ይህ ሺው ዘመን ሲተናቀቅ የአለም ፍጻሜ እንደሚመጣ ያምናል። ይህ የአዲስ ኪዳን ዘመን የአለም ፍጻሜ ዘመን ነው።

አሚሊኒያሊዝም ከፍጻሜው በፊት በሺው ዘመን መነጠቅን ፣ የክርስቶስ መምጣትን ወይም ደግሞ ታላቁ መከራ ከአለም ፍጻሜ አንድ ሺ አመት ቀድሞ እንደሚሆን አይጠባበቁም። ይልቁኑ እነዚህ ሁሉ ክስተቶች በመጨረሻው የሚከሰቱ እና ዘላለማዊ መንግስት እንደሚከተል ያስተምራሉ።

አሚሊኒያሊዝም እንግዲያውስ የ1 ቆሮ 15:51–52 “መለከት” የመጨረሻው እንደሆነ እና ከመነጠቅ በኋላ (1 ተሰ 4፡16-17) ፣ የተመረጡት በሰማያዊ ክብር ከጌታ ጋር እንደሚሆኑ ያስተምራል። በተመሳሳይ በአሚሊኒያል አስተምህሮ በማቴ 24፡29 ላይ የምናገኘው ታላቁ መከራ በቶሎ ክርስቶስ በእውነተኛው መልክ መገለጡ እና የእርሱ ምርጦች እንዲሰበሰቡ የሚያስታውቅበት መለከት መነፋት ይከተለዋል።

አሚሊኒያሊዝም ሁሉም ነገር ከማብቃቱ በፊት ለቤተክርስቲያን ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ሰላም እና ብልጽግናን አያስተምርም-በዚያን መጨረሻው ቀን “የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ” (2 ጢሞ 3:1) ፣ “ክፉ ሰዎች እየሳቱ እና እያሳቱ ፣ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ” የሚሆንበት ዘመን (ቁ. 13) ።

በዚህም ምክንያት አንዳንዶች አሚሊኒያሊዝም አሉታዊ አመለካከት እንደሆነ ይከሱታል። ነገር ግን ይህ አሉታዊነት አመለካከት አይደለም። አሚሊኒያሊዝም ኢየሱስ እንደሚገዛ እና በሉዓላዊ ሃይሉ ሁሉንም ነገር አሳዛኝ የሆነውን እንኳን ሳይቀር በአንድ ላይ ለእርሱ መልካምነት እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል።

.

**ቃል በቃላዊነት (ቀጥታዊነት) እና ራዕይ 20**

ከላይ እንደተመለከትነው አሚሊኒያሊዝም የራዕይ 20ን ሺውን አመት በቀጥ የሚወስድ ሳይሆን ለሙሉው የአዲስ ኪዳን ዘመን ተምሳሌታዊ መሆኑን የሚረዳ ነው።1000 ማለት 10*10*10 ስለሆነ ተምሳሌታዊነቱ 10 ሙሉነትን የመወከሉ እውነታ ላይ ተመስርቶ ነው። ይህን የሺውን አመት ቀጥተኛ ባለሆነ መልኩ መረዳት ልናብራራው የምንመኘው ነው።

በመጽሃፍ ቅዱስ “ሺህ” ሁልጊዜ በቀጥታ እንደማይወሰድ ቀድመን ጠቅሰናል። እግዚአብሄር በሺ ተራሮች ላይ የሚገኙ እንስሶች ብቻ ሳይሆን ሁሉም የእርሱ ናቸው (መዝ 50:10)። “ሺህ” የሚለው ቃል በቃል ሳይሆን

“ሁሉም” የሚል ትርጉምን የያዘ የመዝሙር ንባባት መዝ 84:10 ፣መዝ 91:7 ፣ እና መዝ 105:8 መጥቀስ ይቻላል። ቁጥሮቹ ራዕይ 20ን ጨምሮ ቃል በቃል መወሰድ አለባቸው የሚሉ ተሳስተዋል።

በራዕ 20 ውስጥ ቃል በቃል ልንወስዳቸው የማንችላቸው ነገሮችንም ልንጠቁም እንወዳለን። በቁጥር 1 እና 2 ሰይጣን ቃል በቃል ዘንዶ አልያም መንፈስ የሆነ ፣ ሰይጣን የምርም በሰንሰለት ይታሰራል ማለት አይደለም ( ሉቃ 24:39 ተመልከት)። ብዙዎች ደግሞ፣ በራዕይ 20፡3 ላይ ያለውን “ጥልቁ” የሚለው ማጣቀሻ ፣ የሰይጣን ማደሪያ እንጂ የመሬት ጉድጓድ እንዳልሆነ ይገነዘባሉ። በተጨማሪም በምዕራፉ ውስጥ ቃል በቃል በቁጥር 10 ላይ የክርቶስ ተቃዋሚ “አውሬ” እንዲሁም ቁጥር 12 የህይወት መጽሃፍ የሚለው ቃል በቃል ወረቀት እና ህትመት ያለባቸው ገጾች ማለት አይደለም ።

በርካታ ነገሮች በራዕይ መጽሃፍ ውስጥ ቀጥታዊ በሆነ መልኩ አይወሰዱም። ለምሳሌ ማንም ክርስቲያን ሽልማቱ በነጩ ድንጋይ ላይ ስሙ ተጽፎበት እንደሚሆን (2፡17) ወይም በሰማይ ወደ አምድነት እንደሚቀየር (3:12) ወይም ደግሞ ኢየሱስ ሰይፍ የሆነ ምላስ እንዳለው (1:16) አይጠባበቅም።

የሺህ አመታትን ቀጥተኛ መልኩ እንድንረዳው በጭክ ብለው አጥብቀው የሚሞግቱ እና ሌላ ማንኛውንም ነገር ለቅዱሳት መጽሃፍ ታማኝ አለመሆን ነው የሚሉ እራሳቸው በራዕ 20፡4 ላይ በቀጥታ የነፍስን ማጣቀሻ ለመውሰድ ፈቃደኛ አለመሆናቸው የሚያስደንቅ ነው። በቀጥታ ከአካል የተእዩ ነፍሳት ሳይሆኑ ሙሉ ሰው እንደሆኑ ይሞግታሉ።

አንባቢዎቻችንን መጽሃፍ ቅዱስ ጽንፋዊ እና ጥብቅ ቀጥተኝነትን እንደማይፈልግ እና በእውነት ይህ የሚያመላክተው መንፈሳዊነት ለቅዱሳት መጽሃፍ ትርጓሜ አስፈላጊ መሆኑን ልናስታውሳቸው እንወዳለን። በ 1 ቆሮ 2:14 ላይ “ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሄር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም ፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።” ተብሎ ተነግሮናል። በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ መንፈሳዊነትን ማለበስ (ማመናፈስ) የምናገኝ ሲሆን ገላ 4፡21-31 ያለው ተጠቃሽ ምሳሌ ነው።

ትክክለኛው የቅዱስ ቃሉ አተረጓገም መንገድ ግትር እና የማይቻል ቀጥተኛነት ሳይሆን መጽሃፍ ቅዱስ እራሱን በራሱ እንዲፈታ የምንፈቅድበት መንገድ ነው። ይህን የሚያደርገው “ሺው” አንዳንዴ በተምሳሌታዊ መልኩ ልንረዳው እንደሚገባ (መዝ 84፡10) ፣ የሰይጣን መታሰር ክርስቶስ ስጋ በለበሰ ጊዜ መሆን እንዳለበት (ማቴ 12:29) እና ሺው ዘመን የሚያበቃው ከአለም በፍጻሜ መሆኑን በማሳየት ነው (ራዕ 20:7–15)። ስለዚህ

ሊኖረን የሚችል ብቸኛ ማጠቃለያ በራሱ በመጽሃፍ ቅዱስ መሰረት ሺው ዘመን የሚያመላክተው ሙሉ የአዲስ ኪዳኑን ዘመን ነው።

ይህ ሁሉ ችግር አለው? በርግጥም አለው። የአሁኑን ዘመን ማለቅ ተከትሎ የሚመጣ የሺው ዘመን ካለ የአማኞች ሰማያዊ ተስፋ እና የመጨረሻውን ፍርድ በጣም እሩቅ ስለሚያደርግ ለክርስቶስ መምጣት ዝግጁ እንዲሆኑ የተሰጠውን የጸሎት ጥሪ እና መጠባበቅ ትርጉም የለሽ ያደርገዋል። የሁሉንም ነገር መጨረሻ እንድንመለከት እና እንድንጠባበቅ የተሰጠን ጥሪ አስቸኳይነት የነገሮቹ በፍጥነት የመምጣታቸው እርግጠኝነታችን ላይ ይደገፋል።

### አንዲት ትንሳኤ

ራዕ 20:5 “የመጀመሪያው ትንሳኤ” በማለት ሲናገር ሁለተኛ እና ምናልባትም ሌላ እንደሚኖር ያመላክታል። ከዘመን ፍጻሜ በፊት ከአንድ በላይ የሆነ አካላዊ ትንሳኤ እንዳለ ለሚያስተምረው ትምህርት ከየትኛውም በላይ ለመደገፊያነት የሚተቀሰው ይህ ክፍለ ንባብ ነው። ቅድመ ሺው ዘመን ሁለት ትንሳኤዎች እንዳሉ ሲያስተምር ዲስፔንሽናሊዝም ደግሞ ሶስት ወይም አራት ትንሳኤ እንዳለ ያስተምራል።

ለምሳሌ ቅድመ ሺው አመት ከሚጠበቀው ሺህ አመት በፊት የቅዱሳንን ትንሳኤ እና በዓለም መጨረሻ ላይ ሌላ አጠቃላይ ትንሳኤ እንዳለ ያስተምራል - ሁለቱ በሺህ አመታት ታሪክ ተለያይተዋል። ቅድመ ሺ ዘመናዊያን በሺው ዘመን መጀመሪያ ላይ በትንሳኤው ተካፋይ የሆኑ የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር ለአንድ ሺ አመት ይገዛሉ ብለው ይናገራሉ።

መጽሃፍ ቅዱስ አንድ አጠቃላይ የሙታን ትንሳኤ ብቻ እንደሚያስተምር እና በአለም መጨረሻ ላይ እንደሚሆን እናምናለን። ያን ጊዜ ሁሉም በፍር በእግዚአብሄር ፊት እንደሚቆሙ እና በትንሳኤ ስጋቸው የጸጋን ወይም የስራ ዋጋን ለመቀበል ይነሳሉ። በዩሐ 5፡28-29 ላይ እንዳለው ይህ የመጽሃፍ ቅዱስ አስተምህሮ እንደሆነ እርግጠኞች ነን።  ሐዋ 24:15ም ለጻድቃንም ሆነ ለእርኩሳን አንድ ትንሳኤ እንዳለ ይናገራል።

በዩሐ 6 ላይ ኢየሱስ አራት ጊዜ የአማኞች ትንሳኤ ከአንድ ሺው አመት ቀድሞ ሳይሆን በመጨረሻው ቀናት እንደሚሆ ተናግሯል (ቁ. 39–40 ፣ 44 ፣ 54)። “የመጨረሻው ቀናት” የሚሉት ቃላት በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ

ሁልጊዜ የመጨረሻውን መጨረሻ የሚያመላክቱ ናቸው (በተጨማሪ ዩሐ 6:40 ፣ ዩሐ 11:24 ፣ እና ዩሐ 12:48 ይመልከቱ) ።

እንግዲህ ታድያ የራዕ 20 የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ትንሳኤ ምንድናቸው? የመጀመሪያው ትንሳኤ ነፍሳት ከሞቱ በኋል ከክርስቶስ ጋር አብረው ሲወሰዱ እና እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ በዚያ አካል በሌለው ሁኔታቸው ከእርሱ ጋር ሲነግሱ ፤ በዚያን ሰውነታቸው በሁለተኛው ትንሳኤ ውስጥ የሚነሳ መሆኑን እናምናለን። በዚህ የምናምንበት በርካታ ምክንያቶች አሉ።

የመጀመሪያው ራዕ 20፡4 ስለነፍሳት ይናገራል። የሚገርመው ፣ በትንሹ ለመናገር ራዕይ 20ን በጥብቅ ቀጥታዊ አጥብቀው የሚከራከሩት ቅድመ- ሺው ዘመኒስቶች እና ዲስፔንሽናሊስቶች ስለ ትንሳኤ ያላቸው አመለካከት ለመከላከል እነዚህ ሰዎች እስከ ፍጻሜው ድረስ በሺህ ዓምት ውስጥ አካላቸው የሚነሳው እና ከዚያም ከአንድ ሺህ አመት ጀምሮ በምድር ላይ በትንሳኤ አካላቸው ከክርስቶስ ጋር የሚነግሱ ሙሉ የሆኑ ሰዎች (ነፍስም ስጋም የለበሱ) ናቸው ለማለት ይገደዳል።

በመጽሃፍ ቅዱስ ነፍሳት የሚለው ቃል ሙሉ ሰዎችን ለማመልከት መጥዕቀሙ እውነት ነው (ዘፍ 2:7 ; ዘፍ 46:26–27)። ነገር ግን በእንደዚ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሰዎች የሚለው ቃል ትርጉሙን ሳይለውጠው ነፍሶች በሚለው ቃል ሊተካ ይችላል። ይህ በራዕ 20 የማይቻል ነው። ራዕ 20፡4ን “ስለ ኢየሱስም ምስክር ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ..........አየሁ” በሚል መልኩ ማንበብ ምንም ትርጉም አይሰጥም።

ሁለተኛው ራዕይ 20 ስለ ሁለት ሞት ይናገራል (ቁ.14)። ሁለተኛው ሞት አካላዊ ሞት ወይም የሰውነት ሞት አይደለም ነገር ግን በሲኦል ውስጥ የነፍስ ለዘላለም መሰቃየት ነው። ሁለቱም ትንሳኤዎች የአካል ትንሳኤዎች የሆኑት ለምንድነው?

ሶስተኛ ከትንሳኤ አንጻር ስለ አዲሱ የነፍስ ህይወት የሚናገሩትን ሁሉንም ክፍሎች ትኩረት እንሰጣለን (ዩሐ 5:24–25 ፣ ዩሐ 11:25–26 ፣ ሮሜ 6:13 ፣ ኤፌ 2:5 ፣ ቆላ 2:12)። ታድያ በሞት ጊዜ የአማኞችን ነፍስ መቀበል በራዕ 20 ላይ “ትንሳኤ” ተብሎ መገለጹ ለምን እንደ እንግዳ ሊታሰብ ይገባል?

ስለዚህ በአንድ የክርስቶስ መምጣት ፣ በአንድ አካላዊ ትንሳኤ እና በአንድ ዘላለማዊ ተስፋ እናምናለን።

**ሞት**

ሞት ጠላት ፣ የመጨረሻው ጠላት መሆኑን ምንም ጥርጥር የለውም (1 ቆሮ 15:26)። ሞትን የምንፈራው ስለማይታወቅ ብቻ አይድለም ። ሞት ምን እደሚመስል ሊነግረን ማንም አልተመለሰም ነገር ግን የሞት ፍራቻችን የመጣው በተለይም ሞት የሃጥያት ደሞዝ እንደሆነ በማወቃችን (ሮሜ 6:23) እግዚአብሄር በእርሱ ላይ ባመጹቱ ላይ ያመጣው ፍርድ ነው።

የሞትን አስፈሪነት እና ውድቀት ለመሸፈን የሚደረግ ሙከራ አያስገርምም። ወይም ሞትን ሲጋፈጡት አብዛኞቹ ምሬታቸውን በፈንጠዝያ እና በመጠጥ ለመግለጥ ሲሞክሩ የሚገርርም አይደለም። እራሳቸው ሲሞቱ እንኳን ስለሞት ማውራትም ሆነ ማሰብ አይፈልጉም። ምንም አይነት እርዳታም ወይም መድሃኒት እንደሌላቸው ግልጽ ቢሆንም በብዙ ምክንያቶች በቀላሉ እየሞቱ መሆኑን ይክዳሉ።

እግዚአብሄራዊ ያልሆኑ በፍጥረት ውስጥ ሞትን ሲመለከቱ ሞት ተፈጥሯአዊ ያለመሆኑን እና የእግዚአብሄር ቁጣ የተገለጠበት የመሆኑን እውነታ ለመሸፈን "የበረታው ይኖራል"[2] እና "ተፈጥሮ በጥርስ እና በጥፍር ውስጥ ይነበበል"[3] ብለው ይናገራሉ። ሞት ሁሉም ቦታ ያለ እና የሁሉም ተስፋዎች ፍጻሜ የሆነ በቅርቡ የሚመጣ ጠላት ነው። በሞት ውስጥ በእግዚአብሄር ፍርድ ሁሉም ስራዎች (ትጋቶች) እና ተስፋዎች ሳይፈጸሙ እና እርካታ ሳይኖራቸው ይቀራሉ።

አንድ አማኝ ሞትን መጋፈጥ የሚችለው በእምነት ብቻ ነው ፣ ያኔም ቀላል አይደለም። ምንም እንኳን ድል ቢኖረውም ሞትን በመጋፈጡ ውስጥ እምነት ሊታገል ፣ ሊፋለም እና ድል ሊያደርግ ይገባዋል። በራሱ ሃጥያት መዘዝ ምክንያት የእግዚአብሄር ልጅ አሁንም በእምነት በክርስቶስ መስዋዕትነት እና በሞት ላይ ድል መንሳቱን እና ሞት በድል መዋጡን በሙሉ ልብ ለማመን በእምነት መፈለግ አለበት።

ለአማኞች ሞት ድል ተነስቷል። ሞት ክርስቶስ ሊይዘው አልቻለም (ሐዋ 2:24) ፣ የሞት መውጊያ (የማጥፊያ ሃይሉ) ሃጥያት ቢሆንም (1 ቆሮ 15:56) ክርስቶስ የራሱ የሆነ ሃጥያት የለበትም። እንደ አስታራቂ በራሱ ላይ የወሰደውን ሃጥያት እስከመጨረሻው ከፍሏል። እርሱ በፈቃዱ እራሱን በሞት ሃይል ውስጥ አስገብቶ የቻለውን መጥፎ ነገር ሁሉ እንዲያደርግለት ፈቀደለ ፣ ነገር ግን እርሱ የእግዚአብሄር ልጅ ቅዱስ ስለነበረ ሊያንፈው አልቻለምም አይችልምም። ጆን ኦውን በሚያምር መልኩ እንዳሰፈረው የእርሱ ሞት አባቱ ለእርሱ ለሰጣቸው ሁሉ "የሞትም ሞት"[4] ነበር።

ይህ “ሞት በድል ከተዋጠ አማኞች ለምን ይሞታሉ?” ወይም የሄድልበርግ የእምነት አዋጅ ላይ እደሰፈረው “ክርስቶስ ለእኛ ከሞተልን እኛ ለምን እንሞታለን?” የሚል ጥያቄን ያስነሳል። የእምነት አዋጁ መልስ የመጽሃፍ ቅዱስ መልስ ነው “የእኛ ሞት ለሃጥያታችን ማርኪያ አይደለም። ነገር ግን ሃጥያትን የማስወገድ እና ወደ ዘላለማዊ ህይወት የምንገባበት ብቻ ነው”[5] (በተጨማሪ ዩሐ 5:24 ፣ ፊሊ 1:23 ይመልከቱ)።

ምን አይነት ድንቅ ነው! ያ ወደ ሲኦል እና ወደ መጥፋት ብቻ ተከፍቶ የነበረው የጨለማው በር አሁን ለአማኞች ወደ ክብር ሰማያዊ ህይወት ተከፍቷል። ስለዚህ ምናልባትም ክርስቶስ በእኛ ፈንታ እንዴት ፍጹም ድል እንዳደረገልን ለማሳየት መሞት አለብን ማለት ስህተት አይደለም። ሞት የሃጥያት ሁሉ ፍጻሜ ነው በእርግጠኝነት የክብር በር ነው ነገር ግን ሞት በእርግጥም መዋጥ ለመሆኑ ምስክርም ነው።

ስለዚህም አማኞች “በህይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን ፥ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን” ይላሉ (ሮሜ 14:8)። ሞት ሲመጣብህ ይህ ያንተም አዋጅ ይሆናል?

**የትንሳኤያችን አስፈላጊነት**

ለአማኞችም ሆነ ለማያምኑቱ በአለም መጨረሻ ቅድመ ሺው ዘመን እና ዲስፔንሽናሊዝም እንደሚያስተምሩት በርካታ ሳይሆን አንድ አካላዊ ትንሳኤ ብቻ መኖሩን አጽንተናል። ለእኛ ይህ አንድ ትንሳኤ የእግዚአብሄር ቃል እንድናደርገው እንደሚያስታውሰን የተስፋችን ሁሉ ትኩረት ነው (1 ቆሮ 15:12–19)። በመጨረሻው ቀን የአማኞችን ትንሳኤ በተመለከተ መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን እንመልከት።

የክርስቶስ ትንሳኤ ብቻ ሳይሆን የአማኞችንም ትንሳኤ መካድ ከባድ ስህተት አድርገን ልንመለከተው ይገባል። ለእኛ ከሞት መነሳት ከሌለ ክርስቶስም ከሞት አልተነሳም ማለት ነው። አንዱ ከሌላው ተነጥሎ የሚሆን ያለመሆኑን ያህል የቀረበ ግንኙነት በሁለቱ መካከል አለ። ይህ በ 1ቆሮ 15:16–17 ላይ ተነግሯል።

የክርስቶስን ትንሳኤ የሚክዱ ሁልጊዜም ነበሩ። ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነቱ ክህደት የክርስቶስን መለኮታዊነት ፣ ከድንግል መወለዱን እና የእርሱን የስርየት መስዋዕቱን ከመካድ ጋር ይመጣል። የአማኞችንም ትንሳኤ የሚክዱም አሉ። እንዲህ አይነት ነገር በጥንቷ ቤተክርስቲያን (1 ቆሮ 15:12 ፣ 2 ጢሞ 2:17–18) እና አሁንም በዙሪያዋ አለ።

አንዳንዶች በተለይም በክርስቲያናዊ ተሃድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ ስለ ትንቢት ቅድመ-አለማዊ አመለካከት በሚያዝ በ2 ጢሞ 2፡17-18 ላይ የተጠቀሱትን የሂሜኒዎስ እና ፊሊጦስን ስህተት አስነስተዋል። እነዚህ ሰዎች ብዙም ባይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት  ቀድሞውንም ፍጻሜ አላገኘም ብለው ያምናሉ (ፕሪተሪዝም የትንቢት ፍጻሜ አልፏል የሚል እምነትን የሚያመላክት ነው)። ትንሳኤ ያለፈ መሆኑን መናገር ጀምረዋል።

ነገር ግን ጳውሎስ የአማኞችን ትንሳኤ መካድ ማለት የክርስቶስን ትንሳኤ መካድ እና እምነትን ከንቱ ማድረግ ራሳችንን በሃጥያታችን ውስጥ መተው እንደሆነ ይናገረናል። ስለዚህም ይህ ከባድ ስህተት ነው። ለምድነው ይህ የሆነው?

የመጀመሪያው የወደፊቱን አካላዊ ትንሳኤ መካድ ማለት የክርስቶስን ትንሳኤ መካድ ነው ምክንያቱም የክርስቲያኖች ትንሳኤ የክርስቶስ ትንሳኤ አካል ስለሆነ ነው። አማኞች ለክርስቶስ አካል እና ለቤተክርስቲያን የተገቡ እና በውስጣቸው የክርስቶስ የትንሳኤው ህይወት አላቸው። ውጤቱም እነርሱ ከክርስቶስ ጋር ከሙታን መነሳታቸው ነው። ካልተነሱ ሊኖር የሚችለው ብቸኛ ማብራሪያ የክርስቶስ የትንሳኤ ህይወት ጭራሽ የለም - ክርስቶስ አልተነሳም ሞትንም ድል አልነሳም። በሞት ላይ የክርስቶስ ሃይል እና ድል በእርሱ ትንሳኤ ብቻ ሳይሆን የሚረጋገጠው በአማኞችም ትንሳኤ ነው።

ትንሳኤን መካድ እኛን በሃጥያታችን ውስጥ ይተውናል ምክንያቱም የክርስቶስ ትንሳኤ በእግዚአብሄር ፊት ለመጽደቃችን ማረጋገጫችን ነው። ክርስቶስ ለሃጥያት ስርየት ሲያቀርብ “ተፈጸመ” ብሏል። እግዚአብሄር ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሳው እንደ ዳኛ  “ተፈጸመ” ብሏል። ስለዚህ ትንሳኤው በእግዚአብሄር ፊት የመጽደቃችን መግለጫ ነው። ሮሜ 4፡25 ጌታችን ኢየሱስ “እኛንም ስለማጽደቅም የተነሳው” በማለት የሚናገረው ይህንን ነው።

ተስፋችን ሰማይ ከሆነ እና “ስጋና ደም የእግዚአብሄርን መንግስት ሊወርሱ አይችሉም” (1 ቆሮ 15:50) ከሆነ ትንሳኤውን እንጠባበቃለን። ነገር ግን ሙታን ካልተነሱ እና ሰውነታችን በትንሳኤው ካልተለወጠ ተስፋችን ከንቱ ነው። ስለዚህ በሶስተኛው ቀን ክርስቶስ መነሳቱን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እኛ ከክርስቶስ ጋር ስለምንነሳበት ትንሳኤ የእኛ በስባሽ ስጋችን የእርሱን ክቡር ስጋውን ወደመምሰል እንደሚለወጥ ልናምን ይገባል (ፊሊ 3:21)።

**የትንሳኤው አካል**

ስለሞቱት ትንሳኤ ፣ በትንሳኤው ስለሚኖረን አካል እና በትንሳኤው አካላቸው ለእግዚአብሄር ህዝቦች ቤታቸው ስለሚሆነው ሰማይ አሁን ሊመለሱ የማይቻሉ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ይሁን እንጂ መጽሃፍ ቅዱስ በትንሳኤው አካል እንድናምን እና በተስፋ በጸሎት የምንጠብቀው ነገር ስለመሆኑ በቂ መረጃን ይሰጠናል።

መጽሃፍ ቅዱስ ስለትንሳኤ አካላችን በ 1ቆሮ 15 ላይ ብዙ ይነግረናል። በዚያ እጅግ ድንቅ አራት እውነታዎች ተናግሮናል።

የመጀመሪያው የትንሳኤው አካል የማይበሰብስ ነው (ቁ. 42 ፣ 52). ከሃጥያት ተጽኖዎች - ከመታመም ፣ ከሞት እና ከመቃብር- ነጻ መሆን ብቻ ሳይሆን ለአዳም እንደሆነው በሃጥያት እና ሞት ውስጥ በድጋሚ ለመካተት ፈጽሞ የሚቻል አይደለም። የማይበሰብስ ማለት "መበስበስ የማይቻለው" ማለት ነው!

ሁለተኛው የትንሳኤው አካል የከበረ ነው (ቁ. 43)። ክብሩ የክርስቶስ ክብር እና እግዚአብሄር በክርስቶስ ውስጥ ያለው ክብር ነው። ጳውሎስ "የተዋረደው ስጋችን" ፤ "ክቡር ስጋውን እንዲመስል" ይለወጣል በማለት ይናገራል  (ፊሊ 3:21)። ይህ የሰማዩ ክብር እና የህይወቱ በረከት ነው።

ሶስተኛ የትንሳኤው አካል ሃያል የሆነ ነው (1 ቆሮ 15:43)። ኢሳ 40፡31 ስለዚህ ትንሽ ይነግረናል። መሮጥ መቻል እና አለመታከት የማይገናኙ ነገሮች ናቸው ነገር ግን ይህ በትንሳኤው ከምናገኘው ነገር ትንሹ ነው። አዳም ያጣውን ሃይል መልሰን ማኘታችን ብቻ ሳይሆን ከእርሱ በእጅጉ የሚያልፍ ነገር ይኖረናል። በታወቅነው ልክ የምናውቅበት ሃይል እንኳን ይኖረናል (1 ቆሮ 13:12)። ከሁሉም በላይ እግዚአብሄርን ከሃጥያት ውጪ የምንወድበት ፣ የምናገለግልበት እና የምንታዘዝበት ሃይል ይኖረናል። ምን አይነት ድንቅ ነው!

በመጨረሻም የትንሳኤው አካል መንፈሳዊ ነው (1ቆሮ 15:44)። በዚህ መጽሃፍ ቅዱስ የሚለውን በሙሉ ለመረዳት ቢከብድም ነገር ግን ቢያንስ በእርግጠኝነት ይህን ምድር እና ህይወቱን የተላመደውን "ስጋና ደም" የምንሆን ሳይሆን ነገር ግን ስጋና ደም ሊወርሱት የማይችሉትን እንወርሳለን (ቁ. 50) ።

ሰውነታችን ከሞት ብናኝ ሲነሳ በአካላችን ውስጥ የሚሆነው ለውጥ በምናብ መሳል እንድንሞክረው መጽሃፍ ቅዱስ የተወሰነ ጽንሰ ሃሳብ ሊሰጠን ተገዷል። ጠንካራ እና ህይወት አልባ በሆነው ስንዴ ቅንጣት መካከል ያለው ለውጥ አረንጓዴ እና ህያው ተክል ከእርሱ ማደግ መቻሉ ስለ እኛ መለወጥ የተወሰነ ምስል ይሰጠናል (1ቆሮ 15:37)።

በፍጥረት ውስጥ እንድንረዳው የሚያግዘን ሌላ ምስሎች አሉ። የእጭ (caterpillar) ወደ ቢራቢሮነት የሚያደርገው ዑደት (metamorphosis) አንዱ ምስል ነው። ዑደት (metamorphosis) የሚለው የግሪኩ ቃል በፊሊ 3፡21 ላይ "ለውጥ" ተብሎ የተተረጎመው መጽሃፍ ቅዱስ ለትንሳኤ የሚጠቀመው አንዱ ቃል ነው። ከእግዚአብሄር ፍጥረት መካከል ውብ የሆነው በአፈር ላይ የሚንከባለለው ትል (እጭ) ቢለወጥም በፊት የነበረው ፍጥረት ነው።

ስለ ትንሳኤው ድንቆች ስናስብ የተስፋዎቻችን ትኩረት ይሆናል። ከዚያም "ኢየሱስ ጌታዬ በቶሎ ና! ናና ይህን የተዋረደ ፣ በሃጥያት የሚነዳው ፣ ለሞት እና ለመበስበስ የተጋለጠውን አካላችንን ለውጥልን እና ሁላችንንም አንተን በሚመስለው አካል እንዲሁም መንፈስ አድርገን!" እንላለን።

**የትንሳኤው አስደናቂነት**

የሙታን ትንሳኤ ተዓምር ነው በእምነት ብቻ የምንረዳው እና የምንቀበለው የእግዚአብሄር ድንቅ የሆነ ስራው ነው። የማያምኑት ይህን ሲሰሙ ይቀልዱበታል (ሐዋ 17:32) ፣ ሃሰተኞች ይክዱታል (1 ቆሮ 15:12 ፣ 2 ጢሞ 2:18) ነገር ግን የሙታን ትንሳኤን ተስፋ ለሚያምኑቱ እግዚአብሄር በእርግጥም እውነተኛ አምላክ ፣ ታላቅ ፣ "የማይመረመረውን ታላቅ ነገር የማይቆጠረውንም ተአምራት"  የሚያደርግ የመሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው (ኢዮ 5:9)።

ስለ ትንሳኤ ትንሹ ድንቅ ነገር የሁሉም የግሉ አካል የሚነሳ መሆኑ አስተውል። የአንዳንዶች አካል ቅሪታቸው ሊገኝ እስከማይችል ድረስ ከረጅም ጊዜ በፊት ወደ ብናኝነት ተለውጠዋል። ሌሎቹ በዱር አራዊት እና በባህር አሳዎች ተበልተዋል። አዳንዶች እንደ ጆን ዊይክሊፊ አካላቸውን በማቃጠል ወደ አመድነት ተለውጠው በጠላቶቻቸው ወደ ወንዞች እና ባህሮች ተጥለዋ። ነገር ግን ሁሉን የሚያውቀው እግዚአብሄር የእያንዳንዱን አካል በመከተል በትንሳኤው ለትክክለኛው ባለቤት ይሰጠዋል። ስለዚህ ትንሳኤ የእኛን ብናኝ የማይረሳ ታማኝ አምላክ የመሆኑ ምስክርነት ነው።

ይህ ኢዮብ 19፡25-26 ላይ ኢዮብ በትንሳኤ ያለውን እምነት "እግዚአብሄርን በስጋ አየዋለው" ሳይሆን ነገር ግን "በስጋዬ" በማለት በግልጽ የተናገረው እውነት ነው። እንዲሁም 2ቆሮ 5፡10 ይህንን ነገር ያስታውሰናል። በክፍሉ ሁሉም እንደስራው በሰውነቱ ላይ እንደሚቀበል እናነባለን።  የተፈቀደለት የኪንግ ጄምስ ትርጉም

እንደሚያመላክተው “የእርሱ” የሚለው ቃል በግሪኩ ውስጥ ባይገኝም ነገር ግን ተርጓሚዎቹ “የእርሱ” የሚለውን ቃል ሲጨምሩበት ክፍሉን በተገቢው መንገድ ተረድተውታል። በእርግጥ ክፍሉ ሰው ቅጣቱን ወይም ሽልማቱን በሰውነቱ እንደሚቀበል መልካም የሰሩቱ ሽልማት ክፎዎች ደግሞ ይቀጣሉ ማለቱ ነው።

ትንሳኤው የአጠቃላይ ትንሳኤ የዚህ ድንቁ አካል ነው። የኖሩ እና የሞቱ ቢሊየኖች በመሆናቸው እያንዳንዱ አንድ እስትንፋስ የሌለው ሳይተው ሁሉም የሚነሱ ይሆናል። በመቃብር ስፍራ ቆሞ የተቀበሩት ሁሉ በእግዚአብሄር ሃይል በፊቱ ሊቆሙ ከማቅብር ውስጥ እንደሚነሱ ማመን አንድን ሰው በእግዚአብሄር ታላቅነት እና በስራዎቹ ሁሉ ለመገረም ይተወዋል (ዩሐ 5:28–29) ።

ለአማኞች ከሁሉም በላይ ድንቅ የሆነው ነገር በትንሳኤው የክርስቶስ እንደሆኑ እና ወደ ዘላለማዊው ክብር ከእርሱ ጋር አብረው እንደሚሄድ ቀደም ብለን ተመልክተናል። በፍርድ ውስጥ ማለፍ ቢኖርባቸውም እንኳን ነገር ግን ማይበሰብስ እና ባለክብር ሆኖ በተነሳው አካል (1 ቆሮ 15:42–44) ፣ እጅግ ክቡር ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ አካል ተለውጧል (ፊሊ 3:21)። በፍርዱ ውስጥ የተሰጣቸው ምን አይነት ታላቅ ተስፋ ነው!

ለሚያምኑት ትንሳኤ የሚሆነው መጽሃፍ ቅዱስ ቃል ስለገባ እና ክርስቶስ በእኛ ስጋ በመነሳቱ ምክኛት (1 ቆሮ 15:19–20) ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የትንሳኤው ሃይል በእነርሱም ስለተገለጠ ነው። ቀድሞውኑ በነፍስ እና በመንፈስ በክርስቶስ ኢየሱስ የትንሳኤው ሃይል ከሞት ተነስተዋል። አሁን የሚጠባበቁት እግዚአብሄር ነፍስ እና አካላቸውን የማስነሳቱን ስራ እንዲጨርስ ነው። ትንሳኤ በእነርሱ ላይ መሆንን ጀምሯል! ሙታን የእግዚአብሄርን ልጅ ድምጽ የሚሰሙበት እና በህይወት የሚኖሩበት ሰዓት ይመጣል (ዩሐ 5:28–29) ነገር ግን ሙታን በወንጌል በኩል ድምጹን የሚሰሙበት እና በእርሱ ውስጥ በእምነት የሚኖሩበት ሰዓት መጥቷል (ዩሐ 5:25)። በእርሱ ድምጽ በመንፈሳዊ ትንሳኤያቸው ሰዓት መኖር ጀምረዋል ይህም ዳግም መወለዳቸው ነው። አሁን የሚጠባበቁት የሰውነታቸውን ትንሳኤ ሰዓት ነው።

### የነፍስ አለመሞት

ክርስቲያኖች ስለ “ነፍስ አለመሞት” ሲናገሩ እንሰማለን። ይህም በተለምዶ የሰው ነፍስ ከሞት በኋላ መኖሯን ትቀጥላለች ማለት እንደሆነ እንረዳለን። ከሞት በሁላ የነፍስ መኖሯን መቀጠሏ መጽሃፍ ቅዱሳዊ መሆኑ የምንስማማ እና አንዳንድ ህይማኖቶች እንደሚያስተምሩት የማያምኑ ክፍዎች ለዘልለም በሲዖል ከመቀጣት

ይልቅ ነፍስ እና ስጋ እንደሚጠፋ (annihilated) በሚያስተምሩትን በመቃረን ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባው እንስማማለን።

ነገር ግን የክፉን ነፍስ መኖር መቀጠል "የማይሞት" ብሎ መጥራት የሆነ ቸልተኝነት እና መጽሃፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ የቃሉ አጠቃቀም ነው። መጽሃፍ ቅዱስ ቃሉን የሚጠቀመው ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ላለው ዘላለማዊ ህይወት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑኡ የመጨረሻው በረከታቸው መሆኑን ለማመላከት ብቻ ነው።

ኢ-ሟቲነት ማለት "መሞት አለመቻል" ማለት ነው። በሃጥያት ውስጥ ሲወድቅ ይሞታል ብቻ ሳይሆን በስጋ እና በነፍስ በመሞቱ አዳም የማይሞት አደለም (ዘፍ 2:17)። ሁሉም በበደል እና በሃጥያት በስጋ እና በነፍስ ስለሞቱ የወደቀው የሰው ልጅ የማይሞት አይደለም።ኢየሱስ የማያሙ "ፈጽሞ ህይወትን አያዩም" ብሎ ተናግሯል። ምክንያቱም የእግዚአብሄር ቁጣ በእነርሱ ላይ ስለሚሆን ነው (ዩሐ 3:36)።

መጽሃፍ ቅዱስ ዝምብሎ መኖርን "ህይወት" ብሎ አይቀበለውም "ሰው ከእግዚአብሄር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀር ብቻ አይኖርም" (ማቴ 4:4) ፣ "........ሞገሱ ግን ለህይወት ዘመን......." (መዝ 30:5) ፣ "ለእኔ ህይወት ክርስቶስ ፤ ሞትም ጥቅሜ ነውና" (ፊሊ 1:21)።

በ 1 ቆሮ 15:53–54 ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል ፈጥረታዊው ሰው የማይሞት ሳይሆን "ይህ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋል" በማለት የሚሞት እንደሆነ ያስተምረናል። በጸጋው ብቻ በክርስቶስ የሆኑት የማይሞቱ ይሆናል። አለምሞት ከእግዚአብሄር ለእነርሱ የሆነ ስጦታ ነው። የሰው ልጅ ከአዳም የሚሞት ህይወትን ተቀብሏል። በክርስቶስ ብቻ የእግዚአብሄር ህዝቦች አለመሞትን ይቀበላሉ ምክንያቱም እርሱ ከሰማይ የሆነ ጌታ ስለሆነ ነው (ቁ. 45-47)።

ስለ ቃላት quibbling እያደረግን ብቻ ነው? እንዳልሆነ እናምናለን። አንድ ነገር ፣ የሰው ነፍስ አትሞትም ብሎ መናገር በሃጥያት ምክንያት ስጋ እና ነፍስ ወደ ዘላለም ሞት መውደቁን እና ስጋን እና ነፍስን ማዳን ያለበት በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተው ሞት የመሆኑን እውነታ መደበቅ ነው። በባህሪው ሰው በስጋም በነፍስም በበደሉ እና በሃጥያቱ የሞተ ነው (ኤፌ 2:1)።

ሌላው ነገር የሁሉም ነፍስ የማይሞት ነው የሚለው አሰተምህሮ ሰዎች ነፍስ ከሰውነት በበለጠ አስፈላጊ እንደሆነ እንዲያስቡ እንዲሁም ሰውነት የሚጠፋ እንደሆነ እንዲያስቡ ያደርጋል። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በተለይም ደግሞ በጥንቷ ቤተክርስቲያን እና በሮማ ካቶሊኪዝም ሰውነትን አላግባብ ወደመጠቀም

እና የማሰቃየት  ልምምድ እንዲያመሩ አድርጓቸዋል።መጽሃፍ ቅዱስ በእግዚአብሄር ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ሰውነታችን እንደሚጠፋ ና አለአግባብ የምንጠቀመው ሳይሆን ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደሆኑ ያስተምረናል (1 ቆሮ 6:18–20)።

ስለዚህ "የማይሞት" የሚለውን ቃል መጽሃፍ ቅዱስ እንደሚጠቀመው በክርስቶስ የሆነውን አስንደናቂውን የዘላለም ህይወት ስጦታ መሆኑን ለማመላከት ብቻ ብንጠቀም መልካም አይድል? እኛ በጸጋው የዘላለም ህይወትን ስንቀበል ሞት በድል ስለተዋጠ ከአሁን በኋላ መሞት የማንችል ሆነናል (ራዕ 21:4)።

**መካከለኛው ስፍራ**

በስነመለኮት የመካከለኛ ስፍራ አስተምህሮ በመሞት እና በመጨረሻው ትንሳኤ መካከል ከነፍስ ስፍራ ጋር ይያያዛል። አስተምህሮው "ከሞት በኋላ ምን እሆናለው?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ስለዚህ አማኝ ከሞተ በኋላ ወደ ሰማያዊ ክብር እንደሚገባ እና ከክርስቶስ ጋር እንደሚሆን መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ለአማኝ ዋና ፍላጎት ነው።

How different their experience is from that of the unbelieving and unrepentant, who go into conscious suffering for their sin in hell even before their bodies are raised (Luke 16:22–28).

ይህንን የሚክዱ በርካቶች ናቸው። አንዳንዶች በሰማይ ወይም በሲዖል የሚገኙ ሁሉ በእነርሱ ላይ ምን እንደሚደረግባቸው ምንም ሳያውቅ "ነፍስ ትተኛለች" ብለው ያስተምራል። በተመሳሳይ አንዳንድ ሪኮስንትራክሽኒስት ክርስቲያኖች ነፍስ በሞት ከመኖር ውጪ እንደምትሆን ያስተምራሉ። ይህ ምልከታ ካልቪን ከዘጅም ጊዜ በፊት እንደጠቀሰው በእግዚአብሄር ህዝብ ሊወለድ አይገባውም። This notion, as Calvin pointed out long ago, is perverse and should not be borne by God's people. ይህ በክርስቶስ ያላቸውን ተስፋ ያጠፋዋል ፣ የሞትን ፍርሃት ያድሰዋል እንዲሁም በጠላትቻቸው ፊት ሁሉ መጽናኛ አልባ ያደርጋቸውል።

ከክርስቶስ ጋር ለመክበር ያለን ተስፋ ኢየሱስ በመሞት ላይ ለነበረው ሌባ "ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለ" በማለት በተናገረው ቃል ላይ የተመሰረተ ነው  (ሉቃ 23:43)። ኢየሱስ "በዚያ ትሆናለ ነገር ግን የምታውቀው

አይሆንም” ወይም “ ገነትህ ብዙ ሺ ዘመናት እስኪያልፉ እና በመጨረሻ ፍጻሜው እስኪመጣ የምናሳልፈው ከመኖር ውጪ መሆናችን ነው” ማለቱ እንደሆነ የሚያምን አለ?

ፊሊ 1:23ን በተመለከተ ካልቪን “ እርሱ [ጳውሎስ] ለክርስቶስን ምንም ምኞት ሊኖረው በማይችልበት ሁኔታ ለማንቀላፋት እየተመኘ እንደሆነ ያስባሉ? የምድራዊው ድንኳን የሆነው ቤቱ እንደፈረሰ ሲናፍቀው የነበረው ሁሉ በእጅ ያልተሰራ የእግዚአብሄር ህንጻ እንዳለው ሲናገር የነበረው ይቀራል? (2 Cor. 5:1)። የክርስቶስን ህይወት መኖሩን ሲጠቅስ የነበረው ከክርስቶስ ጋር የመሆኑ ጥቅም የታለ? ምንድነው! አምላክ እራሱን የአብርሃም ፣ የይስሃቅ እና የያዕቆብ አምላክ “የህያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አይደለውም” ብሎ ሲናገር በጌታ ቃል የተደነቁ አይድለም? (ማቴ 22፡32 ፣ ማር 12፡27)። እርሱ አምላክ ሊሆናቸው አይደለምን? እነርሱም ለእርሱ ህዝቦች አይደሉምን?[6]።

ነገር ግን የአማኞችን ሞት እንደ እንቅልፍ ስለሚገልጹት ክፍሎችስ (ማቴ 27:52 ፣ ሐዋ 13:36 ፣ 1 ቆሮ 11:30 ፣ 1 ቆሮ 15:20 ፥ 51 ፣ ኤፌ 5:14 ፣ 1 ተሰ 4:14)? እስካሁን በጠቀስናቸው ምንባባት ብርሃን የነፍስ ማንቀላፋት ስለሚባል ነገር ማለታቸው አይደለም። እያመለከቱ ሊሆን የሚችለው ስለ ሰውነት መበስበስ እና የአማኞች ሞት ፣ ድል የተነሳው ሞታቸው በእንቅልፍ ከከመወሰድ በላይ የሚከብድ ያለመሆኑን እውነታ ነው። የአማኞች ሞት ከድካማቸው ወደ ዘላለሙ እረፍታቸው የሚገቡበት በመሆኑ እንደ እንቅልፍ መገለጹ እንግዳ ሊሆን አይገባም (ኢሳ 57:1 ፣ ራዕ 14:13)።

መጽሃፍ ቅዱስ በሞት እና በመጨረሻው ትንሳኤ መካከል ያለው ጊዜ ነፍስ ከአካሏ ውጪ እግዚአብሄር ቃል የገባውን ክብር እንድታጣጥም የተወሰነ ልዩ የሆነ አቅርቦት አዘጋጅቷል። “ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሰራ የዘላለም ቤት የሚሆን በእግዚአብሄር የተሰራ ህንጻ እንዳለን እናውቃለን።” (2 Cor. 5:1) ። ስለዚህም ምክንያት ከአካላችን መለየት ማለት ከእግዚአብሄር ጋር (በቀጥታ “ቤታችን”) መሆን ማለት ነው (ቁ. 8)። አንዳንዶች ፈቃደኞች አይደሉም ፣ እኛ ግን ከሰውነታችን ለመለየት ፈቃደኞች ነን አይደለንም?

**ታላቁ መከራ**

ብዙ ውይይት ያለበት ነገር እና በክርስቲያኖች መካከል የብዙ ልዩነቶች ምንጭ የሆነ የእግዚአብሄር ሕዝቦች በጣም አሳሳቢ ጉዳይ የመጨረሻው ዘመን መከራ ነው። በማቴዎስ 24:21 የተጠቀሰው ታላቁ መከራ ከዚህ በኋላ ይመጣል ወይስ አልፏል? የመጨረሻው ጊዜ ሲመጣ መከራ ይኖራል? እንደዚያ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን አባላት በዚህ መከራ ያልፋሉ ወይስ የመጨረሻው መከራ ከመምጣቱ በፊት ከዓለም ይነጠቃሉ?

እንደ እነዚህ ያሉት ጥያቄዎች ከወደፊቱ አንጻር ስለ ራሳችን ጥሪ እና ስለቤተ ክርስቲያን ጥሪ ያለን አመለካከት ላይ ተጽእኖ ስለሚያደርጉ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በእርግጥ መከራ እየመጣ ከሆነ እነዚህ ጥያቄዎች ፍጻሜው ሲቃረብ እና እኛ እና ልጆቻችንን ስደት እየገጠመን ሲሄድ ክብደታቸው እየጨመረ ይመጣል።

እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ ስደት የእግዚአብሔር ሕዝብ  ዕጣው እንደነበረ እና ሆኖም እንደሚቀጥል እናምናለን። ይህ እንደ ሮሜ 8፡17 እና 2 ጢሞቴዎስ 3፡12 አይነት ምንባቦች የሚሰጡት ምስክርነት ነው። ስለዚህም የፍጻሜው ዘመን ሲመጣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ዕጣ ይሻሻላል ወይም ስለ ክርስቶስ መሰደድ ስለሚያቆም ለእነርሱ ረጅም የሰላም እና የመንፈሳዊ ብልጽግና ጊዜ ይሆናል ብለን አናምንም። የመጨረሻው ታላቅ መከራ ሲመጣ ቤተ ክርስቲያንም ትነጠቃለች ወይም ትጠፋለች ብለንም አናምንም።

በማቴዎስ 24፡21 ውስጥ የተጠቀሰው ታላቁ መከራ ገና ሊመጣ እንደሆነ እና ጊዜው ለእግዚአብሔር ሰዎች የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን እናምናለን። አንዳንዶች እንደሚያደርጉት፣ የማቴዎስ ወንጌል 24 ሙሉውን ቁጥር 21 ን ጨምሮ ከዚህ በፊት ሆኗል ብሎ ማሰብ ሙሉውን ቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ማስገባት ነው። የአምላክ ሕዝቦች ይነጠቃሉ ወይም ስደት ይቆማል የሚል አመለካከት ከዚህ ጥቅስ ጋር አይስማማም።

ስደት ዝም ብለን የምንታገሰው ብቻ አይደለም። የመዳናችን ዋና አካል ነው። ማቴዎስ 5፡10-12 ስለ ክርስቶስ ስደት ስለሚሰደዱ ሰዎች በረከት እና ደስታ ሲናገር ይህን አስቀድሞ ያመለክታል (በተጨማሪም የሐዋርያት ሥራ 5፡41 ይመልከቱ)። ፊልጵስዩስ 1፡29 ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ካገኛቸው ጸጋዎቹ አንዱ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ይነግረናል። ቆላስይስ 1፡24 እነዚህ መከራዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲባል ወደ ኋላ የተረፈ የክርስቶስ መከራ አካል መሆናቸውን ይናገራል (በተጨማሪ 1 ጴጥ. 4፡13 ተመልከት)።

መከራ ምንም እንኳን ቀላል ወይም አስደሳች ባይሆንም ለእራሳችን ጥቅም እንደሆነ እናውቃለን። ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው እና የሚያጸናው ብልጽግና እና ሰላም ሳይሆን እምነታችን ሲፈተን ነው። መዝሙረ ዳዊት 11፡5፣ የ1ኛ ጴጥሮስ 1፡7  እና ሌሎች በርካታ ምንባቦች የሚነግሩን ይህ ነው።

“የሰማዕታቱ ደም ለቤተክርሰቲያን ዘር ነው”[7] የሚለው የጥንት አባባል የስደትን ዋጋ ያሳያል። ለእግዚአብሔር ጸጋ ኃይል እና ድንቅነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ወንጌልና ስለ ክርስቶስ መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ እንደመሆናቸው ምስክርነት መስጠት የሚችል ምንም ነገር አይኖርም። እንደዚህ አይነት ስቃይ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ለራሳችን መንጻት፣ ለቤተክርስቲያን እና ለእኛ ሲል መከራ ለተቀበለው መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ እና ደስተኞች መሆን አለብን።

### የክርስቶስ ተቃዋሚ

የክርስቶስ ተቃዋሚን በተመለከተ ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ሁል ጊዜ ትኩረት የሚስብ ነው። ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር ህዝብ ጠላቶች አንዱ ሆኖ ስለተሳለ ነው። ማን እንደሆነ እና መቼ እንደሚመጣ ግን ብዙ አለመግባባቶች አሉ።

የክርስቶስ ተቃዋሚ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4 ላይ “እግዚአብሔር ከተባለው ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ወይም የሚሰገድለት” ተብሎ ተገልጿል:: የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው ራሱን በክርስቶስ ቦታ ሰለሚያሰቀምጥ ነው ("እግዚአብሔር ከተባለው በላይ ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል")።

የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚለው ስም በ 1 እና 2 ዮሐንስ ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል (1 ዮሐንስ 2: 18, 22;1 ዮሐንስ 4:3; 2ኛ ዮሐንስ 7) ግን በ2ኛ ተሰሎንቄ 2 ላይ ስሙ አልተጠቀሰም።  ነገር ግን ዮሐንስ በተጠቀመበት ስም እና 2ኛ ተሰሎንቄ 2 የተሰጠው መግለጫ መካከል ያለው መመሳሰል ሁለቱም ምንባቦች ስለ አንድ ሰው የሚናገሩት ነው ወደሚል መደምደሚያ ይመራናል።

በተጨማሪም ዮሐንስ ስለ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሲናገር፣ ተሰሎንቄ ግን አንድ ሰው እንደሆነ እንድናምን እንደሚመራን እናስተውል። ይህ በራእይ 13 ላይ በተገለጸው በኩል የበለጠ መረዳተ ይቻላል፤ እዚያም የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚለው ስም ጥቅም ላይ አይውልም ፣ ነገር ግን ከ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4–10 ምንባብ ጋር ሲነጻጸር ጉዳዩ አንድ መሆኑን ያሳያል።

ራዕይ 13 የሚገልጸው ይህ “አውሬ” በታሪክ እንደ ተገለጠ ያሳየናል። የተለያዩ የአውሬው ራሶች የተለያዩ መንግስታትን ያመለክታሉ (ዳን. 7፡1–8፣ 15–28)። ነገር ግን፣ እነዚህ ሁሉ በመጨረሻ በአንድ ሰው የሚገለጠውን መንግሥቶች ይወክላሉ፣ እርሱም በ2ኛ ተሰሎንቄ 2 “የ የኃጢአት ሰው” እና “ክፉው [አንዱ]” (ቁ. 3፣8) ተብሎ ተጠርቷል።

እነዚህ ስሞች ሁሉንም ግልጽ ያረጉታል። የሰው ልጆች ኃጢአትና በእግዚያብሄር መንግስት ላይ የተደረጉ አመጸች ሁሉ በዚህ ሰው ውስጥ እና በመንግሰቱ ውስጥ እንዳለ ያሳዩናል። እርሱ ውስጥ ያለው እሱ ነው። “እንደ አማልክት ትሆናላችሁ” (ዘፍ. 3:5) የሚለው የሰይጣን ውሸት ግልጽ ሆኖ የሚታየው በእርሱ ነው። በራዕይ 13 ላይ አውሬው ከሰይጣን ጋር እንደሚገናኝ እና እውነተኛ ባህሪውን የቤተ ክርስቲያን.ጠላት እንደ ሆነ ተገልጿል ።

የክርስቶስ ተቃዋሚ መቼ እንደሚመጣ ፣ ማን እንደሆነ፣ እና ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ የክርስቶስ ተቃዋሚ ናቸው ወይ የሚሉት ክርክሮች በ1ኛ ዮሐንስ 2፡18 ላይ በተነገረው መሰረት በተወሰነ ደረጃ ተወግደዋል፡ “አሁን ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች አሉ”። የመጨረሻው የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግሥት መታውቅ እና ኃይል ወደፊት ሊመጣ ይችላል፣ ነገር ግን እኛ እንደምናምነው የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሁል ጊዜ እንዳሉ ፈጽሞ አንረሳውም።

ጳጳሱ እና የጳጳሱ ስርአት“ለዚያ የሀጢያት ሰው” የተሰጠውን መግለጫ የሚያሟላ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር ባይኖርም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ ሌሎች ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች እንዳሉ ልንዘነጋው አንችልም። የአምልኮ እና የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ መሪዎችም የተሰጠውን መግለጫ ይስማማሉ። በእርግጥም ሁሉም ሐሰተኛ ነቢያት የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ስለሆኑ ጥንቃቄ መደረግ አለበት (ማቴ. 24፡ 24)።

ለአምላክ ሕዝቦች በጣም የሚያጽናናው ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ ሰው ብቻ መሆኑ ነው። ብዙ ጥላቻ እና ስደት ቤተ ክርስቲያን ላይ በዘመናት ሁሉ ቢያደርስም የእግዚአብሔርን ልጅ ከሚያስመስለው (ለመምሰል ከሚሞክረው) እና ከሚቃወመው ጋር ሲወዳደር ምንም ማለት አይደለም። ማን እንደሚያሸንፍ ምንም ጥርጥር የለውም። መንግሥቱም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል (ራእይ 19:11–16)።

**ፍርዱ**

የመጨረሻው ፍርድ የዚህን የአሁኑን ዓለም ታሪክ የሚያጠናቅቅ እና የክርስቶስን ዘላለማዊ መንግሥት የሚያመጣ ክስተት ነው። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ፍርዱ ቀን ብዙ ይናገራል።

ፍርዱ አንድ ቀን እና አንድ ክስተት ስለሆነ፣ አለም አቀፋዊ ይሆናል። ሁሉም ሰዎች፣ መላእክት፣ እና ሰይጣን

ከእግዚአብሄር የጸጋን ወይም የዓመፅን ዋጋ በጽድቅ ወይም በአመጻ በኖሩበት ሥጋ ለመቀበል በእግዚአብሄር ፊት ይቀርባሉ።

የፍርዱ ዓለም አቀፋዊነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል። ሁሉም ይፈረድባቸዋል (ማቴ. 16:27፤ ማቴ. 25:31–32፤ ዮሐ. 5:28–29፤ ሮሜ 2:5–6; 2 ቆሮ. 5:10; ራእይ 20:11-14; ራእይ 22:12)። ሊኖር የሚችለው ልዩነት ያለ ፍርድ ወደ እሳት ባሕር የሚጣሉት አውሬው፣ ሐሰተኛው ነቢይ፣ እና ዲያብሎስ ናቸው። ምክንያቱም ክፋታቸው ፈጽሞ የተገለጠ ነውና (ራዕ. 19፡20፤ ራዕ. 20፡10)።

ይህ ፍርድ እንደየ ሥራው ይሆናል (1ቆሮ. 3፡13–15፤ 1 ጴጥ.1:17; ራእይ 2:23; ራእይ 20፡12-13) ነገር ግን በስራ ምክኒያት አይሆንም። ብቁነትን የፍርድ መሠረት ቢሆን እና በሥራ ምክንያት ቢሆን ኖሮ ማንም ሊቆም አይችልም ነበር። በፍርዱ የእያንዳንዱ ሰው ሥራ በክርስቶስ እንዳለ ወይም እንደሌለ ያሳያል። ሥራዎቹ በእግዚአብሔር ፊት ለመጽደቁ ወይም የኃጢአቱና የጥፋቱ ማረጋገጫ ይሆናሉ (ያዕቆብ 2፡14-20) ።

ስለዚህ በእነዚያ ስራዎች መሰረት ሁሉም ሰው ተገቢውን ክፍያ ይቀበላል—የሥራ የዘላለም ኩነኔ የሆነው ክፍያ ወይም የዘላለም ሕይወት የሚሆነው ጸጋ (ማቴ. 16፡27፤ ሮሜ. 4፡4፤ ራዕ. 22፡12)። ይህ ሽልማት ለኃጢአተኞች ፍርድና ኩነኔ በመስጠት እና ለሕዝቡ ያለው የጸጋው ታላቅነት በማሳየት የእግዚአብሔርን ፍትህ ይገልጻል።

ይህ ፍርድና ሽልማት የክርስቶስ ሥራ ነው። ለእርሱ አብ ፍርድን ሁሉ ሰጥቶታል (ዮሐ. 5፡26–27፤ ራዕ. 22፡ 12–13)። ይህ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ሁሉም ፣ ጻድቃን እና ክፉዎች፣ ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ግንኙነት ፍርድን ሊቀበሉ ስለሚገባ ነው። እርሱ ኃጢአተኞች ሰቅለው የገደሉት ነው (ዕብ. 6:4–6፣ ራእይ 1:7 )። እርሱ የራሱ ለሆኑት የሚያጸድቅ ትክክለኛ ፍርድ የሰጠ ነው።

የሕይወት መጽሐፍ የተገባው ለእርሱ ነው። ያ መጽሐፍ (ሉቃስ 10:20) አብ ለክርስቶስ የሰጣቸውን ስዎቸ መዳን ዋስትና ይሰጣል። በዚያ መጽሀፍ ምክኒያት አንዳንዶቾ የሚገባቸው ሳይሆን ጸጋን ይቀበላሉ።

ስለዚህ የፍርዱ ቀን ለአማኝ የተስፋውና የናፈቆቱ ማረጋገጫ እንጂ የፍርሃቱ ቀን አይደለም። እሱም ሊፈረድበት የተገባ ቢሆንም መታመኑ በክርስቶስ እና በክርስቶስ ጽድቅ ላይ ነው።

በእርግጥም በፍርዱ ለአማኞች ታላቅ ተስፋ አለ። ጌታቸው ፣ ታላቅ ወንድማቸው፣ ጻድቃናቸው እና አዳኛቸው የሆነው ክርስቶስ ዳኛቸው ሆኖ ይቀመጣል እና በሚቀርቡበት ጊዜ በእርሱ እንዳሉ ሆነው ይገለጣሉ፤ ከእርሱ ጋር ተነሥተው (በትንሳኤው) ይከበራሉ። ትንሣኤ ከፍርድ ይቅድማል ማለት አማኞች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ሲቀርቡ፣ ቀድሞውንም እርሱን ይመስላሉ ማለት ነው (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። የረከሰው ሰውነታቸው ቀድሞውንም የከበረ ሥጋውን ወደ መምሰል ይለወጣል (ፊልጵ. 3፡21)።

ለተስፋ እንዴት ያለ ማጽናኛ እና መሠረት ነው! የአንተም እንዲህ እንደሚሆን እናምናለን።

### አንድ የመጨረሻ ፍርድ ብቻ

ስለ መጨረሻው ነገር በተመለከተ መጽሃፍ ቅዱስ ከምንም ነገር በላይ ስለመጨረሻው ነገር የሚናገሩት ብዙ ነገር አለ።ስለ ምስክርነቱ በስፋት እንመልከት።

በመጀመሪያ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ፍርድ ብቻ እንደሚኖር ያስተምራል። የበጎች እና የፍየሎች ፍርድ (ማቴ. 25፡31–46)፣ የታላቁ ነጭ ዙፋን (ራዕ. 20፡11–15)፣ እና በቅዱሳት መጽሃፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሌሎች ፍርዶች የተለያዩ ፍርዶች አይደሉም። በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የሚፈጸሙ፣ ግን ሁሉም አንድ እና አንድ የመጨረሻ ፣ የአደባባይ ፍርድ ናቸው።

በእርግጥ በሕይወት ዘመናችን እና በሞታችን ጊዜ የሚፈጸም የተወሰነ ፍርድ አለ ነገር ግን አሁን የምንናገረው ስለ እያንዳንዱ ሰው፣ መልአክ እና የዲያብሎስ የመጨረሻ፣ የአደባባይ ፍርድ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ፍርድ አንድ ብቻ ነው፣ አንዳንዶች እንደሚያስተምሩት ብዙ አይደሉም (የስኮፊልድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማስታወሻዎች ሰባት እንደሆኑ ያስተምራሉ)።

ብዙ ፍርዶችን በሚመለከት የፔንሳሽናሊስት አራማጆች እና ቅድመ-ሚሊኒኒስቶችን ክርክር በዝርዝር ማክሸፍ የእኛ ዓላማ አይደለም። ምን ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት መከራከሪያ እንደሚያቀርቡ ለማሳየት አንድ ምሳሌ ብቻ እንሰጣለን።

በማቴዎስ 25፡31-46 ላይ ያለው ፍርድ ከዓለም ፍጻሜ አንድ ሺህ ዓመት በፊት ያለው ፍርድ እና ከእስራኤል ጋር በተያያዘ በሚኖሩ ህያዋን ህዝቦች ላይ የሚኖር ፍርድ ነው። እነዚህ ህዝቦች እንደተባለው የሚዳኙት በጊዜው በእስራኤል ላይ ባደረጉት አያያዝ በተመለከተ ብቻ ነው።

ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት በማቴዎስ 25 ላይ ስለ ሕያዋን ህዝቦቸ ብቻ አይናገሩም፤ ስለአሕዛብ ሁሉ እንጂ (ቁ. 32)። ራእይ 20 ላይ እንዳለው ፍርድ ይህም ፍርድ እያንዳንዱ ግለሰብ እንደየስራው ስለሚቀበለው እንጂ ስለ ህዝቦች እንዳልሆነ በግልጽ ያሳያል። ሌሎች ምንባቦች ስለመጨረሻው ፍርድ እንደሚናገሩት ሁሉ ማቴዎስ 25፡46 ስለ ዘላለማዊ ቅጣት እና ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ይናገራል።

ይህ ፍርድ የሰው ልጅ በክብሩ መምጣትን ተከትሎ ይሆናል ፣ መምታቱም ደግሞ በማቴዎስ 24፡30-31 ተገልጿል ፣ ይህም በመለከት ድምፅ የሚከወን ይሆናል። ያ መለከት በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡51-52፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡14–17 እና በራዕይ 11፡15–18 የተጠቀሰው የመጨረሻው መለከት ነው። በማቴዎስ 24፡29-30 መሰረት ይህ የክርስቶስ መምጣት በፀሐይ እና ጨረቃ መጨለም ከደመና ጋር ይታወጃል እና ለሁሉም ዓይኖች ይታያል - ይህ ሁሉ የክርስቶስን የመጨረሻ መገለጥ የሚገልጹት በዘመናት ሁሉ ፍጻሜ ነው (2ጴጥ. 3፡10–17፤ ራእ. 1፡7፤ ራእ. 6፡12–17)።

ነገር ግን ግልጽ የሆነ ማረጋገጫ አንድ የመጨረሻ ፍርድ ስለመኖሩ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ውስጥ ሁሉም የሚፈረድባቸው ክርስቶስ ሲመለስ ነው እንጂ አንዳንዶች አሁን እና አንዳንዶቹ በኋላ አይደለም (ዮሐ. 5:28)፣ አንድ ፍርድ ብቻ እንጂ ብዙ ፍርድ የለም(ማቴ. 5፡21–22፤ ማቴ. 12፡41–42)።

ይህንን ማመን አስፈላጊ ነው? መሆኑን እናምናለን ፣ ስለ እስራኤል ፣ ስለ ትንሣኤው እና ስለ ክርስቶስ መምጣት ስላለን አመለካከት ብቻ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ ሳይሆን ፣ ነገር ግን ደግሞ ያ ፍርድ ስለሆነ እና ያ ብቻ፣ 2ኛ ጴጥሮስ 3፡10–18 በመታዘዝ ራሳችንን ማዘጋጀት ስላለብን ነው።

**የፍርዱ ዓላማ**

የመጪው ፍርድ ዓላማ ምንድን ነው? ስለዚህ ጥያቄ አስበህ ታውቃለህ? መጀመሪያ ላይ እንደሚታየው መልስ ለመስጠት ቀላል አይደለም።

በአንድ በኩል ፍርዱ አስቀድሞ ተፈጽሟል። ሰዎች ሲሞቱ ወዲያውኑ ወደ ገነት ወይም ወደ ሲኦል ይሄዳሉ። ቀድሞ በእግዚአብሔር ካልተፈረደባቸው በቀር ይህ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ አብዛኛው ሰው ቀድሞውኑ ስለተፈረደብት ፍርዱ ሲመጣ በገነት ወይም በሲኦል ውስጥ ናቸው ፣ ይህንንም የፍርድ ቀን አይቀይረውም። ታዲያ የፍርድ ቀን ለምን አስፈለገ?

ከኢየሱስ ሞት ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ፍርድም አለ። ይህንንም በዮሐንስ ወንጌል 12፡31 ላይ ስለሞቱ ሲናገር “አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ነው” ብሏል። ክርስቶስ በሞቱ ለአንዳንዶች ዘላለማዊ ድነትን ሰጥቷል ፤ ለአነዳንዶች ግን አልሰጠም (የተወሰነ ስርየት አስተምህሮ )። በእርሱ ሞት አንዳንዶች ከመዳን የተገለሉ ናቸው ፤ የዘላለም እጣ ፈንታቸው ታትሟል ፣ ፍርዳቸውም ተወስኗል። ለምን ታድያ የፍርድ ቀን ይመጣል?

የዚህ ጥያቄ መልስ ቴዎዲዝም በሚለው ሥነ-መለኮታዊ ቃል ውስጥ ይገኛል። ይህ ቃል “የእግዚአብሔር ጽድቅ” ማለት ሲሆን የፍርድ ቀንን ዋና ዓላማ ከጻድቃን እና ከኃጢአተኞች አንጻር ይገልፃል።

የፍርዱ አላማ የሰዎችን እና መላእክትን እጣ ፈንታ ለመወሰን አልያም ለመለወጥም አይደለም። እነዚያ አስቀድሞ በቅድመ ውሳኔ እና በመስቀል ላይ ተወስነዋል። ይልቁንም የፍርዱ ዋና ዓላማ እግዚአብሔር አምላክ ጻድቅና ቅዱስ እንደሆነ ዓመፀኞች ላይ በመፍረድ እና የራሱ የሆኑትን በማዳን ለማሳይት ነው።

ዛሬ የእግዚአብሔር ፍርድ ሁሌም በጥያቄ ውስጥ ይገባል። ለጻድቃን የሚሰጠው ፍርድ በታላቁ የወንድሞች ከሳሽ ሰይጣን ጥያቄ ውስጥ ይገባል(ራዕ. 12፡10)፥ እናም ኃጢአተኞች አማኞችን እንደሌላው ሰው ኃጢአተኞች ናቸው ብለው ይከሳሉ። የእግዚአብሔር ህዝቦች እራሳቸው እንኳን የእግዚአብሔርን ሥራ በራሳቸው መጽደቅ ሲጠራጠሩ.ጥያቄ ያነሳሉ።

እግዚአብሄር በኃጢአተኞች ላይ የሚሰጠው ፍርድም ጥያቄ ውስጥ ይገባል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ስለዚህም ሰዎችን በገሃነም ሊፈርድባቸው አይችልም የሚለው ሃሳብ ጥያቄ ይህንን ያሰነሳል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ሁሉ ኃጢአተኞችን በማውገዙ እና በመፍረዱ ነው።

እነዚህ ቅሬታዎች በመጨረሻው ፍርድ አይሰሙም። ያን ጊዜ እግዚአብሔር ኃጢያተኞችን ወደ ገሃነም በመላክ አመጸኛ እንዳልሆነ በሃጥያተኞች ፍርድ ላይ ግልጽ ይሆናል። በመጻሕፍት መከፈት እና በእግዚአብሔር ቅድስና መገለጥ፣ አፍ ሁሉ ይዘጋል፣ ዓለምም ሁሉ በደለኛ ሆኖ ይገኛል (ሮሜ. 3፡19)። እግዚአብሔር ራሱን ለዘላለም ያጸድቃል።

የእግዚአብሔር ህዝብ የመጨረሻው መፅደቅ ፍትሃዊ እና ሚዛናዊ ይሆናል። እግዚአብሔር እነርሱን ወደ ሰማያዊ ክብር በመቀበል የራሱን ጽድቅ እንዳልካደ በፍርዱ ግልጽ ይሆናል።

የዚህ ሁሉ ማእከል ክርስቶስ ይሆናል። ፈሪሃ እግዚአብሄር የሌላቸው ሰዎች የሚፈረድባቸው ፍትህ በምድር የእግዚአብሔርን ልጅ በመካዳቸው እና በውድቀታቸው ይታያል። እና በተመሳሳይ፣ የጻድቃን ጽድቅ በክርስቶስ ጽድቅ ይገለጣል እንጂ በራሳቸው አይደለም። እግዚአብሔርም በእነርሱ ይጸድቃል።

ያ የእግዚአብሔር ክብር እና የመዳናችን ቀን በፍጥነት ይምጣ!

**ሲኦል**

በዚህ ክፍል ርዕስ ላይ እንዳለው ሲኦል የሚለው ቃል ብቻውን ቆሞ የሚያስደነግጥ ድምፅ አለው እናም እንድንሸማቀቅ ያደርገናል። ዛሬ ብዙዎች ስለ እሱ ማውራት አለመፈለጋቸው ምንም አያስደንቅም።።።

እንደ ክርስቶስ አምላክነት ፣ የሥላሴ እና ስርየት ሁሉ ሲኦል ሁል ጊዜ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሌም ጥቃት የሚደርበት  የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው።  ጥቃቱ ዛሬም ቀጥሏል። ጥቃቱ የመጣው በትምህርታቸው “ዘመናዊ” እና “ሊበራል” ከሆኑት ብቻ አይደለም። በዛሬው ጊዜ ባለው የወንጌላውያን እንቅስቃሴ እንኳ ይህን ትምህርት የሚያጠቁ ሰዎች አሉ።

አዲሱ ኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (NIV) የወንጌላውያን እንቅስቃሴ ውጤት ስለሆነ ይህንን ያስረዳል፡ ። ከብሉይ ኪዳን ሙሉ በሙሉ ሲኦል የሚለውን ቃል አስወግዷል። በKJV ውስጥ ሲኦል የሚለው ቃል ከተገለጸ ሃያ ሁለት ጊዜ ውስጥ NIV በሌላ ትርጉም ቀይሮታል።

በተለይም NIV ቃሉን ከብሉይ ኪዳን ማስወጣቱ ጉልህ ነው። ይህ በድርጅቱ በኩል ካለው ስምምነት ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ይህ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሰዎች ስለ ገሃነም በትክክል አያውቁም ነገር ግን ሁሉም ጻድቃን እና ክፉዎች በሄዱበት በሙታን ቦታ ብቻ ያምኑ ነበር በሚለው ሃሳብ ተርጓሚዎች ሰለተስማሙ ብቻ ነው።

ሲኦል የሚለውን ቃል ከብሉይ ኪዳን መውጣት መጥፎ አተርጓጎም ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲኦል (Sheol) ተብልው የተጠቀሱት ክፍሎች በአብዛኛው በKJV ውስጥ "ሲዖል" ተብለው እንደተቀመጡት መተርጎም ያለባቸው አሉ። ለዚህም ዘዳግም 32:22 እና ኢዮብ 26:6 ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው መዝ 16:10 እንዲሁ መተርጎም አለበት ፤ ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን (የሐዋርያት ሥራ 2:27, 31) ሲኦል ሄድስ (hades) በሚለው ቃል "ሲኦል" የሚል የተለመደ ትርጉም ባለው ቃል ተተክቷል።

የማይስማማውን ቢሆንም ፣ ሲኦል የሚለው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ፣ ከትምህርታችን ወይም ከአስተሳሰባችን ላይ መወገድ የለበትም። ወንጌልን ለመስብክ ወሳኝ ነው። ያለ አስተምህሮተ ሲዖል ፣ የንሰሃ እና የመመለስ የወንጌል ትእዛዝ አስቸኳይነቱ ይቀራል። ሌላው ቀርቶ "ሁኔታዊ ሟችነት" (ለጊዜው ቅጣት፣ ከዚያም መጥፋት) የሚለው የአንዳንድ ወንጌላውያን ትምህርት ፣ ንስሐ ያልገቡ ሰዎች በእግዚአብሔር ቁጣ ለዘላለም መከራን እንደሚቀበሉ ስለሚክድ ንስሐ ካልገባን እንጠፋለን የሚልውን እውነት ያስቀራል።

ከዚህም በላይ ያ አስከፊው ሲኦል የሚለው ቃል በማይነጣጠል መልኩ እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር የተያያዘ ነው። ኢየሱስም "ነፍስና ሥጋ በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ" ብሏል (ማቴ. 10፡28)። ዛሬ ሰዎች በገሃነም ቢያምኑ ኖሮ ምናልባት የበለጠ እግዚአብሄርን መፍራት በአለም እና በቤተ ክርስቲያን ይኖር ነበር። "እግዚአብሄርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው" (ምሳ. 9፡10) ቢሆንም እንኳን ብዙ ቦታዎች ላይ ይሄ ይጎድላል።

**ዘላለማዊ ቅጣት**

የዘላለም ቅጣት አስተምህሮ ተወዳጅ ሆኖ አያውቅም። ነገር ግን ችግሩ በዚህ አስተምህሮ ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት አሁን ከወንጌላውያን ውስጥ የመጣ መሆኑ ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው NIV ሁሉንም ሲኦል የሚለውን ቃል ከእግዚአብሔር ቃል አስወግዷል እና ብዙ መሪ ወንጌላውያን “ሁኔታዊ ያለመሞት” ተብሎ የሚጠራውን እያስተማሩ ነው። የዚህ የሐሰት ትምህርት አራማጆች ኃጢአተኞች ለተወሰነ ጊዜ ወደ ገሃነም ይሄዳሉ ነገር ግን በፍጻሜው ይደመሰሳሉ ስለዚህ ማንም በሲኦል አይኖርም ይላሉ። በእዚያ ቅጣት ይኖራል ግን ዘላለማዊ አይደለም ይላሉ። መሪ ወንጌላውያን ጢሳቸው ለዘላለም ቢወጣም ማንም የሚቃጠል እንደማይኖር ይናገራሉ።

የዘላለም ቅጣት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም ትምህርት እንደሆነ እናምናለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ እንደ ራዕይ 19፡3 ያለ ጥቅስ ግልጽ ያደርገዋል ጥቅሱ የባቢሎን ጭስ ለዘላለም እንደሚወጣ ይናገራል። ማጣቀሻው ፈሪሃ አምላክ የሌላቸው ሰዎች ነው፣ እና ማንም ሰው በገሃነም እሳት ውስጥ እንኳን ሳይኖር ከባቢሎን ጭስ ለዘላለም ሊወጣ የሚችለው እንዴት እንደ ሆነ ለማወቅ በጣም ግልጽ የሆነ ምናብ ያስፈልጋል።

የዘላለም ቅጣት አስተምህሮ አስፈላጊ መሆኑ ለማየት አስቸጋሪ መሆን የለበትም። አንደኛ ነገር፣ ስለ ኃጢአት ትክክለኛ ግንዛቤን ያመጣል። ቅጣቱ ዘላለማዊ ነው የሚለው ሃጥያት  በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እና እጅግ የላቀ ግርማ ላይ መፈጸሙን ያጎላል። የዘላለም ቅጣትን መካድ ኃጢአትን ያቃልላል።

ከዚህ ጋር በቅርበት የተያያዘ ፣ ዘላለማዊ ቅጣትን መካድ የእግዚአብሔርን ፍትህ ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል። እግዚአብሔር መጀመሪያ ሰዎችን ወደ ሲኦል ከላከ በኋላ ያንን ቅጣት እነሱን በማጥፋት ቢያቆመው ሰለማይለወጠው ወይም ስለ እግዚአብሔር ጽድቅና ፍትህ ጥሩ አይናገርም። ይህ ስለ ቅጣታቸው ሀሳቡን እንደሚቀይር እና በተወሰነ ደረጃም በኃጢአታቸው ላይ መቆጣቱ እንደሚጸጸትው ይጠቁማል።

ዘላለማዊ ቅጣትን መካድ እንዲሁ የወንጌልን የንስሐ እና የእምነት ጥያቄ አስቸኳይነትን ይክዳል። ሀጢያተኞች እንደሚጥፉ ካውቁ እነሱ የእግዚያብሄርን ፍርድ አይፈሩም። እነርሱን በጣም የሚያስደነግጣችው የዘላለም ስቃይ አሳብ ነው።

የራሳቸውን የዘላለም ቅጣት ፍራቻ የመካድ ፍላጎጎት ሰዎች የነፍስን ቀጣይነት፥ ገነት ፣ ሲኦል እና የሚመጣው ፍርድ ይክዳሉ። ከምንም በላይ ዘላለማዊ ቅጣትን መፍራት የእግዚአብሔር መኖር መካድ ፣ ሕልውናውን እና ቅድስናውን መቀበል እና እንደ ጻድቅ ፈራጅ ሆኖ መኖሩን እንዲክዱ ያደርጋቸዋል ።

ይህ ማለት ግን ማንም ወደ ሰማይ በመፍራቱ ድኗል ማለት አይደለም። ነገር ግን እግዜአብሄር ብዙውን ጊዜ ህዝቡን ወደ እራሱ የሚያመጣበትን ታላቅ ስራ ለመጀመር የሚጠቀመው የዘላለም ቅጣት አስፈሪነትን ነው፣ ስለዚህም የዘላለም ቅጣት አስተምህሮ ለወንጌል ስብከት አስፈላጊ ነው።

በእነዚህ ምክንያቶች፣ ለክርስቲያኖችም ቢሆን የማይስማማ ቢመስልም ለቅዱሳት መጻሕፍት ዘላለማዊ ቅጣት አስተምህሮ መስገድ አለብን። በክርስቶስ በማመን ለዘላለማዊ ቅጣት አንጋለጥም ብለን በማመን ይህንን ማድረግ አለብን።

## ሰማይ

ስለ ሰማይ ስንናገር፣ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምሀሮ ለመከተል መጠንቀቅ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የማይነግረን ብዙ ነገር አለ፤ ስለዚህም በማይጠቅም መላምት ውስጥ ለመውደቅ እና ከምናውቀው ነገር ለመሳሳት ቀላል ነው።

ስለ  ሰማይ መረጃ ማጣት አንዱ ምክንያት ሰማይ በጣም አስደናቂ መሆኑ እና በምድራዊ አነጋገር በበቂ ሁኔታ ሊገለጽ አለመቻሉ ነው። ስለ ሰማይ አንዳንድ መግለጫዎችን ስናነብ ይህን ስሜት ይሰማናል ፦ ምሽት አይኖርም፣ፀሀይ ወይም ጨረቃ የለም ፣ ባህር የለም ፣ ጋብቻ የለም ፣ ቤተመቅደስም አይኖርም ። ሰማይ “ዓይን ያላየው ጆሮም ያልሰማው በሰው ልብ ያልታሰበ” ነገር (ባለቤት) ናት (1ኛ ቆሮ. 2፡9)።

በዚሁ ተመሳሳይ ምክንያት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሰለ ሰማይ የሚነግረን አበዛኛው ነገር በምልክቶች እና በምሳሌዎች ተሰጥተዋል። እነርሱ ሰማይ በእውነት ድንቅ እንደሆነ ይነግሩናል ነገር ግን ሰማይ በትክክል ምን እንደሚመስል አይነግሩንም። በራዕይ 21 ላይ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መግለጫ ጥሩ ምሳሌ ነው። በምስሉ ላይ ከተገለጸው በመነሳት ሰማይ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል ርዝማኔ፣ ስፋትና ከፍታ ያለው፣ የወርቅ ጎዳናዎች፣ ከትልቅ ዕንቁ የተሠሩ በሮች፣ የከበሩ ድንጋይ መሠረቶች ያላት ከተማ እንደሆነች ብንደመድም ተሳስተናል። ራእይ 21 ከተማይቱ እራሷ “ሙሽሪት፣ የበጉ ሚስት” ማለትም፣ የተከበረችው ቤተክርስቲያን እንደሆነች ይነግረናል (በተጨማሪም ኤፌ. 5፡25–32፤ ራዕ 19፡7-9) ።

ስለ መንግሥተ ሰማያት ማወቅ ያለብን ነገር ኖሮ በቅዱሳት መጻሕፍት አልተጥቀሰም ማለታችን አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንኳን ፍላጎታችንን ባያሟላም አስፈላጊ የሆነውን ሁሉንም ነገር ይነግረናል።

ነገር  ግን ይህ ማለት በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሰማይ ልናውቀው የተገባን ነገር ያነሰ ነው ማለት አይደለም። ምኞታችንን ባያረካም መጽሃፍ ቅዱስ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ነግሮናል።

 መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰማይ የሚናገራቸው አንዳንድ ነገሮች በዚህ ዓለም ውስጥ ለኛ በጣም የሚያጽናኑን ናቸው። በዚያ ከዚህ በኋላ እንባ፣ ህመም ወይም ሞት አይኖርም (ራዕ. 21:4)።  ዕረፍት (ራዕ. 14:13)፣ ደስታ (ማቴ. 25:23) እና የከበረ ነጻነት (ሮሜ. 8፡21) እናገኛለን። እንደ ክርስቶስ እንሆናለን (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። እርኩሱ ሰውነታችን እንኳን የክርስቶስን አካል ወደ መምሰል ይለወጣል (ፊልጵ. 3:21)። ኃጢአት፣ ፈተና፣ እና ክፉ ሰዎች ሁሉ ለዘላለም ይባረራሉ (ራዕ. 21፡27)። ከቅዱሳን እና ከመላእክት ስብስብ ጋር አብረን እንሆናለን ( ዕብ. 12:22–23 )።

ሆኖም እነዚህ ነገሮች እንኳን እውነተኛውን ክብር እና በረከት አይገልጹም እርሱም እግዚአብሔር እና ክርስቶስ በዚያ መኖራቸው ነው፡- “እነሆ፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሰዎች ጋር ነው እርሱም ከእነርሱ ጋር ያድራል እነርሱም ሕዝቡም ይሆናሉ፥ እግዚአብሔርም ራሱ ከእነርሱ ጋር ይሆናል ለእነርሱም ይሆናል።” በሰማይ ያለው ይህ ነው (ራዕ. 21፡3)። ለአማኞች የገነት በረከት "የክርስቶስን ፊት ያያሉ; እና ስሙ በግምባራቸው ይሆናል” (ራዕ. 22፡4) የሚለው ነው።

ብዙ ምንባቦች ስለዚህ ሰማያዊ በረከት የሚናገሩት ሊያመልጠን እንደማይገባ ነው (ኢዮ 19፡26–27፤ መዝ. 16፡11፤ መዝ. 17፡15፤ 1 ቆሮ. 13፡12፤ ፊልጵ. 1፡23)። እግዚአብሔር በዚያ ሰለሆን እና ክርስቶስ በዚያ  ስላለ መንግሥተ ሰማያትን ካልፈለግነው ጭራሹኑ አልፈለግነውም። መንግሥተ ሰማያት ሰንናፍቅ ጸሎታችን  እንደ ፊልጶስ መሆን አለበት፡- “ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል” (ዮሐ. 14፡8)።

## አዲስ ሰማያት እና አዲስ ምድር

ቅዱሳት መጻሕፍት በብዛት ስለ አዲሱ ሰማይና ምድር የመጨረሻው የእግዚአብሔር ህዝቦች ቤት እንደሆነ ይናገራሉ። በዚች አለም ላይ እስካለን ድረስ እኛ እንግዶች እና መጻተኞች የመሆናችን እውነታ ብቻ

እንድንናፍቀው ለማድረግ በቂ ነው። እዚህ የእኛ የምንለው ቤት፣ ሀገር ወይም ከተማ የለንም (ዕብ. 11፡8–10፣ 13–16)። ከብዙ የእንግድነት እና የድካም ጉዞ በኋላ በመጨረሻ ወደቤት መሄድ ፤ አባታችን ፣ ታላቅ ወንድማችን እና ሁሉም ቤተሰባችን እዚያ እንደሚገኙ  እና ደጋሚ ከዚያ እንደማንውጣ ማውቅ ምንኛ ታላቅ ነገር ነው።

ከዚህ በፊት እዚያ ሄደን የማናውቅበት እንዴት ቤት ሊሆን ይችላል? እንዴትስ እንደ ቤት ይናፍቀናል? እንደ እውነተኛው ምድራዊ ቤት፣ ቦታው እዚያ እንዳሉት ሰዎች በጣም አስፈላጊ አይደለም። እነርሱ የምናውቃቸው እና የምንወዳቸው ናቸው። መንግሥተ ሰማይን ፈጽሞ አይተን ባናውቅም በዚያ ያሉት የምናውቃቸው እና እንድንወዳቸው የተማርንባቸው በክርስቶስ  ቤተሰባችን ናቸው።

 አዲስ ሰማያት ለምን መሆን አለበት ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። መልሱ በክርስቶስ ሥራ ውስጥ ይወድቃል። ሰማያት ለእርሱ ስለተፈጠሩ (ቆላ. 1፡16) ፤ ለእርሱ እና የእርሱ ለሆኑት ተስማሚ ቦታ ይሆኑ ዘንድ በእርሱ እና ከእርሱ መታደስ አለባቸው። ምድር በሰው ውድቀት እንደተበላሸች የመጀመሪያው ሰማይ በወደቁ መላእክት ተበላሽቷል። ሰይጣን ፣ የመጀመሪያው ሰማይ አለቃ ፍጥረት ከከፍታው ወድቆ (ኢሳ. 14፡12) ከእርሱ ጋር ብዙ መላእክትን ጥሏል (ራዕ. 12፡4)። ስለዚህ ሰማያዊ ፍጥረት በክርስቶስ መታደስ አለበት።

ለምን አዲስ ምድር? በመጀመሪያ እግዚአብሔር የራሱን እጅ ሥራዎች አይተውም። የፈጠረው ምድር በኃጢአት ምክንያት የተጣለችና የተተወች አይደለች ፤ ነገር ግን ተጠብቃ ቆይታ በመጨረሻ ትታደሳለች። በዚህም ክርስቶስ ይከብራል እና ወደ መጀመሪያው ርስት ብቻ ሳይሆን ከፍ ወዳለ ክብር ይነሳል (ከፍ ይላል) ።

የእግዚአብሔር ድንኳን ከሰማይ በወረደች ጊዜ አዲሲቱ ምድር ከአዲስ ሰማያት ጋር መገናኘቷ የክብሩ አካል ነው።(ራእይ 21:1-2 )። ነገር ግን የታደሰው ፍጥረት ታላቁ ክብር ጽድቅ በእርሱ ማደሩ ነው። ጽድቅና ቅድስና ያድርበት ዘንድ ሊጸዳ እና ሊታደስ ይገባዋል ስለዚህም ኃጢአትና የኃጢአት ሥራ ሁሉ ይወገዳል። የኃጢአተኛ እጆች ስራ የሆነ ምንም ነገር ሊቀር አይችልም። በዚያ የሚኖረው ጽድቅ  በእርሱ የምናገኘው የክርስቶስ የራሱ ጽድቅ ነው።

ስለ እነዚህ ነገሮች ስንናገር እና የምንጠብቀውን ስንገነዘብ በእውነት ሁሉንም ነገር ከመጥፋትና ከመፍረስ እንቆጥራለን (ፊልጵ. 3፡8)። ይህ ዓለምና የዚህ አለም ህይወት፣ ይህ አለም ሊያቀርብ የሚችላቸው ደስታዎች እንኳን ሲነጻጸሩ እንደ አቧራ እና አመድ ናቸው።  ሰማይ የእሱ መኖሪያ እንደሆነ የሚያውቅ ሰው በዚህ ዓለም

ውስጥ ፈጽሞ አይኖርም  መሆን ያለበትም እንደዛ ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡6-8)። ስለዚህም ተስፋችን ይነሳሳል፣ ዓይኖቻችንን ቀና ለማደርግ እንበረታታለን፣ ተስፋ የተገባልንን ቤዛነት እንጠብቃለን፣ ሕይወታቸውም በእግዚአብሔር ዘንድ በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ እንደተሰወረ ሰዎ እንኖራለን።

**ሰማያዊ ክብር**

ስለ ዘላለማዊ የክብር ሁኔታ ወይም ሰማይ እና አማኞች ስለሚገኙበት ስፍራ መጽሐፍ ቅዱስ ሰማይን እና ክብሩን ለመግለጽ የሚጠቀምበትን ቋንቋ በአብዛኛው ተምሳሌታዊ በመሆኑ ልናብራራውን እና ልንረዳው ይገባል። ስለ ህይወት አክሊል በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ ምሰሶዎች ስለመሆን እና የንጋትን ኮከብን ስለ መቀበል  ስናነብ ሰማያዊው ክብር እነዚህን ነገሮች የሚያቅፍ (consists) እንዳልሆነ ልንረዳ ይገባል።

በእርግጠኝነት እንደነዚህ ያሉት ቀጥተና ነገሮች እንደ መላእክት ለሆኑ እና ምድራዊ ላልሆኑ ሰዎች ምንም ዋጋ የላቸውም (1ቆሮ 6፡13) ። ራእይ 21 እና 22 ይህን ግልጽ ለማድረግ ይረዳሉ የተገለጸችው ከተማይ የከበረች ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች እና (21፡9-10) እና የሕይወት ዛፍ ክርስቶስ እራሱ እንደሆነ ይናገራሉ (ራዕ. 2:7፤ ራእ. 22:2, 14)።

ቅዱሳት መጻሕፍት ለምን እንዲህ ዓይነት ቋንቋ ይጠቀማሉ? ይህን የሚያደርገው የሰማይ ነገር "ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው" በመሆኑ ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡9) ። በሌላ አነጋገር  ሰማይ በሥዕሎች እና በምሳሌዎች ካልሆነ በስተቀር ልንረዳው እንኳን የማንችለው እጅግ ክቡር እና ድንቅ ስለሆነ ነው።

ነገር ግን የሰማይ ክብርና ድንቅ  ወርቅና ዕንቍ፡ የከበረ ድንጋይ ካልሆነ ምንድር ነው? ራዕይ 21 እና 22 ይህንን ጥያቄ በግልጽ መልስ ይሰጣሉ። ይህም እግዚአብሔር ራሱ ነው ፣ በተለይም እግዚአብሔር ራሱን በኢየሱስ አዳኛችን ሲገልጥ ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የፈጠረው ለራሱ ነው (ራዕ. 4፡11) ይህም በሰማይ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሕያው እውነት ይሆናል።

መጽሃፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እና ክርስቶስ ለዚያች ከተማ ፣ ለቤተመቅደሱ እና ዜጎቿ ብርሃን እንደሆኑ ይነግሩናል (ራዕ. 21፡23–24፤ ራዕ. 22፡5)። እነዚህ ምዕራፎች  እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ሲኖር እና አምላካቸው ሲሆን ስለሚኖረው እውነተኛው የሰማይ ክብር ይነግሩናል (ራዕ. 21፡3፤ ራዕ. 22፡3-4)።

ከሚያምኑ ሁሉ ጋር መሆን ፣ (በትንሳኤው) መነሳት እና ክርስቶስን ወደ መምስል መለወጥ ፤ የእንባ ሁሉ መታበስ ከኃጢአት ኃይል እና ዕድል እና መገኘት ለዘላለም ነጻ መውጣት - እነዚህ ሁሉ የሰማይ ደስታ ክፍሎች ናቸው። ነገር ግን ከሁሉ የተሻለው የሰማይ ክብር ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንዱም አይደለም። እሱም የእግዚአብሔር መገኘትና እርሱ ብቻ ነው (መዝ. 16፡11፣ መዝ. 17፡15፣ መዝ. 73፡25)።

ይህ ማለት፣ በእርግጥ፣ ለእኛ የሰማይ ክብር የእግዚአብሔር የጸጋ ቃል ኪዳን መገለጡ ነው። ሁል ጊዜ ቃል ኪዳኑ ማለት እግዚአብሔር አምላካችን ፤ እኛም ህዝቡ ነን ማለት ነው። በሰማይ ይህ ወደ ከፍተኛ ክብሩ ይደርሳል ከዛም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር መገኘት ይኖራሉ ፣ ፊቱን ያያሉ ፣ ያውቁታል ፣ ለዘላለምም በእርሱ ደስ ይላቸዋል።

ያንን እንጠብቃለን ግን አሁን ቢሆን ለእኛ ትርጉም አለው። በእውነት የሰማይን ክብር የማየምኙ እንደሚመኙት ማሰብ የለባቸውም። በእግዚአብሔር እና በክብሩ የማይደሰት ሰው ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ኅብረት የማይደሰት እና ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔርን ፊት ማየት የማይፈልግ ምንም ነገር ቢናገር ለሰማይ (ነገር) ፍላጎት የለውም።

ስለዚህ ራሳችንን እና ሕይወታችንን በመመርመር እግዚአብሔር የእኛ ፍላጎት እና ደስታ መሆኑን እንመልከት። ያኔ ሰማያዊ ክብር ምን እንደሆነ ብቻ ሳይሆን በእሱ ውስጥ ስላለን ስፍራ እና ድርሻ እርግጠኞች እንሆናለን።

## ክፍል ፮ - ማጣቀሻዎች


1. Scofield and Rikkers, eds., Scofield Study Bible.
2. “Survival of the fittest,” from Herbert Spencer’s Principles of Biology (1864–1869), was borrowed by Charles Darwin to describe his theory of evolutionism.
3. “Nature red in tooth and claw” is from stanza 4 of Alfred Lord Tennyson’s poem In Memorium, Part 56.
4. “The Death of Death in the Death of Christ: A Treatise on the Redemption and Reconciliation That Is in the Blood of Christ, with the Merit Thereof, and Satisfaction Wrought Thereby” in The Works of John Owen, edited by William H. Goold, vol. 10 in Division 3:c Controversiel (London: The Banner of Truth Trust, 1967), 139–421. Originally published 1850–1853.
5. Heidelberg Catechism, Lord’s Day 16, Q&A 42.
6. John Calvin,“Psychopannychia,” in Tracts and Treatises of John Calvin, vol. 3 (Grand Rapids, MI: William B. Eerdmans Co., 1958), 444.
7. This saying is attributed to Tertullian, a theologian who lived approximately □.□. 160–230.